

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የስነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

በከፍተኛ ትምህርት ተቋም መምህራን የሚታይ ስርዓተየታዊ ዲስኩር
ትንተና፤ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ መነሻነት

በተግባራዊ ስነልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር
የዶክትሬት ዲግሪ ማሚያ ጥናት

በጎሩት ካሳው

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ግንቦት 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የስነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

በከፍተኛ ትምህርት ተቋም መምህራን የሚታይ ስርዓተየታዊ ዲስኩር
ትንተና፤ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ መነሻነት

በተግባራዊ ስነልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር
የዶክትሬት ዲግሪ ማሚያ ጥናት

በኒሩት ካሳው

የጥናቱ አማካሪ

ዶክተር ኑሩ መሀመድ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ግንቦት 2006 ዓ.ም

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADDIS ABABA, ETHIOPIA

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

‹‹በከፍተኛ ትምህርት ተቋም መምህራን በስራ ቦታ ላይ የሚታይ ስርዓተያታዊ ዲስኩር ትንተና፤ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ መነሻነት›› በሚል ርዕስ ለተግባራዊ ስነልሳንና የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ በጎሩት ካሳው የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን ጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል።

የፈታኝ ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

አማካሪ፡- ኑሩ መሀመድ (ፒኤችዲ)

ፊርማ ..... ቀን...13/10/2006

የውጭ ፈታኝ፡- ዘውዱ እምሩ (ፒኤችዲ)

ፊርማ..... ቀን...13/10/2006

የውስጥ ፈታኝ፡- አበበ ገ/ጻድቅ (ፒኤችዲ)

ፊርማ..... ቀን...13/10/2006

ማረጋገጫ

‹‹በከፍተኛ ትምህርት ተቋም መምህራን የሚታይ ስርዓተፆታዊ ዲስኩር ትንተና፤ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ መነሻነት›› በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት በተግባራዊ ስነልሳንና የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ ወጥ የራሴ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናት በትክክል ዋቢ የሆኑና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማየ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡- ኒሩት ካሳው

ፊርማ፡- .....

ቀን፡- 13/10/2006

አህፅሮተ ጥናት

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በገላጭ ጥናት ደረጃ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በወንድና በሴት መምህራን በሚደረግ የስራ ላይ መስተጋብር የሚታየውን ተግባቦታዊ ስልት መግለፅ ሲሆን፤ በተግባራዊ ስነልሳን ጥናት ደረጃ ደግሞ ስርዓተያታዊ የተግባቦት ስልት በስራ ቦታ ላይ የሚያስከትለውን የስርዓተ ያታ ተባልጦን ማሳየት ነው። ስለሆነም የጥናቱ ትኩረት ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በስራ ቦታ ላይ በሚያደርጉት ተግባቦታዊ መስተጋብር ሃሳባቸውንና ራሳቸውን እንዴት እንደሚገልጹ የንግግር አቀራረባቸውን በማየት የተናጋሪዎቹን የድስኩር ስልት መፈተሽ ነው። ጥናቱ የተፈተሸው በአገራችን ከሚገኙ የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች መካከል በአመቺ ናሙናነት በተመረጠው በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ በሶስት ፋካሊቲዎች በሚያስተምሩ ሴትና ወንድ መምህራን ላይ ሲሆን፣ መምህራኑ በስራ ቦታቸው የስራ ጉዳይን አስመልክቶ ባካሄዱት መደበኛና ኢመደበኛ ተግባቦታዊ መስተጋብር ሃሳባቸውንና ራሳቸውን እንዴት እንደሚገልጹ በመመርመር ያተኮረ ነው። የጥናቱ መረጃ በዋናነት በአሳታፊ ምልከታ፤ በደጋፊነት ደግሞ በቡድን ተኮር ውይይት፣ በሰነድ ፍተሻና በመስክ ማስታወሻ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት ተሰብስቧል። መረጃው የሂሳዊ ድስኩር ትንተና (Critical Discourse Analysis) ስልትን በመከተል ተተንትኗል። በዚህም መሰረት በጥናቱ ሁለቱም ያታዎች በስራ ቦታቸው ላይ በሚደረጉ መደበኛና ኢመደበኛ ውይይቶች ላይ ሀሳባቸውን ከመግለጽ አንጻር ልዩነት ታይቷል። ይኸውም በመደበኛ ውይይት ላይ አብዛኛዎቹ ወንዶችና ከቁጥር የማይገቡ ጥቂት ሴቶች ሃሳባቸውን የሚገልጹ ሲሆን፣ አብዛኛዎቹ ሴቶች ግን ሀሳባቸውን በስፋት ሲገልጹ አይታዩም። በሌላ በኩል ግን ሴቶች በበዙበት ኢመደበኛ ውይይት ላይ ሴቶች ሃሳባቸውን በመግለጽ ከፍተኛ ተሳትፎ ሲኖራቸው፤ በዚህ አውድ ደግሞ ወንዶች ሃሳባቸውን ከመግለጽ ይቆጠባሉ። ከዚህ በተለየ ሁኔታ ግን ሴቶች በበዙበት መደበኛ ውይይት ላይ ወንዶች ንቁ ተሳታፊና ሀሳባቸውን የሚገልጹ ሲሆን ሴቶች ግን ሃሳባቸውን አይገልጹም። ይህም ከያታ የበላይነት ጋር የተያያዘ ሊሆን፣ ሴቶች ኢመደበኛ እና የሴቶች ቁጥር የበዛበት ወይም ሴቶች ብቻ ያሉባት የውይይት አውድ ይመቻቸዋል የሚል አንድምታ አለው። የቋንቋ አጠቃቀምን በተመለከተ አብዛኛዎቹ ሴቶች በሀሳብ ልውውጥ ጊዜ ‹‹እህ›› እና ‹‹እሽ›› የሚሉ አጫጭር ድስኩራዊ ቃላትና ጥያቄያዊ ዓረፍተነገሮችን በመጠቀም ያልተሟላና ይልተብራራ ምላሽ ይሰጣሉ። አብዛኛዎቹ ወንዶች ሀሳባቸውን ለመግለጽ አፅንኦታዊና ድምፀታዊ አገላለጾችን፣ ሴቶች ደግሞ ስነምግባራዊ አገላለጾችን ይጠቀማሉ። ወንዶች በእድሜም ሆነ በስራ ልምዳቸው ከፍ እያሉ ሲሄዱ ደግሞ ስነምግባራዊ ቃላትን መጠቀምን እንደሚመርጡ ጥናቱ አሳይቷል። በተቃራኒው ደግሞ ሴቶች በእድሜያቸውም ሆነ በስራ ልምዳቸው ከፍ እያሉ ሲሄዱ ሀሳባቸውንም ሆነ ራሳቸውን ለመግለጽ ደፋር እንደሚሆኑ ያመለክታል። ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በተግባቦት ሂደት የሚያሳዩት ዲስኩራዊ ልማድን በተመለከተ በመደበኛ ውይይት ወቅት አብዛኛዎቹ ወንዶች ተራቸውን ሳይጠብቁ ድርሻ የመንጠቅ፣ የጣልቃ ገብነትና ተደርቦ ?መናገር ድስኩራዊ ልማድ ሲኖራቸው፣ ሴቶች በበዙበት ኢመደበኛ ውይይት ላይ ግን ሴቶች ተራን ያለመጠበቅ፣ የንግግር ድርሻን ብቻ ሳይሆን የውይይት ርዕሰ ጉዳይንም የማስቀየር፣ ተደራርቦ የመናገር፣ የጎንዮሽ ወሬና ያለመደማመጥ ልማድ አላቸው። የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳው አብዛኛዎቹ ወንዶች የሙያ ብቃታቸውንና እውቀታቸውን የውይይት መድረኮችን በመጠቀምና ያላቸውን ቅድመግንዛቤ በመጠቀም ይገልፃሉ። አብዛኛዎቹ ሴቶች ያላቸውን እውቀትና ሙያዊ ብቃት ሲገልጹ አይታዩም። በአጠቃላይ በተግባቦት ሂደት ሀሳብንም ሆነ ራስን በመግለፅ ሂደት ፍርሃት፣ ይሉኝታ፣ በራስ አለመተማመን፣ ድርሻ አለማግኘት፣ በጉዳዩ ላይ ቅድመ ግንዛቤ አለመኖር፣ የወንዶች በንግግር የበላይ መሆንና የስብሰባው ድባብ ከወንዶች ይልቅ ሴቶች እንዳይናገሩ ተፅዕኖ ከሚያደርጉባቸው ጉዳዮች በዋናነት ተጠቃሽ ናቸው። ሆኖም ግን በምልከታ በተወሳደው መረጃ ከሁሉም በበለጠ ቅድመግንዛቤ አለመኖር፣ በራስ አለመተማመንና የንግግር ድርሻ አለማግኘት ዋናዎቹ ተፅዕኖዎች እንደሆኑና የዚህም ችግር ምንጭ ስርዓተያታ እንደሆነ በጥናቱ ታይቷል። በመጨረሻም ችግሩን ለመቅረፍ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በስልጠናቸው ስርዓተያታን መሰረት ያደረገ ‹‹የስራ ቦታ ተግባቦታዊ መስተጋብር ክህሎት›› ቢያካትቱ፣ እንዲሁም መሰል ጥናቶች በተለያዩ ከፍተኛ ተቋማት ቢካሄዱ ስርዓተያታና ተቋማዊ ባህል በተግባቦታዊ መስተጋብር ላይ ያላቸውን ግንኙነት በማሳየት አስተዋፅዖ እንደሚኖረው ተጠቁሟል።

ADADA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADAMA ETHIOPIA

A Study of Gender Based Discourse Analysis on Higher Education Teachers: The Case of Bahir Dar University

Submitted in Fulfillment for the Requirement of the Degree of Doctor of Philosophy in Applied Linguistics and Ethiopian Languages Teaching

By: Hirut Kassaw

Supervisor: Nuru Mohamed (Ph.D)

Summary of the Study

Brown (2007) states that the language we speak and the communication process we use vary according to the subject matter we talk about, nature of the audience, conditions, experiences and on the objective of the speech to be presented. Communication process in a social phenomenon in principle does not represent a specific environmental dialect, but determined individually and in groups. When we talk of discourse or communication process, we assume that it is a sum total of word patterning, phrase organization, facial expressions and bodily movement observed during the discourse. In addition Fairclough (2006) explains that speech process shows the manner of speech in the way that transmits our thoughts, feelings and identity through the process of our speech and bodily movement.

Communication process is not naturally acquired but learnt. Any language speaker acquired his/her speaking styles depending on his/her age range and the nature of the context. Starting from this reality, we can distinguish the speech styles of the children from those of adults. The reason is that, adults change their speech styles depending on the nature of their audience and context while children do not have a capacity to change their style of speech depending on their audience and contextual setting. For example, the speech style of adult while talking with their friends vary from the language used at a time of

conducting interviews seeking an employment Brown (2007). Thus, speech process is gradually acquired, determined by the contextual linguistic variation of the speaker and usually occurs when communities or individuals speak similar dialect, Plat and Plat (1975).

Regarding communication process, different scholars have indicated in their study as there is variation in line with gender. Though there is a controversy, Shan (1999) explains as there are variations of communication process used by men and women. Taking into consideration the gender variation, it is claimed that women but not men talk too much and once women start talking, people assume it to be endless.

There is a general belief that the speech of women focuses on backbiting, debating and sulking. Starting from this communication process of women it is always ascribed to be endless, less useful and fruitless. To that effect, several studies have been conducted. The studies have been conducted involving the communities of English speaking countries such as USA, Great Britain and New Zealand. The study conducted in these countries showed that the communication process used by men and women should have a considerable difference with marked variations from the opinions mentioned above. The result of the study showed us the speech of women covers quite a large portion of the time in meetings held between men and women.

According to the explanation forwarded by Baret and Davidson (2006) artistic and correct common communication contributes to the successful leadership. Particularly, leadership is determined by the leadership in the institution governed. In this respect, personal communication is a force that enhances better understanding among the workers in work places. This process creates productivity. Educators underline the importance of artistic listening developed by the leaders; understand the inner feeling and identity of the people, tolerance and stability geared towards bringing expressive opinions. The reason is that the art of speaking influences the leadership styles overriding among men and women. At work places, men show dominancy over women. As Worz (2001) indicated taking into consideration the study conducted on workers' association, the outlook that people have regarding the variation of speech between men and women stems out from gender perspectives. For example, in North America, to improve working conditions and particularly to bring about a reduction of work load among men and women a necessity was felt to give communication skills training. Consequently, the study indicated that effective communication contributes to good leadership and in that respect enhances the environmental development of an institution.

In general, work place communication regarding gender has been studied by expatriate and local educators. Haylay (2009) has studied the communication variation between men and women of Tigrigna speakers taking in to consideration the novels written by men and women.

The study indicated that both men and women use humble expressions. However, women tend to use short expressions such as 'yes' or 'ok' and further women do not go deep in to the matter but highlight contents which need thorough explanations. Apart of such studies, no study has been conducted in our country regarding workplace communication analysis. Also, no study has been conducted either by expatriates or by nationals regarding workplace communications involving gender. As result, it deems it necessary to conduct a research as to how gender based communication looks like in an institution of higher learning.

The study focuses on individual communication process variation and particularly gives emphasis on gender based linguistic choice of an interested group. Particularly, it focuses on the psychological usage that invites strong thought during speech. In that respect the contextual work place communication selected for the study is the dialogue conducted in the workplace and this becomes very useful in aspects of reflecting once own objective Mumbay (1988). Hence, the study focuses on how people who can communicate with their workmates and how they express their opinion, understand each other and how men and women play their role in their workplace and further examines the speakers based on the process of communication/discourse. This interaction that stems out from workplace enables us to observe the language used in relation to the level of authority, outlook and the like. Further enables us to understand the type and rank of the roles and hidden behaviors of individuals in the community. In addition, it enables us to observe how meeting participants negotiate on the matters of discussion in diversified meetings and how they explain their competency and their gender or social relationship Fairclough (2001). Among the large studies conducted on language and gender, the single and most important study that has drawn attention is the study that focuses on gender and discourse. In this transitional period, political and social conflicts have expanded and consequently gender disparities have gradually crept in to the subject matter Mullany (2007). The reason as to why the research conducted in this sector happened to draw attention was starting from the appearance of women in various workplaces and during this transitional period, political and social contradictions grew up which on the other hand brought about gender inequalities. Such kind of study was dealt in great depth in the 21st century and the objective of the study was geared towards understanding on how discourse is exchanged between the opposite sexes. Mullany (2007), Marion and Friends (1987), advocate that studying the language spoken by professionals in an institution is necessary and first hand function choice.

However, no study or recorded research has been conducted in our country so far regarding the manner on how women explain their thought, inclination, identity, powers and language (discourse) they use while attending a meeting with men. Communication process differs from culture to culture and this shows that it has a strong linkage with culture. The reason is explained through the language that is always used Tannon (1994). As to Tannon (1999) communication process rank varies according to the difference in culture. In some cultures, high ranking community members will have the right to fully explain their thoughts and feelings while the lower stratum of the community remains only as passive listeners. The reason as to why the researcher has come out to conduct a research in this field is due to: -

- Though the number of female teachers in the university is not equal to the number of male teachers, we usually observe as there are quite a number of female teachers. But when viewed in terms of their role in the management, their number is very much limited. When coming to educational meetings such as department council meeting, academic commission meeting, curriculum review meeting, university management meeting, senate meeting, and country wide conferences, women are never included. For example, while I was a member of the academic commission of the education faculty for four years, I was observing as the commission gives assignments to individuals to occupy certain positions of benefit with casting vote. At this juncture, what we usually observed was always the expected, i.e. men get the required position that necessitates fringe benefits. No single woman has ever been suggested for such positions. In fact, though men express their thought publicly, some men remain dominant in some occasions. Such men never deserve positions. The reason is that people judge people in line with publicizing themselves. Such incidents have pushed the researcher to be involved in this study.
- Currently, many women are engaged in various job positions in higher institutions of learning and in many other responsible positions in many workplaces. However, the number of women in leadership positions is marginal; and if at all women occupy leadership positions, they lose their position within a short period of time. According to the study conducted at country level by the Ministry of Education in 2002 and which was presented in what was called '**Country Wide Women Education Strategy)**' document, it was found out that the number of women involved in higher education at management level starting from department head to university president was ascribed to be fewer in number. Hence, the researcher is aiming at investigating as to why the number of women is fewer than men in all such job opportunities. The problem is drawing attention of those concerned. Further, the language used both by men and women is creating a ground whereby women tend to be inferior to men and such conditions need solutions and further recommendation.

- It is viewed by many scholars that the communication process reflects gender bias outlooks. To that effect, cultural outlook is felt detrimental. The researcher would like to investigate this outlook in terms of the cultural and environmental conditions of our country, especially referring to the conditions in higher education of learning.
- No study has been conducted so far at higher educational level regarding gender based communication process. In the end the study shall focus on how gender based communication process is viewed by professionals in institutions of higher learning.

The main objective of this study is to investigate the gender based communication process in the educational institutions of higher learning. Based on this general objective, the study shall encompass the following specific objectives.

1. To investigate how men and women explain their thoughts in the communication process conducted with their workmates.
   - 1.1. To observe how women explain their thoughts in line with the expectation of listeners.
   - 1.2. To investigate how men respect their turns while speaking.
   - 1.3. To observe how men and women get acceptance during expressing their thoughts.
   - 1.4. To investigate the language use variations in communication process.
   - 1.5. To examine the discourse habit of men and women during communication process.
   - 1.6. To study the influencing factors while men and women are engaged in communication process.
2. To examine how men and women explain themselves in the communication process conducted with their workmates.
   - 2.1. To investigate how they try to explain their professional competency.
   - 2.2. To investigate how men and women explain their roles in their workplaces.
   - 2.3. To examine the factors that affect the communication process of men and women.

Fulfilling the above mentioned objectives of the research depends on ethnographic information gathering method and the method to be used is case study. The reason as to why the method was selected is due to the fact that the method enables researchers to go deep in to the subject matter to acquire sufficient amount of information by employing ethnographic information gathering method Robinson (1997). Further, he said that, case study enables us to study the administrative affairs of institutions or workplaces, institutional cultures, and institutional changes. To reach at dependable and acceptable ends, various

methods such as ethnographic information gathering method, group focused interviews, documents, formal and informal discussions, are jointly been employed.

The university selected for the study is a university and this was selected based on random sampling method Bylle (1998), Dorne (2007). The reason is that there are many faculties, colleges and institutions in the university and in that faculties, colleges and institutions have dependable number of staff who would satisfy the target of the research on the discourse analysis and the study gives due emphasis in line with practical experiences, institutions and social perspectives to control parameters.

The college which is selected for the study is one of the thirty three governmental colleges found in our country. Since the focus of the study is participatory interaction and since the type of the study is focus based discourse analysis, the analysis itself focuses on language use, practical experiences, institutional and social values. This will take us to control institutional working habit, number and culture of the workers and the like. Taking the social values of an institution will lead to analyze the subject matter in depth which in the long run brings about dependable results to the study. Singling out culture from an institutions and gathering sufficient amount of information will enable treat the research to the expectation of its readers coupled with the research acceptable ends. Accordingly, the institution selected for the research is Wollo University. The reason as to why Wollo university is selected is because of the researcher is a staff of the university. Further, the reason as to why this university was selected is due to the fact that the researcher could have access to meetings and since the researcher could be able to gather information from colleagues with no restrictions. Also it is anticipated that the target group in their capacity as colleagues could cooperate the researcher while responding their opinion to satisfy what is required in the research.

There are four colleges and three faculties in the selected university. As to the information gathered from Human Resource Administration faculties which have roughly equal number of men and women with similar qualifications have been selected. Among these three faculties which have a reasonable equal numbers of men and women with relatively similar qualification have been selected based on Purposive Sampling method Dourney (2007). However, the number of men and women attending meetings of the faculties has not been found to be equal to with that of the number of women. As a result, the total number of women attending all meetings has been included in the study. In this Stratified Sampling method has been used. In reality, the number of women in the high level of managerial positions is lower than the number of men. In this junction, the Stratified Sampling method has been useful since it treats these kinds of discrepancies in the study Paton (1990), Robinson (1997). In general information has been gathered from university wide meetings and from 18 formal and 5 informal meetings conducted in 3

faculties held from April 2012, to February 2013. Fourteen of them were gathered from participatory observation. Fourteen of them were obtained from video and tape recorded documents of the university information sector. These data were thoroughly investigated. The context has shown as men and women have participated in greater magnitude. The discussion discourse was large and maintained its originality. The discourse units were collected from all meetings conducted in formal and informal meetings of the faculties which were selected to satisfy the research. 4 formal and 2 informal meetings were selected from the two faculties. In general, 6 different discourse units have been selected and analyzed for the study. Also, the article of association of the university, job evaluation forms, selection criteria for job positions have been all taken to serve as a source of information.

Accordingly, the study has used participatory observation method for gathering information. The researcher has stayed for one year in the university. In that respect, she has participated in university wide meetings and also has participated in faculty and department meetings that enabled him to gather the necessary information from the outset to the end. Since the study focuses on discourse analysis, the main information disclosure unit and the observation was done solely on tape recorded materials. At times, when a need arises to collect data outside the tape recordings, field observation has been employed. This process was taken as supplementary information gathering method to supplement the information from tape recordings.

Another point is that, the Group Based Interview is used in the study as an instrument of data collection and the participants were eleven female, eleven male which is in total twenty two people who were selected from the observed three faculties and participants of the meetings conducted in the university. 5 male and 5 female, in total 15 male, 15 female, in total 30 teachers were selected from the teachers available in the three faculties based on the first observation for both men and women who had the chance to speak and who do not have the opportunity to speak by giving equal chance of being selected using Probability Sampling. Next, from the 30 teachers, 12 men and 12 women in total 24 teachers were selected using Probability Sampling to allow equal chance for the faculties speaking and non speaking men and women. In addition to this, the reason for selecting 24 participants is to have 3 group based interview each with 8 members. However, because 1 male and 1 female selected participants were absent from the second round discussion, the group was re-established based on 6 members. Based on this, in general the total number of the study participant was twenty four teachers; two men with a directorial level at the university's responsibility areas, one female at an expert responsibility level, the other men and women beyond teaching and extracurricular activities have no any other share of responsibility. The first discussion was conducted on September 21/2005 E.C. from 9:00 to 11:00 local time and it took two hours and ten minutes. The second discussion was conducted on November 7/ 2005 E.C. from 8:00 to

10:00 and it took two hours. The last discussion was a one hour and 50 minutes discussion held on February 24/2005 E.C. from 4:00 to 5:50 local time.

The questions posed during the discussions focused on what are the factors that influence men and women at higher institution to express their thought and themselves during communication process? The questions are difficult to be answered using observation and document analysis. In addition it was organized to confirm the data collected using observation and to conduct an assessment on how men and women at higher institutions express themselves and their thoughts during communication process.

To confirm the reliability and accuracy of the Group Based Interview, my advisor and three researchers evaluated it and after conducting a pilot study, one question that was found to be redundant was cancelled and the improved Group Based Interview was deployed as an instrument of data collection.

Since the study was mainly focused on Critical Discourse Analysis, its method of data analysis focused on Critical Discourse Analysis Model. The techniques that this approach used was a qualitative research method which analyzed its qualitative information collected using comprehensive data collection method by following the levels of Description → Interpretation → Explanation. Based on this, the qualitative information collection instrument used in this study are participatory observation, Group Based Interview, field visit and document investigation in which the data were analyzed by Fairclough's (2006) Critical Discourse Analysis Model. Hence, it was described using the three analysis methods (approaches); namely, Discourse Unit Analysis, Discourse Habit and Critical Discourse Analysis. Based on these analysis methods, it followed the following six procedures of analysis. The analysis was done in such a way that the procedures follow the three description levels: namely, Description, interpretation and explanation.

The data analysis techniques followed a descriptive qualitative method. In general, the analysis used three discourse analysis instruments/levels. The first level was Discourse Unit Analysis in which the subject of analysis is language utiiization aspect that was observed in the discourse unit created by the communication process. The second discourse habit analysis level is a level in which habits that appear during discourse unit generation process, such as interference, talking over, turn giving, discussion forum utilization, etc are analyzed. Finally, in communication interaction, the role that discussion context, organizational and social culture play in discourse generation process is described at social-cultural habit analysis level. Generally the data collected in this study were analyzed following these levels.

In qualitative research process, whenever data is collected, care has to be taken not to reflect subjectivity feeling in the information. The data was collected using mainly tape recorder. The data was analyzed

based on the social context. This is due to the fact that the theory it follows is social-cultural habit. Hence, the analysis was made based on speech; that means, it was made from the process of how speakers spoke, what they spoke and what they want to mean. Therefore, the data collection and assessment application used the following techniques and to maintain the reliability and accuracy of the study, vast range of information was taken, diverse data gathering and analysis method was used, much time was spent with the subjects of the study, pilot testing was conducted and the data and its analysis was presented to the subjects of the study.

According to the study, the majority of women are not noticed expressing their thoughts widely in formal meeting communication process. In informal meetings where women are found in large numbers, women have much participation in expressing their thoughts and exchanging positive as well as negative thoughts while men refrain from expressing their ideas. Contrary to this, in formal meetings where women are found in large numbers, men are active participants while women refrain from expressing their thoughts. This shows that informal discussion and meeting context where women are found in large numbers or only women are found alone, is suitable for women. Therefore, in communication process, expressing thoughts relative to gender has an influence.

Men have the capacity to appropriately present their thought in a way listeners can understand while a small number of women speakers have the capacity to present in a way listeners can understand better than men. The main reason for this is that they prepare before they speak and express themselves in an organized manner without sidetracking from the discussion point. This indicates that preparation and focusing on the purpose of the meeting has a significant contribution to successful presentation of thought.

With regard to speaking in turn taking during meetings that are conducted at university level, both men and women take a turn to speak by raising hands. Even though there are women that request the chance to speak in such meetings, usually they are deprived of the chance. As repeatedly seen in such context, chairpersons give women a chance to speak at the end of meetings up on the request of meeting participants.

The finding of the study revealed that the speaking chance given to women is not because of the importance of their speech but for mere participation. This not only made women shy away from expressing their thoughts, but also contribute to their lack of confidence.

The majority of men during faculty and departmental level formal meetings and women during numerically women dominated informal discussions, rather than speaking in taking turns, take others' turn. Contrary to this, on meetings conducted at faculty and departmental level, men with higher level

profession and more job experience, rather than taking turns by raising their hands, directly interfere to talk if the chairperson has a job experience less than them.

According to the findings of this study, both sexes use different techniques to take turn by interference or talking over. Women do this by raising their voice and seeking attention while men use descriptions such as, 'excuse me', 'here', 'notice', 'correction', etc as a technique and if this technique fails, they present their idea in writing. The implication of this is that, men's and women's technique for whatever they do is different and this capacity of them can be employed to design strategies for activities planned at workplaces from different perspective. Contrary to this, it shows if organizational plans and strategies are prepared based only on one sex and if both sexes do not participate, problems will surface at the implementation process. On the other hand, the research shows that, since both sexes use different techniques to take others' turn, the capacity obtained from both sexes contributes a lot to prepare teaching methods based on different learning style of students. This indicates that the presence of both sexes in educational institutions has a paramount significance.

The majority of men use emphasis and vocal techniques to describe their idea. However, whenever they grow higher in experience and get older, use courteous words rather than energetic and emphasis ones. To the contrary, whenever women grow higher in experience and age, use emphasis and energetic words to express their thoughts and themselves. From this, it is possible to conclude that whenever men grow higher in experience and age, their powerful dominance in speech gets melted away. To the opposite, whenever women become exposed to different working conditions and acquire experience, their dominant power in speech becomes higher and higher.

With regards to men's and women's discourse habit in communication process, during formal discussion, men have the habit of not taking turns, interference and talking over. In addition to this, they use techniques such as 'notice', 'correction', 'apology', 'here', etc to get acceptance. During informal discussions where women are found in large numbers, women have the habit of not taking turns, not only taking others' turn but also taking point of discussion, talking over, side talking and lack of listening.

In respect of using discussion forum, men have the habit of seizing the opportunity of discussions, but the majority of women and a considerable number of men do not have the habit of using a discussion forum to convey their thoughts and express themselves. The reason for this is the inability of women to provide appropriate answer or explanation to issues forwarded from any audience and men's failure to say on the agenda and inability to be sensitive to the feeling of listeners. This indicates that men and women have problems in utilizing the opportunities created by a discussion form which is caused by gender disparity.

As far as speaking on the topic/agenda is concerned, women's habit of speaking on the topic is better than men due to the reason that they carefully get prepared by taking note. However, if they don't get a turn to speak at the appropriate time, they demonstrate lack of capacity to speak on the topic/agenda. Also men if they think that the issue at hand is inappropriately addressed and on their way aim to express themselves, side track from the discussion point (agenda). This implies that if women get and use the turn to speak, are better than men in speaking at the appropriate time, they have a problem of reversing back discourse.

While the majority men use a discussion form to express their professional competency and job responsibility, the majority of women are not noticed expressing their knowledge not their professional competency.

In fact a small number of women with adequate job experience and awareness of the benefits of assertiveness convey their thoughts and express themselves. This shows that having prior understanding will enable women boost their self confidence, abandon their old habit and express themselves and their professional competency.

According to the finding, politeness, social culture, organizational culture, not being exposed to different working conditions and absence of prior understanding are factors that influence women not to express their thoughts and themselves. Especially, women since they are not exposed to different responsibilities, they don't endeavor to create prior awareness about vast range of issues using different sources. However, the finding of this study revealed that, women able to perform this have demonstrated the capacity to break social and organizational norm.

It is indicated in the finding of this study that men have the ability to explain a variety of issues and provide information and women have the ability to forward solutions to problems that encounter them. The source of this difference is their upbringing and their present exposure. In relation to this, the study pointed out that the majority of men get new information by reading a variety of writings and engaging in communication interaction with different people and the majority of women gain the habit of forwarding solutions to problems using day to day social encounter and job experience rather than reading. The study shows that men and women have different ability in expressing their thoughts in discussions and with this it may vary whenever they get the turn to speak. In addition to this, it indicates that the experience and competence that men and women bring to the workplace is quite different but it is indicated that both abilities are something that should be present together. This shows us that not only the presence of both sexes but also the effort to enable them express their thought is fundamental to organizational success.

Generally, the implication of the aforementioned finding of the study is that the discussion turn taking and order culture that both men and women bring from the family and the society as seen in relation to gender is different and the change they brought about from going to school and learning is very insignificant. Hence, to break this gender habit that they bring from the family and the society, it is necessary to organize the Amharic language educational policy from primary to secondary level in a way that enables them express their thought and themselves.

ምስጋና

በመጀመሪያ ከመነሻ እስከ መድረሻ የጥናቱን ትክክለኛ አቅጣጫ በማመላከት፣ ረቂቁን ያለመሰልቸት በማንበብና አስፈላጊውን እርማትና ምክር በመስጠት ከፍተኛ ሙያዊ ድጋፍ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለዶክተር ኑሩ መሀመድ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በማማከር ብልሃታቸውና ለመልካም ትህትናቸው የተለየ አክብሮትና አድናቆት አለኝ፡፡

ዶ/ር ሥዩም ተሾመ ከመጀመሪያ አስከመጨረሻ የጥናቱን ንድፍና ጽሑፍ ያለመሰልቸት በማንበብ ጠቃሚ አስተያየትና ምክር በመስጠት ያደረገልኝ ድጋፍ ብርታት ሆኖኛል፡፡ አቶ ሙሉጌታ ይታየው ለጥናቱ አስፈላጊና ጠቃሚ የሆኑ መጽሐፍትንና መረጃዎች በማሰባሰብ፣ ከመጀመሪያ እስመጨረሻ ድረስ የጥናቱን ጽሑፍ በማንበብና አስተያየት በመስጠት ያደረገው ድጋፍ ከፍተኛ ነበር፡፡ ሁላቸውንም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ዶ/ር ብርሃኑ ማቲዎስ እና ዶ/ር ኦልጋ ያዝቤክ የምርምሩን ንድፍ በማንበብ፣ እንዲሁም ዶ/ር ጉዳይ እምሩና ዶ/ር እንጉዳይ አደመ የቅድመ ሙከራ ጥናቱን በማንበብ ጠቃሚ አስተያየትና መረጃ በመስጠትና በመጠቀም ላደረጉልኝ ሙያዊ ድጋፍ ከልብ አመሰግናቸዋለሁ፡፡

ይህን መርሀ ግብር ለማሰጀመርና እዚህ ደረጃ ለማድረስ ተስፋ ሳይቆርጡ፣ ውጣ ውረዱን አልፈው የቋንቋ ትምህርቱንም ሆነ እኔና ጓደኞቼን ለዚህ ማዕረግ ላበቁን፣ እንዲሁም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለዚህ ጥናት መሳካት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ላደረጉልኝ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል አባላት ለአቶ ሙሉሰው አስራቴ፣ ለአቶ ደረጀ ገብሬ፣ ለዶ/ር ጌታሁን አማረ፣ ለአቶ ጌታቸው እንዳለማው፣ ለወ/ሮ ስንቅነሽ አጣለ እና በመጀመሪያው የትምህርት ጊዜያት ላስተማሩኝና በዚህ ላይ እንዳጠና ግብዓት ለሰጡኝና ለማከሩኝ ፕሮፌሰር ባየ ይማም፣ ዶ/ር አበበ ገ/ፃዲቅ፣ ዶ/ር ብርሃ ቦጋለ፣ ዶ/ር ዘላለም ልየው፣ ዶ/ር ታየ ረጋሳ፣ ዶ/ር አረጋ ኃ/ሚካዔል ከልብ የመነጨ ምስጋናየ ይድረሳችሁ፡፡

ለጥናቱ መሳካት መረጃ በመስጠት ከፍተኛ ትብብርና ድጋፍ ላደረጉልኝ የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ሃላፊዎችና በዋናው ግቢ ለሚገኙ መምህራን በሙሉ ከልብ የመነጨ ምስጋናየ ይድረሳችሁ፡፡

ለጥናቱ የሚስፈልገኝን ወጪ በመሸፈን ትብብር ላደረጉልኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤትና ለባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕረዚደንት ጽ/ቤት ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ይህ መርሀ ግብር በተሳካ ሁኔታ እንዳጠናቅቅ ቤተሰባዊና ማህበራዊ ሽፋን በመስጠት፣ የጥናቱን ረቂቅ በማረምና በማበረታት ከራሱ በማስቀደም ከዚህ ላደረሰኝ ባለቤቴ ለአቶ ደምሴ አበጋዝ ምስጋናዬ ይድረሰው፡፡ እንዲሁም ልጆቼ ተማሪ ሳባ እና ዳዊት እንዲሁም ህፃን አማኑዔል ደምሴ፤ የልጅነት ጊዜያችሁን ለእኔ በመስጠት ያሳያችሁት ትብብርም ሆነ ትዕግስት የማይረሳ ነው፡፡

በመጨረሻም አባቴ አቶ ካሳው ወንድም፣ እናቴ ወ/ሮ አበበች ደምሴ፤ እህቶቼ አምሳል፣ ማዕዛሽወርቅና ንግስት ካሳው እንዲሁም አቶ ዘለለው አሸኔ ጊዜያችሁን ላእኔ በመስጠት ያደረጋችሁልኝ ትብብር ከፍተኛ ነው፤ ሁላችሁንም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ሙዳየ ቃላት

እንግሊዝኛ ቃላት	በጥናቱ ውስጥ የተሰጣቸው ትርጉም
Artifacts	ጥበባዊ
Case study	ንጥል ጥናት
Casual style	ድንገቴያዊ ስልት
Critical Discourse Analysis (CDA)	ሂሳዊ ድስኩር ትንተና
Communication style	ተግባቦታዊ ስልት
Conceptual	ግንዛቤያዊ
Consultative style	ምክክራዊ ስልት
Convenience sampling	በአመቺ ናሙና
Discursive practice	ድስኩራዊ ልማድ
Deliberative style	ሆነ ተብሎ ስልት
Deictic context	ንግግራዊ አውድ
Discourse	ድስኩር
Ethnographic	ኢትኖግራፊያዊ
Exchange structure	የሀሳብ ልውውጥ
Floor	መድረክ
Focus Group Discussion Interview(FGDI)	የቡድን ተኮር ቃለመጠይቅ(ቡተቃ)
Gender	ስርዓተ ፆታ
Ideology	አመለካከት
Interruption	ጣልቃ ገብነት
Intimate style	ጓዳዊ ስልት
Irony	ምፀት
Kinesics	እንቅስቃሴ
Kinesthetic	ውበታዊ እንቅስቃሴ
Macro level	በላዕላይ ደረጃ
Micro level	በታዕታይ ደረጃ
Mitigation	አፅንኦታዊ ንግግር

Modality	ድምፀት
Multi-dimensional	ብዝሀ መረጃ
Oratorical style	አንደበተ ርቱዕ ስልት
Olfactory Dimensions	ስሜታዊ
Overlap	አለመደማመጥ
Politeness strategies	ስነምግባራዊ ስልት
Power	ሀይል
Pragmatics	የቋንቋ አጠቃቀም
Presupposition	ቅድመ ግንዛቤ
Program	ትምህርት ክፍል
Proxemics	አካላዊ ቅርበት
Pseudonym	የብዕር ስም
Purposive sampling	ባምክንያታዊ የናሙና አመራረጥ
Rare element sampling	የአናሳ ተጠኝ ናሙና
Repair	ማስተካከያ/ተጨማሪ
Sex	ፆታ
Setting agendas	አጀንዳን ማዋቀር
Socio-cultural practice	ማህበረ-ባህላዊ ልማድ
Text	አሃድ
Textual analysis	አሃዳዊ ትንተና
Topic control	ርዕስን መጠበቅ
Transcript notational convention	የፅሁፍ ስምምነት ምልክቶች መግለጫ
Triangulation	ማመሳከር
Turn taking	የንግግር ድርሻ

የፅሁፍ ስምምነት ምልክቶች መግለጫ

በእኔ መረጃ ውስጥ የተጠቀምኩባቸው የፅሁፍ ስምምነት ምልክቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

((×××))	በደንብ የማይሰማ መረጃ
((ሳቅ))	የገልባጩ ገለፃ
…	የተቋረጠ ሃሳብ
…..	ንግግሩ ወደፅሁፍ ሲገለበጥ የወጣ/የተዘለለ መረጃ
[	ተራውን ያልጠበቀ/ጣልቃ ገብ/ ንግግር
:	አጭር ተግታ
—	ረጅም ተግታ
=	ዝቅተኛ ድምፅ
=	ከፍተኛ ድምፅ
!	ስሜት ቀስቃሽ ድምፅ/ንግግር
በ-እ-ው-ነ-ት	የጐቆራረጠ ቃል
= =	በንግግር መነሻ ላይ የሚታይ የሁለትና ከዛ በላይ ሰዎች መደራረብ
(የደመቀ)	የእኔ (የአጥኝዋ ትኩረት)
/	እጅ አውጥተው ድርሻ ያልተሰጣቸው

ከፊርጋላፍ (1992) እና ከሆልምስ(2003) ተወስዶ ለዚህ ጥናት ባሚስማማ መልኩ የተዘጋጀ፡፡

ማውጫ

ይዘት ገጽ

አህፅሮተ ጥናት I

Summary of the Study Ii

ምስጋና xviii

ሙዳየ ቃላት xviii

የፅሁፍ ስምምነት ምልክቶች xviii

ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ 1

1.2 የጥናቱ መነሻ ችግር 11

1.3 የጥናቱ ዓላማዎች 16

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ 18

1.5 የጥናቱ ወሰን 19

1.6 የጥናቱ ውስንነት 20

1.6 የቁልፍ ፅንሰ ሀሳቦች አጠቃቀም ብያኔ 21

ምዕራፍ ሁለት፡- ክለሳ ድርሳን 24

2.1 መግቢያ 24

2.2 የተግባቦታዊ ስልት ፍችና ምንነት 24

2.3 የሂሳዊ ድስኩር ትንተና ምንነት 30

2.4 የሂሳዊ ድስኩር ትንተና መሰረተ ሃሳብ 32

2.5 የሂሳዊ ድስኩር ትንተና እና የበላይነት ስሜት 35

2.6 የሂሳዊ ድስኩር ትንተና ማዕቀፎችና ደረጃዎች 36

2.6.1 ድስኩራዊ አሃድ 39

2.6.1.1 ንግግራዊ አውድ 40

2.6.1.2 ምፀት 40

2.6.1.3 አፅንኦታዊ ንግግር 40

2.6.1.4 ቅድመ ግንዛቤ 41

2.6.1.5 ድምፀት 42

2.6.1.6 ስነምግባራዊ ስልት 42

2.6.2 ድስኩራዊ ልማድ 44

2.6.2.1 ድርሻን ጠብቆ መናገር 47

2.6.2.2 የሀሳብ ልውውጥ 48

2.6.2.3 መድረክ 48

2.6.2.4 አለመደማመጥ 49

2.6.2.6 ጣልቃ ገብነት 49

2.6.2.7 ማስተካከያ/ተጨማሪ 50

2.6.2.8 ርዕስን መጠበቅ 50

2.6.2.9 አጀንዳን ማዋቀር 50

2.6.3 ማህበረ-ባህላዊ ልማድ 52

2.7 ተቋማዊ ባህል 54

2.8 ተቋማዊ ድስኩር 55

2.9 ተቋማዊ የተግባቦት መዋቅር 57

2.10 የስርዓተ-ፆታ ንድፈ-ሃሳብ 59
2.9.1 የበላይነት ንድፈ-ሃሳብ 59
2.9.2 የልዩነት ንድፈ-ሃሳብ 61
2.9.3 ስርዓተ-ፆታ በተግባቦት ላይ ያለው ተፅዕኖ 61
2.10 ጥናቱ ንድፈ-ሃሳባዊና ግንዛቤያዊ ማዕቀፍ 62
ምዕራፍ ሶስት፡- የአጠናን ዘዴ 67
3.1 መግቢያ 67
3.2 የጥናቱ ዘዴ 67
3.3 የጥናቱ ተሳታፊ አመራረጥ ዘዴ 69
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች 71
3.4.1 ተሳትፏዊ ምልከታ 71
3.4.2 የመስክ ማስታወሻ 75
3.4.3 ሰነድ 75
3.4.4 ቡድን ተኮር ውይይት ቃለመጠይቅ (ቡተቃ) 76
3.5 የመረጃ አሰባሰብ ቅደም ተከተል 78
3.6 የመረጃ ትንተና ስልት 80
3.7 የጥናቱ አስተማማኝነትና ትክክለኝነት 85
3.8 ቅድመ ሙከራ ጥናት 87
3.8.1 ቅድመ ሙከራ ጥናት የተደረገበት ምክንያት 87
3.8.2 የቅድመ ሙከራ ጥናቱ የመረጃ አሰባሰብ ቅደም ተከተል 88
3.8.3 ከቅድመ ሙከራ ጥናቱ የተገኙ ትምህርቶች 89
ምዕራፍ አራት፤ የመረጃ ትንተናና ግኝት ማብራሪያ 93
4.1 መግቢያ 93
4.2 የመረጀ ዳራና ገለፃ 93
4.3 የመረጃ ትንተናና ግኝት 95
4.3.1 ድስኩራዊ አሃድ 95
4.3.1.1 ንግግራዊ አውድ 96
4.3.1.2 ምፀት 112
4.3.1.3 አፅንዖታዊ ንግግር 117
4.3.1.4 ቅድመግንዛቤ 126
4.3.1.5 ድምፀት 135
4.3.1.6 ስነምግባራዊ ስልት 137
4.3.2 የድስኩራዊ ልማድ ትንተና 143
4.3.2.1 የንግግር ድርሻን መውሰድ 144
4.3.2.2 የሰብሳቢው ሚና በድርሻ አሰጣጥ 149
4.3.2.3 የሀሳብ ልውውጥ 152
4.3.2.4 መድረክ 157
4.3.2.5 አለመደማመጥ 160
4.3.2.6 ጣልቃ ገብነት 166
4.3.2.7 ማስተካከያ/ተጨማሪ 169
4.3.2.8 ርዕስን መጠበቅ 171
4.3.2.9 አጀንዳን ማዋቀር 174
4.3.2.10 ሀሳብን መግለጽ ወይም መጨረስ 175

4.3.2.11 በስብሰባ ወቅት ሀሳብን ከመግለጽ በፊት የሚደረግ ቅድመ ዝግጅት..... 181
4.3.3 ማህበረ-ባህላዊ ልማድ..... 186
4.3.3.1 ሁኔታዊ ደረጃ..... 186
4.3.3.2 ተቋማዊ ደረጃ..... 191
4.3.3.3 ማህበራዊ ደረጃ..... 195
4.6 የውጤት ማብራሪያ..... 200
4.6.1 በተግባቦት ሂደት ሃሳብን የመግለጽ ሁኔታ..... 201
4.6.1.1 ሃሳበቸውን አድማጭ በሚረዳው ሁኔታ ባግባቡ የመግለጽ ችሎታ..... 202
4.6.1.2 ድርሻን ጠብቆ ከመናገር አንፃር ያላቸው ተሳትፎ..... 203
4.6.1.3 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በንግግር ያላቸው ተደማጭነት..... 204
4.6.1.4 በሴቶችም ሆነ በወንዶች በተግባቦት ሂደት የሚታየው የቋንቋ አጠቃቀም..... 205
4.6.1.5 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በተግባቦት ሂደት የሚያሳዩት ድስኩራዊ ልማድ..... 208
4.6.1.6 በተግባቦት ሂደት ሀሳባቸውን ለመግለፅ ተፅዕኖ አድራጊ ጉዳዮች..... 210
4.6.2 በተግባቦት ሂደት ራስን የመግለፅ ሁኔታ..... 213
4.6.2.1 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በስራ ቦታቸው ላይ ያላቸውን ድርሻ የመግለፅ ልምድ..... 213
4.6.2.1 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በተግባቦት ሂደት ማንነታቸውን ለመግለፅ ተፅዕኖ አድራጊ ዳዮች..... 215
ምዕራፍ አምስት፤ማጠቃለያ፣ መደምደሚያ፣አንድምታና መፍትሄ..... 218
5.1 ማጠቃለያ..... 218
5.2 መደምደሚያ..... 232
5.3 አንድምታና መፍትሄ..... 239
ዋቢ ምች..... 250
አባሪ አንድ፡- የቡድን ተኮር ቃለመጠይቅ (ቡተቃ)ጥያቄዎች..... 257
አባሪ ሁለት፡- አኮ.002..... 258
አባሪ ሶስት፡- አኮ.003..... 281
አባሪ አራት፡- አኮ.004..... 306
አባሪ አምስት፡- አጠመ.006..... 311
አባሪ ስድስት፡- ኢመ.001..... 314
አባሪ ሰባት፡- ኢመ.004..... 316
አባሪ ስምንት፡- ቡተቃ.201..... 320
አባሪ ዘጠኝ፡- ቢተቃ.202..... 334
አባሪ አስር፡- ቡተቃ.203..... 346
አባሪ አስራ አንድ፡- የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መምህራን መገምገሚ መስፈርቶች/በተማሪዎች የሚሞላ መገምገሚያ..... 358
አባሪ አስራ ሁለት፡- የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መምህራን መገምገሚ መስፈርቶች/ለስራ ባልደረባ የሚሞላ..... 360
አባሪ አስራ ሶስት፡- የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መምህራን መገምገሚ መስፈርቶች/በሃላፊው የሚሞላ..... 362
አባሪ አስራ አራት፡- የፕረዚደንት፣ የዳይሬክተርና የዲን የማወዳደሪያ መስፈርት..... 364

የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ አንድ፡- የፅሁፍ ስምምነት ምልክቶች መግለጫ.....xvii
ሰንጠረዥ ሁለት፡- የጥናቱ ዘዴ ማጠቃለያ.....84

የስዕል ማውጫ

ስዕል አንድ፡- ተቋማዊ የተግባቦት መዋቅር.....58
ስዕል ሁለት፡- በስራ ቦታ ላይ የሚታይ ስርዓተ-ፆታዊ የተግባቦት ሞዴል.....65
ስዕል ሶስት፡- የሂሳዊ ድስኩር ትንተና ማዕቀፎችና ደረጃዎች ሞዴል 82

ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ

ተግባቦት ማለት የመልዕክት መቀበያና መልዕክትን የመተርጎም ሂደት እና ምላሽ የመስጠት ቅንብር ነው። አስፈላጊነቱም መልዕክት፣ ሃሳብ፣ መረጃ ከአንዱ ወደ አንዱ ለማስተላለፍ ሲሆን፣ ይህም በተለያዩ የመግባቢያ ዘዴዎች ማለትም በጽሁፍ፣ በአንደበት፣ በምልክት ይተገበራል (ድርያናን፣ 2011)። እንደ ኮንራድ እና ፖል (2002) አገላለጽ ደግሞ መልዕክት እለት ተእለት ጓደኛ ከጓደኛ ቤተሰብ ከቤተሰብ አሰሪ ከሰራተኛ እንዲሁም ለሌሎችም ይተላለፋል፤ አለምም ከዚህ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተያያዘች ነች። ይህም በተግባቦት ከመግባባት ባሻገር ጭቅጭቁም ግጭቱም ሊነሳና ሊሰተናገድበት ይችላል።

ተግባቦት ሰዎች መልዕክት ከሚለዋወጡበት ዘዴ አንዱና ዋነኛው ነው። ይህም ስለሆነ ተግባቦት ከሌለና ከተቋረጠ ግንኙነት ተቋረጠ ማለት ነው። ስለሆነም ተግባቦት ስኬታማ በሆነ መልኩ ሊካሄድ የሚገባው ሲሆን፣ ክንውኑ ደግሞ መልዕክት በማስተላለፍና በመቀበል ብሎም መልዕክቱን በመረዳት ደረጃ ነው (ግርጊን፣ 2009)። ተግባቦት በዕለት ተዕለት በሚደረግ ክንውን የሚፈፀም ተግባር ሲሆን፣ በእያንዳንዱ ተግባር ስኬት የሚመዘገብ ከሆነ የተግባቦት ሂደቱ ስኬታማ እንደሆነ ያመለክታል።

ስኬታማ ተግባቦትን ለመፍጠር ዋናውና ቀዳሚው ጉዳይ የማዳመጥ ችሎታ ነው። ይኸውም ተግባቦትና የማዳመጥ ክሂል የጠበቀ ግንኙነት ያላቸው ሲሆን፣ ስኬታማ ተግባቦት ተፈፀመ ማለት የሚቻለውም ተናጋሪው የተናገረውን አድማጩ ተረድቶ ወደ ተግባር ሲቀይረው ነው። ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ ተግባቦት ማለትም ሆነ የተግባቦት ግብ መልዕክቱን በሰመረ መልኩ ከአንዱ ወደሌላው ማስተላለፍ፣ መረዳትና መግባባት ማስቻል ነው (ጉድኦል፣2002)። ይህን ማድረግ የሚችለው ደግሞ ሂደቱን ጠብቆ ሲከናወን ነው። ይኸውም የተግባቦት ሂደት የሚከናወነው በንግግርም ሆነ ከንግግር ውጭ በሆኑ የመግባቢያ ዘዴዎች ግልፅ በሆነ መንገድ መልዕክት በመላክ፣ በመቀበል፣ በመረዳትና መልሶ በማቀበል ላይ የተመሰረተ ነው። ይህን የተግባቦት/የንግግር ሂደት በመረዳትና በማገናዘብ ደግሞ በሂደት የንግግር ችሎታን ማሳደግ ይቻላል።

በእርግጥ በተግባቦት ሂደት አንዳንድ አሉታዊ ተፅኖ ፈጣሪ ሁነቶች ሊኖሩ እደሚችሉ ይታመናል። ለዚህም መፍትሄ ተብሎ የሚወሰደው በተግባቦት ሂደት ተግባቦትን የሚያሰናክሉ ጉዳዮችን በመረዳት መቀነስና የተግባቦት አቅምን ለማሳደግ መጣር ነው (ኮንራድ እና ፖል፣ 2002)። እንደምሁራኑ አገላለጽ የሰመረ ተግባቦት ለመፈፀም እቅፋት ከሚሆኑት ጉዳዮች በዋናነት የሚጠቀሱት አካላዊ ሁኔታ፣ ምናባዊ፣ ስነልቦናዊ፣ በአግባቡ የመረዳት ችግር፣ ስሜት፣ የተለያዩ ጫናዎች፣ ባህል፣ ስርዓተያታ፣ ማህበራዊ ቦታ ተጠቃሽ ናቸው። በተጨማሪም እነዚህና መሰል አስቸጋሪ ጉዳዮች ሲገጥሙ የተግባቦት ችግርን ለማሻሻልና ብሎም ለማስወገድ በስራ ቦታ ላይ ያሉትን ተፅዕኖዎች ተረድቶ ይህኑ ለማስተካከል መንቀሳቀስ ተገቢ ነው።

የተግባቦት ስልትን በተመለከተ ብራውን (2007) የምንናገረው ቋንቋና የተግባቦት ስልት እንደምንናገረው ርዕሰ ጉዳይ፣ እንደአድማጫችን፣ እንደሁኔታው፣ እንደህይወት ልምዳችንና እንደምናቀርበው የንግግር ዓላማ ሊለዋወጥ ይችላል በማለት ይገልፃሉ። የተግባቦት ስልት ማህበራዊም ሆነ የተወሰነ የአካባቢ ዘዬ የሚወክል ሳይሆን ግላዊና ቡድናዊ ነው። የዲስኩር ወይም የተግባቦት ስልት ስንል የቃላት አመራረጡ፣ የሀረጋት አደራደሩ፣ በዲስኩር ወቅት የሚታየው የፊት ገፅታና የሰውነት እንቅስቃሴ ሁሉ ድምር ውጤት ነው። ከዚህ ሌላ የአነጋገር ስልት የንግግር እንዴትነትን የሚያሳይ ሲሆን፣ በአነጋገራችንና በእንቅስቃሴያችን አማካይነት ሃሳባችንን፣ ስሜታችንንና ማንነታችንን የምንገልፅበት መንገድም ተደርጎ እንደሚወሰድ ፌርክላፍ (2003) ያብራራሉ።

የተግባቦት ስልት በተሰጥዖ የሚገኝ ሳይሆን የሚለመድ ነው። ማንኛውም ቋንቋ ተናጋሪ ከልጅነት ወደጉልምስና በመጣ ቁጥር በማንኛውም ጊዜና የንግግር አውድ መናገር የሚያስችሉትን የራሱ የሆነ የንግግር ስልት ይለምዳል። ከዚህ በመነሳት የህፃናትና የአዋቂዎችን ንግግር መለየት ይቻላል። ምክንያቱም በንግግር ወቅት አዋቂዎች እንደየሁኔታውና ታዳሚያቸውን በሚመጥን አይነትና አውዱ በሚፈቅደው መሰረት የንግግር ስልታቸውን መቀየር ሲችሉ፤ ህፃናት ግን ይህን የማድረግ አቅሙ የላቸውም። ለምሳሌ አዋቂዎች ከጓደኞቸው ጋር በሚነጋገሩበትና በሚጫወቱበት ወቅት የሚጠቀሙት የአነጋገር ስልትና በስራ ቅጥር ወቅት ለቃለመጠይቅ ቀርበው ጥያቄውን ሲመልሱና በስራ

ቦታ መደበኛ በሆነ ንግግር ወቅት የሚጠቀሙበት ስልት የተለያዩ ነው (ብራውን፣2007)። ስለዚህ የአነጋገር ስልት በሂደት የሚለመድ፣ ተናጋሪው እንደሚናገረው የስነልሳን ልዩነት አውድ የሚወሰንና የአንድ ቋንቋ ዘዬ በሚናገሩ ማህበረሰቦችም ሆነ ግለሰቦች ዘንድ ሊከሰት የሚችል ነው (ድርያናን 2011)።

ተግባቦታዊ ስልትን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን ከስርዓተ-ፆታ አንፃር ልዩነት እንዳለው በጥናታቸው አመላክተዋል። ስለተግባቦት የሚነሱ ብዙ አጨቃጫቂ የሆኑ ጉዳዮች እንዳሉ ሆኖ የወንድና የሴት የንግግር ስልት ልዩነት ያለው መሆኑን ሻን (1999) ይገልፃሉ። ከስርዓተ-ፆታ ልዩነት አንፃር ሲታይ ከወንዶች ይልቅ ሴቶች ብዙ እንደሚናገሩና እንዲያውም ሴቶች ከተናገሩ አያባሩም እንደሚሉት አይነት ተደርጎ ይወሰዳል። የሴት ንግግር ያተኩራል ተብሎ የሚታሰበውም በሀሜት፣ በጭቅጭቅ፣ በኩርፊያና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ ነው የሚል እምነት አለ። ከዚህ በመነሳት ይመስላል የሴቶች ንግግር ብዙና የማያቋርጥ ብሎም ርባናና ቁም ነገር የለሽ ተደርጎም ይገመታል (ዋልተን 2005) ። በዚህ ዙሪያ መሰረታዊ ጥናት የተደረገ ሲሆን፣ ጥናቱም የተደረገው እንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪ በሆኑ ሀገሮች ማለትም በአሜሪካ፣ በብርቴይንና በኒው ዚላንድ ውስጥ የተለያዩ ማህበረሰቦችን መሰረት በማድረግ ነበር። ጥናቱም በወንዶችና በሴቶች የንግግር ስልት መካከል የጎላ ልዩነት መኖሩን ያሳየና ከሚባለውም የተለየና ያፈነገጠ ነው። ይኸውም ወንዶች ከሴቶች ጋር ሲሰበሰቡ ከጠቅላላው ንግግር ውስጥ ከሴቶች ጋር ሲነፃፀሩ ብዙውን ጊዜ እንደሚሸፍኑ ተረጋግጧል (ሻን፣1999)።

በተጨማሪም በስፔንደር (1990) እና በስዋን (1989) ጥናቶች ይህ እምነት እንደተረጋገጠና፣ ተናጋሪው በንግግር ወቅት ከሚወስደው ጊዜ አንፃር ሲታይ ወንዶች እጥፍ ሲናገሩ ሴቶች ግን አንድ ሶስተኛውን ጊዜ ብቻ እንደሚሸፍኑ ሻን (1999) ያስረዳሉ። ይህ ፍትሃዊነት የጎደለው ጉዳይ በትምህርት ቤትም የሚታይ ሲሆን፤ በክፍል ውስጥ በሚደረግ ንግግር ወንድ ተማሪዎች ብዙውን ጊዜ ሲሸፍኑ የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ግን ከጊዜ አንፃር ሲታይ ውስን ነው። ይህ የጥናት ውጤትም የመማሪያ ክፍል የማስተማሪያ ስልትን መቀየርና የክፍለ ጊዜ የሰዓት አጠቃቀምን መወሰን አስፈላጊነትን ጠቁሟል። ለምሳሌ የእነዚህ ጥናቶች ውጤት በዩናይትድ ኪንግደም በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሴትና ወንድ ተማሪዎችን እንዲሁም የመምህሩን የንግግር ጊዜ በማከፋፈል ፍትሃዊ ለማድረግ

አስችሏቸዋል። ሌላው የሴቶችንና የወንዶችን ንግግር የሚለያየው አይነተኛ ሁኔታ የፍሬ ነገር (ርእሰ ጉዳይ) አመራረጥ ላይ ነው። ይህም ሴቶች ግላዊ በሆነ በቤተሰብ ዙሪያ፣ በሚሰማቸው ነገርና፣ ስለጓደኞቻቸው መናገር ሲፈልጉ፤ ወንዶች ደግሞ ከዚህ በራቀና በሁነቶች ዙሪያ ያጠነጠነ እንዲሆን ይመርጣሉ። ለምሳሌ በኳስ፣ በመኪና፣ በቤት ግንባታ ዙሪ መነጋገር ይሻሉ።

በታነን (1999) የምርምር ስራና ሻን (1999) የኮትስ (1993)፣ የጀምስ እና ክለርክ (1993)ንና የክለርክ (1993)ን ጥናት በመጥቀስ እንዳቀረቡት ደግሞ የወንድና ሴት የአነጋገር ስልት ልዩነትን አስመልክቶ በጥናቶች ውስጥ ከተገኙት ውጤቶች አንዱ ወንዶች ሴቶችን በንግግር ወቅት ማደናቀፋቸውን ያሳየ ነው። በንግግር ወቅት ወንዶች ወንዶችንም፣ እንዲሁም ሴቶች ወንዶችንም የማደናቀፍ ባህርይ ቢታይባቸውም፤ የበለጠ ግን መደናቀፉ በሴቶች ላይ ይጎላል። ይህም የሚያሳየው ተዕዕኖው በሁለቱም ፆታዎች ዙሪያ ያለ ቢሆንም ሴቶች የበለጠ መጠቃታቸውን ነው። ምንም እንኳ ጥናቱ በፍተሻው ወንዶች ሴቶችን በተደጋጋሚ ችግር ይፈጥሩባቸዋል የሚለውን አጨቃጫቂ ጉዳይ ቢያረጋግጥም፤ ወንዶች ብዙ የመናገር መብት እንዳላቸው ሴቶች ግን ከወንዶች ጋር እኩል የመናገር መብት የሌላቸው አድርገው ማሰባቸው ሁለቱም ፆታዎች ባሉበት መድረክ ወንዶች ብዙውን ጊዜ የመውሰዳቸው ምክንያት እንደሆነ ያሳያል።

ሌላው ግኝት ሴቶች ከሴቶች ጋር መሳለመሳ ሆነው ሲነጋገሩ መደማመጥ እንደማይችሉና ድርሻን ጠብቆ የመናገር ችግር እንዳለባቸው ታይቷል። ይህ መስማማት አለመቻል የሚከሰተው ተራን ጠብቆ ካለመናገር የመጣ ነው። በአንፃሩ ደግሞ ወንዶች ድርሻን ጠብቆ የመናገር ችግር ባይታይባቸውም በሚናገሩበት ጊዜ ሌላ ወንድ ሲናገር ምኞት አይሰማቸውም፤ እንዲውያም ከመስማማት ይልቅ መራራቅ ጎልቶ እንደሚታይ ሻን (1999) እና ውድ(2010) ያስረዳሉ።

ከዚህ በተለየ መልኩ ደግሞ ከወንዶች ይልቅ ሴቶች በንግግር ወቅት የመደጋገፍ ባህርይ ያላቸው መሆኑን የፊሽማን (1985)፣ የዝመርማን እና ዌስት (1975) እንዲሁም የኮትስ (1989) ጥናቶች እንደሚያረጋግጡ ሻን (1999) ይገልፃሉ። ይህም ሴቶች ከኋላ ሆነው በንግግር ወይም በሰውነት እንቅስቃሴ ስሜታቸውን በመግለፅ ለንግግሩ ምላሽ በመስጠት

ተናጋሪው ንግግሩን እንዲቀጥል አለያም እንዲያቆም የማድረግ ሀይላቸው ከወንዶች ይልቅ የጎለበተ ነው። ባሬትና ዴቪድሰን (2006) እንደሚሉት የዚህ አይነቱ ምላሽ ለተናጋሪው ጥንካሬን የመፍጠር፣ የማበረታታትና የማስተካከል አቅም አለው። በተጨማሪም ሴቶች በንግግር ወቅት ለተናጋሪው የሚያሳዩትና የሚሰጡት አዎንታዊ ምላሽ ተናጋሪው ንግግሩን በጥሩ ሁኔታ እንዲቀጥል የማድረግ ሀይል እንዳላቸው ይታመናል። ተናጋሪው ሰሚ አግኝቻለሁ የሚል ስሜት እንዲያድርበትም ያደርጋሉ። ይህ በሌለበት ሁኔታ የተናጋሪው ስሜት የተከፋፈለና ንግግሩንም መሰማት አለመሰማቱን ለማረጋገጥ መደጋገም እንዲታይበት ያደርገዋል። ለዚህም የአድማጭን ስሜት ምን እንደሚመስል ማወቅ ለተናጋሪው መልካም ሁኔታ ይፈጥራል። ይህም ሴቶች ተናጋሪው በሚናገርበት ጊዜ ንግግሩን የተቀላጠፈና የተሳካ እነዲሆን ከመተባበር አንፃር የሚተገብሩት ነው ተብሎ ቢታሰብም አጨቃጫቂ እንደሆነ ግን ጥናቱ ያረጋግጣል።

ከዚህ በተጨማሪም ሌሎች ጥናቶች የሚያረጋግጡት ሴቶች ግጭቶችን የማስወገድ ብቃት እንዳላቸውና፣ ይህም ከትዕዛዝ በራቀ አንደበታዊ አቀራረብ በመጠቀም ማቻቻል ከመቻላቸው የመጣ ችሎታ እንደሆነ ሻን (1999) እና ውድ(2010) ይገልፃሉ። በጥቅሉ ሲታይ የሴቶች የንግግር ፍላጎትና አተገባበር የሚያነጣጥረው በትብብር፣ በጓደኝነት፣ በአንድነት፣ በእኩልነት፣ በመረዳዳት፣ በመገንዘብ ላይ ነው። በእርግጥ ሴቶች በስራቸው ላይ ልምድ እያካበቱ ሲሄዱ በራስ የመተማመን መንፈሳቸው እንደሚጎለብትና በንግግር የበላይነትን እንደሚይዙ በዚህም ስለራሳቸው ‹‹እኔ›› በማለት እንደሚገልጹ ባስ(2001) በጥናታቸው ገልፀዋል። ወንዶች በተፃራሪው ንግግራቸው በግልፅነትና በመቻቻል ላይ ከማተኮር ይልቅ፤ በመታወቅ፣ በበላይነት ስሜትና ደረጃቸውን በመጠበቅ ዙሪያ ያነጣጥራል። ይህም በመሆኑና ሁለቱም የተለያዩ ስሜት በመያዛቸው ሴቶችና ወንዶች በሚያደርጉት ተግባቦት ዙሪያ የመዋለል ስሜት ይንፀባረቃል። ይህም ልዩነትና አለመግባባትን እንደሚፈጥር ታነን (1990,1991) እና ባሬትና ዴቪድሰን (2006) ይገልፃሉ።

ታዲያ ለምን ነው ይህ መሰሉ ልዩነት የተከሰተው የሚለው ጥያቄ መነሳቱ አይቀሬ ነው። ይኸውም ሴቶችና ወንዶች በአንድ ቤተሰብ ውስጥ አብረው አድገው፣ ወደትምህርት ቤት

አብረው ሂደው፣ አንድ ላይ ስራቸውን እያከናወኑና በማህበር አብረው እየኖሩ ይህ የአነጋገር ልዩነት እንዴት ሊከሰት ቻለ የሚለው ጉዳይ ሰፊ ጥናት ያስፈልገዋል።

ታነን (1991) እና ሻን (1999) እንደሚሉት በሴቶችና በወንዶች መካከል ለሚታየው የአነጋገር ስልት ልዩነት መንስዔ አንዱ የወንዶች የበላይነት መንፀባረቅና የሴቶች የበታችነት ስሜት በንግግር ወቅት መታየት ሲሆን፣ የዚህ ክስተት ዋና ምክንያት የበላይነት ስሜት ማሳደር የፈጠረው ተፅዕኖ ይመስላል። ምክንያቱም በአብዛኛው ወንዶች በአካላዊ ብቃት፣ በገቢ መጠን፣ በስራ ቦታ ላይ በሚታየው ተዋረድ የበላይ ሆነው መታየታቸውና ሆነውም በመንቀሳቀሳቸው ምክንያት የተፈጠረ ነው። የፊሽማን (1980) ጥናትም የሚያረጋግጠው በተወሰነ አጋጣሚና አካባቢም ቢሆን ተቀባይነት እንዳለው አረጋግጧል። እንደምሳሌም ሴቶች በንግድና መሰል ተቋማት ዙሪያ በስብሰባ ላይ መናገር እንደሚችሉ ግን ደግሞ ወንዶች ጣልቃ እንደሚገቡባቸውና የሚናገሩትንም እንደቁም ነገር እንደማይወሰድ ተጠኚዎቹ መግለፃቸው በጥናቱ ተመልክቷል። እንደ ሻን (1999) አገላለጽ፣ ለዚህ ችግር ዋናው ምክንያት ሴቶች አቅም የለሽና የጥቃት ሰለባ ተደርገው መወሰዳቸው ሲሆን፤ ወንዶች ደግሞ ሴቶችን የበታችና ስኬታማ ሊሆኑ እንደማይችሉ አድርገው መቁጠራቸው ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ማህበረሰቦች የሴቶችና ወንዶች የአነጋገር ልዩነት ከስነተፈጥሮ ሆርሞን መጠን ጋር የሚያያዝ ነው ይላሉ። ይኸውም ወንዶች ከሴቶች ጋር ሲነፃፀሩ ቁጡ የሆነ ስሜት እንዳላቸውና ለዚህም ምክንያቱ ከሴቶች ይልቅ የወንዶች የሆርሞን መጠን ከፍተኛ ስለሆነ ነው ብለው ያምናሉ። ሌሎች ደግሞ ይህን ልዩነት ከማህበራዊነት ጋር በማያያዝ ሴቶች ከመጀመሪያው ትሁትና የሌላውን ስሜት የሚጠብቁ ሆነው እንዲያድጉ እንደሚጠበቅ ይገልጻሉ። የወንዶች ግን ከዚህ በተቃራኒ ንቁና ቀልጣፋ ሆነው ማደግ እንዳለባቸው ይታመናል። ይህ ማህበራዊ ጉዳይ በማህበረሰብ ዘንድም ተቀባይነት ያለው ነው። ይህም በመሆኑ ሴቶች የሚገፉትና እንዲሆኑም የሚጠበቁት በማህበረሰቡ ዘንድ ሀይል የለሾችና ከወንዶች ያነሰ ሀይል እንዲኖራቸው ነው (ሻን፣1999 እና ዌስት እና ዝመርማን፣1987)።

በአጠቃላይ በቋንቋ አጠቃቀማችን ዙሪያ የምናገኘው ፆታዊ መረጃ ስለስርዓተ-ፆታ ያለንን ግንዛቤ ገላጭነት ይታይበታል። የምናስበውና የተገነዘብነውን ነገር ይሆናል ብለን ከምናስበው ነገር ጋር ስለሚጣረስ ሁሌም ያለን ማህበራዊ ግምት ተጨባጭ ላይሆን እንደሚችል መገመት ያስፈልጋል። ከዚህም አንፃር በተለያዩ የስራ ቦታዎች ለተሰማሩ ሰዎች ለስራቸውም ሆነ ለአነጋገራቸው የምንሰጠው ግምት የተዛባ ይሆናል። ቀጥሎ ደግሞ እስካሁን የተመለከትነው የአነጋገር ስልት ልዩነት ይህ ጥናት በሚተኩርበት በስራ ቦታ ላይ ምን እንደሚመስል የተለያዩ ጥናቶች ተቃኝተው ቀርበዋል።

ንግግር በስራ ቦታ ላይ ሲታይ ውስብስብነት ያለው ሲሆን፣ ንግግሩ ደግሞ እጅግ ሰፊ ደረጃዎች ያሉትን ትርጓሜዎች አካቶ ስለሚይዝ በዲስኩር/በተግባቦት ትንተና ቢታይ የተሻለ ግንዛቤን እንዲኖር ያደርጋል። ይህም ሰፋ ባለሁኔታ የዲስኩር ትንተና ከቋንቋው አጠቃቀም፣ ከማህበራዊና ከባህላዊ አውድ አንፃር ቢታይ ለቋንቋው ተግባቦት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር ጋምፐረዝ (1982) ይገልፃሉ። የቦርድዩ (1977) ጥናትም የሚያረጋግጠው ባህልን መሰረት ያደረገና በዚህም ዙሪያ የሚመጥን የቋንቋ አጠቃቀም በተለይም በስራ ቦታ የሠመረ ጠቀሜታ ማስገኘቱ እውን መሆኑን ነው። ነጋዴ የሠመረ ንግድ ለማካሄድና የተሻለ ለመስራት መልካም ተግባቦት እንዲኖር የሚያስችል የቃል መረጣና የቋንቋ አጠቃቀም ከሌለ ንግዱን እንቅፋት ሊገጥመው እንደሚችል ይገመታል። ስለሆነም በንግግር መግባባት ውስብስብ በመሆኑ እያንዳንዱ ተናጋሪ ሊጠነቀቅበትና ዋጋ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ መሆኑን ሻን (1999) ያሰምሩበታል።

እንደ ባሬት እና ዴቪድሰን (2006) አገላለጽ ጥበብ የተሞላበትና ጥንቃቄ ያልጎደለው የጋራ መግባባት ለጥሩ አመራር ስኬት በጣም አስፈላጊ ነው። ስለሆነም ተሳትፎ የታከለበት አመራር ለአመራሩም ሆነ ለሚመራው ተቋም ወሳኝ ነው። ለዚህ ደግሞ አንደበታዊ ተግባቦት በስራ ቦታ ላይ ጓዳዊ የሆነ ግንኙነት የመፍጠር ሃይል አለው። ይህም ውጤታማ ያደርጋል። ለስራ ሃላፊዎች የሚሰጥ የማዳመጥ ጥበብ፣ የሰዎችን ውስጣዊ ስሜት፣ ማንነትና ልዩነት መገንዘብ መቻልና ተገንዝቦም ተገቢውን የማሻሻያ ገንቢ ሃሳብ እንዲሰጡ የሚያስችል ስልጠናን አስፈላጊነትንም ምሁራኑ ያሰምሩበታል። ምክንያቱም የንግግር ጥበብ ከፆታ ጋር ግንኙነት ያለውና በሴቶችና በወንዶች መካከል በስራ አመራር ላይ ተፅዕኖ ያለው በመሆኑ ነው። ይህም የወንዶች የበላይነት በነገሰበት የስራ ቦታ ላይ ወንዶች

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. BOX 1176
ADDIS ABABA, ETHIOPIA

በአርያነት ስለሚታዩ በሴቶች ላይ ትልቅ የስራ ላይ ተፅእኖ ይፈጥራል። በሁለቱም ፆታዎች ያለው ክፍተት በስርዓተ-ፆታ ዙሪያ ያለው አመለካከት የፈጠረው ጉዳይ እንደሆነ የሰራተኞች ማህበር ጉዳይ ጥናቶች እንዳረጋገጡ ወርዝ (2000) ይገልፃሉ። ለምሳሌ ሰሜን አሜሪካን ስንመለከት በስራ ቦታ ላይ ለመግባባትና የተሻለ ችሎታ እንዲኖር ለማድረግ፣ በተለይም በሴትና በወንድ ሰራተኞች መካከል ያለውን የተግባቦት ጫና ለመቀነስ የስራ ላይ የተግባቦት ክህሎት ስልጠና መስጠት አስፈለጊ እንደሆነ ታምኖበታል። በመሆኑም መልካም ተግባቦት ለጥሩ አመራር አስፈላጊ መሆኑንና የአነጋገር ስልት ለአንድ የስራ ተቋምና ለተቋሙ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ በፍጥነት ለማደግ ወሳኝ መሆኑን የሰራተኞች ማህበር ጉዳይ ጥናት አረጋግጧል(ዝኪከማሁ)።

በመሰረቱ አንድ ማህበረሰብ በወንዶች የበላይነት የሚያምንና የሚመራ ከሆነ በተቋሞቹም ውስጥ የሚኖረው አስተዳደራዊ መዋቅር ወንድ ተኮር ይሆናል። የወንድ የበላይነትም ይንፀባረቃል። ስለሆነም በዚህ ተቋም ውስጥ እንደአርአያ የሚታዩት ወንዶች እንጂ ሴቶች አይደሉም። በዚህም የተነሳ በስራ ቦታ ዋና ሰዎች ወይም አስፈላጊዎች ወንዶች በመሆናቸው ለሴቶች ግምት አይሰጥም። ስለሆነም በእንደዚህ ያለው ተቋምና አካባቢ ይህን አድሏዊ የሆነ አመለካከት ለማስወገድ ወንዶችንም ሆነ ሴቶችን እኩል ትኩረት ሊሰጥ የሚችል የተግባቦት ስልት ሊለመድ ይገባል፤ መፈጠርም አለበት (ባሬት እና ዴቪድሰን፣2006)።

በእርግጥ ባህላዊና ጥንታዊ በሆነው የስራ ቦታ ባህርይ ለወንዶች የበላይነትና አርያነትን ትኩረት የሚሰጥና ሴቶችን ዝቅ የሚያደርግ ልምድ የሚታይበት ነው። ምክንያቱም ወንዶች ችግርን የሚጋፈጡና ለስራ ትኩረት የሚሰጡ ተደርገው ስለሚታዩ ነው። እንደ እነ ወርዝ፣ (2001)፤ ባሬት እና ዴቪድሰን፣(2006) ገለፃ፣ መሆንና መለመድ ያለበት ግን በአንድ የስራ ተቋም ውስጥ እድገት ለማምጣት፣ ጥሩ አመራር ለመፍጠርና በጥምረት ስራን በስኬት ለመወጣት ሴቶችና ወንዶችን ያዳመረ አመራርና ሱፐርቪዥን መቅረፅ ነው። ይህን ለማድረግም የመስማማትና የመደጋገፍ ባህልን በመከተል፣ ከባህሉ አንፃር የተቃኘና የተለመደ የአሰራር ባህል መፍጠርና መተግበር የግድ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ባህል የሚለመድ እንጂ አብሮ ከማህበረሰቡ ጋር የተፈጠረ አይደለም። ማንኛውም ሰው ስርዓተ-ፆታዊ ሚናውንና አበርክቶውን የሚወርሰው ከልጅነቱ ጀምሮ ነው። ስለሆነም የስራ ባህሉም

ከዚሁ ከልጅነት ጀምሮ የሚለመድ ይሆናል። ይህም ለዘለቄታው ከፍተኛ ጫና ከማሳደሩ በላይ በቀላሉ የሚቀየር አይሆንም። የባህል አመለካከት ተዕዕኖ የሴቶችንና የወንዶችን የስራ ሁኔታና የንግግር ስልት ይወስናል። ብሎም ከባቢያዊ ልዩነት በሴቶችና በወንዶች ዙሪያ እንዳለ ያምናል። ይህንም ከስራ ድርሻ አኳያ ብንመለከት የሴቶችንና የወንዶችን የስራ አይነት እስከመወሰን ድረስ ይጓዛል። ወንዶች ጥንካሬ የሚጠይቁ ስራዎችን ለምሳሌ የሽያጭ ሰራተኛ ብሎም ከፍተኛ ውድድር ያለበትን ስራ መስራት እንዳለባቸው ሲታመን፤ ሴቶች ደግሞ ብዙም ጉልበት የማይሻውን እንደመምህርነት፣ በጎ አድራጎት፣ ነርስነትና የመሳሰሉትን እንዲሰሩ እንደሚመረጥና ይህም ባህላዊ ተዕዕኖው የፈጠረው እንደሆነ ከሩ እና ኤግሊ (1999) እንዲሁም ሳረንጂ እና ሮበርት (1999) ያስረዳሉ።

ከዚህም ባለፈ ባህል ውስጣዊ ማንነትን በመወሰን የራሱ ሃይል አለው። ይኸውም ወንዶች ወኪል የመሆን ብቃት ያላቸው፣ በራሳቸውና በችሎታቸው የሚተማመኑና ተወዳዳሪዎች እንደሆኑ፤ በአንፃሩ ሴቶች ደግሞ ማህበራዊነትንና ጓደኝነትን፣ የሚያበረታቱ፣ ሩህሩሆች፣ ስስት የማይታይባቸውና፣ ስሜታቸውን መግለፅ የሚችሉ ተደርገው መታየታቸውን ጥናቶች ያረጋግጣሉ። ከዚህ አንፃር ሲታይ ለመሪነት የሚመረጠው ፆታ ወንድ ሊሆን እንደሚችልና የተወሰነ ተደርጎ ይወሰዳል። ሴቶች በማህበረሰቡ ዙሪያ የሃላፊነቱን ቦታ ለመያዝ፣ ሃላፊ ሆኖ ለመመረጥና በስራው ላይ ስኬታማ ለመሆን የወንድ ጥንካሬን መላበስ ይኖርባቸዋል። በስራ ቦታ ላይ የሴቶች የመምራት ብቃት ዝቅ ተደርጎ ከታየ ደግሞ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ሳይግባቡ ይቀራሉ። በአቻ ደረጃ ተግባብቶና ተነጋግሮ መስራት ይሳናቸዋል፤ መማማርም አይቻልም። ስለሆነም ስርዓተፆታዊ ንድፈ ሃሳብን መሰረት በማድረግና የማህበረሰብን ባህል ብሎም የማህበረሰብን ድርሻ ከፆታዊ እሳቤ ጋር አዋህዶ ሙያዊ እገዛና ስልጠና በማካሄድ የወንድ የበላይነት የሚንፀባረቅበትን ተቋም መለወጥና ማስተካከል ይቻላል። በስራ ቦታ ላይ ደግሞ በጋራና በስምምነት ሃሳብ ለሃሳብ እንዲሁም ባህል ለባህል መለዋወጥ መቻል ትርጉሙ የመግባባት ስሜት ምልክት ነው። ይህም ግጭቶችን ለመፍታት፣ ተግባብቶ ውሳኔ ለማስተላለፍ፣ ለመወያየትና ብሎም ለመከራከርና ለመስማማት ያስችላል በማለት ሳረንጂ እና ሮበርት (1999) ያስረዳሉ።

በቋንቋና በፆታ ዙሪያ የተደረጉ ቀደምት ጥናቶች እንደሚያረጋጡት (ሽን፣1999 እና ድርያናን፣2011) ማንነትንም ሆነ ግንኙነትን ለመግለፅ በርካታ ፆታ ነክ የሆኑ ድስኩራዊ

የስነልሳን ሀብቶች ያገለግሉ እንደነበር አረጋግጠዋል። ይህም ሴቶችና ወንዶች በተግባቦት ሂደት ተመሳሳይ ስልት የሚጠቀሙ መሆኑንና አለመሆኑን እንዲሁም እንዴትስ ሊለያይ እንደቻለ የሚናገሩትን ንግግር በመመርመር ለማየት የንግግር ባህላቸውን መፈተሽ ያስችላል።

በአጠቃላይ በስራ ቦታ ላይ የሚደረጉ ንግግራዊ መስተጋብሮች የእያንዳንዱን ተናጋሪ ባህርይ ምን እንደሚመስልና ምን ለማስተላለፍ እንደፈለገ፣እንዲሁም እምነቱን ያስተላለፈበትን መንገድ አንድ በአንድ ለመለየትና በዝርዝር ለማስቀመጥ ያስችላል። ለምሳሌ ፌርክላፍ (1992) ያጠኑትን ጥናት ብንወስድ አንድ ባለስልጣን በስብሰባ ላይ በሚያደርገው ንግግር ስልጣኑን መከታ በማድረግ የሚናገረውን ከንግግሩ መለየት እንደሚቻልና ለዚህም የሚጠቀምበት ስልት መኖሩንና ስልጣኑ በሰጠው በራስ የመተማመን መንፈሱን በተለያየ ሁኔታ እንደሚያንፀባርቅ አመልክቷል። ለምሳሌ ‹‹በዚህ ስብሰባ ላይ ምን ማድረግ እፈልጋለሁ›› ብሎ ሊናገር ይችላል። ይህም የባለስልጣን ንግግር መሆኑን ማየት ይቻላል። ሌላው የስብሰባ ተሳታፊና ስልጣን የሌለው ደግሞ ማለት የሚችለውና ሲል የሚደመጠው ‹‹ምን ማድረግ ብንችል ይሻላል››፣ ‹‹ይህ ቢደረግ››፣ ወዘተ. የሚል ሲሆን ሙሉ በሙሉ ሊወስን አይደመጥም። ይህም በመሆኑ ምክንያት በስብሰባ ላይ ተሰብሳቢው ማንነቱንና የስልጣን ተዋረዱን አነሰም በዛም በተለየ የንግግር ስልት በመጠቀም ሲገለፅ ይስተዋላል።

ባጠቃላይ በስራ ቦታ የሚፈጠር ተግባቦታዊ ስልት ከስርዓተ ፆታ አንፃር በውጭ አጥኝዎች ይህን ያህል ትኩረት ተሰጥቶት የተጠና ሲሆን፤ በሀገር ውስጥ ሃይላይ (2009) በትግርኛ ቋንቋ በሴትና በወንድ ደራሲያን የተፃፉ ልቦለድ ድርሰቶች በመውሰድ የሴቶችንና የወንዶችን ተግባቦታዊ ስልት ተመልክቷል። በዚህም ወንዶችም ሆኑ ሴት ገፀባህርያት በከፍተኛ ደረጃ ትህትና የተላበሱ አጠቃቀሞችን የሚጠቀሙ እንደሆኑና ሴቶች ግን በተግባቦት ሂደት የሚሰጡት ምላሽ እጅግ አጫጭር ለምሳሌ አዎ፣ እህ፣ የመሳሰሉትን የሚጠቀሙ ከመሆናቸው ባሻገር ጉዳዮችን በግልፅ ከማቅረብ ይልቅ አድበስብሰው እንደሚያልፉ ጥናቱ ያሳያል። ከዚህ በተለየ ግን በአገራችን ተፈጥሯዊ የሆነውን የስራ ቦታ አውድ በመውሰድ በተቋሙ ሰራተኞች መካከል የሚደረጉ መደበኛና ኢመደበኛ ተግባቦታዊ መስተጋብር ትንተና የተደረገ ጥናት፣ በተለይም በከፍተኛ ትምህርት ተቋም በሚገኙ

መምህራን መካከል የስርዓተፆታ ተግባቦታዊ መስተጋብርን የሚመለከቱ ጥናቶች አጥኝዋን አላጋጠሟትም፡፡ ስለሆነም በከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚታይ ስርዓተፆታዊ የተግባቦት ስልት ምን እንደሚመስል መመርመሩ አጅግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

በመሆኑም የዚህ ጥናት ትኩረት በግለሰቦች ተግባቦታዊ ስልት ልዩነት ዙሪያ የሚያጠነጥን ሲሆን በተለይም በተወሰኑና ተናጋሪዎች በይበልጥ በሚጠቀሙትና በሚመርጡት ስርዓተ-ፆታዊ የስነልሳን ምርጫ ላይ ይሆናል፡፡ በተለይም በንግግራቸው ወቅት ሀሳባቸውን አጠንክረው ሊገልፁ በሚፈቅዱበት ስነልሳናዊ አጠቃቀም ላይ ያተኩራል፡፡ በዚህም መሰረት ለጥናቱ የተመረጠው ተግባቦታዊ አውድ የስራ ቦታ ሲሆን፣ ይህም በስራ ቦታ ላይ የሚደረጉ ውይይቶች የራስን አላማ ማንፀባረቅ በማስቻል ረገድ ጠቀሜታው ጠንከር ያለ በመሆኑ ነው (ሙምባይ፣1988)፡፡ ስለሆነም የጥናቱ ትኩረት ሰዎች በስራ ቦታ ላይ ከሌሎች አቻዎቻቸው ጋር የሚግባቡት እንዴት እንደሆነ፣ ሀሳባቸውን እንዴት እንደሚገልፁና እንዴት መስማማት እንደሚችሉ ለማየት፤ እንዲሁም ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በስራ ቦታቸው ላይ ያላቸውን ድርሻ እንዴት እንደሚገልጹና የንግግር አቀራረባቸውን ሁኔታ በማየት የተናጋሪዎቹን የተግባቦት/የዲስኩር ስልት ይፈትሻል፡፡ ይህም በስራ ላይ በሚያደርጉት ንግግራዊ መስተጋብር የቋንቋ አጠቃቀማቸው ስልት የስልጣን ደረጃን፣ የአመለካከትንና የመሳሰሉትን በማሳየት ግለሰቦቹ በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን የግንኙነት ደረጃ ዓይነትና የተደበቀ ባህርይ ለማሳየት ያስችላል፡፡ በተጨማሪም በስራ ላይ በተለያዩ ስብሰባዎችም ሆነ መስተጋብሮች ላይ የሚደረግ የንግግር አቀራረብ ባለሙያዎች (ተሰብሳቢዎች) እንዴት መደራደር እንደሚችሉ፣ የሙያ ብቃታቸውንና ፆታንም ሆነ ማህበራዊነትን እንዴት እንደሚገልፁ ያሳያል (ፌርክላፍ፣2001)፡፡

1.2 የጥናቱ መነሻ ችግር

በቋንቋና በፆታ ዙሪያ በስፋት ከሚደረጉት ጥናቶች መካከል አንዱና ዋናው ትኩረት እያገኘ የመጣው በፆታና ዲስኩር ላይ ያተኮረ ጥናት ነው፡፡ በዚህ የጥናት ዘርፍ ምርምር ማድረግ የተጀመረውና ትኩረት እየሳበ የመጣው፣ የተለያዩ የሙያ መስኮች ባሉባቸው የስራ ቦታዎች ላይ ሴቶች መምጣትና መታየት ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ ሲሆን፤ በዚሁ በሽግግሩ ወቅት የፖለቲካና የማህበራዊ ግጭቶች እየሰፉ በመምጣቸውና በስራ ቦታ ላይ የፆታ

ተባልጦ በመከሰቱ እንደሆነ ሙላኒ (2007) ይገልፃሉ። እንዲህ ዓይነቱ ጥናት በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በስፋት የመጠናት ትኩረት እያገኘ የመጣ ሲሆን፣ የጥናቱ አላማም በስራ ቦታ ላይ ሁለቱ ተቃራኒ ፆታዎች እንዴት ዲስኩር እንደሚለዋወጡ ለማጥናት ነው። ይህም የሚያመለክተው በአንድ ተቋም ውስጥ የሙያው ሰዎች የሚናገሩበትን ቋንቋ ማጥናት አስፈላጊና ቀዳሚ ተግባር መሆኑን ነው (ሙላኒ፣ 2007 እና ዋርተን፣2005)።

ሆኖም ግን በአገራችን በስራ ቦታ ላይ ሴቶች ከወንዶች ጋር በሚያደርጉት ስብሰባም ሆነ ውይይት ላይ ሃሳባቸውን፣ አመለካከታቸውን፣ ማንነታቸውንና ስልጣናቸውን ለመግለፅ የሚጠቀሙበት የንግግር ስልት (ዲስኩር) ምን እንደሚመስል የተጠናና ተመዝግቦ የሚገኝ ነገር የለም። የተግባቦት ስልት ከባህል ባህል የሚለያይ ሲሆን፣ ይህ ደግሞ የሚያሳየን ከባህል ጋር እጅግ የጠበቀ ቁርኝት እንዳለው ነው። ይኸውም ባህል የሚገለፀው በቋንቋ ነውና በየደረጃ የሚደረጉ ንግግሮችን ወስደን ስንመለከት እንደየባህሉ አንፃራዊ ናቸው (ቫን ዲጀክ፣2002)። ለምሳሌ ወስደን ብንመለከት አንዳንድ ማህበረሰቦች ውስጥ ማህበራዊ ደረጃቸው ከፍ ያሉት የመናገርና የፈለጉትን የማድረግ መብት ሲሰጣቸው ተራውና ዝቅተኛው የህብረተሰብ ክፍል ደግሞ ማዳመጥ ብቻ ተግባሩ እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል። ለምሳሌ በእንግሊዝ አዋቂዎች ሲናገሩ ህፃናት መናገር አይፈቀድላቸውም። እንዲያውም የሚያዳምጣቸው የለም። በአንፃሩ አሜሪካዊያን ደግሞ ህፃናት ራሳቸውንና ሃሳባቸውን እንዲገልፁ ያበረታታሉ፤ ይህ ሁኔታ በተመሳሳይ በሴቶቻቸውም ላይ የሚታይ ነው (ታነን 1999)።

ባህል ባብዛኛው ልዩ የሆነውን ግንኙነት በመግለጽና በማሳየት ረገድ ልዩ ቦታ ያለው ከመሆኑ ባሻገር በማህበረሰቡ ውስጥ ከስርኣተ ፆታ አንፃር የሚታየውን ማህበራዊ ደረጃ እና የግንኙነት ድንበርን ከቅርበትና ከርቀት አኳያ የመወሰን ሃይል አለው (ታነን፣ 1994)። ይህንንም ለአብነት በሰሜንና በተወሰኑ የደቡብ ኢትዮጵያ አካባቢ የሚገኙ የቋንቋ ተናጋሪዎችን ብንመለከት ሴቶች የባላቸውን ስም የማይጠሩበት ሁኔታ ሲኖር፣ ባላቸውን ለመጥራት የሚጠቀሙበትን የአነጋገር ስልት ስንመለከት ደግሞ የተለያየ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህም በተለያዩ ቋንቋዎች የሚደረጉ ንግግሮች እንደ ተናጋሪው ባህል የሚወሰን መሆኑን ያሳያል። በተጨማሪም በስራ ቦታ ላይ የሚደረግ ስርዓተ ፆታዊ የተግባቦት ስልት እንደየማህበረሰቡ ባህል ብቻ ሳይሆን እንደ ስራ ተቋሙ ባህልም

የሚወሰን መሆኑን ሻን (1999) ይገልጻሉ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሲሲሊያ (2001) ዝንባቡዌ በሚገኙ አራት ካምፓኒዎች ሃላፊዎቹ በሚያደርጓቸው ስብሰባዎች ላይ የሴቶችንና የወንዶችን የአነጋገር ስልት ምን እንደሚመስል ባጠኑት ጥናት ወንዶች በማኔጅመት ስብሰባ ላይ ሀይል የሚያሳዩ ሲሆን ሴቶቹ በተቃራኒው ስነምግባር የተሞላበት አቀራረብ እንደሚጠቀሙ ገልፀዋል።

እንደ ማክለኒ(2003) አገላለጽ የአነጋገር ስልትን በመመርመርና በመለየት የፆታን የበላይነትና የበታችነት ተባልጦን ማሳየት ይቻላል። ይኸውም የዲስኩር ትንተና ማድረግ የተግባቦት ስልት በስራ ቦታ ላይ በሴትም ሆነ በወንድ መካከል የበላይነትና የበታችነት እየፈጠረ መሆን አለመሆኑን መፈተሽ ያስችላልና ነው። በተጨማሪም ሙላኒ (2007) እንደሚሉት ይህ የጥናት አይነት የቋንቋ አጠቃቀም ሴቶች እድገት እንዳያሳዩ ጫና ማሳደር አለማሳደሩ ለማየት ያስችላል። በመሆኑም እስካሁን የተዳሰሱት ጥናቶችና ንድፈ ሃሳቦች በአገራችን በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች በስራ ቦታ ላይ የሚታየውን ስርዓተ ፆታዊ የተግባቦት ስልት ትንተና ለማካሄድ እንደ መነሻ ሆነዋል:: በአጠቃላይ አጥኚዋ ይህን ጥናት እንድታጠና የተነሳሳችባቸው ምክንያቶች፤

- በኢትዮጵያ አሁን አሁን ቁጥራቸው በርከት ያሉ ሴቶች በከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና በተለያዩ መስሪያ ቤቶች በስራ ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ። ሆኖም ግን በአመራር ደረጃ የሚገኙ ሴቶች በቁጥር ከሚጠበቀው በታች መሆናቸውንና፣ አንዳንዴ ደግሞ ቦታው ላይ ከወጡ በኋላ ወዲያውኑ ሲለቁ ይታያል። እንዲሁም ትምህርት ሚኒስቴር በ2002 ዓመተ ምህረት ባወጣው ‹‹አገር አቀፍ የሴቶች ትምህርት ስትራቴጂ›› በሚለው ሰነድ እንደተገለጸው በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በአመራር ደረጃ ከዝቅተኛው ትምህርት ክፍል ተጠሪነት እስከ ከፍተኛው ፕረዚዳንት ድረስ የሚገኙ ሴቶች በጣም ዝቅተኛ ተሳትፎ ያላቸው መሆኑንና በቁጥርም በየተቋማቱ ከሚገኙት ሴት መምህራን ጋር ሲነፃፀር እጅግ አነስተኛና አሳሳቢ ጉዳይ መሆኑን መግለጹና ይህ ጉዳይ በአሁኑ ወቅት በአገር ደረጃም እንደችግር የተወሰደ በመሆኑ፣ ምናልባትም የቋንቋ አጠቃቀም በሴትም ሆነ ወንድ መካከል በስራ ቦታ ላይ የበላይነትና የበታችነት እየፈጠረ መሆን አለመሆኑን ለመፈተሽ፣

- በሀገራችን በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች የሴት መምህራን ቁጥር ከወንዶች ጋር አቻ ባይሆንም በርካታ ሴት መምህራን ይገኛሉ። ሆኖም ግን በአገር ደረጃም ሆነ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ትምህርታዊ እቅዶች ሲታቀዱ፣ ስርዓተ-ትምህርቶች ሲዘጋጁ፣ የተለያዩ ውይይቶችና ምክክሮች ሲደረጉና ውሳኔዎች ሲወሰኑ ሴት መምህራን በአብዛኛው ተሳታፊ አይደሉም። ይህም በእነዚህ ተግባራት የሚሳተፉት የሃላፊነት ቦታዎች ላይ የሚገኙ ሰዎች በመሆናቸውና በእነዚህ የስራ ቦታዎች ደግሞ ሴቶች ባለመገኘታቸው ምክንያት ነው። እንደግሬይ (2002) በስራ ቦታ የሚገኙ ሴቶችና ወንዶች ከተለያየ ፕላኔት እንደመጡና በዚህም የተለያየ ልምድ ያላቸው እንደሆነ ይገልፃሉ። ይህ ማለት ሴቶችና ወንዶች ባለው ማህበረ-ባህላዊ አመለካከት ምክንያት በተለያየ መንገድ እንደሚያድጉና በዚህ የተለያየ ልምድ እንዳላቸው የሚገልጽ ነው። ጎሩት (1997) በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ ሴትና ወንድ መምህራን የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታቸው ምን እንደሚመስል ባጠናችው ንፅፅራዊ ጥናት የሴቶች የክፍል ውስጥ የአመራር ችሎታቸው ከወንዶች የተሻለ እንደሆነና ከወንዶች በተለየ ሁኔታ ደግሞ በርዕሳነ መምህራንና በተማሪዎች የሚደርስባቸው ተፅዕኖ የበለጠ ስኬታማ እንዳይሆኑ እንዳደረጋቸው በጥናቱ ተገልጿል። ሆኖም ግን ያለውን ተፅዕኖ ተቋቁመውም የተሻለ የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ እንዲኖራቸው ያበቃቸው የእናትነት ግላዊ ተፈጥሯቸውና በዚህ አጋጣሚያቸው ያካበቡት ልምድ እንደሆነ አጥኝዋ ገልፃለች። ከዚህም ባሻገር ይህ የልምድ ልዩነት በሁለቱ ፆታዎች መካከል የተለያየ የቋንቋ አጠቃቀም እንዲኖር ማድረጉንም የተለያዩ ጥናቶች ያስረዳሉ (ታነን፣1994 እና ሻን፣1999)። በመሆኑም ሴቶችና ወንዶች የተለያየ ልምድ ካላቸው በአገር ደረጃም ሆነ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በሚታቀዱ እቅዶች፣ ውሳኔዎችና ተግባራት የሁለቱም ልምዶች፣ እይታዎችና አስተሳሰቦች የማይካተቱ ከሆነ በትግበራው ሂደት ሁሉንም ከማሳተፍ አንፃር ክፍተት ሊኖር ይችላል። ይህ ደግሞ ከተሳታፊዎች አንፃር ብቻ ሳይሆን በስራ ተቋሙ ስኬታማነት ላይም አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖረው ይችላል። እዚህ ላይ ዋናው ነገር ሴቶች ወደስራ ተቋማት ሲመጡ ይዘውት የሚመጡ የአመራር ችሎታ ወይም ልምድ አላቸው (ጎሩት፣1997)። ታዲያ ይህ ከሆነና ሴቶች የአመራር ችሎታው ካላቸው በተለይ በከፍተኛ ተቋማት ወደሃላፊነት ለምን አልመጡም የሚለው ጉዳይ ይነሳል። የዚህ ጥናት አቅራቢ ባለኝ የስራ ልምድ በታዘብኩት መሰረት በአብዛኛው የሃላፊነት

ቦታዎች የሚሰጠው ተግባራዊ ችሎታ ተፈትሾ ሳይሆን የተለያዩ መድረኮችን በመጠቀም ሀሳባቸውንና ራሳቸውን ለሚገልጹ ሰዎች ነው። በዚህም ‹‹ከአነጋገር ይፈረዳል ከአያያዝ ይቀደዳል / አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታል።›› የሚለው የማህበረሰቡ ፍልስፍና አስተዋፅያ ይኖረው ይሆን የሚለውን ጉዳይ በስፋት በማጥናት ለማረጋገጥ መሻት አጥኝዋን ካነሳሳት አብይ ጉዳይ አንዱ ነው።

- መምህራን ሃሳባቸውንና ራሳቸውን ከመግለጽ ባሻገር የሰው ልጅ ሀሳቡን በሰላ ሁኔታ በንግግርም ሆነ በጽሁፍ ራሱን እንዲገልጽ የሚያሰለጥኑም ናቸው። ይህ እውነታ ከመማሪያ ክፍል ውጭ በሚደረጉ የመምህራን የርስ በርስ ትምህርታዊ ውይይቶች ላይ ሲታይ የተለየ ባህርይ ይታያል። አጥኝዋ ባደረገችው የስራ ላይ ምልከታ በአንደኛ ደረጃና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ አብዛኛዎቹ ሴት መምህራን የስራ ጉዳይን በተመለከተ በሚደረጉ ውይይቶች ላይ ሃሳባቸውንም ሆነ ራሳቸውን በመግለጽ ረገድ ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ ነው። ወደከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ስንመጣም ተመሳሳይ ሁኔታ ከመታየቱ በላይ በዚህ ደረጃ ያሉ ሴት መምህራን ከወንድ አቻዎቻቸው ጋር በእኩል ሃሳባቸውንና ራሳቸውን ሲገልጹ አለመታየታቸው፣ ትምህርት ባህልን የመለወጥ አቅሙ ምን ያህል ነው የሚል ጥያቄ ያጭራል። በእርግጥ በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ምሁራን የተግባቦት ስልት በስራ ቦታ ላይ የያታ ተባልጠ የሚያስከትል እንደሆነና ለዚህም ባህል ወሳኝ መሆኑን ገልፀዋል። በመሆኑም የዚህን እውነታ በአገራችን ካለው ባህላዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ አንፃር በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ላይ በስፋት በማጥናት ለማረጋገጥና
- በከፍተኛ ትምህርት በሴትና በወንድ መምህራን መካከል የሚደረገው ስርዓተያታዊ የተግባቦት ስልት ምን እንደሚመስል እስካሁን አልተጠናም። በመሆኑም በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ የሚገኙ የተማሩ ሰዎች እንዴት ስርዓተያታዊ ተግባቦት እንደሚያካሂዱ ለመፈተሽና በዚህ ረገድ ያለውን ንድፈሃሳባዊ ክፍተት ለመሙላት የሚሉት ናቸው።

ስለዚህ በዚህ ጥናት ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ጥያቄዎችን ለመመለስ ጥረት ይደረጋል።

1. ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታ ከስራ ባልደረቦቻቸውቸው ጋር በሚያደርጉት የተግባቦት ሂደት ሀሳባቸውን እንዴት ይገልፃሉ?

   1.1 ሃሳባቸውን አድማጭ በሚረዳው ሁኔታ ባግባቡ እንዴት ይገልፃሉ?

1.2 ድርሻን ጠብቆ ከመናገር አንፃር እንዴት ይሳተፋሉ?

1.3 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በንግግር ያላቸው ተደማጭነት ምን ይመስላል?

1.4 ሰቶችም ሆኑ ወንዶች በተግባቦት ሂደት የቋንቋ አጠቃቀማቸው ምን ይመስላል?

1.5 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በተግባቦት ሂደት የሚያሳዩት ድስኩራዊ ልማድ ምን ይመስላል?

1.6 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በተግባቦት ሂደት ሀሳባቸውን ለመግለፅ ተፅዕኖ አድራጊ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?

2 ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታ ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር በሚያደርጉት የተግባቦት ሂደት ራሳቸውን እንዴት ይገልፁታል?

2.1 የሙያ ብቃታቸውን ለመግለፅ የሚያደርጉት ጥረት ምን ይመስላል?

2.2 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በስራ ቦታቸው ላይ ያላቸውን ድርሻ እንዴት ይገልፃሉ?

2.3 ግላዊ ማንነታቸውን ማለትም በስራ ቦታቸው ላይ ያላቸውን ስልጣን /ደረጃ/ አጉልቶ የማውጣት ስልታቸው ምን ይመስላል?

2.4 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በተግባቦት ሂደት ማንነታቸውን ለመግለጽ ተፅዕኖ አድራጊ ጉዳዮች ምንድን ናቸው? የሚሉት ናቸው።

እነዚህ ሁለት አብይ የጥናቱ ጥያቄዎች የሚስተናገዱት በቋንቋ፣ በስልጣንና በስርዓተ-ፆታ መካከል ባለ ግንኙነት አውድ መሰረት ይሆናል (ቫን፣1993 እና ታነን፣1999)።

1.3. የጥናቱ ዓላማዎች

በገላጭ ጥናት ደረጃ አንድን ጭብጥ ወስዶ በመግለፅና በመተንተን ማጥናት ይቻላል። በዚህም ጥናት ስርዓተፆታን መሰረት ባደረገ ሁኔታ የወንድና ሴት ንግግር(ዲስኩር) በማየትና በመከታተል በከፍተኛ ተቋማት ደረጃ በሚደረግ የስራ ላይ መስተጋብር ወቅት የሚታየውን ተግባቦታዊ ስልት ለመግለፅ ሲሆን፤ በተግባራዊ ስነልሳን ጥናት ደረጃ ደግሞ ስርዓተ ፆታዊ የተግባቦት ስልት በስራ ቦታ ላይ የሚያስከትለውን የስርዓተ ፆታ ተባልጦና ሌሎችንም ችግሮች ለይቶ ለማሳየት ነው።

ከላይ የቀረቡትን የምርምር ጥያቄዎች ለመመለስ ጥናቱ አጠቃላይ ዓላማና ዝርዝር ዓላማዎችን ነድፏዋል። ከዚህም በመነሳት ይህ ጥናት የሚያነጣጥረው በከፍተኛ ትምህርት ተቋም የስራ ቦታ ወንዶችና ሴቶች የሚያሳዩትን የተግባቦት ስልት ልዩነት መኖር አለመኖርን በጥንቃቄ መመርመር ላይ ይሆናል። ይህም እንደባለሙያ በመደበኛና በኢመደበኛ ስብሰባ ላይ እንዴት ለመደራደር ሀሳብ እንደሚያቀርቡ፣ ከሙያቸው አንፃር ያላቸውን የሙያ ሁኔታ እንዴት ማሳየት እንደሚችሉና በዚህም ሂደት የሚታየውን ልዩነት መመዘን የጥናቱ ዋነኛ ዓላማ ነው። በአጠቃላይ ሴቶችና ወንዶች በተግባቦት ወቅት በንግግራቸው እንዴት ለራሳቸው ዋጋ እንደሚሰጡና እንዴት በንግግራቸው ተፅዕኖ ማሳደር እንደሚሞክሩ ለማየት ይሞከራል። በዚህ አጠቃላይ ዓላማ ላይ በመመስረት ጥናቱ ከዚህ በታች የተመለከቱት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል።

1. ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታ ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር በሚያደርጉት የተግባቦት ሂደት ሀሳባቸውን እንዴት እንደሚገልጹ መመርመር፣
   1.1 ሃሳባቸውን አድማጭ በሚረዳው ሁኔታ ባግባቡ እንዴት እንደሚገልጹ መመርመር
   1.2 ድርሻን ጠብቆ ከመናገር አንፃር ያላቸውን ተሳትፎ መፈተሽ፤
   1.3 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በንግግር ያላቸው ተደማጭነት ምን እንደሚመስል መመርመር፤
   1.4 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በተግባቦት ሂደት የሚታየው የቋንቋ አጠቃቀም ምን እንደሚመስል መለየት፤
   1.5 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በተግባቦት ሂደት የሚያሳዩት ድስኩራዊ ልማድ ምን እንደሚመስል መመርመር፤
   1.6 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በተግባቦት ሂደት ሀሳባቸውን ለመግለፅ ተፅዕኖ አድራጊ ጉዳዮችን መለየት፤

2. ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታ ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር በሚያደርጉት የተግባቦት ሂደት ራሳቸውን እንዴት እንደሚገልፁ መመርመር

2.1 የሙያ ብቃታቸውን ለመግለፅ የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል እንደሆነ መፈተሽ

2.2 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በስራ ቦታቸው ላይ ያላቸውን ድርሻ እንዴት እንደሚገልፁ መፈተሽ

2.3 ግላዊ ማንነታቸውን ማለትም በስራ ቦታቸው ላይ ያላቸውን ስልጣን /ደረጃ/ አጉልቶ የማውጣት ስልታቸው ምን እንደሚመስል መመርመር

2.4 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በተግባቦት ሂደት ማንነታቸውን ለመግለጽ ተፅዕኖ አድራጊ ጉዳዮች ምን እንደሆኑ መለየት የሚሉት ናቸው።

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

በስራ ተቋማት ላይ በሚደረግ መስተጋብር አንደበታዊ ተግባቦት፣ ጓዳዊ የሆነ ግንኙነት በመፍጠር ረገድ ቁልፍ መሳሪያ ነው። መግባባት ካለ ደግሞ ስራ በተገቢው መንገድ ስለሚከናወን የስራ ተቋሙም ሆነ ሰራተኛው ውጤታማ ይሆናሉ(ባሬት እና ዴቪድሰን 2006)። ቀደም ብሎ እንደተገለጸው የዚህ ጥናት ዓላማ የአነጋገር ስልትን በመመርመር በስራ ላይ ስርዓተ ፆታዊ ተባልጦን አስከትሎ መሆኑንና አለመሆኑን መረጃዎችን በጥልቀት በመመርመር ማሳየት ሲሆን፣ ውጤቱም የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይገመታል፤

- በተለይም በተግባቦት ስልት ከስርዓተ ፆታ ጋር የተያያዙ ችግሮችን በማሳየት በስራ ቦታ ላይ የሚታይን የተዛባ የስርዓተ ፆታ ግንኙነትን በመቀነስ ረገድ የራሱ ሚና ይኖረዋል።
- ለስራ ተቋማት፣ በተቋማቱ ውስጥ ለሚሰሩ ሴቶችና ወንዶች በስራ ወቅት ውጤታማ ለመሆን የተግባቦት ስልት ወሳኝ መሆኑን ግንዛቤ እንዲያገኙ ከማድረጉም ባለፈ የተግባቦት ስልታቸውን እንዲያሻሽሉ ወይም እንዲያጠናክሩ ያግዛቸዋል። በዚህም ለወንዶች በስራ ቦታቸው ላይ የሚያደርጉት መስተጋብራዊ ተግባቦት ቀና እንዲሆን፤ ለሴቶች ደግሞ በስራ ቦታቸው ሊያገኙት የሚገባቸውን ጥቅማጥቅም ለማስከበር እንዲችሉ ግንዛቤ ይሰጣል።
- ጥናቱ ለተካሄደበት ዩኒቨርሲቲ የተግባቦት ሂደትን ቀና በማድረግ ተቋሙን ውጤታማ በማድረግ ረገድ አስተዋፅኦ ይኖረዋል።

- ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ስርዓተ-ፆታዊ ተግባቦት ምን እንደሚመስል መረጃ በመስጠት በስራ ቦታቸው ቀና የሆነ ተግባቦታዊ መስተጋብር እንዲኖር አስተዋፅኦ ይኖረዋል።
- በመስኩ ተመራማሪዎችን ከማነሳሳት በተጨማሪ፣ ጥናቱ ለተግባራዊ ስነልሳን ጥናት በተለይም ቋንቋን ለተለየ ጠቀሜታ ለማዋል ለትምህርት ተቋም ወይም ለተግባራዊ ትምህርት ለሚውሉ ጥናቶች መነሻ ሊሆን ይችላል።
- በተግባቦታዊ ስልት ትንተና ጥናት ደግሞ የስርዓተ-ፆታ ተላውጦ እስከ ምን ድረስ እንደሆነ መረጃ ይሰጣል።

1.5 የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ትኩረት በግለሰቦች ተግባቦታዊ ስልት ልዩነት ዙሪያ የሚያጠነጥን ሲሆን በተለይም በተወሰኑና ተናጋሪዎች በይበልጥ በሚጠቀሙበትና በሚመርጡት ስርዓተ-ፆታዊ የስነልሳን ምርጫ ላይ ይሆናል። ይህም በንግግራቸው ወቅት ሀሳባቸውንና ማንነታቸውን አጠንክረው ሊገልፁ በሚፈቅዱበት ስነልሳናዊ አጠቃቀም ላይ የሚያተኩር ሲሆን፣ ለጥናቱ የተመረጠው ተግባቦታዊ አውድም የስራ ቦታ ነው። ምክንያቱም ዌስት እና ዘመርማን (1987) እንደሚሉት በስራ ቦታ ላይ የሚደረግ መደበኛም ይሁን ኢመደበኛ ውይይት፣ በአጠቃላይ በመስተጋብራዊ ሂደት የሚደረግ ንግግር የስራ ድርሻን በሚመጥን መልኩ ለመስራት መቻል አለመቻልን ያሳያል። ከዚህ በላይ በመደበኛ ስብሰባም ሆነ መደበኛ ባልሆነ ውይይት የተለያየ ድርሻን ወንዶችም ሆኑ ሴቶች እንዴት እንደሚወጡ ለማወቅና ለመለየት፣ እንዲሁም ማንነትንና የንግግር ሁኔታዎችን ለመለየት ያስችላል። ስለሆነም ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታ ላይ በተለያዩ አውዶች በሚያደርጉት ውይይት ላይ የድርሻቸውን እንዴት ይወጣሉ የሚለውን ሀሳብ መፈተሽ ተገቢ ነው።

ስለሆነም የጥናቱ ትኩረት ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በስራ ቦታ ላይ ከሌሎች አቻዎቻቸው ጋር የሚግባቡት እንዴት እንደሆነ፣ ሀሳባቸውን እንዴት እንደሚገልፁ፣ እንዴት መደራደርና መስማማት እንደሚችሉ፤ እንዲሁም በስራ ቦታ ላይ ያላቸውን ድርሻ

(ሃላፊነት) እንዴት እንደሚገልጹ የንግግር አቀራረባቸውን ሁኔታ በማየት የተናጋሪዎቹን የተግባቦት/የዲስኩር ስልት በመፈተሽ ላይ ያተኩራል።

ሙምባይ እና ክሌር (2000) እንደሚገልጹት ይህ የጥናት ዘርፍ በተግባቦታዊ ጥናት ስር ተቋማዊ መግባቢያ በሚል ዘርፍ ስር የሚታይ ሲሆን፣ ይህ ጥናት የተጠናውና የተፈተሸውም በአገራችን ከሚገኙ የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች መካከል በአመቺ ናሙናነት በተመረጠ አንድ ዩኒቨርሲቲ ላይ ነው።። በመሆኑም የጥናቱ ተተኳሪ በሆነው በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከግንቦት 2004 እስከ ታህሳስ 2005 ዓ.ም ድረስ በማስተማር ላይ ካሉ መምህራን ውስጥ በተገቢው የናሙና አወሳሰድ ስልት በተመረጡ ሴትና ወንድ መምህራን በስራ ቦታቸው የስራ ጉዳይን አስመልክቶ ባካሄዱት መስተጋብራዊ ንግግር ይኸውም በመደበኛና ኢመደበኛ ውይይቶች ላይ የቋንቋ አጠቃቀማቸውን ሁኔታ በመመርመር ያተኮረ ነው። መረጃውን በተግባር በመሰብሰብ ሂደት ግን ሴቶችና ወንዶች ኢመደበኛ በሆነው መስተጋብራዊ ተግባቦት ሂደት አጋጣሚዎችንና ሂደትን መሰረት ባደረገ ሁኔታ የሚከናወነውን ኢመደበኛ አውድ ለማግኘት አልተቻለም። ለምሳሌ በቢሮ፣ በምግብ ቤት፣ በሻይ ቤት፣ ወዘተ. በአንድ ላይ የሚገኙበት አጋጣሚ እጅግ አስቸጋሪ ሆኖ በመገኘቱ ፕሮግራም ተይዞ ከተካሄዱ ኢመደበኛ አውድ እና ከመደበኛ ውይይቶች ላይ ተሰብስቧል።

1.7 የጥናቱ ውሱንነት

የጥናቱ ትኩረት ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በስራ ቦታ ላይ በሚደረጉ መደበኛና ኢመደበኛ ውይይቶች ላይ ሀሳባቸውን እንዴት እንደሚገልፁ፣ እንዴት መደራደርና መስማማት እንደሚችሉ፤ እንዲሁም በስራ ቦታ ላይ ያላቸውን ድርሻ (ሃላፊነት) እንዴት እንደሚገልጹ የንግግር አቀራረባቸውን ሁኔታ በማየት የተናጋሪዎቹን የተግባቦት/የዲስኩር ስልት መፈተሽ እንደሆነ ቀደም ብሎ ተገልጿል። ሆኖም ግን ኢመደበኛ በሆነው አውድ ሴቶችና ወንዶች በአንድ ላይ የሚገኙበትን አጋጣሚ ለማግኘት አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ በዚህ ጊዜና ቦታ አብረው ሊገኙ ይችላሉ ብሎም መገመት አስቸጋሪ ነበር። በመሆኑም ከዚህ አውድ መረጃ ለመሰብሰብ የታሰበው ፕሮግራም ከተያዘለት፣ በሂደት ከሚከሰት፣ በአስቸኳይና በድንገት ከሚደረግ ኢመደበኛ የውይይት አውዶች ቢሆንም መረጃውን መሰብሰብ የተቻለው ግን

ፕሮግራም ከተያዘ አውድ ብቻ ሲሆን፣ ከዚህ አንጻር ጥናቱ ውስንነት ይታይበታል። ከዚህም ሌላ ጥናቱ በአንድ ዩኒቨርሲቲ ተቋማዊ ባህል ላይ ብቻ ትኩረት ማድረጉ የሚደረስበት መደምደሚያ የሁሉንም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ስርዓተ-ፆታዊ ዲስኩር ሊያጠቃልል ስለማይችል በዚህም ረገድ ጥናቱ ውስንነት አለበት።

1.7 የቁልፍ ፅንሰ ሀሳቦች አጠቃቀም ብያኔ

የዚህ ጥናት ቁልፍ ፅንሰ ሃሳቦች ዲስኩር፣ አሃድ፣ ሂሳዊ ዲስኩር ትንተና፣ ሀይል፣ አመለካከት፣ ስርዓተ-ፆታ ናቸው። የአጠቃቀም ብያኔያቸው ደግሞ በ(ፌርክላፍ 1993፣1992፣ ቶሮንቦ 2002፣ኤርያንቶ 2001፣ ጆንስቶን 2002) መነሻነት እንደሚከተለው ቀርቧል።

ዲስኩር፡- ዲስኩር ስንል የሰው ልጅ ራሱንና ዓለምን ብሎም የእለት ተዕለት እንቅስቃሴውን እንዴት እንደገለፀ የሚያሳይበት ጭብጥ ማለት ነው (ፌርክላፍ 2006፣ ዊዶውሰን 2007)።

አሃድ፡- በተግባቦት ሂደት የሚፈጠር ስለአንድ ጭብጥ የተነገረ/የተፃፈ የቋንቋ አፍልቆት ነው። በዚህ ጥናት አሃድ ፅሁፍን ሳይሆን ንግግርን ብቻ የሚመለከት ይሆናል (ዊዶውሰን፣2007)።

ድስኩራዊ (ተግባቦታዊ) ትንተና፡- ድስኩራዊ (ተግባቦታዊ) ትንተና ስንል በቅድሚያ የሚነሳው መሰረታዊ ጉዳይና መታወቅ ያለበት የቀረበውን ጭብጥ መረዳት ማለት ነው። ይህም ማለት የአንድ ንግግር ወይም ጽሁፍ መልዕክት የሚገለጸው በቀረበበት የቋንቋ አጠቃቀም ፍሰት መሰረትነት ነው። በተጨማሪም በንግግር ወቅት ያለውን የምልክት አጠቃቀም፣ እይታንና ድምፅን ጭምር በሚቀርበው ንግግር ውስጥ ትኩረት ሰጥቶ ማየትንም ያጠቃልላል (ፌርክላፍ 1993፣2006)።

ሂሳዊ የዲስኩር ትንተና፡- ትንተናው ቋንቋና ቋንቋ ነክ ጉዳዮች በማህበራዊ መስተጋብርና አወቃቀር ላይ የሚፈጥሩትን ችግር በማሳየትና በመፍታት ላይ ያተኮረ ነው። ይህም

በተለያየ የትንተና ደረጃ ሊታይ የሚችል ቢሆንም እንደፌርክላፍ (2001) እይታ ትንተናው በሶስት መሰረታዊ ማዕቀፎች መታየት እንዳለበት ይጠቅሳል። እነዚህም አሃዳዊ ትንተና፣ ተግባቦታዊ አቀራረብ እና ማህበረ-ባህላዊ ልማድ ናቸው።

ስርዓተፆታ፡- ስርዓተፆታ የሚለው ፅንሰ ሃሳብ በሴትና በወንድ ላይ የሚታየውን የሥነህይወትና ተፈጥሯዊ ልዩነት ከግንዛቤ ያስገባ ሳይሆን፣ ማህበረሰቡ ከሚተዳደርበት ባህል ደንብና እምነት አንፃር የሚሰጥ ሰው ሰራሽ የሆነና ልማዳዊ ስርዓት የፈጠረው ልዩነት ነው። ይኸውም ፆታን አስመልክተው ያላቸው አመለካከት ለምሳሌ ከባህል አንፃር ወንድ ጎበዝ፣ ጉልበታም፣ ተፎካካሪ፣ በራሱ የሚተማመን፣ ውሳኔ ሰጪ በማድረግ ሲመለከቱ፤ በተቃራኒው ሴት ዝምተኛ፣ ደካማ፣ በራሷ የማትተማመን፣ የወንድ ጥገኛ አድርገው ይመለከታሉ። በመሆኑም ስርዓተፆታ ከባህል ባህል፣ ከማህበረሰብ ማህበረሰብ፣ ከስርዓት ስርዓት ከቦታ ቦታ ከዘመን ዘመን የሚለያይና የሚወሰን፤ እንዲሁም በማህበረሰብ እይታ ለወንድና ለሴት ተብሎ በተሰጠ ድርሻ ላይ የሚመሰረት ነው (ቻንት፣2007፣ ባሬት እና ዴቪድሰን፣2006፤ ጃኔት፣ 1990፣ ሰንደርላንድ፣1994 እና ሻን፣1999)።

በዚህ ጥናት "Gender" ስርዓተፆታ የተባለ ሲሆን፣ አጥኝዋ ከላይ በተገለፀው ብያኔ መሰረት ስርዓተፆታ ማህበረሰቡ ለፆታ ያለውን እይታ፣ አመለካከትና ፍልስፍና የሚመለከት ሲሆን ‹‹ስርዓተ›› የሚለው መነሻ ተጣማሪ ቃል የገባውም ማንኛውም ማህበረሰብ ማህበረ ባህላዊ ልማዱን በማህበራዊነቱ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ የሚጠቀምበት ልማዳዊ ስርዓትን የሚያሳይ በመሆኑ ነው።

ሀይል፡- በተግባቦት ሂደት ሀይል እንደተቋሙ ሁኔታ፣ እንደማህበራዊ ደረጃው፣ እንደፆታውና እንደጎሳው ይወሰናል። ስለሆነም በሂሳዊ ዲስኩር ትንተና አቀራረብ ዲስኩር ተናጋሪው በዲስኩር ወቅት እንዴት ሀይሉን ማንፀባረቅ፣ መጫንና ቋንቋውን እንዴት መጠቀም እንደቻለ ይዳሰሳል (ፌርክላፍ 1993፣2001፣2006፤ ቶሮንቦ፣2002፣ ጆንስቶን 2002)።

ርዕዮት፡- ሰዎች ነገሮችን የሚያዩበትን መንገድ የሚመለከት ሲሆን፣ በተለይ ሀይል ባላቸው መደቦች ሊተገበርና ሊቀነቀን እንደሚችልም ይታመናል። እንደ ፌርክላፍ (1993፣2001፣2006) አገላለጽ ርዕዮት የሀይል መተግበሪያ መሳሪያ ማለት ነው። ይህም

በተግባቦት ሂደት የሚገለጽና በሌሎች ላይ የሚጫን ነው። በተጨማሪም የሌሎችን ርዕዮት በመቆጣጠር የራስን ሃሳብ በሌሎች ላይ የመጫን ሀሳብ ነው። ስለሆነም ዲስኩር ፍልስፍናዊ ነው፣ በመሆኑም ሀይልን በሌሎች ላይ በመጫን ረገድ ትልቅ ድርሻ አለው። ሀይልና አመለካከት የዲስኩር ዋና የትኩረት ነጥቦች ናቸው። ኤርያንቶ (2001) እንደሚሉት አሀድ፣ ንግግርና ሌሎችም የዲስኩር ማስተላለፊያ ዘዴዎች በሙሉ የፍልስፍና ነፀብራቅ ናቸው። በአጠቃላይ ድስኩራዊ ርዕዮት በቡድንም ሆነ በተናጠል የሚንፀባረቅና በሌሎች ላይ የራስን የበላይነት ለመጫን የሚጠቅም አዕምሯዊ ይዘት ነው።

ፕሮግራም፡- ፕሮግራም የሚለው ቃል ይህ ጥናት በተካሄደበት ጊዜ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የአንድ የትምህርት መስክ ስርዓተ ትምህርትን የሚወክል ነው። ይህ ቃል በዚህ ዩኒቨርሲቲ ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ከዚህ ዘመን በፊት ትምህርት ክፍል የሚል መጠሪያ የነበረው ቃል ነው።

ምዕራፍ ሁለት፤ክለሳ ድርሳን

2.1 መግቢያ

ይህ ምዕራፍ ለጥናቱ በማጣቀሻነት የሚያገለግሉ በተለያዩ ምሁራን የተፃፉ መጻሕፍትና መጣጥፎች ተዳሰው ለጥናቱ በማጣቀሻነት የሚያገለግሉ ንድፈሃሳባዊ መሰረቶች የተዳሰሱበት ክፍል ነው፡፡ በስፋት ለማየት የተሞከረው የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ በተመለከተ በተለያዩ ምሁራን የቀረቡ ንድፈሃሳባዊ መሰረቶች ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት የተግባቦታዊ ስልት ምንነትና አይነቶች፣ የሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ምንነትና እንዴትነት፣ የተቋማዊ ባህልና ዲስኩር ምንነት፣ የስርዓተፆታ ንድፈሃሳብንና የጥናቱን ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍ በሚመለከት በስፋት ተዳሰዋል፡፡

2.2 የተግባቦታዊ ስልት ፍችና ምንነት

ተግባቦታዊ ስልት እንደየክንዋኔው ልዩነት የተለየ ስልታዊ ትርጉምና ተግባር እንዳለው ይስተዋላል፡፡ አንደኛ፣ ግንኙነትንና ተለምዶን ከማሳየት አንፃር የአንድን ተቋም የተግባቦት ሁኔታ ለማሳየት፤ ሁለተኛ፣ የተናጋሪውን የማንነት ሁኔታ ከማሳየት አንፃር ለምሳሌ የተናጋሪውን ቀልደኛነት፣ የትምህርት ደረጃ፣ የየትኛው መደብ ቡድን አባል እንደሆነ፣ በምን ተግባራት ላይ ተሳትፎ እንደሚያደርግ፣ ወዘተ. ለማሳየት፤ ሶስተኛ፣ የአቀራረብ ሁኔታን መጥኖ ለማቅረብ ለምሳሌ ለልጆች፣ ለውጭ ዜጎች...ለማሳየት፤ አራተኛ፣ ግንኙነትን የተሻለ ከማድረግ አንፃር የሚታይ ስልት ለምሳሌ ትህትና፣ ርቀት፣ ቅርበት እና አምስተኛ፣ የሂደትን ቅደም ተከተል ከመጠበቅ አንፃር የሚታይ ሲሆን በአጠቃላይ የተጠቀሱትን ተግባራት በማሳየት ረገድ ከፍተኛ ሚና አለው (ቫን፣1997)፡፡

በተደጋጋሚ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው የሚነገሩ የንግግር ሂደቶችን ስንመለከት የቡድኖችን ወይም የግለሰቦችን የንግግር ስልት እንድንገነዘብ ያግዙናል በማለት ታነን (194) ይገልፃሉ፡፡ የንግግር ስልቱ ቅደም ተከተል ደግሞ መሰረት የሚያደርገው የቋንቋውን ተናጋሪ ባህል በመሆኑ ሁልጊዜም ቢሆን የተግባቦታዊ ስልት ቅደም ተከተል ባህል ተኮር

ነው። የተግባቦታዊ ስልቶች በግለሰብም ሆነ በቡድን ደረጃ ተደጋግመውና የራሳቸውን ቅደም ተከተል ጠብቀው የሚመጡ በመሆናቸው ማን መቼ ምንና እንዴት እንደሚናገር ስለሚታወቅ ተገማችም ናቸው።

ዋና ዋና የተግባቦት ስልት የሚባሉትን ታነን(1994) እንደሚከተለው ገልፀዋቸዋል። እነዚህ ተግባቦታዊ ስልቶችም በተለይ በስራ ቦታ ላይ በሴቶችና በወንዶች መካከል በሚደረግ የተግባቦት ሂደት ወቅት በአብዛኛው እንደችግር የሚታዩ መሆናቸውንም ጠቁመዋል። ከስልቶቹ መካከል ጥቂቶቹም፡-

‹‹ይቅርታ ማለት››፡- አብዛኛውን ጊዜ በየታ ዙሪያ የሚደረግ ተግባቦት መቋጫ የለውም። በዚህም ምክንያት አለመግባባት ሊፈጠር ይችላል። ስለሆነም ‹‹...በማለትህ አዝናለሁ›› ወይም ‹‹ይቅርታ›› ማለት በንግግር ሂደት ለብዙ ሴቶችና ጥቂት ለማይባሉ ወንዶች ይቅርታ መጠየቅ ማለት ብቻ አይደለም። ይልቁንስ የተጀመረውን ንግግር በሰላማዊ መንገድ እንዲቀጥል ማመቻቸት እንጂ። ሴቶች አዝናለሁ ሲሉ በንግግራቸው ግንኙነትን በተሻለ መልኩ በእኩልነት ለማስኬድ እንደሆነ ጥናቶች የሳያሉ። ወንዶች ደግሞ ባንፃሩ ሲያመነቱ፣ ይቅርታ ለመጠየቅና ጥፋታቸውን ለማመን ይጠቀሙበታል።

ሂስ መስጠት፡- ሴቶች ሂስ የሚሰጡት ፍላጎታቸውንና ማንነታቸውን በተመጣጠነ መልኩ ለማስኬድ ሲባል ነው። ባንፃሩ የወንዶቹ ደግሞ ለመጋፈጥና የበላይነትን ለማረጋገጥ የሚደረግ ነው። መገለጫውም በንግግር የበለጠ ‹‹እችላለሁ››፣ ‹‹አሳይሃለሁ ጠብቀኝ!›› በማለት የሚገለጽ ሲሆን፣ ይህም የሀይል ማሳያቸው ነው። ሂስን በተመለከተ በሁለቱም ፆታዎች መካከል የጎላ ልዩነት አለ። ይኸውም የወንዶች ንግግር የሌላውን ሞራል ከመጠበቅ አኳያ ጥንቃቄ የጎደለውና ሀይል የተሞላበት ሲሆን፣ የሴቶች ደግሞ በተቀራኒው የሌላውን ስሜት የጠበቀና ሀይል የለሽ ነው።

ማግባባት፡- በተግባቦት ሂደት አለመግባባት ካለና አንዱ አንዱን መረዳት ካልቻለ ማለትም ተቃራኒና የማይጣጣሙ ሰዎች ከሆኑ ጠብ ይነሳል። ይህን ተረድቶ መቻቻል፣ ማግባባትና ነገሮችን ማለዘብ ካልተቻለ ወደአላስፈላጊ ግጭት መግባቱ አይቀሬ ነው። ብዙውን ጊዜ ወንዶች ወደጭቅጭቅና ንትርክ ሲገቡ ሴቶች ግን በቀጥታ ወደንትርክ መግባት

አይፈልጉም። ይልቁንም የማግባባትን ስልት በመጠቀም በመጀመሪያ ደረጃ ጉዳዩን በማለስለስ ለመመካከር ይጥራሉ።

ምን ታስባለህ? /ምን ይመስልሃል? ሴቶች በንግግር ወቅትና ሂደት ምን ታስባለህ?/ ምን ይመስልሃል? ሲሉ ተግባቦት በስምምነት እንዲቀጥል መፈለጋቸውን የሚሳዩበት መንገድ ነው። ይህ ማለት ተናጋሪው ለመናገር እምነት ባጣ ጊዜና ይህ ፍላጎት ከግንዛቤ ካልገባ የሚያስከትለው ችግር ይኖራል።

ቀልድ፡- በጨዋታም ጊዜ ቢሆን ወንዶችና ሴቶች ልዩነት ያሳያሉ። የወንዶቹ ጣፋጭነት የጎደለው አጉል የወሲብ ቀልድ ላይ ሲያተኩር፣ ሴቶች ደግሞ ማሳቅን ይወዳሉ። በመሰረቱ በተግባቦት ሂደት ቀልድ ጥሩ የማነቃቂያ መንገድ ከፋች ሊሆን ይችላል። ይህም ሆኖ አንዳንዴ አላስፈላጊ የወሲብ መተንኮሻ ሊሆን ይችላል። ቀልድን በቀልድነቱ ከተቀበልነው ጎጅነት ላይኖረው ይችላል። ሆኖም ግን ጓደኝነትን ማስቀጠልና ተቀባይነትን ለማግኘት ሲባል በወንዶች የሚቀርብ ቀልድ ግን ከአስደሳችነቱ ባሻገር አሉታዊ ጎንም ሊኖረው ይችላል።

ጥያቄ፡- ጥያቄ መጠየቅ ስንል በወንዶችና በሴቶች አተያይ የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው። ስለሆነም ይህ ጭብጥ መታየት ያለበት በተለያየ መልኩ ነው። እንደ ታነን(1994) አገላለፅ በቋንቋ መነጋገር ማለት ለሴቶች የቋንቋ ዘገባ ማለት ነው። ይህም ማለት በመደራደር፣ በመቻቻልና በመግባባት ላይ ትኩረት ያደረገ ንግግር ነው። በአንፃሩ የወንዶች ደግሞ መረጃ ማግኛ፣ ነፃነት ማወጃና በማህበረሰቡ ዘንድ ደረጃ መጠበቂያ ተደርጎ የሚወሰድ ነው። በጥናት የተረጋገጠውም ወንዶች ጥያቄ መጠየቅን የሚቃወሙና መጠየቅም የማያስደስታቸው መሆናቸው ነው። ባንፃሩ ሴቶች የመጠየቅም፣ የመመለስም፣ የመግባባትም ችግር የለባቸውም። ሆኖም ግን በሴቶች ተግባቦት ላይ የሚታየው ችግር መጋፈጥና መቋቋም አለመፈለጋቸው ላይ ነው። ስለዚህ ሴቶች የበለጠ ተባባሪና ተግባቢም መሆናቸው ታይቷል። ይህም ማለት ሲታይ ወንዶች መልዕክት የሚያስተላልፉት በበላይነት ስሜት ሲሆን ሴቶች ደግሞ በደጋፊነትና በተባባሪነት ስሜት እንደሆነ ግሪይ (1992) በጥናታቸው ማጠቃለያ ገልፀዋል።

የተግባቦት ቀጥተኛ መሆን አለመሆን፡- ሴቶች ለምን የተሻለ ቦታ እንደማይዙና ሀላፊ ወንዶች ደግሞ ሴቶችን በራሳቸው የማይተማመኑ አድርገው እንደሚቆጥሯቸው ለሚለው ነጥብ ታነን (1990) እንደምክንያት የሚጠቁሙት የሴቶችን አቀራረብና ምላሽ አሰጣጥ ዘዴ እንደሆነ ይገልፃሉ። ይኸውም ሴቶች ለሚቀርብላቸው ጥያቄ ቀጥተኛ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ በሚያግባባ መልኩና በተለሳለሰ ሁኔታ ለምሳሌ ‹‹ብለህ ነው?››፣ ‹‹ይሻላል?››፣ ‹‹ከመሰለህ?›› እያሉ ሲግባቡና ሲመልሱ፤ ወንዶች ግን ቀጥተኛ የሆነና የመሰላቸውን መመለስ ይቀናቸዋል። ይህም የሁለቱን ባህርይ የሚያሳይ ሲሆን፣ በርካታ ጥናቶችም ይህንን የታነን ሀሳብ የሚጋሩ ናቸው።

ችግር ፈች ንግግር፡- በመግባባት ረገድ የወንዶቹ ተግባቦት በብዙ ችግር የተሞላ ሲሆን፣ የሴቶቹ ግን ጓዳዊ ስሜትን የተላበሰ ነው። ታነን(1990) እንደሚሉት ሴቶች ችግርን መካፈል የበለጠ መቀራረብ ነው ብለው ስለሚያስቡ ችግር ለመፍታት የሚደረግ ተግባቦት በሴቶች ዘንድ ተቀባይነት እንዳለው ሲያረጋግጡ፤ ወንዶቹ ግን ይህን የተግባቦት መንገድ ምክር እንደመፈለግ አድርገው ስለሚቆጥሩት ለመምከር ይዘጋጃሉ። በመሆኑም የሴትና የወንድ የንግግር ስልት የተለያየና ከየባህርያቸው የሚመነጭ እንደሆነ ጥናቶች ይጠቁማሉ። ይህም ቀረቤታን ከመግለጽም ሆነ ምክር በመለገስ ዙሪያ ስልቱ የተለየ ነው። አንድን በችግር ዙሪያ የቀረበን ንግግር ወንዶችና ሴቶች የሚገነዘቡበትና የሚፈቱበት ዘዴ የተለያየ ስለሚሆን ይህ ግጭት ሊፈጠርና አለመግባባት ሊያስከትል ይችላል።

የንግግር ርዕሰ ጉዳይ፡- ሴቶችና ወንዶች በሚነጋገሩበት ወቅት የቋንቋ አጠቃቀምና የቃላት አመራረጣቸውን ማየት ተገቢ ነው። በንግግር ወቅት ሴቶች ባብዛኛው ሲያደርጉ የሚታየው ቀረቤታን መሰረት ያደረገ፣ ጓደኝነትንና ቤተሰባዊ ስሜትን የሚያንፀባርቅ ንግግር ነው። በተቃራኒው ወንዶች ደግሞ ግልጽነት በጎደለውና ጥቅል በሆነ ጉዳይና በራሳቸው ስሜት ዙሪያ ብቻ ያነጣጠረ ንግግር ያደርጋሉ። ይህም በፍፁም ቅርበትን የሚያመለክት አይሆንም። የሴቶቹ ግን በሚገባ ሌሎችን በማዳመጥ ግንኙነትን በማጠናከር ላይ ያተኮረ ነው።

የንግግር ጊዜ፡- ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ሴቶችና ወንዶች በሚገኙበት መድረክ ከሴቶቹ በላቀ ሁኔታ ወንዶች በብዛት ብዙ ጊዜ የመናገር ፍላጎት ያሳያሉ። ይህም በንጽጽር

የወንዶች ከሴቶቹ እጥፍ የሚበልጥ ይሆናል። ረዘም ያለ ጊዜ ወስዶ መናገርን በተመለከተ ወንዶች የበላይነታቸውን የሚያሳዩበት ሁኔታ አድርገው ሲቆጥሩት፣ ባንፃሩ ደግሞ ሴቶች ሲሶ እንኳ ቢናገሩ ብዙ ጊዜ እንደተናገሩ ይቆጠራል።

በሌላ በኩል ደግሞ ብራውን (2007) የአነጋገር ስልትን አስመልክቶ ርዕሰ ጉዳይ፣ አድማጭና ሁኔታ የሚሉትን መደበኛ መስፈርቶችን በመጠቀም አምስት ተግባቦታዊ (የዲስኩር) ስልት ደረጃዎችን አስቀምጠዋል።

1. አንደበተ ርቱዕ ስልት፡- ይህ ማለት በህዝባዊ መድረኮች ንግግር በሚደረግበት ጊዜ ለንግግሩ ትኩረት መስጠትን ማለትም የቃላት አመራረጥ ብቃት፣ የንግግሩ ድምፀት በሚገባ የተስተካከለ ንግግርን ይመለከታል።
2. ሆነ ተብሎ ስልት፡- ይህ የንግግር ስልት ታዳሚን መሰረት የሚያደርግ ሲሆን፣ በተናጋሪውና በአድማጩ መካከል በጣም ሰፊና ጠቃሚ የሆነ የሃሳብ ልውውጥ ይደረጋል። ስለሆነም የንግግሩ ቅርፅ እንደአንደበታዊ ስልት ጥርት ያለ አይደለም። ለዚህም የንግግር ስልት ዋቢነት በዩኒቨርሲቲ መማሪያ ክፍል ውስጥ የሚደረግ የመምህር ገለፃ በዋናነት ሊጠቀስ ይችላል።
3. ምክክራዊ ስልት፡- በምልልስ የሚቀርብና በመጠኑም ቢሆን ጥንቃቄ ያልተለያቸው ቃላት የሚተገበሩበት ስልት ነው። ለምሳሌ ሀኪም ከበሽተኛው ጋርና በግብይት ወቅት በሻጭና በገዥ መካከል የሚደረጉ ንግግሮችን የሚመለከት ነው። እንደነዚህ ያሉ ንግግሮች ብዙውን ጊዜ ሲታዩ ምክክራዊ ተፈጥሮ ያላቸው በመሆናቸው በተግባቦት ወቅት ለሚጠቀሙበት ቃላት ጥንቃቄ ሲያደርጉ ይስተዋላል።
4. ድንገቴያዊ ስልት፡- በጓደኛና በስራ ባልደረባ ወይም አንዳንድ ጊዜ በቤተሰብ መካከል የሚደረግ የንግግር አይነት ሲሆን፣ ምንም አይነት ጥንቃቄ ያልታከለበትና በነፃነት የሚነገር ነው።
5. ጓዳዊ ስልት፡- ይህ ስልት ሙሉ በሙሉ የማህበራዊ ደረጃ ልዩነት የሌለበት ሲሆን፣ ከቤተሰብ፣ ከፍቅረኛና ከቅርብ ጓደኛ ጋር የሚደረግ ንግግርን ይመለከታል። በአብዛኛው ጓዳዊ ስልት የተባለው ውስጣችንን ገልፀን የምናወጣበት ንግግር በመሆኑ ነው።

የንግግር ስልት ቃላዊና ቃል አልባ በሆነ መንገድ ሊቀርቡና ሊገለጹ ይችላሉ። ይህም በሰውነት እንቅስቃሴ፣ በአይን ግንኙነትና በመሳሰሉት ማለት ነው። ቃል አልባ ተግባቦትን

በቀላሉ ለመማርና ለማወቅ አስቸጋሪ ነው። የዚህም ምክንያት የቋንቋ ተለዋዋጭ መሆንና በምልክት ብቻ ተገልጾ ማለቅ አለመቻሉ ነው።

ተግባቦት በሚከናወንበት ወቅት ቃላዊ ተግባቦቱን ወደጎን በመተው በቃል አልባ ተግባቦታዊ ዘዴ በመጠቀም መልዕክት ማስተላለፍ ይቻላል። በቃል አልባ መግባቢያ የሚተላለፍ መልዕክት በቋንቋው ተናጋሪ ዘንድ በተለምዶ የሚተገበር ሲሆን፣ ከንግግር ቋንቋ ቀጥሎ በተነፃፃሪ የሚነገርና መጠነኛ የሆነ ጥበብና ችሎታ የሚታይበት ነው። ባህል በአብዛኛው ቃል አልባ በመሆኑ ባህልን በመማር ሂደት ብዙ ጊዜ እንቅፋቶች ይኖራሉ። ቃል አልባ ተግባቦት የሚባሉትን ብራውን (2007) እንደሚከተለው ይገልጿቸዋል።

እንቅስቃሴ፡- በማንኛውም ባህል ሆነ ቋንቋ በመግባባት ወቅት የሰውነት እንቅስቃሴ መጠቀም የተለመደ ነው። መስማት የተሳናቸውም ቢሆኑ እንኳ በሰውነታቸው እንቅስቃሴ መግባባት ይችላሉ። በሰውነት እንቅስቃሴ አማካይነት መልዕክት ማስተላለፍ አሁንም ሆነ ትናንት ያለና የነበረ ነው። ሆኖም ግን የአካል እንቅስቃሴ ተግባቦት ከባህል ባህል የተለያዩ መልዕክትና ትርጉም ይኖረዋል። እንደየማህበረሰቡና ባህሉ የሰውነት እንቅስቃሴ፣ የአይን እይታና የአንገት እንቅስቃሴ የተለያየ መልዕክት ሊኖረው እንደሚችል መገመት ያስፈልጋል። ለምሳሌ በብዙ የአውሮፓ አገሮች ራስን መነቅነቅ የአዎንታ ምልክት ተደርጎ ሲወሰድ፣ በጃፓን ደግሞ እጅን ወደልብ አስጠግቶ በመወዝወዝ እሽታንና ፈቃደኝነትን ይገለፃል።

አካላዊ ቅርበት፡- አካላዊ ቅርበት ከንግግር ዋና ክፍሎች አንዱ እንደሆነ ይታመናል። በንግግር ወቅት ባህልን ለመግለፅ በሚደረገው ሂደት ከባህል ባህል መለያየት ይከሰታል። ይህን አስመልክቶ ኤድዋርድ (1966) ተቀባይነት ያላቸው ማህበራዊ ርቀቶች የሚባሉት ማህበራዊ ምክክር፣ ህዝባዊ፣ ግላዊና ጓዳዊ ዲስኩሮች እንደሆኑ ገልፀዋል። ለምሳሌ በአሜሪካ አንድ እንግዳ ከመጣ ከአሜሪካዊያኑ ቢያንስ ሃያና ሃያ አራት ኢንች ርቆ መቆም አለበት የሚል ባህላዊ ልምድ ሲኖር፣ በላቲን አሜሪካኖች ደግሞ ከዚህም እጥፍ ድርብ በሆነ ርቀት ሊቆም ይገባል የሚል እምነት አላቸው።

ጥበባዊ፡- አንደበታዊ ካልሆነ የመግባቢያ ስልቶች መካከል አልባሳትና ጌጣጌጥ ተጠቃሽ ናቸው። አልባሳት የሰውየውን ማንነት፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃውንና አጠቃላይ ባህሪውን የመግለፅ አቅም አላቸው። በመሆኑም አለባበስ ከንግግር አድራጊው ሰው ባህርይ ጋር የተቆራኘ ነው። የተለያየ ባህል በሚከተሉ ሰዎች መካከል በሚደረግ ንግግር ወቅት ጌጣጌጦች የራስን ማንነት ከማጉላት አልፈው ተፅዕኖዎችን በማስወገድ፣ የነፃነትን ስሜትና አጠቃላይ የሆነ ደስታ የመፍጠር አቅም አላቸው።

ውበታዊ እንቅስቃሴ፡- ከንግግር ውጭ ከሆኑ የተግባቦት መፍጠሪያ ዘዴዎች ውስጥ አንዱ ውበታዊ እንቅስቃሴ እንደሆነ ይጠቀሳል። ሰዎች እንዴትና መቼ እንደምንግባባቸውና በምልክት ቋንቋ ማወቅ ብዙ ጊዜ ስኬታማነቱ ቢያጠራጥርም፤ መነካካት ከባህል አንፃር በጣም ቀረቤታንና የራስ መሆንን የሚያመለክት ነው። ይህንም ጠንቅቆ ማወቅ አጠራጣሪና ግልፅነት የጎደላቸውን መልዕክት ለይቶ ለማወቅ ይረዳል።

ስሜታዊ፡- አፍንጫችን ስሜታዊና ቃል አልባ የሆነ መልዕክትን ይቀበላል። በተግባቦት ወቅት የሚታይ የሰውነት ጠረን ጥሩና መጥፎ መሆን ለንግግር መሳካትና አለመሳካት ወሳኝ ድርሻ አለው። ይህም በአፍንጫ አማካይነት አንደበታዊ ያልሆነ ግን ስሜታዊ የሆነ መልዕክት ለመተላለፍ ምክንያት ነው። በ21ኛው ክፍለ ዘመን በአብዛኛው ቴክኖሎጂ ተኮር ማህበረሰብ የተፈጠረበት ዘመን ነው። በዚህም ሽቶ፣ ሎሽን. ክሬምና ፓውደር ተቀባይነት ያላቸው ጠረኖች ተደርገው ከመወሰዳቸውም ባላይ በሁሉም ሰው የሚኖሩና አስፈላጊ የሰው ልጅ ጠረኖች ተደርገው ተወስደዋል።

2.3 የሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ምንነት

እንደቫን (1999) እና ፌርክላፍ (1993፣2006) አገላለጽ ሂሳዊ የዲስኩር ትንተና አንድ የጥናትና ምርምር መስክ ሆኖ በማህበራዊ የሃይል ሚዛን በሚኖር አሉታዊ ሂደት፣ የበላይነትና የበታችነት ባለበት ሁኔታ፣ እኩልነትን ባግባቡ ካለማስተናገድ፣ወዘተ. የሚከሰቱ ሁነቶችን በማካተት ከማህበራዊ መስተጋብርና ከፖለቲካዊ ሁኔታ ማህበረሰቡ ከሚጠቀምባቸው የጽሁፍ መልእክት/ንግግር በመነሳትና መሰረት በማድረግ ያጠናል። በተለይም አግባብነት ያለው ድስኩራዊ ትንተና በግልጽና በማያሻማ ሁኔታ በአንድ

ማህበረሰብ ውስጥ ያለውን የበላይነትና የበታችነትን ደረጃ በሚገባ ማሳየት የሚችል የመተንተኛ ዘዴ ነው።

የሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በፊት በተለይም በፍራንክ ፈርት ትምህርት ቤት በሂሳዊ ንድፈሃሳብ አማካይነት የተጀመረ ነው። ይህም ወቅታዊ ንድፈሃሳብ በወቅቱ ትኩረት ያደረገው በቋንቋና በዲስኩር ላይ ሲሆን፣ በስነልሳን የጥናት ዘርፍ የሚበረታታና የሚደገፍ ሲሆን በአብዛኛው በእንግሊዝና በአውስትራሊያ የበለጠ ጎልቶ ታይቷል (ቫን፣1999)።

ሂሳዊ ዲስኩር ትንተና በማህበራዊ ስነልሳን፣ በስነልቦናና በማህበራዊ ሳይንስ ዙሪያ ድጋፍ የተቸረው ከመሆኑም በሻገር በበርካታ ምሁራን ዘንድም ድጋፍ ያገኘ የትንተና ዘዴ ነው። በዚህም ምክንያት ሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ተቀባይነት ያለውና ወሳኝ የጥናት መስክ በመሆን በስፋት ቀጥሏል። የሂሳዊ ዲስኩር ትንተና እንደሚታወቀው ሁሉ ሙሉ የሆነ አቅጣጫና ትምህርት ቤት ያለው እና በልዩ ስልጠና የሚካተት የሙያ መስክ አይደለም። ይሁን እንጂ ይህ መስክ የተለያየ ይዘትና አላማ ያለው፣ በንድፈሃሳብ የታገዘ፣ የሚተነተንና ወደተግባር ለማምራትና ለመተግበር የሚያስችል በየትኛውም መስክ ቢሆን ዓላማ ያለውና ተመራጭ የዲስኩር ትንተና ጥናት ነው (ቫን፣ 1999፤ ፌርክላፍ፣2003)።

በዚህ ትንተና ዙሪያ የተለያዩ ይዘቶችን ማየት ይቻላል። እነሱም የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ትርጉም፣ የንግግር ልውውጥ ሂደቶችን፣ ንድፈሃሳቦችን፣ የአነጋገር ስልቶችን፣ የማህበራዊ ስነልሳን ሁነቶችን፣ የማህበረሰብ ሁነቶችን፣ የስርዓተፆታና የመገናኛ ብዙሀን ትንተናዎችንና ሌሎችንም በዚህ መስክ ናቸው።

ለሂሳዊ ድስኩራዊ ትንተና ዋናው ጉዳይ ማህበረሰቡን ማወቅና ማጥናት ነው። ከሙያ የተገኘም ሆነ ሳይንሳዊ ዲስኩር የአንድ ማህበረሰብ የኑሮ ገጽታ ተጽዕኖ ያርፍበታል። ሁልጊዜም ቢሆን ማህበራዊ ገጽታና ድርሻ አለው። የአንድ የዚሁ መስክ የንድፈሃሳብ ቀመር፣ ገለፃና ትንተና፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ የሆኑ ጉዳዮችን ማንፀባረቁ አይቀሬ ነው። ስለሆነም የዲስኩር ተንታኞች ጥናትና ምርምር ሲያካሂዱ ወሳኝ ከሆነው አካል ሁሉ ስምምነትና ትብብር ሊያገኙ ይገባል። ይህም ለተግባራዊነቱ ትልቅ ሚና ይኖረዋል (ቫን፣ 1999) ።

2.4 የሂሳዊ ዲስኩር ትንተና መሰረተ ሃሳብ

እንደሚታወቀው ሁሉ ሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ብቸኛ የጥናት መስክ አይደለም፤ለብቻው የተቀመጠ ንድፈሃሳብ የለውም፡፡ ስለሆነም በተጨባጭም ሆነ ወጥነት ባለው መንገድ አንድ ንድፈሃሳብ ያለው ሳይሆን ከየሙያ መስኩ የተለያዩ የዲስኩር ትንተና ንድፈሀሳቦችን የያዘና ብዙ አይነት የዲስኩር ትንተና ዘዴዎች ያሉት ነው፡፡ በሂሳዊ ዲስኩር ትንተና አንድን ንግግር ወስደን በምንተነትንበት ጊዜ ከዜና ትንታኔ እና በትምህርት ከሚቀርብ ይዘት ጋር አንድ ሊሆን አይችልም፡፡ ሆኖም ግን ከጠቅላላ አላማ አንፃር ስናየው ንድፈሃሳቦቹ ብዙም የተራራቁና የተለያዩ አይደሉም (ጊ፣1999 እና ቫንና ቲዩን 2001)፡፡

ቀደም ብሎ ለመግለፅ እንደተሞከረው ሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ውስጥ የሚቀርቡት ይዘቶች ከማህበረሰቡ አንፃር ስለሆነ የዜና ትንተናም ሆነ ወሬ ማውራትና የመሳሰሉት ቢሆኑም ባቀራረብ ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ ሆኖም ግን ተናጋሪው የሚጠቀምበት ቃል/ቃላት በሂሳዊ ዲስኩር ትንተና የበላይነትን፣ አመለካከትን፣ስልጣንና ደረጃን ማሳያ፣ ፆታን፣ ዘርንና ፍላጎትን መግለጫ፤ ተቋማዊ አደረጃጀትን፣ ማህበራዊ መዋቅርንና ማህበራዊ ደረጃን የሚያሳዩ በመሆናቸው የዲስኩር ትንተና መሰረተ ሃሳቦች ናቸው፡፡

እንደ ፌርክላፍ እና ወዳክ (1997) አገላለፅ ሂሳዊ ዲስኩር ትንተና የማህበረሰብን ችግር ማእከል የሚያደርግ፣ ማህበረሰብንና ባህልን የሚዳኝ፣ አመለካከትን የሚያንፀባርቅ፣ የሃይል ሚዛንን በጥልቀት የሚያሳይ፣ ማህበረሰብንና አሃድን የሚያገናኝ፣ ተገላጭና ገላጭ የሆነ፣ የማህበረሰብ ትግበራ ነው፡፡ በዚህም መነሻነት የሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ከሌሎች መስኮች በተለየ የራሱ የሆነ ባህርያት አሉት፡፡ ይኸውም በምርምሩ ቅድሚያ የሚሰጠውና የሚያተኩረው ወቅታዊና ፋሽን ከሆኑ ጉዳዮች ይልቅ በማህበረሰብ ችግር፣ በፖለቲካና በሀይል ግንኙነት ዙሪያ ማነጣጠሩ፤ ትንተናው የሚመሰረተው ከዲስኩር መዋቅሩ ይልቅ በማህበራዊ መስተጋብርና በተለይም በማህበረሰቡ አወቃቀርና ማንነት ላይ ያተኩራል፡፡ ሌላው በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን የሀይል ሚዛንና የሀይል መጠን ምንነት ማየትና መተንተን መቻሉ ሲሆን፣ ከዚህም በላይ ብዙውን ጊዜ ማህበረሰባዊ ችግርን ለመተንተን የሚጠቀመው ስልት የተለያዩ የሙያ መስኮችን መሆኑ የብዝሀ ባህርይ እንዲኖረው

አድርጎታል። ይህም ከምርምር ታሪክ አንፃር ሲታይ ምርምር እውነት እንዲኖረው በማድረግ ረገድ ሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ከሌሎች የጥናት ስልቶች የተሻለ መሆኑ የሚሉት ጉዳዮች ሁሉ የተለየ ባሕርያቱ ናቸው።

በርካታ የሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ንድፈሃሳብ አመንጭዎች የሂሳዊ ዲስኩር ትንተናን አጠቃላይ በሆነ መልኩና በራሳቸው እሳቤ ለማቅረብ ሞክረዋል። ለዚህም ቫን(1993)፣ ወዳክ(1996)፣ ፌርክላፍና ወዳክ(1997)፣ ሜር (2001) ተጠቃሽ ናቸው። አንዳንዶቹ ለሂሳዊ ዲስኩር ትንተና መሰረት የጣሉ ሲሆኑ የአንዳንዶቹ ንድፈሃሳብ ደግሞ አጨቃጫቂ እንደሆነ ይነገራል። በይበልጥ ተጠቃሽ የሆነው ንድፈሃሳብ ፌርክላፍና ወዳክ (1997) ያቀረቡት ሲሆን፣ በውስጡም ስምንት የሂሳዊ ዲስኩር ትንተና መሰረተ ሀሳቦችን ይዟል። ይዘቶቹም እንደሚከተለው ቀርበዋል።

አንደኛው የተግባቦታዊ የዲስኩር ትንተና መሰረተ ሀሳብ ማዕከል ያደረገው ማህበረሰቡን መሆኑ ሲሆን፣ ይህ ትንተና ቋንቋንና በቋንቋ ትንተና ብቻ ላይ ያተኮረ አለመሆኑ ይልቁንስ ማህበረሰቡ የሚጠቀምበትን ስነልሳናዊ ባህርይና ማህበራዊ ህልውና ላይ ማተኮሩ ነው። ዲስኩር ትንተና በማህበረሰብ ችግርና ኑሮ ዙሪያ ያተኮረ በመሆኑ ግልጽ በሆነ መልኩ በማህበረሰቡ ዘንድ ያለውን በግልጽ የማይታይ የሀይል ግንኙነት ጭምር በማሳየት ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁነቶች በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ጠቀሜታ ያሳያል (ፌርክላፍና ወዳክ፣1997)።

ሁለተኛው መሰረታዊ ባህርይ ደግሞ ተግባቦታዊ የዲስኩር ትንተና የሚያሳየው በማህበረሰቡ ውስጥ ያለ የሀይል ሚዛን እንዴት እንደሚተገበር ነው። ሶስተኛው የዲስኩር መሰረቱ ማህበረሰቡና የማህበረሰቡ ባህል ነው። ይህም ማለት ቋንቋ የማህበረሰቡን ማንነት ለመግለጽ የበኩሉን ድርሻ እንደሚወጣ መግለጽ ይቻላል። ብሎም የሀይል ሚዛኑን ጉድኝት ጭምር ያሳያል።

አራተኛው መሰረተ ሀሳብ ደግሞ ዲስኩር በተጨማሪም አመለካከትንና የግል ፍልስፍናን የሚያሳይ መሆኑ ነው። አመለካከት በዲስኩር ሊገለጽ ይችላል። አመለካከትን ለይቶ ለማወቅ የቀረበውን አሀድ መተንተን ብቻ በቂ አይደለም። ይልቁንስ አሃዱ እንዴት

እንደተተነተና ተቀባይነቱ በማህበረሰቡ ዘንድ ምን እንደሚመስል ማየትና መመርመሩ ተገቢ ነው።

አምስተኛው ጠቃሚ ጉዳይ ዲስኩር ታሪክ መሆኑን ማወቅ ነው። አንድን ዲስኩር ማወቅና መረዳት የሚቻለው ታሪካዊ አመጣጡን ስንረዳ ብቻ ነው። ስለሆነም የዲስኩር ትንተና ለየት ያለ የቋንቋ አጠቃቀም ባህርይ ያለው ነው። ይኸውም ባህልን፣ ማህበረሰብንና አመለካከትን ታሪካዊነትን በተላበሰ አገላለጽ መግለጹ ልዩ ያደርገዋል።

ስድስተኛው ነጥብ ደግሞ የዲስኩር መርህ በሚቀርበው አሀድና ማህበረሰብ መካከል በመገኘት ሁለቱን ማቆራኘት መቻሉ ነው። ስለሆነም ዲስኩር የሚያየው የማህበረሰቡን እንቅስቃሴና ማህበራዊ መዋቅሩን ብሎም ይህን ለመግለጽ የቀረበውን አሀድ ነው። በዚህም መሰረት ፌርክላፍ በሚቀርበው አሀድና በማህበረሰብ መካከል ያለውን ውህደት ምን እንደሚመስል የዲስኩርን ቅደምተከተል በመመርመር አጥንተዋል። ይህም በማህበረሰብ ደረጃ ያለውን እውቀት ያስተዋወቀ ነው።

ሰባተኛው የሂሳዊ ዲስኩር ትንተና መሰረተ ሀሳብ መነሻ ዲስኩር ተተንታኝና ተገላጭ የመሆኑ ጉዳይ ነው። ሂሳዊ ዲስኩር ትንተና አሀድ ከመተንተን በላይ የሚሄድ ሲሆን፣ ይህም የሚተነትን ብቻ ሳይሆን ገላጭም ነው። በተጨማሪም በአዲስ ንባብና ተጨማሪ በሚገኝ አዲስ መረጃ ይጠናከራል። ሜየር (2001) ይህን አሰመልክቶ ዲስኩር የቀረበን የተጓዳኝ ወገንን መልእክትና ትርጉም በመረዳትና የትርጉሙ ተዛምዶ በማዋሀድ የሚተገበር እንደሆነ ይገልፃል።

ስምንተኛው የመጨረሻው ጉዳይ ከሂሳዊ ዲስኩር ትንተና አጠቃላይ እሳቤ በመነሳት ዲስኩር ማህበራዊ ቅርፅ ያለው እንደሆነ መደምደም ይቻላል። የሂሳዊ ዲስኩር መሰረታዊ አላማም እስካሁን ያልተዳሰሰውን የሀይል ግንኙነትንና መጠንን ማየትና መተንተን ሲሆን፣ ከዚህም በላይ ማህበራዊ ተልዕኮ ያለው አንድ ሳይንሳዊ የተግባቦት ትንተና ሞዴል ነው። የትንተናው ግብም በተግባቦታዊ ሂደት፣ በማህበራዊና በፖለቲካዊ ልማዶች ላይ ለውጥ ማምጣት እንደሆነ ይገልፃሉ።

2.5 የሂሳዊ ዲስኩር ትንተና እና የበላይነት ስሜት

በየትኛውም ምክንያት ይሁን ሀይል (የበላይነት ስሜት) በየትኛውም የህብረተሰብ ክፍል ውስጥ ይከሰታል። በፖለቲካ፣ በዜና፣ በህግ፣ በትምህርት፣ በሳይንስ፣ወዘተ. በምሁሩ፣በስራ ተቋማት፣ በህጉ፣ በሌላ ተራ ጉዳዮች ሁሉ ቢሆን የየራሳቸው ባህርይ መግለጫ ነው። በፖለቲካ የበላይነትን የጨበጡ ሁሉ የሚጠቀሙት ንግግርም ሆነ ዲስኩር ሰለባ ደግሞ ተራው ህዝብ ነው። ለምን ቢሉ ተማሪው፣ የቢሮ ሰራተኛው ሌላው ህብረተሰብ ሁሉ የሚመራው በዚሁ አንደበት ስለሆነ ነው (ቫን፣1999 እና ቶርንቦሮ 2005)።

በዲስኩር ውስጥ ዋናው ጉዳይ ሀይል ነው። በማህበረሰብ ውስጥ ያለው ማህበራዊ ሀይል የሚገለፀው በቡድን አለያም በተቋም ነው። ምንጊዜም ቢሆን ቡድን ሀይልና ተሰሚነት አለው። ይህም ቡድናዊነት ለተሰሚነትና ሀያል ለመሆን መሰረት ከመሆኑም በላይ በማህበረሰቡ ውስጥ ጎልቶ ለመታየት ያስችላል። የዚህም ጎልቶ መታየት ጉልበት፣ ገንዘብ፣ እውቅና፣ እውቀት፣ መረጃ ከማስገኘት አንፃር ይሆናል። ስለሆነም ውስብስብ የሆነውን በህብረተሰብ ውስጥ የሚታየውን ፍልስፍናም ሆነ ማህበራዊ ጉዳይ መሰረት ያደረገውን በበላይነት ስሜት የሚቆጣጠረውን ሀይልና የመምራት ስሜትን ወስዶ ማየት ተገቢ ነው። በመሆኑም የበላይነትን ከማሳየት አንፃር የሀይል ሚዛንን ከተለያየ አቅጣጫ ለያይቶ ማየት ይቻላል (ቫን፣1999)። ይኸውም፡-

- ሀይል ያላቸውና አመፀኞች በሀይል ከመመካታቸው አንፃር፣
- ሀብታሞች በገንዘብ ከመኩፈሳቸው አንፃር፣
- እውቀት አለን የሚሉት ደግሞ ለምሳሌ ፕሮፌሰር፣ ጋዜጠኛ፣... በእውቀታቸው መረጃ ከማግኘታቸው አንፃር፣
- አንድ ቡድን ሌላውን ቡድን በመቆጣጠር ሙሉ በሙሉ አለያም በተወሰነ ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የበላይነትን ከማሳየት አንፃርና
- ተጨቋኝ የህብረተሰብ ክፍሎች ጭቆና በቃኝ ሲሉና እምቢ አልቀበልም ማለት ሲጀምሩ በመሳሰሉት የሀይል ሚዛን ተከፋፍሎ ሊታይ ይችላል።

የበላይ የሆኑ ቡድኖች የበላይነታቸውን ለማንፀባረቅ ህግን፣ ሀይልን፣ ተለምዷዊ ባህልን፣ ሊጠቀሙ ይችላሉ። ለዚህም መደብ፣ ፆታ፣ ዘረኝነት፣የመሳሰሉት የበላይነት ማሳያና

መገለጫ ባህርያት ናቸው። በእርግጥ ሀይል ሁልጊዜ ህብረተሰብን የመጨቆኛ መሳሪያ ሆኖ ላይተገበር ይችላል። ሆኖም ግን ለሀያሉ ቡድን አስተማማኝ የሆነ የእለት ተዕለት ኑሮ ለመምራት አስተማማኝ መተግበሪያ የሚሆንበት ጊዜ አለ። ይህም በፆታ፣ በመደብና በዘረኝነት ብሎም በንዋይ ይገለፃል። በተመሳሳይ መልኩ በአንድ ቡድን ያለ አባል ሁሉ ምንጊዜም ሀይል ያለው ሆኖ አይቀጥልም። ሀይል ያለው ቡድኑ እንጅ ሁሉም የሀያሉ ቡደን አባላት አይደሉም።

በዲስኩር ትንተና ሂደት በሀይል ሚዛንና በዲስኩር ዙሪያ ያለው ግንኙነት የሚታየው የዲስኩር መገለጫ ይዘቶች ከሚባሉት ከፖለቲካ፣ ከዜና ማሰራጫ፣ ከሳይንስ አንፃር ስንመለከት ነው። ተግባር የሚመራውና የሚተገበረው በአእምሯችን ነው። በዚህም መሰረት የሰውን ልጅ አስተሳሰብ ለመያዝና ለመግዛት አመለካከቱን መቆጣጠርና መረዳት መቻል ይገባል። ስለሆነም ዋናው ዲስኩረኛ የሰውን ተግባርና አእምሮ የመቆጣጠር ብቃት እንዳለው መረዳት ያስፈልጋል። በመሆኑም የሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ምርምርን ስናካሂድ አንደኛ ሀይል ያላቸው ቡድኖች እንዴት ህዝባዊ ዲስኩርን መቆጣጠር ይችላሉ? ሁለተኛ ዲስኩር በህብረተሰብ ዘንድ የሚያስከትለው ተፅዕኖስ ምንድን ነው? ብሎ መመርመርና መተንተን ያስፈልጋል (ፌርክላፍ፣1989፤ ፌርክላፍና ወዳክ፣2000)።

2.6 የሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ማዕቀፎችና ደረጃዎች

ሂሳዊ የዲስኩር ትንተና የሚያተኩረው የቋንቋን ጠቀሜታ ከማህበረሰባዊ አውድና ከግለሰቡ አንፃር እንዴትነቱን ማየት ነው። ይህም ማህበራዊ ልምድን በማፍለቅ ወይም በመለወጥ ላይ ያተኩራል ፌርክላፍ(1992)። እንደምሁሩ አተያይ የዲስኩር አተገባበር ስርኣትን ከሶስት ዋና ዋና ጭብጦች አንፃር ያዩታል። ይኸውም የግለሰቡ ማንነት፣ የግለሰቦቹ (የቡድኑ) ግንኙነት ሁኔታና አመለካከትን ጭምር ያካትታል። ይህም የዲስኩሩን ምንነት ማንነትና ውህደት ያሳያል። በተጨማሪም የህብረተሰብን የኑሮ ውጣ ውረድ በማሳደግም ሆነ በመለወጥ ደረጃ ሀይል አለው። ስለሆነም የዲስኩርን ተግባር ከላይ ከተገለጹት ጭብጦች አንፃር ለማየትና ለመተንተን ዲስኩርን በጽሁፍ(በንግግር) በተጠኝዎቹ መካከል ያለውን ግንኙነትና ማህበራዊ ሂደቱን ማየት ተገቢ ነው።

ቋንቋ ሁልጊዜ የምንናገረውን ጭብጥና ጭብጡ የሚሸከረከርበትን አውድ የሚያንፀባርቅ መሳሪያ ነው። ጭብጥ ሰንል በማንኛውም ማህበራዊ አውድ ዙሪያ ስንነጋገርና ተግባቦት ስንፈፅም የምንነጋገርበት ርዕሰ ጉዳይ ማለት ነው። በዚህም ጉዳዮች ጭብጡን ለማቅረብ በምንነጋገርበት ወቅት አብረው የሚጓዙ ነጥቦችን ቀጥሎ በቀረቡት ጭብጦች መግለጽና ማቅረብ ይቻላል ሲሉ ጊ(1999) ይገልፃሉ።

- ተግባቦት መፈፀሚያ ተግባራት፡- ቋንቋ፣ ምልክት፣ የሰውነት እንቅስቃሴና ሌሎችን ግንዛቤ ማስጨበጫዎችና መልዕክት ማስተላለፊያዎች ናቸው። እነዚህም በጣም ጠቃሚና ተተግባሪ ጉዳዮች ናቸው።
- ተግባራዊ ጉዳይ፡- ንግግሩ (ውይይቱ) ሲካሄድ ተሳታፊዎቹ እየፈፀሙት ያለው ማህበራዊ ተግባር ወይም እንቅስቃሴን ነው። ይህም ተሳታፊዎቹ ንግግሩን ሲያካሂዱ እየፈፀሙት ያለውን ተግባር ወይም እንቅስቃሴያቸውን በቅደም ተከተል መግለፅ ያስፈልጋል።
- ማቴሪያል ጉዳዮች፡- ተግባቦታዊ ሂደቱ የተከናወነበትን ጊዜ፣ ቦታ፣ አካልና ቁስ ይመለከታል።
- ፖለቲካዊ ጉዳዮች፡- ማህበረሰቡ እንደጥሩ ነገር የወሰዳቸው ጉዳዮች ምሳሌ ሀያልነት፣ የስልጣን ደረጃ፣ የመሳሰሉት የህብረተሰብን ክፍፍል የሚያሳዩ ጉዳዮች ሲሆኑ፤ ቁንጅና፣ ማህበራዊ ደረጃ፣ ብርታት፣ ስልጣን፣ ዘር፣ ፆታ፣ የስርዓተፆታ ግንዛቤ እንዚህንና ሌሎችንም ማህበራዊ ክፍፍልን የሚያሳዩትን ሁሉ ይይዛል።
- ማህበረ-ባህላዊ ጉዳዮች፡- ግላዊ፣ ማህበረሰባዊና ባህላዊ ጉዳዮችን እንዲሁም ማንነትን፣ የሀይል ግንኙነትንና ባህላዊ ምልክታዊ ዘዴዎችን ሁሉ የሚያጠቃልል ጉዳይ ነው።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ጉዳዮች ሁሉ በህብረት የተግባቦት ዘዴውን የሚመሰርቱ ይዘቶች ናቸው። በመሆኑም ንግግር ትርጉም እንዲኖረው በማድረግ፣ ትርጉም በመስጠት ጎን ለጎን በመደጋገፍ ያገለግላሉ። በተግባቦት ሂደት ጭብጥ ሲባል ታሪካዊ ድርሰት ማለት ሳይሆን በአንድ ቅጽበት የሚደረግና የሚታይ ጉዳይ ማለት ነው። ይህንንም በተቋም ውስጥ የሚደረግን የእለት ተዕለት ተግባር ወስዶ በምሳሌ ማየት ይቻላል። ለምሳሌ አንድን መምህር ወስደን ብንመለከት መምህሩ ክፍል ውስጥ ሆኖ ሲያስተምር የሚያከናውነውን ተግባር ክፍሉ አንደሁነት መከሰቻ ተደርጎ ሲወሰድ፣ አንድ ሁነት ማለትም ማህበራዊ

ድርጊት ይኸውም የማስተማር ተግባር እየተፈፀመ መሆኑ ይገባናል። በዚህም ወቅት አመለካከት፣ ማንነትና ደረጃ ይንፀባረቃል። ክፍሉም የመምህሩ የበላይነት የሚንፀባረቅበት፣ ተማሪው ደግሞ ተከታይ የሚሆንበት ስርዓት ነው። ስለሆነም ክፍሉ፣ እንቅስቃሴው ሁሉ፣ ቋንቋው፣ ማህበራዊ እውቀቱ፣ አመለካከቱ፣ ማንነቱ፣የፖለቲካ ግንኙነቱ ሁሉ የማስተማር ሂደት ትኩረት ባይሆንም፣ በጠቅላላው ያለው ሁነት ግን የአለምን ምሉዕነት የምንገልጥበት ተጨባጭ ሂደት መሆኑን መረዳት ይቻላል። ስለሆነም ሁሉም ነገር ከተግባቦት ሂደትና ባህርይ ጋር የተያያዘ ነው።

የዲስኩር ትንተና በቋንቋ አጠቃቀም፣ በማህበረሰብና በባህላዊ መዋቅር ግንኙነት ላይ ያተኩራል። ይህም ማለት በአንድ በተወሰነ ተግባቦታዊ ጭብጥ ዙሪያ ለምሳሌ ስለአንድ ጉዳይ የተመለከተ ተግባቦታዊ ክስተት የያዘን ጋዜጣ በመውሰድ፣ በዲስኩሩ አጠቃላይ ሂደት ላይና በዲስኩሩ ዙሪያ በሚደረገው የቋንቋ አጠቃቀም ስልት ያለውን ግንኙነት በስፋት መመልከት ይቻላል (ፌርክላፍ፣1992፤2003)። ከዚህም አጠቃላይ ግንዛቤ በመነሳት ፌርክላፍ ሶስት ማዕቀፎች ያሉት የዲስኩር ትንተና ማዕቀፎችን አዘጋጅተዋል። አንደኛ የቀረበው ጭብጥ የቀረበበት የዲስኩር አሃድ፣ ሁለተኛ ዲስኩሩ የቀረበበት ስልት ወይም ድስኩራዊ ልማድና ስስተኛው ደግሞ የማህበረሰቡን የሃይል ግንኙነትና ፖለቲካዊ ሁኔታ ከአመለካከትና ከባህል አንፃር በጥልቀት የሚታይበት ማህበረ-ባህላዊ የትንተና ማዕቀፎች ናቸው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ድስኩራዊ አሃዱ በሶስቱ ማዕቀፎች ለመተንተን የመረጃ ገለፃ፣ ትርጎማና ማብራሪያ በሚሉ የትንተና አቀራረብ ደረጃዎች ላይ በመመስረት እንደሆነ ምሁሩ ገልፀዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ቫን(1993፣2000) የፌርክላፍን ሶስት የመተንተኛ ማዕቀፎችን በሁለት ደረጃዎች እንደሚታዩ ይገልፃሉ። እነሱም የመጀመሪያውንና ሁለተኛውን ማዕቀፍ በላዕላይ ደረጃ፤ በሶስተኛው ማዕቀፍ የበላይነት፣ ሀይል፣ ተባልጦ፣ ፖለቲካዊ ሁኔታና የመሳሰሉት ደግሞ በታዕታይ ደረጃ የሚታዩ ናቸው። ይህም ማለት ሂሳዊ የዲስኩር ትንተና የንድፈሃሳብ ድልድዮች እንዳሉት መረዳት ይቻላል። ድልድዮቹም ዝቅተኛና ከፍተኛ የአቀራረብ ደረጃዎች ተብለው ይለያሉ።

2.6.1 ድስኩራዊ አሃድ

የመጀመሪያው የትንተና ማዕቀፍ ድስኩራዊ አሃድ ሲሆን፣ አሃዱ በጽሁፍም ሆነ በንግግር ሊቀርብ ይችላል። በመሆኑም የተንታኙ ትኩረትና የትንተናው አይነት የቀረበው ይዘት እንዴት በተቀናበረ መልኩ እንደቀረበ ማየት ነው። ድስኩራዊ አሃድን በተመለከተ የቀረበው የፊርክላፍ (1992) ስራ በሚገባ ትኩረት ያገኘ ስራ ሆኗል። በዚህ ስር ትኩረት ተሰጥቶት የሚታየው የቋንቋ አጠቃቀም ሲሆን፣ ይኸውም በቃላት አጠቃቀምና ልዩ ትርጉም፣ በሰዋስው፣ በዘይቤያዊ አጠቃቀምና በመሳሰሉት ላይ ያተኩራል።

ክሪስታል(1987) እንደሚገልጹት የቋንቋ አጠቃቀም የምንለው የቋንቋ አጠቃቀም ምርጫችንን፣ የአነጋገር ስልታችንና፣ እንዲሁም የቋንቋ ምርጫችን ለሌሎች ያለው ተገቢነት ወዘተ. የሚያጠና የጥናት ዘርፍ ነው። ቋንቋ ስንናገር ብዙ ማህበራዊ ህጎችን እንጠቀማለን። ለምሳሌም ባህላዊ ህጎችን ስንጠቀም የእድሜ ባለጠጎችን በእድሜያቸው ልናከብራቸው ይገባል። የበላዮችንና ተቃራኒ ፆታንም እንዲሁ በማክበር ቋንቋን ባግባቡ መጠቀም ይገባል።

ከዚህም ሌላ የቋንቋ አጠቃቀም በንግግር ሂደት እንዴት መግባባት እንደምንችልና በምንግባባበት ወቅት የምናሳየውን እንቅስቃሴ ጭምር ያጠናል። በየትኛውም የንግግር አውድ መለየትና መምራት ያስችላል። ይህም ማለት የመጀመሪያው ጠቋሚ ንግግር የንግግሩ ቋንቋ ትርጉምና የአድማጩ ምላሽ ማለት ነው።

በድስኩራዊ አሃድ የንግግር ቋንቋ አተገባበርና መርህ፣ እንዲሁም የሰዋስው ግምባታና የቃላትን ቅርጽ እንዲሁ ይጠናል። በተጨማሪም የሰዎችን ንግግር ስሜት፣ሀሳብ ብሎም ተናጋሪው ሀሳቡን የሚያስተላልፍበት የቋንቋ መረጣ ይታያል። ይኸውም ቋንቋው ተለምዷዊም ሆነ ውበት የተላበሰ ምርጫ መሆኑን ጭምር የሚዳስስበት ክፍል ነው። ስለሆነም በቋንቋ አጠቃቀምና በቃላት ምርጫ ዙሪያ ማህበራዊ የበላይነት መንፀባረቅ አለመንፀባረቁን በጥልቀት ለመመርመር ያስችላል።

ቀጥሎ የተዘረዘሩት በድስኩራዊ አሃድ የቋንቋ አጠቃቀምን በተመለከተ በመረጃ መሰብሰቢያነትና በትንተና መሰረትነት የምንጠቀምባቸው ይዘቶች ናቸው። ይኸውም

የንግግር አድራጊዎቹን ንግግር በመሰብሰብ እንዴት በንግግሩ ሂደት ላይ ራሳቸውን እንዳቀረቡ ለማየት ያስችላሉ (ፌርክላፍ፣1992)።

2.6.1.1 ንግግራዊ አውድ

ንግግራዊ አውድ የምንለው የአገላለጽ ሂደት በንግግር ወቅት የተናጋሪውን አጠቃላይ ስዕል የሚያሳይ ነው። ይህም ማለት የተናጋሪውን ማንነት፣ የተናገረበትን ጊዜና ወቅት በንግግራዊ ዲስኩሩ ማሳየት የሚያስችል ይዘት ነው (ሃድሰን፣1985)። በንግግር ትንተና ጥናት ወቅት መደረግ ያለበት ተናጋሪው ራሱን እንዴት መግለጽና ማቅረብ እንደቻለ በተለያየ መልኩ ማየትና ማሳየት ነው። ሀድሰን እንደሚሉት ተናጋሪው በንግግሩ ወቅት እንዴት ከአንደኛ መደብ ወደ ሁለተኛ መደብ፣ ከሁለተኛና ከአንደኛ መደብ ወደሶስተኛ መደብ እንደሚሸጋገር በማየት ማህበራዊ ደረጃውን መለየት ማለት ነው። አንድ ተናጋሪ በአንድ ጭብጥ ላይ በጋራ ንግግር ሲያደርግ ወይም በተናጠል የድርሻውን ለመወጣት እንደሚጥር አያጠያይቅም። ይህም በተናጋሪዎች ዘንድ እውቅና ያሰጠዋል።

2.6.1.2 ምፀት

ምፀት የቋንቋ አጠቃቀም ጥበብ ነው። ይህም በተናጋሪውና በአድማጩ መካከል ያለውን ክፍተት ለማጥበብና ንግግሩ የበለጠ ተሰሚ ለማድረግ የሚደረግ የንግግር ጥበብ ነው። ስለሆነም እንደአቀራረቡ ብስለት ይመዘናል። ይህም ከንግግሩ ውጭ ሲሆንና አሉታዊ በሚሆንበት ወቅት ቁጣ ሊያስነሳና ከጠቀሜታው ይልቅ ጉዳትም ይኖረዋል። ምፀታዊ ንግግር ባግባቡ ከተጠቀምንበት የምንናገረውን ርዕሰ ጉዳይ በሚገባ አጉልቶ ሊያሳይ ይችላል። ስለሆነም ምፀቱ መቅረብ ያለበት በትክክልና በእርግጠኝነት ከምንናገረው ነገር ጋር የተቆራኘ መሆኑ ከታወቀ በኋላ ነው(ፌርክላፍ1992)።

2.6.1.3 አፅንኦታዊ ንግግር

አፅንኦታዊ ንግግር የምንለው ተናጋሪው በንግግር ወቅት የሚያሳየው የአነጋገር ሁነት(ዲስኩር) ከሚነጋገርበት ሁኔታ ጋር በአግባቡ መቃኘትን ያመለክታል። ይህንም አስመልክቶ ፍራሰር (1980) ሲገልፀ፣ ተናጋሪው በሚናገርበት ወቅት ለአድማጭ ቅርብ ለመሆን መጣርን፣ ንግግር ለዛ እንዲኖረው ማድረግን፣ የአድማጭን እንቅስቃሴ ባግባቡ

መከታተልን ሁሉ ያካትታል። በዚህም ውስጥ የሚያገለግሉ የአነጋገር ሞዴሎች ለምሳሌ ልንገርህ፣ መናገር አልፈልግም፣ ማለቴ፣ የሚሉና መሰል ሞዴሎች ይካተቱበታል (ዲዳክ 2004)።

ለምሳሌ ተናጋሪው በመናገር ላይ እያለ አድማጭ ተራውን ሳይጠብቅ ሊናገር ይችላል። በዚህ ወቅት ተናጋሪው ‹‹አድምጠኝ ልጨርስ፣አስጨርሰኝ›› ከማለት ይልቅ በተረጋጋና በሰከነ መንፈስ ‹‹ አንተ መናገር ከመጀመርህ በፊት ነገሬን ብታዳምጠኝና ብጨርስ ምን እያልኩ እንደሆነ ይከሰትልሃል›› ብሎ አለሳልሶ መናገር የአፅንኦታዊ አነጋገር ስልት ባህርይ ነው። ‹‹አሁንም ግልጽ ያልሆነ ነገር ካለ ከተፈቀደልኝ ግልጽ አድርጌ ላቀርብልህ እችላለሁ›› በማለት ንግግርን በተለሳለሰ መልኩ ማቅረብ ማለት ነው። ሆኖም ግን በእንደዚህ አይነቱ የአነጋገር ስልት ወቅት አንዱ አንዱን እንደሚያጣርስ ሀቅ ነው።

2.6.1.4 ቅድመ ግንዛቤ

ባግባቡ የሚቀርብ ንግግራዊ ምልልስ ሊተነተንና ሊታይ የሚችለው ንግግር በተግባር ሲፈጸምና ሲታይ ነው። ይህም በተናጋሪውና በአድማጩ መካከል ያለምንም ችግር ተግባቦትና መረዳዳት መኖር በመቻሉ ይገለፃል። ውጤታማ የሆነ ተግባቦት ሊፈፀም የሚችለው በተናጋሪውና በአድማጩ መካከል በሚፈጠረው የጋራ ሊያግባባ በሚችል ጉዳይ ዙሪያ ላይ ሲያጠነጥን ነው። ንግግር አግባብነት ሊኖረውና የጋራ ሊሆን የሚችለው ተሳታፊዎቹን ሊያግባባ የሚችል የጋራ የሆነና ሊያደርጉት የሚችል ጉዳይ ሲኖር ነው። ብራውንና ዬል (1991) እንደሚገልጹት ተናጋሪው ሆነ አድማጩ በሁለቱም መካከል ሊያግባባ የሚችል ጉዳይ ሊኖርና ሁለቱም በዚ ጉዳይ ላይ እውቀቱ ሊኖራቸው እንደሚገባ ያምናሉ። ተናጋሪው የሚያስተላልፈው መልዕክት ምንጊዜም ቢሆን ለአድማጩ ልምድ በሚመጥንና ሊገባ በሚችል መልኩ መሆን አለመሆኑ ማረጋገጥ መቻል አለበት። ስለሆነም ተናጋሪው የሚናገረው ነገር ለአድማጩ እንግዳ የሆነና አጨቃጫቂ የሆነ እውነታ የተላበሰ መሆን አይኖርበትም።

2.6.1.5 ድምፀት

በተግባቦት ሂደት የሚታዩ ድምፀቶች የአጽንኦትና የትኩረት መስጫ መገለጫ ቃላት ናቸው። ይህም ከድምፀት የሚጀምር ሲሆን፣ መልዕክትን በማስተላለፍ ረገድ አስተዋፅኦ አለው። መልዕክቱ ሲተላለፍ ግን ድምፀቱ የከረረና ለየት ባለ ስሜት የተሞላ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል። ሁከን (2007) እንደሚገልጹት የስሜት መግለጫ ድምፀቶች የሚባሉት ምናልባት፣ የግድ፣ እንደሚመስለኝ፣ ያለጭቅጭቅ፣ያለጥርጥር፣ አይቻልም፣ ወደፊት፣ የመሳሰሉትን አገላለጾችን ያካትታል። ይህም ሀይልን ለመግለጽና በንግግር ሂደት ጊዜ በድንፋታ ድምፀት ሰዎች እንዳይናገሩ ለማፈን ያገለግላሉ። በመሆኑም የዚህ አይነቱን ፈሊጣዊ ንግግር በማየትና ተናጋሪው ሲናገር በመከታተል ተመራማሪው የተናጋሪውንም ሆነ የአድማጩን ሁኔታ በቅርብና በትክክል በመከታተል ምን እንደሚመስል መተንተን ያስችለዋል።

በዲስኩር ትንተናና ምርምር ተግባራዊ ንግግር ጠቃሚ ነው። ይኸውም ንግግር በሚካሄድበት ወቅት የሴቶችንና የወንዶችን የንግግር ተፈጥሯዊ ሁኔታና ልዩነት ለመፍረድና ለመተንተን ያስችላልና ነው። ይህንንም በስራ ቦታ ላይ በሚደረግ መስተጋብር በርስ በርስ ንግግርም ሆነ በስብሰባ ላይ በሚደረግ ንግግር ማየትና መከታተል ይቻላል። በንግግር ወቅት የቋንቋ አጠቃቀም ሁኔታ ከሰው ሰው መለያየቱ እሙን ነው። ስለሆነም በዚህ ዙሪያ ያለውን የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነት ለማወቅ በጥናት ለማረጋገጥ መፈለጉ እያደገ የመጣ የጥናት መስክ ሆኗል። በዚህም ዙሪያ በተለይም በሴቶችና በወንዶች መካከል በሚደረግ ውይይትም ሆነ ንግግር ልዩነት መኖር አለመኖሩን የማረጋገጡ ጉዳይ ትኩረት ስቧል።

2.6.1.6 ስነምግባራዊ ስልት

በአንድ የንግግር ሂደት ተናጋሪው ሙያውንና በስብሰባው ላይ ያለውን የተሳትፎ ድርሻ ለተሰብሳቢው መግለጽ ማለት ተሰብሳቢው ለተናጋሪው የሚሰጠውን ማህበራዊ እውቅና በንግግሩ ሂደት ላይ ሊሰጡት እንደሚችሉ ማሰብ ተገቢ ነው። ፌርክላፍ (1989) እንደታዘቡትና እንደሚነግሩን ከሆነ ስነምግባር (ትህትና) የተሞላበት አቀራረብ እውቅናን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ የማህበራዊ ቅርበት ደረጃ መሰረት ያደረገ ጉልህ ነገር ነው።

ንግግር በተመልካች የፈካ ፊት ከታገዘ ንግግሩ ስኬታማ መሆኑን አያጠያይቅም። ብራውንና ሌቪንሰን(1978) እንደሚያምኑት አንድ ሰው በሚያደርገው ንግግር እጅግ ሊከበር አለያም ሊወገዝ እንደሚችል ለማሳየት ይቻላል። በእኛ ብሂል ‹‹ ከአነጋገር ይፈረዳል፣ ከአያያዝ ይቀዳል።›› እንዲሉ፣ ይኸውም ንግግር የተናጋሪውን ማንነት ማሳየት በመቻሉና ሌሎችም ስለሰውየው ማንነት መገመት እንዲችሉ በማገዙ ነው።

በምንነጋገርበት ጊዜ ትህትና ያለው አቀራረብ ሃላፊነትን በግልጽ በሚያሳይ መልኩ መሆን አለበት። ለምሳሌ የእኔ እመቤት፣ የኔ ጌታ በማለት አይነት የግል ባህርይን በተለያዬ የቋንቋ ስልት መግለጽ ይቻላል። ከዚህም ሌላ በተጋነነ መልኩም ሆነ በሌላ ዘዴ ትህትናን መግለጽ ይቻላል። ለምሳሌ በማቅማማት፣ ይቅርታ በመጠየቅ፣ መልካም ገጽታ በማሳየት ሊሆን ይችላል። እንደሚታወቀው ሁሉ ጥቁር ፊት ለበጎ ስነምግባር ምላሽ አይደለም። አሉታዊ የሆነ ነገርን ሁሉ የበጎ ስነምግባር ስልቶችን በመጠቀም አሉታዊ ስሜትን በማለዘብ ትሁት መሆን ይቻላል። ይኸውም ዝቅ ባለድምጽ በትህትና መናገርን ይጨምራል። ለምሳሌ ምናልባት፣ ቢቻል፣ ቢሆንም፣ በማለት ትህትናን መግለጽ ይቻላል። በሌላ መልኩ ቀና የሆነ ፈገግታ በራሱ ለትህትና መግለጫ ከምንላቸው ጉዳዮች በተለይም ቅርበትን ከመጋበዝ አንፃር አንዱና ዋናው ነው። ሌቪንሰን (1987) የትህትና ጽንሰሃሳብን ሲገልፅ፣ ከልብ የሆነ የአቀራረብ ስልት ባህርይ ከተናጋሪው ፊት ይታወቃል ይላል። ይህም የፊት ገጽታ የተናጋሪውንም ሆነ የአድማጩን ስሜት አሉታዊ መሆንና አለመሆንን የመግለጽ ሀይል ያለው በመሆኑ ለትህትና መገለጫ ዋና ድርሻ አለው።

ላኮፍ(1977) ሶስት የትህትና መገለጫ ስልቶች እንዳሉ ገልፀዋል። እነሱም ተለምዷዊ፣ ማቅማማትና እኩልነትን ማሳየት የሚሉት ሲሆኑ፣ እንደገና በሊች(1983) ደግሞ ሌሎችን ማስቀደም፣ የሎሎችን ጥቅም አለመጉዳት ፣መግባባትና መስማማት፣ራስን ማድነቅን ማስወገድ፣አለመግባባትን ማስወገድ፣ሌሎችን መርዳት/ማገዝ የተባሉ የመልካም ስነምግባር ስልቶች እንዳሉ ያስረዳሉ። ከዚህም በላይ ትህትና የተላበሰ ተግባቦት መገለጫው እኔን አድምጡኝ ከማለት ይልቅ ሌሎች ተናጋሪዎችን መቀላቀልና በትህትና መከታተል ነው። በመሆኑም ትህትና በማሳየት ሀይልንም ሆነ ማንነትን በንግግራችን ማሳየት ይቻላል። በዚህም በተግባቦት ሂደት አንፃራዊ በሆነ መልኩ የተናጋሪው የደረጃ ሁኔታና በማህበረሰቡ ዘንድ ያለው ከበሬታ ጭምር ይንጸባረቃል (ጎፍማን፣1968)።

2.6.2 ድስኩራዊ ልማድ

ሁለተኛው ማዕቀፍ ደግሞ በዲስኩሩ አቀራረብና አረዳድ ላይ የተመሰረተ ነው። ይህም ዲስኩሩ ተገላጭ መሆኑንና ከዚህም ባለፈ የሚፈልቅ፣ የሚዛወር፣ የሚሰራጭ፣ ለማህበራዊ ጠቀሜታ የሚውል መሆኑን በስፋት ይዳስሳል። ይህ ሂደት ባጠቃላይ የቋንቋ ውጤት እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል (ፌርክላፍ፣1992)።

በዚህ የትንተና ማዕቀፍ ለመግለጽ የሚሞከረው ተወያዮች በሚወያዩበት ወቅት ውይይታቸውንም ሆነ ንግግራቸውን እንዴት እንደሚቆጣጠሩና በሃሳብ ልውውጥ ወቅት ሀሳብን እንዴት ባግባቡ መለዋወጥ እንደሚችሉ ነው። የተግባቦት ትንተና በቋንቋ አጠቃቀም ዙሪያ ለሚደረግ ጥናት በጣም አስፈላጊ ነው። ስለሆነም የሃሳብ ልውውጥና ፊት ለፊት የምናደርገው ውይይት ለዲስኩር ትንተና ወሳኝና የመጀመሪያውን ደረጃ ይይዛሉ። ሌቪንሰን(1983) እንደሚገልጹት ተግባቦታዊ ትንተና አንዱ የዲስኩር ትንተና የጥናት ዘርፍ ሲሆን በሀሳብ ልውውጥ ወቅት ምን አይነት ቅደም ተከተል መኖር እንዳለበት፣ ምን መናገር እንዳለበትና ለዚህም ምን ግብኣት እንደሚያስፈልገው ለማወቅ የሚረዳ የጥናት መስክ ነው። በተጨማሪም የዲስኩር ትንተና ሀሳብ ልውውጥ ልክ እንደ ዲስኩር ሁሉ ስርዓት ያለውና በስርዓት የሚተገበር መሆኑን ያሳያል። የቀደመ የቋንቋን ህግና የቋንቋ አጠቃቀምን መሰረት በማድረግ ንግግር አድራጊዎች በንግግር ወቅት እንዴት ለራሳቸው ስልጣንና ክብር እንደሚሰጡና አንባራዊ በሆነ መልኩ በየቅፅበቱ ንግግር ሲያደርጉ የሚጠቀሙበት የስነልሳን ስልት አጠቃቀምን ያሳየናል። በዲስኩር ትንተና ሰዎች በንግግር ወቅት የሚጠቀሙበትን የአነጋገር ዘዴና ስልት እንዲሁም እንዴት እንደሚሳተፉና ተግባቦትን እንዴት እንደሚረዱ ማሳየት ያስችላል። ከዚህም በላይ የተግባቦት ትንተና የመጀመሪያና ተፈጥሯዊ የሆነውን የሰውን ልጅ ማህበራዊ ግንኙነት ማሳያ ተደርጎ ይወሰዳል።

ሌላው የተግባቦት ትንተና ጠቀሜታ ዋናውን ቁምነገርና የነገሩን ቅደም ተከተል በመልክ በመልኩ በማድረግ የተግባቦቱን ሂደት በከፍተኛ አስተዳደራዊ ጉዳይም ቢሆን ማሳየት መቻሉ ነው። ንግግር መነሻ የሚሆነው ጭብጥ ሁልጊዜም ቢሆን ይኖረዋል። ይህም በቅደም ተከተል የታጀበ ነው። ከዚህም ተነስቶ የተናጋሪውን ማንነትና ፍላጎት መተንበይና

መገመት ይቻላል። በመሆኑም የተግባቦት ትንተና የሴቶችንም ሆነ የወንዶችን የንግግር ሂደት ለማጥናት ጠቃሚ መሳሪያ ነው።

ጋምፐረዝ(1999) እንደሚገልጹት የተግባቦት ትንተና ጥቅም በመረጃ ትንተና ሂደት እንዴት ንግግሩ በቅደም ተከተል እንደተካሄደና አላማውን እንደመታ ብሎም ብስሉን ከጥሬ በመለየት ቁምነገሩ የተነገረበትን አውድ መርጦ በመውሰድ ለመተንተን ያስችላል። የማህበረሰቡንም ሂደታዊ ቅደም ተከተል በማሳየት በንግግር ሂደት ወቅት የንግግሩ ተናጋሪዎች እንዴት በንግግሩ ሂደት ላይ ድርሻቸውን እንደሚጠብቁ፣ ድርሻቸውንም መቼ ባግባቡ እንደሚጠቀሙበትና ሲናገሩም የሚናገሩት ቋንቋና ቃላት ለአውዱ ግልጽ መሆን አለመሆኑን በፊት ከተነገረው ጋር የሚናገሩት መጣጣም አለመጣጣሙን ለማየትም ይረዳል። ይህም ሲሆን የንግግር ትንተና ንግግር አድራጊዎች ምን እንደተረዱና ተረድተውም ምን ምላሽ እንደሰጡ በመፈተሽ በቋንቋ ዙሪያ ለሚደረግ የድርሻ ክወና በሚደረግበት ወቅት አገልግሎት ይሰጣል። ስለሆነም የተግባቦት ትንተና ውይይት ተሳታፊዎች ሀሳብ ለሀሳብ መግባባት እንዴት እንደሚችሉ፣ እንዴትም በውይይቱ ሂደት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ፣ የንግግር ወግና ስርዓት እንዴት እንደሚጠብቁ ከማሳየትና ብሎም የንግግር ባህርይን ከመግለጽ አንፃር ጠቀሜታው የጎላ ነው።

በዲስኩር ስልት የሀሳብ ልውውጥ ስርዓት መከተል የንግግሩን ርእሰ ጉዳይ መነሻ በማድረግ ሀሳብን የማዋቀርና የማሳለጥ ብቃትን ከማሳደጉም በላይ ድርሻን ጠብቆ የመናገር አቅምን ያበረታታል። በዚህም ተናጋሪው በንግግር ሂደቱ ንቁ ተሳታፊና ሂደቱን የመቆጣጠር አቅም ይፈጥርለታል።

በውይይት ላይ ጥናት ያደረጉ እነፊሸማን(1983)፣ ሳክስና ጓደኞቹ (1974)፣ ሳርጌይና ሮበርትስ (1999) እንደሚገልጹት የንግግር ፍሰት በተለያየ ርዕሰ ጉዳይ ሲደረግ ተናጋሪው ምንጊዜም ራሱን የሚያዘጋጀው ምንም እንቅፋት እንዳይገጥመውና የጎላ ችግር እንዳይኖር አስቦና አቅዶ ነው። ፌርክላፍ(1992) በበኩሉ የንግግር ስልትና ቅንብር ምንጊዜም ቢሆን በድርሻ ነጠቃ ወቅት እኩል ይሆናል ተብሎ እንደማይታሰብና አንዱ ተናጋሪ ረጅም ጊዜ ሌላው ደግሞ አነስተኛ ጊዜ የሚወስድ እንደሆነና ይህም ጠቀሜታ ያለው ጉዳይ መሆኑን ይገልፃል።

በመድረክ ዙሪያ ተናጋሪውም ሆነ ተከራካሪው ድርሻውን ጠብቆ መናገርና መከራከር ያለ ነው። ሆኖም ግን በመድረኩ ላይ አንዳንዱ ተራውን ሳይጠብቅ ጣልቃ ገብቶ ይናገራል። አንዳንዱ ደግሞ ከምን ተነስቶ ምን እንደሚናገር ላይታወቅ ይችላል። ያንዳንዱ ደግሞ ግራ የሚያጋባ ይሆናል። በእነዚህና በመሳሰሉት ጉዳዮች ምክንያት የውይይት ሂደት ግራ መጋባት ሊያጋጥም ይችላል።

በሌላ መልኩ ተሳታፊዎች ለመድረኩ ትኩረት በመስጠት መድረኩ ባማባቡ እንዲመራና እንዲከናወን ሲፈልጉ ምልክት በማሳየት የሚፈልጉትን የንግግርና የውይይት ሂደት እንዲመጣ ሊጠይቁ ይችላሉ። ይህም ተሳትፏቸውን በመግታትና በማሳደግ ሊሆን ይችላል። በዚህም መሰሉ ሂደት ተሳታፊዎች ውይይቱን ባማባቡ የመምራትና የመቆጣጠር ሀይል ይኖራቸዋል።

ኩክ(1990) እንደሚገልጹት የቀደመ እውቀት መኖር አእምሮ መዝግቦ የያዘውን ነገር እየመነዘሩ መጠቀም ስለሆነ ለዲስኩራችን የምንጠቀመውን ይዘት በሚገባ ለማሳየትና አጉልቶ ለማውጣት ያስችላል። ሌላው ተጨማሪ ጉዳይ መሰረታዊ እውቀት ወይም ግንዛቤ ካለን ያለውን የተለያየ ነገር ለመግለጽና ለመናገር ብቻ ሳይሆን ወደፊትም ተጨማሪ ለማሰብ ያግዛል። በአንድ ስብሰባ ክፍል ውስጥ ተመሳሳይና ተቀራራቢ እውቀት ያላቸው ተሰብሳቢዎች የሀሳብ ልውውጥ ለማድረግ ምቹ ናቸው። ስለሆነም የውይይቱ ሂደት ቀና ይሆናል።

በአንድ ተናጋሪ አእምሮ ውስጥ ያደረና የዋለ መሰረታዊ እውቀት ካለ የውይይቱን ርዕሰ ጉዳይ በማሳጠርም ሆነ በማስረዘም፣ ቅደም ተከተሉን በመጠበቅ ረገድ ከፍተኛ ሚና ያለው ከመሆኑም በላይ በሌሎች ላይ ጣልቃ በመግባትና ተናጋሪውን ለመንጠቅም፣...አቅም ይሰጣል። በሴቶችና በወንዶችም ቢሆን በውይይቱ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ እኩል እውቀት ካላቸው ንግግራቸው ተዛማጅና አቻ ይሆናል።

የተዘጋጀ ንግግርን ቅደም ተከተል በማየት መልዕክት ለማስተላለፍ የምንጠቀምበትን የንግግር ስልት በተለይም በስራ ቦታ ላይ ሂደቱን በመዘገብና በመዘርዘር የውይይቱ ተሳታፊዎች በውይይቱ ሂደት ዙሪያ ሀሳብን መረዳት መቻል፣ አለመቻልና የተሳታፊዎችን ፍላጎትና ስሜት ለማጤን ከሰበሰብነው መረጃ ማየትና ማግኘት ይቻላል። ሳሬንጅና

ሮበርት(1999) እንደሚስማሙት በውይይት ወቅት የሚደረግ የንግግር ትንተና አስፈላጊ ነው። ስለሆነም በውይይት ሂደት ሊከናወን ይችላል። ይህም የንግግርን ሂደት ባግባቡና ትርጉምን ጭምር ለመረዳት ያስችላል።

በስራ ቦታ ላይ በተጠኝዎቹ መካከል የሚደረግ የዲስኩር ትንተና ትኩረቱ ምን ያህል ዲስኩር እንደተመሰረተ፣ እንዴት እንደቀረበና የአረዳዱን ሁኔታ መመርመር ነው። በዚህ የትንተና ሂደት ትኩረት የሚደረገው በተጠኝዎቹ መካከል በሚደረግ ተግባቦታዊ መስተጋብር የሴቶችና የወንዶች ግንኙነት ምን እንደሚመስል፣ ሁለቱም እንዴት የድርሻቸውን እንደሚወጡና የሁነቶችን ገለፃ ማሳየትና መተንተን ላይ ነው።

ድስኩራዊ ልማድ በተግባቦት ሂደት የተሰበሰበን መረጃ በሂሳዊ ዲስኩር ለመተንተን የተመረጠ ሰልት ነው። ምክንያቱም በየትኛውም የንግግር አውድ በሚደረግ ዲስኩር ዙሪያ በመረጃነት ስለሚገኝ ነው። ቀጥሎ ዘርዘር ባለ መልኩ የድስኩራዊ ልማድ መተንተኛ መሳሪያዎች ለማሳየት ይሞከራል። የዚህም መረጃ ቅንብር ሂደት ተናጋሪዎች በንግግር ሂደት ንግግሩን እንዴት እንደሚተገብሩ ለማሳየት ይሆናል (ፌርክላፍ፣2006፤ ጊ፣1999)።

2.6.2.1 ተራን ጠብቆ መናገር

ይህ የትንተና ይዘት የውይይቱ ተሳታፊዎች እንዴት ድርሻቸውን ከሌላው ተናጋሪ ጠብቀው እንደሚናገሩና ድርሻቸውን እንደሚወጡ ያሳያል። በዚህ ሂደት በአንደበት የሚነገር ማንኛውም ነገር ተራን ጠብቆ የሚነገር ይሆናል። ቅደም ተከተል ማለት ከሌላው ተሳታፊ ጋር በተገናዘበ መልኩ የንግግሩን ርዕስ ጠብቆ በተራ ተራ ሲደርስ መናገር ማለት ነው። ይህም በሌሎች መደመጥን መሰረት ያደረገ ሲሆን አድማጭ እስከሚረዳ ድረስ የሚቀጥል ነው። ሌላው በድርሻ ክወና ሊታወቅ የሚገባው ተናጋሪው መቼ መናገር መጀመር እንዳለበት፣ በየትኛው ቅደም ተከተል የሚነገርበትን የጊዜ መጠን፣ መቼ ድርሻው እንደሚያልቅና እንዳለቀ የመሳሰሉትን ጉዳዮች ማየትና ማጤን ተገቢ ነው። እነዚህ ተላውጦዎች ለመናገር መብት እንዳለን አመላካችም ናቸው።

ንግግር የሚደረገው ደረጃ በደረጃ በሂደት ነው። ተናጋሪዎች ንግግር በሚለዋወጡበት ወቅት የሚነጋገሩት መርህ ተከትለው ነው። በእርግጥ መርህ ስንል የግድ የተደነገገ ባህል

የለውም፤ ያው የንግግሩ ይዘትና ሂደት የሚገዛው እንጂ። ይህም የሚመራው አንዱ ሲናገር መላሽ መኖር አለበት፤ ይህ ከሌለ ግን ድርሻን ጠብቆ ንግግርን ማስኬድ አይቻልም። አንድ ተናጋሪ በንግግሩ ወቅት በተደጋጋሚ የሚደመጥና የሚናገር ከሆነ የንግግሩን የበላይነት መያዙን ያመለክታል (ሙላኔ፣2007 እና ሳክስ፣1992)።

2.6.2.2 የሀሳብ ልውውጥ

ፌርክላፍ (2006) እንደሚገልጹት የተግባቦት ትንተና መሰረት ከሚያደርጋቸው ጉዳዮች አንዱ ተናጋሪ ሲናገርና አድማጩ የተረዳውን ነገር መሰረት አድርጎ ምላሽ ሲሰጥ የሚታየውን ክንውን መተንተን ነው። ምላሹም አዎንታዊም አሉታዊም ሊሆን ይችላል። ዋናው ቁም ነገር ምልልስ መከሰቱ ነው። የተናጋሪውን ድርሻ ክወና ምልልስ ለመተንተን ደግሞ የተግባቦት ትንተና የግድ አስፈላጊና ቀዳሚ ነው። ይህም እሳቤ ከእነ ሲ.ሲራሌና ኮልታርድ(1975) ጥናት ጋር ይዛመዳል። በዚህም ጥናት የሚታየውና የሚገልፀው ምጋቤ ምላሽ፣ ስሜታዊ ምላሽ የመሳሰሉት በውይይቱ ሂደት ውስጥ መከሰት የንግግሩ ሂደት ድርሻን መሰረት ባደረገ መልኩ እንዲቀጥል ማድረጉን ነው። የንግግር ልውውጥ ባግባቡ መቃኜት ለድርሻ ክወና መተግበር አመቺነት ብቻ ሳይሆን የመናገር ድርሻን የሚያሳይና በዲስኩር ሂደትም ውስጥ የንግግር ድርሻ እንዲጎላ ያስችላል።

2.6.2.3 መድረክ

መድረክን ባግባቡ መከታተልና መቆጣጠር ጠቀሜታ አለው። ጠቀሜታውም በመድረኩ ዙሪያ የሚደረገውን ጠቅላላ ሂደት በመከታተል የድርሻን ለመወጣትና ለማበርከት ብሎም በንቃት ለመሳተፍ ያስችላል። ይህም አንዱ ድርሻን ባግባቡ የመወጣት ብቃትን መላበሻ ዘዴ ነው። ፌርክላፍ (2006) እንደሚገልጹት መድረክና የንግግር ድርሻ በመድረክ አካባቢ ሰዎች ለውይይቱ ትኩረት ሰጥተው ከብዙ ሰዎች መካከል የድርሻቸውን የሚወጡበት ሂደትም ጭምር መሆኑን ነው።

2.6.2.4 አለመደማመጥ

ሳክስና ሌሎቹ(1974) እንደሚገልጹት በተግባቦት ሂደት ውስጥ አንድ ተናጋሪ ንግግሩን ከጨረሰ በኋላ ማቆም አለበት። ይህ ሳይሆን ከቀረና አንዱ ተናጋሪ እየተናገረ እያለ ሌላው ከተናገረ ጣልቃ መግባት ነው። ይህም አለመደማመጥንና መንጫጫትን ይፈጥራል። ይህን መሰሉ የንግግር እንቅፋት ለመቆጣጠርና ለመቅረፍ ቀድሞ እየተናገረ ያለው ሰው ቀጥሎ የሚናገረውን ሰው ስም በመጥራት፣ አለያም በምልክት በመጠቆም፣ መናገር የሚፈልግ ካለ በመጠየቅ፣ የመሳሰሉትን አማራጮች ቢጠቀም በስሜት ለመናገር ጣልቃ የሚገቡትን መቆጣጠር ይችላል። ይህ ስልት በሌለበት ሁኔታ ግን ጣልቃ ገብነት ሊከተል ይችላል። ይህም ማለት ተናጋሪው እየተናገረ ዝምታ ካበዛና ተግታ ካበዛ ሌሎች የንግግሩ ተሳታፊዎች ተናጋሪው ንግግሩን የጨረሰ ስለሚመስላቸው ጣልቃ ሊገቡ ይችላሉ። ኩክ (1952) ይህን አስመልክተው ሲገልፁ ጣልቃ ገብነት አንዳንዴ ጠቀሜታ አለው ብለዋል። ይኸውም አድማጮች ጣልቃ የሚገቡት ስህተት አለ ብለው ሲያምኑ ስህተቱ እንዲስተካከል ለመጠየቅ፣ አለያም ግራ መጋባት ሲኖር ግራ መጋባትን ለመቀነስ ስለሆነ ከዚህ አንፃር የጎላ ጠቀሜታ አለው።

2.6.2.5 ጣልቃ ገብነት

አንድ ተናጋሪ በሚናገርበት ጊዜ በንግግሩ ላይ ጣልቃ ገብነት ሊያጋጥመው ይችላል። ይህም በሽግግር ወቅት የሚጠቀምባቸው ዘዴዎች ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ። ድርሻን ለመውሰድ በምናደርገው የድምፅ ብክለት ሊከሰት ይችላል። ብዙ በመናገር በቆዩ ቁጥር ተናጋሪው ከአድማጭ ጭቅጭቅና ብጥብጣ ሊያጋጥመው ይችላል። ተናጋሪዎች ከአደንቋሪ ጨኽትና ከችኮላ ንግግር ራሳቸውን ባራቁ ቁጥር የተመልካችን ጣልቃ ገብነት ይቀንሳሉ። ከዚህም ሌላ ንግግርን ለማራዘም ሲባል የማይሰብ ንግግር በተግባቦት ሂደት ማስገባት ተመልካችን ለብጥብጣ ሊዳርግ ይችላል።

በሌላ በኩል ግን የንግግር ተሳታፊዎች በተናጋሪው ላይ ጣልቃ ገብቶ የመናገር መብት የሚኖርበት ጊዜ አለ። ይህም የሚሆነው ተናጋሪው ሲናገር የተናገረው ነገር ለአድማጩ ርባና የሌለውና መስተካከል ያለበት ጉዳይ ሆኖ ከተገኘ ለማስተካከል ሲባልም ጣልቃ እንደሚገባ ኩክ(1990) ያስረዳሉ።

2.6.2.6 ማስተካከያ/ተጨማሪ

በንግግር ሂደት ላይ የሚገኙ ተሳታፊዎች የራሳቸውን ንግግርም ሆነ የሌሎቹን የማስተካከል መብራ ሲያደርጉ ይታያል። ይህም የሚሆነው ብዙ ንግግር ሲደረግና ተናጋሪው የማስተካከያ ሀሳብ ካለ እንዲቀርብ ሲጋበዝ የሚተገበር ነው። ባብዛኛው ይህ ሲደረግ የሚታየው ተናጋሪው ሳይናገረው የቀረ ነገር አለ ብሎ አድማጩ ሲያስብ ‹‹ተጨማሪ›› ለማለት የምንናገረው ሂደት አይነት ነው የሚሆነው። ለዚህም ተጨማሪ በማለት ያልተሟላውን አሟልቶ ለማቅረብ ንቁ ተሳታፊ መሆን ያስፈልጋል። ይህንም አቲኪንሰን (1999) ማስተካከያ ለንግግር ቀጣይነት አስፈላጊ ነው በማለት ተገቢነቱን ይገልፃሉ።

በሌላ መልኩ በንግግሩ ዙሪያ የጠበቀ እውቀትና ልምድ ያላቸው፣ በእድሜ የበለጡ፣ በስልጣን የተሻሉ ወዘተ. ማስተካከያ እንዲሰጡ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል። ተገቢም የሚሆንበት ሁኔታ ሰፊ ነው። ይህም የንግግሩን ቅደም ተከተል ፈር ለማስያዝ፣ ነገሮችን የበለጠ ግልጽ ለማድረግና ተጨማሪ መረጃ ለመስጠት ሲባል አስፈላጊና ተገቢ ነው።

2.6.2.7 ርዕስን መጠበቅ

ሳክስ(1972) እንደሚገልጹት ተግባቦት የሚፈፀመው በሁለት ሰዎች መካከል የሚደረግ የንግግር ጭብጥ ፍሰት ባለው መልኩ ሲተገበር ነው። እንደዚህ ሲሆን አንዱ ለአንዱ ለሚናገረው ነገር ቅደም ተከተሉን ጠብቆ በመነጋገር ይተገበራል።

2.6.2.8 አጀንዳን ማዋቀር

የተቀናበረ (የተዘጋጀ) ርዕስ (ንግግር) ስንል ፍላጎታችንን በንግግር ቋንቋ አቀናብሮ ወይም ሲያስፈልግ እንደሁኔታው ቀያይሮ ማቅረብን ያሳየናል። ሳክስና ሌሎቹ (1974) እንደሚሉት ሀሳቦችን በቅደም ተከተል በሚያግባባ መልኩ ተዋህደውና አደናጋሪ ነገር ሳይቀላቀል ፍሰት ባለው መልኩ ሲቀርብ ተገቢ ተግባቦት ተፈፀመ እንላለን፤ ወይም የተግባቦት ትክክለኛነት መግለጫ እንደሆነ እንረዳለን።

በተግባቦት ሂደት ንyግግር ሲደረግ የሚታየው የበላይነቱን በወሰደና የበላይ በሆነው አካል ነው። በአብዛኛው ንግግር ወጥነት ባለው መንገድ ተግባራዊ ሲሆን አይታይም፤ አይሆንምም። ለዚህም ብዙ ምክንያቶች አሉ። ከእነዚህም ውስጥ ስልጣን፣ በተቋም ውስጥ ያለ የስራ ደረጃ፣ የሙያ ብቃት፣ እንዲሁም ፆታ በምክንያትነት ይጠቀሳሉ።

በንግግር ወቅት ዋናው ነገር ርዕሰ ጉዳዩን መቆጣጠር መቻል ነው። ይህም ማለት የርዕሰ ጉዳዩን ጭብጥ መገንዘብ፣ ርዕሰ ጉዳዩን ማንፀባረቅ፣ አስፈላጊም ሲሆን ነጥቡን መቀየር መቻል ነው። ርዕሰ ጉዳዩን መቃወምም ሆነ ከርዕሱ ጋር የተያያዘ ነገር አፍልቆ መናገር አለመቻል የንግግር ተሳታፊውን ከንግግር ተሳታፊነት ሊያገለው ይችላል። ሆኖም ግን በዚህ ዙሪያ ብዙም ጥናቶች ባይደረጉም ከወንዶች ይልቅ ሴቶች በንቃት እንደሚሳተፉና የወንዶቹን ድርሻ እንደማይነኩ፤ ወንዶች ግን የሴቶችን ድርሻ እንደሚነጥቁ (ዌስትና ጋሪሲ፣1988፤ፊሸማን፣1983)ጥናቶች አረጋግጠዋል። ምሁራኑ በጥናታቸው እንዳረጋገጡት አብዛኛውን ጊዜ በርዕሰ ጉዳይ መረጣ ዙሪያ ሴቶች በስፋት ሲሳተፉ ወንዶች ደግሞ አነስተኛ ርዕሰ ጉዳዮችን ያቀርባሉ። ሆኖም ግን ተመራጭ የሚሆነው በወንዶች የሚቀርበው ርዕሰ ጉዳይ ነው። ሌሎች ተመራማሪዎች ደግሞ በሁለቱም ፆታዎች መካከል ልዩነት እንደሌለ ይናገራሉ (ፌርክላፍ፣2006)።

በአብዛኛው በሁለቱም ቡድኖች የሚታየው ሴቶች የሚያቀርቧቸውን ርዕሰ ጉዳዮች ውድቅ ሲደረጉና የወንዶቹ አሸንፎ የመነጋገሪያ ርዕሰ ጉዳይ ሆኖ ሲፀድቅ ነው። ብዙ ጊዜ እንደሚታየው ብዙ ለማሳመን የሚጥሩት ሴቶች ይሁኑ እንጂ ምንም ይሁን ምን የሚጠናቀቀው በወንዶች ሀሳብ የበላይነት ነው። ይህ የሚያሳየው ‹‹ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ›› እንዲሉ ሴቶች ብዙ መሪ ሃሳብ ቢያቀርቡም ተቀባይነታቸው አናሳ መሆኑን ነው። በውይይት ርዕስ መረጣ ወንዶችም ሴቶችም ባብዛኛው ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም በስብሰባ አመራር ላይ ግን እያንዳንዱ መሪ የራሱን ስለሚከተል ልዩነት መኖሩ አይቀርም። በድርሻ ክወና የመብት ጥሰት ስንመለከት ወንዶች ለሴቶች እኩል መብት መሰጠትን ብዙም ሲደግፉ አይታይም። የሴቶችን መብት ከመከልከል አልፎ የድርሻቸውን እንኳን ሸፍነው እንዲናገሩ አይፈቅዱላቸውም። ይህም ሀሳባቸውን የማንፀባረቅና የማጎልበት አቅም ያሳጣቸዋል (ፊሸማን፣1983)።

2.6.3 ማህበረ-ባህላዊ ልማድ

ሶስተኛው የሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ማዕቀፍ መከሰቻ ደግሞ ማህበራዊና ባህላዊ እንቅስቃሴዎች ናቸው። ከዚሁ ከስሙ እንደምናዬው ዲስኩር ከተለያዬ ማህበረሰባዊ ተቋም አንፃር ልናዬው እንችላለን። ቲተስቸር እና ሌሎቹ(2000) እንደሚገልጹት ማህበራዊ ተቋም ስንል የማህበረሰቡን ሁኔታ፣ የተቋሙን አውድና የብዙሀኑን ወይም ማህበራዊ አውድን ሁሉ ያጠቃልላል። የእነዚህም ዋና ማዕከላዊ መገለጫ ስልጣን (ሀይል) ነው። ሀይልና አመለካከት በየትኛውም አውዳዊ ደረጃ ሚና አላቸው።

ማህበረ-ባህላዊ እንቅስቃሴ በቀጥታ ከቀረበው አሀድ ጋር የተያያዘና የተዛመደ ላይሆን ይችላል። ሆኖም ግን አንድ አሀድ ሲዘጋጅ ባህሉን የሚገልጽ መሆን ይኖርበታል። ኤርያንቶ (2001) እንደሚሉት የማህበረሰባዊ ባህልና የአሀድ ግንኙነት በአግባቡ ሊገለጽ የሚችለው በዲስኩር አማካይነት ነው። ይህንም መሰረት በማድረግ ፌርክላፍ (1992፣2006) የማህበረ-ባህላዊ ልማድን ለመተንተን ሶስት የመተንተኛ ደረጃዎችን አቅርበዋል። እነዚህም የመተንተኛ ዘዴዎች ሁኔታዊ፣ ተቋማዊና ማህበራዊ ደረጃዎች ናቸው። ሁኔታዊ ደረጃ ስንል አሃዱ በሚመሰረትበት ወቅት የነበረውን አጠቃላይ ሁኔታ የሚመለከት ሲሆን፣ አንድ አሀድ የተለያዬ ሁኔታን ስለሚገልጽ አሀዶች ሁሉ አንድ አይነት ሊሆኑ አይችሉም። ሁለተኛው ተቋማዊ ደረጃ የምንለው ዲስኩሩ በተቋሙ ዙሪያ ያነጣጠረ ስለሚሆን ትንተናውም ከተቋሙ ባህል አንፃር መታየት እንደሚገባው የሚያሳይ ነው። ምክንያቱም በአንድ ተቋም ውስጥ ያለው ተግባቦታዊ ሂደት በተቋሙ ወይም ከተቋሙ ውጭ ባለው ሁኔታ ተፅእኖ ላይ ሊወድቅ ይችላል። ሶስተኛው ደግሞ የማህበረሰቡን ሁኔታ በስፋት የሚያሳይ ደረጃ ነው። ይህም ማለት የማህበረሰቡን የፖለቲካ፣ የሀይል፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ኑሮ ሁኔታ ያጠቃለለ ነው። በዚህም ማን እንደሚመራና ማን ክብር እንዳለው የሀይል ግንኙነቱ የሚወሰንበት ነው።

በአጠቃላይ በዚህ የትንተና ማዕቀፍ የተጠኝዎች ንግግር ከሚከተሉት ርዕዩተ አለምም ሆነ ስልጣንን ከመተግበር አንፃር የሚገለጽ ነው። በዚህ ስር የሚደረገው ትንተና መስተዋድዶችና አያያገሮች በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ልማድና እምነት አሉታዊም ሆነ ቀና በሆነ መልኩ እንዴት እንደሚገለገሉበት ማሳየት ነው። የትኩረት አቅጣጫውም

ABABA UNIV
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ABABA

የዚህኑ ውጣ ውረድ ሀቅ ላይ ማተኮር ነው። ትንተናውም ትኩረት የሚያደርገው በአመለካከት ዙሪያ ሲሆን፣ ይህም በስራ ሂደት በምንና እንዴት መግባባት እንደሚቻልና ተግባብቶ መኖር እንደሚቻል ማሳየት ነው።

በእለት ተዕለት ተግባቦት ሂደትና ልምድ አንባር ሁለቱም አንድነት የሚፈጥሩ ናቸው። ለምሳሌ የዘረኛነት ንግግር በፓርላማ በዝቅተኛ ደረጃ የተወሰነ ማህበራዊ ጉዳይ ይዞ ሊታሰብ ሲችል፣ ባንባሩ በከፍተኛ ደረጃ ደግሞ ከህግ ጋር የተያዘና ፖለቲካዊ አንደምታ ያለው ሆኖ በከፍተኛ ደረጃ ሊቀርብ ይችላል።

በአጠቃላይ እንደፌርክላፍ (1995፣ 2006) ገለፃ እስካሁን የተመለከቱት የዲስኩር ትንተና ማዕቀፎች መሰረት በማድረግ የዲስኩር ትንተና ለማካሄድ ገለፃ፣ ትርጎማና ማብራሪያ የተሰኙ ሶስት ደረጃዎች ይኖራሉ። ይኸውም በመጀመሪያ ደረጃ አሃዳዊ ትንተናውን በተመለከተ በአሃዱ የተመለከቱትን ስነልሳናዊ ይዘቶች መግለፅ። በመሰረቱ የተግባቦታዊ ዲስኩር ትንተና መጀመር ያለበት የቀረበው ይዘት ምን እንደሚመስልና ምን እንደያዘ በትኩረት በመለየት ነው። በገለፃ ወቅት ተንታኙ በመጀመሪያ የተነገረውን ነገር በጥልቀት ማየትና ማስተዋል፣ ከዚያም በንባብ የቀረበውን አሃድ በትኩረት ማጥናትና በተለያዩ አይን መመልከት ያስፈልጋል። ከዚያም በኋላ በሚገባ በመረዳት ወደትንተናው መግባት ነው። ምሁሩ እንደሚሉት ተናጋሪው ሲናገር ይህን ለምን አለ? ለምን ተጠቀመ? የሚለውን ጭብጥ ለመለየት ያስችላልና ነው። ከዚህም ተነስቶ ተንታኙ ዲስኩሩ እንዴት ነው የቀረበው፣ ምን አይነት ጥያቄዎች ቀርበዋል፣ ንግግራዊ ሂደቱስ እንዴት ቀርቧል የሚሉትን በማየት በተግባቦት ሂደቱ በትክክል ምን እንደተባለና የአቀራረብ ድምፀቱ ምን እንደሚመስል መግለጽ ነው (ሁክን፣2007)።

ቀጥሎም በተመሰረተው አሃድና (በንግግሩና) በአድማጩ ግንዛቤ ሂደት መካከል ያለውን የዲስኩር አቀራረብ ግንኙነት መተርጎም ነው። በዚህ ደረጃ ሊከናወን የሚገባው የቀረበውን አሃድ ከዲስኩር መርህ አንባር መተንተን ነው። ፌርክላፍ(1989) እንደሚሉት አንድ ጽሁፍም ሆነ የንግግር ርዕስ ተወደደም ተጠላም በተዘዋዋሪ መንገድ ከማህበረሰብ ጋር የተቆራኘ ነው። ይህም በቋንቋውና ቋንቋውን ስንጠቀም የምንጠቀምበት የአገላለጽ ስልት ትርጉም ይኖረዋል።

በመጨረሻም በዲስኩሩ አቀራረብና በማህበረ-ባህላዊ ልማድ መካከል ያለውን ግንኙነት ማብራራት ሲሆን፤ በዚህ ደረጃ የምናየውና ትኩረት የምንሰጠው ለምንጠቀምበት ቋንቋ ነው። ሂሳዊ የዲስኩር ትንተና ስንል በትክክል የሚገልፀው በዲስኩርና በማህበረሰብ ውስጥ ያለውን የጠበቀ ግንኙነት መግለጽ በመሆኑ የዲስኩሩ አገላለጽም የሚሆነው በማህበረሰቡ ዙሪያ በሚታይ የተለያዬ ማህበረሰባዊ እንቅስቃሴ፣ ትግል፣ በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ባለው ተቋማዊ እንቅስቃሴና የሀይል ግንኙነት ላይ ያተኮረ ይሆናል (ፌርክላፍ1992)።

2.7 ተቋማዊ ባህል

በአንድ ተቋም ውስጥ ያለን የተግባቦት ሁኔታ ለማጥናትና ለመመርመር የተቋሙን የስራ ባህልም ሆነ አጠቃላይ ሁኔታ ማወቅ ተገቢ ጉዳይ ነው። ባህል የአንድ ህዝብ የአኗኗር ዘዴ ወይንም ብሂል ሲሆን፣ ከአለው ማህበረሰብ የተወሰደና ይሁነኝ ብሎ የተለመደ እንደሆነ ምሁራኑ ይገልፃሉ። በዋናነትም ባህል መግባባት ሲሆን፣ ሰዎች ለመኖር ሲሉ የሚለምዱትና ማህበራዊ ስነልቦና መሰረት ያደረገም ነው ይሉታል (ሃሪሰን፣1972)።

ተቋማዊ ባህል ከዚያው ከማህበረሰቡ የሚለመድና የተቋሙም ውጤት ነው። በመሆኑም ባህሉ የሚፀነሰውና የሚወለደው የተቋሙ ሰራተኞች በሚያደርጉት ግብብነት መሰረት ነው። አፈጣጠሩ በዚያው በተቋሙ ሰራተኞች በመሆኑ የተቋሙን ባህል በሚገባ መልመድና መቆጣጠርም ይችላል። ይህ ደግሞ የተቋሙ ሃላፊዎች ተገቢና አመቺ የሆነ ተቋማዊ ባህል ለመፍጠር ያስችላቸዋል።

በተቋማዊ ባህል ረገድ የተለያዩ ልማዶች እንዳሉም ይታመናል። ሃሪሰን(1972) እና ሞርጋን(1997) ይህኑ አስመልክተው ሲገልጹ፣ የተቋማት ባህል የሀይል ሚዛን ባህል፣ ሚና ተኮር ባህል፣ ተግባር ቀመስ ባህልና ግላዊ ባህል በመባል እንደሚጠሩ ጠቁመዋል። ይሁን እንጂ ማንኛውም ተቋም የራሱ የሆነ ባህል እንዲኖረው የግድ ነው። በመሆኑም የተቋሙ ሰራተኞች በተቋሙ ውስጥ አብረው መሄድ ከቻሉ ለተቋሙ ጥሩ አመለካከት ይኖራቸዋል። የአንድ ተቋም ባህል የሚያድገው በሂደት በመሆኑ ችግሮችንም የሚፈታው በሂደት ነው። ሰራተኛውም ይህን የሚረዳው በጊዜ ሂደት በመሆኑ የተቋሙን ቋሚ ባህልና

የሚመርጠውን ባህል ለማወቅ ጊዜ ይወስድበታል። ይህም የግልጽነት ችግር ቀስ በቀስ የተቋሙን ባህል ሰራተኛው እንዲሸከምና በአሰሪው የበላይነት እንዲመራ ያደርገዋል። በዚህም ሂደት ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ያላቸው ምርጫ የአለቃ ትዕዛዝን መቀበል አለያ ደግሞ በራስ አቋም ፀንቶ መጋፈጥን ምርጫ ያደርጋሉ።

አሁን አሁን ተቋማት እያደጉ በመምጣታቸው የግድ ተቋማዊ ባህልና አመራር አስፈላጊ እየሆነ መጥቷል። ይህም ተቋሙን ባግባቡ መምራት ያስችላል ከሚል እሳቤ በመነሳት ነው። ለዚህም ሃነይ(1986) የትምህርት ደረጃ፣ እድሜና ፆታ ወሳኝ ጉዳዮች እንደሆኑና ለግለሰባዊ ብቃት፣ ደረጃና መለያ አስፈላጊ መሆናቸውን ይገልፃሉ። ሌሎችም ተጨማሪ አስፈላጊ ነገሮች በመጨመር ለእድገት ሽግግር መሰረት መጣል ተገቢ እንደሆነ ያምናሉ።

2.8 ተቋማዊ ዲስኩር

የሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ድርሻ በንግግር ወቅት ተናጋሪው በእኩልነት መደመጥ አለመደመጥን መመርመር ነው። ይህም አላግባብ ሀይልን ከመጠቀምና የተወሰነ የህብረተሰብ ክፍልን ከማግለል አንፃር የታየ ነው። የተለያዩ ጥናቶችም ቢሆኑ ከሂሳዊ ዲስኩር ትንተና በተለየ መልኩ በተለያዩ ተቋማት ውስጥ በሙያዊ ዲስኩር ለምሳሌ በጽሁፍና በቃል የቀረበ ንግግርን እንዲሁም በፍርድ ሂደት ላይ የተካሄደን ንግግር ሳይቀር አጥንተዋል (ሙምባይ፣ 1993)።

የስራ ቦታ ማንኛውንም የተግባቦት አይነት ንግግርን ጨምሮ በተለያዩ ሁኔታ የሚከናወንበት ቦታ እንደሆነ ስትዩብ (2003) ይገልፃሉ። ይህም ባብዛኛው የሚደረገው ንግግር በስብሰባ ላይ ይተገበራል። አተገባበሩም በስራ ጓደኛሞች ፊት ለፊት የሚከናወን ሲሆን በጣም ጠቃሚ ነው። ባብዛኛው የስራ ላይ ስብሰባ የሚከናወነው በሙያ ዙሪያና በስልጣን ተዋረድ ሲሆን ማህበራዊ ጉዳዮችን አንስቶ ይጥላል፣ይወያያል። በዚህም የተሰብሳቢው ማንነትና የሙያ ብቃት ይንፀባረቅበታል። በስብሰባ ላይ የተናጋሪው ስልጣን ለማሳየትና ጎልቶ ለመውጣት ውድድር ይኖራል። ለዚህም በዲስኩር ወቅት የተለያዩ ዘዴ መጠቀምና ግብን ለማሳካት የሚደረግ እንቅስቃሴ ይታያል። ስለሆነም ማንኛውንም

የንግግር ዘዴና ስልት መጠቀም በዲስኩር ሂደት ማንነትን ለማሳየት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል።

በርካታ ስብሰባዎች የሚካሄዱት ሙያ ነክ በሆነ ጭብጥ ዙሪያ ሲሆን ተሰብሳቢዎችም እንዲሁ የተለያዩ ስልጣን ደረጃ ያላቸው ሆነው በርካታ ማህበራዊ ጉዳዮችን የሚያነሳ ይሆናሉ። ስለሆነም ተሰብሳቢዎቹ የድርሻቸውን ለመወጣት ጥረት ያደርጋሉ። በዚህም ሂደት ግባቸውን ለመምታት የንግግር ስልታቸውን ተግባራዊ ያደርጋሉ። ምክንያቱም የንግግር ግብኣትን በስልት መጠቀም ጠቃሚ ነውና።

የስራ ላይ ተግባቦት ትንተና በሁለት ጉዳዮች ዙሪያ ያጠነጥናል። የመጀመሪያው የዲስኩሩን ይዘትና የተናጋሪውን ማንነት ለማወቅ፣ ለመረዳትና ይህም ማን ምን ተናገረ የሚለውን ለመተንተን የሚጠቅም ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ዋናውና ጠቃሚው ጉዳይ ተናጋሪው በንግግሩ ወቅት የንግግሩ ሁኔታ ማንነትን በሚያሳይ መልክ፣ ስነልቦናዊ፣ ማህበራዊና ስርዓተያታዊ የቋንቋ አጠቃቀሙን ለማየት ይጠቅማል። ኤድሌይና ዌዘርል (1997) በሴትና በወንድ መካከል በሚደረግ የእውቀት ልውውጥ ዙሪያ የወንዱ የበላይነት እንዳለው በጥናታቸው ተረድተዋል። ይህም የማናጅመንት ስብሰባ ባብዛኛው የሚመራው በወንዶች የበላይነት መሆኑን የሚያመለክት ነው። ስለሆነም ስብሰባ የህብረተሰብን ድርሻ ምን እንደሚመስል ማሳየት የሚያስችል በመሆኑ የስልጣን ተዋረድን በሚገባ ለማጥናት ጠቃሚና ተመራጭ ሁነት ነው።

በተግባቦት ሂደት ላይ በመመስረት የአንድን ተቋም አጠቃላይ ሁኔታ ለማወቅና ለመለየት ስብሰባ ጠቃሚ ጉዳይ ነው። ሰዎች በስብሰባ ሊወስኗቸውና ሊወያዩባቸው የሚፈልጓቸው ጉዳዮች ይኖሯቸዋል። ይህም በተሰብሳቢዎችና በውሳኔ ሰጭው መካከል ያለውን የስልጣን ደረጃ ለማየት ያስችላል (ኤዶማና ወዳክ ፣1999፤ ሙባይ፣1988)።

በአንድ ተቋም ስብሰባ ወቅት በሚወሰን ውሳኔ የሀይልና የስልጣን ጉዳይ ይነሳል። ስብሰባዎች የእነዚህ ማሳያ ምልክቶች ናቸው። የአንድ ስብሰባ መሪ በስብሰባው ላይ ያለው የስራ ድርሻ ትኩረት የሚያሻው ነጥብ ነው። ይህም በዲስኩርና በማህበራዊ ስልጣን ዙሪያ መስተጋብር እንዳለ ያሳያል። ከዚህ አንፃር ማን በምን ወቅት ምን መናገር እንዳለበት

ከመወሰኑም በላይ ሀይል ያለው በማህበረሰቡ ዘንድ ብዙ የመናገር መብት እንዳለው ተደርጎ ይወሰዳል (ሙምባይ፣1988)።

ተቋማዊ ዲስኩር በተወሰነ ደረጃ ለተወሰነ አገልግሎት አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ አለ። በመጀመሪያ ደረጃ ዲስኩር ማህበራዊ እውነትን ይገልፃል። ቀጥሎም ስልጣንና ስልጣንን የመቆጣጠር ሀይል በተቋም ውስጥ ያለውን ድርሻ ይጠቁማል። ዲስኩር አንድን ማህበረሰብ እንዴት ሀሳብ ይለዋወጣል የሚለውን አብይ ቁም ነገር ብቻ ሳይሆን የሚያስተናግደው የተለያዩ ቡድኖች እንዴት እንደሚወዳደሩ፣ ፍላጎታቸውን እንዴት እንደሚያሳኩና ማንነታቸውን እንዴት እንደሚያሳዩ ጭምር ነው (ፌርክላፍ፣1992 እና ቫን፣1993)።


የዲስኩር ተንታኞች የስልጣን ተዋረድን በተቋማት ውስጥ እንዴት እንደሚተገበርና ተሳታፊዎች በተቋሙ ውስጥ ያላቸውን የስራ ድርሻ፣ የኢኮኖሚ ሁኔታ፣ ፆታ፣ ዘር፣ የመሳሰሉትን ሁሉ ያያሉ። ለዚህም ይህን ሁሉ ለማየት ንግግር ወሳኝ ድርሻ አለው። የተግባቦት ትንተና አቀራረብም ይህኑ ዲስኩር ሰዎች በተዋረድ እንዴት በቋንቋቸው እንደሚጠቀሙበት ያሳያል(ቶርንቦሮ፣2001)።

2.9. ተቋማዊ የዲስኩር መዋቅር

ተቋማዊ የተግባቦት መዋቅር ሲባል በተቋሙ በሚገኙ ማህበረሰብ መካከል መዋቅሩን የጠበቀ መልዕክት ከአንዱ ወደ አንዱ ባግባቡ የመተላለፍ ሂደትን ያመለክታል። የተቋማዊ ተግባቦት ሂደት መደበኛና ኢመደበኛ ተብሎ በሁለት መንገድ ይከፈላል። መደበኛ የሆነውም ሆነ ያልሆነው ተግባቦት ተቋሙንና ሰራተኛውን የማገናኘትና የማግባባት ተልዕኮ ያነገበ ነው (ሲቬዝ 2010)።

መደበኛ ተግባቦት፡- መደበኛ ተግባቦት የሚያቅፈው የተወሰኑ የስልጣን ተዋረዶችን ሲይዝ፣ ይህም በተቋሙ ባለስልጣናትና በተቋሙ ዙሪያ የሚደረግ አስተዳደራዊ ተግባቦቶችን ያቀፈ ተግባቦት ነው። በዚህ ስር ሶስት ዘርፎች ሲኖሩ የሚከተለውን ይመስላሉ (ድርያናን 2011)።

ስዕል አንድ፡- ተቋማዊ ዲስኩር መዋቅር



ምንጭ፣ (ድርያናን 2011፣4)

የመጀመሪያው የተግባቦት ፍሰት ከአለቃ ወደ ሰራተኛው፣ የሁለተኛው ከሰራተኛው ወደ አለቃ እንዲሁም ሶስተኛው አቻ ለአቻ (ከሰራተኛው ወደ ሰራተኛው) ጋር የሚደረግን የተግባቦት ሂደትን ያመለክታል። እንደ ጉድኦልና ጉድኦል (2002) እና ድርያናን (2011) አገላለጽ የተግባቦት ፍሰት ሁሉንም አቅጣጫ ካልያዘ ተግባቦቱ የአንድ ወገን ብቻ ስለሚሆን የሚተላለፈው መልዕክት እንቅፋት ይገጥመዋል። ዘመኑ የመረጃ ዘመን በመሆኑ ተግባቦት ውስብስብነት ይታይበታል። ይህም መረጃ የሚገኘው በተለያዬ ዘዴ ሲሆን አለቃ ከሰራተኛ (ከላይ ወደታች)፣ ሰራተኛ ከአለቃ (ከታች ወደላይ) እና ሰራተኛ ከሰራተኛ (የጎንዮሽ) ተግባቦት ይፈፀማል።

ቀደም ብሎ የነበረው የተግባቦት ባህል ከላይ ወደታች የሚፈስና የአንድ ወገን የነበረ ሲሆን፣ አሁን አሁን ግን የመረጃ ዘመን በመሆኑ ተግባቦት ከላይ ወደታች መሆኑ ቀርቶ በተቋሙ ውስጥ በየትኛውም ደረጃ መረጃ ለማግኘት ሲፈለግ የሚደረግ የግንኙነትን ሂደት መከተል እየሆነ መጥቷል (ድርያናን 2011 እና ሲቬዝ 2010)። አንድ ጥሩ መሪ/አስተዳዳሪ በየትኛውም ተግባቦትን ሊያሰተምር በሚችል መልኩ በአጫጭር ስብሰባ፣ በጽሁፍ፣ ፊት ለፊት በመገኘት ተግባቦትን ይተገብራል። ይህም በሰራተኛውና በአለቃ ብቻ ሳይሆን የሰራተኛው የርስ በርስ ግንኙነትን በማጠናከር ለስራው ስኬታማ መሆን እጅግ ጠቃሚ ነው (ኮንራድ፣2002)።

ኢመደበኛ ተግባቦት፡- ይህ የተግባቦት አይነት ተዋረዳዊ ግንኙነት በሌለበት በነፃ የሚተገበር የተግባቦት አይነት ነው። በዚህም አራት ደረጃዎች የሚካተቱ ሲሆን፣ በፕሮግራም የተያዘ ተግባቦት፣ በሂደት ላይ የሚከሰት ተግባቦት፣ በአስቸኳይና በድንገት የሚደረግ ተግባቦት

ናቸው። በፕሮግራም የሚደረገው መደበኛ ያልሆነ ግንኙነት የሚባለው በየስራ ክፍሉ የሚደረግ ሲሆን በሂደት ላይ የሚከሰት ተግባቦት ደግሞ አስፈላጊ ሲሆን ለምክክር የሚደረግ ውይይት ነው። ሌላው አስቸኳይ ውይይት ደግሞ በስራ ላይ የሚጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የሚደረግ ጓደኛዊ የሆነ የርስ በርስ ተግባቦት ሲሆን የመጨረሻው በማንኛውም ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ በአጋጣሚ የሚደረግ ተግባቦት ነው (ድርያናን 2011)።

2.10 የስርዓተፆታ ንድፈሃሳብ

ሰዎች ሁልጊዜ ማየት የሚፈልጉት በሚነገረው ጭብጥ ዙሪያ ሳይሆን ከተናጋሪው ፆታ አንፃር ማየት የተለመደ ነው። ከዚህም በመነሳት ተመራማሪው ውድ (2010) እንደሚሉት በወንዶችና በሴቶች መካከል ብዙ የሚታዩ ልዩነቶች መኖራቸው እሙን ቢሆንም ዋናው ልዩነት ግን ፆታቸው አይደለም። የልዩነቱ ዋናው መሰረት በሴቶችና በወንዶች መካከል ባለው የስልጣን ደረጃና የማህበረሰብ ድርሻ የሚንፀባረቅ እንደሆነ ያስረዳሉ። እንዲያውም አንዳንድ የቋንቋ ጥናትና ምርምሮች አሁን አሁን ሴትና ወንድ ተብሎ ከሚጠና ይልቅ ሁለቱ ካላቸው የስልጣን ሁኔታ አንፃር ቢታይ የሚሻል እንደሆነ ዋርተን (2005) ይገልፃሉ።

የስርዓተፆታ ንድፈሃሳብን በተመለከተ ሻን(1999) እና ዋርተን (2005) የበላይነትና የልዩነት ንድፈሃሳቦች በማለት በሴቶችና በወንዶች መካከል የሚታየውን የልዩነት ምክንያት ለማሳየት ሞክረዋል።

2.10.1 የበላይነት ንድፈሃሳብ

የበላይነት ንድፈሃሳብን ከተግባቦት አንፃር ስንመለከት የወንዶች የበላይነት መንፀባረቅና የሴቶች የበታችነት ስሜት በንግግር ወቅት መታየት ዋና ምክንያት የበላይነት ስሜት ማሳደር የፈጠረው ተፅዕኖ እንደሆነ ይገለፃሉ። ምክንያቱም ወንዶች በአካላዊ ብቃት፣ በገቢ መጠን፣ በስራ ቦታ ላይ በሚታየው ተዋረድ ሁሉ የበላይ ሆነው መታየታቸውና ሆነውም በመንቀሳቀሳቸው ምክንያት የተፈጠረ ነው። ስለሆነም ልዩነቱን ከፈጠሩት ጉዳዮች አንዱ የገቢ መጠን ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል። ይህም ሁኔታውን ለመቀበል እንደጤናማ

ምክንያት ሆኖ እንዲታይ ያስገድዳል። የእነፊሽማን (1980) ጥናትም የሚያረጋግጠው የወንዶች የበላይነትን በተዉሰነ አጋጣሚና አካባቢም ቢሆን ተቀባይነት እንዳለው አረጋግጧል። እንደምሳሌም በንግድና መሰል ተቋማት ዙሪያ በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ ሴቶች መናገር እንደሚችሉ፣ ነገር ግን ወንዶች ጣልቃ እንደሚገቡባቸውና የሚናገሩት ሃሳብም እንደቁም ነገር እንደማይወሰድ ተገልጿል።

በዚህ የበላይነት ንድፈሀሳብ ዙሪያ ሁለት ጉዳዮች እንደችግር ተነስተዋል። አንደኛው ጉዳይ ሴቶች አቅም የለሽና የጥቃት ሰለባ ተደርገው መወሰዳቸውና ወንዶች ደግሞ ሴቶችን የበታችና ርባና የለሾች አድርገው መቁጠራቸው ነው። ሁለተኛው የልዩነት ጉዳይ ደግሞ በህፃንነት ጊዜ የምንለምደው የአቻ ፆታ ጉድኝት ሲሆን፣ ከአደግንም በኋላ የተመሳሳይ ፆታ ጉድኝት የሚያሳድረው ተፅዕኖ ሴቶችንም ሆነ ወንዶችን የዚሁ የአቻ ፆታ ልማድ ባህል ተገዥ ያደርጋቸዋል። ይህም ባህርይ ይሆንና የመናገር ልምዳቸውም የዚሁ ባህላቸው ሰለባ እንዲሆኑ ተፅዕኖ ያሳድርባቸዋል በማለት እነ(ፊሽማን፣1980፤ሻን፣1999) ይገልፃሉ።

በዚህ ንድፈሃሳብ መሰረት የሴቶች የንግግር ፍላጎትና አተገባበር የሚያነጣጠረው በትብብር፣ በጉድኝት፣ በአንድነት፣ በእኩልነት፣ በመረዳዳት፣ በመገንዘብ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ነው። ወንዶች በተፃራሪው በመታወቅና የበላይነት ስሜትና በደረጃቸው ዙሪያ ያነጣጥራል። ለግልፅነትና ለመቻቻል ጉዳይ የላቸውም። ይህም በመሆኑ የተለያዬ ስሜት በመያዛቸው ሴቶችና ወንዶች በሚያደርጉት ንግግር ዙሪያ የመዋለል ስሜት ከመንፀባረቁም በላይ በመካከላቸው ያለው ልዩነት በተግባቦት ሂደት አለመግባባት እንዲፈጠር ከፍተኛ አስተዋፅዖ ይኖረዋል።

ሌላው የበላይነት አቀራረብ መገለጫ መታዬት ያለበት ከአካዳሚ ብቃት ይልቅ ቢታይ የሚሻለው የሴቶች በተቋሙ ውስጥ ካላቸው ተሳትፎ ማነስ አንፃር ነው። ይህም እንደወንዶች የበላይነትን በሚያላብስ የንግግር ሰልት ባለመናገራቸውና ተሳታፊነታቸው ጎልቶ ባለመውጣቱ ምክንያት በሙያዊ ብቃታቸው ላይ አሉታዊነት እንደሚፈጥር ዋርተን (2005) ያስረዳሉ።

2.10.2 የልዩነት ንድፈሃሳብ

በልዩነት ንድፈሃሳብ የሴቶችና የወንዶች የአነጋገር ልዩነት ከስነተፈጥሮ ሆርሞን መጠን ጋር የሚያያዝ ነው። ይኸውም ወንዶች ከሴቶች ጋር ሲነፃፀሩ ቁጡ የሆነ ስሜት እንዳላቸውና ለዚህም ምክንያቱ ከሴቶች ይልቅ የወንዶች የሆርሞን መጠን ከፍተኛ ስለሆነ ነው ብለው ያምናሉ። ሌሎች ደግሞ ይህን ልዩነት ከማህበራዊነት ጋር በማያያዝ ሴቶች ከመጀመሪያው ትሁትና የሌላውን ስሜት የሚጠብቁ ሆነው እንዲያድጉ ይጠበቃል። የወንዶች ግን ከዚህ በተቃራኒ ንቁና ቀልጣፋ ሆነው ማደግ እንዳለባቸው ይታመናል። ይህ ማህበራዊ ጉዳይ በማህበረሰብ ዘንድም ተቀባይነት ያለው ነው። ይህም በመሆኑ ሴቶች የሚገፉትና እንዲሆኑም የሚጠበቁት በማህበረሰቡ ዘንድ ሀይል የለሾችና ከወንዶች ያነሰ ሀይል ያላቸው ተደርጎ ነው (ባሬትና ዴቪድሰን፣2006)።

የሁለቱም ንድፈሃሳቦች ዋና ድክመት የሚመነጨውም ይህኑ ደካማ ሃሳብ ከመጋራቱ ጀምሮ ነው። ሆኖም ግን እድሜ፣ ሃይማኖት፣ መደብ፣ አካባቢና ባህል የመሳሰሉት በሴቶች ላይ ተፅዕኖ አያሳድሩም አይባልም። በአጠቃላይ በቋንቋ አጠቃቀማችን ዙሪያ የምናገኘው ፆታዊ መረጃ ስለፆታ ያለንን ግንዛቤ ገላጭ ነው። የምናስበውና የተገነዘብነውን ነገር ይሆናል ብለን ከምናስበው ነገር ጋር ስለሚጣረስ ሁሌም ያለን ማህበራዊ ግምት ተጨባጭ ላይሆን እንደሚችል መገመት ያስፈልጋል (ሻን፣1999)።

2.10.3 ስርዓተፆታ በተግባቦት ላይ ያለው ተፅዕኖ

በተግባቦት ሂደት እንቅፋት ከሚፈጥሩ ጉዳዮች አንዱ ስርዓተፆታ ነው። በየትኛውም ተግባቦት አውድ ዙሪያ በሴትና በወንድ መካከል በሚደረግ ተግባቦታዊ መስተጋብር የሚታይ የንግግር ስልት ልዩነት አለ። ውድ(2010) ተግባቦት፣ ስርዓተፆታና ባህል በሚለው ጽሁፋቸው እንደገለጹት ስርዓተፆታዊ ተግባቦት ከህፃንነት ጀምሮ የሚመጣ ሲሆን ወንዶችና ሴቶች ከመጀመሪያው ሲያድጉ የተለያዩ ስነልሳናዊ የተግባቦት ስልት እንደሚያዳብሩ በሚያደርግ ከባቢ እንደሚያድጉ ገልፀዋል። ይህም አብዛኛውን ጊዜ የሴቶች ንግግር ለወንዶች የማይመች እየሆነና እየተለመደ ያድጋል፣ የሚያቀርቡት ሃሳብም ተቀባይነት አይኖረውም። በእኔ ልምድ ይላሉ ጸሐፊዋ ሴቶች ርኃታ የተሞላበት የሴትነትን ወግ የሚገልጽ ቃላት እንዲናገሩ ባህሉ ሲያዝ ወንዶች ደግሞ ከህፃንነታቸው ጀምሮ

በጨዋት እንዲጫወቱ፣ በሀይል እንዲናገሩ እንደሚፈቅድ የታመነና ይህ ልማድ አሁንም እንደቀጠለ ይገኛል። እንደታነን (1990) አገላለጽ ደግሞ ወንዶችና ሴቶች ራሳቸውን የሚገልጹበት መንገድ የተለያየ ሲሆን፣ ወንዶች በንግግራቸው ራሳቸውን የቻሉ ጠንካራ መስለው ለመታየት ሲሞክሩ ሴቶች ደግሞ በመግባባትና በፍቅር ላይ የተመሰረት ተግባቦትን ይመርጣሉ። ይህ ተግባቦታዊ ልዩነት ከልጅነታቸው ጀምረው ሲያድጉ ወንዱ ጠንካራ ሴታ ደካማ እንደሆነች ተደርጎ በማደጋቸው ምክንያት የተፈጠረ ነው። ለምሳሌ ሴት ልጅ በትንሽ ጉዳት ብታለቅስ አይፈረድባትም፤ ወንድ ልጅ ግን በትንሽ ጉዳት ፈጽሞ ሲያለቅስ መታየት የለበትም። ይህም የሚያሳየው በወንድና በሴት ላይ ያለውን የአመለካከት ልዩነት ነው(ወድ 2010)። በሌላ በኩል የወንዶችና የሴቶች ተግባቦታዊ ስልት እንደሚለያይና የልዩነቱ ምክንያት ደግሞ የሁለቱ ፆታዎች አመጣጥ የተለያየ በመሆኑ እንደሆነ ግሪይ(2002) ያስረዳሉ። ይኸውም ወንዶች ከማርስ ሴቶች ደግሞ ከቬኑስ የመጡ የሁለት ዓለም ሰዎች በመሆናቸው ነው በማለት በአስተዳደጋቸው ምክንት የተፈጠረውን ልዩነት ጠንከር አድርገው ገልፀውታል።

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት ማየት የተፈለገው በስራ ተቋም የሚደረግን ተግባቦታዊ ስልት በሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ዘዴ በመጠቀም ማሳየት ነው። የትንተናው ትኩረት በቋንቋ (በተግባቦት ስልት)፣ በስርዓተፆታና በሀይል መካከል ያለውን ግንኙነት በማሳየት ላይ የሚያተኩር ሲሆን፤ ጥናቱም ይዞት የተነሳውን የምርምር ጥያቄ ከዚህ በታች በቀረበው ንድፈሃሳባዊ ማዕቀፍ መነሻነት በሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ስልት ለመፈተሽ ነው።

2.11 የጥናቱ ንድፈሃሳባዊና ግንዛቤያዊ ማዕቀፍ

የጥናቱ መሰረት ገለፃው፣ ትንተናውና ግኙቱ ሁሉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ማህበረሰብ ነው። ይህም በስራ ቦታ በሚደረግ ተግባቦት ላይ የሚገለጽ ሲሆን ትኩረቱ ማህበረሰቡ የገነባውን ስርዓተፆታዊ ተግባቦት የሚመለከት በመሆኑ፣ ጥናቱ የግንባታውያንን ፍልስፍና አቅጣጫ ይከተላል (ፌርክላፍ፣ 2002)። በዚህም የበላይነትና የልዩነትን ንድፈሃሳቦች መሰረት በማድረግ በከፍተኛ ተቋማት ያሉ መምህራን ትምህርታዊ ጉዳዮችን አስመልክተው በሚያደርጉት ተግባቦታዊ መስተጋብር የገነቡትን ስርዓተፆታዊ የቋንቋ አጠቃቀም ይገልፃል፣

የተዛቡ ድስኩራዊና ማህበራዊ ልማድን ይተነትናል፣ እንዲሁም ምን አይነት ለውጥ መካሄድ እንዳለበት ይጠቁማል (ፌርክላፍ፣ 2006፤ ይን፣2011)።

ዲስኩር በውስጡ አሃድ፣ መስተጋብርና ማህበራዊ አውድ የተሰኙ ሶስት መሰረታዊ ነገሮችን የያዘና ከእነዚህም የሚመሰረት ነው። በዚህ መነሻ የሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ሂደት ሶስት ማዕቀፎችንና ደረጃዎችን ይከተላል። አንደኛ ድስኩራዊ አሃዱን መግለፅ፣ ሁለተኛ በድስኩራዊ አሃዱና በመስተጋብሩ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመለከተውን ድስኩራዊ ልማድ መተንተን፣ ሶስተኛ በመስተጋብሩና በማህበራዊ አውዱ መካከል ያለውን ግንኙነት መተርጎም ናቸው (ፌርክላፍ፣2006 እና ቫን፣2008)።

በዚህ ምዕራፍ ለመግለፅ የተሞከረው የቀረቡት የሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ንድፈሃሳቦችና ዘዴዎች እርስ በርሳቸው በመደጋገፍ በተግባቦት ሂደት ተናጋሪዎቹ ሃሳባቸውን እንዴት እንደሚገልጹ ሁኔታውን በየፊርጁ ለማሳየትና ለመግለጽ እንደሚያስችሉ በስፋት ተዳሷል። ይህም የሂሳዊ የዲስኩር ትንተና ማዕቀፎች በተግባቦት ፈፃሚዎቹ መካከል ያለውን ሂደት ለመለየትና ለመናገር ብሎም እንዴት መልዕክት ለማስተላለፍ እንደሚቻልና የአድማጭን ስሜት መጋራት እንደሚቻል ጠንካራና ብቁ መተንተኛዎች ናቸው።


የድስኩራዊ አሃድ ትንተና፣ ድስኩራዊ ልማድና ማህበረ-ባህላዊ ዲስኩር ትንተና በውህደትና በቅንጅት ውጤታማ የሆነ የተግባቦት ትንተና ማዕቀፍ መፍጠር ያስችላሉ። በስራ ቦታ ላይ የሚደረግ መስተጋብራዊ ንግግር ላይ ያተኮረ ጥናት በተፈጥሮው ኢትኖግራፊያዊ ምርምርን መሰረት ያደርጋል። ለምሳሌ ወስደን ስንመለከት በአንድ የስራ ተቋም ውስጥ በሚገኝ የቦርድ ስብሰባ ሂደት ላይ በሚደረግ ንግግር የስነልሳንና የባህልን ሁኔታ በሚገባ በማሳየት ረገድ ንግግር ጠቃሚነቱ የጎላ ነው። በተጨማሪም የንግግር ችሎታን በተመለከተ የሚታዩ የተዛቡ አመለካከቶችን ብሎም በግልም ሆነ በተቋም ደረጃ የሚደረጉ መገለሎችን ሁሉ ለማሳየት ያስችላል። የድስኩራዊ አሃድና የድስኩራዊ ልማድ የመተንተኛ መሳሪያዎች የፈለቀውን ድስኩራዊ አሃድ በተለየ ሁኔታ ለመግለፅና ለመተንተን ያስችላሉ።

በዚህም መሰረት በምዕራፍ አራት በቀረበው የመረጃ ትንተና የተጠቀምኩት ሶስቱን የፌርክላፍን (2006) የተግባቦት ትንተና አቅጣጫዎች ሲሆን፤ እነሱም ድስኩራዊ አሃድ፣

ድስኩራዊ ልማድና ማህበረ-ባህላዊ ልማድ /ሂሳዊ ዲስኩር ትንተናዎች ናቸው። እንደመተንተኛ መሳሪያ የተወሰዱት ድስኩራዊ አሃድና ድስኩራዊ ልማድ ተለምዷዊ በሆነ ሁኔታ የንግግርን ተግባቦትና የቋንቋ አጠቃቀም ችሎታን ለመግለፅ የሚያስችሉ ሲሆን የንግግሩን ሂደት ማለትም ምላሹን፣ ድርሻውን፣ ምን ይናገራል፣ ምን ይመስላል፣ ወዘተ. የሚሉትን ቅንብሮች ሁሉ ይመለከታል። ማህበረ-ባህላዊ ትንተና ደግሞ የንግግሩን ሂደትና የሚያስተላልፈውን መልዕክት ባግባቡ ማስተላለፉን በጥልቀት በመተንተን የሃይል ግንኙነቱንና ማህበራዊ አመለካከቱ ምን እንደሚመስል ያብራራል። በአጠቃላይ ይህ የሶስትዮሽ አቀራረብ ጠንካራና ተመራጭ የሆነና በስራ ቦታ በወንዶችና በሴቶች መካከል የሚደረግን የስብሰባ ላይ ንግግርን አስመልክቶ እንዴት እንደሚተገብሩት ግልጽ መረጃ ይሰጣል።

በተጨማሪም ተናጋሪዎች በንግግር ወቅት የሚናገሩት ንግግር የተለመደ ብቻ አይሆንም። ይልቁንስ ከተቋሙ አንፃር የሙያ ብቃትን ጭምር ከንግግሩ አውድ በመነሳት እንደሚናገሩ ይጠበቃል። ስለሆነም በሂደት የቅደም ተከተሉ መዋቅር በራሳቸው ቋንቋ የራሳቸውን ስሜት መግለጽ ይሆናል። ስለሆነም የተግባቦታዊ ትንተና ትኩረትና አላማ በንግግር ትንተና ወቅት የንግግር ድርሻን ቅደም ተከተል እንዴትነት ማሳየትና ብሎም የንግግሩን ጭብጥና የተነገረበትን ቋንቋ ተግባቦታዊ ሂደት በንግግር ሂደቱ ወቅት የታየውን ክስተት ማሳየት ነው።

በአጠቃላይ ስርዓተ-ፆታዊ ተግባቦት ስልትን ለመተንተን ከላይ የተነሱት የግንባታውያንን የፍልስፍና አቅጣጫና የሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ሞዴልን መነሻ ማድረግ ተገቢ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። ይህ ጥናትም ይዞት የተነሳው ጥያቄ ከዚህ በታች በቀረበው ሞዴል መነሻነት የሚተገበሩ ሂደቶችን ተከትሎ በሚከሰት ውጤት የሚመጣውን አስተዋፅኦ ለመፈተሽ ያስችላል ተብሎ ተገምቷል።



ስዕል ሁለት፡- በስራ ቦታ ላይ የሚታይ ስርዓተፆታዊ የተግባቦት ሞዴል

ከላይ የቀረበው ሞዴል በጥናቱ ሊፈተሽ የታሰበው ስርዓተፆታዊ የተግባቦት ስልት በስራ ቦታ ላይ እንዴት መካሄድ እንዳለበት የሚያሳይ ነው። በሞዴሉ እንደተመለከተው ከተመሳሳይ ማህበረሰብ የመጡ ግን ደግሞ በአስተዳደጋቸው ልዩነት ምክንያት የተለያየ ዳራ ያላቸው ወንዶችና ሴቶች በአንድ የስራ ቦታ ላይ በአንድነት ስራን ያከናውናሉ። በዚህ አውድ የስራ ጉዳያቸውን መሰረት በማድረግ የተለያዩ ድስኩሮችን (ውይይቶችን) ያካሂዳሉ። ተቋማዊ ዲስኩር ደግሞ የተግባቦት ቅደም ተከተልን፣ የንግግር ድርሻንና ስርዓተ ፆታዊ የተግባቦት ጭብጥ ውጤትን መሰረት በማድረግ መመስረት ይኖርበታል። ይኸውም የውይይቱ ሂደቱ ከመነሻ እስከ መድረሻ የራሱ የሆነ ቅደም ተከተላዊ አካሄድ ያለው ሲሆን፣ በዚህ ሂደት ሃሳባቸውን በማቅረብ ተሳታፊ የሆኑት ሴቶችና ወንዶች የንግግር ድርሻን በተገቢው ጊዜ ይወስዳሉ። የግባቦት ቅደም ተከተሉም ሆነ የንግግር ድርሻው ደግሞ

የተለያየ ልምድ ያላቸውን ሴቶችና ወንዶች ግብዓት ሊያስገኝ በሚችል ስርዓተ ፆታዊ የተግባቦት ጭብጥ ውጤት ላይ መመስረት ይገበዋል።

በአጠቃላይ በስራ ተቋም የሚደረግ ተግባቦት እነዚህን ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች መሰረት ያደረገ የተግባቦት ስርዓት የሚኖረው ከሆነ በየትኛውም ውይይት ላይ ሁሉም ተሳታፊዎች በሚነሱት የውይይት ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ልምድ፣ እውቀትና አስተሳሰብ መሰረት በማድረግ ሀሳብ ያቀርባሉ። በዚህ ሂደት በሰብሳቢም ሆነ በተሳታፊዎች የንግግር ድርሻ በአግባቡ በመስጠትና በመውሰድ ወንዶችና ሴቶች የተግባቦትን ቅደም ተከተል በመጠበቅ በእኩል ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ሁኔታዎች ምቹ ስለሚሆኑ ሁሉም የድርሻቸውን ለመወጣት እድሉን ያገኛሉ። በዚህም የውይይቱ ተሳታፊዎች በሚያቀርቧቸው ሀሳቦች የስራ ተቋሙን አሰራር ያሻሽላሉ፣ ይለውጣሉ፣ እነሱም በስራ ቦታ ላይ በሚደረግ አጠቃላይ ክንውን ላይ እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ ይሆናሉ። የዚህ ውጤት ደግሞ ተቋሙም ሆነ ሰራተኛው በሚሰሯቸው ስራዎች ስኬታማ ይሆናሉ። ይህም የስራ ተቋሙ በድስኩራዊ ተራክቦው ተፅዕኖ የሚደርስበት ሲሆን በተመሳሳይ ድስኩራዊ ተራክቦው ደግሞ በስራ ተቋሙ (በተቋማዊ ባህሉ) ተፅዕኖ እንደሚደርስበት ያሳያል።

ምዕራፍ ሶስት፤ የአጠናን ዘዴ

3.1 መግቢያ

የዚህ ጥናት ዋና ኣላማ በከፍተኛ ትምህርት ተቋም በስራ ቦታ ላይ የሚታየውን ስርዓተፆታዊ የተግባቦት ስልት ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው። ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ጥናቱ የተለያዩ ዘዴዎችን በመከተል ተከናውኗል። በዚህ ምዕራፍም የአጠናን ዘዴ፣ የናሙና አመራረጥ ዘዴ፣ የምርምሩ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች፣ የመረጃ አሰባበሰብ ቅደም ተከተል፣ የመረጃ ትንተና ዘዴ፣ የጥናቱ አስተማማኝነትና ትክክለኝነት እንዲሁም የቅድመ ሙከራ ጥናት የሚሉት ርዕሰ ጉዳዮች ተብራርተው ቀርበዋል።

3.2 የጥናቱ ዘዴ

በስራ ቦታና በተቋማት ላይ በሚደረጉ ተግባቦታዊ መስተጋብር ዙሪያ የሚደረጉ ጥናቶች በባህሪያቸው ውስብስብነት ያላቸው ናቸው። በዚህ መሰሉ ምርምር በመጀመሪያ የንግግሩ መነሻ ምን እንደሆነ፣ ለምን እንደሆነና በምን ዙሪያ ተግባቡቱ እንደሚሸከረከር ለማየት የሚደረጉ ጥያቄዎች ይነሳሉ፤ ይጠየቃሉም። በዚህም ሂደት መረጃ መሰብሰብና ማጠናቀር ሳይሆን ቀዳሚው የንግግሩን እንዴትነት ቀድሞ ለማወቅና ለመረዳት የሚደረግ ሂደት ነው (ሲልቨርማን፣ 1997)። ይህም ሂደት በስራ ቦታ አካባቢ ስለሚደረጉ ንግግሮች ፍንጭ ይሰጣል። የሚሰበሰበውንም መረጃ ምን አይነት መሆን እንዳለበትና እንዴት መሆን እንዳለበት ይጠቁማል። በተጨማሪም ግለሰብም ሆነ ቡድን በቋሚነት የሚናገሯቸውን ዘዴዎችና ስልቶች ለመለየት ያስችላል። በዚህ ሂደት ዋናው ቁም ነገር ሰዎች በቋንቋ እንዴት ከማህበረሰባቸው ጋር በማህበራዊ ሕይወት ዙሪያ ተግባብተው መኖር እንደሚችሉና በተናጠልም የሚደረግ የግንኙነት አውድ ምን እንደሚመስል ይመለከታል።

ቀደም ባሉት ምዕራፎች የተገለጹትን የጥናቱ ዋና ዋና አላማዎች ለመመርመር ጥናቱ ኢትኖግራፊያዊ (ተሳትፏዊ) የመረጃ አሰባሰብ ስልትን የተጠቀመ ሲሆን የምርምር ዘዴ ምርጫው ደግሞ ንጥል ጥናት (Case study) ነው። ይህ ዘዴ ተመራጭ የሆነበት

ምክንያት አንድ የተወሰነን ነገር በጥልቀት ለመመርመርና ለመፈተሽ የሚያስችል ከመሆኑም በላይ በኢትኖግራፊያዊና በቡድን ተኮር ቃለመጠይቅ (ቡተቃ) የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አማካኝነት ተደራራቢና ሰፊ መረጃን ስለሚያስገኝ ነው (ሮቢንሰን1997)፡፡ ምሁሩ አክለው እንደገለጹት ንጥል ጥናት አንድ ተቋም ብሎም የስራ ቦታ ሁኔታን፣ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን፣ ተቋማዊ ባህሎችንና የተቋሙን የለውጥ ሂደት ለማየትና ለማጥናት ያስችላል፡፡

ዘዴው አስፈላጊ የሆነ መረጃን ለመሰብሰብና ተገቢ ጽንሰ ሀሳቦችን ከማስገኘቱ ባሻገር በክትትል መረጃን ተዓማኒ ከማድረግ አንፃር ተመራጭ ነው (ፓቶን፣ 1990)፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አንድና ቋሚ የሆነ ብቸኛ መንገድ የማይከተልና የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችንና ቴክኒኮችን የመጠቀም ባህሪ ስላለው አስተማማኝና ተቀባይነት ያለው ውጤት ላይ ለመድረስ የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡ በተለይም ይህ ዘዴ በስራ ቦታ ላይ ለሚደረግ ጥናት አመቺ ዘዴ ከመሆኑም በላይ በአንድ አካባቢ ያለን ክስተት ምን እየተደረገ ነው የሚለውን በጥልቀት መርምሮ ለማጥናት አመቺ ነው፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ዓላማ በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ስርዓተ ፆታዊ የተግባቦት ስልት ምን እንደሚመስል የሚፈትሽ በመሆኑና ንጥል ጥናት ለዚህ ጥናት መረጃዎችን በተለያዩ ዘዴዎችና ምንጮች በመሰብሰብና በጥልቀት በመመርመር አስተማማኝና ተቀባይነት ያለው ውጤት ላይ ለመድረስ ተግባር ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

ንጥል ጥናት ተገቢ የሆነ የጥናት ስራ ለማከናወን ስንፈልግ በገላጭ፣ በትንተናና በግምገማ ዘዴዎች ለማከናወን መረጃን ከተለያየ ሁኔታ አንፃር የተለያዩ ጭብጦችን ለማየትና መረጃዎቹን በተለያየ መንገድ ሰብስቦ የተሻለውን ለመውሰድም በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ዙሪያ ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታቸው ላይ እንዴት ተግባቦትን እንደሚፈፅሙ ለማሳየት መረጃውን በዚሁ የጥናት ዘዴ መሰብሰቡ ጠቃሚ በመሆኑ ነው፡፡ ምክንያቱም ወደጥናቱ ጭብጥ በትክክል ለመግባት ከማስቻሉም በላይ በጥናቱ ዙሪያ የአጥኝዋን ግንዛቤ እንዲሰፋ ያደርጋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ይህ ዘዴ መረጃ የሚያቀርበው በገለፃ በመሆኑ በአይነት ላይ እንጂ በመጠን ላይ መሰረት አያደርግም፡፡ ከዚህም አልፎ በክትትል ለሚደረግ ጥናት መረጃን በተለያዩ ዘዴዎችና በተገቢው ሁኔታ ለመሰብሰብ ይጠቅማል (ዲዩፍ፣ 2008)፡፡ ይህም

ስለሆነና የተግባቦት ትንተና ጥናት አስቸጋሪና ውስብስብ በመሆኑ በዚህ ጥናት አስተማማኝና ተቀባይነት ያለው ውጤት ላይ ለመድረስ ይቻል ዘንድ መረጃ ለመሰብሰብ የተለያዩ ዘዴዎችን እነዚህም ኢትኖግራፊዊ (ተሳትፏዊ ምልከታ)፣ ቡድን ተኮር ቃለመጠይቅ (ቡተቃ) እና ሰነድን፣ በመረጃ ምንጭነት መደበኛና ኢመደበኛ ውይይቶችን በጥምረት ተጠቅሟል።

3.3 የጥናቱ ተሳታፊዎች አመራረጥ ዘዴ

ባግባቡ የተያዘና የተሰበሰበ መረጃ የጥሩ ጥናት መገለጫ ነው። መረጃ መሆን ያለበት ጥሩ ወኪል ነው። ስለሆነም ወካይ መረጃ ሰብስቦ የመረጃ ውስንነት እንዳይኖር መጣር አለበት። ተጠኝ ማለት በዚህ አንደምታ በጥናቱ ውስጥ ያለውን ምክንያታዊ ጉዳይ ሁሉ በመግለጽ በኩል ሀይል ያለውና የያዘ ተደርጎ ይወሰዳል (ስሚዝ፣1975)።

በዚህም መሰረት ለጥናቱ የተመረጠው የስራ ቦታ ዩኒቨርሲቲ ሲሆን አመራረጡም በአመቺ ናሙና ዘዴ በመጠቀም ነው (ባይለይ፣1987፤ ዶርኔይ፣2007)። ምክንያቱም በአንድ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የተለያዩ ፋኩሊቲዎች፣ ኮሌጆችና ተቋሞች ስለሚገኙ በእነዚህ ውስጥ በአይነትም ሆነ በመጠን ተገቢና በቂ ተጠኝዎች ከመገኘታቸውም ባሻገር ከጥናቱ ዓላማ አኳያ ተቋማዊ አደረጃጀታቸው ለጥናቱ አተገባበርም ሆነ የታየውን ለመተንተን ምቹ ይሆናሉ ተብሎ ስለታሰበ ነው። እንዲሁም በከፍተኛ ተቋማት በአብዛኛው በሁለቱም ፆታ በትምህርት ደረጃቸው ተመሳሳይና ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ያላቸው መምህራን ይገኛሉ ተብሎ ስለሚታመን ነው። በእርግጥ ሴቶችም ሆነ ወንዶች የትምህርት ደረጃቸው ተቀራራቢ ስለሆነ ብቻ አንድ አይነት ባህርይ ይላበሳሉ ማለት አስቸጋሪ ነው። እንደባህል፣ እድሜ፣ የስራ ልምድ፣ ግላዊነት፣ የመሳሰሉት ሁሉ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ ስለሚችሉ ትኩረት ማድረግ አስፈላጊ ነው።

ለጥናቱ የተመረጠው ዩኒቨርሲቲ በአገራችን ከሚገኙ ሰላሳ ሶስት የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች መካከል አንዱ ብቻ ነው። ይህም የጥናቱ ትኩረት በተግባቦታዊ መስተጋብር ላይ መሆኑና የጥናቱ አይነትም የሂሳዊ ዲስኩር ትንተና እንደመሆኑ መጠን ትንተናው ከቋንቋ አጠቃቀም፣ ከተግባቦታዊ ልማድ፣ ከተቋማዊና ማህበራዊ ባህል አንፃር

የሚያተኩር በመሆኑ በተቋማት የአሰራር ባህል፣ በሰራተኛው ብዛትና ባህል፣ በመሳሰሉት ምክንያት የሚከሰተውን ልዩነት ለመቆጣጠር ሲባል ነው። በዚህም አንድ ተቋማዊ ባህልን ብቻ በመውሰድ ጉዳዩን በጥልቀት በመመርመር ሰፋ ያለ መረጃ በመውሰድ የጥናቱን አስተማማኝነት ከፍ በማድረግ ተቀባይነት ያለው ውጤት ላይ ለመድረስ ታስቦ ነው። በዚህም መሰረት ለጥናቱ የተመረጠው የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ሲሆን፣ የተመረጠበት ዋና ምክንያት አጥኝዋ የዚህ ዩኒቨርስቲ አባል በመሆኗ በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ ለመሳተፍ የእንግድነት ባህርይ ስለማይኖርና በዚህም ተጠኝዎቹ እውነተኛውን ባህሪያቸውን የመግለፅ ሁኔታ እንዲኖር ስለሚያግዝ ነው። ከዚህም ሌላ ጥናቱ የተጠኝዎችን ከፍተኛ ትብብር የሚጠይቅ በመሆኑ ተጠኝዎቹ በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ በሚያደርጉት ተግባቦታዊ መስተጋብር ላይ አጥኝዋ ተሳታፊ እንድትሆንና መረጃ እንድትሰበስብ ተባባሪ ሊሆኑ ይችላሉ ተብሎ ስለታሰበ ነው።

ለጥናቱ በተመረጠው ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ (ፔዳ)፣ ኢንጅነሪንግ ግቢ (ፖሊ)፣ ዘንዘልማ ግቢ (አግሪካልቸር)፣ ይባብ ግቢ (ህግና መሬት አስተዳደር)፣ አባይ ግቢ (ቢዝነስና ኢኮኖሚክ) የተባሉ አምስት ግቢዎች ያሉት ሲሆን በእነዚህም ውስጥ 4 ኮሌጆች፣ 3 ፋካሊቲዎች፣ 1 ትምህርት ቤት፣ 3 ተቋሞችና 2 አካዳሚዎች ይገኛሉ። በዚህም መሰረት ከዩኒቨርሲቲው የሰው ሀብት አስተዳደር በተገኘው መረጃ መሰረት ከአምስቱ ግቢ መካከል ሴትና ወንድ መምህራን በተመጣጣኝ ቁጥርና በተቀራራቢ የትምህርት ደረጃ የሚገኝበት ዋናውን ግቢ (ፔዳ) ተመርጧል። በዚህ ግቢ ሁለት ኮሌጆች፣ ሶስት ፋካሊቲዎችና ሁለት አካዳሚዎች ያሉ ሲሆን፣ ከእነዚህ መካከል ደግሞ የሴትና የወንድ መምህራን ጥምርታ ከቁጥርና ከትምህርት ደረጃ አንፃር በተሻለ መጠን የሚገኙባቸውን ሶስት ፋካሊቲዎች በምክንያታዊ የናሙና አመራረጥ ስልት ተወስዷል (ዶርኔይ፣ 2007)። ሆኖም ግን ለጥናቱ በተመረጡት ፋካሊቲዎች በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ የሚገኙ ሴቶች በቁጥር ከወንዶች ተመጣጣኝ ሆነው አልተገኙም። በመሆኑም በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ የተገኙት ተጠኝዎችን እንዳለ የተወሰዱ ሲሆን፣ በዚህም የአናሳ ተጠኝ ናሙና አወሳሰድ ዘዴ ተግባራዊ ሆኗል። እንደሚታወቀው ሁሉ በከፍተኛ የስልጣን እርከኖችና የስራ መስኮች ውስጥ የሚታየው የሴቶች ቁጥር አንሶ የወንዶች ቁጥር በርካታ ነው። ስለሆነም ይህ የአናሳ ናሙና ተጠኝ ናሙና ዘዴ የተገኙትን ተጠኝዎች (ሴቶች) በሙሉ በመውሰድ እንዲህ ያለውን ችግር በማስተናገዱ ረገድ ናሙና ጠቀሜታው የጎላ ነው (ፓቶን፣ 1990፤ ሮቢንሰን፣1997)።

በአጠቃላይ በዋናው ግቢ ከሚያዝያ 2004 እስከ የካቲት 2005 ዓ.ም ድረስ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ከተደረጉ አጠቃላይ ስብሰባዎችና በሶስት ፋካሊቲዎች ከተደረጉ 18 መደበኛና 5 ኢመደበኛ ስብሰባዎች መረጃው ተሰብስቧል። አስራ አራቱ በተሳትፏዊ ምልከታ ሲሰበሰቡ፣ ዘጠኙ ደግሞ በዩኒቨርሲቲው መረጃ ክፍል በድምፅና በድምፅወምስል ተቀርፀው ከተቀመጡት የተወሰዱ ናቸው። እነዚህ መረጃዎች በደንብ ከተፈተሹ በኋላ ሁለቱም ፆታዎች በተሻለ ሁኔታ የተገኙባቸውንና ሀሳብን በመግለጽ ተሳትፎ ያደረጉበትን አውድ፣ እንዲሁም በድስኩራዊ አፍልቆቱ ሰፊና የተለያዩ ተግባቦታዊ ይዘቶችን ያካተቱ ድስኩራዊ አሃዶች ከሁሉም ፋካሊቲዎችና በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ከተካሄዱ መደበኛ የውይይት አውድ አንድ አንድ ኢመደበኛ ከሆነው አውድ ደግሞ በድስኩራዊ አፍልቆታቸው ሰፊና ወጥ የሆነ ፍሰት ያላቸውን ከሁለት ፋካሊቲዎች አንድ አንድ በድምሩ 4 መደበኛ እና 2 ኢመደበኛ ውይይቶች በመምረጥ ሲወሰዱ፣ በአጠቃላይ ስድስት የተለያዩ ድስኩራዊ አሃዶች ለዚህ ጥናት በመረጃነት ተወስደው ተተነትነዋል።

ሌላው በስራ ላይ ያሉ የዩኒቨርሲቲው መተዳደሪ ደንብ፣ የስራ አፈፃፀም መገምገሚያ ቅፆች፣ ሃላፊነትን ለመስጠት የሚገለግል የመወዳደሪያ መስፈርት ምንም ሳይቀነሱ እንዳሉ ለጥናቱ በመረጃ ምንጭነት ተወስደዋል።

3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

3.4.1 ተሳትፏዊ ምልከታ

የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ በከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚገኙ የሴትና የወንድ መምህራን ተግባቦታዊ ስልት ምን እንደሚመስል ጥናት ማድረግ ነው። ስለዚህ ጥናቱ በዋነኛነት ለመረጃ ስብሰባ የተጠቀመው ዘዴ ምልከታ ሲሆን አጥኝዋ በዩኒቨርሲቲው በሚከናወኑ ተግባራትና ውይይቶች ላይ ተሳታፊ በመሆን የጥናቱ መረጃ ተሰብስቧል። ስለሆነም በዚህ ጥናት በዋናነት የአይነታዊ ምርምር ዘዴ የሆነው ተሳትፏዊ ምልከታ ተግባራዊ ሆኗል። ተሳትፏዊ ምልከታ የምንለው በአብዛኛው የሚከናወነው አጥኚው በጥናቱ ቦታ ከተጠኝዎቹ ጋር ረዘም ላለ ጊዜ አብሮ በመቆየት

ሂደቱን ከመጀመሪያ እሰከ መጨረሻ በመከታተልና ማስታወሻ በመያዝ አጠቃላይ የተጠኝዎቹን ክንዋኔና ባሕርይ ለመገምገም የሚያስችል የምልከታ ስልት ነው (ዶርኔይ፣ 2007፤ ሪቻርድ እና ኑናን፣ 1991፤ ዋላስ፣ 1991)::

በተጨማሪም እንደ ሜሎይ እና ጎርደን (2003) አገላለጽ የማህበረሰባዊ ጥናት በስነልሳን ዙሪያ ሲካሄድ አሳታፊ ምልከታ ማካሄዱ በጣም አስፈላጊና ተመራጭ ነው። የዚህ ጥቅሙም የሚሰበሰበው መረጃ የጠራና ሰፊ ከመሆኑም በላይ ተዛማጅነት ያለው መረጃ መሰብሰብ ማስቻሉ ነው። የአሳታፊ ምልከታ ዋናው አላማ በማህበራዊ ጥናት ዘርፍ ውስጥ ዋና የሆነውን ተለምዷዊ ባህል ማየትና መዳሰስ ማስቻሉ ነው። ስለሆነም ቢዚህ ጥናት ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ተግባራዊ የሆነው መደበኛና ኢመደበኛ በሆኑ ስብሰባዎች ላይ ነው። ይህም በተለያዩ የውይይት አውዶች ተዛማጅነት ያላቸው መረጃዎችን ለማግኘት አስችሏል።

ሆልመስ እና ስቱብ (2003) ስብሰባን እንደመስሪያ ቤት ስራ ይመለከቱታል። ይህም ከአስተዳደር ስራ ጋር ተያያዥነት ያለው በመሆኑ ነው። ቦርደን (1994) ስብሰባን የአስተዳደር የተግባቦት ስልት ነው ይሉታል። ስለሆነም ተመራማሪዎች ይህን በስነልሳን ጥናት ውስጥ እንደመረጃ ሊወስዱት እንደሚገባ ያስረዳሉ። ሙምባይ (1988) በበኩላቸው ተመሳሳይ እሳቤ ያላቸው ሲሆን፣ ስብሰባ የአንድ ተቋም የሀይል መግለጫ በመሆኑ ጠቃሚ እንደሆነ ይገልፃሉ። ይህም በተለይ ማን በምን ስልጣን ላይ እንዳለ በማሳየት ረገድ ጠቃሚ ነው። እንደሆልመስ እና ሌሎች (1999) እንደሚሉት ደግሞ ስብሰባ የስራ ሃላፊዎች ማንነታቸውንና የስልጣናቸውን ደረጃ የሚያሳዩበት ስልትም ነው። ሌላው የስብሰባ ጥቅም በስብሰባ ወቅት መረጃን በትክክል ለመከታተልና ለመመዝገብ በማስቻል ረገድ ጠቀሜታው ላቅ ያለ ነው። ሆልመስ እና ስቱብ (2003) እይታ ስብሰባን ባግባቡ ማዋቀር በተለይም ለማህበራዊ ጥናትና ምርምር ተገቢውን መረጃ ለማግኘት ጠቃሚ መሆኑን ይገልፃሉ። ይኸውም በስብሰባ ወቅት የሰዎችን ማንነት፣ብቃት፣ የተጋባዥ እንግዳ ማንነት መግለጫ፣ ማን ከማን እንደሆነና እንደቆመ መለያ ነው።

በዚህም መሰረት ይህ ጥናት የአሳታፊ ምልከታ ዘዴን መረጃ ለመሰብሰብ በዋናነት የተጠቀመ ሲሆን አጥኚዋ በተቋሙ ለአንድ ዓመት በመቆየት በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በተደረጉ አጠቃላይ ስብሰባዎች፣ እንዲሁም በፋካሊቲና በት/ክፍል ደረጃ በተደረጉ ውይይቶች ላይ

በመሳተፍና ሂደቱን ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ በመከታተል መረጃውን ለመሰብሰብ ችላለች፡፡ ጥናቱ በዲስኩር ትንተና ላይ ከማትኮሩ አንፃር ለትንተና የሚያውለው ዋነኛ መረጃ ድስኩራዊ አሃድ በመሆኑ ምልከታው ሙሉ በሙሉ የተካሄደው በመቅረፀ ድምፅ አማካኝነት ሲሆን፣ አልፎ አልፎ በድምፅ ሊቀረፁ የማይችሉ እንቅስቃሴዎችን ለመያዝ ደግሞ በደጋፊነት የመስክ ማስታወሻ ተግባር ላይ ውሏል፡፡ ይህም በውይይቱ ወቅት የማይደመጡ ግን ደግሞ የሚታዩ ሁኔታዎችንና ስሜቶችን በማስታወሻ በመመዝገብ በመቅረፀ ድምፅ የተገኘውን መረጃ አስተማማኝነት ከፍ ለማድረግ በደጋፊነት ተተግብሯል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ቤስት (1993) እንደገለጹት ተጠኝዎች ጥናቱ በምን ርዕሰ ጉዳይ ላይ እንደሚካሄድ ከተረዱ ከተለመደው ባህሪያቸው የተለየ ባህርይ ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡ ይህንንም ለማስወገድ ጥናቱ ‹‹በዲስኩር ትንተና›› ላይ ያተኮረ ጥናት እንደሆነና ይህም በመቅረፀ ድምፅ በአጥኝዋ እንደሚቀረፅ በተገለፀላቸው መሰረት ሁሉም ተስማምተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአጥኝዋና በተጠኝዎቹ መካከል የእንግድነት ስሜት ባለመኖሩና በውይይቱም አጥኝዋ በአብዛኛው እኩል ተሳታፊ በመሆን ተጠኝዎቹ የተለመደውን ባህሪ እንዲያሳዩ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

ሌላው በዩኒቨርሲቲው የመረጃ ክምችት ክፍል በድምፅወምስል ተቀርፀው ከተቀመጡ መደበኛና ኢመደበኛ ውይይቶች መካከል ሴቶችና ወንዶች የተሳተፉባቸው ስብሰባዎች አንድ ከመደበኛ፣ አንድ ከኢመደበኛ አውድ ተወስደው ወደፅሁፍ ተገልብጦ በጥናቱ ተካተዋል፡፡ ይህም በተሳትፏዊ ምልከታ በመቅረፀ ድምፅ በሚገኘው መረጃ ሊፈጠር የሚችለውን ያልተለመደ ባህርይ ለመቀነስ ከማገልገሉም በላይ በመደበኛም ሆነ በኢመደበኛ ውይይቶች ላይ ሁለቱም ፆታዎች የሚገኙበትን አውድ የያዘ መረጃ የማግኘት እድል ሰፊ እንዲሆን አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

በአጠቃላይ በአሳታፊ ምልከታ የተሰበሰበው መረጃ የተገኘው በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ከተደረጉ አጠቃላይ ስብሰባዎች፣ በሶስት ፋካሊቲዎች በተደረጉ የአካዳሚክ ኮሚሽን መደበኛ ስብሰባና በትምህርት ክፍሎች ደረጃ በተደረጉ አጠቃላይ ስብሰባዎች ላይ ነው፡፡ በአጠቃላይ የጥናቱ የመረጃ ምንጮችን በተመለከተ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

የጥናቱ መረጃ በሶስት ፋካሊቲዎችና በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ከተደረጉ ውይይቶችና አውደጥናቶች ተሰብስቧል። ውይይቶቹ መደበኛና ኢመደበኛ ይዘት ያላቸው ሲሆን፣ መደበኛ የተባለው የውይይቱ ጊዜና ቦታ ቀድሞ ታቅዶና ታውቆ፣ ሰብሳቢ፣ ተሰብሳቢ፣ የውይይት አጀንዳና ቃለጉባዔ የተሰኙትን ያሟላና ሂደቱም በቅደም ተከተል የሚተገበር ነው። በዚህ ጥናት በመደበኛነት የተወሰዱት በዩኒቨርሲቲና በፋካሊቲ ደረጃ የተደረጉ ቀደም ብሎ የተገለጹትን አለባውያን የሟሉ ውይይቶች ናቸው። በሌላ በኩል ኢመደበኛ ውይይት የተባለው ጊዜና ቦታው ቀድሞ ሊታቀድም ላይታቀድም የሚችል፣ የውይይት መሪ ሊኖረውም ላይኖረውም የሚችል፣ በስራ ሂደት እንዲሁም በድንገት ሊፈፀም የሚችል ሲሆን፣ በቃለጉባዔ ያልተደገፈና በአብዛኛው የመደበኛ ውይይት ቅደም ተከተልን የማይጠብቅ ሂደት የሚታይበት ነው። ከዚህ አንፃር በዚህ ጥናት ሴቶችና ወንዶች የሚገኙበት በስራ ሂደትና በድንገት የሚካሄዱ ኢመደበኛ ውይይቶችን ለማግኘት አስቸጋሪ ሆኖ በመገኘቱ መረጃው የተወሰደው በፋካሊቲ ደረጃ ከተደረጉ አውደጥናትንና ስልጠናን ተከትለው በተዘጋጁ የምሳና የእራት ግብዣ ላይ የፈለቁ ድስኩራዊ አሃዶች ናቸው። እነዚህ ግብዣዎች በሂደት ወይም በድንገት የተፈጠሩ ሳይሆን ፕሮግራም ተይዞላቸው የተካሄዱ በመሆናቸው ሁለቱን ዓይነቶች በአንድ ላይ ለማግኘት አስችሏል።

በዚህም መሰረት 18 መደበኛና 5 ኢመደበኛ ውይይቶች በመረጃ ምንጭነት የተወሰዱ ሲሆን፣ አስራ አራቱ በተሳትፏዊ ምልከታ ሲሰበሰቡ፣ ዘጠኙ ደግሞ በዩኒቨርሲቲው መረጃ ክፍል በድምፅና በድምፅወምስል ተቀርፀው ከተቀመጡት የተወሰዱ ናቸው። በአጠቃላይ 23 መደበኛና ኢመደበኛ ውይይቶች በመረጃ ምንጭነት ሲያገለግሉ፣ እነዚህን መረጃዎች ደጋግሞ በመፈተሽ ሁለቱም ዓይነቶች በተሻለ ሁኔታ የተገኙባቸውንና ሀሳብን በመግለጽ ተሳትፎ ያደረጉበትን አውድ፣ እንዲሁም በድስኩራዊ አፍልቆቱ ሰፊና የተለያዩ ተግባቦታዊ ይዘቶችን ያካተቱ ድስኩራዊ አሃዶች ከሁሉም ፋካሊቲዎችና አውድ አንድ አንድ በመምረጥ ተወስደዋል። በአጠቃላይ ከመደበኛ ውይይት በአሳታፊ ምልከታ ከተሰበሰቡት 3፣ ከዩኒቨርሲቲው መረጃ ክፍል ከተሰበሰቡት 1 በድምሩ 4 መደበኛ ውይይቶች ተወስደው ተተንትነዋል። ከኢመደበኛ ውይይት ደግሞ በአሳታፊ ምልከታ ከተወሰዱት 1፣ ከዩኒቨርሲቲው መረጃ ክፍል ከተሰበሰቡት 1 በድምሩ 2 ኢመደበኛ ውይይቶች ተወስደው ተተንትነዋል (ለዝርዝሩ አባሪ2-7ይመልከቱ)።

3.4.2 የመስክ ማስታወሻ

የመስክ ማስታወሻ ማለት የጽሁፍ ማስታወሻ መያዝ ማለት ሲሆን ይህም በጉዞ ላይ የነበረን አጠቃላይ ክስተት በሰነድ በመመዝገብ በመረጃነት ለጥናቱ መያዝ ማለት ነው። ሳረንጂ እና ሮበርት (1999) እንደሚሉት በመስክ ከተያዘ ማስታወሻ ይልቅ በሪከርደር የተመዘገበ ድምፅ በጣም ጠቃሚና የተሻለ ነው። ስለሆነም ምልከታው ከመቅረፀ ድምፅ በተጨማሪ በውይይት ላይ የሚታዩ ሁነቶችንና ስሜቶችን ለመመዝገብ የመስክ ማስታወሻ ተጠቅሟል። በዚህ ጥናት በማስታወሻ የሚመዘገበውም ሆነ በድምፅ የሚቀረፀው መረጃ በተመሳሳይ ሁነት ላይ ተግባራዊ ስለሚሆኑ ተደጋጋፊነት ያላቸው ከመሆኑም በላይ የመረጃውን ምሉዕነት ከፍ ያደርጉታል። በአጠቃላይ በመረጃነት የተያዘ አንድ መረጃ በማንኛውም ጊዜ ሲፈለግ አጠቃላይ የሆነ የታየውን ስዕል በመስጠት ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ስላለው በመቅረፀ ድምፅ የተያዘውን መረጃ ምሉዕ ሊያደርጉ የሚችሉ ክስተቶችን በመመዝገብ ተግባራዊ ሆኗል።

3.4.3 ሰነድ

በአንድ የስራ ተቋም ውስጥ ያታዊ ሁኔታን ሊገልፅ የሚችል ማንኛውንም መረጃ መሰብሰብ ተገቢ እንደሆነ ይታመናል። ጥናቱ የሂሳዊ ዲስኩር ትንተና እንደመሆኑ ሶስቱን ማለትም ድስኩራዊ አሃድ፣ ድስኩራዊ ልማድ እና ማህበረ-ባህላዊ ልማድ የትንተና ደረጃዎች የሚከተል ነው። በዚህም መሰረት በሶስተኛው የዲስኩር ትንተና ማዕቀፍ ውስጥ ድስኩሩ የፈለቀበት ሁኔታዊ፣ ተቋማዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ይታያሉ። የተቋሙን ስራ በተመለከተ በሚደረጉ ተግባቦቶች የሚፈልቀው ዲስኩር በተቋሙ ዙሪያ ያነጣጠረ ስለሚሆንና ትንተናውም ከተቋሙ ባህል አንፃር መታየት ስለሚገባው በተቋሙ የሚገኙና የተቋሙን የአሰራር ባህል የሚያሳዩ ሰነዶችን መፈተሽ ተገቢ ነው (ፌርክላፍ፣2006፤ ቫንዲጅክ፣1999)። በመሆኑም የዩኒቨርስቲውን የአሰራር ባህል የሚያመለክቱና ከመምህራን ጋር ብቻ ግንኙነት ያላቸውን መተዳደሪያ ደንብ፣ ልዩ ልዩ መመሪያዎችን በመውሰድ በመረጃነት እንዲያገለግሉ ተደርጓል (አባሪ 11፣12፣13፣14 መልከቱ)። ይህም በተለይ ከስርኣተ-ያታና ከሀይል ጋር ተያያዥነት ያላቸው ደንቦችና ህጎች ካሉ በተግባቦት ሂደት

የዲስኩሩን ሁኔታና ቅደም ተከተል መወሰን አለመወሰናቸውን ለማረጋገጥ ስለሚያግዝ ነው።።

ስለሆነም በዚህ ጥናት የዩኒቨርሲቲው መተዳደሪያ ደንብ፣ የስራ አፈፃፀም መገምገሚያ ሶስት ቅፆችና ሃላፊነት ለመስጠት የሚሞላ የመወዳደሪያ ቅፆች እንዳሉ ተወስደው ከስርዓተፆታ አንፃር እንዴት እንደቀረቡ ተቋማዊ ባህልን በመፈተሽ ሂደት ተግባራዊ ሆነዋል።።

3.4.4 ቡድን ተኮር ቃለመጠይቅ (ቡተቃ)

ዶርኔይ (2006) እና ላንጊሌር እና ሆል (1998) እንደሚሉት የቡድን ተኮር ቃለመጠይቅ (ቡተቃ) የልምድ ልውውጥ ግብዓት በመሆኑ ይህን ዘዴ በአንድ ጥናት ውስጥ መጠቀሙ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያስገኛል።። ለምሳሌ ቃለመጠይቅ ስናደርግ ሴቶችና ወንዶች እኩል ራሳቸውን የመግለጽ መብት እንዳላቸው ይታመናል።። ስለሆነም በዚህ ሂደት ቡተቃ በወንድና በሴቶች መካከል ሲደረግ ሂደቱን በመታዘብና በመከታተል በሁለቱ ፆታዎች መካከል ያለውን ልዩነት ለማወቅ የሚያስችል መረጃ መሰብሰብና መተንተን ያስችላል።።

በዶርኔይ (2007) መሰረት የቡድን አመሰራረቱ ከ6-12 አባላት እንዲኖሩት የሚጠበቅ ሲሆን፣ ይህ ዘዴ ተሳታፊዎች ሰፊ የንግግር ድርሻ እንዲያገኙ ከማድረጉም በላይ በቃለምልልስ ሂደት ቃለምልልስ አድራጊዎች እንዴት ምላሽ መስጠትና ጭብጡን ማብራራት እንደሚችሉና ልምድ እንዴት እንደሚለዋወጡ ለማነፃፀር ያስችላል።። በጋራ ውይይት በሚደረግበት ሂደት የሚነሱት ማህበራዊ ጭብጦች ብዙ በመሆናቸው አመለካከታቸውንና እምነታቸውን ሲገልጹ ይስተዋላል።። ይህም የሚተገበረውና የሚገለጸው በንግግር በመሆኑ አጥኝዎችም ይህን የጋራ ንግግር በውይይት በመጠቀም መረጃ መሰብሰብ ያስችላቸዋል፤ ብሎም በቡተቃ ሂደት ወቅት አጥኝው መረጃ ሲሰበስብ ግንኙነቱ ተዋረዳዊ እንዳይሆንና በአጥኝውና በተጠኝዎቹ መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት እንዲኖር ያግዛል።። የቡተቃ የተደረገው ለአጠቃላይ ተጠኝዎቹ ሳይሆን ለጥቂት ሴቶችና ወንዶች ነው።። ይህም የተደረገው የበለጠ መረጃውን ለመፈተሽና

የተግባቦት ስልትንና ውጤቱን ለማየት ነው፡፡ በዚህ አይነት ዘዴ ከግለሰቦች የሚገኝ መረጃን ሰብስቦ ለትንተና ማዘጋጀት አስቸጋሪ መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡ በመሆኑም በቡድን ውይይት የሚደረገውን ንግግር በመቅረፀ ድምፅ ቀርፆ ምን እንደሚመስል ተንትኖ ማሳየቱ ተገቢ በመሆኑ በዚህ ጥናትም የተደረገው ቡተቃ በመቅረፀ ድምፅ ተቀርፆ ወደፅሁፍ ተገልብጧል (ላንግሌር እና ሆል፣1989) (አባሪ8፣9፣10ይመልከቱ)፡፡

የቡድን ተኮር ቃለመጠይቁ (ቡተቃ) የተካሄደው በሶስት ዙር ሲሆን፣ የውይይቱ ተሳታፊዎች ምልከታ ከተደረገባቸው ሶስት ፋካሊቲዎችና በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በተካሄዱ ስብሰባዎች ተሳታፊ ከነበሩት የተውጣጡ አስራ አንድ ሴቶችና አስራ አንድ ወንዶች በድምሩ ሃያ ሁለት ሲሆኑ፣ አሰራረጣቸው ደግሞ በመጀመሪያ በምልከታ ወቅት የታየውን መሰረት በማድረግ በሶስቱ ፋካሊቲዎች የሚገኙ መምህራንን በምልከታ በተወሰደው መረጃ መሰረት በተለያዩ ውይይቶች ላይ የንግግር ድርሻ ለነበራቸውና ምንም ድርሻ ላልነበራቸው ሴቶችና ወንዶች እኩል እድል በመስጠት በእጣ ናሙና 5ወንድ 5ሴት በድምሩ 15ወንድ 15 ሴት 30መምህራን ተመረጡ፡፡ ቀጥሎም ከ30ዎቹ መካከል 12 ሴት 12 ወንድ በድምሩ 24 መምህራን በእጣ ናሙና የተመረጡ ሲሆን፣ ይህም ለፋካሊቲዎቹ፣ ለሴቶችና ለወንዶች፣ ለተናጋሪዎችና ለማይናገሩ እኩል እድል ለመስጠት ስለሚያስችል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ብዛታቸው 24 የተደረገበት ምክንያት ስምንት አባላት ያሉት ሶስት የቡተቃ ለማድረግ ታቅዶ ነው፡፡ ሆኖም ግን ከተመረጡት መካከል በሁለተኛው ዙር በሚካሄደው ውይይት አንድ ወንድና ሴት በመቅረታቸው ቡድኑ በስድስት አባላት ተዋቅሯል፡፡ በዚህም መሰረት በአጠቃላይ በውይይቱ የተሳተፉት ሃያ ሁለት መምህራን ሲሆኑ፣ ሁለት ወንዶች በዩኒቨርሲቲው ባሉ የሃላፊነት ቦታዎች የዳይሬክተርነት ደረጃ ያላቸው፣ አንድ ሴት በባለሙያ (Expert) ደረጃ ሃላፊነት ያላት ስትሆን ሌሎቹ ሴቶችና ወንዶች ከመምህርነትና ተጓዳኝ ስራዎች በስተቀር የሃላፊነት ድርሻ የላቸውም፡፡ ውይይቶቹ የተካሄዱት የመጀመሪያው መስከረም 21/2005 ዓ.ም፣ ከቀኑ 9፡00-11፡10 ሲሆን ሁለት ሰዓት ከአስር ደቂቃ የሚሆን ጊዜ ወስዷል፡፡ ሁለተኛው ህዳር 7/2005፣ ከቀኑ 8፡00-10፡00 ሲሆን ለሁለት ሰዓት ያህል የተካሄደ ውይይት ነው፡፡ የመጨረሻው የካቲት 24/2005 ዓ.ም፣ ከጧቱ 4፡00-5፡50 ሲሆን ይህም አንድ ሰዓት ከሃምሳ ደቂቃ የወሰደ ውይይት ነው፡፡

በውይይቱ የቀረቡት የመወያያ ጥያቄዎችም በምልከታና በሰነድ ምርመራ ሊደረስባቸው በማይችሉ ጉዳዮች ማለትም በከፍተኛ ተቋም የሚገኙ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በተግባቦት ሂደት ሃሳባቸውንም ሆነ ማንነታቸውን ለመግለጽ ተፅዕኖ አድራጊ ጉዳዮች ምንድን ናቸው? በሚለው ላይ ያነጣጠረ ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪ በከፍተኛ ተቋም ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በተግባቦት ሂደት ሃሳባቸውናና ራሳቸውን እንዴት እንደሚገልጹት ለመፈተሽ በምልከታ የተሰበሰበውን መረጃም ለማመሳከር በሚያስችል መልኩ የተደራጀ ነው፡፡ የቡተቃን አስተማማኝነትና ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አማካሪዬና ሶስት ተመራማሪዎች እንዲገመግሙት ከተደረገ በኋላ የሙከራ ጥናት ተካሂዶበት አንድ ጥያቄ ድግግሞሽ ሆኖ በመገኘቱ እንዲወጣ ተደርጎ፣ የተሻሻለው ቡተቃ በዋናው ጥናት ለመረጃ መሰብሰቢያነት ውሏል (አባሪ አንድን ይመለከቷል)፡፡

3.5 የመረጃ አሰባሰብ ቅደም ተከተል

የጥናቱ መረጃዎች በሚከተሉት ቅደም ተከተል መሰረት ተሰብስበዋል፡፡

- ለንጥል(ለኬዝ) ጥናት የሚሆንና በውስጡ የተለያዩ ተቋማትን የያዘና ሰፊ የስራ ልምድ ያለውን ዩኒቨርሲቲ መምረጥ፤ በዚህም መሰረት በአገራችን ነባርና ሰፊ የስራ ልምድ ካላቸው ዩኒቨርሲቲዎች አጥኝዋ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲን በአመቺ ናሙና ዘዴ መርጣለች፡፡ ይህም የሆነበት አጥኝዋ የዚህ ዩኒቨርሲቲ አባል በመሆኗ የመረጃ ሰጭዎችን ትብብር ለማግኘት አመቺ በመሆኑ ነው፡፡
- ሴትና ወንድ መምህራን በተመጣጣኝ ወይም በተቀራራቢ መጠን ማግኘት ይቻል ዘንድ በዩኒቨርሲቲው በሚገኙ ግቢዎች ያሉትን ሁሉንም ፋካሊቲዎች፣ ኮሌጆች፣ ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶችና አካዳሚዎች ቅኝት ተደርጓል፡፡ በቅኝቱም በዩኒቨርሲቲው ከዋናው ግቢ ውጭ ያሉት ሴቶች አነስተኛ ከመሆናቸው ባሻገር በፕሮግራም ካውንስልም ሆነ በፋካሊቲ አካዳሚክ ኮሚሽን አባልነት ያላቸው ተሳታፊነት ዝቅተኛ በመሆኑ ለጥናቱ የተመረጠው ዋናው ግቢ ነው፡፡ በዚህም የሚገኙት ሁለት ኮሌጆች፣ ሶስት ፋካሊቲዎችና ሁለት አካዳሚዎች ሲሆኑ፣ ከእነዚህም ውስጥ በሶስቱ ፋካሊቲዎች የሴቶች ቁጥር ተመጣጣኝ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በተደረጉ አጠቃላይ ስብሰባዎችና አውደ

ጥናቶች ላይ ደግሞ ሁሉም ፋካሊቲዎች የተካተቱ ሲሆን የሴቶቹም ቁጥር በተሻለ መጠን ተገኝቷል።

- የጥናቱ ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ በመቅረፀድምፅ በተደገፈ አሳታፊ ምልከታ ሲሆን፣ በቅድመ ሙከራ ጥናት ተፈትሾና ተሻሽሎ በዋናው ጥናት ተግባር ላይ ውሏል። በዚህ መሰረት ለትንተናው የተወሰደውን አሃድ በተመለከተ በአጥኝዋ በፋካሊቲው በሚደረጉ የተለያዩ መደበኛና ኢመደበኛ ውይይቶች ላይ ለአንድ አመት ያህል በመሳተፍ በመቅረፀ ድምፅና በመስክ ማስታወሻ የተደገፈ ምልከታ ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪ የመረጃውን አስተማማኝነት ከፍ ለማድረግ ከዩኒቨርሲቲው መረጃ ክፍል በድምፅ ወምስል ተቀርፀው የተሰነዱ መረጃዎችም ተወስደዋል። ከተሰበሰበው መረጃ ለጥናቱ የተወሰዱት አሃዶች ከሁለቱም ፆታዎች ተመጣጣኝ ቁጥር የተገኙበትንና በአሃዳዊ አፍልቆቱም ሰፊና ወካይ የሆኑት ተመርጠዋል። ስለሆነም የመረጃው ስፋት ስንልሳናዊም ሆነ ተግባቦታዊ ይዘቶችን በአንድ ላይ አጭቆ የያዘ ነው።

- በመቅረፀ ድምፅ ተመዝግቦ የተያዘው አሃዳዊ መረጃ ወደፅሁፍ እንዳለ በመገልበጥ መረጃው ኮድ የተሰጠውና የተጠኝዎቹ ስም በብዕር ስም የተተካ ሲሆን፣ የፋካሊቲውና የትምህርት ክፍሎቹ መጠሪያ ኮድ ተሰጧቸዋል። በመጨረሻም መረጃውን እንዳለ በመውሰድ የሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ደረጃዎችን በመከተል ተተንትኖ ቀርቧል።

- የጥናቱን ዓላማ መሰረት በማድረግ ለቡተቃ የሚሆነው ቃለመጠይቅ ተዘጋጅቷል። የተዘጋጀው ቃለመጠይቅ ከአማካሪየና ከሶስት የመስኩ ባለሙያዎችና ተመራማሪዎች ጋር ሰፊ ውይይት ከተደረገበት በኋላ በቅድመ ሙከራ ጥናት ተፈትሾና ተሻሽሎ በዋናው ጥናት ስራ ላይ ውሏል።

- ቡተቃ የተደረገው በሶስት ዙር ሲሆን ተሳታፊዎቹ ምልከታ ከተደረገባቸው ተጠኝዎች መካከል በመጀመሪያውና በሶስተኛው ዙር አራት ሴት አራት ወንድ፣ በሁለተኛው ዙር ደግሞ ሶስት ወንድ ሶስት ሴት የተወሰደ ሲሆን፣ አስራ አንድ

ሴት አስራ አንድ ወንድ በድምሩ ሃያ ሁለት ተጠኝዎች ተሳትፈዋል። አወሳሰዱ በፋካሊቲው ከሚገኙ አራት ትምህርት ክፍሎች ምልከታ ከተደረገባቸው ተጠኝዎች የተወሰዱ ናቸው። በዚህ መሰረት ምልከታ በተደረገባቸው ውይይቶች ላይ ሀሳብን በመግለጽ ተሳትፎ የነበራቸውና ምንም ተሳትፎ የሌላቸው በእጣ ናሙና ተወስደዋል።

- ቡተቃ በተዘጋጀው የውይይት ቃለመጠይቅ መነሻነት የተደረገ ሲሆን አልፎ አልፎ ከተናጋሪዎቹ ምላሽ በመነሳት በአጥኝዋም ሆነ በተጠኝዎች አማካይነት ቆስቋሽ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ሁሉም ውይይቶች በአብዛኛው ሁለት ሰዓት የፈጁ ሲሆን እጅግ አወያይና አሳታፊ ነበሩ። መረጃዎቹም በዋናነት በመቅረፀ ድምፅ የተመዘገበ ሲሆን ወደጽሁፍ ተገልብጠው በዚህ ጥናት ትንተና በመረጃነት ቀርበዋል።


3.6 የመረጃ ትንተና ስልት

ጥናቱ በዋናነት በሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ላይ የተመሰረተ በመሆኑ የመረጃ አተናተን ስልቱ በሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ሞዴል ላይ ያተኮረ ነው። ሞዴሉ የሚከተለው የአይነታዊ ምርምር ዘዴን ሲሆን ሁለገብ የመረጃ መሰብሰቢያዎችን ተጠቅሞ የሰበሰባቸውን አይነታዊ መረጃዎች ገለጻ→ትረካማ→ማብራሪያ የሚሉትን ደረጃዎች በመከተል ይተነትናል። በዚህም መሰረት በዚህ ጥናት የተተገበሩት አይነታዊ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አሳታፊ ምልከታ፣ ቡድን ተኮር ቃለመጠይቅ (ቡተቃ)፣ የመስክ ማስታወሻና የሰነድ ፍተሻ ሲሆኑ በአጠቃላይ መረጃዎቹ በፌርክላፍ (2006) የሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ሞዴል አማካኝነት ተተንተነዋል። በዚህም በሶስቱ መተንተኛ መሳሪያዎች (አቀራረቦች) ማለትም በድስኩራዊ አሃድ ትንተና፣ በድስኩራዊ ልማድና በሂሳዊ ዲስኩር ትንተና የተገለፀ ሲሆን እነዚህን የመተንተኛ ስልቶች መሰረት በማድረግ ቀጥሎ የቀረቡትን ስድስት የትንተና ቅደም ተከተሎችን ተከትሏል። ቅደም ተከተሎቹ ደግሞ ሶስቱን የገለፃ ደረጃዎች ማለትም ገለፃ፣ትርጎማና ማብራሪያ የተሰኙትን የትንተና አቀራረቦችን በመከተል ትንተናው ተካሂዷል።

1. በመጀመሪያ ለትንተና የሚሆኑ ወካይ የስነልሳን ይዘቶችን በመምረጥ፣
2. የተመረጠው የስነልሳን ይዘት የተነገረበትን ሁኔታ በመግለጽ
3. ተሳታፊዎቹ በንግግሩ ላይ ያላቸውን ድርሻ በመወሰን፣
4. በንግግሩ ሂደት ላይ የታየ አካላዊ እንስቃሴ ብሎም በሂደቱ ላይ የተንፀባረቁና ሊተነተኑ የሚገባቸው ነጥቦች ካሉ በመግለፅ፣ በቃላት ሊገለጹ የማይችሉትን ደግሞ በፅሁፍ ስምምነት ምልክቶች በመወክል (በጥናቱ መጀመሪያ ገፅ ላይ ቀርቧል)፡፡
5. የድስኩራዊ አሃድ፣ ድስኩራዊ ልማድና የሂሳዊ ዲስኩር ትንተናን በመጠቀም መረጃውን በቅደም ተከተል በመግለፅ በመተንተንና በመተርጎም፤
6. በመጨረሻም በተግባቦት ሂደት የተንፀባረቁ የስርዓተ ፆታ ሚና በማህበራዊ ግንባታ፣ በልዩነት፣ በበላይነትና በመዋቅራዊነት ንድፈሃሳብ መሰረት በመግለፅ ትንተናው ተካሂዷል፡፡ በአጠቃላይ ጥናቱ ቀጥሎ የቀረበውን በአሃድና በማህበራዊ አውድ መካከል ያለውን ግንኙነት ለመተንተን የሚያስችሉ የዲስኩር ትንተና ማዕቀፎችንና ደረጃዎችን የያዘ ሞዴል በመጠቀም የመረጃ ትንተና ተደርጓል፡፡

የመረጃ ትንተናው ስልት ገላጭ አይነታዊ ስልትን የተከተለ ሲሆን፣ በአጠቃላይ በትንተናው ሶስት የዲስኩር መተንተኛ መሳሪያዎች/ደረጃዎች ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ ይኸውም የመጀመሪያው ደረጃ የድስኩራዊ አሃድ ትንተና ሲሆን፣ በዚህም የሚፈተሸው በተግባቦት ሂደት በፈለቀው ድስኩራዊ አሃድ ውስጥ የሚታየው የቋንቋ አጠቃቀምን የተመለከቱ ይዘቶች ናቸው፡፡ በሁለተኛው ድስኩራዊ ልማድ የትንተና ደረጃ ድስኩራዊ አሃዱን በማፍለቅ ሂደት የሚከሰቱ እንደጣልቃ ገብነት፣ ተደርቦ መናገር፣የድርሻ አሰጣጥ፣ የመድረክ አጠቃቀም የመሳሰሉትን ልማዶች በተመለከተ የሚተነተንበት ደረጃ ነው፡፡ በመጨረሻም በተግባቦታዊ መስተጋብር ዲስኩርን በማፍለቅ ሂደት የውይይቱ አውዳዊ ሁኔታ፣ የተቋሙና የማህበረሰቡ ባህል ያላቸው ሚና የሚገለፅበት ደረጃ የማህበረ-ባህላዊ ልማድ የትንተና ደረጃ ሲሆን በአጠቃላይ በጥናቱ የተሰበሰቡት መረጃዎች እነዚህን ደረጃዎች በመከተል ተትንትነዋል፡፡

ስዕል ሶስት፡- የሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ማእቀፎችና ደረጃዎች የትንተና ሞዴል



ምንጭ፣ (ፌርክላፍ፣2006፡73)

ከቀረበው ሞዴል እንደምንረዳው ፌርክላፍ (2006) ሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ለማካሄድ የሚያስችሉ ሶስት ማዕቀፎችን አስቀምጧል። እነዚህም ድስኩራዊ አሃድ፣ ድስኩራዊ ልማድ እና ሂሳዊ ማህበረ-ባህላዊ ልማድ ሲሆኑ፣ ትንተናውም ገለፃ፣ ትርጎማና ማብራሪያ በሚሉ ደረጃዎች ላይ ይመሰረታል።

በዚህም መሰረት የመጀመሪያውን የትንተና ማዕቀፍ በመጠቀም አስር የተለያዩ አለባውያንን መሰረት በማድረግ ተተንትኗል። እነዚህም ንግግራዊ አውድ፣ ምፀት፣ አፅንኦታዊ ንግግር፣ ቅድመ ግንዛቤ፣ ድምፀት፣ ስነምግባራዊ ስልት ሲሆኑ፣ በዚህ ደረጃ ድስኩራዊ አሃዱ የሚፈተሸው ከቋንቋ አጠቃቀም አኳያ ነው።

በሁለተኛው የትንተና ማዕቀፍ ስር ደግሞ የድርሻ ክወና፣ የሀሳብ ልውውጥ፣ መድረክ፣ አለመደማመጥ፣ ጣልቃ ገብነት፣ ማስተካከያ/ተጨማሪ፣ ርዕስን መጠበቅ፣ አጀንዳን ማዋቀር ከሚሉት የድስኩራዊ ልማድ ይዘቶች አንፃር ይተነተናል። ይህም ዲስኩር አፍላቂው አሃዱን በማፍለቅ ሂደት የሚያሳየውን ተግባቦታዊ ልማድ በማየት ላይ ያነጣጠረ ነው።

በሶስተኛው የዲስኩር ትንተና ማዕቀፍ የሚታየው ማህበራዊና ባህላዊ እንቅስቃሴዎችን መሰረት በማድረግ የሃይል ግንኙነቱ ምን እንደሚመስል የሚታይበት ደረጃ ነው። ኤርያንቶ (2001) እንደሚሉት የማህበረሰባዊ ባህልና የአሀድ ግንኙነት በአግባቡ ሊገለጽ የሚችለው በዲስኩር አማካይነት ነው። ይህንም መሰረት በማድረግ ፌርክላፍ (2006) የማህበረ-ባህላዊ ልማድን ለመተንተን ሁኔታዊ፣ ተቋማዊና ማህበራዊ የተባሉ ሶስት የመተንተኛ መሰረቶችን አቅርበዋል።

ሁኔታዊ ደረጃ ስንል አሃዱ በሚመሰረትበት ወቅት መድረኩ የውይይቱ ተሳታፊዎች ድስኩራዊ አሃድ ለማፍለቅ የሚያስችላቸው ሁኔታ መኖር አለመኖሩንና በዚህም የሚያፈልቁትን አሃድ ባህርይ የሚወስን አጠቃላይ አውዳዊ ሁኔታን የሚመለከት ነው። ለምሳሌ በአኮ 003 የቀረበውን ድስኩራዊ አሃድ የፈለቀበትን ሁኔታ ስንመለከት ሁለት አይነት ሁኔታዎችን እንመለከታለን። በመጀመሪያ በኮሚሽኑ መደበኛ ስብሰባ ላይ በመገኘት በዲን የአመራረጥ ሁኔታ ኮሚሽኑን ያወያዩት የዩኒቨርሲቲው ሃላፊ ሲሆኑ፣ በዚህም አውድ ሃላፊው ሰፊ የንግግር ድርሻና ጊዜ ሲወስዱ ከኮሚሽኑ አባላት ደግሞ አንድ ሰው ተደጋጋሚ ድርሻ በመውሰድ ሲናገር፣ ሌሎቹ ያልተሳተፉበትና የመናገር ፍላጎት ያላሳዩበት አውዳዊ ሁኔታ ነበር። ሃላፊው ውይይታቸውን ጨርሰው ከወጡ በኋላ ድግሞ ስብሰባውን የመሩትው የፋካሊቲው ዲን ስትሆን፣ ተሰብሳቢው ሁሉም ተሳታፊ የሆነበት፣ የንግግር ድርሻ እጅ በማውጣት ሳይሆን ቀድሞ በተናገረ ወይም በጣልቃ ገብነት የሚወሰድበት አውዳዊ ሁኔታ ነበር። በዚህም በስብሰባው መጀመሪያ ባለው ድስኩራዊ አሃድና ቀጥሎ በፈለቀው ድስኩራዊ አሃድ መካከል የውይይቱ አውዳዊ ሁኔታ በሰብሳቢዎች የሃይል የበላይነት ልዩነት በመኖሩ ድስኩራዊ አሃዱ የፈለቀበት ሁኔታ እንዲለያይ ያደረገው ይመስላል።

ተቋማዊ ደረጃ የሚለው ደግሞ ዲስኩሩ በተቋሙ ዙሪያ ያነጣጠረ ስለሚሆን ትንተናውም ከተቋሙ ባህል አንፃር መታየት እንደሚገባው የሚያሳይ ነው። ምክንያቱም በአንድ ተቋም ውስጥ ያለው ተግባቦታዊ ሂደት በተቋሙ ወይም ከተቋሙ ውጭ ባለው ሁኔታ ተፅእኖ ላይ ሊወድቅ ይችላልና ነው። በዚህም የተቋሙ አባላት ስራቸውን በተመለከተ በሚደረጉ ውይይቶች ላይ ሃሳባቸውን ለመግለጽ በተቋሙ በፅሁፍ የተቀመጡና ስራ ላይ የዋለ ህግና መመሪያ እንዲሁም በፅሁፍ ያልተቀመጠ በተግባር የሚታይ ተቋማዊ ባህል ምን ያህል አስተዋፅዖ አለው የሚለው የሚፈተሸበት ደረጃ ነው።

ሶስተኛው ደግሞ የማህበረሰቡን ሁኔታ በስፋት የሚያሳይ ደረጃ ነው። ይህም ማለት የማህበረሰቡን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎችን ያጠቃለለና ማን እንደሚመራና ማን ክብር እንዳለው የሚወሰንበት ነው። በዚህ ደረጃ በሚደረገው ፍተሻ የማህበረሰቡ ባህል ምን ያህል በተቋሙ ውስጥ በመግባት አስተዋፅኦ እንዳደረገና የተቋሙ አባላት ስራቸውን በተመለከተ በሚደረጉ ውይይቶች ላይ ሃሳባቸውንና ራሳቸውን በመግለጽ ሂደት ያለው ሚና ምን ያህል እንደሆነ ይፈተሻል።

ሰንጠረዥ አንድ፡- የጥናቱ ዘዴ ማጠቃለያ

ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች (የጥናቱ ዓላማዎች)	የመረጃመሰብሰቢያ መሳሪያዎች		የመተንተኛ መሳሪያዎች	የመተንተኛ ሰልት ደረጃዎች
	በዋናነት	በደጋፊነት		
1. ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታ ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር በሚያደርጉት የተግባቦት ሂደት ሀሳባቸውን እንዴት ይገልፃሉ?	አሳታፊና ኢተሳትፏዊ ምልከታ	✓ ቡተቃ ✓ የመስክ ማስታወሻ	የዲስኩር ትንተና (discourse analysis)(የቋንቋ አጠቃቀም) • (ድስኩራዊ ልማድ አቀራረብ /Discursive Practice) (የአፍልቆት ሂደት እና የአረዳድ ሂደት)	ገለፃና ትርጎማ
2. ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታ ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር በሚያደርጉት የተግባቦት ሂደት ራሳቸውን እንዴት ይገልፀታል?	አሳታፊና ኢተሳትፏዊ ምልከታ	✓ ቡተቃ ✓ የመስክ ማስታወሻ ✓ የሰነድ ምርመራ	ሂሳዊ ዲስኩር ትንተና (ማህበረ-ባህላዊ ልማድ (Socio-cultural practice)	ማብራሪያ

3.7 የጥናቱ አስተማማኝነትና ትክክለኝነት

በአይነታዊ ጥናት ሂደት መረጃ ሲሰበሰብ በመረጃው ላይ የግላዊነት ስሜት እንዳይኖር መቆጣጠር ያስፈልጋል። መረጃው በዋናነት የተሰበሰበው በመቅረፀ ድምፅ ነው። ይህ መረጃም ሲተነተን መሰረት ያደረገው ማህበራዊ አውዱን ነው። ይኸውም የሚከተለው ንድፈ ሃሳብ ማህበረ ባህላዊ ልማድ በመሆኑ ነው። ስለሆነም ትንተናው ከንግግር በመነሳት የተተነተነ ሲሆን፣ ይህም ተናጋሪዎቹ እንዴት ተናገሩ፣ ምን ተናገሩ፣ ምን ለማለት ፈልገው ነው ከሚለው ሂደት በመነሳት ትንተናው ተካሂዷል። ስለሆነም የመረጃው አሰባሰብና የትንተናው አተገባበርም ከዚህ በታች የቀረቡትን ብልሃቶች በመጠቀም የጥናቱን አስተማማኝነትና ትክክለኝነት ለመጠበቅ ተሞክሯል።

- ሰፊ መረጃ መውሰድ፡- በተቋም ደረጃ ለሚደረጉ ጥናቶች የዚህ የጥናት አይነት (የመስክ ጥናት) መረጃን በስፋት ለማግኘት አስፈላጊነቱ ከፍተኛ ነው። በተለይም በስራ ቦታ አካባቢ በተለያየ ጊዜ በሚኖረው ተራክቦ የሚፈጠረው ተግባቦት ከፍተኛ በመሆኑ በስፋት የስነልሳንና የተግባቦት ሂደትን በአንድነት አከማችቶ የያዘ መረጃ ለመሰብሰብ ምቹ ነው (ጆርንሰን እና ፊሊፕስ፣2002) ። በመሆኑም በዚህ ጥናት በጥናቱ ቦታና ከተጠኝዎች ጋር ለረጅም ጊዜ (ለአንድ አመት) አብሮ በመቆየት ሰፊ መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን፣ ለትንተናው የተመረጡት አሃዳዊ መረጃዎች ረጅም ሰዓት የወሰዱ ከመሆናቸውም በላይ ስነልሳናዊና ድስኩራዊ ልማዶችን በስፋት አከማችተው የያዙ ናቸው።

- ብዝሀ የመረጃ መሰብሰቢያና ትንተና ዘዴ መጠቀም፡- እንደ(ዲንዚን፣1988 እና ይን፣2011) የብዝሀ ዘዴን እንደ ጥናት ስልት በመጠቀም መረጃ ለመሰብሰብም ሆነ ለመተንተን የተለያየ የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ ዘዴዎች ተግባር ላይ በማዋል የመረጃ መሰብሰቢያውንና መተንተኛ መሳሪውያውን አስተማማኝነትና ትክክለኛነት መጠበቅ እንደሚቻል ያብራራሉ። በመሆኑም በመረጃ መሰብሰቢያነት አሳታፊ የመረጃ መሰብሰቢያን በመከተል የተለያዩ ዘዴዎችን ለምሳሌ የስራ ቦታ ላይ ምልከታ በማድረግ፣ መረጃውን በመቅረፀ ድምፅ በመቅረጽ፣ የመስክ ማስታወሻ በመያዝ፣ ቡተቃ በማድረግ፣ ከተጠኝዎች ጋር መደበኛ ያልሆነ ግንኙነት በማድረግ፣ ከድምፅ

ቀረፃው በፊትና በኋላ ለተጠኝዎች አስፈላጊውን ማብራሪያ በመስጠትና በመቀበል፣ እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው መረጃ ክፍል በምስልወድምፅ ተሰንደው የተቀመጡ መረጃዎችን በመውሰድና ሰነዶችን በመፈተሽ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያውን ትክክለኝነትና አስተማማኝነት ለመጠበቅ ተሞክሯል፡፡

በተጨማሪም የጥናቱን ውጤት አስተማማኝና ትክክለኛ እንዲሆን በተለያየ የመረጃ መሳሪያ የተሰበሰበውን መረጃ በተለያየ የትንተና ስልት ተተንትኗል፡፡ ይኸውም በሶስቱ የሂሳዊ ዲስኩር መተንተኛ መሳሪዎች በድስኩራዊ አሃድ፣ በድስኩራዊ ልማድና በማህበረ ባህላዊ የመተንተኛ መሳሪያዎች በመጠቀም የመረጃ ገለፃ፣ትርጎማና ማብራሪያ ተደርጓል፡፡

- ከተጠኝዎች ጋር ለረጅም ጊዜ አብሮ በመቆየት፡- ሂደቱ ግንኙነትን በመከታተል የሚከናወን ነው፡፡ መረጃው ረጅም ጊዜ ተወስዶ የሚሰበሰብ ሲሆን ከተሰበሰበ በኋላ ደግሞ ጊዜ ተወስዶ ክትትል በማድረግና ከተጠኝዎች ጋር መደበኛ ያልሆኑ ግንኙነት በማድረግ ይተገበራል፡፡ ይህም ባግባቡ ለማመሳከር ይጠቅማል (ዶርኔይ፣2007፤ጉባና ሊንኮን፣1994)፡፡ በዚህም መሰረት አጥኝዋ ለአንድ አመት ጥናቱ በሚካሄድበት ዩኒቨርሲቲ በመገኘት ከተጠኝዎቹ ጋር መደበኛና መደበኛ ባልሆኑ የስራ ግንኙነቶች አብሮ በመሳተፍ መረጃው ተሰብስቧል፡፡

- ቅድመ ሙከራ ጥናት ማካሄድ፡- ቀደም ብሎ በቀረበው ክፍል እንደተመለከተው ከዋናው ጥናት ቀደም ብሎ የቅድመ ሙከራ ጥናት የተካሄደ ሲሆን አብይ ዓላማውም ለዋናው ጥናት የሚሆኑ ትክክለኛነታቸውና አስተማማኝነታቸው የተረጋገጠ የምርምር መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችንና ዕቅዶችን ማዘጋጀት ነው፡፡ በዚህ መሰረት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችና የመረጃ ምንጮች ትክክለኛነት ተፈትሾና አስፈላጊው ማስተካከያ ተደርጎ በዋናው ጥናት ስራ ላይ የዋለ ሲሆን ይህም የጥናቱን አስተማማኝነትና ትክክለናነት ለማረጋገጥ አግዟል፡፡

- መረጃውንና ትንተናውን ለተጠኝዎች በማቅረብ፡- የተሰበሰበውን መረጃና ትንተናውን በተመለከተ ለተጠኝዎቹ በማቅረብ ስለትክክለኛነቱ ማረጋገጫ ማግኘት፡፡ ይህም እንደ

ሁግስ (2003) አገላለጽ በአሳታፊ ጥናት የተሰበሰበውን መረጃና መረጃው እንዴት እንደተተነተነ ለተጠኝዎቹ በማቅረብ ውይይት ማድረግ ተጠኝዎቹ የተዛባ ወይም ያልተገለፀ ጉዳይ ካለ በማስተካከልና በመሙላት የመረጃውንና የትንተናውን ትክክለኛነት በማረጋገጥ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው። በመሆኑም ይህ ጥናት ጥናቱ ለተካሄደባቸው ፋካሊቲዎችና ትምህርት ክፍሎች በሳምንታዊ ሴሚናር፣ እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው በተደረገ አገር አቀፍ አውደ ጥናት ላይ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል።

3.8 ቅድመ ሙከራ ጥናት

ከዋናው ጥናት በፊት የተወሰኑ መረጃዎችን በናሙናነት በመውሰድ የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ መሳሪያዎቹን እንዲሁም የመረጃውን አካሄድ ለመፈተሽ ተሞክሯል። በዚህም መሰረት በአሳታፊ ምልከታ፣ በመስክ ማስታወሻ፣ በቡተቃና በሰነድ ፍተሻ አማካይነት የተሰበሰቡት መረጃዎች ተተንትነዋል።

3.8.1 ቅድመ ሙከራ ጥናት የተደረገበት ምክንያት

የቅድመ ሙከራ ጥናቱ የተደረገበት ዋና ዓላማ ለዋናው ጥናት ትክክለኛነታቸውና አስተማማኝነታቸው የተረጋገጠ የምርምር መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችንና ዕቅዶችን ለማዘጋጀት ነው። በተጨማሪም በዓይነታዊ ጥናት የቅድመ ጥናት ሙከራው ዋና ዓላማ አጥኝው ለዋናው ጥናት የሚሆኑ አካሄዶችን እንዲያርምና የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችን ጥንካሬና ድክመት ለመለየት ስለሚያስችል ነው። በሌላ አገላለጽ የጥናቱ ዕቅድ ምን እንደሚፈልግ የበለጠ ትኩረት ማድረግ ነው (ዲቪስ፣ 2002)። ይህ ማለት ደግሞ አጥኚዋ የበለጠ ትኩረት የምታደርገው በመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ይዘት ጥራትና ትክክለኛነት፣ የመሣሪያዎች አጠቃቀም ሂደት እንጂ በጥልቅ የመረጃዎች ትንተና ላይ አይደለም ማለት ነው።

በዚህ ሂደትም የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ትክክለኛነት ተፈትሾ በዋናው ጥናት ስራ ላይ የዋሉ ከመሆናቸውም በላይ አስፈላጊ የሆኑ ማሻሻያዎችን ለማከናወንም ተችሏል።

ምክንያቱም «ስህተቶች በአንድ ሰው ቀላል ምልከታ ብቻ ሊቃኑ ወይም ሊወገዱ አይችሉምና» (ዌርስማን፤ 2000፣ 171)። ስለዚህ በቅድመ ጥናት ሙከራው መነሻነት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችን ሁለንተናዊ አስተማማኝነትና ትክክለኛነት በተለያዩ ዘዴዎች በመፈተሽ አስፈላጊ የሆኑ ማስተካከያዎች ለማድረግ ጥረት ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪ የቅድመ ሙከራ ጥናት ውጤቱ የጥናቱ ዋና ግኝት በመጨረሻው ምን ዓይነት መልክ እንደሚይዝ ቅድመ ፍንጭ በመስጠትም አገልግሏል። ጥናቱ የተከናወነው የዋናው ጥናት ከተካሄድባቸው ናሙናዎች በጥቂቱ ተቀንሶ ነው። ስለዚህ የቅድመ ጥናት ሙከራው ዓላማውን መነሻ አድርጎ ተከናውኗል።

3.8.2 የቅድመ ሙከራ ጥናቱ የመረጃ አሰባሰብ ቅደም ተከተል

የቅድመ ሙከራ ጥናቱ የተካሄደው በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ በ2005 ዓ.ም ከተደረገ አንድ አጠቃላይ የዩኒቨርሲቲው መምህራን ስብሰባ እና በአንድ ፋካሊቲ ከተካሄደ መደበኛ ትምህርታዊ ውይይት ላይ ነው። በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በተካሄደው አጠቃላይ መደበኛ ስብሰባ ላይ አሳታፊ ምልከታ የተደረገ ሲሆን መረጃው የተሰበሰበው በመስክ ማስታወሻ ብቻ ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት ከተሰብሳቢው ብዛት አኳያ በመቅረፀ ድምፅ ለመቅረፅ አስቸጋሪ በመሆኑ ነው።

በፋካሊቲ ደረጃ የተካሄደው ስብሰባ መረጃው የተወሰደው በመቅረፀ ድምፅ በተደገፈ አሳታፊ ምልከታ ነው። በዚህም የውይይቱ ተሳታፊዎች 6ሴት 9ወንድ በድምሩ 15 መምህራን ናቸው። የእድሜ ሁኔታ ሲታይ ወንዶቹ ሶስቱ በ30ዎቹ፣ ሁለቱ በ40ዎቹ የእድሜ ክልል ያሉ ሲሆኑ የቀሩት አራቱ ደግሞ ከ50 ዓመት በላይ የሆኑ አንጋፋ መምህራን ናቸው። የሴቶቹን በተመለከተ አንዷ ሴት ከ40-45 አመት የእድሜ ክልል ውስጥ ስትሆን ሌሎቹ ደግሞ በ30ዎቹ የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ናቸው። የትምህርት ደረጃቸው ከአንጋፋዎቹ መካከል አንደኛው የፒኤችዲ ዲግሪ ያለው ሲሆን ሌሎቹ ሁሉም የማስተርስ ዲግሪ ያላቸው ናቸው። የስልጣን ሁኔታን በተመለከተ ደግሞ ሰብሳቢው የፋካሊቲው የፕሮግራም ማናጀር፣ አንድ ሴትና ወንድ የትምህርት ክፍል ተጠሪ፣ አንዷ ሴት በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የ... ተጠሪ ስትሆን ሌሎቹ ግን በትምህርት ፕሮግራማቸው ውስጥ በመማር ማስተማሩ ብቻ የሚሳተፉ ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ከ40 ዓመት በላይ ያሉት ሁሉም ወንዶችና አንዷ

ሴት ከአሁን በፊት በማስተማርም ሆነ በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ቦታዎች ላይ የሰሩ ከፍተኛ የስራ ልምድ ያላቸው ናቸው።

በቡተቃ አማካኝነት መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን በዩኒቨርሲቲ ደረጃና በፋካሊቲ ደረጃ በተደረገው ውይይት ከተሳተፉት መካከል በቡተቃ ላይ ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸውን እና ውይይቱ በሚካሄድበት ጊዜ ለመሳተፍ ፈቃደኛ የሆኑትን በመምረጥ ተወስደዋል። በአጠቃላይ አራት ወንድ፣ አራት ሴት በድምሩ ስምንት መምህራን ተሳትፈዋል።

በመጨረሻም የሰነድ ምርመራ የተደረገ ሲሆን በዚህም የዩኒቨርሲቲው መተዳደሪያ ደንብ ከተቋሙ ባህል አንፃር ተፈትሿል። በአጠቃላይ የተሰበሰቡት መረጃዎች በፌርክላፍ (2006) የሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ማዕቀፎችን (ድስኩራዊ አሃድ፣ ድስኩራዊ ልማድ እና ማህበራ-ባህላዊ ልምድ) መሰረት በማድረግ ትንተናው ተካሂዷል።

3.8.3 ከቅድመ ሙከራ ጥናቱ የተገኙ ትምህርቶች

የቅድመ ሙከራ ጥናቱ በመደረጉ ለዋናው ምርምር ሊጠቅሙ የሚችሉ ልምዶች ተገኝተዋል። ይኸውም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችንና የመረጃ ምንጮችን ትክክለኝነትና አስተማማኝነት ለማሳካት የሚያስችሉ ማስተካከያዎችና ልምዶች እንዲገኙ አግዟል። በዚህም ዋናው ጥናት ሲካሄድ ቀጥሎ የቀረቡት ማሻሻያዎችን ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ ከቅድመ ሙከራ ጥናቱ ልምድ ተገኝቷል።

ሀ. አሳታፊ ምልከታውን በተመለከተ፡- በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በሚደረጉ ትልልቅ ስብሰባዎች የሚደረገው ምልከታ በመቅረፀ ድምፅ ለመቅረፅ አዳጋች በመሆኑ፣ መረጃው የተወሰደው በመስክ ማስታወሻ ብቻ ነው። በመሆኑም በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በሰፊ አዳራሽ ብዙ ታዳሚ የሚገኝበት ውይይት ሲኖር ምልከታው ከመስክ ማስታወሻ በተጨማሪ በቪዲዮ ካሜራ ቢደገፍ መረጃው የበለጠ አስተማማኝ ይሆናል። በመሆኑም በዋናው ጥናት ላይ በመቅረፀ ድምፅ ከተደገፈ ምልከታ በተጨማሪ ትልልቅ ስብሰባዎች የተመለከቱ በዩኒቨርሲቲው የመረጃ ክፍል ተቀርፀው የተቀመጡትን በመውሰድ

ኢተሳትፏዊ የመረጃ መሰብሰቢያ-መሳሪያ ተግባር ላይ እንዲውል ከፍተሻው በተገኘው መረጃ መሰረት በዋናው ጥናት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

ከዚህም ሌላ አንዳንድ ተጠኝዎች በስብሰባ ላይ ያላቸው የንግግር ተሳትፎ በስብሰባው ከተሰጣቸው ድርሻ በላይ ወይም በታች ሆነው ይታያሉ፡፡ ሰዎቹ ከተሰጣቸው ድርሻ በታች ወይም በላይ ለምን እንደሆኑ በስብሰባው ላይ የሚገኘው መረጃ ብቻውን አስተማማኝ ስለማይሆን ከስብሰባው በኋላ ይህን ባህርይ የሚያሳዩትን ተጠኝዎች ቃለመጠይቅ በማድረግ በቂ መረጃ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በዋናው ጥናት ከድርሻቸው በላይ ወይም በታች ሆነው የሚታዩ ተጠኝዎች በሚኖሩበት ጊዜ ከስብሰባው በኋላ ቃለመጠይቅ በማድረግ መረጃ እንዲሰበሰብ ልምድ ተገኝቷል፡፡

ለ. ቡተቃን *በተመለከተ*፡- በቡድን ውይይቱ ላይ ማስታወሻ በሚያዝበት ጊዜ ከተሳታፊዎች ጋር የነበረው የአይን ግንኙነት ከመቋረጡ በተጨማሪ ቆስቋሽ ጥያቄዎችንም ለማቅረብ ተዕዕኖ ነበረው፡፡ ሆኖም ግን በድምፅ የተቀረፀው መረጃ ወደፅሁፍ ተገልብጦ ሲታይ በማስታወሻ የተያዘው መረጃ በዚሁ የተካተተ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም በዋናው ጥናት ላይ ሰፊ የሆነ ማስታወሻ እንዳይያዝና በምትኩ ከተሳታፊዎች ጋር የአይን ግንኙነት እንዲኖር በማድረግ ጥንቃቄ የተሞላበት ውይይት እንዲደረግ ረድቷል፡፡

ለቡድን ውይይቱ በተዘጋጀው ጥያቄ ላይ ከነበሩት ጥያቄዎች በተራ ቁጥር አራት የቀረበው ‹‹ሴቶችና ወንዶች በስብሰባ ወቅት የተለያየ ባህርይ ያሳያሉ ብላችሁ ታስባላችሁ?›› የሚለው ጥያቄ በሌሎቹ ጥያቄዎች ላይ ስለሚነሳ ድግግሞሽ ከመሆኑ በላይ የውይይቱ ተሳታፊዎችም ለዚህ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ሲታይ በተራ ቁጥር ሶስት ላይ የተጠየቁትን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥያቄ በዋናው እንዳይካተት አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

ሐ. *የመስክ ማስታወሻውን በተመለከተ*፡- በመስክ ማስታወሻ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ አማካኝነት ሰፊ መረጃዎችን ማሰባሰብ እንደሚቻል በዚህ ቅድመ ሙከራ ጥናት ግንዛቤ ተገኝቷል፡፡ ሆኖም ግን ብዙ ታዳሚ ባለበት የሚደረግ ትልልቅ ስብሰባዎች ላይ ከእይታ ውጭ የሆኑና ግን በተሳታፊው ላይ ለምን የሚል ጥያቄ የሚስከትሉ ጉዳዮች ይከሰታሉ፡፡

ለአብነት ያህል በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በተደረገ አጠቃላይ ስብሰባ በነበረ ውይይት ላይ ከአንድ አጀንዳ ወደሌላ አጀንዳ ለመሸጋገር በስብሰባው መሪ አማካይነት የመጀመሪያው አጀንዳ ውይይት እንዲያበቃና ወደሁለተኛው አጀንዳ እንዲኬድ ፍላጎት ያላችሁ፣ በመጀመሪያው አጀንዳ ላይ ውይይቱ ይቀጥል የምትሉ፣ ድምፀ ተአቅቦ የምትሉ እጃችሁን በማውጣት አሳዩ ሲባል ሁሉም ተሰብሳቢ ወደሁለተኛው አጀንዳ እንዲኬድ በማለት እጃቸውን ሲያወጡ አንዲት ሴት ድምፀ ተአቅቦ በማለት እጇን አውጥታለች። ምክንያቷን እንድትናገር ድርሻ ሲሰጣት ደግሞ በውይይቱ ላይ ያልተነሳ ያለችውን ጉዳይ በማንሳት ማብራሪያና ጥያቄ ነበር ያቀረበችው። እዚህ ላይ ይህች መምህርት ለምን መጀመሪያ አልተናገረችም? ለምን ድምፀ ተአቅቦ አለች? የሚሉ ጥያቄዎች መልስ ቢያገኙ መረጃው ሙሉ ከመሆኑም በላይ አስተማማኝም ይሆናል። የዚህን ጥያቄ መልስ ለማግኘት ደግሞ ንግግር አድራጊዋን ከስብሰባው በኋላ አግኝቶ መጠየቅ አስፈላጊ ነው። በመሆኑም በመስክ ማስታወሻው የሚሰበሰበው መረጃ አስተማማኝ እንዲሆን አሻሚና ግልፅ ያልሆኑ ጉዳዮች በሚኖሩበት ጊዜ ከስብሰባው በኋላ ተጠኝዎችን በግል በማወያየትና በመጠየቅ መረጃውን ማጠናከር አስፈላጊ መሆኑን ከቅድመ ሙከራ ጥናቱ የተገኘ ሌላው ግንዛቤ ነው። በመሆኑም በዋናው ጥናት ላይ አጠራጣሪና ግልፅ ያልሆኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ከስብሰባው በኋላ ተጠኝዎችን በግል የማወያየትና የመጠየቅ ተግባር ተከናውኗል።

መ. የሰነድ ምርመራ በተመለከተ፡- በቅድመ ሙከራ ጥናቱ የተወሰዱት የሰነድ መረጃዎች የዩኒቨርሲቲው መተዳደሪያ ደንብ ነው። ሆኖም ግን በዩኒቨርሲቲው የሚወጡ የተለያዩ ተጨማሪ ህጎችና መመሪያዎችንም መመርመሩ በተለይም ተቋማዊ ባህሉን በማሳየት በኩል አስተዋፅኦ ይኖረዋል የሚል እምነት ስላለ በዋናው ጥናት ማካተት አስፈላጊ መሆኑን ግንዛቤ አስገኝቷል። በመሆኑም በዋናው ጥናት ላይ በዩኒቨርሲቲው የሚወጡ ተጨማሪ መመሪያዎችን በተለይም ከሀላፊነት አሰጣጥና ከስራ አፈፃፀም ግምገማ ጋር የተያያዙ መመሪያዎችና መገምገሚያ መስፈርቶች ከተቋማዊ ባህል አንፃር እንዲተነተኑ ተደርጓል።

ሠ. የመረጃ ምንጮችን በተመለከተ፡- የመረጃ አሰባሰብ ሂደቱን በተመለከተ መረጃው ይሰበሰባል ተብሎ የታቀደው መደበኛና መደበኛ ባልሆነ መንገድ ነበር። ሆኖም ግን መደበኛ ባልሆነው የመምህራን ተግባቦታዊ ተራክቦ በአብዛኛው የታየው ለምሳሌ በቢሮና በሻይ ቤት አካባቢ ሁለቱ ፆታዎች በተናጠል እንጅ በጥምረት ለማግኘት አልተቻለም። ሌላው

ኢመደበኛ የሆነውን ተግባቦት ለማግኘት ነባራዊ ሁኔታው ሲታይ መምህራኑ መቼና እንዴት ሊገኙ እንደሚችሉ አስቀድሞ የሚታወቅ ነገር ስለማይኖር መረጃውን በዚህ መንገድ መሰብሰብ አስቸጋሪ መሆኑን ከቅድመ ሙከራ ጥናቱ የተገኘ ትምህርት ነው። ይህን ችግር ለመፍታት ፕሮግራም ተይዞላቸው የተካሄዱ ኢመደበኛ ውይይቶችን በተሳትፏዊ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተወሰደ ሲሆን፣ በተጨማሪም በዩኒቨርሲቲው መረጃ ክፍል በድምፅወምስል ተቀርፀው የተሰነዱ መረጃዎችን በመውሰድ የመረጃውን አስተማማኝነት ከፍ ለማድረግ ልምድ ተገኝቷል። ይህም በተሳትፏዊ ምልከታ መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት ሊፈጠር የሚችል የተጠኝዎችን የማስመሰል ባህሪ በማመሳከር ለመረጃ አስማማኝነትና ትክክለኛነት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያደርግ በተገኘው ልምድ መሰረት በዋናው ጥናት ኢተሳትፏዊ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ተግባራዊ ተደርጓል።

መረጃ ለመሰብሰብ የታቀደው በሁለት ዩኒቨርሲቲዎች ቢሆንም በቅድመ ሙከራ ጥናቱ እንደታየው ጥናቱ በአንድ ዩኒቨርሲቲ ላይ ብቻ መካሄድ እንዳለበት ያመለክታል። ምክንያቱም የሁለቱ ዩኒቨርሲቲዎች ተቋማዊ ባህል የተለያዬ ስለሚሆን ቅድመ ሙከራ ጥናቱን በአንዱ ላይ አካሂዶ ዋናውን ጥናት በሌላ ላይ ማካሄድ ምናልባትም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹንም ሆነ የመረጃውን አይነት ለመወሰን ሊያስቸግር ስለሚችል ነው። ከዚህም ሌላ በአንድ ዩኒቨርሲቲ የሚገኙ የተለያዩ ፋካሊቲዎች፣ ኮሌጆች፣ ተቋማትና ትምህርት ቤቶች በመኖራቸው ወካይ ናሙና በተመሳሳይ ተቋማዊ ባህል ውስጥ ሰፊ መረጃ ማግኘት ስለሚቻል የሚሉት ናቸው።

በአጠቃላይ በዋናው ጥናት መረጃ የተሰበሰበው መደበኛና ኢመደበኛ ውይይቶችን በተሳትፏዊና በኢተሳትፏዊ ምልከታ ዘዴ ነው። የጥናቱ የተካሄደውም በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ሲሆን የጥናቱ ርዕስ ‹‹በከፍተኛ ትምህርት ተቋም በስራ ቦታ በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ የሚታይ ስርዓተፆታዊ የተግባቦት ስልት ትንተና፡ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ መነሻነት›› በሚለው ለማስተካከል አስችሏል።

ምዕራፍ አራት፤ የመረጃ ትንተናና ግኝት ማብራሪያ

4.1 መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ የቀረበው የመረጃ ትንተና ለጥናቱ ከተመረጡት ተጠኝዎች በምልከታ፣ በቡተቃ እና በመስክ ማስታወሻ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት የተገኙ መረጃዎች ናቸው። መረጃዎቹ የጥናቱን ጥያቄ መሰረት በማድረግ በጭብጥ በጭብጥ ተደራጅተው በቅንጅት አንዱ በአንዱ እየተመሳከረ ተተንትነው ግኝታቸው የተጠቀመበትና የተብራራበት ክፍል ነው። ከምልከታና ከቡተቃ የተወሰዱት መረጃዎች ለትንተና እንዲመች በተሳታፊዎቹ ቅብብሎሽ መሰረት ቁጥር የተሰጠ ሲሆን ትንተናው የተካሄደው በሂሳዊ ዲስኩር ትንተና አማካኝነት ነው። የሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ሂደት ሶስት ደረጃዎችና የአቀራረብ ሂደቶች እንዳሉት ቀደም ባለው ክፍል ቀርቧል። ስለሆነም ለጥናቱ የተመረጡትን ድስኩራዊ አሃዶች በመጠቀም ይህኑ የትንተና ደረጃዎችና አቀራረቦች በጠበቀ ሁኔታ ትንተናው ተካሄዷል።

4.2 የመረጃ ዳራና ገለፃ

የጥናቱ መረጃ የተወሰደው በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በዋናው ግቢ ከሚያዝያ 2004 ዓ.ም እስከ የካቲት 2005 ዓ.ም ከተደረጉ አጠቃላይ የዩኒቨርሲቲው መምህራን ስብሰባዎች፣ አውደ ጥናቶችና በሶስት ፋካሊቲዎች ከተካሄዱ መደበኛ እና ኢመደበኛ ትምህርታዊ ውይይቶች ላይ ነው። ለትንተናው የተመረጡት ድስኩራዊ አሃዶች ደግሞ መደበኛ ከሆኑት ከአጠቃላይ የዩኒቨርሲቲው ስብሰባና ከሶስቱ ፋካሊቲዎች አንድ አንድ እንዲሁም በሁለት ፋካሊቲዎች የተደረጉ ሁለት ኢመደበኛ ውይይቶች በጠቅላላው ስድስት ድስኩራዊ አሃዶች ተወስደዋል። የአመራረጣቸው ምክንያት ደግሞ ሰፋ ያለ ጊዜ የወሰዱ በመሆናቸውና ከሌሎቹ ስብሰባዎችና ውይይቶች ጋር ሲነፀፀሩ ሴት ተሳታፊዎች በተሻለ ሁኔታ የተገኙባቸውና የተሳተፉባቸው በመሆኑ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ለትንተናው የሚሆኑ ስነልሳናዊና ድስኩራዊ ልማዶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን አከማችተው የያዙ ናቸው ተብለው በመታሰባቸው ነው።

ከመደበኛ ውይይቶች የተወሰዱትን በተመለከተ አንደኛው በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ለሶስት ቀን ከተካሄደ አጠቃላይ ስብሰባ የተወሰደ ሲሆን፤ በዚህ ስብሰባ የሴቶች ተሳትፎ ያልታየበት ቢሆንም በስብሰባው ማጠናቀቂያ ላይ ከተሳታፊው ሴቶችን እንዲያሳትፉ ለሰብሳቢዎቹ በደረሳቸው ማስታወሻ መሰረት ለአንዲት ሴት ድርሻ ተሰጥቷት ረጅም ንግግር አድርጋለች፡፡ ለዚህ ጥናት የዚህን ስብሰባ ሙሉ መረጃ መውሰዱ አስፈላጊ ባለመሆኑ በስብሰባው ማጠቃለያ አካባቢ ያለው የሴቷ ንግግርና ከእሷ በፊት የነበረ የሶስት ወንዶች ንግግር ያለበት መረጃ ብቻ ተቆርጦ ተወስዷል፡፡ ሌሎች ሶስቱ ከመደበኛ የአካዳሚክ ኮሚሽን ስብሰባዎች ላይ የተወሰዱ ሲሆን ስብሰባዎቹ ሰፊ ጊዜ የወሰዱና የተለያዩ አከራካሪና አወያይ ጉዳዮችን የያዙ መረጃዎች ናቸው፡፡

ከኢመደበኛ ውይይቶች የተወሰዱ ሌሎች ሁለት መረጃዎች ደግሞ በፋካሊቲ ደረጃ ከስልጠናና ከአውደጥናት በኋላ በተደረገ በምሳና በእራት ግብዣ ላይ ከተካሄደ ኢመደበኛ ውይይት የተወሰዱ ናቸው፡፡ እነዚህ መረጃዎች አንደኛው ከዩኒቨርሲቲው የመረጃ ክምችት ክፍል የተገኘ ሲሆን ሁለተኛው ደገም በአሳታፊ ምልከታ የተሰበሰበ መረጃ ነው፡፡ በአብዛኛው ስብሰባዎቹ በመማር ማስተማሩ ዙሪያ ላይ ያነጣጠሩ በመሆናቸው የተወሰዱት አሃዶች ትምህርታዊ ዲስኩር ናቸው፡፡ ሆኖም ግን ከኢመደበኛ ውይይት የፈለቀው አሃድ አውዱ ከትምህርት ተቋም ዙሪያ ቢሆንም አልፎ አልፎ ከትምህርታዊ ዲስኩር ወጣ ያሉ ጉዳዮችንም የያዙ ናቸው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ውይይቱ ኢመደበኛ ከመሆኑ አንፃር የመጣ ነው፡፡

ለትንተናው በተወሰዱት ድስኩራዊ አሃዶች የተመለከቱት የተጠኝዎች ስም እውነተኛ ስማቸው ሳይሆን በአጥኝዋ የተሰጠ የብዕር ስም ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት በምርምር ስነምግባር ደንብ መሰረት የመረጃ ሰጭዎችን ደህንነትና ግላዊ ማንነታቸውን የመጠበቅ ግዴታና ሃላፊነት ከተመራማሪዋ የሚጠበቅ ተግባር በመሆኑ ነው፡፡ ሌላው ሰዋዊ ስማቸው በቁጥር ከመተካት ይልቅ በሰዋዊ ስም የተተካበት ምክንያት ደግሞ ቁጥር ሰዋዊ መጠሪያ ባለመሆኑ ኑባራዊነትን ለማሳየት ተብሎ ነው፡፡ በአጠቃላይ ለትንተናው የተወሰዱት ድስኩራዊ አሃዶች በአባሪ ሁለት፣ ሶስት፣ አራት፣ አምስት፣ስድስት እና ሰባት የቀረቡት የመለያ ቁጥር አኮ002፣ አኮ003፣ አኮ004፣ አጠመ006፣ ኢመ001፣ ኢመ004 ሲሆን፤ ለገለፃውና ለትንተናው እንዲመች ሲባል በውይይቱ ቅብብሎሽ ቅደም ተከተል መሰረት ተከታታይ ቁጥር ተሰጥቷቸዋል፡፡ በገለፃው (ወ) የተባለው ወንድ

የሚለውን፣ (ሴ) የተባለው ደግሞ ሴት የሚለውን ያታ የሚወክሉ ሲሆን፣ ጭብጡም ንግግሩ በየትኛው ያታ እንደተነገረ የሚያመለክት ነው።

እንደፌርክላፍ (2006) እና ቫን(2008) አገላለፅ፣ በሂሳዊ ዲስኩር ትንተና አቀራረብ ድስኩራዊ አሃድ፣ ድስኩራዊ ልማድና ማህበረ-ባህላዊ ልማድ የተባሉ የመተንተኛ ማዕቀፎችና ገለፃ፣ ትንተናና ትርጎማ የሚሉ ሶስት የትንተና አቀራረብ ደረጃዎችን በመከተል የጥናቱ መረጃ ተተንትኗል። በዚህም በመጀመሪያው በገለፃ ደረጃ የሚከናወነው የድስኩራዊ አሃድ መሳሪያዎችን በመጠቀም ለጥናቱ የተመረጠው አሃድ የቋንቋ አጠቃቀሙ ምን እንደሚመስል የሚገለፅበት ደረጃ እንደሆነና ይህም ለትንተናውና ለትርጎማው ቅድመ ግንዛቤ በመስጠት መሰረት የሚጣልበት ክፍል ነው።

4.3 የመረጃ ትንተናና ግኝት

4.3.1 ድስኩራዊ አሃድ

ለጥናቱ የተወሰዱት መደበኛ ውይይቶች ድስኩራዊ ይዘታቸው ሲታይ በወንዶችና በሴቶች መካከል ከተሳትፎ አንፃር የተለያየ ባህርይ ይታያል። ይኸውም አብዛኛዎቹ ወንዶች ሀሳባቸውን በመግለጽ ተሳታፊ ሲሆኑ፤ አብዛኛዎቹ ሴቶች ደግሞ ሀሳባቸውን አይገልጹም። አልፎ አልፎ ሃሳባቸውን የሚገልጹ ሴቶች ደግሞ የንግግር ድርሻ የሚጠይቁት በውይይቱ መካከልና መጨረሻ አካባቢ ነው(አባሪ ሁለትን እና አባሪ አምስትን ይመልከቱ)።

በሌላ በኩል በኢመደበኛ ውይይት ላይ የወንዶች ቁጥር ጥቂት በሆነበት አውድ ሴቶች የንግግር የበላይነትን የመያዝ ባህሪ ሲኖራቸው በአንፃሩ ደግሞ የወንዶች ተሳትፎ ቀንሶ ታይቷል (ኢመ.001 ይመልከቱ)። በተመሳሳይ ወንዶች በበዙበት ኢመደበኛ ውይይት ላይ ደግሞ ወንዶች ከፍተኛ ተሳትፎ ሲኖራቸው ሴቶች ግን ዝቅተኛ ተሳትፎ አላቸው (ኢመ.004 ይመልከቱ)። ይህንም ቀጥሎ ቀረበው ከቡተቃ የተገኘው መረጃ ያጠናክረዋል።

ቢንያም፡ የታዘብኩት ነገር ብዙ ጊዜ ስብሰባዎችን ላይ ሴቶች ተለምነው ነው የሚናገሩት፡፡ አንዳንድ ጊዜ በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ የወንዶችና የሴቶች ቁጥር ሲታይ ብዙ ሴቶች እያሉ ግን ቁጥራቸው ትንሽ የሆነ ወንዶች እጅ በማውጣትይናገራሉ፡፡ ይህን በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ አጢኛለሁ፡፡ ከዛ በኋላ ደግሞ ምንድን ነው ሴቶች እጅ ሲያወጡ ምናልባት ትንሽ በተለያዩ ኮካሪኩላር ስራዎች ላይ ተሳትፎና ልምድ ያላቸው ሴቶች ሲናገሩ በምንም ነገር ውስጥ ሳይገቡ ወይም ያልተሳተፉ ሴቶች ምንም አይናገሩም፡፡ አዳምጠው ነው በብዛት የሚወጡት፡፡ ስለዚህ በትላልቅ ስብሰባዎች ላይ የሚታየው ነገር ሴቶች ወደማዳመጡ የዘነብላሉ የሚል ግምት አለኝ፡፡ ሴቶች እስቲ እባካችሁ፣ ተለምነው፣ ተፈልገው ነው ከተናገሩም የሚናገሩት (ቡተቃ 202፣ መስመር 213-22)::

የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው ሴቶች በበዙበት መደበኛ ውይይት ላይ በቁጥር አናሳ የሆኑ ወንዶች የንግግር የበላይነት ሲኖራቸው፣ ሴቶች ግን ሃሳባቸውን በመግለጽ አይሳተፉም፡፡ አልፎ አልፎ ሲሳተፉ የሚታዩት ሴቶችም በተለያየ የስራ አጋጣሚዎች ልምድ ያካበቱ ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ግን የአድማጭነት ድርሻ ብቻ ያላቸው እንደሆኑ መረጃው ያመለክታል፡፡ ቀጥሎ የድስኩራዊ አሃድ መተንተኛ መሳሪዎችን በመጠቀም ለጥናቱ የተሰበሰቡት ድስኩራዊ አሃዶች እንደሚከተለው በዝርዝር ተገልፀው ቀርበዋል፡፡

4.3.1.1 ንግግራዊ አውድ

የተወሰዱት ድስኩራዊ አሃዶች ከንግግር ጊዜ አንፃር ሲታዩ በአብዛኛው ወንዶቹ ስብሰባው ከተጀመረ ጀምሮ እስከመጨረሻው ሲናገሩ ሴቶቹ ግን በመጀመሪያ ከመናገር በመቆጠብ በአጀንዳዎቹ መካከልና መጨረሻ አካባቢ ይናገራሉ፡፡ ለምሳሌ በአኮ 002 ድስኩራዊ አሃድ ውብነሽ በነበረው የሃሳብ ልውውጥ ባላት ሃላፊነት ስለጉዳዩ ሃሳብ እንድትሰጥ ከመጀመሪያው ብትጠበቅም እሷ ግን ከአስራ ሰባት የንግግር ድርሻ በኋላ ሃሳቧን ገልፃለች (አባሪ 2፣መስመር 152 ይመልከቱ)፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በአጀንዳዎቹ መካከልም የመናገር ፍላጎት እንዳላቸውና ድርሻው ግን ወዲያውኑ እንዳልተሰጣቸው ከምልከታ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

አበበ፡- ቃለጉባዔውን እንግዲህ ቼክ ማድረግ ያለብኝ ይመስለኛል...
አገሬ፡- /
መለሰ፡- አንዳንደዜ እኮ ይቅርታ አድርግልኝና.....
አገሬ፡- /
አለማየሁ፡- ኦኬ፣ ሪፖርቱ ላይ በተወሰነ መልኩ ክፍተት አለበት...
አበበ፡- ጥሩ ነው፡፡ ኤሲ ላይም ኮሜንት ተሰቷቸዋል ይህን((×××))
አገሬ፡- /
ደበበ፡- እኔ እንትን የማደርገው ምንድን ነው...

ፋሲል፡- [እዚህ ጋ ማስተካከያ ስላለኝ ነው፡፡ እዚህ ጋ ማስተካከያ ስላለኝ ነው፡፡
አበበ፡- አንተ ብዙ ስለተናገርክ በኋላ እሰጥሃለሁ፤ እሰጥሃለሁ ችግር የለም፡፡
አገሬ፡- /
ከበደ፡- ይሄ ካሪክለም ከቀረፁት ውስጥ አንዱ እኔ ነኝ፡፡ መጀመሪያ...
አበበ፡- አቶ አስናቀ
አስናቀ፡-((×××)) (ሰብሳቢው እንዲናገር ቢጠይቀውም መናገር እንደማይፈልግ በድምፅና በጭንቅላቱ መናገር እንደማይፈልግ ገለፀ)
አበበ፡- ያልተባለ ነገር ነው? (ጥያቄው ለአገሬ ነው ለመናገር እጇን በማውጣቷ)
አገሬ፡- እሽ፡፡ ከጋሽ ከበደ ጋር ነው ሀሳቤ የሚስማማ፡፡ በተለይ ...
(አባሪ2፣ አኮ.200-310 ይመልከቱ)

አገሬ የንግግር ድርሻ የጠየቀችው ውይይቱ ተጀምሮ ሰላሳ የንግግር ድርሻ ከተሰጠ በኋላ ሲሆን፣ ድርሻውንም ለመውሰድ አራት ጊዜ እጇን በማውጣት ድርሻ ጠይቃ የተሰጣት ግን በአምስተኛው ጥያቄዋ ነው፡፡ ከመረጃው እንደምንመለከተው ሰብሳቢው ድርሻ ላልጠየቀው አስናቀ እንዲናገር ድርሻ ቢሰጠውም ለመናገር ፍላጎት እንደሌለው ከገለፀ በኋላ ለአገሬ ድርሻውን ሰጥታል፡፡ ሆኖም ግን በድርሻ አሰጣጡ ‹‹ያልተባለ ነገር ነው?›› የሚል ጥያቄ ቢጠይቅም አገሬ በቀጥታ ንግግሯን ቀጥላለች፡፡ ይህም ሰብሳቢው ሁሉም ነገር ተብሎ እንዳለቀና ድርሻው ለመስጠት ፍላጎት እንደሌለው ጠቋሚ ነው፡፡ ከቡተቃ የተገኘው ድስኩራዊ አሃድም ሴቶች መጀመሪያ አካባቢ መናገር እንደማይፈልጉና እጅ በማውጣት ድርሻ ሲጠይቁም እንደማይሰጣቸው ያመለክታል፡፡

ሮዛ፡ እኔ ቶሎ አልናገርም፡፡ ማብራሪያ እስኪሰጥ እጠብቃለሁ፡፡ ከዛ በኋላ ግን መናገር ከፈለኩ እጀን አወጣለሁ፡፡ ካላየኝ ደግሞ እዚህ ጋ ጥያቄ አለ እላለሁ የዲፓርትመንት ብሎም የፋካሊቲ ሲሆን በዛ መልኩ እንዲያልፈኝ ካልፈለኩ ማለት ነው፡፡ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ያው ቅድም እንደገለጽኩት ለመጀመሪውም አልናገርም፡፡
አልማዝ፡ እኔ የታዘብኩት ምን መሰለሽ በየትኛውም ስብሰባ ላይ ለሴቶች እድል አይሰጥም፡፡ ቢሰጥም እንኳ ለተሳትፎ ሴቶች ተብሎ ጉዳዩ ከተጠናቀቀ በኋላ ይሰጥሻል፡፡ እኔ ሶስት ቀን ሙሉ እጀን ሳወጣ ውየ አልሰጠኝ ብሎ በኋላ ስብሰባው ተጠናቀቀ ሲባል ለሴቶች እድል ስጡ ተብለው ለእኔ ተሰጠኝና... (አባሪ አስር፣ ቡተቃ. መስመር 203 78-88 ይመልከቱ)

የቀረበው መረጃው ሮዛ በውይይት መጀመሪያ ላይ ድርሻ ወስዳ መናገር እንደማትፈልግና መናገር ስትፈልግ ደግሞ እጇን በማውጣት ድርሻ እንደምትጠይቅና ካልተሰጣት ‹‹እዚህ ጋ›› የሚል የድርሻ መጠየቂያ ብልሀት እንደምትጠቀም ያሳያል፡፡ ይህንም የምታደርገው በትምህርት ክፍልና በፋካሊቲ ደረጃ እንጂ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ፊዕሞ ሀሳቧን አትገልፅም፡፡ ከዚህ በተለየ ሁኔታ አልማዝ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በሚደረጉ ውይይቶች ሃሳቧን ለመግለፅ

ፍላጎት ያላት ቢሆንም እጇን በተደጋጋሚ አውጥታ ድርሻ እንደማታገኝና ሰብሳቢዎቹ ከተሳታፊ ለሴቶች እድል እንዲሰጡ በሚጠየቁት ጥያቄ እንደተሰጣት መረጃው ያሳያል።

ሌላው በንግግራዊ አውድ ትንተና መሰረት የሴቶችና የወንዶች የቃላት አጠቃቀም ሲታይ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች የጋራ ሀሳብንና ተቆርቋሪነትን ለማቅረብ እንዲሁም አብሮነትን ለማሳየት አንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር ‹‹እኛ›› የሚለውን ተውላጠ ስም ይጠቀማሉ። ለአብነት ቀጥሎ የቀረቡትን አብሮነትን የሚገልፀውን ‹‹እኛ›› የሚለውን ንግግራዊ አውድ የሚያሳዩ ከአባሪ ሶስት፣አኮ003 የተወሰዱትን ቅንጫቢ አሃዶች እንመልከት።

ዶ/ር ሀይሉ፤ ህዝቡ ይተቻቸው ምክንያቱም እኛ ((xxx))ስለማናስጠራቸው ራሳቸው... ስለዚህ በእኛ እንትን ራሳቸው አመልክተው፣ እኛም አፕሮች አድርገናቸው፣ ፈቃደኛ የሆኑ አሁን አራት ሰዎችን አቅርበናል (መስመር112-113)
ሮዛ፤ እኛ ኮምሽን ላይ ስለምንመርጥ ኮሚሽን ከሚገቡ ሰዎች ውጭ የሆነ ነበር ያልኩት (መስመር 184-85)
ጌትነት፤ እንደገና ደግሞ እኛ የወሰን ነው የሚመስለው (መስመር 251)
ጌትነት፡- እኛ ግን አንቀበልም የምንለው እሱን ነው መነሻችን (መስመር 281)
መቅደስ፡- የእኛ ሪዝን ጠቅሰን ነው ሪጀክት የምናደርገው እንጂ (መስመር 282)
በእውቀቱ፡- ምን መሰለህ? ይኸ ሰውየ ከእኛ ቢመጣ በዚ በጣም የራቀ ነው (መስመር)83
መቅደስ፡- አይደለም እኛ ነው ያልነው፤ እኛ ነን ያልነው (መስመር 399)
ጌትነት፤ እኛ ግን የሆነ ነገር መወሰን አለብን (መስመር 996)
ሮዛ፡- እኛ ዝም ብለን ቁጭ እንበል? (መስመር 1080)

የወንዶቹንም ሆነ የሴቶቹን ንግግር ስንመለከት ግላዊ ሀሳባቸውንና ማንነታቸውን ለመግለጽ አንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ‹‹እኔ›› የሚለውን ተውላጠ ስም ይጠቀማሉ። (እኔ) የሚለውን በመጠቀም ሀሳባቸውን የሚያቀርቡበት የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። ይህም ሀሳቡ የራሳቸው ሲሆን፣ ግላዊ አመለካከት (እይታ) ሲሆንና ግለሰቡ ጉዳዩን እንዴት እንደተረዳው ለማሳየት፣ በአንድ ጉዳይ ላይ ያላቸውን ግላዊ አቋም ለማሳየት፣ እንዲሁም የላቸውን የስራ ልምድ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ቅድመ-ግንዛቤ፣ የስራ ድርሻ፣ ሃላፊነትና ስሜታቸውን ለመግለፅ ተጠቅመውበታል። ቀጥሎ የቀረቡትን መረጃዎች ዋቢ በማድረግ እንመልከት፡-

የስራ ድርሻን ለማሳየት፡-

...እኔ አስቤ የመጣሁት ይህን ስለነበር...(ወ) (አኮ.002 መስመር 4)
...እኔ አሁን ... ኮርስ ቼር ነኝ(ሴ) (አኮ.002፣መስመር 616)

ከአኮ 002 የተወሰደውን ድስኩራዊ አሃድ ስንመለከት የውይይቱ ሰብሳቢ ‹‹እኔ አስቤ የመጣሁት ይህን ስለነበር›› በማለት የሰብሳቢነት ድርሻውን ሲገልፅ፣ ከተሳታፊዎች መካከል ደግሞ አንዲት ሴት ‹‹እኔ አሁን...ኮርስ ቼር ነኝ›› በማለት ያላትን የስራ ድርሻ ገልፃለች፡፡ ይህም ሴቶችም ሆነ ወንዶች ያላቸውን ድርሻ ለመግለፅ አንደኛ መደብ ተውላጠ ስም እንደሚጠቀሙ ይጠቁማል፡፡

ሃላፊነትን ለመግለፅ፡-

...ለምሳሌ እኔን የጠየቀኝ ለምሳሌ ጋሽ ደበበ ቢኖር ጥሩ(ወ) (መስመር 41-42)
...እኔ አሁን በተለይ ...እኔ ካቀረብኩ በኋላ... እኔን...(ወ) (መስመር 38-39)
...እና እኔ በጣም እኔ አፍራያለሁ በጣም (ወ) (መስመር 114)
(አባሪ 2፣ አኮ 002)
...እንዲህ አይነት ውሳኔ መወሰን ይከብዳል እኔ(ወ) (መስመር 553- 54)
... ያው መወሰን ስንችል ነዋ እኔ አሁን ምግብ (ሴ) (መስመር 697)
...አንዳንዴ ወጥነት እንደሌለው አያለው እኔም ራሴ(ወ) (መስመር 20)
...አንድ አባባል አለ እኔ በጣም የሚመቸኝ (ወ) (መስመር 61-62)
...እኔን የሚያሳስበኝ ዲን ሲባል (ወ) (መስመር 70)
(አባሪ 3፣አኮ. 003)

በተወሰዱት ድስኩራዊ አሃዶች ወንዶች ሃላፊነታቸውን ለመግለጽ ‹‹እኔ›› የሚለውን ተውላጠ ስም በመጠቀም ራሳቸውን ሲገልጹ፣ ሴቶቹ ግን በዚህ መልኩ ሲገልጹ አይታይም፡፡ ምናልባትም ሴቶች በተቋሙ ያላቸው የሃላፊነት ድርሻ ዝቅተኛ ሊሆን እንደሚችል የሚጠቁም ሊሆን፣ ይህም በቡተቃ የተገኘው መረጃ እንደሚሳየው ለሴቶች የተሰጠው የሃላፊነት ቦታ ዝቅተኛ እንደሆነና ስልጣኑ ሁሉ የተያዘው በወንዶች በመሆኑ ሴቶች የመናገር አቅማቸው ውስን እንደሆነ ተገልጿል፡፡

አስረጅ፡-

አገሬ፡- ...የተለያዩ ነገሮች አሁን ከአካዳሚክ ነገር ውጭ ሌላ ኢክስፒሪንስ ላይኖራት ይችላል አንድ ሴት ልጅ፡፡ እና ምንም ኤክስፐሪያንስ በሌለበት ቦታ ስልጣኑን ሁሉ ወንዶች በያዙበት ሁኔታ ውስጥ የመናገር አቅሟ ውስን ነው፡፡
(ቡተቃ.202፣ መስመር 413-415)

የስራ ልምድ ለማሳወቅ፡-

...ይሄ ካሪክለም ከቀረፁት ውስጥ አንዱ እኔ ነኝ(ወ) (አኮ002፣መስመር 260)
...እኔ የትምህርት ክፍሉንም የማስተዋወቅ ስራም ሰርቻለሁኝ(ወ)
(አኮ002፣መስመር 265)

ADAMA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADAMA, ETHIOPIA

...እኔ ...ከመግባቴ በፊት ...አስተምሬዋለሁ(ወ) (አኮ002፣መስመር 1037-380
...እኔ እዚ 002 ውስጥ ከመግባቴ በፊት እኔ... እያለሁ የ..... እና የ.....
ኮርሶችን ሞጁል አዘጋጅቻለሁ(ወ) (አኮ002፣መስመር 578-79)
...የአንድ አምስት ፋካሊቲዎች፣ ኮሌጆች፣ ስኩል ካሪኩለማቸውን ብቻ ሳይሆን እስከ ጋይድ ቡካቸው በእጄ አለ። ያን አሰስመት ስሰራ ያየሁት እነዚህ ጉዳዮች ተካተው በይዘታቸው ውስጥ አሉ (ወ) (አጠመ.006፣ መስመር 33-35)

የትምህርት ደረጃ የሚያመለክቱ፡-

...እኔ ራሱ ስማር.....ተብየ ነው የተማርኩት ፒኤችዲዬን ራሱ፣(ወ) (አኮ 002፣መስመር 459-60)
...ስለዚህ የሰለጠንኩበትን ጊዜየንም ያጠፋሁበትን ብዙም ነገር የፃፍኩበትም ኮርስ ስለሆነ ማለት ነው(ወ) (አኮ 002፣መስመር 795-96)
...ተምሬያለሁ እኔ ኢዱኬሽን ነው የተማርኩት(ወ)(ኢመ 004፣ መስመር 69)
...እኔ አድቫንስ ነኝ ዲፕሎማ አስተማሪ ነበርኩ(ወ) (አጠመ.006፣ መስመር25-26)

እውቀት / ችሎታን ለመግለፅ፡-

...በዛን ሰዓት ንባቢ እንዲያውም አድርጌያለሁ ..... የሚለውን መፅሀፍ አንብቤያለሁ (ወ) (አኮ መስመር 02፣265-66) እና ችግራችን አሁን እኔ እዚህ ጋ የምጠራጠረው ምንድን ነው አስፍቶ ከማንበብ የመጣ ችግር እንዳይሆን እጠራጠራለሁ፡(ወ)(አኮ 002፣ መስመር 274-75)
...እኔ አንዳንዴ እንደ ገጣሚ ያደርገኛል። እናም አሁን ሀሳቤን እንዴት ልግለጽ አልኩና እዚሁ አሁን አንዲት ግጥም እኔኑ ከገለፀች ብየ (ወ) (ኢመ.004፣ መስመር 147-48)
...እኔ አንድ አክቲቪቲ ከኢንተርኔት ባገኝ ወዲያውን ዳውን ሎድ አድርጌ ፕሪንት አድርጌ ለተማሪዎቼ ማሰራት እችላለሁ (ወ) (አጠመ 006፣መስመር 17-18)
...እንዴት ነው አንድ ጊዜ አንድ መጽሀፍ ሳነብ ባልና ሚስት ለምን ይጣላሉ? ለምንድን ነው ሴትና ወንድ የሚጣሉት የሚል(ወ) (አጠመ 006፣ መስር 47-48)

ወንዶች ‹‹እኔ›› የሚለውን ተውላጠ ስም በመጠቀም የስራ ልምዳቸውን፣ የትምህርት ደረጃቸውንና ያላቸውን እውቀት/ችሎታቸውን ለመግለፅ ሲጠቀሙበት፣ ሴቶቹ ግን በዚህ መንገድ ራሳቸውን ሲገልጹ አይታዩም። ለዚህም ባህሉ ተፅዕኖ እንዳለውና ስለራስ መናገር የትህትና መገለጫ ባለመሆኑ ሴቶቹ ‹‹እኔ›. የሚለውን ተውላጠ ስም በመጠቀም ስለራሳቸው እንዳይገልጹ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ከቡተቃ የተገኘው መረጃ ያመላክታል።

አገሬ፡- ...ግን እንደአጠቃላይ ስናየው በባህላችን ብዙም አይበረታታም እንዲህ አይነት ነገር፣ ማለት ሰው ይናገርልህ እንጅ አንተ ስለራስህ አትናገር የሚል አለ ማለት ትክክለኛ ጥቅሱን ባላገኘውም... (ቡድን 201፣ መስመር 524-26)

የግል አቋም፡- ድጋፍ/ተቃውሞ፡-

...እኔ እንስማማ ብሎ ባይቋጭ ደስ ይለኛል(ሴ)(አኮ002፣መስመር 464)
...አይ፣ እኔ በልዩነት ይያዝልኝ! (ወ) (አኮ002፣መስመር 1094)
...እነሱ እንዲሰጡላችሁ የሚባለው እኔ ሀሳብ አልቀበልም (ወ)(መስመር 795)
...እኔን አስጨርሰኝና በኋላ ከዛ አንተ ትጨርሰዋለህ(ሴ) (አኮ002፣መስመር 468)
...እኔ የ002 ፕሮግራም ለእነኚህ ኮርሶች ባለቤት መሆን አይችልም ከተባለ ውድቀት ነው(ወ) (አኮ002፣መስመር 971)
...እኔ አሁን ጥሩ ነው የምለው ነገር አለ። በእኛ ፋካሊቲ በተለይ እኔ አንዳንዶች ሊኖራቸው ይችላል። እኔም አሁን የምለው ነገር አለ። በበኩሌ እኔ አሁን የተደረገልኝ ነገር ምንድን... (አጠ. 006፣መስመር 13-23)
... አይደለም! እኔ እንደዛ አይደለም ያልኩህ(ሴ) (አኮ 003፣ መስመር 175)
...እኔ ከዚህ በፊት ጥፋት የለበትም አላልኩም። (ወ) (አኮ.003፣መስመር 398)
...እኔ ተናግሬአለሁ እኮ።(ወ) (አኮ 003፣መስመር 569)

የቀረበው አሃዳዊ መረጃ የተወሰደው ከመደበኛ ውይይቶች ላይ ሲሆን፣ በዚህ አውድ የግል አቋምን ለመግለጽ ‹‹እኔ›› የሚለውን ተውላጠ ስም ከሴቶች ይልቅ ወንዶች የሚጠቀሙበት ሲሆን፣ አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ሴቶችም እንዳሉ ይጠቁማል። የግል አቋሟን በመደበኛ አውድ የገለጸችውን ሴት ዳራ ስንመለከት ከፍ ያለ የስራ ልምድ ያላት በመሆኗ በዚህም በራስ የመተማመን መንፈስ ያዳበረች ልትሆን ትችላለች። በሌላ መልኩ ግን ሴቶች ኢመደበኛ በሆነና ሴቶች በበዙበት አውድ ላይ ‹‹እኔ›› የሚለውን ተውላጠ ስም በመጠቀም አቋማቸውን እንደሚገልጹ ቀጥሎ የቀረበው መረጃ ያመለክታል።

አዳነች፡ እኔ ግን የማይመቹኝ ሰው ማን ናቸው ዶር. ከበደ ናቸው።
ማርቆስ፡ ኧረ ባክሽ! አታውቂያቸውም?
አዳነች፡ ብዙ ኦፖርቺንቲስ ላይ አግኝቻቸው አልወዳቸውም።
ማርቆስ፡ ዶር ከበደ?
መዓዛ፡(በመደራረብ) እኔ ደግሞ በጣም ነው የምወዳቸው። ሲያስተምሩ እኮ... በጣም ጎበዝ ናቸው። እሳቸው!...
አዳነች፡ እህ
ማርቆስ፡ ለምን? ...
[ሶፍያ፡ (ጣልቃ በመግባት) እኔ ደስ የሚሉኝ ዶር ይመር... (አባሪ 6፣ኢመ.001፣ መስመር26-45)

መረጃው እንደሚያመለክተው ሴቶች በበዙበት ኢመደበኛ አውድ ላይ ‹‹እኔ›› የሚለውን ተውላጠ ስም ሴቶች እንደሚጠቀሙና በዚህም ስለሚጠሉትና ስለሚወዱት ጉዳይ ያላቸውን አቋም በቀጥታ ይገልፃሉ፡፡ በሌላ በኩል ግን ወንዶች በመደበኛው አውድ የተጠቀመበትን ‹‹እኔ›› የሚለውን ተውላጠ ስም በመጠቀም የግል አቋማቸውን ሲገልጹ አልታዩም፡፡ በአዳነችና በመዓዛ መካከል ያለውን የሃሳብ ለውውጥ ስንመለከት አዳነች አልወዳቸውም ስትል፣ መዓዛ ደግሞ በጣም ነው የምወዳቸው በማለት ያላቸውን አቋም በቀጥታ አፅንኦት በተላበሰ መልኩ ሲያቀርቡ፤ ወንዶቹ ግን ስለራሳቸው አቋም ከመግለፅ በመቆጠብ ጥያቄ በመጠየቅ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ይህም ሴቶች ወንዶች የበዙበት አውድ እንደማይመቻቸው ሁሉ ወንዶችም ሴቶች የበዙበት አውድ እንደማይመቻቸው ጠቋሚ ሊሆን የሚችል ሲሆን፣ በቡተቃ ‹‹ከወንዶቹ ጋር ችግር የለብኝም ሴቶቹ ጋር ግን በጣም የማላውቃቸው ከሆኑ ትንሽ ነፃ ያለመሆን ችግር አለ፡፡›› (ቡድን 201፣መስመር 27-28) ተብሎ የተገለፀው ሴቶች በበዙበት አውድ ወንዶች ሃሳባቸውን በመግለጽ እንደማይሳተፉ ያመለክታል፡፡

ቅድመ ግንዛቤ መኖሩን/አለመኖሩን፡-

ውይይቱን ሂደት ተከትሎ ስለሚነሱ ጉዳዮች የሚያውቅትንና የማውቁትን ‹፣እኔ›› በማለት ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ይገልፃሉ፡፡ ቀጥሎ ለአብነት የቀረቡት አሃዶችን ይህንኑ ሳያሉ፡፡

...ሎጅክ የሌለበት ትምህርት እኔ አላውቅም ሎጂካሊ ነው (ወ) (አኮ 002፣መስመር 418)
...የሚል የለውም እኔ እስከማውቀው ድረስ ማለት ነው(ሴ)(አኮ 002፣መስመር 827-28)
...እኔ አሁን... የሚለውን ፅጌ ስትሰጥ አይቻለሁ(ሴ) (አኮ 002፣መስመር 313)
...ዶ/ር ከበደን እኔ በዝና ነው የማውቃቸው (ሴ) (ኢመ.001፣ መስመር 35)
...እነዚህ ላይ ነው እኔ ያስተዋልኩት (66)እኔ የማውቃት ትንሽ (ሴ) (አጠ.006፣ መስመር 66)
...እኔ የማውቃት ትንሽ በሃይማኖቴ...(ሴ) (አጠ.006፣ መስመር 87-88)
...ለእኔ በቢፒ አር ውስጥ የማይቀየር ነገር የለም (ወ) (አኮ 003፣ መስመር 148-50)
...በቃ ብሪፍ ማድረግ እችላለሁ እኔ፡፡ ባለፈው ስለነበርኩ (ወ) (አኮ 003፣አመስመር 195)
...ገብቶሃል እኔ የምልህ(ወ) (አኮ 003፣መስመር 349)
... እኔ ሌላ ያየሁት ትምህርት ክፍሎችን የማወዳደር ሁኔታም ያለ መሰለኝ(ወ) (አኮ 004፣ መስመር 21)

ከተለያዩ ድስኩራዊ አሃዶች የተወሰዱት መረጃዎች እንደሚያሳዩት ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ስለሚያውቁት ጉዳይ ‹‹እኔ›› የሚለውን ተውላጠ ስም በመጠቀም ሀሳባቸውንም ሆነ ራሳቸውን ይገልፃሉ፡፡ ሆኖም ግን ሁለቱም ፆታዎች የሚገልጹበት መንገድ የተለያየ ይመስላል፡፡ ይኸውም ወንዶች ስለሚያውቁት ጉዳይ ለምሳሌ ‹‹ሎጅክ የሌለበት ትምህርት እኔ አላውቅም፣ ለእኔ በቢፒአር የማይቀየር ነገር የለም፣ በቃ ብሪፍ ማድግ እችላለሁ›› በማለት በእርግጠኝነት ሲያቀርቡ፤ ሴቶቹ ድግሞ በተለሳለሰ ሁኔታ ‹‹የሚል የለውም እኔ እስከማውቀው ድረስ፣ እኔ...አሁን...ፅጌ ስትሰጥ አይቻለሁ›› በማለት ገልጸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በውይይት ሂደት በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ቅድመግንዛቤ የሌላቸው መሆኑን ለመግለፅ አንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተውላጠ ስምን ይጠቀማሉ፡፡

አስረጅ፡-

ቅድመ ግንዛቤ አለመኖር፡-

> ...እኔ በተለይ አላውቅም...አይ ሃቭ ኖት አይዲያ፡፡ አሁን በማናውቀው እኔ በተለይ በማላውቀው ነገር ነው አሁን እንትን አድርግ እየተባልኩ ያለሁት(ወ) (አኮ 002፣ (መስመር 7-14)
> ...አሁን ግን እኔ ያልገባኝ ነገር አሁን ይሄ ልጅ እንደገና ኮርሱን (ሴ) (አኮ 003. መስመር 641)
> ...አይ እኔ ግን የሚመስለኝ ምናልባት አንተ ሀጉን ስለምታውቅ ልታርመን ትችላለህ፡፡ (ወ) (አኮ፣ 003፣ መስመር 678-79)
> ...ግን እኔ ይሄ ጥያቄ ሁለተኛው ላይ ባለትዳርና ልጅ የሌለው ይላል፡፡ ባለትዳር ሆኖ ልጅ የሌለው ለምንድን ነው ከባለትዳርና ልጅ ካለው እንትን የሚባለው የሚለየው? (ሴ) (አኮ 004፣ አመስመር 82-83)
> ...እኔ ለራሴ የማውቀው ነገር አልነበረኝም፡፡ አሁን ግን በጣም ተገንዘቤያለሁ... (ሴ) (አጠመ. 006፣ መስመር 143-44)

የቀረበው መረጃ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች የማያውቁትን ጉዳይ በግልጽ ‹‹አላውቅ፣ የማውቀው ነገር አልነበረኝም›› በማለት የሚያቀርቡ እንደሆነ ሲያሳይ፤ አንዳንድ ሴቶች ደግሞ የማያውቁትን ጉዳይ አላውቅም ከማለት ይልቅ በጥያቄ መልክ ለምሳሌ ‹‹እኔ ያልገባኝ ነገር...?፣ ግን እኔ ልምንድን ነው...?››በማለት ሲቀርቡ፣ አንዳንድ ወንዶች ደግሞ አላውቅም ብሎ በመግለጽ ፋንታ ‹‹አይ እኔ ግን የሚመስለኝ...›› የሚለውን ሲጠቀሙ ይታያል፡፡ ይህም ሴቶች በጥያቄ መልክ፣ ወንዶች ደግሞ ግምታዊ አቀራረብን በመጠቀም ቅድመግንዛቤ የሌላቸው መሆኑን በማድበስበስ ለማቅረብ እንደሞከሩ መረጃው ያመላክታል፡፡

በአጠቃላይ የስራ ድርሻን፣ ሃላፊነትን፣ የስራ ልምድንና የትምህርት ደረጃን፣ ቅድመግንዛቤን በመግለጽ በኩል አብዛኛዎቹ ወንዶች ‹‹እኔ›› የሚለውን ተውላጠ ስም ተጠቅመው የሚገልጹ ሲሆን፣ አብዛኛዎቹ ሴቶች ግን ይህን ሲያደርጉ አይታዩም። ይህም አብዛኛዎቹ የስራ ድርሻና ሃላፊነቶች በወንዶች እንደተያዙ የሚያመላክት ሲሆን ሴቶች የተሰጣቸው የስራ ድርሻ ካለ ደግሞ እኔ እንዲህ ነኝ ብለው እንደሚናገሩ ከምልከታና ከቡተቃ የተገኘው መረጃ ያመላክታል። ከዚህ በተለየ ግን ኢመደበኛ በሆነና ሴቶች በበዙበት አውድ ሴቶች ‹‹እኔ›› የሚለውን ተውላጠ ስም በመጠቀም ራሳቸውን ሲገልጹ፣ ይህ አውድ ለወንዶች ነፃ እንደማያደርጋቸው መረጃው ይጠቁማል።

መፍትሄ ሰጭ፡-

በውይይት ወቅት ለሚነሱ ችግሮች መፍትሄ ከመስጠት አንፃርም በሴቶችና በወንዶች መካከል ልዩነት ያለ ይመስላል። ይኸውም አብዛኛዎቹ ወንዶች ችግሩን እና የችግሩን ስፋትና አሳሳቢነት በማሳየት ላይ የሚያተኩሩ ሲሆን ሴቶች ደግሞ ለችግሩ መፍትሄ ነው የሚሉትን ነገር በማቅረብ ላይ ያተኩራሉ። ለአብነት በዩኒቨርሲቲው በተደረገ አጠቃላይ ስብሰባ ላይ የተወሰደውን ድስኩራዊ አሃድ እንመልከት፡-

> ...ያን ተሸክሜ በር ላይ እጠብቃለሁ እየተንቀጠቀጥኩ። ይወጣልኛል ከዛ ገብቼ ማስተካከል እጀምራለሁ ስንት ደቂቃዎች ናቸው የሚባክኑት በዚህ መሀል። እናም እዚህ ላይ መሰራት አለበት(ወ) (አጠመ 006፣መስመር 21-23)

> ...መቼም የጉዳዩ አሳሳቢነት ምንም ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ አልመሰለንም። በጣም አሳሳቢነቱ ይሰማኛል። ደሞ በጣም የሚያሳስበኝ ሜቶዶሎጂው ነው። እንዴት እንግባባ ምን ብንል እንግባባለን፣ ምን ባንል ደግሞ አንግባባም የሚለው ነገር ያሳስበናል።...እና እንዲህ እንዲህ ያሉ ነገሮች ናቸው ናላየን የሚያዞሩት እና እኔ የተጨበጠ ነገርም የለኝም ግን ዝም ብየ የሚያሳስበኝ ነገር አለ። አመሰግናለሁ(ወ) (አጠመ 006፣ መስር 44-60)

> ...ይሄ እንግዲህ አንድ ችግር መኖሩን ያሳየናል ወደኋላ (ወ) ... (አጠመ006፣መስመር 42-43

> ...ስለዚህ አሁንም...ጥበቃ ሊያደርግበት ይገባል። ..ስለዚህ የህዝብ ችግር እስካለ ድረስ መፍትሄ መፈለግ ይገባል። ለዚህ ደግሞ መጀመሪያ ህዝቡ ምን ችግር እንዳለበት ቆም ብሎ መንግስት መስማት አለበት። ... ደግሞ ህዝቡን አሳምነን... በሚጠቅም መልኩ ብናደርገው ...እስቲ ቆም ብለን መጀመሪያ ...እንጨረስ (ሴ)(አጠመ.006፣ መስመር64-138)።

በቀረቡት ቅንጫቢ ድስኩራዊ አውድ ላይ ሀሳባቸውን የገለጹትን የሶስቱን ወንዶች አገላለጽ ስንመለከት አለ የሚሉትን ችግር በዝርዝር በማሳየትና አሳሳቢነቱን በማስረዳት ላይ ያነጣጠረ ነው። የሴቷን ገለፃ ስንመለከት ግን ችግር የምትላቸውን ጉዳዮች ካነሳች በኋላ ጎን ለጎን መፍትሄ የምትላቸውን ሀሳቦች ከማስቀመጧ በላይ የቋንቋ አጠቃቀሟን ስንመለከት ደግሞ በአብዛኛው ‹‹ይገባል፣ አለበት›› የሚሉ አፅንዖታዊ ቃላትን የተጠቀመች ሲሆን ‹‹ብናደርገው›› የሚል ስነምግባራዊ ቃላትን በንግግሯ በመጨረሻ ላይ በመጠቀም ለስለስ ባለ ሁኔታ ንግግሯን አጠቃላለች። ሆኖም ግን ጉዳዩን ያቀረበችበትን መንገድ ስንመለከት በአንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ‹‹እኔ›› በመጠቀም ሳይሆን፣ ጉዳዩን በጥቅሉ በማቅረብ የመፍትሄ ሃሳብ ያቀረበችበት ሁኔታ ይታያል። በአጠቃላይ ሴቶች ለችግሮች መፍትሄ የመስጠት አቅማቸው ከፍተኛ እንደሆነ ከቡተቃ የተገኘው መረጃም ያረጋግጣል።

> በትልልቅ ስብሰባዎች አዎ መናገር የምፈልገው ያውም የመፍትሄ ሀሳብ ይሆናል የምለውን ሀሳብ ስለምፈራ ብቻ ሳልናገር ሁሌም እወጣለሁ። እንዳልኩሽ ሀሳቤን አጠገቤ ላለች ወይም ወንድ ሲሆን ይችላል እነግረዋለሁ (ሴ) (ቡተቃ 203፣ መስመር144-46)

ሴቶች ለመናገር ፍላጎት እንዳላቸውና መናገር የሚፈልጉትም የመፍትሄ ሀሳብ እንደሆነ መረጃው ይጠቁማል። ሆኖም ግን በተለይም በትልልቅ ስብሰባዎች ላይ በፍርሃት ምክንያት እንደማይናገሩና ጉዳዩ ቢነገር ጠቃሚ ነው የሚሉት የመፍትሄ ሀሳብ ካላቸው አጠገባቸው ላለ ሰው በመንገር እንዲናገርላቸው ያደርጋሉ። በተጨማሪም ሴቶች የመፍትሄ ሃሳብ በማቅረብ የተሻለ ችሎታ እንዳላቸው ቀጥሎ የቀረቡት ማስረጃዎች ይጠቁማሉ።

> በሴቶችና በወንዶች መካከል ለአንድ ነገር ቶሎ ብሎ መፍትሄ ማግኘት፣ መላ ማግኘት መቻል ሴቶች ላይ ከፍተኛ ሲሆን፣ ወንዶች ለይ ይህ ችሎታ ዝቅተኛ ነው። በምሳሌ ላስረዳ፣ በድሮ ጊዜ ..(ወ) (ቡተቃ 203፣ መስመር 218-220)

> ...ብዙ ጊዜ በንግግር ላይ ሴቶች የተቃውሞ ሀሳብ ሲያነሱ አላይም። የመጠየቅ መፍትሄ ሀሳብ የመስጠት ነገር፣ እንዲህ ቢሆን የሚል ነገር ነው (ወ) (ቡተቃ 203፣መስመር 238-243)

...ሴቶቹ ግን መፍትሄ ላይ ነው የሚያተኩሩት፤ ልክ ሲናገሩ ይሄ ነገር አልሆነም ግን እንዲህ ቢሆን ኖሮ ብለው ይናገራሉ። የወንዶቹ ግን እንደዚህ አይነት ነገር ላይ አያተኩሩም። በኋላ የመፍትሄ ሀሳብ ተብለው ተጠይቀው ካልሆነ በስተቀር የመፍትሄ ነገር እንትን የማለት ነገር ብዙም እኔ ካየሁት አንፃር ማለት ነው (ወ) (ቡተቃ 202፣ መስመር174-77)

...ለምሳሌ አሁን ባለፈው ስብሰባ ላይ ሴቶችም ነበሩ። ግን ሴቶችስ የት አሉ? የሴቶች ተሳትፎ ምናምን ተብሎ ተጠይቆ ነው የተናገሩት የተወሰኑ ሴቶች። እና ሲናገሩ ላይ ወንዶቹ ለምሳሌ ትዝ ይላችሁ እንደሆነ እንዴት እንደዚህ ይሆናል? ይህ እኮ ራሳችሁ የመጣችሁት ችግር ነው ምናምን ብለው ስሜታዊ ሆነው ነበር ሲናገሩ የነበረ። ሴቶቹ ግን እንደዚያ አይነት ባህሪ አልነበራቸውም ለስለስ ብለው ነበር የሚናገሩት። እና ቅድም እንደተባለው ወደፊት መሆን የሚገባውን መፍትሄ በማቅረብ ነበር የተናገሩት። እና እኔ የተረዳሁት ምንድን ነው ወንዶቹ ከበስተጀርባው መቆጣታቸውን ለማሳወቅ የሞከሩበት ሁኔታ ነበር በዚያ ንግግር (ሴ)(ቡተቃ 202፣ መስመር179-87)

ከቡድን ተኮር ቃለመጠይቆቹ የተወሰዱት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ብዙ ጊዜ ወንዶች በተቃውሞና ያለውን ችግር ስሜታዊ ሆነው የማቅረብ አዝማሚያ ያላቸው ሲሆን፣ ብዙ ጊዜ የመፍትሄ ሀሳብ የሚሰጡት ሲጠየቁ እንደሆነ መረጃው ያሳያል። የሴቶቹ ንግግር ደግሞ በአብዛኛው በመጠየቅና መፍትሄ በመስጠት ላይ ያተኮረ እንደሆነና ሴቶች ለሚቀርቡ ችግሮች መፍትሄ የማቅረብ ችሎታቸው ከፍተኛ እንደሆነ ያስረዳል። ሆኖም ግን ሴቶች የተለያዩ መድረኮችን በመጠቀም ሀሳባቸውን ስለማይገልጹ ይህን ችሎታቸውን ለተቋሙ በማበርከት በኩል ደካማ ሲሆኑ ከዚህ በተጨማሪም በተቋሙም የሴቶች ሀሳብ ጠቃሚ ነው ተብሎ እንዲናገሩ ከማድረግ ይልቅ ለተሳትፎ ተብሎ እንዲናገሩ ድርሻ እንደሚሰጣቸው መረጃው ያመለክታል።

በአጠቃላይ በአኮ002 እና በአጠመ006 ድስኩራዊ አሃድ ላይ የመፍትሄ ሰጭ ድርሻን ይዘው የምናገኛቸው ሴቶችን ስንመለከት በስራ ልምዳቸው ከፍ ያሉት ሲሆኑ ይህም ሴቶች በተለያየ አጋጣሚ የስራ ልምድና ለተለያዩ ጉዳዮች ግንዛቤ ሲኖራቸው ሀሳባቸውን ከመግለጽ ባለፈ መፍትሄ የመስጠት ችሎታው እንደሚኖራቸው ያመላክታል። ይህንም ቀጥሎ የቀረበው ከቡተቃ የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል።

ሌላው ግን የሚመስለኝ ሁለት ነገሮች አሉ ከዚህ ጋር ተጽዕኖ የሚያደርጉ። እድሜ እና እውቀት። እውቀት ያላት ከሆነች ዝም ብለው ያዳምጣታል፣ እድልም በተደጋጋሚ ይሰጣታል። እድሜም ደግሞ ብዙ ልምድ ሲኖራትና ልምዷን ተጠቅሞ ሰፋ ያለ ነገር ስለምታቀርብና የመፍትሄ ሀሳብ የመስጠት

ችሎታዋ ስለሚታይ ተደማጭነትና ተቀባይነት ይኖራታል (ወ) (ቡተቃ 203፣ መስመር342-46)::

የቀረበው መረጃ ሴቶች በእውቀት የተሻሉ ከሆኑ የንግግር ድርሻ የማግኘትና የመደመጥ እድል እንደሚያገኙና እድሜያቸው ከፍ ሲል ደግሞ ብዙ ልምድ ስለሚያካብቱ ልምዳቸውን ተጠቅመው የመፍትሄ ሀሳብ የመስጠት ችሎታ እንዳላቸውና በዚህም ተደማጭነትና ተቀባይነትን እንደሚያገኙ ያስረዳል::

ከዚህም ሌላ ወንዶች ‹‹እኔ›› እና ‹‹እኛ›› የሚሉትን ተውላጠ ስሞችን በመጠቀም አብሮነትንም ሆነ ራስን ለመግለፅ በጥምረት የሚጠቀሙባቸው ሲሆን፣ አቀራረባቸውን ስንመለከት ግን አንዳንዶቹ ከአንደኛ መደብ ነጣላ ቁጥር (እኔ) ወደ አንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር (እኛ) /እኔ→ እኛ/፣ አንዳንዶቹ ደግሞ በተቃራኒው ከእኛ ወደእኔ /እኛ→ እኔ/ በሚያመራ መልኩ ሲጠቀሙበት ይታያል:: ቀጥሎ በዋቢዎች መነሻነት የቀረቡትን እንመልከት:-

እኔ→ እኛ፣

አስረጅ1:-

> አበበ:- እሽ የኮርስ ባለቤትነት ላይ፣ እኔ አስቤ የመጣሁት ይህን ስለነበር በተነሳው ሁለተኛው አጀንዳ ላይ አውርተን በዛ መንፈስ መነጋገር እንችላለን:: የሁለቱን ፕሮግራሞች በሚመለከት አንሱና ከዛ በመቀጠል ወደኮርስ ባለቤትነት መሄድ እንችላለን (አኮ 002፣መስመር 4-6)::

የቀረበውን ድስኩራዊ አሃድ ስንመለከት ሰብሳቢው የውይይት አጀንዳ ማቅረብ የእሱ ድርሻ እንደነበረ ‹‹እኔ አስቤ የመጣሁት ይህን›› በማለት ጠቁሟል (እኔ) የምትለዋ ተውላጠ ስም የሰብሳቢውን ሃላፊነትና ሀይል ታመላክታለች:: የአበበ ንግግር ከአንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር (እኔ) ወደ አንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር (እኛ) የመሸጋገር ሁኔታ ያሳያል:: ይህም በስራ ቦታው ላይ ያለውን የሃላፊነት ቦታ ያሳየበትና ውይይቱን ደግሞ የጋራ በማድረግ በአንድ ጊዜ ራሱንና አብሮነትንም የገለፀበትን መንገድ ያሳያል::

አስረጅ 2፡-

> ከበደ፡- ይሄ ካሪክለም ከቀረፀት ውስጥ አንዱ እኔ ነኝ፡፡ ... በተለይም እኛ ለምን ለውጥ ተካሄደ፣ ተቃውሞ የለኝም ... እኔ የትምህርት ክፍሉንም የማስተዋወቅ ስራም ሰርቻለሁኝ፤ይሄ ይሄ ቅሬታ ፈጥሮብኝ ስለነበር እኔ በቀጥታ ስለሞንን አናግሬዋለሁ፤ ... ኮርሱ የእኛው ነው በሚለው መንፈስ የተግባባን ይመስለኛል፡፡ ...ለምን እኛ ነን ተደራጅተን ....(አኮ 002፣መስመር 260-285)፡፡

ከበደ የንግግሩ አካሄድ በመጀመሪያ ስለራሱ እኔ በማለት ከገለፀ በኋላ፣ ቀጥሎ ደግሞ እኛ በማለት ጉዳዩን የጋራ በማድረግ ያቀረበ ሲሆን ከአንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር በመነሳት ወደብዙ ቁጥር ተውላጠ ስም የመለዋወጥ ሁኔታ ይታያል፡፡ በመጀመሪያ በአንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር (እኔ) እኔ በማለት በመጀመሪያ ስለራሱ ከገለጸ በኋላ ቀጥሎ እኛ በማለት የሚያቀርባቸው ሀሳቦች መጀመሪያ ያቀረበው ሀሳብ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ለማድረግ የተጠቀመበት ይመስላል፡፡

አስረጅ 3፡-

> ግርማ፡- ...እኔ አሁን ጥሩ ነው የምለው ነገር አለ፡፡ በእኛ ፋካሊቲ በተለይ እኔ አንዳንዶች ሊኖራቸው ይችላል፡፡ እኔም አሁን የምለው ነገር አለ፡፡ በበኩሌ እኔ አሁን የተደረገልኝ ነገር ምንድን ነው ላጥቶፕ አለኝ ተሰቶኛል፡፡ ኦቨር ሄድ ፕሮጀክተር ማግኘት (አጠመ፣006፣ መስመር 13-15)

የግርማን የተውላጠ ስም አጠቃቀም ስንመለከት በአብዛኛው የራሱን ስሜትና በስራ ቦታው ለየት ያለ ተቀባይነት እንዳለው ለመግለፅ ‹‹እኔ›› የሚለውን ተውላጠ ስም በድግግሞሽ የተጠቀመበት ሲሆን፤ ‹‹እኛ›› የሚለውን አንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር ተውላጠ ስምን በመጠቀም በእኔ ፋካሊቲ ከማለት ይልቅ ‹‹በእኛ ፋካሊቲ›› በማለት ጉዳዩ የጋራ መሆኑን በማሳየት የፋካሊቲውን መልካም ነገር ጠቁሟል፡፡ ወዲያው ደግሞ ወደ ‹‹እኔ›› አጠቃቀም በመሸጋገር ራሱን ከፋካሊቲው አባላት ለይቶ በማውጣት የራሱን ማንነትና የበላይነት የገለፀበት ሁኔታ ይታያል፡፡

እኛ→ እኔ

> መለሰ፡- ካሪክለም ሪቪዥኮን በሚመለከት እኛ ውስጣዊ ይዘቱን አናውቅም። እኔ በተለይ አላውቅም። እዛ ውስጥ እንዴት አድርጌ ኮሜንትስ ለማድረግ የምችለው። አሁን ባለፈው እነፋሲል ነግረውኝ ነበር።ታያለህ ብለውኝ ነበር ፈተና ላይ ስለነበርኩ አላየሁትም። ያየ ሰው ከሌለ በስተቀር ለውይይት አይመቸንም እኮ። ወይ እኛ ሰጥተውን እንድናይ ተደርጎ ቢሆን፣ወይ ደግሞ እናንተ አይታችሁት የሆነ ኮንትሮቨርሻል የሆኑ ነገሮች ተነስተው ቢሆን እሱን አንስታችሁልን ካልሆነ በስተቀር ካሪክለሙ ላይ የት ቦታ ላይ ለውጥ እንዳለው፣ የት ቦታ ላይ ችግር እንዳለ፣ አይ ሃቭ ኖት አይዲያ። አሁን በማናውቀው እኔ በተለይ በማላውቀው ነገር ነው አሁን እንትን አድርግ እየተባልኩ ያለሁት። ግር ስላለኝ ነው (አባሪ ሁለት መለያ ቁጥር 002፣ መስመር 7-14)።

የመለሰን አገላለፅ ስንመለከት ጉዳዩን መጀመሪያ የጋራ በማድረግ ይጀምርና ቀጥሎ ወደግሉ የመውሰድ ሁኔታ (እኛ→እኔ→ እኛ→እኔ) ይታያል። መለሰ ንግግሩን ሲጀምር ተሰብሳቢውን በመወከል ይጀምርና ቀጥሎ የሚናገረው ግን ስለራሱ ‹‹እኛ ውስጣዊ...እኔ በተለይ...ያየ ሰው ከሌለ በስተቀር ለውይይት አይመቸኝም እኮ... አሁን በማናውቀው እኔ በተለይ›› በማለት ነው። እኛ ሲል በዚህ ውይይት ውስጥ ያለው የሀይል ሚዛን ከተሰብሳቢዎቹ ጋር አቻ መሆኑንና የአብሮነት ስሜት መኖሩን ያሳያል። ነገር ግን ‹‹እኔ በተለይ›› እያለ ደጋግሞና ስለራሱ ትኩረት ሰጥቶ መናገሩ ከሌሎቹ ተሰብሳቢዎች የሚለየው አንድ ነገር መኖሩን ይጠቁማል።

> ዶ/ር ሀይሉ፡- ..እኛም አጥሮች አድርገናቸው፣ ፈቃደኛ የሆኑ አሁን አራት ሰዎችን አቅርበናል። አይ እዚህ ለምሳሌ አንዱ ፐርሰናሊ እዚህ ውስጥ ካሉት መወዳደር የሚችል ምናልባትም የሚሻል ፈቃደኛ የሚሆን አለ ካልከኝ አይ ካን ዲሳይድ (አኮ 003፣ መስመር 113-114)።

ዶ/ር ሀይሉ በመጀመሪያ ለምርጫ የቀረቡትን ሰዎች እንዲወዳደሩ ያደረገው እሱ ብቻ ሳይሆን በጋራ እንደሆነ ይገልፃል። ሆኖም ግን አሁን በሚናገርበት አውድ ላይ ደግሞ ለምርጫ የሚቀርብ ሰው ካለ ማቅረብ እንደሚችልና ይህንም መወሰን እንደሚችል ‹‹አይ ካን ዲሳይድ /እኔ መወሰን እችላለሁ›› በማለት ያለውን የመወሰን የሀይል የበላይነት የገለፀበት ሁኔታ ይታያል። የዶ/ር ሀይሉን የተውላጠ ስም አጠቃቀም ስንመለከት እኔ-እኛ-እኔ በማለት ሁለቱንም አካሄዶች በመለዋወጥ የመጠቀም ችሎታ እንዳለው የቀረበው መረጃ ያመላክታል።

በሌላ በኩል ደግሞ ‹‹እኔ›› እና ‹‹እኛ›› የሚሉትን ተውላጠ ስሞች በቀጥታ ሳይሆን በማሰሪያ አንቀጹ ውስጥ በመጠቀም ሀሳባቸውን ከእኛ ወደ እኔ በመለዋወጥ ሲጠቀሙበት ይስተዋላል። ለአብነት ተከታዩን እንመልከት፡-

> መልካሙ፡ መቼም የጉዳዩ አሳሳቢነት ምንም ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ አልመሰለንም። በጣም አሳሳቢነቱ ይሰማኛል። ደሞ በጣም የሚያሳስበኝ ሜቶዶሎጂው ነው። እንዴት እንግባባ ምን ብንል እንግባባለን፣ ምን ባንል ደግሞ አንግባባም የሚለው ነገር ያሳስበናል። (አጠመ.006፣ መስመር 44-47)

የመልካሙ ንግግር ከ‹‹እኛ→እኔ›› የሚል አካሄድ ሲኖረው ተውላጠ ስሞቹን በቀጥታ ሳይሆን በማሰሪያ አንቀጹ ውስጥ የተገለፀ ሲሆን፣ የራሱንና የሌላውንም ስሜት ለማሳየት የሞከረበትን ሁኔታ ያሳያል። ሆኖም ግን የራስንና የጋራ ስሜትን በመግለፅ በኩል ሀሳቡን ግላዊና የጋራ አድርጎ ለማቅረብ ከእኛ ወደ እኔ የሚያደረገው አካሄድ ለመግለጽ የፈለገውን ጉዳይ በትክክል የማሳየት አቅሙን ተፈታትኖታል። በአጠቃላይ /እኔ→ እኛ፣/እኛ→ እኔ/ የሚሉትን ተውላጠ ስሞች በማቀላቀል የሚጠቀሙት በስራ ልምዳቸው ከፍ ያሉት ወንዶች ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ሴቶችና ወንዶች ሲጠቀሙበት አይታዩም።

ሌላው ተቀባይነትንና ድጋፍ ለማግኘት በንግግራቸው ዋቢዎችን በመጥቀስ ሃሳባቸውን ሲያቀርቡ ይታያል። በአብዛኛው ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በእድሜና በስራ ልምዳቸው ከፍ ያሉትን ወንዶች አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በእውቀታቸውና በችሎታቸው የተሻሉ ናቸው ብለው የሚያምኑባቸውን ሰዎች የተፀውዖ ስማቸውን በመጥራትና እነሱን ዋቢ በማድረግ ሃሳባቸውን ሲያቀርቡ ይታያል። ለምሳሌ፡-

> ....ከጋሽ ከበደ ጋር ነው ሀሳቤ የሚስማማ(ሴ) (መስመር 310)
> ...ስለዚህ አሁን እኔ ምንድነው ጋሽ ከበደ ያለውን እቀበላለሁ እስማማለሁ፤ ጋሽ ደበበ ያለውንም እቀበላለሁ ከሌሎቻችሁም በተመሳሳይ(ወ) (መስመር 371-72)
> ...ምንም በቃ አቶ አለሙ ያለው እኮ ነው ኢት ወዝ አርቲፊሻል(ወ) (መስመር 1019)
> ...አሁን አቶ ደበበ እንዳለው ዴሊቬሪ ላይ የሚነሳ (ወ) (መስመር 953)
> ... ጋሽ ከበደ እንዳለው ነው (ወ)(መስመር 727)
> ...የማስቀምጠው ጋሽ አለሙ አሁን ያነሳው ነገር ጠንከር ተብሎ መያዝ ያለበት ይመስለኛል(ሴ) (መስመር 472)
> ...አይሻልም በእውቀቱ? (አኮ 003፣መስመር 359)
> ...እኔ ባለፈው ለምሳሌ ጌትነት ላነሳ እችላለሁ(ወ) (አኮ 003፣ መስመር108-110)

...ኮሚሽን ከሚገቡ ሰዎች ውጭ የሆነ ነበር ያልኩት፡፡ እንደዛ አይደለ?
ጌትነት (ሴ) (አኮ003፣ መስመር 184-185)
...ጋሽ ጌትነትም አስወጥተኸው ነው አይደል?(ሴ) (አኮ003፣ መስመር 541)

በዋቢነት የተወሰዱት አሃዶች እንደሚያሳዩት መምህራኑ ለሚያቀርቡት ሃሳብ ድጋፍና ማረጋገጫ ሲፈልጉ እንዲሁም ሀሳባቸውን በመረጃ አስደግፎ በማቅረብ ተቀባይነትን ለማግኘት የተፀውዖ ስሞችን በመጠቀም በዋቢነት ያቀርባሉ፡፡ እነዚህ የሚያቀርቧቸው ሰዎች በእድሜና በስራ ልምድ ከፍ ያሉ እንደሆነ ‹‹ጋሽ ከበደ፣ አቶ አለሙ፣ ጋሽ አለሙ፣ጋሽ ጌትነት›› የሚሉት አስረጅዎች ናቸው፡፡ ከዚህም ሌላ የተሻለ ግንዛቤ አላቸው የሚሏቸውን አቻዎቻቸውንም በዋቢነትና በድጋፍ ሰጭነት ይጠቅሷቸዋል፡፡ ለምሳሌ፡-

ጌትነት፡- ግን አንዳንድ ነገር ከቶፒኩ ጋር የማይሄድ ነው ወደመጨረሻ ብናደርገው ደስ ይለኝ ነበር፡፡ የ-አፀደን በተመለከተ፡፡
ሮዛ፡- እህ
ጌትነት፡- ታይትሉ የሚለው መጀመሪያ ምንድነው ክላስ መዝጋትን በተመለከተ ነው....
ሮዛ፡- አዎ
ጌትነት፡- ከተወያየ በኋላ ከዛ ግን የተሰጣቸውን ሃላፊነት አያሚሉም ምናምን ይላል፡፡ ስለዚህ ልናደርግ የምንችለው 1.1 ስለአፀደ በላይ ክላስ.....ቢባል ጥሩ የሚሆነው፡፡
ሮዛ፡- እህ
በእውቀቱ፡- ይኸ ነገር የተዘረዘረው ለምን መሰለህ.....
[መቅደስ፡- እህ ማቅለያና ማክበጃ
[ጌትነት፡- ገብቶሃል እኔ የምልህ፣ እላይ ርእስህ በተደጋጋሚ ክፍል የማይገቡ ..... በእንድ ቶፒክ መሆን የለበትም ነው እኔ፡፡...
ሮዛ፡- እህ
መቅደስ፡- እህ..
ጌትነት፡- አይሻልም በእውቀቱ?
በእውቀቱ፡- እሱማ እንዳልከው ነው፤የ-አቀማመጡ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ..... የስትራክቸር ጉዳይ ነው፡፡
ጌትነት፡- ኦኬ ስትራክቸር ነው የሚሆነው
በእውቀቱ፡- አንጂ ሃሳቡ ከአንተ ውጭ አይደለም፡፡ (አኮ003፣ መስመር 334-364)

በዋቢነት የተወሰደው ቅንጫቢ ድስኩራዊ አሃድ እንደሚየሳየው ሮዛ የሚወያዩበትን አጀንዳ በንባብ ካቀረበች በኋላ ጌትነት በቀረበው አጀንዳ ውስጥ ያሉት አንዳንድ ርዕሶች ያለቦታቸው መቅረባቸው ትክክል እንዳልሆነና ወደኋላ እንዲሆን ሀሳብ አንስቷል፡፡ ጌትነት ላቀረበው

ሀሳብ ሰብሳቢዋ እና መቅደስ ጭንቅላታቸውን በማወዛወዝ ‹‹እህ›› ከማለት ውጭ ትክክል ነው አይደለም የሚል ምላሽ ያልሰጡበት ሁኔታ ሲሆን በእውቀቱ ግን ጉዳዩ የቀረበበትን ምክንያት ለጌትነት ለማስረዳት ሞክሯል። በዚህ ሂደት ሮዛና መቅደስ ሀሳባቸውን በግልጽ አለማቅረባቸው ምናልባትም ስለጉዳዩ ያላቸው ግንዛቤ አናሳ እንደሆነ ጌትነት የተረዳ ይመስላል። ምክንያቱም ሀሳቡ ውሳኔ እንዲያገኝ ‹‹አይሻልም በእውቀቱ?›› በማለት ጌትነትን መልሶ ድጋፍ እንዲሰጠው መጠየቁና ከዚህም በተጨማሪ ሁለቱም ‹‹የስትራክቸር ጉዳይ ነው።›› በማለት በሃሳቡ መስማማታቸው በእውቀቱ ከእነሮዛ የተሻለ ግንዛቤ እንዳለው አመላካች ነው።

ከተወሰዱት መረጃዎች እንደምንረዳው ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ለሚያቀርቡት ሃሳብ ድጋፍም ሆነ ማረጋገጫ የሚጠይቁትና ዋቢ የሚያደርጉት ወንዶቹን አንጂ ሴቶቹን ሲጠቅሱ አይታዩም።

በአጠቃላይ የተውላጠ ስሞችን አጠቃቀም ስንመለከት ከፆታና ከእድሜ አንፃር ልዩነት እንዳለ መረጃው ያመለክታል። ይኸውም ‹‹እኔ›› የሚለውን በአብዛኛው በመጠቀም የራስን ማንነት የሚገልጹት በስራ ልምዳቸው ከጀማሪ እስከ መካከለኛ ደረጃ ያሉ ወንዶችና እንዲሁም በስራ ልምዳቸው ከፍ ያሉት ሴቶች ናቸው። በተለይም በኢመደበኛ ውይይት ላይ ሴቶች ‹‹እኔ›› በማለት በነገሮች ላይ ያላቸውን ስሜት፣ ያዩትንና የሰሙትን ለመግለፅ ይጠቀሙበታል። በሌላ በኩል ግን በስራ ልምዳቸው ከፍ ያሉት ወንዶች በአብዛኛው ንግግራቸው እኔ→እኛ/እኛ→እኔ የሚል የተቀላቀለ አካሄድ ይከተላሉ። ከዚህ በተጨማሪም ወንዶችም ሆኑ ሴቶች የተፀውዖ ስምችን በመጠቀም በሚያቀርቡት ሀሳብ ተቀባይነትንና ድጋፍን እንዲያገኙ ለማድረግ ሲሞክሩ ይታያል። በዚህም በዋቢነት የሚጠራው የተፀዎዖ ስም (ፆታ) የወንዶች እንደሆነ መረጃው ያመለክታል።

4.3.1.2 ምፀት

ምፀታዊ አገላለፅ በአግባቡ ከቀረበ ተደማጭነትን ለማግኘት የሚያስችል የንግግር ጥበብ እንደሆነና ከንግግሩ አውድ የሚወጣ ከሆነ ግን ወዳልተፈለገ አቅጣጫ ሊወስድ እንደሚችል ፌርክላፍ (1992) ያስረዳሉ። ከዚህም በመነሳት የቀረቡትን ድስኩራዊ አሃዶች ስንመለከት በተለይ በመደበኛ ውይይት ምፀታዊ አገላለፅ በስፋት የቀረበበት

ሁኔታ ያልታየ ቢሆንም፤ የቀረቡትንም ቢሆን ስንመለከታቸው አቀራረባቸው ጠንካራ ሳይሆን ለስለስ ያሉ ናቸው። ለአብነት የሚከተሉትን እንመልከት፤

> አበበ፡- ...የሁለቱ ፕሮግራሞች ልዩነት፣ መንፈሱ አቶ አለሙ አሁን ባለው መልኩ እስካሁንም አልሆነም፤ ተባብሮ በውይይት እንደሰለጠነ ሰው መስራት (አባሪ ሁለት አኮ 002፣ መስመር 29-31)።

በዚህ ላይ ሰብሳቢው የማሳሰቢያውን መንፈስ ሁሉም እንደሚረዳው፣ ችግሩ ከአሁን በፊት እንደሌለና በትብብር እስካሁን ድረስም እንደሚሰራ ‹‹እንደሰለጠነ ሰው...›› በማለት በምፀታዊ አገላለፅ በመጠቀም ተሰብሳቢውን ጎሸም በማድረግ ማሳሰቢያውን አቅርቧል። ሰብሳቢው በምፀታዊ አገላለጹ ማስተላለፍ የፈለገው ተሰብሳቢዎቹ ችግር ካለ በውይይት መፍታትና ተባብሮ መስራት የሰለጠነ ሰው ባህርይ እንደሆነና እነሱም የተማሩ በመሆናቸው ውይይቱን በተገቢው መንገድ በማካሄድ ውጤት ላይ መድረስ እንደሚጠበቅባቸው ለማሳየት ተጠቅሞበታል።

> ፋሲል፡- አለ ጋሽ ደበበ፣ ኦኬ፣ አናግሮኝ ስለነበር። ጋሽ ከበደ ደግሞ ሰለሞንን አናግሯል። እና እዚህ ላይ ውብነሽ ሚስአንደርስታንድ አድርጋቸዋለች ብዬ አስባለሁ። ኮርሶችን ምናምን። 002 ኤንድ ..... ትምህርት ክፍል የሚሰጥልን ሰው እንጋብዛለን። ....፣ ወዘተ. እነዚህን የተረዱት እነሱ ሁለተኛ ውብነሽ የተረዳችው እነዚህ ኮርሶች ከፋካሊቲያችንም አስወጣችኋቸው፣ ከሶሻል ሳይንስ ምናምን ነገር ወጡ። ዊች ሚንስ ከእኛ ፕሮግራም ወጥተው እንደለቀቅናቸው አይነት ነገር ነው የተሰማቸው፤ ያለኝ ነገር ማለት ነው። እና በመካከላችን ፊት ለፊት መነጋገር ባይኖር እነዚህን ኮርሶች ከእኛ እንዳስወጣናቸው፤ ዊች ሚንስ እናንተ ካልቻላችሁ ለምን ወደእኛ አታስጠጓቸውም አይነት ነገርም ይመስላል ክሊርሲ ለመነጋገር። ከጋሽ ደበበ ጋር በዚህ ትናንት ተነጋግረናል። ወደውጭ ወደውጭ የሚሉ ኮርሶችን ወደዲፓርትመንታችን፣ ካልቻልንም ደግሞ ወደፋካሊቲያችን የማስጠጋት ስራ ነው የሰራነው። እና እነዚህ ኮርሶች በትናችኋቸዋል የሚል ነገር፣ ነገር ነው ያለው። እዚህ ጋ ሚስአንድርስታንዲግ አለ የምለው፣ ሌሎች ጓደኞቼም ሊያነሱ ይችላሉ። ከዛ ተነስቼ ግን ካሪክለሙ ለምን ሪቫይዝድ ማድረግ አስፈለገው ወደሚለው ነገር ስመጣ...(አባሪ ሁለት አኮ 002፣ መስመር 45-58)።

ፋሲል በገለፃው ‹‹ምናምን... ምናምን ነገር...አይነት ነገር ነው›› በማለት በተደጋጋሚ ይገልፃል። በዚህም (ምናምን) የሚለው ቃል ውብነሽ የተረዳችውና ለመምህራኑም ያስረዳችው ጉዳይ ትክክል እንዳልሆነ የሚገልጽ ሲሆን፣ ሀሳቧ ፍሬ የሌለው አድርጎ

ለማሳየትና ለማጣጣል የገባ ቃል ይመስላል። ፋሲል ከደበበና ከከበደ ጋር በተነጋገሩትና ባገኙት መረጃ መሰረት የ001 ትምህርት ክፍሎችን ፍላጎት መረዳቱን መሰረት በማድረግ ጉዳዩን የሁሉም መምህራን ፍላጎት እንደሆነ ‹‹ለምን ወደእኛ አታስጠጓቸውም አይነት ነገርም ይመስላል›› በማለት በምፀት ገልጿል። በዚህ ገለፃው ‹‹አይነት ነገርም ይመስላል›› የሚለው በጥቅሉ አሉታዊ ስሜት ለማንፀባረቅ የተጠቀመበት ምፀታዊ አገላለፅ ሲሆን (-ም፣ ይመስላል) የሚሉት አጠቃቀሞች ደግሞ አገላለጹ ምፀታዊ እንዲሆን ያደረጉ ናቸው። በዚህም ፋሲል የ001 ፕሮግራም መምህራን ፍላጎት ምን እንደሆነ መረዳቱንና ፍላጎታቸው ደግሞ ትክክል አለመሆኑን ለመግለፅ የተጠቀመበት ኢቀጥተኛ አገላለፅ ሲሆን፣ ሁለት ነገሮች ተንፀባርቀውበታል።

አንደኛው በስርዓተትምህርቱ ማን ይስጣቸው በሚለው እያከራከሩ ያሉትን ኮርሶች የ002 መምህራን ለማስተማር ችሎታው እንደሌላቸው ተደርጎ በ001 መምህራኖች እንደታሰበና ይህን ለመቃወም ያለመ ነው። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የ001 መምህራኖች በካሪክለሙ ላይ የሚከራከሩት ለራሳቸው ጥቅም እንደሆነና ኮርሶቹ ለሌላ ከሚሰጥ ለእኛ ይሰጥ የሚል ድብቅ ፍላጎት እንዳላቸው ለመግለፅና ግን ደግሞ ኮርሶቹን እነሱ ማስተማር እንደሌለባቸው ለመንገር የቀረበ ነው። ‹‹ወደእኛ አስጠጓቸው›› በሚለው (አስጠጓቸው) የሚለው ቃል ኮርሶቹ ጥግ መያዝ የለባቸውም በተገቢው ቦታቸው መቀመጥ አለባቸው የሚል መልዕክት ያስተላልፋል። የፋሲልን ምፀታዊ አገላለፅ ስንመለከት ለስለስ ያለና ግን ደግሞ ማስተላለፍ የፈለገውን መልዕክት ማስተላለፍ የቻለበት ሁኔታ ይታያል።

> አገሬ፡- ... ከዛ ውጭ አሁን የሪፖርቱም ነገር ላይ የካሪክለሙ ነፀብራቅ ስለሆነ ሪፖርቱ ያ ነው ወደስህተት የመራው ነገር እዛ ጋ ነው፣ፋሲልም ትንሽ፡ ብየ ነው የማስበው። ምክንያቱም ካሪክለሙ የሚለው ሌላ ከሆነና ሪፖርቱ የሚለው ሌላ ከሆነ አሁንም መጣረስ አለ ማለት ነው። እዛ ጋ መስተካከል ያለበት ነገር አለ፣ በዚህ ከተስማማን... (አባሪ ሁለት፣ አኮ 002፣መስመር 319-323)።

አገሬ ፋሲልን መሳሸም የፈለገች ቢሆንም በቀጥታ ከመግለፅ ግን ተቆጥባለች። ‹‹ፋሲልም ትንሽ›› ብላ ልትገልፅ የፈለገችውን ጉዳይ አንጠልጥላ በመተውና በዝምታ ተዳሚው እንዲደርስበት አልፈዋለች። ይህም ጉዳዩን በግልፅና በቀጥታ ከማቅረብ ይልቅ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ መቅረቡን ያሳያል።

ሌላው ምፀታዊ አገላለፅ በስፋት የመጠቀም ሁኔታ ካለ የተግባቦት ሂደቱ ማግባባት ሳይሆን ግጭትን የሚያስተናግድ ይሆናል። ለምሳሌ፦

አበበ፦ ያልተነገረ ነገር ነው? (ለኢሌኒ እጇን ስላወጣች የተጠየቀ ጥያቄ)
ኢሌኒ፦ እኔ እንስማማ ብሎ ባይቋጭ ደስ ይለኛል።
አበበ፦ እንጣላ ብለን እንቋጨው።
ኢሌኒ፦ አይደለም! አይ አይደለም ማሾፊ አይደለም።
አበበ፦ አይ እኔም እውነቴን ነው የምልሽ።
ኢሌኒ፦ እኔን አስጨርሰኝና በኋላ ከዛ አንተ ትጨርሰዋለህ።

(አባሪ 2፣ አኮ.002፣ መስመር 463-68)

ከቀረበው ድስኩራዊ አሃድ እንደምንመለከተው ኢሌኒ የንግግር ድርሻ እንደተሰጣት ‹‹እኔ እንስማማ ተብሎ ባይቋጭ ደስ ይለኛል›› በማለት ንግግሯን ስትጀምር ሰብሳቢው ጣልቃ በመግባት ‹‹እንጣላ ብለን እንቋጨው!›› በማለት የኢሌኒን ሀሳብ በቀልድ መልክ የተቃረነበት መንገድ ነው። ይህን አገላለፅ ኢሌኒ የተረዳችው በአሉታዊ መንገድ እንደሆነ ‹‹እያሾፍኩ አይደለም›› በማለት የሰጠችው ሀይል የተላበሰ ምላሽ ይጠቁማል። የሰብሳቢው ምፀታዊ አገላለፅ በተናጋሪውና በአድማጯ መካከል የተግባቦት ግጭት እንዲፈጠር እንዳደረገ ከኢሌኒ አመላለስ መረዳት ይቻላል።

በአኮ 003 ላይ የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው ደግሞ ምፀታዊ አገላለፅ በመጠቀም በቀጥታ ሳይሆን ጉዳዩን ዘወር በማድረግ የራስን የበላይነትና የሌሎችን ደካማ ጎን ለማሳየት ሲጠቀሙበት ይታያል።

ጌትነት፦ ...መምህር ደግሞ ለምንድን ነው የሚባል። ጋምቤላ አካባቢ ሰርቶ የሚያውቅ ሰው ነው መምህር ማለት የሚወድ። መምህር መምህርት.. አቶ እና ወ/ሮ ለምን አይባልም?ፎርማል አይሆንም (እኮ 003፣ መስመር 411-13)።

ጌትነት የዩኒቨርሲቲ መምህር ‹‹መምህር›› መባል እንደሌለበት በአፅዕኖት የገለፀ ሲሆን እግረ መንገዱን ግን ‹‹መምህር›› የሚለውን ቃል የሚጠቀም ሰው በገጠር አካባቢ የሰራ እንደሆነና ያለውን የደረጃ ልዩነት በመጠቆም የበላይነቱን በኢቀጥተኛ መንገድ ለመግለፅ ሞክሯል።

ጌትነት፡-...መንገደኛ የለ፣ ልብስ ሰፊ የለ፣ ደላላ የለ መፈተን የለብህም፡፡ ...ተማሪ ብቻ ነው፡፡ አስፈራርቶህ ይሆናል አንተን፤ እንጅ አሁን አኛ እንትን አላልንም፤ ክላስ አቴንድ ስላላረክ አላስገባልህም ግሬድ ብየዋለሁ (አኮ 003፣ መስመር 497-515)፡፡

በዚህ ድስኩራዊ አሃድ ደግሞ በእውቀቱ ተማሪውን ማስፈተኑ ትክክል እንዳልሆነና ሙያው የሚጠይቀውን ተግባር አለመፈፀሙን ‹‹...መንገደኛ የለ፣ ልብስ ሰፊ የለ፣ ደላላ የለ መፈተን የለብህም፡፡›› በማለት በምፀት የገለፀ ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር አያይዞም መምህሩ ፈሪ እንደሆነና እሱ ደግሞ ፈሪ እንዳልሆነ ‹‹አስፈራርቶህ ይሆናል...›› የሚለውን ምፀታዊ አገላለፅ በመጠቀም የበላይነቱንም ለማሳየት ተጠቅሞበታል፡፡

እስካሁን በቀረቡት መደበኛ ውይይቶች ላይ አብዛኛዎቹ ምፀታዊ አገላለጾች የፈለቁት በወንዶች ነው፡፡ ሆኖም ግን ሴቶች በበዙበት በኢመደበኛ ውይይት ላይ ከወንዶች ይልቅ ሴቶች ምፀታዊ አጠቃቀምን እንደሚጠቀሙ ቀጥሎ ከቀረበው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡

ሶፍያ፡-...በስመ አብ እያንዳንድሽ ሙልጭ አርገሽ ነው የበላሽው አይደል፡፡
አዳነች፡ አንዳንዶች አላቅማቸው አንስተው አልጨረስንም ይላሉ፡፡
ሶፍያ፡ አይ አዳነች እኔን ለመንካት ነው አይደል፡፡ ማያጣ ጠፍቶብኝ ነው እንጂ፤ ማያያጣ ጠፍቶብኝ ነው ከምር፡፡
ሶፍያ፡- አቶ ዮናስ እንዴት ነው ፕሮግራሙን እንዴት አገኘሽው
አዳነች፡- የጎሪጥ ነው የማየው፡፡ እኔ እንደሆንኩ የጎሪጥ
ዮናስ፡ አሪፍ ነው፡፡ ፕሮግራሙ ከምግቡ ይበልጣል፡፡ ፕሮግራሙ ከምግቡ ይበልጣል፡፡ አሁን ምንድን ነው የሚጠበቀው ያንን ያልጨረስነውን ምግብ ወደብር ተቀይሮ ቢሰጠን፡፡
ሶፍያ፡- እ
አዳነች፡ ሂሳቡ ይሰጠን ወይም ደግሞ ለራት እንድንመጣ ይዘጋጅልን
ሶፍያ፡ እሱን አስተያየት እቀበላለሁ፡፡ አቤም እሱ ነው አስተያየትሽ
አቦነሽ፡ እናመሰግናለን፡፡ በዚሁ ይቀጥል ነው የምንለው፡፡
አዳነች፡- የዛሬ ወርም እንደዚሁ
ሶፍያ፡ እንብላ
መዓዛ፡ ..ፍቅር እስከመቃብር እንዴት ተባፉ ብለሽ
ሶፍያ፡ ተንትነሽ ሰርተሽ እንዳታመጭው
አዳነች፡- ከዛ በኋላ ደግሞ እኛ ኮሜንት ለማድረግ አታስቡ ችግር የለም
ሶፍያ፡-ሬዲ ነሽ
አዳነች፡ አዎ
ሶፍያ፡- ወ/ሪት መዓዛ እንግዲህ እንደ02 ዲፓርትመንት ሃላፊነትሽ...
መዓዛ፡- ኖ አይ አም ኖት
ሶፍያ፡ 02 ዲፓርትመንት በምግብ ዙሪያ እንዴት ነው
አዳነች፡ ይሄ ምግብ እንዴት ተዘጋጀ ብለሽ ይዘሽ ነይ በሚቀጥለው
(አባሪ ስድስት፣ኢመ 001፣ መስመር 60-86)

ከኢመደበኛ ውይይት የተወሰደውን አሃድ ስንመለከተው ከወንዶች ይልቅ ሴቶች ምፀታዊ አገላለፅን በስፋት ይጠቀማሉ፡፡ በቀረበው አሃድ ውስጥ ካሉት አራት ሴቶች መካከል ከአቦነሽ በስተቀር ሶስቱ ሴቶች በተደጋጋሚ ምፀታዊ አገላለፅን በመጠቀም በተካሄደው አውደጥናት ያላቸውን ቅሬታ ‹‹የጎሪጥ ነው የማየው...የዛሬ ወርም እንደዚሁ ...እንብላ...ፍቅር እስከመቃብር እንዴት ተባፈ ... ይሄ ምግብ እንዴት ተዘጋጀ ብለሽ ይዘሽ ነይ በሚቀጥለው›› በማለት በምፀት ገልፀዋል፡፡ በዚህ ውይይት ተሳታፊ የሆነው ዮናስ ‹‹ፕሮግራሙ ከምግቡ ይበልጣል...ያልጨረስነውን ምግብ ወደብር ተቀይሮ ቢሰጠን›› በማለት ፕሮግራሙን ከምግቡ በማነፃፀር እንዲሁም የተዘጋጀው ምግብ ከመጠን አንፃር ተገቢ እንዳልሆነ በምፀት የገለፀ ቢሆንም፤ አገላለፁ ግን ‹‹አሪፍ ነው...ቢሰጠን›› የሚሉትን በመጠቀም ምፀታዊ አገላለፁን በተለሳለሰ ሁኔታ ለማቅረብ ሞክሯል፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከተው በመደበኛ ውይይቶች ላይ በፈለቁት ድስኩራዊ አሃዶቹ የተገለፁት ምፀታዊ አገላለጾች የቀረቡት በአብዛኛው በወንዶቹ ነው፡፡ የሴቶቹ አገላለፅ ደግሞ ቀጥተኛና የመለሳለስ ሁኔታ የታየበት ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን በኢመደበኛ ውይይት ላይ ሴቶች በቁጥራቸው የበላይነት በያዙበት አውድ የሴቶች ንግግር በምፀታዊ አገላለፅ የተሞላ ሲሆን፤ ይህም ሴቶች ከመደበኛ አውድ ይልቅ ሴቶች በበዙበት በኢመደበኛ አውድ ላይ የተለያየ ይዘት ያላቸው ድስኩራዊ አሃዶችን እንደሚያፈልቁ ያመለክታል፡፡

4.3.1.3 አፅንኦታዊ ንግግር

በአፅንኦታዊ ንግግር ላይ በዋናነት መንፀባረቅ ያለበት ለዛ ያለው ንግግር ሲሆን ተናጋሪው በሚናገርበት ጊዜ ለአድማጭ ቅርብ መሆንና የአድማጭን እንቅስቃሴና ስሜት መረዳትን ይመለከታል (ፍራሰር፤1980)፡፡ በዚህ መሰረት በቀረበው መረጃ የተንፀባረቁ አፅንኦታዊ ንግግር ቀጥለን እንመልከት፡፡

አባሪ ሁለት፣አኮ.002፦
ፋሲል፦ ...በግልጽ መናገር ያለብኝ ለምንድን ነው 001 ዲፓርትመንቶችን
ትፈሯቸውአላችሁ በአራት ነጥብ፡፡ የተጠየኩት ኤሲ ላይ ውብነሽም
ስለምትናገር135-37)፡፡
...በአራት ነጥብ ተዕፏል፡፡ እሷም ነበረች የዛኔ በሁለተኛው ቀን ላይ
(መስመር 188-89)
...ለካሪኩለምና ስታንዳርድ ኮሚቴ እንዲላክ ተወስኗል አራት ነጥብ!
...ሁለቱም ኮፒ አድርገን ነው የሰጠነው፡፡ ለምንድን ነው አንዱን ብቻ

የሰጠችው ነው?(መስመር 388)
ውብነሽ፡- ...ለሁሉም ነገር ማብራሪያ ለመስጠት አይደለም!

አባሪ ሶስት፣አኮ 003
ዶ/ር ሀይሉ፡- እዚያ ሊያደርስ የሚችል ሰው በትክክል ከቀረቡት ውስን አማራጮች ውስጥ እንድትመርጡ ነው (አኮ 003፣ መስመር 63-64)
ዶ/ር ሀይሉ፡-ለምንድነው ሃርድሽፕ የማይፈልገው? ለምንድነው?(አኮ03፣ መስመር138)
...ያልኩት ጥያቄና መልስ አይደለም፡፡ ለምን መሰለህ እ-እንደአስተማሪ ጥያቄ እዚህ ጋ አልቀበልም፡፡ ...መሆን ግን አልነበረበትም፤ መሆንም የለበትም፡፡ (አኮ 003፣ መስመር 154-57)
ሮዛ፡- በየተራ አድርጉት (አኮ 003፣መስመር 574)
ሮዛ፡- ያለው አይሰረዝም (አኮ 003፣ መስመር 615-18)
ሮዛ፡- አይደለም መቅደስ ሄዳ ነግራው ሌላ ቦታ ሄደ፡፡ ኤኒ ዌይስ ሌላ ልንለው እንችላለን ምክንያቱ ችግር የለውም (አኮ 003፣ መስመር 313)

በመረጃነት በቀረቡት ድስኩራዊ አሃዶች ለማሳያነት የተወሰዱት አፅንዖታዊ ንግግሮች ስንመለከት ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ለጉዳዩ አፅንዖት ለመስጠት ‹‹ለምን፣ ለምንድን ነው፣ ምንድን ነው፣ አራት ነጥብ፣ በቃ፣ አይደለም›› የሚሉትን አፅንኦታዊ ቃላት ተጠቅመዋል፡፡ በተጨማሪ አንዳንዶች ደግሞ ቃላትን በመደጋገምና አቆራርጦ በመናገር አፅንዖትን ለመስጠት እንደስልት የሚጠቀሙባቸውም አሉ፡፡ ለምሳሌ፡-

ፋሲል፡- ...001 ዲፓርትመንቶችን ትፈራላችሁ በአራት ነጥብ፡፡ አንፈራቸውም እናከብራቸዋለን በአራት ነጥብ አይደለም(አባሪ 2፣ አኮ 002፣ መስመር 137-38)
...የፀደቀው ‹‹ኤሲ ናምበሩ›› ስላለኝ ማለቴ ነው... አለ፣ አለ... አፅድቀነዋል፣ድቀነዋል...ተስማምተናል፣ተስማምተናል፣ተስማምተናል አይደለም (አባሪ 2፣ አኮ 002፣ መስመር 180-88)
...አይደለም! አይደለም! አሁንም አልተረዳሽኝም (መስመር 390)
...ለምሳሌ አሁን ኤክስቴንሽን እኛ የለንም፤ ዲስታንስ የለንም፤ ሰመር የለንም፡፡ እኛ ሬጉላርና ሬጉላር! ነው (አባሪ 2፣ አኮ 002፣ መስመር 19-720)፡፡
ኢሌኒ፡- ...አይደለም! አይ አይደለም ማሾፌ አይደለም (አባሪ 2፣ አኮ 002፣ መስመር 466)
ዶ/ር ሀይሉ፡- ....ለምንድን ነው.....ለምንድን ነው....መሆን አልነበረበትም...መሆን የለበትም (አባሪ 3፣አኮ 003፣ መስመር1232)
ሮዛ፡- ....አይደለም.....አይደለም (አባሪ 3፣አኮ 003፣ መስመር 1269)

ከቀረበው ድስኩራዊ አሃድ እንደምንመለከተው ፋሲል በንግግሩ ‹‹.....አፅድቀነዋል አፅድቀነዋል... ተስማምተናል፣ ተስማምተናል፣ ተስማምተናል..... አለ፣ አለ.... አይደለም፣ አይደለም..... ሬጌላርና ሬጉላር››፤ ዶ/ር ሀይሉ ደግሞ ‹‹ለምንድን ነው...ለምንድን ነው››፤ እንዲሁም ኢሌኒና ሮዛ በተመሳሳይ ‹‹አይደለም...አይደለም›› በማለት ቃላትን በመደጋገም ሃሳባቸውን በአፅንዖት ገልፀዋል። ከዚህም ሌላ ፋሲል ቃልን አቆራርጦ ት-ፈ-ሯ-ቸ-ዋ-ላችሁ በማለት አፅንዖት እንደመስጫ አድርጎ ተጠቅሞበታል።

እነዚህን አፅንኦታዊ ቃላት የተጠቀሙባቸውን ምክንያት ስንመለከት ደግሞ የተለያዩ ሆነው እናገኛቸዋለን። ይኸውም በውይይቱም ሆነ በስራ ቦታቸው ላይ ያላቸውን ድርሻ፣ ሃላፊነት፣ ተቃውሞን፣ ቅድመ ግንዛቤን፣ የበላይነትን ለማሳየት ተጠቅመውበታል። ለምሳሌ አበበ ‹‹...የዚህ ስብሰባ ዓላማ ወደ ኮንሰንሰንስ መምጣት ነው ሌላ ነገር የለውም!›› በሚለው አገላለጹ የሰብሳቢነት ድርሻውንና ሃላፊነቱን ገልጿል። ይኸውም የሰብሳቢው ድርሻ የስብሰባውን አጀንዳ ማስተዋወቅና ከስብሰባው የሚጠበቀውን ውጤት መጠቆም እንደሆነ እንመለከታለን። ‹‹የዚህ›› የምትለዋ ገለፃ አፅንኦት መስጫ ስትሆን ከዚህም ጋር ተያይዞ ‹‹ሌላ ነገር የለውም›› የሚለው ደግሞ ስብሰባው የሚደረስበት ውጤት አንድ ነገር ላይ ብቻ መሆኑን በአፅንኦት ለመግለፅ የገባ ነው።

በተጨማሪም ሰብሳቢው በሌላ የንግግር ድርሻው ላይ ‹‹ያው ፀሀፊ ስለሆንሽ››(መስመር 32 ይመለከቷል) በሚለው አፅንዖታዊ አገላለጹ የቀረበው ‹‹ያው›› የሚለው ቃል የአገሬ ፀሀፊነት የታወቀ መሆኑንና አሁንም ይህን ቃለጉባዔ የመፃፉ ድርሻ የእሷ መሆኑን ለማሳየት ነው። ድምፀቱ አሉታዊ ከመሆኑም በላይ የአገሬንና የሰብሳቢውን የመሪነትና የደጋፊነት ድርሻ ይገልፃል። በዚህም አገሬ ጸሀፊ ስለሆንሽ የሚለውን የተቀበለች አይመስልም ‹‹እ!›› (መስመር 33) በማለት ግርምታ በተላበሰ ድምፅ አሉታዊ መልዕክት የያዘ አፅንኦታዊ ምላሽ ሰጥታለች።

ከአኮ 004 ድስኩራዊ አሃድ የተወሰደውን አፅንኦታዊ አገላለፅ ስንመለከት ዶ/ር ሀይሉ የአስመራጭነት ድርሻውን ‹‹...እንድትመርጡ ነው››(መስመር 64) በማለት በአፅንኦት ከማሳየቱ በላይ ስለምርጫው ባደረገው ገለፃ ላይም የሚነሳ ጥያቄ እንደማይቀበል ‹‹...ጥያቄ እዚህ ጋ አልቀበልም›› እንዲሁም በተሰብሳቢዎቹ የቀረበው ችግር ትክክል እንዳልሆነ ‹‹

መሆን ግን አልነበረበትም፣ መሆን የለበትም›› በማለት ያለውን የሃላፊነትና የስልጣን ደረጃ በአፅዕኖት የገለፀበት ሁኔታ እንደሆነ ይጠቁማል፡፡

በዚህ ውይይት ዶ/ር ሀይሉ ምርጫውን በተመለከተ ካወያየ በኋላ ከስብሰባው ወጥቷል፡፡ በመቀጠል ስብሰባው የተመራው በሮዛ ሲሆን በዚህም ሂደት ሮዛ አፅንኦታዊ አገላለፅን በስፋት ባትጠቀምም አልፎ አልፎ ግን የሰብሳቢነት ድርሻዋን ‹‹በየተራ አድርጉት›› በማለት ሃላፊነቷን ደግሞ ‹‹...ያለው አይሰረዝም›› በማለት የከረረ አፅንኦታዊ አገላለፅ በመጠቀም ለማሳየት ሞክራለች፡፡ ሌላው ተስፋ ስብሰባ እንዲመጣ መልዕክት ልካ እሱ ግን መልእክቱን ሰምቶ ወደሌላ ስብሰባ መሄዱ ትክክል እንዳልሆነ ‹‹...አይደለም መቅደስ ሄዳ ነግራው ሌላ ቦታ ሄደ፡፡ ኤኒ ቄይስ ሌላ ልንለው እንችላለን ምክንያቱ ችግር የለውም፡፡›› በማለት በአፅንኦት የገለፀች ሲሆን በዚህም እንደሃላፊነቷ ያዘዘችውን አለመፈፀሙ ቅር እንዳሰኛት ‹‹ምክንያቱ ችግር የለውም›› የሚለው አፅንኦታዊ አገላለፅ ይጠቁማል፡፡

ከዚህም ሌላ አፅንዖታዊ ንግግርን ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ተቃውሞን ወይም አለመስማማትን ለመግለፅ በስፋት ሲጠቀሙበት ይታያል፡፡ ለአብነት የተወሰዱት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

አባሪ ሁለት፣አኮ 002፡-

ፋሲል፡- ...አይሆንም! አጀንዳውን ሚስ እንዳናደርገው ብዬ ነው፡፡ ለምሳሌ እኔን የጠየቀኝ ለምሳሌ ጋሽ ደበበ ቢኖር ጥሩ ነበረ እሱ ፐርሰናሊ አናግሮኛል (መስመር 41-42)፡፡
...እና እዚህ ላይ ውብነሽ ሚስአንደርስታንድ አድርጋቸዋለች ብዬ አስባለሁ!
(መስመር 46)
...ይሄ ክፍተት እያለ ዝም ብለን ልንቀመጥ አንችልም (መስመር 103)
...አይደለም! አይደለም! አሁንም አልተረዳሽኝም (መስመር 390)
ውብነሽ፡- ...ለሁሉም ነገር ማብራሪያ ለመስጠት አይደለም!
ኢሌኒ፡- ...እኔን አስጨርሰኝና በኋላ ከዛ አንተ ትጨርሰዋለህ (መስመር 468)
...አይደለም! አይ አይደለም ማሾፌ አይደለም(466)

ፋሲል ‹‹...አይሆንም አጀንዳውን ሚስ እንዳናደርገው ብዬ ነው፡፡ ለምሳሌ እኔን የጠየቀኝ ለምሳሌ ጋሽ ደበበ ቢኖር ጥሩ ነበረ እሱ ፐርሰናሊ አናግሮኛል፡፡›› በማለት ሰብሳቢውን በከረረ አፅንዖታዊ ቃል በመጠቀም ተቃውሟል፡፡ ይህም አጀንዳውን ያለመረዳት ወይም

የመዝለል ሁኔታ ያለ ስለመሰለው ነው። ሀሳቡን ላለማቆም ‹‹ለምሳሌ›› በማለት አቅርቧል። ፋሲል ‹‹ ለምሳሌ›› የሚለውን ቃል ተቀባይነትን በማግኘት ንግግሩን በሀይል ለመቀጠልና የጀመረውን ሀሳብ ላለመቀየር እንደ ስልት የተጠቀመበት ነው።

አኮ 003፦
ሮዛ፦ አይደለም! እኔ እንደዛ አይደለም ያልኩህ ...አይደለም እንደዛ አይደለም
ኮምሽን ላይ ያለን ሰዎች እዛ ስለምንመርጥ
ተስፋ፦ ያማ አይሆንም
ጌትነት፦ አይደለም እኔ ክላስ አልተከታተለም ነው የሚለው የእኔ፤
በእውቀቱ፦ በፍፁም ግን ግሬድ የማይገባለት ከሆነ አትፈትነው ነው የሚለው
መቅደስ፦ መፈተን እኮ መብቱ ነው፤ ከተፈነ በኋላ ውጤቱን አንትን ማለት
መብቱ ነው፤መጀመሪያ ማስፈተን ነው ...
ጌትነት፦ መብት የለውም መብት የለውም
ዶር. አበበ፦ ፈተና ከፈተንክ ውጤት ማስገባት የግድ ነው
ተስፋ፦ ኤፍም ቢሆን ምንም ቢሆን ፈተና ከፈተንክ ውጤት ማስገባት ነው
ጋሻው፦ አይደለም
ጌትነት፦ አላስገባም
ተስፋ፦ ስለዚህ ያለው ግሬድ በሙሉ ይሰረዝና
[መቅደስ፦አይደለም
[ጌትነት፦ አይደለም
[ሮዛ፦ ያለው አይሰረዝም
ጋሻው፦ እናገኛለን፤ለምን አናገኝም።
ጌትነት፦ በፍፁም አታገኝም።
በእውቀቱ፦ እ
ጌትነት፦ አዲስ ነገር ሊገኝ አይችልም።

በዚህ ድስኩራዊ አሃድም ሴቶችም ሆኑ ወንዶቹ ተቃውሟቸውን በአፅንዖታዊ አገላለጽ ያቀረቡ ሲሆን፤ አጠቃቀማቸውን ስንመለከት ደግሞ አብዛኛዎቹ ተናጋሪዎች ቃላትን በመደጋገም ያቀረቡበትን ስልት እንመለከታለን። በዚህም ሴቶች እንደወንዶቹ በስፋት አፅንኦታዊ አገላለፅን ባይጠቀሙም አልፎ አልፎ ግን ስሜታቸውን የሚይዝ ጉዳይ ሲገጥማቸው አፅንኦታዊ አገላለፅን የሚጠቀሙ ሲሆን፤ ቃላትንም እንደወንዶቹ በመደጋገም አፅንዖት ለመስጠት እንደስልት እንደሚጠቀሙበትም መረጃው ያመላክታል። ከዚህ ሌላ ግን ሴቶች አከራካሪና አጨቃጫቂ ጉዳይ ሲገጥማቸው ተቃውሟቸውንም ይሁን ድጋፋቸውን እስከመጨረሻው ድረስ ገፍተው እንደማይቀጥሉ በዚህ ድስኩራዊ አሃድ ውስጥ ታይቷል። ይኸውም ሮዛ በመጀመሪያው ውይይት አካባቢ በእውቀቱ ላቀረበው ሃሳብ ተቃውሞ አቅርባ የነበረ ቢሆንም እስከመጨረሻው ገፍታ በማስረዳት ለማሳመን አልሞከረችም (አኮ 003፣ መስመር186-87)። በሌላ አጀንዳ በተማሪ ፈተና ውጤት አያያዝ ጉዳይ በሚወያዩበት ጊዜ ደግሞ አወዛጋቢ፣ አጨቃጫቂና አከራካሪ ሃሳብ የቀረበ ሲሆን በክርክሩ ላይ ሮዛና

መቅደስም በመጀመሪያ በተለሳለሰ ሁኔታ ሃሳባቸውን ሲያቀርቡ ከቆዩ በኋላ ሁኔታው እየተወሳሰበ ሲሄድ ግን እነሱም የተቃውሞ ሃሳባቸውን በከረረ አፅንኦታዊ አገላለፅ አቅርበዋል። ሆኖም ግን ይህ ተቃውሚቸው እስከመጨረሻው ገፍቶ ከመሄድ ይልቅ ከሀሳብ ልውውጡ በመውጣት የአድማጭነት ቦታን ይዘው ይታያሉ (ከመስመር 619-641 ይመለከታል)።

በሌላ በኩል ሁለቱም ዖታዎች በአንድ ጉዳይ ላይ ተመሳሳይ ይዘት ያለው ሃሳብ በተለያየ የአፅንኦት ደረጃ ሲያቀርቡ ይታያል። ለምሳሌ ከአኮ 003 የተወሰደውን ድስኩራዊ አሃድ እንመልከት፡-

> ሮዛ፡- ...ምንድን ነው የሚለው ዘርዘር ተብሎ ቢገለፅ፣ባለፈውም ተነጋግረን ነበር።
> ጌትነት፡- ያለበለዚያማ ሌላም የማይፈለግ ነገር ተጨምሮ ፀድቋል ልንል ነው።
> ሮዛ፡- አዎ እንደዛ ተነጋግረን ነበር
> [ጌትነት፡- ስፔስፋይድ አድርጎ ይኸ በዚህ የሚስተካከል ተብሎ ነው መባፍ ያለበት። (መስመር 226-30)

በሮዛና በጌትነት የቀረበው ሀሳብ ቃለጉባዔ ሲጸድቅ የተሰጠው ማስተካከያ በጥቅሉ ሳይሆን የማስተካከያው አይነትና ዝርዝር ሁኔታው መገለፅ አለበት የሚል ሲሆን ሀሳባቸውን ያቀረቡበትን ሁኔታ ስንመለከት ግን ሮዛ ‹‹ቢገለፅ፣ እንደዛ...ነበር›› የሚሉ ማለሳለሻ ቃላት ስትጠቀም፤ ጌትነት ደግሞ በተቃራኒው ‹‹ያለበለዚያማ፣ ያለበት›› የሚሉትን ጠንካራ አፅንኦታዊ መግለጫ ቃላትን በመጠቀም አቅርቧል። ከዚህ በተጨማሪ በአኮ 004 የቀረበውን ድስኩራዊ ምልልስ እንመልከት፡-

> በለጠ፡- ምን ያደርግልሃል? ዩኒቨርሲቲው ሊያዝናናህ አይደለም አላማው። እንድትቆይ ነው...
> ህይወት፡- ለላጤ እኮ ስቲዲዮ ሁላ ሊሰጥ ይችላል ማለት ነው። ፊር ግን አይደለም። መኝታ ቤት ትጠላለህ እንዴ አንተ። ሳኖል ትጠላለህ ላጤ ስትሆን።...ኧረ ፊር ግን አይደለም። ወይ የስቲዲዮን ነገር ሊያስቡበት ይገባል።
> ህይወት፡- ኧረ ፊር ግን አይደለም
> ዶር. በለጠ፡- እንዴ ፊር አይደለም! .....ምን ታደርጊያለሽ (90-108)

በበለጠና በህይወት መካከል ያለው ምልልስ በተመሳሳይ አቋም ላይ የተመሰረተ ሲሆን ሁለታቸውም በዩኒቨርሲቲው የመኖሪያ ቤት ለማግኘት የቀረበው መስፈርት ፍትሃዊ አይደለም የሚል ሲሆን ይህን ለመግለፅ የተጠቀሙበት አፅንኦታዊ አገላለፅ ግን ይለያያል።

ይኸውም ህይወት ‹‹እኮ፣ ግን›› የሚሉትን ማለዘቢያ ቃላት ስትጠቀም በለጠ ደግሞ ‹‹አይደለም›› የሚለውን ቃል በመጠቀም ሀሳቡን ከረር ባለ አፅንኦት የገለፀበትን ሁኔታ እንመለከታለን፡፡

ከዚህ በተለየ ሁኔታ ግን የድስኩራዊ አሃድ ማቅረቢያ ስልት የሆነውን አፅንኦታዊ ንግግርን ከፍተኛ የስራ ልምድ ያላቸው ወንዶች የበላይነትን ለማሳየት ሲጠቀሙበት አይታዩም፡፡ አፅንዖታዊ አቀራረባቸው ‹‹...ለማለት ፈልጌ ነው››፣ ‹‹እንዲያው ይሄን እኮ አስቡበት ነው ያልኩ፡፡ እንዲህ ይሆናል ይሄን አድርጉ አልወጣኝም፤ አስቡበት፡፡›› የመሳሰሉትን እናገኛለን፡፡ በዚህ አቀራረባቸውም አፅንኦታዊ አቀራረብን በተለሳለሰ ሁኔታ በመጠቀም ውይይቱ አዎንታዊ ሆኖ እንዲቀጥል ለማድረግ ሲጠቀሙበት ታይቷል፡፡ ይህም ከረጅም ጊዜ የስራና የህይወት ልምድ የተገኘ ይመስላል፡፡ በተቃራኒው ግን በስራ ልምዳቸው ከፍ ያሉ ሴቶች የከረረ አፅንኦታዊ አጠቃቀም ሲጠቀሙ ይታያሉ፡፡ ለምሳሌ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በተደረገ አጠቃላይ መደበኛ ውይይት ላይ የተወሰደውን ድስኩራዊ አሃድ በዋቢነት መመልከት ይቻላል፡፡

> አልማዝ፡- ...እኔ አላየሁትም!...ማን ማንን ነው የሚገለው? ለምንድን ነው ...አይቻልም፡፡ ይሄን ቤት የሚያፈርስ ቢመጣ እኛ ዝም ብለን አናይም (አጠመ.006፣ መስመር 95-99)

በዚህ አጠቃላይ ውይይት መጨረሻ ላይ በተከታታይ ከተናገሩት የሶስት ወንዶችና የአንድ ሴት (አልማዝ) ንግግር ለዚህ ጥናት የተወሰደ ሲሆን፣ ወንዶቹም ሆኑ ሴቷ ከፍተኛ የስራ ልምድ ያላቸው ሲሆኑ ሶስቱም ወንዶች ሀሳባቸውን ያቀረቡት በተለሳለሰ ሁኔታ ሲሆን የአገሬ አቀራረብ ግን ከረር ያለ አፅንኦት ያለበት እንደሆነ ‹‹ለምንድን ነው፣ ማን ማንን ነው፣ አይቻልም፣ ዝም ብለን አናይም...›› የሚሉት አገላለፆቿ አመላካች ናቸው፡፡ አልማዝ ከፍተኛ የሕይወትና የስራ ልምድ ያላት ስትሆን ለዚህም በንግግሯ ከቀዳማዊ ሀይለስላሴ ዘመነ መንግስት ጀምሮ ያለውን ሁኔታ እንደምታውቅ በንግግሯ የገለፀች ሲሆን ይህም ከፍተኛ የስራ ልምድ እንዳላት ማሳያ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ከመስክ ማስታወሻ የተወሰደው መረጃ እንደሚያመለክተው በዩኒቨርሲቲው በአገር አቀፍ ደረጃ በተካሄደ አውደ ጥናት ላይ እንደታየው ብዙ ሴቶች

የታደሙ ቢሆንም ሀሳብ በመስጠት ግን ተሳታፊ አልነበሩም። ከነበሩት ሴቶች መካከል ሶስት ሴቶች በተደጋጋሚ እጃቸውን ቢያወጡ ድርሻ ሳይሰጣቸው ከቆየ በኋላ በአውደ ጥናቱ መጨረሻ ላይ ከተሳታፊዎች ‹‹ለሴቶች እድል ስጡ›› ተብሎ በተሰጠ ማሳሰቢያ መሰረት የተናገረች መምህርት ንግግሯ በአፅዕኖታዊ አገላለፅ የቀረበ ሲሆን፣ የመምህርቷ የንግግር አቀራረብ ምክንያት ካቀረበችው ሀሳብ ስንመለከት የተለያዩ የስራ ልምዶችና ከፍተኛ የስራ ልምድ ያላት ከመሆኑ አንፃር የመጣ በራስ መተማመን ሲሆን ሲችል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከቡተቃ የተወሰደው መረጃ እንደሚጠቁመው ሴቶች ሀይል በተላበሰ ሁኔታ ንግግር የሚያደርጉት የተናቁ ሲመስላቸው እንደሆነ ይጠቁማል።

አስረጅ፡-

> ህይወት፡ አብዛኛውን ጊዜ ወንዶች እንዲታወቅላቸው የሚፈልጉትን እኔ እንደዚህ አደረኩ፣እንደዚህ ሰራሁ፣ እኔ እንደዚህ ቦታ ላይ ነው ያለሁት፣ እውቀት ደረጃቸውን ለማሳወቅ ጥረት የሚያደርጉ ብዙ ናቸው። ሌላው ደግሞ ሴቶችን ስንመለከት አብዛኛዎቹ ስራቸውን በመስራት ሰው በራሱ እንዲያውቅላቸው የሚፈልጉ አሉ። አንዳንዶች ደግሞ ከስንት አንድ ቢሆኑም ራሳቸውን እንዲህ ነን ብለው በማስተዋወቅ እወቁኝ እወቁኝ የሚሉ አሉ። ብዙ ጊዜ እንደነዚህ አይነቶቹ የተናቁ አይነት መስሎ ከታያቸው ማንነታቸውን ለማሳወቅና ለማሳየት ስለራሳቸው ኮስተር ብለው ይገልፃሉ (አባሪ ዘጠኝ፣ ቡተቃ.202፣መስመር 342-49።

እንደህይወት አገላለጽ ስለራሳቸው የሚገልጹት ወንዶች ሲሆኑ፣ ሴቶች ግን ራሳቸውን ማሳወቅ የሚፈልጉት በስራቸው እንደሆነና አንዳንድ ስለራሳቸው የሚናገሩ ሴቶች ቢኖሩም ምክንያታቸው ግን የተናቁ ስለሚመስላቸው ያንን ለማካካስ እንደሆነ ያሳያል። ህይወት ሴት ልጅ ስለራሷ መናገር እንደሌለባት የምታምን ትመስላለች። ምክንያቱም በአገላለጿ ‹‹...እወቁኝ እወቁኝ የሚሉ አሉ› በማለት ስለራሳቸው የሚገልጹ ሴቶችን ትነቅፋለች።

ከቡተቃ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ደግሞ ሀሳባቸውን በአፅንዖት የሚገልጹ ወንዶች ሲሆኑ ሴቶች ግን ሀሳብን ሀይል በተላበሰ መልኩ የማቅረብ ሁኔታ እንደሌለ ተገልጿል ለምሳሌ በቡድ 203፣ መስመር 238-239 ‹‹...በቁጣ ይዤ በሀይል የመናገር ነገር ወንዶች ላይ ታያለሽ። ሴቶች ላይ ግን እንደዛ አይነት ስሜት አላይም(ወ)›› በማለት የተገለጸ ሲሆን ይህም ከምልከታ ከተወሰደው መረጃ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ቢሆንም፣ አንዳንድ ሴቶች አፅንዖታዊ አገላለፅን እንደሚጠቀሙ ከታየው ጋር ደግሞ ልዩነት ይታያል። በሌላ በኩል ደግሞ

ከቡተቃ 202 የተገኘው መረጃ ሴቶች ሃሳባቸውን በአፅዕኖት የሚያቀርቡበት አውድ እንዳለም ይጠቁማል፡፡

ለምሳሌ፡-

> ቢንያም፡ ወንዶችና ሴቶች አንድ ላይ በተሰበሰቡበት ሁኔታ በቁጥርም እኩል ቢሆኑም እንኳ ሴቶች ወንዶችን ዶሚኔት አድርገው ያንን የሚሰራ የሚተገብር ስራ ሰርተው ወንዶችን በንግግርም፣ በማሳመንም፣ በተፅዕኖ ስር አድርገው የመምራት አቅም ችሎታ ነገሮችን የማሳመን ነገር አላቸው ብየ አላምንም፡፡ ነገር ግን የመብት እኩልነት ላይ ወይም እንደዚህ ቀለል አድርገሽ ከፖለቲካ ከምናምን አቀላቅለሽ ተናገሩ ብትይ በጣም ልዩ እንደሆኑ ልንግርሽ እችላለሁ፡፡ ነገር ግን እዚሁ አካዳሚካሊ ግን እስካሁን ከተገነዘብኩት ነገር ካጋጠመኝ አጋጣሚ ሴት ዶሚኔሽን አላየሁም (ቡተቃ 202 መስመር 152159)፡፡

ከቢኒያም ገለፃ እንደምንመለከተው ሴቶች አካዳሚያዊ ጉዳይን መሰረት ባደረጉ ውይይቶች ላይ በቁጥርም እኩል ቢሆኑም እንኳን ወንዶችን በመጫን ስራን በመስራት ወይም በንግግር በማሳመን ተፅዕኖ የማሳደር ችሎታ እንደሌላቸውና ነገር ግን ከዚህ አውድ ውጭ የሴቶች መብትና እኩልነትን ከፖለቲካ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በሚደረግ ውይይት ላይ በንግግራቸው ተፅዕኖ የማድረግ ችሎታ እንዳላቸው መረጃው ይጠቁማል፡፡

ከዚህ በተለየ ሁኔታ ደግሞ ሴቶች በኢመደበኛ ውይይት ላይ ሀይል የተላበሰ አፅንኦታዊ አቀራረብን እንደሚጠቀሙ ቀጥሎ የቀረበው ድስኩራዊ አሃድ አመላካች ነው፡፡

> መዓዛ፡ ዶር ከበደ እኮ ናቸው አስተምረው ጨርሰው ሊወጡ ሲሉ፣ ብርሀነ አይናችሁን ይግለጥላችሁ››ይላሉ
> አዳነች፡ እኔ ግን የማይመቹኝ ሰው ማን ናቸው ዶር. ከበደ ናቸው፡፡
> ማርቆስ፡ ኧረ ባክሽ! አታውቂያቸውም?
> አዳነች፡ ብዙ ኦፖርቹንቲስ ላይ አግኝቻቸው አልወዳቸውም፡፡
> ማርቆስ፡ ዶር ከበደ?
> መዓዛ፡እኔ ደግሞ በጣም ነው የምወዳቸው፡፡ ሲያስተምሩ እኮ... በጣም ጎበዝ ናቸው፡፡ እሳቸው!... (ኢመ. 001፣ መስር 24-31)

በዚህ ኢመደበኛ ውይይት ላይ የሚታየው ድስኩራዊ አሃድ የሴቶቹ አቀራረብ ሲታይ ከመደበኛው ለየት ባለ መልኩ አዎንታዊና አሉታዊ ስሜታቸውን በግልጽና ተፅዕኖ ማድረግ በሚችል መልኩ እንዳቀረቡ ያመላክታል፡፡ የተጠቀሙባቸውን አገላለጾች ስንመለከት ‹‹የማይመቹኝ ሰው...ናቸው፣ አልወዳቸውም፣ በጣም ነው የምወዳቸው›› የሚሉ ሀይል የተላበሱ አገላለጾች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ አፅንዖታዊ አገላለፅን በተመለከተ ከመደበኛና ከኢመደበኛ ውይይት የተወሰዱት መረጃዎች እንደሚያሳዩት በሴቶችና በወንዶች አገላለፅ መካከል ልዩነት አለ። ይኸውም ወንዶች በመደበኛ ውይይት ላይ በንግግራቸው ሃይል በመፍጠር ሃሳባቸው ተቀባይነት እንዲያገኝ አፅንዖታዊ አገላለፅን ይጠቀማሉ። ሴቶችን በተመለከተ ደግሞ አንዳንድ ሴቶች በመደበኛ ውይይት ላይ ልክ እንደወንዶቹ ሃሳባቸውን በአፅንዖት የሚያቀርቡ ያሉ ሲሆን በአብዛኛው ግን ከመደበኛ ውይይት ይልቅ በኢመደበኛ ውይይት ሃሳባቸውን ሀይል በተሞላ ሁኔታ ማቅረብ እንደሚመቻቸው መረጃው ይጠቁማል።

4.3.1.4 ቅድመግንዛቤ

አብዛኛዎቹ ወንዶች በስራ ቦታቸው ያሉና የሚካሄዱ ጉዳዮችን በስፋት የሚያውቁ ሲሆን፤ ሴቶቹ ግን ስለስራ ቦታቸው የስራ ሁኔታ በአብዛኛው ቅድመግንዛቤ የሌላቸው ይመስላል። ይኸውም ወንዶች በሚሳተፉባቸው ውይይቶች ላይ የሚቀርቡ ጉዳዮችን በተመለከተ ያነበቡትን፣ የስራ ልምዳቸውን፣ የሄዱባቸውን አገሮች እና ከተለያዩ ሰዎች ጋር የነበራቸውን ተጋልጦ መሰረት በማድረግ ሀሳባቸውን በመረጃ በማስደገፍ ተቀባይነት ሊያገኝ በሚችል ሁኔታ ያቀርባሉ። ለምሳሌ፦

ሀ. የስራ ልምድን መሰረት በማድረግ

ከበደ፦ .....ይሄን የምልበት እኔ ያለሁበት የራሴን ፕሮግራም ጉዳይ ስለማውቅ ነው ((አጠመ 006፣ መስመር 3-4)

እሱባለው፦ ..... ጉዳይ 2004 ዓ.ም ላይ አንስተነዋል። ምን እናድርግ ይህን ስጋት ለመቅረፍ በሚል ተነስቷል። ...ከዚህ ጋር ተያይዞ ስለብዝሀነት የምለው ነገር አለን...ስለብዝሃነት ስናነሳ እኔ ከማጠናው ጥናት ውስጥ ምናልባት ፊዚክስ (አጠመ 006፣ መስመር፣26-29)

ዶ/ር ሀይሉ፦ መመሪያችን ባይ ዘ ወይ አይከለክለውም። የሌሎችን መምረጥ ይችላል። ግን ከዚህ በፊት ኮምፕሌን ያስነሳብን ነገር አለ። ማለት መመሪያው ባይከለክለውም በአንደርስታንዲንግ እሱን እሊጅብል የሆነ.....(አኮ 003፣ 168-70)

ከበደ፦ይሄ ካሪክለም ከቀረፁት ውስጥ አንዱ እኔ ነኝ (አባሪ ሁለት መለያ ቁጥር 02፣ መስመር 260-260)

አገሬ፦ እኔ አሁን ... የሚለውን ፅጌ ስትሰጥ አይቻለሁ። ..... ገስት አድርጋ ጋብዛለች (አባሪሶስት መለያ ቁጥር 02፣ መስመር 312-314)

አለሙ፦ ...እና አንዳንዴ ዲፓርትመንት መኖር አለበት ብዬ የምከራከረው .....በእኛም በማስተርስ ፕሮግራም ላይ እየተፈጠረ ያለ ችግር ስላለ ነው (አባሪሶስት መለያ ቁጥር 02፣ መስመር። 415-418)

ኢሌኒ፡- ስለዚህ ይሄ ፕሮግራም ሲከፈት የአማርኛ ውስጥ ያሉ የ01 እና 02 ሰዎች ስራ እንዳይፈቱ ብሎም ደግሞ የ02 ባለሙያ በዚህ አካባቢ እጥረት ስለነበረ ያንን ለመሸፈን፡፡ ከትምህርት ክፍሉም ቀጣይነት፣ ለሀገሪቱም ደግሞ ለማበርከት የተከፈተ ነው (አባሪ ሶስት መለያ ቁጥር 02፣ መስመር 483-485)፡፡
እየሩስ፡- በጣም ብዙ ነገር ተስተካክሏል፡፡ የትዳር ሁኔታ እኮ አሁን በጣም ትንሽ ማርክ ነው ያለው፡፡ በፊት እኮ አስር ማርክ ምናምን ነበር ያለው (አኮ 004፣ መስመር 114-115)::

የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በስራ ልምዳቸው ያገኙትን ቅድመግንዛቤ በውይይት ላይ በማቅረብ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ፡፡ በመረጃነት የተወሰዱትን ድስኩራዊ አሃዶች ስንመለከት ሁሉም ወንዶችና ኢሌኒ ወንዶቹ ከፍተኛ የስራ ልምድ ያላቸው ሲሆኑ አገሬና እየሩስ ደግሞ እንደወንዶቹ ከፍተኛ የስራ ልምድ ባይኖራቸውም ያላቸው መጠነኛ የስራ ልምድ አሁን ካሉበት የሃላፊነት ቦታ ጋር ተቀናጅቶ ስለተቋሙ የስራ ሁኔታ ቅድመግንዛቤ እንዲያገኙ እንደረዳቸውና ይህንም በመጠቀም ተግባቦታዊ መስተጋብራቸውን ከፍ እንዳደረገላቸው ያስረዳል፡፡ ሴቶች አብዛኛውን ጊዜ በጉዳዩ ላይ ያላቸው ቅድመግንዛቤ ዝቅተኛ ቢሆንም፣ ግንዛቤው የሚኖራቸው ከሆነና ሀሳቡን ሌላ ሰው ቀድሞ ካላቀረበው እንዲሁም አቅርቦትም በትክክል ያልቀረበ መሆኑን ሲገነዘቡ የቀደመ ግንዛቤያቸውን መሰረት አድርገው እንደሚናገሩ ቀጥሎ ከቀረበው ከሮዛ ንግግር መረዳት ይቻል፡፡

ጌትነት፡- አውቃችሁታል አይደለም አሞላሉን...አበቃ ብሪፍ ማድረግ እችላለሁ እኔ፡፡ ባለፈው ስለነበርኩ፣እንደዚህ እያለ ...(አኮ 003፣ መስር 193-219)
ሮዛ፡- ገብቷችኋል? እዚህ ጋ ከ1.1 እስከ 1.4 ያሉት አሉ፡፡ ስለዚህ እዚህኛው ፊት ... (አኮ 003፣ መስመር 193-219)
ጌትነት፡- ቴብሉስ የምናስገባው?(አኮ 003፣ መስመር193-220)

ይህ ድስኩራዊ አሃድ የፋካሊቲ ዲን ምርጫ ቅፅ አሞላልን በተመለከተ የፈለቀ ዲስኩር ሲሆን በጌትነት ‹‹.....አበቃ ብሪፍ ማድረግ እችላለሁ እኔ፡፡ ባለፈው ስለነበርኩ...›› በማለት በማስረዳት ላይ እያለ ሮዛ እንደሌሎቹ ካዳመጠች በኋላ በትክክል አለማስረዳቱን በመገንዘቧ ምክንያት ‹‹...ገብቷችኋል? እዚህ ጋ ከ1.1 እስከ 1.4 ያሉት አሉ፡፡ ስለዚህ እዚህኛው ፊት ለፊት.....›› በማለት ከአሁን በፊት ያላትን ልምድ መሰረት በማድረግ ስለጉዳዩ ያላትን ቅድመ ግንዛቤ ለሌሎቹ አስረድታለች፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ጌትነት በመጀመሪያ እኔ ግልጽ ማድረግ እችላለሁ ብሎ ሲያስረዳ የነበረ ቢሆንም የሮዛን ገለፃ ተከትሎ ግን እሱም ግልጽ እንዳልሆነለት ‹‹.....ቴብሉስ? የምናስገባው ምንድን ነው?›› በማለት ጥያቄ አቅርቧል፡፡

ይህም ወንዶች የሚያውቁትን ነገር መሰረት አድርገው ሀሳባቸውን ለማቅረብ ፈጣን ሲሆኑ ሴቶቹ ግን ቀድሞ ከመናገር ይልቅ በሌሎች አልተገለፀም ብለው ሲያስቡ ብቻ የሚናገሩ መሆናቸውን ያመላክታል። ይህን ጉዳይ ከቡተቃ የተገኘው መረጃም ሴቶች ሃሳባቸውን የሚያቀርቡት በሌሎች አልተገለፀም ብለው ሲያስቡ እንደሆነና እንዲያውም መናገር የሚፈልጉት ሀሳብ በሌሎች ሲባልላቸው ደስ እንደሚላቸው ተገልጿዋል (ቡድ 202፣ መስመር 69-72 ፤203፣ መስመር 18ን ይመልከቱ)።

ለ. ንባብን መሰረት በማድረግ

> ...አንድ ጊዜ አንድ መጽሀፍ ሳነብ ባልና ሚስት ለምን ይጣላሉ? (ወ)(አጠመ፣መስመር 47-48)
> ...እና ችግራችን...አስፍቶ ከማንበብ የመጣ ችግር እንዳይሆን እጠራጠራለሁ (ወ) (አኮ 002፣ መስመር 274-75)
> ...ሌላው የግራጁየት ፕሮፋይላችን ላይ የሚያሳየው ተማሪዎቻችን የህዝብ ግንኙነት ሆነው ይሰራሉ፣ጋዜጠኛ ሆነው ይሰራሉ የሚል ግራጁየት ፕሮፋይል ላይ አለ የሚል ነው(ወ) (አኮ 002፣መስመር 128-129)
> ...በዛን ሰዓት ንባብ እንዲያውም አድርጌያለሁ...የሚለውን መፅሀፍ አንብቡያለሁ(ወ) (አኮ 002፣ መስመር 265-66)

ንባብን ለወንዶች የቅድመግንዛቤ ምንጭ ሲሆን ለሴቶች ግን ያለው አስተዋፅዖ ዝቅተኛ እንደሆነ የቀረበው መረጃ ጠቋሚ ነው። ከቀረበው ድስኩራዊ አሃድ እንደምንመለከተው ወንዶች ‹‹መጽሐፍ ሳነብ፣ ግራጁየት ፕሮፋይል ላይ አለ፣ ንባብ አድርጌያሁ፣ ...የሚለውን መፅሀፍ አንብቤያለሁ›› የሚሉት አገላለጾች ማንበባቸውን የሚያስረዱ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ‹‹...ችግራችን አስፍቶ ከማንበብ የመጣ ችግር እንደሆነ...›› በማለት ሌሎች እንደማያነቡም ይጠቁማሉ። በእርግጥ ይህ አገላለጻቸው ስርዓተፆታን መሰረት ያደረገ ሳይሆን አብዛኛው ሰው አንደማያነብ ለመግለጽ የተጠቀሙበት እንደሆነ ከድስኩራዊ አውዱ መረዳት ይቻላል። ከዚህ ሌላ ግን ከቀረበው መረጃ እንደምንመለከተው ሴቶች በንባብ ያገኙትን ቅድመግንዛቤ መሰረት አድርገው ሃሳባቸውን ያላቀረቡ ሲሆን፣ ለጥናቱ በተሰበሰቡት ሌሎች ድስኩራዊ አሃዶችም አንድም ሴት በንባብ ያገኘችውን ቅድመግንዛቤ ተጠቅማ ሃሳቧን ስትገልጽ አልታየችም። ይህን ሁኔታ በቡተቃ ላይ ሴቶች አንባቢ እንዳልሆኑና በዚህም በስብሰባ ላይ ሀሳብ የማያቀርቡት ግብዓት ስለሌላቸው እንደሆነ የተገለጸበት ሁኔታ ይታያል።

አስረጅ፡-

> እሱባለው፡- ሴቶች ጋር በአብዛኛው ያለማንበብ ችግር አለ፡፡ እናም ሴቶች ጋ የመግለጹ ሁኔታ ትንሽ ደከም ያለ ሁኔታ አለ፡፡ ምክንያቱም ከንባብ ማነስ የመነጨ ነው ወይ ደግሞ አንድም በንባብ እውቀት ማነስ ነው፡፡ ያለዚያም ደግሞ በዛ በሚነገረው አውድ ውስጥ ከዚህ በፊት ያላቸውን እውቀት ያለማምጣት (ወ) (ቡተቃ. 203፣ መስመር 264-67)

እሱባለው ሴቶች በአብዛኛው ያለማንበብ ችግር እንዳለባቸው በዚህም የግብዓት ችግር ስላለ ሃሳባቸውን በማፍለቅ ሂደት ተፅዕኖ እንዳደረገባቸው የገለጸ ሲሆን፣ በተቃራኒው ደግሞ ሁሉም ሴቶች አያነቡም ብሎ መደምደም ትክክል እንዳልሆነ በመግለጽ የመከራከሪያ ሃሳብ ቀርቧል፡፡

አስረጅ፡-

> መቅደስ፡ ሁሉም ወንዶች እኮ አንባቢ አይደሉም፡፡ የሚያነቡ ሴቶችም አሉ በተለይ በእኛ ደረጃ በእርግጥ ሁሉም ሴትም ሆነ ወንድ የሚያስተምረውን ነገር ያነባል፡፡ አሁን የሚያነጋግረን ከዛ ባለፈ የሚለው ነገር ነው፡፡ እንዲያው በጀንደር ላይ ብዙም ስለሰራሁ ብቻ ሳሆን ሴንሲቲቭ በመሆኔ ስለምታዘብ ሴቶች ከምናስተምረው ባለፈ አናነብም፡፡ በጣም በጣት የሚቆጠሩ ናቸው ጋዜጣ፣ መጽሄት ሌላም የሚያነቡት፡፡ እንደዚሁም ብዙ ወንዶችም ከሚያስተምሩት ውጭ የማያነቡ ኢቭን የሚስተምሩትንም የማያነቡ አሉ፡፡ ልዩነቱ ግን በእይታ ስትመለከቸው ሁሉም ወንዶች አንባቢ መስለው ይታዩሻል፡፡ ለምን መሰላችሁ ከሚያነቡ ወንዶች ጋር ስለሚውሉ መረጃ ያገኛሉ ልክ እንዳነበቡ አድርገው ይነግሯችኋል፤ሴቶች ደግሞ ይህ አጋጣሚ የላቸውም እና እኔ ይህ ነው ልዩነቱ ነው ብየ ነው የማስበው (ሴ) (ቡተቃ 203፣ መስመር 307-316)
>
> አልማዝ፡ በሃሳቡ እስማማለሁ፡፡ ግን ሴቶች አያነቡም ብሎ መደምደም ትክክል ነው ብየ አልወስድም (ሴ) (ቡተቃ 203፣ መስመር 317-318)

ከመቅደስና ከሮዛ አገላለጽ እንደምንመለከተው ሴቶችም ሆኑ ወንዶች የሚስተምሩትን የሚያነቡ ሲሆን ከዚህ ሰፋ ባለ የተለያዩ ጽሁፎችን በማንበብና በዚህ የሚገኝን ቅድመ ግንዛቤ በተመለከተ በወንድና በሴት መካከል ልዩነት እንዳለ ይጠቁማል፡፡ ይኸውም አብዛኛዎቹ ወንዶች የማንበብ ልምድ እንዳላቸው፣ የሚያነቡ ሴቶች ደግሞ ጥቂት እንደሆኑና አብዛኛው ሴት ግን ከሚያስተምሩት የትምህርት አይነት ያለፈ ነገር የማንበብ ልምዳቸው አናሳ እንደሆነ መረጃው ይጠቁማል፡፡ ቢሆንም ግን የሚያነቡ ወንዶችም እንዳሉና እነዚህ ወንዶች ግን ከአንባቢ ወንዶች ጋር ባላቸው ተግባቦታዊ መስተጋብር አማካኝነት የሚያገኙትን ቅድመ ግንዛቤ በመጠቀም አንባቢ መስሎ የመታየት አጋጣሚ ያለ

በመሆኑ ሁሉም ወንዶች አንባቢ ናቸው ብሎ መናገር እንደማይቻል ከቀረበው መረጃ መረዳት ይቻላል።

ሐ. ከተለያዩ ቦታዎችና ሰዎች ጋር ባለ ተጋልጦ

> ሰሎሞን...ስቱዲዮ ለማስተርስ ተማሪ ነው። ለምሳሌ ውጭ ስትሄዱ ስቱዲዮ የሚባል ነገር አለ። ስቱዱዮ ትገባለችሁ። ሌላ ነገር አይደለም። በቃ ስቱዲዮ አላማዋ(ወ) (አኮ 004፣ መስመር 145- 46)
> ጌትነት... ጎንደር ያየሁት ኤክስፐሪያንስ አምና ማድረግ ነበረብን። ፕሮባብሊ ለማ ነው ማድረግ የሚገባው፤ የመጀመሪያ የየፊሊዱ ግራጁቶችን (ወ) (አኮ 003፣ መስመር 1125-32)
> መልካሙ፡- .....እንዲያው አምልኮትን እንተውና አሁን ዛፍ በኢትዮጵያ እና በአለም አሳሳቢ ነገር ሆኗል። አንድ ፊረንጅ እንድ ጊዜ እኛን ልታሰለጥን የመጣች ልጂ የኢትዮጵያን ዛፍ ሰላም በይልኝ ብላኛለች ብላ እዚህ ግቢ ያለውን ዋርካ ሰላም ስትል አይቻለሁ። ... እና እንዲህ እንዲህ ያሉ ነገሮች (ወ) (አጠመ 006፣ መስመር 51-59)

ለጥናቱ በተወሰዱት ድስኩራዊ አሃዶች ወደተለያዩ አገሮች በመሄድና ከተለያዩ ሰዎች ጋር በመገናኘት ያላቸውን ቅድመግንዛቤ መሰረት በማድረግ ሀሳባቸውን ያቀረቡ ጥቂት ወንዶች ናቸው። ይህም መረጃው ከሰዎች ጋር ባለ ተጋልጦና የተለያዩ ቦታዎችን በማየት የሚገኘው ቅድመግንዛቤ ለሴቶች ብቻ ሳይሆን ለአብዛኛው ወንዶችም ተደራሽ አለመሆኑን ያመለክታል። ሆኖም ግን የተለያዩ ቦታዎችን በማየትና ከተለያዩ ሰዎች ጋር በነበረ ግንኙነት አማካኝነት የተገኘን ቅድመግንዛቤ በመጠቀም ሃሳብ በመግለጽ ሂደት ወንዶች የተሸሉ እንደሆኑ ከሰሎሞን፣ ከለማና ከመልካሙ አገላለጽ መረዳት ይቻላል። በሌላ በኩል ደግሞ ወንዶች ውጭ አገር ሄደው ከተማሩ በተለያዩ አጋጣሚዎች በተደጋጋሚ የተማሩበትን ዩኒቨርሲቲና ከተማ የሚጠሩ እንደሆነ፣ ሴቶችም ይህ የቅድመግንዛቤ ምንጭ ሊኖራቸው የሚችል ቢሆንም እንደወንዶቹ መግለፅን እንደጉራ ስለሚቆጥሩት መግለጽ እንደማይፈልጉ ከቡተቃ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።

አስረጅ፡-

> ወንዶችና ሴቶች ውጭ አገር ሂደው ቢማሩ፣ በማንኛውም ወሬም ሆነ ስብሰባ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የተማሩበትን ከተማ፣ ዩኒቨርሲቲ በተደጋጋሚ ሊያወሩ ትሰሚያለሽ። ሴቶች ደግሞ ጉራ ነው የሚመስላቸው። ስብሰባም ከሆነ ስለተሰበሰቡበት ጉዳይ ነው የሚያስቡት አንጂ ራሳቸውን የማስተዋወቅ እንትን የላቸውም (አባሪ ሰባት፣ቡተቃ 203፣መስመር 364-78)

በሌላ በኩል ደግሞ በመድረክ ላይ የሚታዩ የቅድመ ግንዛቤ ክፍተቶች በመሙላት ውይይቱ እንዲቀጥል ከፍተኛ ሚና ያለው ሰብሳቢ ነው። በዚህ ጥናት የተወሰዱት መረጃዎች ስብሰባን በመምራት ሂደት በመድረክ የሚፈጠርን የቅድመግንዛቤ ክፍተት ከመሙላት አንፃር ስርዓተፆታዊ ልዩነት እንዳለ ይጠቁማሉ። ለምሳሌ በአኮ 002 ፋሲል ካሪክለሙን ሪቫይዝድ ማድረግ የእሱ ሃላፊነት ብቻ አድርጎ መውሰድ እንደሌለበትና የ001 ፕሮግራም መምህራንም በፕሮግራሙ ሚና እንዳላቸው ሰብሳቢው (አበበ) የሚከተለውን ግንዛቤ ለማስጨበጥ ሞክሯል።

> [አበበ፡- ይሄ ካሪክለም፣ ሶሪ ተሰርቶ የነበረው በ001 ትምህርት ክፍል ስለነበረ ነው። እና ሁሉም አእምሮው ውስጥ ሊኖር ይችላል ይህ ጥያቄ ለምንድን ነው መቀየር ያስፈለጋቸው? የሚለውን። (አባሪሶስት መለያ ቁጥር 02፣መስመር 59-61)

ሰብሳቢው ፋሲልን በማቋረጥና ጣልቃ በመግባት ካሪክለሙ መጀመሪያ የተሰራው በእነሱ እንደሆነና በዚህ ምክንያት ጥያቄያቸው ተገቢ እንደሆነ አቅርቧል። ‹‹እና›› የምትለው ቃል ሁሉም ጥያቄውን ቢጠይቅ ተገቢ መሆኑንና ለዚህም ምክንያታዊ እንደሆነ ለማመልከት የገባ ነው። በዚህ ላይ የሰብሳቢው ጣልቃ ገብነት አላማ አለው። ይኸውም ፋሲል ካሪክለሙ በመጀመሪያ በማን እንደተሰራ ያወቀ ስላልመሰለውና በዚህም ምክንያት በትምህርት ክፍሉ የሚጠየቀው ጥያቄ ምክንያታዊ እንደሆነ ለማሳወቅ ነው። ይህም የፋሲልን የቅድመግንዛቤ ክፍተት የመሙላት ተግባር ነው።

ሰብሳቢው በተሰብሳቢው ለሚነሱ ጉዳዮች ትክክለኛ መረጃ፣ ማስተካከያ በማቅረብና የቅድመግንዛቤ ክፍተቶችን በመሙላት ስብሰባውን ወደሚፈለገው አቅጣጫ መምራት ይጠበቅበታል። ለአብነት የሚከተለውን እንመልከት፡-

> ...የሚባለው የኮርስ ባለቤትነት ጥያቄዎች ለምን እንደተነሱ እኔ ልንገራችሁ። እነፋሲልም አይደሉ ያነሷቸው እነዚህን ጥያቄዎች እነፋሲልም አይደሉም ያነሷቸው እነዚህን ጥያቄዎች... የሞጁላር ካሪክለም ሪቫይዝድ ሲደረግ ላስት ይር እላይ ሲፀድቅ ነው፣ ካሪክለም ኤንድ ስታንዳርድ ኮሚቴ ላይ ሲፀድቅ ለመሆኑ 002 ኤንድ ሳይኮሎጂ ማነው የሚያስተምርላችሁ ብሎ ብሄቬራል ሳይንስ ይጠይቃል። ... እስከዛሬ ድረስማ የሚሰጠው ራሱ ፋካሊቲው ነው ተብሎ ተመለሰለት። እና ሊሆን አይችልም ተብሎ ነው እዛ ላይ ተነስቶ የነበረው። በባለሙያ መሰጠት አለበት። ያ ጥያቄ ነው ወደነፋሲል እንዲወርድ

የተደረገው፡፡ ... እና እነዚህ ነገሮች ፖሊሽ አድርጋችሁ ወደ002 አስጠጉ የሚል ሲሆን የባለቤትነት ጥያቄ እየሰፋ እየሄደ ነው፡፡ ስለዚህ ጫናው የመጣባቸው ከላይ ነው፡፡ በዛ መሰረት ግን አሁን እየተስተካከለ የመጣ ነው እንጅ የማስወጣት ስራ አልሰሩም እንዲያውም ማለት ነው (አባሪሶስት መለያ ቁጥር 02፣ መስመር 326-351)፡፡

ለዚህም ኮርሶች በማን ይሰጡ የሚለው ጉዳይ እንዴትና በማን እንደመጣና ነገሩ በነፋሲል አለመምጣቱን ለቤቱ ግልፅ በማድረግ የቅድመግንዛቤ ክፍተትን ሞልቷል፡፡ አበበ የቅድመግንዛቤ ማስጨበጫውን መረጃ ለማስተላለፍ አፅንዖታዊ ንግግር ያደረገ ሲሆን ለዚህም ‹‹ማለት ነው›› የሚለውን አፅንዖት መስጫ ቃል ተጠቅሟል፡፡

በሌላ በኩል ግን በአኮ 003 የቀረበውን ድስኩራዊ አሃድ ስንመለከት በአብዛኛው በውይይቱ ተሳታፊዎች የሚታዩ የግንዛቤ ክፍተቶችን በመሙላት የሚሳተፉት ተሰብሳቢዎቹ ናቸው፡፡ ሮዛ እንደሰብሳቢነቷ ለምታቀርባቸው አጀንዳዎች ማብራሪያ ከመስጠት ይልቅ ጥያቄ የመጠየቅና ሌሎቹ ሃሳብ ሲሰጡ ‹‹እህ›› የሚል መከታተያ ቃል እና አጠር አጠር ያሉ ንግግሮችን በማፍለቅ ላይ የተመሰረተ ድስኩራዊ ተግባቦት ማድረጓ በጉዳዩ የቅድመ ግንዛቤ ክፍተት እንዳለ አመላካች ነው፡፡

ዋቢ፡-

ሮዛ፡- የመምህር ጉዳይ ነው ሌላ፤ ... በህመም ምክንያት ወደውጭ ወደሀገሩ ሂዷል ለመታከም፡፡ ... ተመልሶ ሊያስተካክል እንደሚችል ነበረ...
ሮዛ፡- እና ደመወዝ ይከፈለዋል? ወይስ ምንድን ነው የምናደርገው?
ሮዛ፡- ምን?
ሮዛ፡- እህ
ሮዛ፡- እኛ ዝም ብለን ቁጭ እንበል?
ሮዛ፡- ለማን?
ሮዛ፡- አዎ
ሮዛ፡- ለነማን?
ሮዛ፡- ይቅር?
ሮዛ፡- እሽ ሌላው ኩንትራት ማረዘም ነው፡፡ . አይ ኮንትራ የማይራዘም ከሆነ ያለብኝ ራሱ ለመመለስ ጊዜው አይበቃኝም ክሊር ለማድረግ
ሮዛ፡- ለራሷ ሌላ ስራ የምታፈላልግበት ምናምን እንደሆነ ነው፤ እሷ የነገረችን ኢንፎርሜሽን ነው እንግዲህ፡፡
ሮዛ፡- እህ
ሮዛ፡- እንዲራዘምላት መጠየቅ አንችልም?
ሮዛ፡- ኮሚሽን አይያዝም አይደል? ... (አኮ003፣መስመር1065-1119)

በቀረበው መረጃ ሮዛ ሁለት አጀንዳዎችን ያቀረበች ሲሆን ጉዳዮቹን ለመድረኩ ካቀረበች በኋላ የእሷን ድስኩራዊ አፍልቆት ለብቻ ስንመለከት በአብዛኛው ጥቂያዊና እህ የሚል

የመከታተያ ቃል ሲሆን፣ እንደሰብሳቢነቷ ሊኖራት የሚገባው ቅድመ ግንዛቤ ባለመኖሩ ለተሰብሳቢዎቹ የተብራራ መረጃና የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ አልቻለችም። መረጃ በመስጠትም ሆነ የውሳኔ ሀሳብ በማቅረብ ጉዳዩ እንዲቋጭ ያደረጉት ቅድመ ግንዛቤ ያላቸው ወንዶች እንደሆነ ከአኮ 003፣ መስመር 2065-1119 ያለውን ሙሉ ድስኩራዊ አሃድ መመልከት ይቻላል።

ከዚህ በተጨማሪ ሴቶች በመደበኛ የአካዳሚክ ኮሚሽን ውይይት ላይ በአብዛኛው ሀሳባቸውን በእርግጠኝነት ‹‹እንዲህ ነው›› ብለው ከማቅረብ ይልቅ ‹‹አይደል?›› በማለት በጥያቄ መልክ ሲያቀርቡ የታዩ ሲሆን ቀጥሎ ለማሳያነት የቀረበው ከአኮ 003 የተወሰደው የሮዛ ንግግርም ይህ ባህርይ ይታይበታል።

> ‹‹...አይ ነው የምትሆነው አይደል? (መስመር 233)...እንዲሰጣቸው።የቃል ማስጠንቀቂያ በፅሁፍ ነው እንዴ ያልነው እኛ? የቃል ማስጠንቀቂያ ነው አይደል? (መስመር 392-93) ...አቶ ተስፋ አኮ 23 ብለህ ቀን ምናምን ፅፈሃል አይደል? (መስመር 456) ...የሰከንድ ሴሚስተር ኮርስ በሙሉ ነው አይደል ያልወሰደ? (መስመር 516)...ጋሽ ጌትነትም አስወጥተኸው ነው አይደል? (መስመር 542)››

ሮዛ የምታውቀውን ነገር በጥርጣሬ ‹‹አይደል›› በማለት ከማቅረቧ በተጨማሪ ስብሰባውን በመምራት ሂደት ለምታቀርባቸው ጉዳዮች ቅድመግንዛቤ ባለመኖሩ የተነሳ ተሰብሳቢውን በመጠየቅ ግንዛቤ ለማግኘት ስትሞክር ይታያል። ሮዛ በአብዛኛው የዕለቱን አጀንዳና የሚፀድቀውን ቃለ ጉባዔ በንባብ ከማሰማት ባለፈ የሃሳብ ልውውጧ ‹‹እህ፣ አዎ›› በሚሉ ቃላት የተሞላ ነው። በዚህም ምክንያት የሰብሳቢነት ድርሻዋ በጌትነት የንግግር የበላይነት የተወሰደ እንደሆነ ከድስኩራዊ አሃዱ መረዳት ይቻላል። በዚህ ድስኩራዊ አሃድ የንግግር ድርሻን ከሁሉም ተሳታፊ በላይ ወስዶ የምናየው ጌትነት ሲሆን ለዚህም እንደዋና ምክንያት የሚሆነው ሮዛ እንደሰብሳቢነቷ በአጀንዳነት ባቀረበቻቸው ጉዳዮች ላይ ቅድመግንዛቤ የሌላት በመሆኑ ነው። የሚከተለውን ድስኩራዊ አሃድ በዋቢነት እንመልከት፦

> ሮዛ፦ በህመም ምክንያት ወደውጭ ወደሀገሩ ሂዷል ለመታከም። በአጭር ጊዜ ታክሞ እንደሚመጣ ነበር ነግሮን የሄደ። የሰከንድ ሴሚስተር ኮርሶችንም ቴሲስ አድቫይዝ የሚያደርጋቸውንም ተመልሶ ሊያስተካክል እንደሚችል ነበረ፣ በደብዳቤም በቃልም ነግሮኝ የሄደው፤ አሁን ከሶስት ወር በኋላ ምናምን እንደሚመጣ ነው።
> ጌትነት፦ እህ

ሮዛ፡- እና ደመወዝ ይከፈለዋል? ወይስ ምንድን ነው የምናደርገው?
ጌትነት፡- አድምንስትሬቲቭ ይመስለኛል። ሪፖርት ማድረግ ነው።
[በእውቀቱ፡- አለ እንትን አላቸው።
ሮዛ፡- ምን?
በእውቀቱ፡- ውል የሚይዙት ውል አላቸው። ከዩኒቨርሲቲው ወይም ከትምህርት ሚኒስቴር ኢዱኬሽን ጋር። ስለዚህ የትራንስፖርቱን የህክምናውን ምኑን በተመለከተ እዛ ስላለ፤
ሮዛ፡- እህ
በእውቀቱ፡- እዛው ነው የሚጨርሱት ውል አላቸው።
ሮዛ፡- እኛ ዝም ብለን ቁጭ እንበል?
ጌትነት፡- ኖ ኖ ኮምኒኬት ማድረግ ትችያለሽ።
በእውቀቱ፡- አንቺ ራስሽ ነሽ የምታደርጊው።
ሮዛ፡- ለማን?
ጌትነት፡- ለልጅቱ ለዛች ለዝናሽ፤ ዝናሽ አይደል የሚመለከታት?
ሮዛ፡- አዎ
ጌትነት፡- እሷ ኮምንኬት ታድርጋቸው። ሶስት ወር እንደማይኖር።
ሮዛ፡- ለነማን?
(አባሪ 3፣ አኩ.003፣ መስመር2159-2176)

በዚህ ምልልስ እንደምንመለከተው ሮዛ እንደሰብሳቢነቷ ላቀረበችው አጀንዳ ቅድመግንዛቤ እንደሌላትና ወደስብሰባው ከመምጣቷ በፊት ግንዛቤ እንዲኖራት ዝግጅት አለማድረጓን ያሳያል። ወንዶቹ (በእውቀቱና ጌትነት) ግን በጉዳዩ ላይ በልምድ ያገኙት ቅድመ ግንዛቤ መኖሩን ወይም ቅድመ ዝግጅት አድርገው እንደሚመጡ ከምልልሱ እንረዳለን። ይህ ደግሞ ሴቶች ስብሰባን እንደስራ እንደማይቆጥሩትና ቅድመ ዝግጅት አድርገው እንደማይመጡና በተቃራኒው ወንዶች ለስብሰባ ትልቅ ትኩረት እንደሚያደርጉና ቅድመ ዝግጅትም አድርገው እንደሚገቡ ከቡተቃ የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል።

አስረጅ፡-

ከፍያለው፡ በየትኛውም ስብሰባ ይሁን አንድም ሰው የምናገርበት ከሆነ እና በስብሰባ ፎርም የምሰበሰብ ከሆነ እዘጋጃለሁ። መጀመሪያ ማለት ነው። ከዛ ሰው ጋር ምን መነጋገር አለብኝ፣ ምንድን ነው የማወራው፣ ምን ሊያነሳ ይችላል፣ ይህን ስል እንዲህ ሊል ይችላል እሰከሚለው ድረስ አስባለሁ። ትንሽም ትልቅም ስብሰባ ቢሆን። የጊዜ ማጠር እንጂ ዝግጅቱ ተመሳሳይ ነው። ለአንድ ግለሰብም ብዙም ቢሆን። ከዛ ባሻገር ደግሞ ማጠቃለያ፣ ምናምን እንትኖች አሉ። ያራሱ ፊዞች አሉ። ግን ለእነዛ ሁላ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ምን ላደርግ እንደምችል ቀድሜ ነው የማስበው።
እየሩስ፡ እኔ ግን ተቃራኒ ነገር ነው። ማለት እኔ ስብሰባን እንደስራ ስራየ አድግሬ አልወስደውም። ይህን ያህል አልጨናነቅበትም። በዛው ሰኣት አጀንዳዎቹን ካወኩ በኋላ መናገር ካለብኝ እናገራለሁ (ቡተቃ 202፣ መስመር 15-24)።

የቀረበው መረጃው ወንዶች ወደስብሰባ ከመምጣታቸው በፊት ዝግጅት እንደሚደርጉ ያሳያል። ዝግጅታቸው ደግሞ አንድም ሰው ይሁን ሰፊ ታዳሚ ያለበትም ቢሆን፣ እያንዳንዷን የውይይት ሂደት ቀድመው በማሰብ ሊነሳ የሚችለውን ሀሳብ ሁሉ መሰረት አድርገው እንደሚዘጋጁ መረጃው ያሳያል።

በአጠቃላይ ከቀረበው መረጃ እንደምንረዳው የስራ ልምድ፣ ንባብ፣ ወደተለያዩ አገሮች የመሄድ አጋጣሚና ከተለያዩ ሰዎች ጋር የመገናኘት አጋጣሚዎች ስለተለያዩ ጉዳዮች ግንዛቤ እንዲኖረን እንደሚደርጉና በውይይት ወቅትም በውይይቱ ላይ ስለሚነሱ ነገሮች ቅድመ ግንዛቤ እንዲኖር በማድረግ ሃሳብን በማፍለቅ ረገድ ከፍተኛ ሚና አላቸው። እነዚህን ቅድመ ግንዛቤ ለማግኘት የሚረዱ አጋጣሚዎችን የማግኘትና የመጠቀም እድሉና ልምዱ ያላቸው ደግሞ ወንዶች ሲሆኑ በዚህም መሰረት ወንዶች የሚያገኙትን ቅድመግንዛቤ መሰረት በማድረግ ሀሳባቸውን ሲያቀርቡ፣ አብዛኛዎቹ ሴቶች ግን በተለይም በንባብ ሊያገኙት የሚገባው ቅድመግንዛቤ ዝቅተኛ በመሆኑ በተለያዩ ውይይቶች ላይ ሃሳባቸውን በማፍለቅ ሂደት ተፅዕኖ እንዳደረገባቸው አመላካች ነው። ቢሆንም ይህ ሃሳብ ከቡተቃ ከተገኘው መረጃ ጋር ይኸውም ቅድመግንዛቤ ቢኖራቸው ይህን አንብበን፣ ይህን ሰው አግኝተን፣ እዚህ ቦታ ሄደን ብሎ መናገር ጉራ ስለሚመስላቸው አይናገሩም ከሚለው ጋር የሚጣረስ ይመስላል። ከዚህ በተለየ ሁኔታ ግን በስራ ልምዳቸውም ሆነ በተለያየ መንገድ ቅድመግንዛቤ ሲኖራቸውና ሃሳቡ ካልተገለፀና በትክክል አልተገለፀም ብለው ሲያስቡ ቅድመግንዛቤያቸውን በመጠቀም ሃሳባቸውን እንደሚያቀርቡ ከምልከታ የተገኘው ድስኩራዊ አሃድ ያመለክታል።

4.3.1.5 ድምፀት

የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው አብዛኛዎቹ ወጣት ወንዶች ሀሳባቸውን በንግግር በሚገልጹበት ጊዜ ድምፀታዊ ቃላትን በመጠቀም ሀሳባቸውን ሀይል በተሞላበት ሁኔታ ይገልፃሉ። ለማሳያ ከሚሆኑ አሃዶችን ጥቂቱን እንመልከት፡-

> ...አንተ ባነሳኸው መንፈስ ብቻም ቢታይ የአካዳሚክ ኪሊቲው ምንም ጥርጥር የለውም ይደመሰሳል(መስመር 450-451).....እሱን ካልወሰዱ የሆነ ነገር ይጎላል ምንም ጥርጥር የለውም (ወ)(አከ 002፣መስመር 988-989)።

...ምናልባት የእኔ አባላቶች ከተስማሙ ዌል... (አኮ 002፣ መስመር 1077).....ባህልን ለማጥናት ቋንቋውን የግድ ማወቅ አስፈላጊ... (ወ) (መስመር 93-94)
...እንግዲህ ምናልባት እንዴት እንዳላላየቻቸው ሚስአንደርስታንዲግ የተፈጠረ በዚህ ነው አኮ 002፣መስመር 176).....አሁን የመጣልኝ ሀሳብ ምናልባት ኤኒ ነገር መሄድ እንችላለን (ወ) (አኮ002፣መስመር 1049-1050)።
...ማማረጥማ የግድ ነው (መስመር121).... አይፈልግማ! ሰው አይፈልግም ባይ ዘ ወይ። ለመኖር ያክል ነው እንጅ፤አፓርትመንት ውስጥ ስቱዲዮ አድርገሽ ገስት ሀውስ ማድረግ አይቻልም (መስመር150-51).....የፈለገው ሊሆን ይገባል። ምንም ጥርጥር የለውም(ወ) (አኮ 004፣መስመር136)
...አቴንድ አላረገም ብሎ የሚል ከሆነ አይ ማስተላለፍ የግድ ነው (አኮ 003፣መስመር 909)
... ፈተና ከፈተንክ ውጤት ማስገባት የግድ ነው (አኮ 003፣መስመር 581)

ለአብነት በተወሰዱት ድስኩራዊ አሃዶች ውስጥ ያሉትን ድምፀታዊ ቃላት ስንመለከት ምንም ጥርጥር የለውም፣ ምናልባት፣ ለወደፊት፣ የግድ፣ አይፈለግማ! የተሰኙት ድምፀታዊ ቃላትን እናገኛለን። ይህም በተለይ ወጣት ወንዶች ሀሳባቸውን ድምፀቱ በከረረና ሀይል በተሞላበት መንገድ በማቅረብ የበላይነትን ለማንፀባረቅ እንደሚጠቀሙበት አመላካች ነው። ሴቶቹና በእድሜያቸውና በስራ ልምዳቸው ከፍ ያሉት ወንዶች ግን በአብዛኛው ድምፀታዊ ቃላትን ሲጠቀሙ አይታዩም። ድምፀታዊ ቃላትን ከተጠቀሙ ወንዶች መካከል ለአብነት እንመልከት፡-

...አንድ አይነት ሃሳብ አንድ አይነት ፍላጎት ሲኖር፣ ምናልባት ችግር ካለ ከ001፣ ምናልባት ከ002 ችግር ካለ፣ እ እየተነጋገሩ ያንን እያጠፉ መጠናከር ነው...(ወ) (አኮ002፣መስመር 252-253)

...ምናልባት መጀመሪያ ሀሳቡ እንደተጀመረ ብዙ ነገሮች ይመጡ ነበረ (መስመር 21-22) ...ሌጅስሌሽኑም ስለሚቀየር ምናልባት አሁን የምንከተለው ሂደት የመጨረሻው ሊሆን ይችላል (አኮ 003፣ መስመር 37-38) .....ተጨማሪ መልስ መሆን ያለበት አይመስለኝም። ምናልባት አንደኛ እ አሲስታንስ ፕሮፌሰር የሚለው እ እስካሁን ድረስ አልሆነም ባሉብን እጥረት ምክንያት (ወ) (አኮ 003፣ መስመር 82-83)

...ምናልባት ያች ቤት ለስራ ተፈልጋ ከሆነ ለመምህሩ ትክ ቤት ይለጠዋል የሚል ነገር ቢኖር(አኮ 004፣መስመር 44)

ደበበ፣ ዶ/ር ሀይሉ እና ኤፍሬም ‹‹ምናልባት›› የሚለውን ድምፀታዊ ቃላት የተጠቀሙት በዝቅተኛ ድምፀት ሲሆን፣ አጠቃቀማቸው ሀይልን ለመግለፅ ሳይሆን በቀረበው ጉዳይ ላይ ምክርና መረጃ ለመስጠትና መፍትሄ ለማቅረብ ነው። እዚህ ላይ ወንዶች በእድሜያቸው

እየገፉ ሲሄዱ ሀይል ከተሞላበት ንግግር ይልቅ እንደሴቶቹ የተለሳለሰና ስነምግባር የተሞላበት አነጋገር የማቅረባቸው ምክንያት ከልዩነት ንድፈሃሳብ ጋር በማያያዝ ማየት የሚቻል ይመስላል። ይህም ወንዶች በስነተፈጥሯቸው በሰውነታቸው ያለው ከፍተኛ ሆርሞን በእድሜ እየገፉ ሲሄዱ ዝቅ እያለ ይሄድ ይሆን የሚል ግምታዊ ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል።

4.3.1.6 ስነምግባራዊ ስልት

ስነምግባራዊ አቀራረብን በተመለከተ በሴቶችም በወንዶችም የሚታይ ድስኩራዊ አጠቃቀም ሲሆን፣ በዚህ ጥናት በወንዶችና በሴቶች እንዲሁም በሴቶች ደግሞ በመደበኛና በኢመደበኛ አውድ ስነምግራዊ አጠቃቀማቸው እንደሚለያይ የተገኙት መረጃዎች ይጠቁማሉ። ቀጥሎ ከሁለቱ አውዶች የተወሰዱትን ድስኩራዊ አሃዶች ዋቢ በማድረግ የአጠቃቀሞቹ ልዩነት ቀርበዋል።

ኢመደበኛ አውድ 1፦

አዳነች፡ እኔ ግን የማይመቹኝ ሰው ማን ናቸው ዶር. ከበደ ናቸው።
ማርቆስ፡ ኧረ ባክሽ! አታውቂያቸውም?
አዳነች፡ ብዙ ኦፖርቺንቲስ ላይ አግኝቻቸው አልወዳቸውም።
ማርቆስ፡ ዶር ከበደ?
መዓዛ፡(በመደራረብ) እኔ ደግሞ በጣም ነው የምወዳቸው። ሲያስተምሩ እኮ...
በጣም ጎበዝ ናቸው። እሳቸው!...
አዳነች፡ እህ
ማርቆስ፡ ለምን?
ሶፍያ፡-አንዳንዶች ቃላችሁን ስጡ በእውነት።
አልማዝ፡ (ጣልቃ በመግባት) እናመሰግናለን
[ሶፍያ፡- አቶ ዮናስ እንዴት ነው ፕሮግራሙን እንዴት አገኘኸው
አዳነች፡- የጎሪጥ ነው የማየው። እኔ እንደሆንኩ የጎሪጥ
ዮናስ፡ አሪፍ ነው። ፕሮግራሙ ከምግቡ ይበልጣል። ፕሮግራሙ ከምግቡ ይበልጣል። አሁን ምንድን ነው የሚጠበቀው ያንን ያልጨረስነውን ምግብ ወደብር ተቀይሮ ቢሰጠን።
ሶፍያ፡- እ
አዳነች፡ ሂሳቡ ይሰጠን ወይም ደግሞ ለራት እንድንመጣ ይዘጋጅልን
ሶፍያ፡ እሱን አስተያየት እቀበላለሁ። አቤም እሱ ነው አስተያየትሽ
አቦነሽ፡ እናመሰግናለን። በዚሁ ይቀጥል ነው የምንለው።
አዳነች፡- የዛሬ ወርም እንደዚሁ
ሶፍያ፡ እንብላ
መዓዛ፡ ..ፍቅር እስከመቃብር እንዴት ተባፈ ብለሽ
ሶፍያ፡ ተንትነሽ ሰርተሽ እንዳታመጭው
(ኢመ. 001መስመር፣ 64-75)

የቀረበው ድስኩራዊ አሃድ ከኢመደበኛ አውድ የተወሰደ ሲሆን፣ በዚህ ውይይት ላይ የተሳተፉት አብዛኛዎቹ ሴቶች ሲሆኑ የወንድ ተሳታፊ ቁጥር ሁለት ብቻ ናቸው። በአሃዱ እንደተመለከተው ሴቶች ሀሳባቸውን በመግለጽ ከፍተኛ ድርሻ የወሰዱ ሲሆን፣ የቋንቋ አጠቃቀማቸው ከስነምግባራዊ አቀራረብ አንፃር ሲታይ ‹‹አልወዳቸውም፣ አይመቹኝም፣ በጣም ነው የምወዳቸው፣ የጎሪጥ ነው የማየው›› የሚሉ ሀይል የተላበሱ አገላለጾችን ተጠቅመዋል። በአንጻሩ ወንዶች ደግሞ ‹‹ኧረ ባክሽ! አታውቂያቸውም? ዶር ከበደ? ለምን? ›› የሚሉትን ጥያቄ አዘል አገላለጾችን የተጠቀሙ ሲሆን የንግግር ድርሻቸውም ከሴቶቹ ያነሰ እንደሆነ ያሳያል። ይህ የኢመደበኛ አውድ አጠቃቀም ወንዶች በበዙበት ከሆነ ደግሞ የተለየ ባህርይ እንዳለው ቀጥሎ የቀረበው መረጃ ያመለክታል።

ኢመደበኛ አውድ 2፡-

ከፍያለው፡ እንግዲህ ያላችሁን ሃሳብ እያቀረባችው እንጨዋወት፣ተጫወቱ
ካሳ፡ እኔ ስለ... በጣም ነው የምናመሰግነው። ይሄንን በማዘጋጀታችሁ። የሚያጓጓ ነገር ነው። ... እንዴት ብለን እንደተከታተልን አይታችኋል። በጣም አመሰግናለሁ።
ሊድያ፡ አመሰግናለሁ። እኔ ብዙ የምለው ነገር የለኝም። ... ን በጣም አመሰግናለሁ። በተጨማሪም ደግሞ ለተሳታፊው ምክንያቱም እንዲህ አይነት ተሳትፎ ሲኖር እርስ በርሳችን የመማማር ሁኔታ ከፍተኛ ነው የሚሆነው። ተሳታፊው ዝም ቢል ኖሮ ደባሪ ይሆን ነበር። ያው በዘመኑ ቋንቋ። እና በጣም አመሰግናለሁ ለአስተባባሪውም ።
ዳምጤ፡ እና በጣም የሚገርመው ስለሱ ጥንካሬ ከፊቱ ባይሆንም
ዘወር ብዬ ልናገር። በሌለበት...
ዶ/ር ሲሳይ(ጣልቃ በመግባት)፡ ችግር የለም ሀቁን እስከሆነ ድረስ መናገር መቻል አለብን፣ ፊት ለፊት መናገር መልመድ አለብን።
ዳምጤ፡-...በሚቀጥለውም ሌላ ስልጠና አለ
ተብሏል። በደንብ እንደሚሰጠን ተስፋ እናደርጋለን። በጣም ለሀገራች እሴት ነው ብየ ነው የምገልፀው። እንወድሃለን።
ታደለ፡ እኔ ቦታው ማለትም የስልጠና ክፍሉ አልተመቸኝም። እዛ ክፍል ተምሬበትም ሆነ አስተምሬበት አላውቅም ለመጀመሪያ ጊዜ ነው። ስልጠናውን ማቆም የፈለኩት ገና በመጀመሪያው ቀን ነበር። ግን ሁኔታው ስለተመቸን ጨረስኩት
አስናቀች፡ እኔ የመጀመሪያውን ክፍለ ጊዜ እንደተሳተፍኩ አይደለም መቅረት ማርፈድም አልፈልግም። ...አመሰግናለሁ፡ (ኢመ. 004፣ መስመር1-45)።

በዚህ ኢመደበኛ አውድ ያሉት ተሳታፊዎች ሃያ አንድ ወንዶችና ስድስት ሴቶች ሲሆኑ አብዛኛዎቹ ወንዶችና ሁለቱ ሴቶች ሃሳባቸውን በመግለጽ ተሳትፈዋል። በዚህም አብዛኛዎቹ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ሀሳባቸውን ትህትና በተላበሰ መልኩ የገለጹ ሲሆን

ለዚህም በንግግራቸው መጨረሻ አመሰግናለሁ የሚለውን አገላለጽ ተጠቅመዋል። በዚህ አውድ ታደለ ብቻ ሃሳቡን ከረር ባለ መልኩ ‹‹...አልተመቸኝም...›› በማለት ከመግለጹ በተጨማሪ እንደሌሎቹ ‹‹አመሰግናለሁ የሚል አገላለጽ አልተጠቀመም። በአጠቃላይ በኢመደበኛ ውይይት ላይ ሴቶች የበዙበትና ወንዶች የበዙበት አውድ ሲሆን የወንዶችም ሆነ የሴቶች የቋንቋ አጠቃቀም እንደሚለያይ የቀረቡት መረጃዎ ይጠቁማሉ። ቀጥሎ ደግሞ በመደበኛ አውድ በሴቶችና በወንዶች የሚፈልቀው ድስኩራዊ አሃድ ከስነምግባራዊ አጠቃቀም አንፃር ምን እንደሚመስል እንመልከት።

መደበኛ አውድ

1፡-

ሮዛ፡-.....ግን ለወደፊቱ ምን ምን ነው ማስተካከያ የሚለው ዘርዘር ተብሎ ቢፃፍ ጥሩ ነው (ሴ)
ጌትነት፡-... እሱ ይቀራል(ወ)
ሮዛ፡-...ምን ምን ማስተካከያ ስፔሊንግ ነው! ምንድን ነው የሚለው ዘርዘር ተብሎ ቢገለፅ፤ባለፈውም ተነጋግረን ነበር። አዎ(ሴ)
ጌትነት፡-...ያለበለዚያማ ሌላም የማይፈለግ ነገር ተጨምሮ ፀድቋል ልንል ነው።
ሮዛ፡- አዎ እንደዛ ተነጋግረን ነበር(ወ)
ጌትነት፡-...በዚህ የሚስተካከል ተብሎ ነው መፃፍ ያለበት (ወ) (አኮ003፣ መስመር 223-30)

መረጃው እንደሚያሳየው ሮዛ ‹‹ቢፃፍ፣ ቢገለፅ›› በማለት ሀሳቧን ስነምግባር አዘል የሆኑ ቃላትን በመጠቀም ስታቀርብ ጌትነት ግን ‹‹ያለበለዚያማ፣ ተብሎ ነው መፃፍ ያለበት›› በማለት ሀሳቡን አፅንዖት በተላበሰ ሁኔታ አቅርቧል።

2፡-

ሰሎሞን፡- ዲዛይኑ ውስጥ ስቱዲዮ መጥፋት ነበረበት።
ህይወት፡- ስቱዲዮ ወይ እንደስቶር ምናምን ነበር..
ሰሎሞን፡- ስቱዲዮ ለማስተርስ ተማሪ ነው። ለምሳሌ ከዛ ውጭ ስትሄዱ ስቱዲዮ የሚባል ነገር አለ። ስቱዱዮ ትገባለችሁ። ሌላ ነገር አይደለም። በቃ ስቱዲዮ አላማዋ።
ህይወት፡- ግን እሱን አስተያየት እኛ መስጠት አንችልም አሁን?
እየሩስ፡- የትኛውን?
ህይወት፡- ስቱዲዮችን ለገስት ሀውስ ምናምን ምናምን ወይም ለስቶር
ሰሎሞን፡- አይፈልግማ! ሰው አይፈልግም ባይ ዘ ወይ። ለመኖር ያክል ነው እንጅ፤አፓርትመንት ውስጥ ስቱዲዮ አድርገሽ ገስት ሀውስ ማድረግ አይቻልም። ማንም ልጅ እንዲጫጫበት አይፈልግም።
ህይወት፡- ኧረ ማንም እሽ አይልም (አኮ 104፣ መስመር144-51)

በምሳሌ ሁለት የቀረበውን ድስኩራዊ አሃድ ስንመለከት የመኖሪያ ቤት ጉዳይ የሁሉም አንገብጋቢ ጥያቄ በመሆኑ ሁሉም ስሜታቸውን በመግለጽ የተሳተፉ ሲሆን ሰሎሞን ‹‹ነበረበት፣ በቃ፣ ማድረግ አይቻልም›› በማለት ሃሳቡን ረገጥ በማድረግ እንዳቀረበ ያሳያል። በሌላ በኩል ደግሞ እየሩስና ህይወት ሃሳባቸውን ያቀረቡት ‹‹ምናምን›› እና ‹‹ኧረ›› የሚሉ ማለሳለሻ ቃላትንና በመጠቀም ያቀረቡ ከመሆኑ በላይ ጉዳዩን አስረግጦ ከመናገር ይልቅ በጥያቄ መልኩ ‹‹ማን...እኛ መስጠት አንችልም አሁን?›› በማለት ገልጸዋል። ሴቶች ሃሳባቸውን በሚገልጹበት ጊዜ ስነምግባራዊ አቀራረብ የሚከተሉ እንደሆነና በተቃራኒው ወንዶች ህይል በተላበሰ መልኩ እንደሚያቀርቡ ከቡተቃ የተወሰደው መረጃም ይጠቁማል።

> ቢንያም፡ አሁን እሱ ባነሳው ስብሰባ ላይ የሴቶቹ ቁጥር ብዙ ነበር። ግን ምንድን ነው ሪፖርት አቅርቡ ሲባል ወንዶች ገና ከመጀመሪያው ኖ ማለት ጀመሩ። ይሄ ሀሳብ እንደዚህ ማለት ነው ብለው ተከራከሩ። ሌላው ሴቶቹ ሪፖርት አቅርቡ ሲባሉ በትንሹ አጠር አጠር አድርገው ምንም ሪአክት ሳያደርጉ ተናገሩ። ሌላው ያላቸው ልዩነት ሴቶች ይመስለኛል፣ ይሆናል፣ እንደዚህ ቢደረግ መልካም ነው በማለት ማለሳለሻ ቃላትን ይጠቀማሉ። ወንዶቹ ግን በሚያቀርቡት ጉዳይ ላይ‹‹ነው›› የሚል ማስረገጫ ይዘው ይነሳሉ። እንደዚህ እንደዚህ መደረግ የለበትም፣ ይሄ ስህተት ነው ይላሉ። ሴቶች ግን ከዛች ባውንደሪ እንዳይወጡ ጥንቃቄ ሲደያርጉ አያለሁ። ምናልባት ከአቅም ጋር የሚገናኝ፣ ከአስተዳደግ፣ ከባህል ጋር የሚገናኙ ነገሮች በውስጣቸው ሊኖርባቸው ይችላሉ የሚል ግምት አለኝ። በተለይ በተለይ እንዲያው ወደፖለቲካ የሚያስነካ ጉዳይ ሲመጣ ሴቶች ምንም አየነት ተሳትፎ የላቸውም (አባሪ ሰባት፣ቡተቃ፣202፣ መስመር 178-99

የቀረበው የቡድንተኮር ቃለመጠይቅ እንደሚያሳየው ከስነምግባራዊ አቀራረብ አንፃር ሴትና ወንዶች የተለያየ አቀራረብ እንዳላቸውና በዚህም ወንዶች ‹‹ነው›› የሚል ማስረገጫ በመያዝ ህይል በተላበሰ መልኩ የማቅረብ ባህርይ እንዳላቸው ይጠቁማል። ሴቶች ደግሞ ‹‹ይመስለኛል፣ እንደዚህ ቢደረግ፣ ይሆናል›› የሚሉ ማለሳለሻ ቃላትን በመጠቀም ሃሳባቸውን በተለሳለሰ መንገድ እንደሚቀርቡና ይህም መረጃው ያመለክታል። ከዚህም በተጨማሪ ደግሞ የሴቶች ንግግር ጥያቄ በመጠየቅና መፍትሄ በመስጠት ላይ ያነጣጠረ እንደሆነ በቡድን ውይይቱ የተሳተፈው እሱባለው ‹‹ሴቶች የተቃውሞ ሀሳብ ሲያነሱ አላይም። የመጠየቅና መፍትሄ ሀሳብ የመስጠት ነገር፣ እንዲህ ቢሆን የሚል ነገር ነው(ቡድ 203፣ መስመር 227-40) በማለት የሌሎቹን ሀሳብ አጠናክሯል። ሴቶች ንግግራቸው ከስነምግባራዊ አቀራረብ እንዳይወጣ ጥንቃቄ እንደሚደርጉና ለዚህም ምክንያቱ

ከአቅም፣ ከአስተዳደግና ከባህል ጋር የተገናኘ ሊሆን እንደሚችል ቀደም ብሎ በቀረበው መረጃ ተጠቁሟል።

በአብዛኛው የትህትና ማላበሻ የሆኑ ቃላትን በመጠቀም ሀሳባቸውን ስነምግባር በተሞላበት ሁኔታ የሚያቀርቡ ከሴቶች በተጨማሪ በእድሜና በስራ ልምዳቸው ከፍ ያሉት ወንዶችም ይገኙበታል። ከስር በዋቢነት የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው እነዚህ ወንዶች ድምፀታዊና አፅንኦታዊ ቃላትን በመጠቀም የበላይነታቸውን ለማሳየት ሲሞክሩ አይታዩም። የአጠቃቀማቸውን ምክንያት ስንመለከት ደግሞ ውይይቱ ወደመልካም አቅጣጫ እንዲሄድና ችግሩ በውይይት እንዲፈታ ለማድረግና አብሮነትንም ለማሳየት የሚጠቀሙበት ስልት ይመስላል።

> መለሰ፡- ‹‹አንዳንደዜ እኮ ይቅርታ አድርግልኝና ቃለጉባኤ ሲፃፍም ስህተት ሊኖር ይችላል። መንፈሱ ነው እንግዲህ ፋሲልን ይዞት ወይ እሷን ቅድም እንዳሰብነው ተፅፎ ሊሆን ይችላል ...››(ወ) (አኮ 002 መስመር 201-202)

መለሰ ጉዳዩ በቃለጉባዔ ፀድቆ ሊሆን እንደሚችል ጥርጣሬ አለው ‹‹ወይ እሷ...ተፅፎ ሊሆን ይችላል›› በሚለው ገለፃ (ወይ) የገባው አንደኛውን ብቻ ለመደገፍ ወይም ለመቃወም ባለመፈለጉ ሲሆን፣ (ሊሆን ይችላል) የሚለው ደግሞ ጥርጣሬ እንዳለው ያመለክታል። ግን ደግሞ ቢፃፍም ስህተት ሊሆን እንደሚችል ‹‹አንዳንደዜ እኮ ይቅርታ›› በማለት እንደሚከሰት ይገልፃል። አገላለፁ ደግሞ (ይቅርታ) የሚለውን የትህትና ቃል በመጠቀም ትህትና በተላበሰ ሁኔታ አቅርቧል። (እኮ) የሚለው የዲስኩር ቃል ደግሞ አንዳንዴ ስህተት የሚፈፀም ለመሆኑ ማሳያ ናት።

> [አለሙ...ማሳሰቢያ! እዚህ ጋ ይቅርታ፣ ከትናነት ወዲያ ኢንፎርማል ስብሰባ ነበር በዚህ ጉዳይ (ወ)(አኮ 002፣መስመር 19)

አለሙ‹‹ማሳሰቢያ›› በማለት የንግግር ድርሻን ጣልቃ በመግባት ለመንጠቅ የተጠቀመበት ስልት ሲሆን፤ የድርሻ ነጠቃው ግን አዎንታዊ እይታ እንዲኖረውና ተቀባይነት ለማግኘት ‹‹...እዚህ ጋ ይቅርታ›› በማለት በተለሳለሰ አቀራረብ ለማቅረብ ሞክሯል

> አለማየሁ፡-...ስለዚህ ይሄ መጣረስ ስለነበረበት የተነሳው አስተያየት ጥሩ ነበረ፡፡ ይህን የመሰለ ክፍተት የተፈጠረው በዚህ ምክንያት ይመስለኛል (ወ) (አኮ 002፣ መስመር 213-214)፡፡

አለማየሁ ፋሲል ግልፅ ያላደረገውን የሪፖርቱን ሁኔታ በማቅረብ (በተወሰነ መልኩ ክፍተት አለበት) በማለት ስህተት እንደነበረና የተነሳውን አስተያየት በበጎ ጎኑ እንደተመለከተው ‹‹ጥሩ ነበር›› በማለት አቅርቧል፡፡ የአለማየሁ ንግግር ትህትና የተላበሰ ሲሆን፣ ‹‹ይመስለኛል›› የሚለውን አገላለጽ መጠቀሙ ንግግሩ ትህትና የተላበሰ ከመሆኑም ባሻገር ሀይል አልባ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

> ደበበ፡- እኔ እንትን ... እንግዲህ የእኛ እንትን የተናገርነው፡፡ ... እና ከእኛ እንትን ያረገው ምንድ ነው ይሽ ነገር፡፡ አንደኛ ካሪክለም ሲቀረፅ የሚመለከታቸው ክፍሎች ኮንሳልት ይደረጋል፡፡ ለምሳሌ ... እንትን አለ፡፡ እና እዚህ ላይ ነው እንግዲህ ትልቁ እንትን፡፡ አንደኛ ኢንፎርሜሽኑ የለንም፤ አሁን እንደተባለ ያንን አገኘን እኛ፡፡ ... ይህን ያህል እንትን ሳይኮሎጂ ብቻ ግን ይገባል፡፡ ... እና አንዱ ትልቁ ፋሲል በውብነሽ አንትን አደረገ እንጂ የእነሱ የራሳችሁ ሪፖርት ነው፡፡ ...እንግዲህ ለመነጋገር እንትን ያልነው፡፡ ... እንትን ያረገ፣ የፎክለር ማጠቃለያ ተብሎ የተሰጠው ያ አሳስቷል፡፡ ስለዚህ ውብነሽ እንትን አላረገችም፡፡ ያንኑ ነው ያየነው፡፡ እና በዚህ አንፃር ብትቀበሉ ጥሩ ነው (ወ)(አኮ 002፣ መስመር 217-256)፡፡

ሌላው የደበበ አገላለፅ በዋናነት ሊገልፀው የሚፈልገውን ጉዳይ ‹‹እንትን›› በሚል ቃል በመተካት አድማጭ እንዲሞላው በማድረግ የቀረበበት ሁኔታ ይታያል፡፡ አቀራረቡን ስንመለከተው ድግግሞሽ የበዛበት ሲሆን፣ የአጠቃቀሙ ዓላማ ደግሞ (እንትን) በሚለው ምትክ ትክክለኛ ቃሉን ቢያቀርበው ድምፀቱ የከረረ ይሆንና አሉታዊ ይዘት ይኖረዋል፡፡ ስለሆነም ሃሳቡን በተለሳለሰ ሁኔታ በማቅረብ አዎንታዊ ይዘት እንዲኖረው ለማድረግ የተጠቀመበት ስልት ይመስላል፡፡ ለምሳሌ ‹‹የእኛ እንትን የተናገርነው›› እና ‹‹ውብነሽ እንትን አላረገችም›› የሚሉትን ወስደን ከገቡበት አውድ በመነሳት ብንመከት በመጀመሪያው ውስጥ ያለው እንትን ‹‹ተቃውሞ/ችግር፣ በሚቀጥለው ውስጥ የገባው እንትን ደግሞ ‹‹ስህተት›› የሚሉትን ውይይቱን አከራካሪ ነጥቦች ተክተው የገቡ ሊሆኑ እንደሚችሉ መረዳት ይቻላል፡፡

በደበበ ገለፃ ‹‹እንትን›› የሚለው ቃል ድግግሞሹ ከፍተኛ መሆኑና አንዳንድ ጊዜም አጠቃቀሙ ተገማች ባለመሆኑ ምክንያት ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልዕክት ሀይል የለሽ

ADABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADABA, ETHIOPIA

ከማድረጉም በላይ በተለይም በጉዳዩ ላይ ቅድመግንዛቤ የሌላቸው ታዳሚዎች ካሉ ሀሳቡን ላይረዱት የሚችሉበት ሁኔታ ስለሚፈጠር ተግባቦትን የሚያደናቅፉም እንደሆኑ የቀረበው አሃድ ይጠቁማል።

በአጠቃላይ ስነምግባራዊ ድስኩራዊ አሃድን በተመለከተ በሴቶችና በወንዶች መካከል ልዩነት እንዳለና በዚህም ወንዶች በአብዛኛው በንግግራቸው የሚጠቀሙባቸው ቃላት ‹‹ነው፣ መደረግ አለበት›› የመሳሰሉትን ቃላት በመጠቀም ሃሳባቸውን ጠንከር ባለ መልኩ እንደሚያስተላልፉ በምልከታ የተወሰደው ድስኩራዊ አሃድ ያሳያል። በሌላ በኩል ደግሞ ከተወሰዱት ድስኩራዊ አሃዶች የተገኘው መረጃ እንደሚመለክተው ሴቶች ስነምግባራዊ የቋንቋ አጠቃቀምን በተመለከተ ሁለት አይነት ባህርይ ያላቸው ሲሆን፣ ይኸውም በመደበኛ ውይይቶችና ወንዶች በበዙባቸው ኢመደበኛ ውይይቶች ላይ ሃሳባቸውን ለመግለጽ የሚጠቀሙባቸው አገላለጾች ለስለስ ያሉና እርግጠኝነትን የማያሳዩ ለምሳሌ ቢሆን ይሻላል፣ ቢደረግ፣ ይመስላል የመሳሰሉትን በመጠቀም ሀሳባቸውን ትህትና በተላበሰ መልኩ ያቀርባሉ። ከዚህ በተጨማሪም ንግግራቸው በአብዛኛው የሚያተኩረው ጥያቄ በማቅረብና መፍትሄ በመስጠት ላይ ነው። ለዚህም በምክንያትነት የተጠቀሰው አስተዳደግ፣ባህልና አቅም እንደሆኑ ከቡተቃ የተገኘው መረጃ ያመላክታል። በሌላ በኩል ግን ሴቶች ኢመደበኛ በሆነና ሴቶች በበዙበት አውድ ያላቸው ስነምግባራዊ የቋንቋ አጠቃቀም ከመደበኛው ለየት ብሎ ታይቷል። ይኸውም በመደበኛው አውድ ያልታየ ስሜታዊነትን የሚገልጹና ከረር ያሉ አገላለጾችን ሲጠቀሙ ተስተውሏል። ይህ አቀራረባቸውም በቡተቃ ላይ ሴቶች የተለሳለሰ ድስኩራዊ አቀራረብ አላቸው ከሚለው ጋር ይጣረሳል።

4.3.2 የድስኩራዊ ልማድ ትንተና

በሂሳዊ ዲስኩር ትንተና አቀራረብ ሂደት በሁለተኛ ደረጃ የሚከናወነው ቀደም ብሎ በድስኩራዊ አሃድ መተንተኛ ይዘቶች የተገለፀውን የቋንቋ አጠቃቀም መሰረት በማድረግ በድስኩራዊ አሃዱና በዲስኩር አፍላቂዎቹ መካከል ያለውን መስተጋብር መሰረት በማድረግ በግልፅ የሚታየውን ድስኩራዊ ልማድን በመተንተን ላይ ያተኩራል። ለዚህም የተለያዩ የድስኩራዊ ልማድ ይዘቶችን ለምሳሌ የንግግር ድርሻን፣ ጣልቃ ገብነትን፣ የመድረክ አያያዝን፣ የሃሳብ ልውውጥን፣ አለመደማመጥንና የመሳሰሉትን በመጠቀም ትንተናውን

ያካሂዳል (እንደፌርክላፍ፣2006፤ ቫን፣2008)። በዚህ መሰረት ቀጥሎ ለጥናቱ የተወሰዱትን ድስኩራዊ አሃዶች ከድስኩራዊ ልማድ ይዘቶች አንፃር ተተንትነው ቀርበዋል።

4.3.2.1 የንግግር ድርሻን መውሰድ

የንግግር ድርሻ አወሳሰድን በተመለከተ በተወሰዱት መረጃዎች የተለያዩ ድስኩራዊ ልምዶች ተስተውለዋል። በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በተካሄዱ ትልልቅ መደበኛ ስብሰባዎች ላይ የንግግር ድርሻ የሚሰጠው በሰብሳቢው አማካኝነት ስም በመጥራትና የንግግር ተራ በመስጠት ሲሆን በእዚህ አውድ ጣልቃ ገብነትና የመደራረብ ሁኔታዎች አይታይም (አጠመ፣006 ይመለከቷል)። ከዚህ በተጨማሪ ምልከታ በተደረገባቸው በፋካሊቲ ደረጃ በተካሄዱ ስብሰባዎች ላይ ድርሻ የሚሰጠው በሰብሳቢው እና እጅ በማውጣት የንግግር ድርሻ የሚወሰድ ቢሆንም አንዳንድ ወንዶች ከሚሰጣቸው ድርሻ በተጨማሪ ጣልቃ በመግባት፣ ድርሻ ሲወስዱ ይታያሉ። አንዳንዶች ደግሞ በተለይም ከፍተኛ የስራ ልምድ ያላቸው ድርሻን እጅ በማውጣት የማይወስዱ ሲሆን መናገር ሲፈልጉ በቀጥታ ጣልቃ በመግባት ድርሻን በመንጠቅ ይናገራሉ። ከዚህ ሌላ ግን በዚህ ጥናት ከተካተቱት የአካዳሚክ ኮሚሽን ስብሰባዎች መካከል የአንዱ ኮሚሽን ሰብሳቢ ሴት የነበረች ሲሆን በዚህ ድስኩራዊ አሃድ የድርሻ አሰጣጡ ከሌሎቹ የተለየ ባህርይ አለው። ይኸውም ሰብሳቢዋ እከሌ ተናገር በማለት ምንም አይነት ድርሻ ስትሰጥ አልታየችም። በዚህ ምክንያት ድስኩራዊ አሃዱን ስንመለከት ከፍተኛ የሆነ ጣልቃ ገብነትና መደራረብ የታየበት አሃድ ነው (አኮ 003 ይመለከቷል)። ለዚህም ሰብሳቢዋ ድርሻን በመስጠት ሚናዋን በትክክል ያልተወጣች ሲሆን አለመደማመጥ በሚፈጠርበት ጊዜ ስም በመጥራት ወይም የንግግር ተራ በመስጠት ድርሻቸውን በአግባቡ ወስደው የሃሳብ ልውውጥ እንዲያደርጉ ከማድረግ ይልቅ ‹‹በየተራ አድርጉት›› (አኮ 003፣ መስመር 585) እና ‹‹ወደጉዳያችን እንግባ›› (አኮ 003፣መስመር 220) በማለት ድርሻቸውን እንዲጠብቁ ለተሳታፊዎቹ በኢቀጥተኛ መንገድ ስትገልጽ ይታያል።

ባንፃሩ ደግሞ ሴቶች ተራቸውን በመጠበቅ የንግግር ድርሻ እንዲሰጣቸው እጃቸውን በማውጣት ይጠይቃሉ። ሆኖም ግን በዚህ ጥናት በታዩት ስብሰባዎች ሴቶች እጃቸውን እንዳወጡ የንግግር ድርሻ ከመስጠት ይልቅ መናገር የሚፈልጉ ወንዶች ተናግረው ሲጨርሱና አጀንዳው ከተጠቃለለ በኋላ የሚሰጡ እንደሆነ ከአኮ 002 ለአገሬና ለኢሌኒ የተሰጠውን ድርሻ በመረጃነት ማየት ይቻላል። አገሬና ኢሌኒ የመናገር ድርሻ እንዲሰጣቸው

በተደጋጋሚ እጃቸውን ቢያወጡም አልተሰጣቸውም፡፡ በመጨረሻም ድርሻው የተሰጣቸው የሚያቀርቡት ሀሳብ አስፈላጊ ነው በሚል ሳይሆን ድርሻው እንዲሰጣቸው በማስገደዳቸው ምክንያት ሲሆን ለዚህም ሰብሳቢው ‹‹ያልተባለ ነገር ነው›› እና ‹‹ያልተነገረ ነገር ነው?›› በማለት ያቀረበው የአገላለፅ ብልሃት አመላካች ነው (ኣባሪ ሁለት፣አኮ.002፣መስመር 307፣463ን ያገናዝቧል)፡፡

በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በተካሄዱ ሁለት ትልልቅ ስብሰባዎች ላይ የተወሰኑ ሴቶች በተደጋጋሚ እጅ በማውጣት ድርሻ ቢጠይቁም እንዳልተሰጣቸውና በኋላም ከተሳታፊዎች ለሴቶች እድል ስጡ በተባሉት መሰረት ሰብሳቢዎቹ ድርሻውን ሲሰጡ ተስተውሏል፡፡

አስረጅ፡-

> ሰብሳቢው፡ እሽ ከማጠናቀቃችን በፊት አንድ ማስተዋሻ ደርሶናል፡፡ እባካችሁ ሴቶች ሃሳብ እንዲሰጡ አድርጉ ይላል፡፡ ጊዜ ስለሌለን ለአንድ ሴት እድሉን እንሰጣለን፡፡ እሽ አዛ ጋ
> አልማዝ፡ የተሰማችኝን ነገር ወደእናንተ ለማቅረብ ነው... (አጠመ.006፣ መስመር61-64)

የተወሰደው አሃድ እንደሚያመለክተው ሰብሳቢው የንግግር ድርሻውን ለሴቶች ለመስጠት ያስገደደው ከተሰብሳቢው የደረሰው ማስታወሻ ሲሆን ድርሻውን ለመስጠትም ጊዜ ስለሌለ ለአንድ ሴት ብቻ እንደሚሰጥ መግለጹ ሌሎችም ሊናገሩ የሚችሉ ሴቶች እንዳሉ ይጠቁማል፡፡ አልማዝ ድርሻውን ከወሰደች በኋላ ረጅም ንግግር ከማድረጓ በላይ በሰጓቱ ከቀረበው አጀንዳ ውጭ ያለፉትን ሁሉ አሰባስባ በዘገባ መልኩ አቅርባለች፡፡ ይህም በተገቢው ጊዜ የንግግር ድርሻ አለማግኘቷን ያመላክታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በዩኒቨርሲቲው በተካሄደ አንድ አገር አቀፍ አውደጥናት ላይ በተመሳሳይ መልኩ በአውደጥናቱ መጠናቀቂያ ላይ ለሴቶች እድል ስጡ የሚል ማስታወሻ ከተሳታፊው በቀረበላቸው መሰረት ጊዜ ስለሌለ በሚል ለሁለት ሴቶች ብቻ ድርሻው የተሰጣቸው ሲሆን፣ ድርሻው ከተሰጣቸው አንዷ ሴት ከአጀንዳው በመውጣት ስላለፉት አጀንዳዎች በማቅረብ ዲስኩሩን ወደኋላ ስትመልስ ተስተውሏል፡፡ ሴቶች በትልልቅ ስብሰባዎች ላይ ድርሻ እንደሚነፈጋቸው ከቡተቃ የተገኘው መረጃም ያመለክታል፡፡

አልማዝ፡- እኔ የታዘብኩት ምን መሰለሽ በየትኛውም ስብሰባ ላይ ለሴቶች እድል አይሰጥም። ቢሰጥም እንኳ ለተሳትፎ ሴቶች ተብሎ ጉዳዩ ከተጠናቀቀ በኋላ ይሰጥሻል። እኔ ሶስት ቀን ሙሉ እጄን ሳወጣ ውየ አልሰጠኝ ብሎ በኋላ ስብሰባው ተጠናቀቀ ሲባል ለሴቶች እድል ስጡ ተብለው ለእኔ ተሰጠኝና ያደረኩት ምንድን ነው የሶስት ቀን ስብሰባ ስለነበረ በአጠቃላይ የነበረኝን ሀሳብ አቀረብኩ በሰዓቱ ከሚባለው ጉዳይ ጋር አይያያዝም ግን መናገር ስለነበረብኝ ተናገርኩ። እና እኔ ትልቅ ትንሽ ስብሰባ አልልም መናገር ካለብን እጄን አውጥቼ ካልሰተጠኝ ማሳሰቢያ ማለቴ አይቀርም። ትልልቅ ስብሰባዎች ላይ በአብዛኛው እጅ ቢያወጡም

ውብነሽ፡- ትልልቅ ስብሰባ ላይ እጅ አውጥተሽ የማትታይባቸው አጋጣሚዎች አሉ። በተሌዩ ምክንያቶች። ያጋጠመኝም ነገር አለ። እኛ ጋ አንድ ጊዜ በነበረው ስብስባ ላይ እጄን አንስቼ አልታየሁም። እና መሪዎቹ አላየኝ ብለው ተስፋ ቆርጬ እጄን መልሻለሁ። ድምፅም ብታሰሚ አይሰማም ሩቅ ነበር። ተስፋ ትቆርጫለሽ። ለምን እንደማያዩ ምናልባት አይናቸውን ፊት ለፊት ብቻ ስለሚያዩ ዳር ለዳር ላታዩ ይችላሉ። እኔ ደግሞ አጋጣሚ ሆኖ በዳር በኩል ነበርኩ። እና አንዳንዴ እድሉ ይነፈግሻል (ቡተቃ 201፣ መስመር90-105)።

የስብሰባው መሪ እንደማያያቸውና ድርሻ እንደማይሰጣቸው በዚህም ተስፋ እንደሚቆርጡ የሚያሳይ ሲሆን ለዚህም የሰብሳቢው እይታ ወደአንድ አቅጣጫ መሆኑንና ምናልባትም ፊት ለፊት አለመቀመጥ ላለመታየና ድርሻ ላለማግኘት እንደአንድ ተፅዕኖ ሊሆን እንደሚችል የውብነሽ ጥርጣሬ ይጠቁማል። አቀማመጥ ድርሻ ለማግኘት አስተዋፅያ እንዳለውና ወንዶች ይህን ብልሃት እንደሚጠቀሙ ከቡተቃ የተገኘው መረጃ ያሳያል።

አስረጅ፡-

ከፍያለው፡ አይ እኔ ብዙ ጊዜ የሚያጋጥመኝ ስለሆነ በተለይ አካዳሚክ ኮሚሽን ስንሰበሰብ፣ ሰብሳቢው ብዙ ጊዜ እኔን አያየኝም። የምቀመጠው ከሰብሳቢው ወደጎን በኩል በመሆኑ። እና እሱ የሚያየው ፊት ለፊት የተቀመጠውን ብቻ ነው፡፤ እና ለመናገር ስፈልግ እጄን አወጣለሁ። እጄን ሳላወጣ መናገር አልፈልግም። ግን ስለያየኝ ‹‹እእ...›› እላለሁ። ካልተሳካልኝ ግን መጨረሻ ላይ ጥልቅ ብዬ መግባት ነው። ሌላም እየተናገረ ቢሆን እናገራለሁ ማለት እድሉ በትክክል የማይሰጠኝ መስሎ ከታየኝ።

ቢንያም፡ ለመናገር መጀመሪያ የማደርገው ምንድን ነው በዛ ስብሰባ ላይ መናገር እንዳለብኝ እርግጠና ከሆንኩኝ ሰብሳቢው ወይም ስብሰባውን የሚመሩት ሰዎች ሊያዩኝ የሚችሉበት ቦታ በእነሱ ፊት ለፊት እቀመጣለሁ። ከተሳካልኝ ማለት ነው ከዛ እጄን ላወጣ እችላለሁ፡፤ ነገሮች እነኚህን ሁሉ አድርጌ ሊሳኩልኝ ካልቻሉ ግን ሃሳቤን በወረቀት ፅፌ እሰጣለሁ።

(አባሪ ዘጠኝ፣ ቡተቃ. 202፣ መስመር 91-108)

የቀረበው መረጃ እንደሚሳየው ከፍያለው በአካዳሚክ ኮሚሽን ስብሰባቸው የሚቀመጠው ከሰብሳቢው ጎን በመሆኑ ለመናገር እጅ በማውጣት ድርሻ ሲጠይቅ ሰብሳቢው የሚያየው

ፊት ለፊት ስለሆነ ድርሻ አይሰጠውም። ሆኖም ግን የተለያዩ ብልሃቶችን በመጠቀም ለምሳሌ ድምፅ በማሰማት ካልተሳካ ደግሞ ጣልቃ በመግባት ድርሻ ወስዶ ይናገራል። በሌላ በኩል ገን ቢንያም ወደስብሰባ ሲገባ መናገር እንዳለበት ካመነ መጀመሪያ የሚያደርገው አቀማመጡን ማስካከል ነው። ይኸውም ለሰብሳቢ እይታ አመቺ ይሆናል ባለው ከሰብሳቢዎቹ ፊት ለፊት ይቀመጣል። በዚህ መንገድ ሃሳቤን ለመግለፅ ድርሻውን ካላገኘ ሃሳቡን በወረቀት ፅፎ ለሰብሳቢዎቹ ያቀርባል።

ከዚህ ሌላ ከቡተቃ የተገኘው መረጃም እንደሚያመለክተው ወንዶች ለመናገር ድርሻ ሲፈልጉ እጅ አውጥተው የማይሰጣቸው ከሆነ የተለያዩ ስልቶችን ለምሳሌ ‹‹እእእ›› የሚል ድምፅ በማሰማት፣ ጣልቃ በመግባት፣ ‹‹እዚህ ጋ›› በማለት ራስን በመጠቆም፣ በሰውነት እንቅስቃሴ በመጠቀም ድርሻ እንደሚጠይቁና እንደሚነጥቁ ታይቷል። ከዚህ ባለፈም አንዳንዶች መናገር ሲፈልጉ እጅ ሳያወጡ እንደሚናገሩና አንዳንዶቹ ደግሞ ድርሻ የማይሰጣቸው ከሆነ መድረክ ረግጠው እንደሚወጡም ከቡተቃ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

አስረጅ፡-

> አለሙ፡- በጣም አስፈላጊ ነው ብየ ካሰብኩ መናገሬ፣ እድል እንኳ ባይሰጠኝ ይቅርታ ብየ እገባለሁ። ብዙ ጊዜ ግን ጣልቃ የመግባት እንትን አሳያለሁ እኔ መናገር ካለብኝ።
> መሰረት፡- ... በክፍተት የመግባት አይነት ነገር ነው እንጂ ቀድሜ እንደሰው እጅ አውጥቼ ምናምን አልናገርም። አጀንዳው ሊዘጋ እንኳ ቢሞክር በተለይ ተሰብሳቢው ትንሽ ከሆነ ልክ እንዲፓርትመንት ቁጥር የምፈልገው ነገር ካለ አዚህ ጋ ብየ እናገራለሁ።
> በእውቀቱ፡- አጀንዳው ለእኔ በጣም ጠቃሚና የማቀርበው ሀሳብ ስትሮንግ ከሆነ ጣልቃ እገባለሁ ቅድም ጋሽ አለሙ እንደተናገረው። ግን እንዳንዴ ምናልባት ተናጋሪ ከመሆን በአንዳንድ ምክንያት እድሉ ላይሰጥሽ ይችላል። የዛን ጊዜ እኔ እንዲያውም መድረክ ረግጬ የምወጣበት አጋጣሚ አለ።
> ሳባ፡- የተለየ ነገር የለም፣ ምናልባት መናገር አለብኝ ብየ ካመንኩኝ፣ ወይም አልተነገረም ብየ ካሰብኩኝ ያው እነሱ እንዳሉት እድል ይሰጠኝ ብየ እጠይቃለሁ።
> አገሬ፡- እኔ እድል እንዲሰጠኝ እጅ ነው የማወጣው መጀመሪያ። ያለበለዚያ እንደመቁነጥነጥ ነገር አይነት ነገር ያደርገኛል። (አባሪ ሶስት፣ ቡተቃ 201፣ መስመር 35-62)

በአንፃሩ ደግሞ አብዛኛዎቹ ሴቶች ድርሻ የሚወስዱት እጅ በማውጣት ሲሆን አልፎ አልፎ የመቁነጥነጥ ሁኔታ የሚያሳዩ ቢኖሩም ጣልቃ በመግባትም ሆነ የተለያዩ ስልቶችን

በመጠቀም ድርሻ ለመንጠቅ አይሞክሩም። ሆኖም ግን በትላልቅ ስብሰባዎችና በትንንሽ ስብሰባዎች ላይ የሚያሳዩት ባህርይ የተለያየ ነው። ለምሳሌ በትልልቅ ስብሰባ ላይ ብዛት ያለው ታዳሚ ስለሚኖር ለመናገር ፍላጎት የሌላቸው ሲሆን፤ መናገር ከፈለጉ እንኳን ቀድመው እጃቸውን አውጥተው እንደማይናገሩና በማስታወሻቸው ከያዟቸው ነጥቦች መካከል ያልተነገሩ ነገሮች ካሉ ብቻ እጃቸውን አውጥተው እንደሚናገሩ ገልፀዋል። በተመሳሳይ በትላልቅ ስብሰባዎች ላይ አንዳንድ ወንዶችም መናገር እንደማይፈልጉ ሲገልጹ ለዚህም ብዙዎች ስለሚናገሩ አድማጭ መሆን እንደሚመርጡ ገልጸዋል። ሆኖም ግን መነገር ያለበት ጉዳይ ካለና የተዛባ መረጃ ከቀረበ እጃቸውን በማውጣት ድርሻ የሚጠይቁ ሲሆን ካልተሰጣቸው ግን ጣልቃ በመግባት ድርሻ በመንጠቅ እንደሚናገሩ ገልፀዋል (ቡድን 203፣ መስመር76-77ይመልከቱ)። አንዳንዶች ደግሞ መናገር ሲፈልጉ በሌሎች ሰዎች ቢነገርም ሃሳባቸውን ሳይናገሩ እንደማይወጡ መረጃው ያሳያል (ቡድን 201፣ መስመር 86-89 ይመልከቱ)።

በትንንሽ ስብሰባዎች ደግሞ ለምሳሌ በፕሮግራም ደረጃ በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ አብዛኛዎቹ ሴቶች እጃቸውን በማውጣት እንዲሁም አንዳንድ ሴቶች ደግሞ መናገር ሲፈልጉ ‹‹እዚህ ጋ›› በማለት ድርሻ እንደሚወስዱ ከውይይቱ የተገኘው መረጃ ያመለክታል። ከዚህ በተጨማሪም ከመስክ ማስታወሻ የተሰበሰበው መረጃ እንደሚያመለክተው የንግግር ድርሻ መውሰድን በተመለከተ በትልልቅ ስብሰባዎችም ሆነ በትንንሽ ስብሰባዎች ላይ ወንዶች በውይይቱ መጀመሪያ ላይ የሚናገሩ ሲሆን ሴቶቹ ደግሞ በውይይቱ ወይም በአጀንዳው መጨረሻ ላይ ይናገራሉ። በትልልቅ ስብሰባዎች እጃቸውን በማውጣት ድርሻ ለሚጠይቁ ወንዶች ተራ በማውጣት በቅደም ተከተል እንዲናገሩ ድርሻ ይሰጣቸዋል። አንዳንዶች ደግሞ ድርሻው ካልተሰጣቸው ወይም ድጋሜ ድርሻ ማግኘት ከፈለጉና ካልተሰጣቸው ጣልቃ በመግባት ድርሻን በመንጠቅ ሀሳባቸውን ይገልፃሉ። ከዚህ በተለየ ግን በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ከተደረገው አጠቃላይ ውይይት የተወሰደው መረጃ እንደሚያሳየው ሴቶች በመጀመሪያ ድርሻ የማይጠይቁ ሲሆን፣ ውይይቱ መገባደጃ ላይ ከሁለት የማይበልጡ ሴቶች ለመናገር እጃቸውን በተደጋጋሚ በማውጣት ድርሻን ቢጠይቁም በሁለቱም ስብሰባዎች ላይ ድርሻ አልተሰጣቸውም። አንደኛው ስብሰባ የሁለት ቀን ሲሆን ሁለተኛው ስብሰባ ደግሞ ለሶስት ቀናት የተካሄደ ነበር። በሁለቱም ስብሰባዎች የመጨረሻ ቀናትና በውይይቱ ማጠቃለያ ጊዜ ከተሳታፊ ወንዶች ‹‹ለሴቶች እድል ስጡ››

የሚል ማስታወሻ ወረቀት ስለደረሳቸው በሁለቱም ስብሰባዎች መጨረሻ ላይ እንዲናገሩ ተደርጓል።

በፋካሊቲ ደረጃ በሚደረጉ ትንንሽ ውይይቶች ላይ ከትልልቅ ስብሰባዎች በተሻለ መልኩ እጃቸውን በማውጣት ለመናገር ድርሻ ይጠይቃሉ። ሆኖም ግን ድርሻ በሚነፈጉበትና በሚነጠቁበት ጊዜ ግን ድርሻን የመንጠቅ ተግባርን አይፈፅሙም።

ከዚህ በተለየ በኢመደበኛ አውድ ያለውን ሁኔታ ስንመለክት ደግሞ ሁለት አይነት መልክ እንዳለ የተወሰደው መረጃ ይጠቁማል። ወንዶች በበዙበት ኢመደበኛ ውይይት ላይ ድርሻን ጠብቆ የመናገር ሁኔታ ሲታይ (ኢመ.004 ይመልከቱ)፤ ሴቶች በበዙበት ኢመደበኛ ውይይት ላይ ደግሞ ድርሻን ጠብቀው የሃሳብ ለውውጥ ከማድረግ ይልቅ በምትኩ ጣልቃ ገብነት፣መደራረብና የጎንዮሽ ውይይት ልማድ እንዳለ መረጃው ያመለክታል (ኢመ. 001 ይመልከቱ)።

4.3.2.2 የስብሳቢው ሚና በድርሻ አሰጣጥ

በዩኒቨርሲቲ ደረጃም ሆነ በፋካሊቲ ደረጃ በተካሄዱት ውይይቶች ላይ የነበሩት የስብሰባ መሪዎች ሴቶችና ወንዶች ለመናገር እጃቸውን በተመሳሳይ ጊዜ ሲያወጡ የንግግር ድርሻ የሚሰጡት ለወንዶች ነው። ሌላው ወንዶች ድርሻ የሚሰጣቸው እጃቸውን ሲያወጡ ብቻ ሳይሆን እጃቸውን የማያወጡ ከሆነ ደግሞ ስማቸውን በመጥራት እንዲናገሩ ይጠየቃሉ። በአብዛኛው ለሴቶች ድርሻ የሚሰጣቸው በውይይቱ ማጠናቀቂያ ጊዜ ሲሆን በዚህ ላይም ቢሆን ‹‹ያልተባለ ነገር ነው? ያልተነገረ ነገር ነው?››የሚል ጥያቄ ይጠየቃሉ (አኮ 002፣ መስመር 307 እና 463 ይመለከቷል)።

በምልከታው ወቅት በማስታወሻ ከተመዘገቡ ዋና ዋና ገፅታዎች ውስጥ አንደኛው ተሰብሳቢዎቹ ለመናገር ድርሻ የሚወስዱት እጃቸውን በማውጣት፣ ጣልቃ በመግባትና ስብሳቢው ስማቸውን በመጥራት እንዲናገሩ ሲጠይቃቸው ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ስብሳቢው ለተሰብሳቢዎቹ እንዲናገሩ ድርሻ የሚሰጣቸው ደግሞ እጃቸውን ካወጡት መካከል በእድሜ፣በትምህርት ደረጃና በስራ ልምዳቸው ከፍ ያሉትን በመምረጥና እንዲናገሩ

ADDIS ABABA

የሚፈለጉ ሰዎች ደግሞ እጅ ካላወጡ ስማቸውን በመጥራት እንዲናገሩ በመጠየቅ ነው። ከዚህም ሌላ ከየታ አንባር ለወንዶች ቅድሚያ ድርሻ ሲሰጣቸው ለሴቶቹ ግን ወንዶቹ ድርሻ ተሰጥቷቸው ተናግረው ሲጨርሱ በመጨረሻ ላይ ይሰጣል።

ሌላው በአብዛኛው ሴቶች እጃቸውን በተደጋጋሚ ቢያወጡም ሰብሳቢዎቹየመጀመሪያውን ድርሻ ለመስጠት ፍላጎት አለማሳየታቸው ነው። ከአኮ 002 ለአገሬና ለኢሌኒ እንዲሁም በአጠመ 006፣ ለአልማዝ የተሰጣቸውን ድርሻ ስንመለከት መጨረሻ ላይ አጀንዳው ከተጠቃለለ በኋላ ነው። በመጨረሻም ቢሆን ድርሻው የተሰጣቸው እጃቸውን ማውጣቱን ባለማቆማቸው ምክንያት ሰብሳቢዎቹ እድሉን ለመስጠት የተገደደዱበት ሁኔታ ታይቷል።

ከዚህ በተጨማሪ ሰብሳቢዎችን በተመለከተ የሁሉም ሰው ሀሳብ ጠቃሚ ነው በማለት ለሁሉም ሰው በተለይም ለሴቶች ድርሻ የመስጠት ችግር እንዳለ ከቡተቃ የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል። አብዛኛውን ጊዜ በተለይም በትላልቅ ስብሰባዎች ላይ ስብሰባውን የሚመሩ ሰዎች ለሴቶች እድል እንዲሰጡ በወረቀት ማስታወሻ ተፅፎ ከተሰጣቸው በኋላ ድርሻ ለመስጠት ሲሞክሩ በተደጋጋሚ እንደተመለከቱ የቡድን ውይይቱ ተሳታፊዎች ገልፀዋል። ይህም መናገር ለወንዶች ብቻ የተሰጠ በመሆኑ ሴቶች ድርሻ እንደማያገኙና ሀሳባቸውን በመግለፅ ሂደት ጫና እንዳለባቸው በውይይቱ ተንፀባርቋል። የሴቶች አለመናገር የሚጠበቅ እንደሆነና ‹‹እድል እንስጣቸውና ይናገሩ›› (አባሪ ስምንትቡተቃ 201፣መስመር 247)ማለት ወንዶች ሲፈቅዱላቸው ብቻ ነው መናገር የሚችሉት የሚል እንደሆነ ገልፀዋል።

አስረጅ፡-

> ውብነሽ፡- ስብሰባ ቦታም እኮ ሰብሳቢውም እኮ ማንን ነው የሚያየው ለማን ነው እድል የሚሰጠው። ትናንትና እንኳን በነበረው ስብሰባ እስካሁን ሴቶች እድል አላገኙም ተብሎ ተፅፎለት ነው እስኪ ለሴቶች እድል ልስጥ ያለው። ለምን ከዛ በፊት ማበረታታቱን አላመጣውም። ከዛም የሚሰጠው ትኩረት ለሴቶች ሳይሆን ለወንዶች ነው። በዚህ ምክንያት የሴትና የወንድ የመናገር ተሳትፎ ልዩነት አለው(አባሪ ስምንት፣ ቡተቃ 201፣ መስመር188-92)።

> አገሬ፡ ለምሳሌ ባለፈው የተደረገው አጠቃላይ ስብሰባ ላይ ሶስት ቀን ሙሉ እጁን ባወጣ ባወጣ ሊሰጠን አልቻለም። ግን ካስታወሳችሁ የሆነ ሰው ማን እንደሆነ አላውቅም በወረቀት ፅፎ እባካችሁ ሴቶችን አሳትፉ ብሎ ለሰብሳቢዎቹ ሰቶ ሰብሳቢዎቹም ማስታወሻውን አንብበው እንዲህ ተባልን ብለው ነግረውን እሽ ሰዓት ስለሌለ ለአንዲት ሴት እንስጥ አሉ (አባሪ ዘጠኝ ቡተቃ 203 131-41)

በስብሰባ ወቅት ፍትሃዊ የሆነ ድርሻ እንዳይኖር ከሚያደርጉት አንዱ ድርሻ የሚሰጠው እጁን ላወጣ ብቻ በመሆኑና የአንተ ወይም የአንቺ ሃሳብ ይፈለጋል በማለት ድርሻ የሚሰጥበት ሁኔታ አለመኖሩ እንደሆነ በውይይቱ ተገልጿል። ሌላው ችግር ‹‹እድል›› የሚለው ቃል ትክክለኛውን የእንግሊዝኛ ትርጓሜ አለመያዙ ነው። ምክንያቱም እድል በማህበረሰቡ ዘንድ የታወቀና የሚጠበቅ ነገር ሲሆን ከዚህ አልፋ ከተናገረች መረን እንዳለፈች ስለሚቆጠር ለጋብቻና ለመሳሰሉት ነገሮች የማትመረጥበት ሁኔታ ይኖራል (ቡድ 201፣ መስመር1391-1399 ይመለከታል)። በዚህ አውድ ስንመለከተው ከሴቶች የሚጠበቀው አለመናገር በመሆኑ ሴቶች እንዲናገሩ እድሉ አይሰጣቸውም ማለት ነው። ለአብነት ያህል በዚሁ በዩኒቨርሲቲው በተደረገ አገር አቀፍ ውይይት ላይ ሴቶች ድርሻ ባለመሰጠታቸው ምክንያት ስብሰባው ሊጠናቀቅ ጥቂት ደቂቃዎች ሲቀሩ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጡ ሴቶች እጃቸውን በተደጋጋሚ በማውጣት ድርሻ ቢጠይቁም እንዳልተሰጣቸውና አሁን መናገር እንዳለባቸው በጩኸት በመግለጽ በመጨረሻ ለአንዷ ሴት ድርሻው ተሰጥቷት መናገሯ የድርሻ አሰጣጥ ችግር መኖሩን አመላካች ነው(አባሪ ስምንት፣ቡተቃ 201፣ መስመር 264 -269 ይመልከቱ)።

ይህም ሴቶች ጠቃሚ ሀሳብ ያቀርባሉ ተብሎ ሳይሆን ለተሳትፎ ያህል እንደሆነ መረጃው ይጠቁማል። ከሴቶች ጠቃሚ ነገር ይኖራል ብሎ አስቦ የንግግር ድርሻ የመስጠቱ ሁኔታ በተቋሙ ያልተለመደ እንደሆነና ዘመኑ የሴቶች ተሳትፎ ስለሚባል ብቻ ለተሳትፎ ያህል እንዲናገሩ ይደረጋል። ለዚህም የማህበረሰቡ ባህል በተቋሙ ላይም ተፅዕኖ ማድረጉን ከቡተቃ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

አስረጅ፡-

> ከፍያለው፡ እኔ እንዲያውም እስካሁን አላሰብኩትም ነበር አሁን እዚህ ቁጭ ብየ ሳስበው ባህሉ በጣም ተፅዕኖ እያደረገብን ያለው በእኛም ጭምር ነው። ለምን መሰለሽ ተፅዕኖ አድራጊዎቹ እኛ ነን። አሁን ባለንበት ሁኔታ ሴቶች ሲናገሩ መቼ እናደንቃቸዋለን። እንዲያውም የሚገርመው በጣም ስማርት የሆነ ሀሳብ ተናግረው እንዴት ተናገረች የሚለውን ነው የምናስበው እንጅ አናበረታታም። እኔም አድርጌ አላውቅም ሰው ሲያደርግም አላይም። ዝም ተብሎ ለተሳትፎ ያህል ሴቶች ተሳተፉ ሲባል ነው የምሰማው ሁልጊዜ እንጅ ከእነሱ ጠቃሚ ነገር ይኖራል እስቲ ሲባል አላውቅም። ዘመኑ የሴቶች ተሳትፎ ስለሚባል ብቻ ነው የሚመስለኝ (ቡተቃ 202፣ መስመር 282-89)

በአጠቃላይ የሰብሳቢው ሚና ድርሻ በመስጠት በኩል የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው ከሴቶች ጠቃሚ ሃሳብ ይኖራል ተብሎ ሳይሆን ሴቶችን ማሳተፍ እንደመመሪያ ሆኖ የተወሰደ በመሆኑ ይመስላል። በዚህ ጥናት እንደታየው በተለይም በዩኒቨርሲቲው ትልልቅ ስብሰባዎች ሲካሄዱ በውይይቱ ማጠናቀቂያ አካባቢ ሴቶች ለተሳትፎ ተናገሩ የሚለው አካሄድ በሰብሳቢዎቹ የተለመደ ሆኗል።

4.3.2.3 የሀሳብ ልውውጥ

አንድ ተናጋሪ ሲናገር አድማጩ ደግሞ የተረዳውን ነገር መሰረት አድርጎ በጎም ይሁን አሉታዊ ምላሽ መስጠት ይጠበቅበታል። ሆኖም ግን አድማጩ ምላሽ የሚሰጠው ተናጋሪውን በተረዳበት ሁኔታ ሳይሆን እሱ መናገር የሚፈልገውን ጉዳይ የሚናገር ከሆነ ዲስኩሩ ድርሻን መሰረት ባደረገ መልኩ ሊቀጥል አይችልም። ይህ ሁኔታ በዚህ ጥናት የታየ ሲሆን ዋቢዎችን መሰረት በማድረግ ቀጥለን እንመልከት።

በአኮ 002 ድስኩራዊ አሃድ ላይ ከመስመር 163-171 የቀረበው አሃድ እንደሚያመለክተው ፋሲል ያዳመጠውን መሰረት በማድረግ ምላሽ በመስጠትና ተገቢውን የሀሳብ ልውውጥ በማደረግ በኩል አልፎ አልፎ የሚታይ ጉድለት አለ።

ለምሳሌ፡-

አበበ፡- አመሰግናለሁ። እስቲ ፋሲል እኔ ያልፀደቀ ካሪክለም ወደላይ አይሄድም።
ፋሲል፡- ላቭ የሚለውን ነገር እናንሳና እዛው ጋ እንሂድ። ላብ ያስፈልገዋል...
[አለማየሁ፡- እዚህ ጋ ይቅርታ ማስተካከያ?
ፋሲል፡- ሌላው ኤሲ ላይ የተባለው። ኤሲ ላይ ምንድን ነው...
(አባሪ ሁለት፣አኮ 002፣መስመር 170-82)

ፋሲል በሰብሳቢው(አበበ) እንዲመልስ ወይም እንዲያብራራ የሚጠየቀውን ጉዳይ በመተው እሱ እንዲመለስለት የሚፈልገውን ነገር ብቻ በተደጋጋሚ በሚያገኘው ድርሻ ሲያቀርብ ይታያል። ይህ ደግሞ የዲስኩሩን አካሄድ ከማጓተቱና ከመለወጡ በተጨማሪ ሰፊ ድርሻንና የንግግር ጊዜን እንዲወስድ አደርጎታል። ከዚህም ሌላ ፋሲል በተለይም

አድማጭን ባለመረዳቱ ምክንያት አድማጩ እንዲሰላች ከማድረጉም በላይ ራሱ መናገር የሚፈልገውን ነገር በሙሉ እንዳልተናገረና የተሰጠው ድርሻም ሆነ የንግግር ጊዜ ለራሱ በቂ እንዳልሆነ በመጨረሻ ድርሻ ጠይቆ በሰብሳቢው ‹‹አንተ ብዙ ስለተናገርክ በኋላ እሰጥሃለሁ፤ እሰጥሃለሁ ችግር የለም›› (አኮ 002፣መስመር 258) መባሉ አመላካች ነው፡፡

በአጠመ.006 በቀረበው ድስኩራዊ አሃድ ደግሞ እሱባለው ድርሻውን እንዳገኘ ንግግሩን የጀመረው ለቀረበው አጀንዳ ምላሽ በመስጠት ቢሆንም ‹‹....ከዚሁ ጋር ተያይዞ ..... ስለብዝሀነት የምለው ነገር አለኝ›› (መስመር 28-35) በማለት እሱ መናገር ስለሚፈልገው ጉዳይ ከመናገሩ በተጨማሪ ሀሳቡን አድማጭን መሰረት በማድረግ በአጭሩ ከማቅረብ ይልቅ የተለያዩ ሀሳቦችን በማንሳት የተራዘመ ንግግር አድርጓል፡፡ ንግግሩ የተራዘመ ለመሆኑና ከውይይቱ አጀንዳ ጋር የማይሄዱ አድማጩን መሰረት አድርጎ የሀሳብ ልውውጡን ላለማድረጉ ‹‹....አንድ ምሳሌ ልነግራችሁ እችላለሁ›› በማለት ንግግሩን ሲቀጥል ታዳሚው በጫጫታና በጭብጨባ (መስመር 36) እንዲያቆም ሲጠይቅ የሚያሳየውን አሃድ በአስረጅነት መመልከት ይቻላል፡፡ እሱባለው በታዳሚው እንዲያቆም ቢጠየቅም ንግግሩን ያለምንም ችግር ተደማጭነቱን ለመጨመር ድምፁን ከፍ በማድረግ ንግግሩን በመቀጠል መግለፅ የፈለገውን ሀሳብ ጨርሶ ገልጿል (መስመር 37-43)፡፡ በዚህም እሱባለው ታዳሚውን በመረዳት የሀሳብ ልውውጡን ባለመፈፀሙ እንቅፋት የገጠመው ሲሆን፤ በሌላ በኩል ግን ማስተላለፍ የፈለገውን ጉዳይ የቀረበበትን ተቃውሞ ተቋቁሞ ማቅረብ እንደቻለ እንመለከታለን፡፡ ከቡተቃ የተገኘው መረጃም እንደሚመለክተው አንዳንድ ወንዶች ሀሳባቸውን በሚያቀርቡበት ጊዜ እግረ መንገዳቸውን ራሳቸውን ለመግለፅ በሚያደርጉት ሂደት ከአጀንዳ እንደሚወጡና በጭብጨባና በጩኸት አቁሙ ሲባሉ እንኳን እንደማያቆሙ ቡተቃ 202፣መስመር 239-41 እና ቡተቃ 203፣ መስመር 282-85 የቀረበው መረጃ ያመለክታል፡፡

ከዚህ በተለየ ደግሞ በአኮ 002 ድስኩራዊ አሃድ ላይ ፋሲል በተደጋጋሚ ‹‹ለምንድን ነው አንዱን ብቻ የሰጠችው ነው?›› በማለት ለሚያቀረበው ጥያቄ ውብነሽ በስበሰባው ላይ ያላትን ድርሻና ሃላፊነት መሰረት አድርጋ ምላሽ አለመስጠቷን እንመለከታለን፡፡ ይህ ደግሞ ከተሰጣት ሚና በታች ንግግር ያደረገች መሆኗን ያመለክታል፡፡ ከዚህ ስብሰባ በኋላ አጥኝዋ ከውብነሽ ጋር ባደረገችው ውይይት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ልትሰጠው

የምትችለው ምላሽ ለፋሲል አሉታዊ በመሆኑና እሱም ሊቀበል ስለማይችል አላስፈላጊ ጭቅጭቅ ውስጥ መግባት ባለመፈለጓ ምክንያት የሃሳብ ልውውጡን እንደገታችው ገልፃለች፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በዚሁ ድስኩራዊ አሃድ ላይ በኢሌኒና በሰብሳቢው መካከል የነበረው የሀሳብ ለውውጥ ተናጋሪው/ዋ በተረዳበት/ችበት ሁኔታ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ መናገር በሚፈልጉት ጉዳይ ላይ የተመሰረተና ተቃርኖ ያየለበት እንደሆነ ቀጥሎ የቀረበውን አሃድ በዋቢነት እንመለክት፡-

አበበ፡- ያልተነገረ ነገር ነው? (ኢሌኒ የንግግር ድርሻ እንዲሰጣት እጇን ስላወጣች የተጠየቀ ጥያቄ)
ኢሌኒ፡- እኔ እንስማማ ብሎ ባይቋጭ ደስ ይለኛል፡፡
አበበ፡- እንጣላ ብለን እንቋጨው፡፡
ኢሌኒ፡- አይደለም! አይ አይደለም ማሾፌ አይደለም፡፡
አበበ፡- አይ እኔም እውነቴን ነው የምልሽ፡፡
ኢሌኒ፡- እኔን አስጨርሰኝና በኋላ ከዛ አንተ ትጨርሰዋለህ፡፡ እንሰማማ ብለን ከሄድን ፎርማል የሆነ ነገር አይሆንም፡፡ አሁን እኔ በተረዳሁት መሰረት...ነው የማስበው፡፡ ጨርሻለሁ፡፡
አበበ፡- ይሄ የዲፓርትመንት ጉዳይ ለምን ተነሱ የሚለው
[ኢሌኒ፡- ለምን ተነሱ ጥያቄ የለኝም፤ ይመለሱ ነው ጥያቄዬ፡፡
ከበደ፡- ይሄ የሚቀጥለው አጀንዳ አይገባም ይሄ?
አበበ፡- እ እ
ከበደ፡- በሚቀጥለው አጀንዳ ውስጥ የሚገባ መሰለኝ፡፡
መለሰ፡- ጊዜያችንን ባናጠፋ ይሄ ጉዳይ በጣም ከእኛ ጉዳይ የዘለለ ነው፡፡
አበበ፡- ስላልገባት ግን በአጭሩ በጣም ሪፍሌክት እድርጌላት ብሄድ ብዬ ነው፡፡
መለሰ፡- እሽ
አበበ፡- ዲፓርትመንቶች ወደፕሮግራም ጥናቶች ሲቀየሩ የቢፒአር ጥናት ነው፡፡
[ኢሌኒ፡- ገብቶኛል (አባሪ 2፣ አኮ 002፣ከመስመር 463-509 ያገናዝቧል)፡፡

ከቀረበው ድስኩራዊ አሃድ እንደምንረዳው በመጀመሪያ ኢሌኒ ለመናገር አጇን አውጥታ የንግግር ድርሻ ስትጠይቅ ሰብሳቢው/አበበ ‹‹ያልተነገረ ነገር ነው? ብሎ ሲጠይቃት፣ ለተጠየቀችው ጥያቄ ምላሽ ሳትሰጥ መናገር የምትፈልገውን ሃሳብ በቀጥታ በማቅረብ ንግግሯን ጀመረች፡፡ በዚህም ‹‹እኔ እንስማማ ብሎ ባይቋጭ ደስ ይለኛል፡፡›› ብላ ንግግሯን ስትጀምር በተቃራኒው ሰብሳቢው ‹‹እንጣላ ብለን እንቋጨው፡፡›› የሚል ምፀታዊ ምለሽ ሲሰጣት፣ ‹‹አይደለም! አይ አይደለም ማሾፌ አይደለም፡፡›› በማለት በአፅንዖት ቁጣዋን ገልፃለች፡፡ ሰብሳቢውም ‹‹አይ እኔም እውነቴን ነው የምልሽ፡፡›› ወዘተ. በማለት ዲስኩሩ ተናጋሪዋን በተረዳችበት ሁኔታ ሳይሆን በተቃራኒው እስከመጨረስ ቀጥሏል፡፡ ይህ ደግሞ

ድስኩራዊ ምልልሱ የሰብሳቢው ጣልቃ ገብነትና ተቃርኖ የነበረበት በመሆኑ ምክንያት የሀሳብ ልውውጡ በሁለቱ መካከል የሚታየው የሀይል ግንኙነት አቻዊ ያልነበረና የሰብሳቢው የበላይነት የታየበት እንደነበር ከመረጃው መረዳት የሚቻል ነው። ከዚህ በተጨማሪም እንዲህ አይነት የሰብሳቢ የበላይነት ሴቶች ሀሳባቸውን ከማቅረብ ሊገታቸው እንደሚችል ቀደም ብሎ የቀረበው ኢሌኒ የሀሳብ ልውውጥ አመላካች ሲሆን ሌሎቹም በውይይቱ ያልተሳተፉ ሴቶችም ከአጥኝዋ ጋር በተደረገ ኢመደበኛ ውይይት በገለጹት መሰረት ጭቅጭቅ ባለበት ሁኔታና ከሰብሳቢ የሚሰጠው ምላሽ በጎ መስሎ ካልታያቸው ከመናገር እንደሚቆጠቡ ገልፀዋል። ከዚህም በተጨማሪ በቡተቃ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ጭቅጭቅ ባለበትና ከሰብሳቢው የሚሰጠው ምላሽ ተገቢ መስሎ ካልታያቸው እንደማይናገሩ ገልፀዋል።

አስረጅ፡-

> እየሩስ፡ አትሞስፔሩ ካልተመቸኝ። በጣም የሚያናድድ ነገር ካየሁኝ፣ በጣም ተናድጄ ሳልናገር እወጣለሁ።፤ ምክንያቱም ብናገር ስሜታዊ ሆኜ በጣም መጥፎ ነገር ከምናገር ብዬ ስለማስብ(ሴ)...አዎ በስብሰባው ላይ ሌሎች ‹‹ሚስትሪት›› ሲደረጉ ካየሁኝ እናደዳለሁ።፤ ከዛ ሳልናገር እወጣለሁ (ሴ) ቡተቃ፣202፣ መስመር120-24
>
> አገሬ፡- በተለይ ሰብሳቢዎች ቂመኞች ይሆኑብሻል። ስህተታቸውን በሰው ፊት ብትነግሪያቸው እንዲያርሙ ብትናገሪ በዛ ስብሰባ ጠቃሚ እንኳ ቢሆንም ሌላ ቀን ሊበቀሉሽ ይፈልጋሉ። ስለዚህ ባልናገርስ ትያለሽ (ሴ)(ቡተቃ 203፣መስመር 329-331
>
> አልማዝ፡ ሲቀጥል ሰብሳቢ ሆነው የሚመጡት ሰዎች ከተሰብሳቢው ጋር መግባባት ከሌለና ጭቅጭቅ ያለበት ስብሰባ ከሆነ ዝም ብለሽ እንደ ተማሪ ያሉሽን ተቀብለሽ ትወጫለሽ (ሴ) (ቡተቃ 203፣መስመር334-336)

ሴቶች ጭቅጭቅና ቂመኛ ሰብሳቢ ባለበት ውይይት የሃሳብ ልውውጥ ማድረግ እንደማይፈልጉ መረጃው ያመለክታል። ይህም ከውይይቱ ከወጡ በኋላ ሊደርስባቸው የሚችለውን ተፅዕኖ ከወዲሁ በማሰብ የሚያደርጉት እንደሆነ ከአገሬ ገለፃ ‹‹ሌላ ቀን ሊበቀሉሽ ይፈልጋሉ›› ከሚለው ገለፃ መረዳት ይቻላል።

በሌላ በኩል ከፍተኛ የስራ ልምድ ያላቸውና ለተለያዩ የዩኒቨርሲቲው የስራ ሁኔታ የተጋለጡ ሴቶች የተሟላና ረጃጅም የሀሳብ ልውውጥ የሚያደርጉ ሲሆን፤ በተቃራኒው ደግሞ አብዛኛዎቹ ሴቶች በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በሚደረጉ ትምህርታዊ ውይይቶች ላይ

የሀሳብ ልውውጥ ከማድረግ ከመቆጠባቸው በተጨማሪም በጣም አጫጭርና አዎንታዊና አሉታዊነታቸውን የማያሳዩ ምላሾችን ይሰጣሉ።

ለአብነት ያህል በአኮ 003 በፈለቀው ድስኩራዊ አሃድ የሮዛንና የሀሳብ ልውውጥ ስንመለከት በአብዛኛው ለሚቀርቡት ጉዳዮች የሚሰጡት ምላሽ ‹‹እህ›› የሚል ሲሆን አልፎ አልፎ ደግሞ ለምን እና እንዴት የሚሉ ጥያቄዎችን የሚያስነሱ ማብራሪያ የሌላቸውን ቃላትና ሀረጎችን በመጠቀም ነው።

አስረጅ፡-

ጌትነት፡- እህ ኧረ! ሌላ ሮዛ ለነገሩ የ-ሌላ ሰው እየተካሽ ነው እንጂ፤
ሮዛ፡- እህ
ጌትነት፡- ጎንደር ያየሁት ኤክስፐሪያንስ
ሮዛ፡- እህ
ጌትነት፡- አምና ማድረግ ነበረብን። ፕሮባብሊ ለማ ነው ማድረግ የሚገባው፤ የመጀመሪያ የየፊሊዱ ግራጁቶችን
ሮዛ፡- እህ
ጌትነት፡- ትልቅ ሆቴል ወስደው መስተንግዶ ምናምን ከሚባል ነገር ያወጡና ትልቅ ዝግጅት ያደርጋሉ።
ሮዛ፡- እህ
ጌትነት፡- ተማሪና መምህር ያገናኛሉ።
ሮዛ፡- እህ
ጌትነት፡-የመጀመሪያ ባች ተመራቂ ለምሳሌ በ... አስመርቀናልና
ሮዛ፡- አዎ
ጌትነት፡-እንደዛ ማድረግ እንችል ነበረ።
ሮዛ፡- ባለፈው አመት ነው?
ጌትነት፡- እ
ሮዛ፡- ባለፈው አመት ነው?
ጌትነት፡-ባለፈው አመት፤አሁን ለእኔ አላቅም እንግዲህ አዲስ ለጀመርናቸው ነገሮች ለምሳሌ እንደፒኤችዲ አይነት ፕሮግራሞች አሉን
ሮዛ፡- እህ
ጌትነት፡- ያው ለሚመጣው ሰው ኢንፎርሜሽን ትነግሪያለሽ
ሮዛ፡- ሲመረቁ
ጌትነት፡- አዎ ሲመረቁ ኢቭን የሆነ ታይም ላይ እንትን ነው ሪላክስድ ነው የጎንደር ኢንቫሮመንት
ሮዛ፡- አኬ (አኮ 003፣ መስመር1122-1146)

ከቀረበው አስረጅ እንደምንመለከተው ሴቶች በውይይት ሂደት የሃሳብ ልውውጥ በማድረግ በኩል ችግር እንዳለባቸውና ድስኩሩ የአንድ ወገን እንዲሆን በማድረግ የሃሳብ ልውውጡ እንዲገታ እንደሚደርጉ ያሳያል። በዚህ መረጃ ጌትነትና ሮዛ ያደረጉት የሀሳብ

ለውውጥ የአንድ ወገን ብቻ ሲሆን፤ ጌትነት ላቀረበው ሀሳብ ሮዛ በተረዳችው መሰረት አሉታዊም ይሁን አዎንታዊ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ‹፣እህ›› በማለት ጌትነት ንግግሩን እንዲቀጥል አድርጋለች፡፡ በዚህም በሁለቱ መካከል ያለው የሃሳብ ልውውጥ የአንድ ወገን ብቻ በመሆኑ የሮዛ ምላሽ አዎንታዊ ይሁን አሉታዊ ጌትነት መረዳት ያልቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

በአጠቃላይ ለጥናቱ በተወሰዱት ድስኩራዊ አሃዶች የሃሳብ ልውውጡ ሲታይ በአብዛኛው የተሳተፉት ወንዶች ሲሆኑ በዚህም የወንዶች የሃይል የበላይነት ሲታይ፣ ሴቶች በአብዛኛው በሃሳብ ልውውጡ ያላቸው ድርሻ ዝቅተኛ ሲሆን በሚሳተፉበት ሁኔታዎችም ሲታዩ የተብራራ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ አጫጭር መልዕክቶችን በማስተላለፍና በጥያቄ ላይ የተመሰረተ ምላሽ ይሰጣሉ፡፡ አልፎ አልፎ ደግሞ ለቀረበ ሃሳብ ምላሽ ሲሰጡ በወንዶች የሚሰጠው ምላሽ እነሱ ባቀረቡበት ሳይሆን አድማጩ በተረዳበት ሁኔታ ሲቀርብና ተቃርኖ ሲፈጠር ይታያል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ በንግግር ያላቸውን ተሳትፎ እንደሚቀንሰው ሰብሳቢው የሚሰጠው ምላሽ ተገቢ ካልሆነና ጭቅጭቅ ባለበት ሁኔታ መናገር እንደማይፈልጉ ከቡተቃ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል፡፡ በተጨማሪም ሴቶች ሀሳባቸው በዝርዝር ከመግለጽ ይልቅ ጭንቅላታቸውን በማወዛወዝ ‹‹እህ›› የሚል የአድማጭ መከታተያ ድስኩራዊ ቃልን በስፋት የሚጠቀሙ ሲሆን የእዚህ ቃል አጠቃቀም በአውዱ ስንመለከተው ተናጋሪው አድማጭ እንዳለውና ንግግሩን እንዲቀጥል ከማሳየት በስተቀር ለተናጋሪው ሀሳብ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ምላሽ የሚሰጥ አይደለም፡፡

4.3.2.4 መድረክ

የሰብሳቢነትንም ሆነ የተሳታፊነትን ሚና ይዞ መድረክን ባግባቡ መከታተልና መቆጣጠር ድርሻን ባግባቡ የመወጣት ብቃት መላበሻ ነው፡፡ በዚህ ጥናት በተወሰዱት መረጃዎች የመድረክ አጠቃቀምን ሁኔታ ከስርዓተፆታ አንፃር ስንመለከተው የተለያዩ ባህርያት ይታያል፡፡ በአብዛኛው ወንዶች የሚያገኟቸውን መድረኮች በመጠቀም ሀሳባቸውንና ራሳቸውን የመግለፅ ልማድ እንዳለቸው ታይቷል፡፡ በእርግጥ ወንዶች አንዳንድ ጊዜ ሴቶች በበዙበት አውድ ላይ ሀሳባቸውን ላይገልጹ እንደሚችሉ ከኢ.መ.001 የተወሰደው ድስኩራዊ አሃድ የሚጠቁም ሲሆን ይህ ሁኔታ ግን በተቃራኒው ሴቶች የበዙበት መደበኛ ውይይት

ሲሆን ወንዶች መድረኩን በመጠቀም ሀሳባቸውን ሲገልጹ ሴቶች ግን የማይሳተፉበት ሁኔታ እንዳለ ከመስክ ማስታወሻ የተገኘው መረጃ ያመለክታል። በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኛዎቹ ሴቶች መደበኛ የሆኑ ውይይቶች የሚደረጉባቸውን መድረኮች የመጠቀም ልምድ የሌላቸው ሲሆን፣ በተለይም ብዙ ወንዶች የተሰበሰቡባቸውን መድረኮች ተጠቅመው ሀሳባቸውን እንደማይገልጹና በምትኩ መናገር የሚፈልጉት ጉዳይ ካለ ከጎናቸው ለተቀመጠ ሰው በሹክሹክታ እንደሚናገሩ ወይም ከመድረክ ጀርባ ማለትም ከስብሰባው ሲወጡ ለሚመለከታቸው ሰዎችና ለጓደኞቻቸው ሀሳባቸውን እንደሚያቀርቡ ከቡተቃ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

> መቅደስ፡- በትልልቅ ስብሰባዎች አዎ መናገር የምፈልገው ያውም የመፍትሄ ሀሳብ ይሆናል የምለውን ሀሳብ ስለምፈራ ብቻ ሳልናገር ሁሌም እወጣለሁ። እንዳልኩሽ ሀሳቤን አጠገቤ ላለች ወይም ወንድ ሊሆን ይችላል እነግረዋለሁ። ካልሆነ ስወጣ ለጓደኞቼ ይሄ ነገር እኮ እንዲህ ነበር ብየ እናገራለሁ። በጣም ጥሩ ሀሳብ ነበር ይሄ ሲሉኝ ደግሞ በጣም እናደዳለሁ ባለመናገሬ። የሚገርማችሁ ግን አንድ ሁለት ቀን ከሆነ ወንድ ባልደረባየ ጋር ተቀመጥኩና መናገር የምፈልገውን ሀሳብ ይሄ እኮ እንዲህ ማለት ነው እና እንዲህ ቢሆን ይሻል ነበር ብየ ነገርኩት። እሱም እጁን አወጣ ሁለቱንም ቀን እድሉ ተሰጠው የእኔን ሀሳብ ከራሱ ጋር አዋህዶ አቀረበው (ቡተቃ 203፣ መስመር145-153)።

ይህ ሃሳባቸውን የሚገልጹበት ሂደት ደግሞ አንዳንዴ ቁጭት እንደሚፈጥርባቸው ገልፀዋል። ይኸውም ከጓደኞቻቸው የሚያገኙት ምላሽ ጥሩ ከሆነ ያን መድረክ ተጠቅመው ሀሳባቸውን ባለማቅረባቸው ይቆጫሉ። በተቃራኒው ሴቶች ብቻ የተሰበሰቡበት መድረክ ከሆነ በነፃነት እንደሚናገሩና መድረኩ ምቹ እንደሆነ ይገልፃሉ። ቀጥሎ የቀረበውን ዋቢ እንመልከት፡-

> እየሩስ፡ ሴቶች ነፃ ሆነው መደበኛ ባልሆነ ስብሰባ ሃሳብን ለመግለጽ ወይም ነገሮችን ለማቅረብ ሲፈለግ ለብቻቸው ሲሰበሰቡ ጥሩም ይሆናል እርግጠኛም ነኝ። እንደዛ መደበኛ በሆኑ ስብሰባዎች የማይናገሩትን ኢመደበኛ ስብሰባ ከሆነ ሊናገሩ ይችላሉ። ካለኝ ልምድ ነው። ለብቻችን እንሰባሰባለን አንዳንዴ መሪ የምሆንበት ወቅትም አለኝ። ፕሮሲጀራል የሆነ ነገር አይደለም። እና ደስ ይላል። እና ያ ሁኔታ በጣም ይመቸኛል እኔ። ...እናም ኢንፎርማል በሆኑ ስብሰባዎች ከሴቶች ጋር መሆን ደስ ይለኛል። (ቡተቃ 202፣መስመር 198-204)

ሴቶች የንግግር ድርሻን በተገቢው ጊዜ በመውሰድ መድረክን በአግባቡ ሲጠቀሙ አይታይም። ለመስሌ በአኮ.002 ውብነሽ የፋሲል ንግግርን አዳምጣ በተረዳችው መሰረት መመለስ ሲገባት ጉዳዩን የማቃለልና ምላሽ ከመስጠት የመቆጠብ ሁኔታ ማሳየቷ እሷም መድረኩን በመቆጣጠር የድርሻዋን እንዳትወጣ አግዷታል። ከዚህ በተጨማሪም የንግግር ድርሻ በተገቢው ጊዜ ባለመውሰዷ ድስኩሩን ወደኋላ የመመለስ ሁኔታ እንዳሳየች የሚከተለውን አሃድ በዋቢነት መመልከት ይቻላል።

> ውብነሽ፡- ... አበበ መጀመሪያ ስትናገር ከካሪክለሙ ኤሲ ላይ ሲፀድቅ አልክ፤ ኤሲ ላይ አልፀደቀም አልተነሳም (አባሪ 02፣ መስመር162-163)።

ውብነሽ ንግግሯን ወደኋላ በመመለስ ‹‹አበበ መጀመሪያ ስትናገር›› በማለት ሰብሳቢው ኤሲ ላይ ፀድቋል ያለውን ካሪክለም እንዳልፀደቀ ተቃውማለች። በመሰረቱ በዲስኩር ንድፈሃሳባዊ አካሄድ ስንመለከተው ዲስኩር ወደፊት እንጅ ወደኋላ አይመለስም (ሮጀርስ፣2004)። ውብነሽ ዲስኩሯን ወደኋላ ወይም ወደመጀመሪያው አጀንዳ የወሰደችው የንግግር ድርሻ በተገቢው ጊዜ ባለመውሰዷ ነው። ጉዳዩ ሲነሳ ወዲያውኑ ሀሳቧን በማቅረብ በወቅቱ ማስተካከያ እንዲደረግ በማድረግ ግንዛቤ ማስያዝ ትችል ነበር። ይህ የሚያሳየው በውይይቱ ላይ የሚሳተፉ ሰዎች በተገቢው ጊዜ መድረኩን ካላገኙ ውይይቱን (ዲስኩሩን) ወደኋላ እንደሚጎትቱ አመላካች ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ከተሰጣቸው ሚና በላይ ድርሻ በመውሰድ አንድን ጉዳይ ከሚገባው በላይ ደጋግሞ በማንሳት አድማጭን ያለመረዳትና መድረክን በአግባቡ ያለመጠቀም ችግር ተስተውሏል። ለዚህም በአኮ 002 የፋሲልን፣ በአጠመ.006 የእሱባለውን ድርሻ አወሳሰድ ብንመለከት ሁለቱም ላይ ታዳሚው ንግግራቸውን እንዲያቆሙ የተንጫጫባቸው ሲሆን ይህም የተሰጣቸውን የንግግር ድርሻ በተገቢው መጠን መጥኖ መቼ ማቆምና መናገር እንዳለባቸው አለመረዳታቸውንና የመድረክ አጠቃቀማቸው ተገቢ እንዳልሆነ ያስረዳል።

መድረክን መጠቀም ሲባል በተሰብሳቢነት ብቻ ሳይሆን የሰብሳቢነት ድርሻንም ይዞ በተገቢው ሁኔታ ድርሻን መወጣትንም ያካትታል። ከዚህ አኳያ ሲታይ በተወሰዱት ድስኩራዊ አሃዶች በአብዛኛው ስብሰባዎች የተመሩት በወንዶች ሲሆን፣ የመድረክ አጠቃቀማቸውን ስንመለከት ለተሳታፊዎች ድርሻ በመስጠት ረገድ ችግር ያለባቸው

ቢሆኑም የራሳቸውን ሀሳብና ማንነት በመግለጽ መድረኮቹን በመጠቀም ረገድ ግን ጥሩ ልምድ እንዳላቸው የተወሰዱት መረጃዎች ያሳያሉ። በዚህ ጥናት ከተወሰዱት መረጃዎች ስብሰባን የመምራት ድርሻ የነበራት አንድ ሴት ስትሆን ይህች ሴት የሰብሳቢነት ድርሻዋን በመጠቀም ሀሳቧንም ሆነ ራሷን በመግለጽ ረገድ እንዲሁም ለተሰብሳቢዎቹ ድርሻ በመስጠትና ድርሻቸውን ጠብቀው እንዲናገሩ በማደርግ በኩል ከፍተኛ ጉድለት የታየበት ነው። ለዚህም በአኮ003 የቀረበውን ድስኩራዊ አሃድ ሙሉውን ብንመለከት ሮዛ አንድም ጊዜ ለተሳታፊዎች የንግግር ድርሻ ስትሰጥ አትታይም። ከዚህ በተጨማሪም ሀሳቧን ስታቀርብ ሌሎች ጣልቃ በመግባት የንግግር ድርሻዋን ስትነጥቅ በተደጋጋሚ ይታያል። ይህም ሮዛ በሰብሳቢነት ያላት የመድረክ አጠቃቀም ልምዷ አናሳ እንደሆነና በሰብሳቢነት ሚናዋና በተሰብሳቢዎች ድርሻ መካከል ያለው የሀይል ሚዛን ተገቢ እንዳለሆነም አመላካች ነው።

4.3.2.5 አለመደማመጥ

ብዙ ጊዜ በውይይት ሂደት አለመደማመጥ የሚፈጠረው ድርሻን ጠብቆ ካለመናገርና ተደራርቦ የመናገር ሁኔታ ሲኖር የሚፈጠር ድስኩራዊ ልማድ ነው። በዚህ ጥናት የተወሰዱት ድስኩራዊ አሃዶች ሲፈተሽ በአብዛኛው በትላልቅ መደበኛ ስብሰባዎች ላይ እና የዩኒቨርሲቲው ሃላፊዎች በሚሰበስቧቸው ስብሰባዎች ላይ ድርሻ ጠብቆ የመናገር ሁኔታ ያለ ሲሆን በእንደዚህ አይነት አውድ በመደራረብና ጣልቃ በመግባት የተፈጠረ አለመደማመጥ የታየበት አጋጣሚ የለም (አጠመ 006 ይመለከቷል)። ሆኖም ግን በፋካሊቲና በፕሮግራም ደረጃ በሚደረጉ ውይይቶች ላይ ግን ብዙ ጊዜ አለመደማመጥ ያጋጥማል። ለዚህም ዋቢ የሚሆኑ መረጃዎችን ቀጥለን እንመልከት፡-

አኮ 003 የቀረበውን ድስኩራዊ አሃድ ወስደን ስንመለከት በመጀመሪያ ውይይቱ በዩኒቨርሲቲው ምክትል ፕረዚዳንት በሚመራበት ጊዜ ሰብሳቢው ለረጅም ጊዜ ንግግር በማድረግ መድረኩን ተቆጣጥረውት የነበረ ሲሆን ሌሎቹ ተሳታፊዎች ደግሞ ባዳመጡት መሰረት ምላሽ ከመስጠት የተቆጠቡበት ነበር። ሰብሳቢው ለታዳሚው ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ድርሻ ሲሰጡ ድርሻ የጠየቀና የወሰደ በእውቀቱ ብቻ ነው። ይህም ተሳታፊዎቹ የመናገር ፍላጎት ያልነበራቸው በመሆኑ ጣልቃ በመግባትም ሆነ በመደራረብ የተፈጠረ

አለመደማመጥ ብዙም አልታየም (መስመር16-190 ይመልከቱ)። ሆኖም ግን ሰብሳቢው (ዶ/ር ሀይሉ) ስለምርጫው ሂደት የተመለከተውን ውይይቱን ከጨረሰ በኋላ መድረኩን ለአካዳሚክ ኮሚሽኑ አባላት ትቶ የሄደ ሲሆን፣ ቀጥሎም የፋካሊቲው ዲን ሮዛ ይህን የኮሚሽን ስብሰባ ለረጅም ሰዓት መርታለች። በዚህ ሂደት የነበረውን መድረክ ስንመለከት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው ድረስ የነበረው ውይይት የንግግር ድርሻ ሰጭም ሆነ ተቀባይ ያልነበረበት፣ የንግግር ድርሻ የሚወሰደው ቀድሞ በተናገረ ከመሆኑ ጋር ተተያይዞ ጣልቃ ገብነትና ተደራርቦ የመናገር ሁኔታ በስፋት ታይቷል።

አስረጅ፡-

ሮዛ፡- ስለሚችል እንደገና ውል ማደስ አያስፈልግም በማለት የትምህርቷ
በእውቀቱ
ጌትነት፡- የመምህርቷ
ሮዛ፡- የመምህርቷ የትምህርት ጊዜ ከህዳር (መስመር 431-34)
ተስፋ፡- ስንተኛ አመት?
ጌትነት፡- ሶስተኛ አመት
ሮዛ፡- ሶስተኛ አመት
መቅደስ፡- የ2003 ተመራቂ ነበረ (መስመር468-71)
ጌትነት፡- መብት የለውም መብት የለውም (መስመር 580)
ዶር. አበበ፡- ፈተና ከፈተንክ ውጤት ማስገባት የግድ ነው (መስር 581)
ተስፋ፡- ኤፍም ቢሆን ምንም ቢሆን ፈተና ከፈተንክ ውጤት ማስገባት ነው
ጋሻው፡- አይደለም (መስመር 583)
ተስፋ፡- ስለዚህ ያለው ግሬድ በሙሉ ይሰረዝና
[መቅደስ፡-አይደለም
[ጌትነት፡- አይደለም
[ሮዛ፡- ያለው አይሰረዝም
[ጋሻው፡- አልገባህም እንዴ! አንድ ተጨማሪ ማብራሪያ አለኝ6 (መስመር15-19)
ጋሻው፡- ኤፍ ይሆናል
ተስፋ፡- አዎ
ጌትነት፡- አዎ አዎ (መስመር 669-71)
ጌትነት፡- አሁኑኑ መወሰን አለበት ይኸ ጉዳይ፤ የኮሚሽኑ ውሳኔ እንዲሆን
በእውቀቱ፡- ኮምፕሊት ዲስሚሳል ከሆነማ ምን አማራጭ አለው።
ተስፋ፡- ምን ታደርገዋለህ
ጌትነት፡- ኖ ሪቨርስ ማድረግ ይገባን ይሆን ወይ (መስር 733-36)
ጌትነት፡- ለቀረበት ምክንያት
[በእውቀቱ፡- ማስረጃ ያምጣ ያን ማስረጃ እስኪያመጣ ድረስ ግን ክላስ አቴንድ ያድርግ ተብሎ... (መስመር 773-75)
ሮዛ፡- እህ
[ተስፋ፡- ለማንኘውም እሱን እናናግረው
ጋሻው ፡- አዲስ ነገር ሊኖር ስለሚችል እንየው።
ሮዛ፡- አሃ አቴንዳስና...
መቅደስ፡- ካልገባስ ክላሳቸው
በእውቀቱ፡- እ

[መቅደስ፡- ካልገባስ ክላሳቸው፣ 85 ፐርሰንቱን እኮ መከታተል አለበት (መስመር 900-03)
ተስፋ፡- አቴንድ አላረገም ብሎ የሚል ከሆነ አይ ማስተላለፍ የግድ ነው...
ሮዛ፡- አዎ
መቅደስ፡- አዎ
ጌትነት፡- አዎ (መስመር906-09)
ጌትነት፡- አዎ ቲሲሱን እንድቀጥልበት ነው የሚለው
መቅደስ፡- ቴሲሱን እንዲጨርስ...አዎ(መስመር 975-76)
ሮዛ፡- ያ... ካቀረበ በኋላ አስተካክሎ መምጣት ምናምን ነው።
በእውቀቱ፡- አድቫይዘሩ አሁን...
ተስፋ፡- አመልክቷል? (መስመር 979-81)
ሮዛ፡- አለ እኔ ጋ፣ አንድ የተማሪ ጉዳይ እ፡ ያጭበረበሩ ተማሪዎች ናቸው፤ ፈተና
[ጌትነት፡- ማስረጃ ካለ ዜሮ
[መቅደስ፡- ውይ!ማስረጃ ካለ ዜሮ ቀጥታ 1034-36
በእውቀቱ፡- አዎ
ጌትነት፡- አዎ (መስመር 1089-90)
በእውቀቱ፡- የመምህራን ራሱ
ጌትነት፡- የመምህር ራሱ (መስመር 1110-1111)

ከቀረበው ቅንጫቢ መረጃ እንደምንረዳው ድርሻን በተገቢው መንገድ ባለመውሰዳቸው የተፈጠረ መደራረብና ጣልቃ ገብነት ሲሆን በዚህም የሚያፈልቁት ዲስኩር አጫጭር ከመሆኑም በላይ ያልተሟላ ነው። ይህ ሁኔታ በዚህ ኮሚሽን በአብዛኛው ድርሻን በየተራ በመውሰድ ተደማምጦ የመናገር ልምዱ እንደሌለ ይጠቁማል። ለዚህም ሰብሳቢዋ ለተሳታፊዎቹ የንግግር ድርሻን ተራ በተራ በመስጠት እንዲናገሩ በማድረግ በኩል ሚናዋን በትክክል እንዳልተወጣች መረጃው ይጠቁማል (መስመር 229-1123 ይመለክቱ)።

በአኮ 002 የተወሰደው ድስኩራዊ አሃድ ሲፈተሽ ደግሞ በተወያዮቹ መካከል የተፈጠረ ተደራርቦ የመናገር ሁኔታ ብዙም ባለመኖሩ እንደ ችግር የሚታይ ያለመደማመጥ ሁኔታ አልታየም። ሰብሳቢው እጅ ላወጡ ሰዎች የንግግር ድርሻ በመስጠትና እሱ እንዲናገሩ የሚፈልጋቸውን ሰዎች ደግሞ ስም በመጥራት ጣልቃ ገብነትን በመቆጣጠር ተደራርቦ መነጋገር እንዳይፈጠር ጥረት ሲያደርግ ታይቷል። ሆኖም ግን አንዳንዴ የንግግር ድርሻን ለመንጠቅ ጣልቃ የሚገቡ ሰዎች እንዳሉ መረጃው ይጠቁማል። ከዚህ በተለየ ሁኔታ ግን በውይይቱ መጨረሻ ላይ ሰብሳቢው ባቀረበው የመፍትሄ ሀሳብ ዳኞቹው ባለመቀበሉ ምክንያት በተፈጠረ አለመግባባት ተወያዮቹ ጣልቃ በመግባትና ተደራርቦ

በመናገራቸው ምክንያት ያለመደማመጥ ሁኔታ ታይቷል። ቀጥሎ የቀረበውን አሃድ በዋቢነት እንመልከት፡-

ዳኛቸው፡- ምናልባት የእኔ አባላቶች ከተስማሙ ዌል። ለእነኚህ ለሁለት ኮርሶች ግን እኔ በዚህ ስንት አመት ስሰራ ቆይቼ ለሌላ አሳልፌ መስጠት ከፕሮግራሙ ህልውና አንፃር አይታየኝም።
[አበበ፡- አሳልፎ በመስጠት መንፈስ ባታያቸው ደስ ይለኝ ነበር።
ዳኛቸው፡- ስለዚህ እኔ
ተሰብሳቢው፡- (ሁሉም ለመናገር በመደራረብ ተናገሩ)
አለሙ፡- ለዚህ እኮ ነው እንዲህ ያልኩት ምክንያቱም አሁን የምንግባባ አልመሰለኝም።
አበበ፡- አሁን እኮ ተግባብተናል፤ ተግባብተናል አሁን፤ በቃ ኢት ኢዝ ናችሯል
አለሙ፡- ዶሚኔትድ እንዳይሆን እሰጋለሁ።
መለሰ፡- ሶሪ የስብሰባ ደንብም እንከተል እንጅ በጣም ሁለታችን ወደአንድ ፎረም ከመጣን የሃሳብ ልዩነት ብዙም እኮ ሊኖር አይገባም። ፕርሰንቱን እንይ፣ የሀሳብ ልዩነት አሁን ሁለት ሶስት ጊዜ እዋዣቅ የለ፣ ምን እንትን አለ። አሰራር ላይ ችግር ከተፈጠረ ፋሲል እንደሚለው በመግባባት እዚህ አለን፣ ኮርስ ቼር አለች፣ ፕሮግራም ማናጀሩ አለ የእሱም ምስክርንት የሚስፈልገው ለዚህ ነው። ሲኒየር ስታፎችም እዚህ አለን በመግባባት ሶልቭ እናደርገዋለን። በቃ በዛ መንገድ ነው መኬድ ያለበት። ወደፎርማሉ በጭራሽ እኔ አልደግፍም።
ደበበ፡- የሊትሬቸር በሁለቱም ትምህርት ክፍሎች ያሉት ስታፍ እንትን እንዳለ....
[መለሰ፡- በቃ እንደዚህ ይሁንና በቃ...የሌላሰው ችግር ሄደን የምናቃልል ሰዎች የራሳችን
አበበ፡- አዎ በቃ፣እናመሰግናለን! በዚሁ ተፈታ ማለት ነው።
ዳኛቸው፡- አይ፣ እኔ በልዩነት ይያዝልኝ! (መስመር 1077-1094)

ድስኩራዊ አሃዱን እንደምንመለከተው ሶስት ጊዜ ጣልቃ ገብነት ሶስት ጊዜ መደራረብ የተፈጠረ ሲሆን፣ሁሉም የየራሱን ሃሳብ ብቻ በማቅረብ አንድ ውሳኔ ላይ ሳይደረስ መድረኩ ተበትኗል። ሰብሳቢው ‹‹አዎ በቃ፣ እናመሰግናለን! በዚሁ ተፈታ ማለት ነው።›› ቢልም በምን እንደተፈታ ግን የተጨበጠ ነገር የለም። በመሆኑም በመደራረብና ጣልቃ በመግባት የተፈጠረው አለመደማመጥ ውይይቱ ወደአንድ ማጠቃለያ እንዳይደረስና የተበታተነ ስሜት እንደተያዘ ስብሰባው እንዲበተን አስገድዷል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከኢመደበኛ ውይይት የተወሰዱት ድስኩራዊ አሃዶች እንደሚያሳዩት ከሆነ አለመደማመጥ እንደውይይቱ አካሄድ የሚወሰን ይሆናል። ለምሳሌ በኢመ 004 የፈለቀውን ድስኩራዊ አሃድ ስንመለከት መደራረብም ሆነ ጣልቃ ገብነት ባለመኖሩ

ውይይቱ መደማመጥ የነበረበት አውድ ነው። ለዚህም ምክንያቱ ተሳታፊዎች ሀሳባቸውን እንዲገልጹ የውይይቱ መሪ ድርሻ በመስጠት ሚናውን በተገቢው ሁኔታ በመወጣቱ ነው።

ከዚህ በተለየ ሁኔታ ግን በኢመ 001 ላይ የታየው ውይይት መደራረብ፣ ጣልቃ ገብነትና የጎንዮሽ ወሬ የበዛበት ስለነበረ በከፍተኛ ደረጃ አለመደማመጥ የታየበት አውድ እንደነበረ መረጃው ያመለክታል። የውይይቱ ተሳታፊዎች አብዛኛዎቹ ሴቶች ሲሆኑ በአንድ ሰው የሚቀርብን ሀሳብ በማዳመጥ ድርሻቸውን ጠብቀው የሀሳብ ልውውጥ ሲያደርጉ አይታዩም።

አስረጅ፡-

አዳነች፡ እኔ ግን የማይመቹኝ ሰው ማን ናቸው ዶር. ከበደ ናቸው።
ማርቆስ፡ ኧረ ባክሽ! አታውቂያቸውም?
አዳነች፡ ብዙ ኦፖርቺንቲስ ላይ አግኝቻቸው አልወዳቸውም።
ማርቆስ፡ ዶር ከበደ?
መዓዛ፡(በመደራረብ) እኔ ደግሞ በጣም ነው የምወዳቸው። ሲያስተምሩ እኮ... በጣም ጎበዝ ናቸው። እሳቸው!...
አዳነች፡ እህ
ማርቆስ፡ ለምን?
[ሶፍያ፡ዶር. ከበደን እኔ በዝና ነው ያማውቃቸው። አንዷ ልጅ መጣችና ቢሯቸው ‹‹ምን ፈልገሽ ነው›› አሏት ‹‹ዶር. ከበደን ፈልጌ ነበር አለቻቸው ›› ‹‹የለሁም›› ‹‹መቼ ይመጣሉ ልጠብቃቸው››((ሳቅ)) ስትላቸው በይ ግቢ ብለው አስተናገዷት ይባላል። ተረቴን መልሱ አፌን በዳቦ አብሱ ((ሳቅ))።
[መዓዛ፡ (ለውብነሽ ብቻ ገለፃ ስታደርግ)እንዴት መሰለሽ ልጅቷ ተማሪያቸው የነበረች አሁን ግን ጋዜጠኛ ነች። ቢሯቸው በር ላይ ቆማ አይተዋታል። ግን ረስተዋት ሌላ ስራ ሲሰሩ ቆዩና ቀና ሲሉ ቆማለች። ‹‹ምን ፈልገሽ ነው›› አሏት። ‹‹ዶር ከበደን ፈልጌ ነበር›› ‹‹የለሁም›› መቼ ይመጣሉ ልጠብቃቸው›› ስትላቸው በይ ግቢ ብለው አስተናገዷት። ሌላው አመላቸው ደግሞ ደህና አደሩ ስትያቸው ምንአገባሽ፣ ያንች ጉዳይ ነው የእኔ ደህና ማደር
[ሶፍያ፡ (ጣልቃ ገብነት)እንዴት አደሩ ሲባሉ እንዴትስ ባድር ምን አገባሽ(ሳቅ) እንዴት አደሩ ተብሎ ይጠየቃል ይሉሻል ሁሉም በመደራረብ ስለሚናገሩ መደማመጥ የለም
[ሶፍያ፡ እኔ ደስ የሚሉኝ ዶር ይመር...
[አዳነች፡ ዶር ይመር ፈኒ! በእውነት አንድ ቀን ሲያወሩ ሲያወሩ (ኢመ 001፣ መስመር 26-46)።

የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በአዳነች የተገለፀው የዶክተር ከበደ ጉዳይ መዓዛና ሶፍያ ጣልቃ በመግባትና በመደራረብ ያቀረቡት ሀሳብ አዳነች ሀሳቧን እንድታቋርጥ ከመሆኗ በላይ እንዳትደመጥ ተፅዕኖ አድርገዋል። በዚህም ምክንያት የጀመረችውን ሀሳብ አቋርጣና በማርቆስ ለተጠየቀችው ጥያቄ ማብራሪያ ሳትሰጥ ወደሌላ ርዕሰ ጉዳይ እንድትገባ

አድርጓታል። ያሶፍያ ጣልቃ ገብነት የንግግር ድርሻን በመንጠቅ ብቻ ሳይሆን የውይይት አጀንዳንም በማስቀየር ሌላ ርዕሰ ጉዳይ ጣልቃ በማስገባት የውይይቱ ጭብጥ እንዲቀየር አድርጋለች።

በሌላ በኩል ደግሞ ሀሳባቸውን በጋራ ከማቅረብ ይልቅ ከጎናቸው ካለ ሰው ጋር የጋራ የሆነውን ርዕሰ ጉዳይ ወደሁለትዮሽ በመውሰድ ያለመደማመጥ እንዲፈጠር ሲያደርጉ ይታያል። ለምሳሌ ከቀረበው መረጃ እንደምንመለከተው በሶፍያ ለጋራ ውይይት የቀረበው ርዕሰ ጉዳይ መዓዛ አጠገቧ ለተቀመጠችው ለውብነሽ ደግማ አቅርበዋለች። ይህም ሶፍያ ስለ ዶ/ር ከበደ ያቀረበችው ሀሳብ አንደኛ ያልተሟላ እንደሆነ በመዓዛ የተጨመሩት ‹‹.....ልጅቷ ተማሪያቸው የነበረች አሁን ግን ....ጋዜጠኛ.....አይተዋት ግን ረስተዋት.....ቀና ሲሉ....›› እና በሶፍያ የቀረበው ‹‹....በዝና ነው የማውቃቸው.... ተረቴን መልሱ አፌን.....›› የሚሉት አሃዶች መቅረባቸው እና ከዚህም በተጨማሪ ለዚህ መረጃ ዋናዋ ምንጭ መዓዛ ለመሆኗ ያቀረበቻቸው ተጨማሪ መረጃዎች የእሷ ለመሆኑ በንግግሯ መነሻ ላይ ‹‹....እንዴት መሰለሽ...›› ብላ መጀመሯ አመላካች ሲሆን ይህን በማድረግ ሂደት ግን የሀሳብ ልውውጡ በጋራ ሳይሆን የጎንዮሽ በመሆኑ አለመደማመጥ እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል። በዚህ ውይይት ሳባና ውብነሽ አንድም ጊዜ ሀሳባቸውን ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ ለጋራ ውይይት ሲያቀርቡ ያልታዩ ሲሆን በተቃራኒው ግን የሚቀርበውን ሀሳብ ካዳመጡ በኋላ ያላቸውን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ሀሳብ ሳባ፣ ውብነሽና አልማዝ ለብቻቸው በሹክሹክታ በመነጋገር ሀሳባቸውን ሲለዋወጡ ይታያሉ። ይህ ሁኔታ አሁንም አለመደማመጥ እንዲፈጠር ከማድረጉም በላይ ሀሳብ ለሚያቀርቡ ሰዎች ምን እያሉን ነው የሚል አሉታዊ ጎን ሊፈጥር ይችላል(መስመር 23 እና 60ን ይመለክቱ)። ከዚህ በተጨማሪም በኢመ 004 እና በአጠመ 006 ውይይቶች ላይ ሴቶች ሀሳባቸውን ለአጠቃላይ ውይይት ከማቅረብ ይልቅ ከጎናቸው ካለ ሰው ጋር (ወንድም ይሁን ሴት) በሹክሹክታ ሲያወሩ ይታያሉ። ይህ ደግሞ ሴቶች ሀሳብ ሲኖራቸው ለመድረኩ ከማቅረብ ይልቅ አጠገባቸው ላለ ሰው እንደሚናገሩ ከቡተቃ የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል (ቡድን 203፣ መስመር144-48 ይመልከቱ)።

4.3.2.6 ጣልቃ ገብነት

በውይይት ላይ የሚደረግ ጣልቃ ገብነት የግለሰብ ባህርይና ልማድ ቢሆንም፤ ይህ ልማድ በጉልህ እንዲታይ ደግሞ የስብሰባው አይነትና የሰብሳቢው ማንነት ይወስኑታል። በዚህ ጥናት የተወሰዱት መረጃዎች ከኢመደበኛና መደበኛ ስብሰባዎች አንፃር ስንመለከታቸው በአብዛኛው መደበኛ በሆኑና የተሰብሳቢዎቹ ቁጥር ከፍ ባለበት አውድ ጣልቃ ገብነት ያልታየበትና በምትኩ መደማመጥ የሰፈነበት ሆኖ ይታያል። ለአብነት ምልከታ በተደረገባቸው በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የተካሄዱ አጠቃላይ ስብሰባዎች ላይ ጣልቃ ገብነት ያልታየ ሲሆን ለዚህም አጠመ. 006ን በዋቢነት መመልከት ይቻላል። ከዚህ በተለየ መልኩ ግን መደበኛ ሆነው የተሰብሳቢዎቹ ቁጥር ዝቅተኛ በሆነበት አውድ ጣልቃ ገብነትን የሰብሳቢዎቹና የተሰብሳቢዎቹ ባህርይና የሀይል ግንኙነት ሲወስኑት ይታያል። ለምሳሌ አኮ 003ን ወስደን ብንመለከት በዚህ አሃድ ሁለት ባህሪያትንና ሁኔታን እንመለከታለን። አንደኛው በስብሰባው መጀመሪያ ላይ የዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ ሃላፊ ስብሰባውን የመሩበት አውድ ሲሆን በዚህ ሂደት ከተሰብሳቢዎቹ ምንም አይነት ጣልቃ ገብነት ያልነበረ ተሳታፊው የማዳመጥን ድርሻ ብቻ የያዘበት ሰብሳቢው ደግሞ የንግግር የበላይነትን ያሳዩበት አውድ ነው። በዚሁ ስብሰባ ላይ ሃላፊው (ዶ/ር ሀይሉ) ጨርሶ ከወጣ በኋላ ሮዛ የሰብሳቢነት ድርሻውን የያዘች ሲሆን የነበረው አውድ ግን የንግግር ድርሻ ሰጭና ተቀባይ ያልነበረበት፣ ጣልቃ ገብነትና ተደራርቦ መናገር በከፍተኛ ደረጃ የታየበት አውድ ሲሆን ይህም የሰብሳቢው ማንነት የስብሰባውን አወድ እንደሚወስነው ያሳያል (አኮ 003 ይመለከታል)። በሌላ በኩል ደግሞ ከአኮ 004 የተወሰደውን አሃድ ስንመለከት አውዱ እንደ አኮ003 ተመሳሳይ የአካዳሚክ ኮሚሽን ስብሰባ ሲሆን በዚህ አውድ እንደታየው ሰብሳቢው ለተሰብሳቢው የንግግር ድርሻ የሚሰጥ ሲሆን ተሰብሳቢዎቹ ደግሞ የንግግር ድርሻን በመውሰድ ይናገራሉ። በዚህም ምክንያትም መደማመጥ የሰፈነበትና ጣልቃ ገብነት ያልታየበት አውድ ነበር (አኮ 004 ይመልከቱ)።

በኢመደበኛ ውይይት ላይ ያለውን ጣልቃ ገብነት ስንመለከት ከተወሰዱት ሁለት ኢመደበኛ ውይይቶች መካከከል በኢመ004 በቀረበው ዲስኩር አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች ወንዶች ሲሆኑ ከፍተኛ መደማመጥ ያለበትና ጣልቃ ገብነት ያልታየበት አውድ ነው። ለዚህም ውይይቱ ኢመደበኛ ቢሆንም የውይይቱን ሂደት የሚመራና ለተሳታፊዎቹ የንግግር ድርሻ የመስጠት

ሚና የነበረው ሰው በመኖሩ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ከአውዱ መገመት ይቻላል። በኢመ001 በቀረበው ዲስኩር ደግሞ አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች ሴቶች ሲሆኑ ውይይቱን የመምራት ሚና ለማንም ያልተሰጠ ሲሆን ተወያዮቹ የውይይቱን ጉዳይ የሚወስኑትም ሆነ የንግግር ድርሻን የሚወስዱት ቀድሞ በተናገረ በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ ጣልቃ ገብነትና አለመደማመጥ የታየበት አውድ ነው። ይህም ሴቶች ኢመደበኛ በሆነና ሴቶች በበዙበት ውይይት ላይ ሀሳባቸውን በመግለጽ እንደሚሳተፉና በእንዲህ አይነት አውድ ላይ የጣልቃ ገብነት ልማድ እንዳላቸው መረጃው ይጠቁማል (ኢመ001 ይመልከቱ)።

ጣልቃ ገብነትን ከስርዓተ ፆታ አንፃር ስንመለከተው በመደበኛ ውይይት ላይ ወንዶች ጣልቃ በመግባት በመናገሩ ረገድ ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳሉ። ይህንም ለማድረግ የተለያዩ ብልሃቶችን ሲጠቀሙ ይታያሉ። ቀጥሎ የቀረቡትን ዋቢዎች እንመልከት፡-

> አለሙ፡-‹‹...ማሳሰቢያ! እዚህ ጋ ይቅርታ›› (አኮ.002፣መስመር 19)
> አለማየሁ፡- ‹‹...እዚህ ጋ ይቅርታ ማስተካከያ?›› (አኮ.002፣መስመር 179)
> ፋሲል፡- [እዚህ ጋ ማስተካከያ ስላለኝ ነው። እዚህ ጋ ማስተካከያ ስላለኝ ነው (አኮ.002፣መስመር 257)
> [ደበበ፡- ማስተካከያ(ኮ.002፣ አመስመር 380)

የቀረበው መረጃ እንደሚጠቁመው ወንዶች ማሳሰቢያ፣ ይቅርታ፣ ማስተካከያ... የሚሉትን ሀይል የሚሆኑ ቃላት በመጠቀም ጣልቃ በመግባት የመናገር ባህሪያቸው ከፍተኛ ይመስላል። የሴቶቹን ባህሪ ስንመለከት ደግሞ በመደበኛ ውይይቶች ላይ ጣልቃ በመግባት ለመናገር ሲደፍሩ አይታዩም። ሆኖም ግን ኢመደበኛ በሆነና ሴቶች በበዙበት አውድ የጣልቃ ገብነት ልማድ እንዳላቸው ከኢመ001 የተወሰደው ድስኩራዊ አሃድ አመላካች ነው። ጣልቃ ሲገቡ የሚጠቀሙበት ስልት ደግሞ ከወንዶቹ የተለየ ሲሆን፣ ማቅረብ የሚፈልጉትን ሃሳብ በቀጥታ ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ የአድማጭን ጆሮ በመያዝ ያቀርባሉ።

አስረጅ፡-

> አዳነች፡ ብዙ ኦፖርቹንቲስ ላይ አግኝቻቸው አልወዳቸውም።
> ማርቆስ፡ ዶር ከበደ?
> _መዓዛ፡ እኔ ደግሞ በጣም ነው የምወዳቸው። ሲያስተምሩ እኮ... በጣም ጎበዝ ናቸው። እሳቸው!...
> አዳነች፡ እህ

ማርቆስ፡ ለምን?
[ሶፍያ፡ ዶር. ከበደን እኔ በዝና ነው የማውቃቸው። አንዷ ልጅ መጣችና .....
[መዓዛ፡ እንዴት መሰለሽ ልጅቷ ተማሪያቸው የነበረች .....
[ሶፍያ፡ እንዴት አደሩ ሲባሉ እንዴትስ.....በመደራረብ ስለሚናገሩ መደማመጥ የለም
[ሶፍያ፡ እኔ ደስ የሚሉኝ ዶር ይመር...
[አዳነች፡ ዶር ይመር ፈኒ! በእውነት አንድ ቀን .....
[ሶፍያ፡ እሳቸው ሶደሬ ሄጀ አሉ፣ ውይ ሰው ውይ ሰው ልብስ እኮ.....
[አዳነች፡ ኤርትራውያን አሉ ደግሞ.... (ኢመደ001፣ መስመር 28-64)

ከቅንጫቢው ድስከራዊ አሃድ እንደምንመለከተው ለምሳሌ አዳነች ዶ/ር ከበደን ‹‹... አልወዳቸውም›› በማለት ላቀረበችው ሀሳብ መዓዛ ድምጿን ከፍ በማድረግ ‹‹እኔ ደግሞ በጣም ነው የምወዳቸው›› በማለት ጣልቃ ገብታ የአዳነችን የንግግር ድርሻ በመንጠቅ ሀሳቧን አቅርባለች። የሶፍያንና የአዳነችን ጣልቃ ገብነትንም ስንመለከት ጣልቃ ገብነታቸው ተደማጭነት እንዲያገኝ በመጀመሪያ የሚያቀርቡት ሀሳብ ስለ ዶ/ር ከበደና ይመር ማንነት የሚያውቁትን ማሳወቅ ላይ የተመሰረተ ነው። ጣልቃ ገብነታቸው ደግሞ ተደማጭነትን እንዲያገኝ ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ ያቀረቡ ሲሆን ከዚህም በላይ የንግግራቸው ድምፀት ስንመለከት ስነቃላዊ የሆኑ ‹‹...ሲባሉ፣አሉ›› የሚሉ አገላለጾችን መጠቀማቸው ንግግራቸው ለዛና ተደማጭነት እንዲኖረው ያደረገ ይመስላል።

የወንዶች ጣልቃ ገብነትን ስንመለከት ሁለት መልክ ያለው ነው። አንደኛው ድርሻ ጠይቀው ሲከለከሉ ድርሻን በሀይል ለመውሰድ ሲሆን፤ ሁለተኛው ግን ድርሻን እጅ በማውጣት መውሰድ የማይፈልጉና ድርሻቸውን መውሰድ በፈለጉበት ጊዜ የሰብሳቢውን ፈቃድ ሳይጠይቁ ጣልቃ በመግባት የሚናገሩበት ሁኔታ ነው። ድርሻን እጅ በማውጣት ከመውሰድ ይልቅ በሀይል ጣልቃ በመግባት የሚፈፅሙ በእድሜ፣ በትምህርት ደረጃና በተለያዩ የሃላፊነት ቦታዎች ያገለገሉ ወንዶች ሲሆኑ ጣልቃ ገብነትን የሚፈፅሙት ደግሞ ሰብሳቢው በስራ ልምድ ወይም በሃላፊነት ከእነሱ ያነሰ ሆኖ ሲገኝ ነው። ለዚህም የዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ ሃላፊዎች በሰበሰቡት ስብሰባ ላይ የፈለቁትን ድስኩራዊ አሃድ ለምሳሌ በአጠመ.006 ድስኩራዊ አሃድ ጣልቃ ገብነት አልታየም። በተለይም ደግሞ አኮ.003ን ስንመለከት በመጀመሪያ በዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ ሃላፊ የተመራው ውይይት ምንም ጣልቃ ገብነት ያልታየ ሲሆን፣ያው ውይይት በሮዛ ሲመራ ከፍተኛ የሆነ ጣልቃ

ገብነት የታየ ሲሆን፣ ይህም በሰብሳቢውና በተናጋሪው እንዲሁም በተናጋሪውና በአድማጮች መካከል ያለውን የሀይል ግንኙነት የሚያመለክት ነው።

4.3.2.7 ማስተካከያ/ተጨማሪ

ማስተካከያ ወይም ተጨማሪ በውይይት ሂደት ተናጋሪው ያጓደለው ወይም ሳይናገር የቀረው ሀሳብ አለ ተብሎ ሲታመን በሰብሳቢው ወይም በተሰብሳቢው ጠያቂነት ሀሳብ እንዲቀርብ የሚደረግበት ስልት ነው። በአብዛኛው በዚህ እንዲሳተፉ የሚገፋፉት በእድሜና በስራ ልምዳቸው ከፍ ያሉት ናቸው (አቲክሰን1999 እና ፌርክላፍ 2006)። በዚህ ጥናት በተወሰዱት መረጃዎች በሰብሳቢው አማካኝነት ማስተካከያ/ተጨማሪ ተብሎ ከተሰብሳቢው ሀሳብ እንዲቀርብ የተጠየቀበት ሁኔታ አላጋጠመም። ይልቁንም አከራካሪና አጨቃጫቂ ጉዳዮች በሚነሱበትና በዚህም አውድ ድርሻ የሚሰጠው በሰብሳቢው አማካኝነት በሚሆንበት ጊዜ ተሳታፊዎች ድርሻ በማያገኙበትና ተደጋጋሚ ድርሻ ፈልገው በሚከለከሉበት ጊዜ ማስተካከያ/ተጨማሪ አለኝ በማለት የንግግር ድርሻ ለማግኘት እንደብልሃት ሲጠቀሙበት ይታያል።

አስረጅ፡-

[ደበበ፡- ማስተካከያ...(መስመር 380)
[ፋሲል፡- እዚህ ጋ ማስተካከያ ስላለኝ ነው። እዚህ ጋ ማስተካከያ ስላለኝ ነው(አኮ002፣ መስመር 257)
[አለማየሁ፡- እዚህ ጋ ይቅርታ ማስተካከያ? (አኮ 002፣ መስመር179)

በአኮ 002 የቀረበው ድስኩራዊ አሃድ ከውይይቱ መጀመሪያው እስከ መጨረሻው ከፍተኛ የሆነ ጭቅጭቅና ክርክር የታየበት አውድ ነው። ሰብሳቢው ለተናጋሪዎች እጅ ሲያወጡና በእድሜና በስራ ልምዳቸው ከፍ ላሉት ደግሞ ስም በመጥራት ድርሻ በመስጠት ውይይቱን መርተዋል። በዚህ ሂደት ሰብሳቢው ተጨማሪ ወይም ማስተካከያ ሀሳብ እንዲሰጥ ተሰብሳቢዎቹን ያልጠየቁ ሲሆን፤ ተሰብሳቢዎቹ ግን በተለይም ድርሻ በተደጋጋሚ ለመውሰድ የሚፈልጉ አብዛኛዎቹ ወንዶች ማስተካከያና ተጨማሪን እንደብልሃት በመጠቀም ድርሻ ሲነጥቁ ይታያል። ከውይይቱ እንደምንመለከተው ሰፊ ልምድና እውቀት ያላቸው፣ በእድሜና በስልጣን የተሻሉት እና ወጣት ወንዶችም ‹‹ማስተካከያ›› በማለት

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES

ጣልቃ በመግባትና ተጨማሪ መረጃ በመስጠት ውይይቱን ፈር ለማስያዝ እንዲሁም ድርሻ ለመንጠቅ ሲሞክሩ ይታያል።

ለምሳሌ ደበበ በአኮ 002 እንደተመለከተው ‹‹ [ደበበ፡- ማስተካከያ...›› በማለት ማስተካከያን ድርሻ ለመንጠቅ እንደስልት ሲጠቀምበት ይታያል። ሆኖም ግን ሰብሳቢው (አበበ) ‹‹ አይ ችግር የለም። እናስተካክለዋለን...›› (መስመር 381-87) ማለቱና ድርሻውን መከልከሉ በደበበ ሊሰጥ የነበረው ማስተካከያ ምን እንደሆነና አላስፈላጊነቱንም የተረዳ ይመስላል። በተመሳሳይ ፋሲልም በተደጋጋሚ ‹‹ማስተካከያ ስላለኝ ነው›› በማለት ድርሻን ለመውሰድ ቢሞክርም ሰብሳቢው ግን ድርሻውን እንዲወስድ አልፈቀደም። ሌላው አለማየሁ ፋሲል ማብራሪያ በሚሰጥበት ሂደት ጣልቃ በመግባት ‹‹እዚህ ጋ ይቅርታ ማስተካከያ›› ቢልም ፋሲል ድርሻውን ባለማስነጠቁና ሰብሳቢውም ለማስተካከያው ቅድሚያ ባለመስጠቱ የአለማየሁ ማስተካከያ አልቀረበም (መስመር 178-80 ይመልከቱ)። ሰብሳቢውም ፋሲል ንግግሩን እንደጨረሰ የአለማየሁ ማስተካከያ እንዲቀርብ ከማድረግ ይልቅ የእሱን ጥያቄ በማቅረብና ቀጥሎ ያለውንም ድርሻ ለሌሎች ከሰጠ በኋላ በመጨረሻ አለማየሁ ድርሻ የተሰጠ ሲሆን ማስተካከያውንም በትክክል አቅርቧል (መስመር 210-14 ይመልከቱ)። ከቡተቃ የተገኘው መረጃም ማስተካከያ/ተጨማሪን ድርሻን ለማግኘት የሚጠቀሙበት ስልት እንደሆነ ያረጋግጣል።

አስረጅ፡-

> አገሬ፡- በአብዛኛው እጅ በማውጣት ነው። ካልሆነ ግን ይቅርታ እዚህ ጋ የተረሳ ነገር አለ፣ ማስተካከያ፣ማሳሰቢያ ሁሉ እላለሁ። ማሳሰቢያና ማስተካከያ ከተባለ ስለሚሰጥ ያቀረብሽው ማሳሰቢያ ነው ይበሉም አይበሉም ዝም ብየ በቀጥታ ሀሳቤን አቀርባለሁ (ቡተቃ 203፣መስመር 82-84)
>
> ካሳ፡- .....ብየ ዝም አልልም። ሀሳብ ካለኝ መግለፅ እፈልጋለሁ ወደኋላ አልልም። እጄን በማንሳት ሊሆን ይችላል ወይ ደግሞ በሰውነት እንቅስቃሴ ወይ ደግሞ ተጨማሪ አለኝ በማለት መናገር ስፈልግ ሳልናገር ቀርቼ አላውቅም። (ቡተቃ 202፣ መስመር182-83)

ማስተካከያን ድርሻ ለማግኘት እንደስልት የሚጠቀሙበት ከፍተኛ ስራ ልምድ ያላቸው ወንዶችም ሴቶችም ናቸው። መረጃው እንደሚያመለክተው አገሬና ካሳ ባካበቱት የስራ ልምድ ሀሳባቸውን መግለጽ ሲፈልጉ ማስተካከያ/ተጨማሪ በማለት እንዲሁም ሌሎችንም ብልሃቶች እንደሚጠቀሙ ያሳያል።

በሌላ በኩል ግን በዚህ ጥናት በተወሰዱት በሌሎቹ መረጃዎች ማስተካከያ/ተጨማሪ የሚሉ አጠቃቀሞች አልታዩም። ለዚህም ሌሎችን ስብሰባዎች ስንመለከት በአብዛኛው አጨቃጫቂና አከራካሪ ጉዳዮች የሌሉባቸው መሆናቸው ሲሆን ቢችልም አከራካሪና አጨቃጫቂ ሁኔታ ባለበትም ቢሆን ማስተካከያ የሚለው አጠቃቀም አልታየም። ለምሳሌ በአኮ 003 ስለአንድ ተማሪ ውጤት ጉዳይ ሰፊ ክርክር ከመደረጉ በላይም ጉዳዩ አጨቃጫቂ እንደነበረ ይታያል (አኮ 003፣ መስመር 463-930 ይመልከቱ)። ሆኖም ግን በዚህ ድስኩራዊ አውድ ድርሻ ስጭና ተቀባይ ባለመኖሩ ማንም ሰው በመደራረብም ይሁን ጣልቃ በመግባት መናገር የሚችልበት ሁኔታ ስለነበረ ድርሻ ለመንጠቅ ወይም ለመቀበል ጣልቃ መግባት ወይም ተደርቦ መናገርን እንደ ልምድ ስለወሰዱት ማስተካከያን ቀደም ብለን እንዳየነው ድርሻን ለመንጠቅ እንደስልት ሲጠቀሙበት አይታይም።

በአጠቃላይ ማስተካከያን/ተጨማሪን ድርሻን ለመንጠቅ እንደብልሃት መወሰዱ በዲስኩር ውስጥ ማስተካከያ/ተጨማሪ የሚለውን የአጠቃቀሙን መሰረታዊ ዓላማ ከመቀየሩም በላይ በተለይ ልምድ ለሌላቸው መምህራን በዲስኩር ውስጥ ማስተካከያ/ተጨማሪ ማለት ያለባቸው መቼ እንደሆነ ትክክለኛውን ግንዛቤ እንዳያገኙ በማድረግ ረገድ አስተዋፅኦ እንዳለው ያመለክታል።

4.3.2.8 ርዕስን መጠበቅ

አጀንዳን ወይም የውይይትን ርዕስ ከመጠበቅ አኳያ የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ርዕስ ያለመጠበቅ ሁኔታ ይታይባቸዋል። ርዕስ የማይጠብቁበትን ምክንያት ስንመለከት ደግሞ ርዕስን ካለመረዳት አንፃር የታየ ችግር ሳይሆን ሆን ተብሎ ኣላማ ባለው ምክንያት ከርዕስ ሲወጡ ይታያል። ሆኖም ግን ከርዕስ የሚወጡበት ምክንያት የሁለቱም የተለያየ ሆኖ ይገኛል። ወንዶቹ ማለት የሚፈልጉት ጉዳይ ተገቢውን ምለሽ አላገኘም ብለው ሲያስቡ ከውይይቱ ርዕስ (አጀንዳ) ወጣ በማለት ይናገራሉ። ለምሳሌ፦

> ፋሲል፦ ላብ የሚለውን ነገር እናንሳና እዛው ጋ እንሂድ። ላብ ያስፈልገዋል ፕራክቲካል ፎነቲክስ ብለን አላልንም። አሁን ውበነሽ ለዲፓርትመንቱ የሰጠቻቸው ካሪክለሙ ቁጭ ብሎ እያለ ካሪክለሙን ኮፒ አድርገን ሰጠን እያለ፤

ለዶር. አለባቸው እንዲያመቸው በሪፖርት መልክ የተሰራውን ሪፖርት ነው ያመጣችው ዲፓርትመንት። ካሪክለሙ ላይ ግን ከየት ዲፓርትመንት ምን ያህል ሰዓት ሊሰጡልን እንደሚችሉ ሁሉ የተቀመጠ ነገር አለ። እሱን እንግዲህ ምናልባት እንዴት እንዳላላየቻቸው ሚስአንደርስታንዲግ የተፈጠረ በዚህ ነው። ሁለት ወረቀት ነው እዚህ ጋ እንትን ተደርጎ የተባለ። ካሪኩለማችንን አላላየቻቸውም ሪፖርቱን ነው እሷ ያሳየቻቸው(አኮ 002፣ መስመር171-78)።

ፋሲል በሰብሳቢው የተጠየቀውንና በውብነሽ የተነሳውን ማስተካከያ ሀሳብ (የካሪክለሙን መፅደቅ አለመፅደቅ) እንዲመልስ ሲጠበቅ እሱ ግን ዲስኩሩን ወደጎላ በመመለስ (እዛው ጋ እንሂድ) በማለት ውብነሽ ትምህርት ክፍሉን እንዳሳሳተች በመግለፅ ላይ ያተኩራል። ግን ደግሞ ውብነሽ ቀደም ብላ እንደገለጸችው ለትምህርት ክፍሉ የሰጠችው ወረቀት ራሳቸው የፃፉት ወረቀት እንደሆነ በማመን ሌላም ወረቀት እንደነበርና ለምን እንዳላላየቻቸው በመግለፅ በውብነሽ የተሰጠው ምላሽ እንዳላረካው ይገልፃል። እዚህ ላይ ፋሲል የመድረኩን አካሄድና የተናጋሪዎቹን ስሜት መሰረት ያላደረገ ዲስኩር ነው ያቀረበው።

ከዚህ ሌላ ደግሞ ወንዶች በቀረበው አጀንዳ በመመስረት ራሳቸውን ለመግለጽም ሲጠቀሙበት ይታያል።

አስረጅ፡-

> እሱባለው፡ ጉዳዩ ግልፅ ነው። ምንም እንትን የለውም። ተፅዕኖው እኛ ላይ ያርፋል የሚል፣.... ከዚህ ጋር ተያይዞ ስለብዝሀነት የምለው ነገር አለን። ስለብዝሃነት ስናነሳ እኔ ከማጠናው..... እኔ እንደነገርኳችሁ የአንድ አምስት ፋካሊቲዎች፣ ኮሌጆች፣ ስኩል ካሪኩለማቸውን ብቻ ሳይሆን እስከ ጋይድ ቡካቸው በእጄ አለ። ያን አስስመት ስሰራ ያየሁት .... እንድ ምሳሌ ልነግራችሁ እችላለሁ። ተሳታፊው፡ ጫጫታ፣ጭብጨባ (አቁም በቃን) እኔ ህዝብ ግንኙነት መምህር ሆኜ ሳስተምር ...ከዛ በተጨማሪ ስለ ሪስክ ኮምንኬሽን ሳወራ የማነሳቸው ጉዳዮች ነበሩኝ። ለምሳሌ...ስለአንድ ፕሮጀክት ማውራት ካለብኝ ጥሩ ምሳሌ አድርጌ ስወስደው የነበረው.... (አጠመ 006. መስመር 24-43)።

ከቀረበው ድስኩራዊ አሃድ እንደምንመለከተው እሱባለው መጀመሪያ ይዞት የተነሳውን ሀሳብ መሰረት በማድረግ እሱ የሚያጠናውን፣ የሚሰራውን፣ ያለውን፣ ሲያስተምር የነበረውን፣ በማንሳት ስለራሱ ማንነት ለመግለጽ ሞክሯል። በዚህም ታዳሚው በጫጫታና በጭብጨባ እንዲያቆም ሲጠይቅ ይታያል። ይህ ደግሞ ከአጀንዳ ለመውጣቱ አመላካች ነው። ከዚህ በተጨማሪ ራስን ከመግለጽ አንፃር ከአጀንዳ የሚወጡት ወንዶች እንደሆኑ

ከመስክ ማስታወሻ የተወሰደው መረጃ ያሳያል። ቀደም ብሎ እንደተመለከትነው ከአጀንዳ የሚወጡት ከግንዛቤ ጉድለት ሳይሆን የቀረበውን አጀንዳ ጥግ በማድረግ ስለሰሩት፣ ስለተማሩት፣ ስለተመለከቱት፣ ስለአነበቡት፣ ከአሁን በፊትም ሆነ አሁን ስላላቸው ስልጣን፣ ስለሚያውቁት ትልቅ ሰውና አገር የመሳሰሉትን በመግለጽ ራሳቸውን ለማሳወቅ እንደሆነ መረጃው ያመለክታል። ከአጀንዳ በመውጣት ራሳቸውን ለመግለፅ የሚሞክሩት ደግሞ በሚሰጡት አስተያየት፣ ጥያቄና ማብራሪያዎች ላይ ምሳሌ በማቅረብ ነው።

በሌላ በኩል ሴቶች በተለይም በመደበኛ ውይይቶች ላይ የሚገኙ መድረኮችን በመጠቀም ሀሳባቸውንም ሆነ ራሳቸውን ሲገልጹ በአብዛኛው ባይታዩም፤ የሚናገሩትን ጥቂት ሴቶች ስንመለከት ከአጀንዳ ሲወጡ ይታያሉ። በእርግጥ ከአጀንዳ የሚወጡበት ምክንያት ከወንዶቹ የሚለይ ሲሆን ይህም በመጀመሪያ አጀንዳው ሲቀርብ የንግግር ድርሻ ባለማግኘታቸው ወይም ባለመውሰዳቸው የተነሳ በውይይቱ መጨረሻ ላይ በሚሰጣቸው ድርሻ ከአጀንዳው ሲወጡ ይታያሉ። በዚህም ስላለፈው ርዕሰጉዳይ በመናገር ዲስኩርን ወኂላ የመመለስ ሁኔታ ያሳያሉ። ለምሳሌ በአኮ 002 ውብነሽ ድርሻ ወስዳ ስትናገር በንግግሯ መጨረሻ ላይ ሰብሳቢው መጀመሪያ ላይ የተናገረውን ሃሳብ ‹‹አበበ መጀመሪያ ስትናገር ከካሪክለሙ ኤሲ ላይ ሲፀድቅ አልክ፤ ኤሲ ላይ አልፀደቀም አልተነሳም።›› በማለት አዲስ ውይይት እንዲጀመር አድርጋለች (መስመር 162-163 ይመለከቷል)።

ከዚህ በተጨማሪ ኢሌኒ በስብሰባው መጀመሪያ አካባቢ በአለሙ ተነስቶ የነበረውን የትምህርት ክፍል መፍረስ ጉዳይ በስብሰባው መጨረሻ አካባቢ ድርሻ ሲሰጣት እንደአዲስ በማንሳት የውይይቱን አጀንዳ አስቀይራለች። የሚከተለውን ዋቢ እንመልከት፡-

> ስለዚህ እኔ መሆን አለበት ብዬ እንደመፍትሄ የማስቀምጠው ጋሽ አለሙ አሁን ያነሳው ነገር ጠንከር ተብሎ መያዝ ያለበት ይመስለኛል። ሁለቱ ዲፓርትመንቶች ፕሮግራሞች ነው መሰለኝ አሁን ፕሮግራሞች እንደአንድ ዲፓርትመንት ሆነው ራሳቸውን ችለው የሚቀመጡበት መፍትሄ ቢቀመጥ ጥሩ ነው። እንደዲፓርትመንት አንድ ዲፓርትመንት ሆነው ሁለቱ ፕሮግራሞች ...(አኮ 002፣ መስመር 471-475)

በአጠመ 006 የቀረበውን ድስኩራዊ አሃድ ስንመለከት ደግሞ ውይይቱ የሶስት ቀን ሲሆን አልማዝ ሶስቱንም ቀናት ለመናገር እጇን ብታወጣም ድርሻውን ያገኘችው በስብሰባው

ማጠናቀቂያ የመጨረሻዎቹን ደቂቃ ነው። በዚህ ንግግሯ ያቀረበችው ጉዳይ በሰዓቱ ከነበረው ርዕሰ ጉዳይ የወጣ ብቻ ሰይሆን ብዙ ርዕሰ ጉዳዮችንም የያዘ ነበር። ይህም በወቅቱ ድርሻን ካለማግኘት ጋር የተያያዘ እንደሆነ ይጠቁማል።

አስረጅ፡-

> አልማዝ፡ የተሰማችኝን ነገር ወደእናንተ ለማቅረብ ነው። ህገ መንግስት ቨርሰስ ሃይማኖት፤ ሃይማኖት ቨርሰስ ሃይማኖት፤ አክራሪነት ቨርሰስ መንግስት፤ የገበያ ንረት ቨርሰስ ድህነት። እነዚህ ላይ ነው እኔ ያስተዋልኩት (አጠመ 006፣ መስመር 63-66)

አልማዝ በእነዚህ በዘረዘረቻቸው ርዕሰ ጉዳዮች ሰፊና ዘርዘር ያለ፣ በምሳሌ የተደገፈ ገለፃ አድርጋለች። እዚህ ላይ ከአጀንዳ መውጣት ብቻ ሳይሆን ከሁሉም ተናጋሪዎች የበለጠ ጊዜ ወስዳ ስትናገር ታዳሚው በጽሞና ያዳመጣት ሲሆን ከእሷ ቀደም ብሎ እንደተናገረው እሱባለው ላይ እንደተደረገው ከታዳሚው አቁሚ የሚል ጭብጨባም ሆነ ጫጫታ አልቀረበባትም። ለዚህም ያቀረበችው ርዕሰ ጉዳይና ማብራሪያ ስለራሷ የሚገልጽ ባለመሆኑና ሁሉንም የሚመለከት የጋራ ጉዳይ በመሆኑ ይመስላል።

4.3.2.9 ርዕስን (አጀንዳ) ማወቀር

በዚህ ጥናት በተወሰዱት ድስኩራዊ አሃዶች አጀንዳን ማቅረብና ማስተዋወቅን በተመለከተ በአብዛኛው የሰብሳቢው ሚና ሲሆን፣ በተለይም በአካዳሚክ ኮሚሽንና በትምህርት ክፍል ደረጃ በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ ሁለቱም ፆታዎች አጀንዳ ሲያቀርቡ ይታያል። ለምሳሌ በአኮ 002፣መስመር 3 ላይ እንደቀረበው ከበደ በኮርስ ባለቤትነት ላይ ውይይት እንዲደረግ ጠይቆ አጀንዳው እንዲያዝ አድርጓል። አለሙ ውይይቱ በመረዳዳትና በመተሳሰብ እንዲካሄድ ማሳሰቢያ አቅርቦ በፋሲልና በሰብሳቢው ተቀባይነት አግኝቷል (አኮ002፣ መስመር19-26 ይመልከቱ)። ሌላው በኢሌኒ የቀረበው የፕሮግራም ወይም የትምህርት ክፍል ጉዳይ ተነስቶ በከበደ የቀረበው በሁለተኛው አጀንዳ የሚካተት እንደሆነ፣ በመለሰ ከተሰብሳቢው በላይ እንደሆነና ጉዳዩ እንዲታለፍ የሚልና በሰብሳቢው ደግሞ አቅራቢዋ ‹‹ስላልገባት›› ማብራሪያ እሰጣለሁ የሚሉ ሶስት የተለያዩ አስተያየቶች ቀርበው ሰብሳቢው

ማብራሪያ የሰጠ ሲሆን ኢሌኒ ያቀረበችው ሀሳብም ተቀባይነት ሳይኖረው ቀርቷል (አኮ002፣ መስመር500-509)።

በሌላ በኩል ከመስክ ማስታወሻ የተወሰደው መረጃ እንሚያሳየው በአካዳሚክ ኮሚሽንና በትምህርት ክፍል ደረጃ በሚደረጉ ውይይቶች ላይ የሚሳተፉት አባላት ሴቶችም ይሁኑ ወንዶች ሁሉም የትምህርት ክፍል ሃላፊዎች በመሆናቸው ትምህርት ክፍሎቻቸውን በተመለከተ አጀንዳ የማስያዝ ሃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ ጉዳይ ሲኖራቸው አጀንዳ በማቅረብ ሁሉም ይሳተፋሉ። ከዚህ በተለየ ሁኔታ ግን በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በሚደረጉ ውይይቶች ላይ አጀንዳዎች የሚቀርቡት በሰብሳቢዎች አንጂ ከተሰብሳቢዎች አጀንዳ ሲቀርብ የታየበት ሁኔታ የለም። ቡድ 203፣156-61

4.3.2.10 ሀሳብን መግለጽ ወይም መጨረስ

በስብሰባ ወቅት የተፈጠረውን መድረክ ተጠቅሞ ሀሳብን ሰይጨርሱ ወይም ሳይናገሩ መውጣትን በተመለከተ አብዛኛዎቹ ወንዶች ሃሳባቸውን ሳይጨርሱም ሆነ መናገር ፈልገው ሳይናገሩ የወጡበት ሁኔታ ብዙ አይታይም። ከቡተቃ የተገኘው መረጃ እንደሚያስረዳው ወንዶች መናገር ከፈለጉ ታዳሚው ይከፋል፣ ንግግሬን ወደሌላ ሊተረጎም ይችላል ወዘተ. የሚል ስሜት ሳያድርባቸው የተሰማቸውን ነገር በግልጽ ይናገራሉ (ቡተቃ 201፣ መስመር 130-141 ይመለከቷል)። ከዚህም በተጨማሪ በቀረቡት ሃሳቦች ላይ የማይስማሙ ከሆነ አለመስማማታቸውን ለመግለጽ፣ ሌሎች ተናጋሪዎች መነገር ያለበትን ሀሳብ መነገር ባለበት መንገድ ያልተናገሩት ሲመስላቸውና ሃሳቡ አቅጣጫውን የሳተ ሲመስላቸው እንደሚናገሩና በስብሰባ ላይ ቢያንስ አንድ ጊዜ ሳይናገሩ እንደማይወጡ ገልፀዋል።

ዋቢ፡-

> ...በማውቃቸው ጉዳዮች ላይ ግን በጣም እናገራለሁ። አንደኛ ..የሚነገሩት ጉዳዮች የማልስማማባቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ ካልተስማማሁ አለመስማማቴን መግለፅ ይኖርብኛል። አንዳንዴ ደግሞ ሁኔታው መነገር ባለበት መልኩ ሳይነገር ይቀራል የሚል ሀሳብ ሲኖረኝ።...ስለዚህ በጣፈጠ መንገድ ወይም መነገር ባለበት መንገድ አልተነገረም የሚል ሃሳብ ሲኖረኝ፣ራሱ አቅጣጫውን የሳተ ሲመስለኝ እናገራለሁ። ቢያንስ እንድ ጊዜ ሳልናገር አልወጣም (ወ) (ቡተቃ 201፣መስመር153-61)

በእርግጥ አንዳንድ ወንዶች በትልልቅ ስብሰባ ላይ የመናገር ፍላጎት ስለሌላቸው ሳይናገሩ የሚወጡበት ጊዜ እንዳለ ጠቁመዋል።

> ...በትልልቅ ስብሰባ እኔ ብዙ ጊዜ አልናገርም። ቅድም ጋሼ ከበደ እንዳለው ነው ሪዘርቭ ነው የምሆነው። ግን በዲፓርትመንትና ኮሚሽን ከሆነ ግን ሃሳቤን ሳልጨርስ ወይም ሳልናገር የወጣሁበት ጊዜ የለም (ወ) (ቡተቃ 201፣ መስመር 90-92)

> ...በመናገሬ የማመጣው ነገር ከሌለ አልናገርም። ለምሳሌ ተወስኖ ያለቀለትን ነገር ተወያዩበት ተብሎ ሲመጣ ብሞት አልናገርም ዝም እንዳልኩ እወጣለሁ። ምክንያቱም በመናገሬ ሌላ ትርጉም ወደእኔ ከማምጣቱ ባሻገር የምጨምረው አንድም ነገር አይኖርም። ስለዚህ ከመናገር ዝም ይሻላል(ወ) (ቡተቃ 202፣ መስመር 126-30)

> ... እኔ ብዙ ጊዜ ሳልናገር የምወጣባቸው ጊዜያት ብዙ ናቸው። ለምን ቢባል የጉዳዩን ተደጋጋሚነትና የቸከ ሁሌም እየተነሳ ምላሽ የማያገኝ ጉዳይ ከሆነብን ብናገርም መልስ ስለማይሰጠው አልናገርም። ሌላው የጊዜ ማነስ ራሱ አንዱ ምክንያት ነው። ከተሳታፊዎች ሀሳብ ላለማስተናገድ የራሳቸውን ጉዳይ ብቻ ለመፈፀም ስለሚፈልጉ ጊዜ የለም ምናምን ይላሉ። በእንደዚህ አይነት ምክንያቶች አልናገርም(ወ) (ቡተቃ 203፣ መስመር 156-61)

የቀረቡትን ዋቢዎች ስንመለከት ወንዶች በስብሰባ ላይ ሳይናገሩ የሚወጡ ሲሆን፣ ምክንያታቸው ግን ከሴቶቹ የተለየ ነው። ይኸውም የውይይቱ ድባብ በጎ ካልሆነና የእነሱ መናገር ለውጥ አያመጣም ብለው ካሰቡ፣ በተደጋጋሚ የሚነሳና ምላሽ የማያገኝ ጉዳይ ከሆነና ሰብሳቢዎቹ የተሳታፊን ሀሳብ ለመቀበል ፍላጎት እንደሌላቸው በተረዱበት አውድ ዝምታን እንደተቃዎሞ መግለጫ በመጠቀም ሳይናገሩ ይወጣሉ።

በሌላ መልኩ አንዳንድ ሴቶች ብዙ ጊዜ አድማጭ እንጂ ተናጋሪ እንዳልሆኑና በዚህም መናገር ጀምረው ሀሳባቸው የተቋረጠበት ሁኔታ እንደሌለ፣ ግን ደግሞ መናገር እየፈለጉ ሰብሳቢዎቹ በሌሎች ተናጋሪዎች የሚቀርብላቸውን ሃሳብ የማይቀበሉ ከሆነ እነሱም ተቀባይነትን ላለማጣት ሲሉ፣ እንዲሁም ማብራሪያ ከመስጠት ይልቅ ዙሪያ ጥምጥም የሚዞርበት ሁኔታ ሲኖርና ለሚነሱ ሃሳቦች በተለመደ አቅጣጫ ምላሽ የማይሰጥ ከሆነ ሀሳብ ቢኖራቸውም ሳይናገሩ ይወጣሉ (ቡተቃ 201፣ መስመር 162-64)። አንዳንዶቹ ደግሞ ሀሳባቸውን ሳይጨርሱም ሆነ ሳይናገሩ የወጡባቸው አጋጣሚዎች እንዳሉ ይጠቅሳሉ። ይኸውም ትንንሽ ስብሰባዎች ላይ ድርሻ ወስደው በመናገር ላይ እያሉ ሌሎች

መናገር የሚፈልጉ ወንዶች ጣልቃ በመግባት እንደሚያቋርጧቸውና በዚህም ማስጨበጥ የፈለጉትን ሀሳብ ሳያስጨብጡ ጉዳዩ ወደሌላ አቅጣጫ ይሄድና ስብሰባው እንደሚጠናቀቅ ገልፀዋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሴቶች የተነጠቁትን ድርሻ በማስመለስ ሃሳባቸውን ለመቋጨት ምንም ሙከራ አያደርጉም። ለዚህም በምክንያት ያቀረቡት ወንዶች በጣም በመናገር የበላይነትን ለማሳየት በሚያደርጉት ሂደት ጫና ስለሚያደርጉባቸው ነው።

> ሮዛ፡ ያ ክፍተት ማለት ለእኔ ጥሩ እንትን የላቸውም ስለዚህ ምንድን ነው የእኔ መናገር የሚፈይደው በማለት። አገሬ፡ በተለይ አንዳንድ ጊዜ ውስጤ እየበሸቀ ራሱ ሳልናገር እወጣለሁ። ምክንያቱም የሰብሳቢዎቹ አላማ አንድ ነገር አስቀምጦ መሄድ እንጅ ከእኛ ሀሳብ መቀበል አይፈልጉም። በዚህ ጊዜ መናገሬ ለውጥ የማያመጣ ከሆነ እልና ዝም እላለሁ። አንዳንዴ ደግሞ የማደርገው ለውጥ ባመጣም እንኳ ጭንቅላታቸው ውስጥ አስቀምጠውት አንድ ቀን ይህ ሀሳብ ይቀይራቸዋል ብየ ካሰብኩ እናገራለሁ። ስናገር ግን ይቅርታ ጊዜ ስለሌለ ብለው አቋርጠውኝ ያውቃሉ። በተለይ ዲፓርትመንት አካባቢ (ወ)(ቡተቃ 203፣ መስመር120-28)

ከዚህም ሌላ ሴቶች በትልልቅ ስብሰባዎች ላይ አንዳንድ ጊዜ የስብሰባውን ጭብጥ ስለማይረዱና በቂ መረጃም ስለማይኖራቸው ለመናገር ሀሳብ የለሽ ይሆናሉ።

> ትላልቅ ስብሰባ ላይ አንዳንዴ በጣም ሀሳብ የለሽ ሆኜ ማለት ነው። ትዝ ይለኛል አንዴ አስተዳደር የሆነ በትምህርት ጉዳይ ላይ ይመስለኛል የሆነ ውይይት ተደርጎ ነበርና ሰዎቹ የሚያወሩት አማርኛ ቋንቋ ነው ግን ምንም ሊገባኝ አልቻለም እና እንዴት ነው አማርኛም የማይገባበት ጊዜም መጣ ወይ ብየ አውቃለሁ እንኳን ሀሳብ ልናገር፤የሚነገረው ነገር አንዳንዴ ካልገባኝ ሃሳብ ሳልሰጥ እወጣለሁ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ለመናገር ፈልጌ ፈርቼም ሳልናገር የወጣሁበት ጊዜ አለ። ...ድምፄ እየተንቀጠቀጠ እጄ እየተንቀጠቀጠ መናገር አልፈልግም፡፤ በኮንፊደንት ነውና። እሱ ነገር ውስጤ ካልሞላና ሀሳቤን በድፍረት መግለፅ አልችልም ብየ ካሰብኩ እንትን አደርጋለሁ። ግን እድናገር የሚጎተጉተኝ ነገር አለ ውስጤ። (ቡተቃ 201፣ መስመር103-05 ይመለከቷል)።

የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው አንዳንዴ በፍርሃት ምክንያት ሳይናገሩ የሚወጡበት ሁኔታም እንዳለና በተለይም ለመናገር የሚያስችላቸውን ድፍረት ካላገኙ እየተንቀጠቀጡ መናገር ባለመፈለጋቸው ምክንያት ከመናገር ይቆጠባሉ። በተለይም በጣም ትልልቅና የማያውቋቸው ሰዎች ባሉበት ስብሰባ ላይ ስለሚፈሩ እንዲናገሩ ውስጣቸውን የሚጎተጉታቸው ጉዳይ ቢኖርም ሃሳባቸውን ሳይገልጹ ይወጣሉ።

ዋቢ፡-

> መቅደስ፡- በትልልቅ ስብሰባዎች አዎ መናገር የምፈልገው ያውም የመፍትሄ ሀሳብ ይሆናል የምለውን ሀሳብ ስለምፈራ ብቻ ሳልናገር ሁሌም እወጣለሁ፡፡ እንዳልኩሽ ሀሳቤን አጠገቤ ላለች ወይም ወንድ ሲሆን ይችላል እነግረዋለሁ፡፡ ካልሆነ ስወጣ ለጓደኞቼ ይዤ ነገር እኮ እንዲህ ነበር ብየ እናገራለሁ፡፡ በጣም ጥሩ ሀሳብ ነበር ይዤ ሲሉኝ ደግሞ በጣም እናደዳለሁ ባለመናገሬ፡፡ የሚገርማችሁ ግን አንድ ሁለት ቀን ከሆነ ወንድ ባልደረባየ ጋር ተቀመጥኩና መናገር የምፈልገውን ሀሳብ ይዤ እኮ እንዲህ ማለት ነው እና እንዲህ ቢሆን ይሻል ነበር ብየ ነገርኩት፡፡ እሱም እጁን አወጣ ሁለቱንም ቀን እድሉ ተሰጠው የእኔን ሀሳብ ከራሱ ጋር አዋህዶ አቀረበው (ቡተቃ 203፣144-52)

መቅደስ በስብሰባ ላይ የመናገር ፍላጎት ያላትና ሀሳቧም በመፍትሄ ሃሳብ ላይ ያተኮረ ቢሆንም በፍርሃት ምክንያት እንደማትናገርና ከስብሰባ ውጭ ልትናገር የነበረው ሃሰብ ለሌሎች በማካፈል ጥሩ እንደነበረ ሲነገራት እንደምትናደድ መረጃው የመለክታል፡፡ ሆኖም ግን አንዳንዴ አጠገቧ ላለ የስራ ባልደረባዋ ሀሳቧን በመንገር በእሱ በኩል እንዲተላለፍ የማድረግ ስልት የተጠቀመች ሲሆን፣ ይህም ሃሳቤ ትክክል ነው ብሎ በራስ የመተማመን ችሎታ ዝቅተኛ መሆኑን አመላካች ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሃሳብን በቀጥታ ለመድረክ ከማቅረብ ይልቅ ከአጠገብ ላለ ሰው መንገር እንደስልት የተወሰደ ይመስላል፡፡ በመስክ ምልከታ እንደታየው ግን ሴቶች ብዙ ጊዜ ከአጠገባቸው ካለ ሰው ጋር በሹክሹክታ የጎንዮሽ ወሬ ሲያወሩ ከመታየታቸው ጋር ተደጋጋፊነት ያለው ሲሆን ምክንያቱም በቡተቃ የተገለፀው ሃሳብን ለመድረክ ለማቅረብ ስለሚፈሩ ለጓደኛ ለመንገር ሲባል የተፈጠረ መሆኑን ይጠቁማል፡፡

በትናንሽ ስብሰባዎች ላይ ሴቶች ሃሳባቸውን ሳይገልጹም ሳይጨርሱም እንደሚወጡና ለዚህም የወንዶች ጣልቃ ገብነት እንደሆነ ቀጥሎ የቀረበው መረጃ ይጠቁማል፡፡

> አገሬ፡- ሀሳቤን ሳልጨርስ የወጣሁበት ጊዜ አለ፣ ሳልናገርም የወጣሁበትም ጊዜ አለ፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ማለት ነው፡፡ ሀሳቤን ሳልጨርስ ወጥቼ የማቅበት ምክንያት በትናንሽ ስብሰባዎች ላይ ነው፡፡ ቅድም እንደተጠየቀው እድል ለማግኘት የሚፈልጉ ሰዎች ያቋርጡሻል ሃሳብሽን እየተናገርሽ፡፡ ...ተሰብሳቢዎች አንዳንዶቹ ዶሚኔት ማድረግ የሚቀናቸው ሰዎች አሉና ያንንም በመናገር ለማሳየት ለሚፈልጉ ሰዎች በጣም እድል በመስጠት አምናለሁ፡፡ ነገሩን ታቂዋለሽ እውነቱን ታቂዋለሽ ግን በጨዋት በምናምን

እንትን ሊሉሽ ሊጫኑሽ ይፈልጋሉ። ስለዚህ ካለ በደንብ እንዲጮህ እድሉን እሰጠዋለሁ (ቡተቃ 201፣ መስመር 101-112)።

አገሬ በተለይም በትንንሽ ስብሰባዎች ድርሻ የመንጠቅ ልምድ ያላቸው ወንዶች ሃሳቧን ሳትጨርስ እንደሚያቋርጧትና የተነጠቀችውን ድርሻ መልሳ ከመውሰድ ይልቅ በንግግር የበላይነት ላላቸው እንደፈለጉ እንዲናገሩ ድርሻው የሰጠች ሲሆን ይህም ሴቶች ሃሳባቸውን በመግለጽ ሂደት ድርሻ ለመውሰድም ሆነ ለመንጠቅ ያላቸው ፍላጎት ዝቅተኛ እንደሆነ ይጠቁማል።

ከዚህ ሌላ አንዳንድ ሴቶች የሚናገሩት ሃሳብም ሆነ ስለጉዳዩ መረጃ ከሌላቸው ሳይናገሩ የሚወጡ ሲሆን ሃሳብ ካላቸው ግን ድርሻ ተሰጧቸው ቢናገሩም ድጋሜ እንደሚጠይቁና ካልተሰጣቸው ደግሞ ማይክ ቀምተው እንደሚናገሩ መረጃው ያመለክታል (ቡድ 201፣መስመር 1262ን ያገናዝቧል)። ሌላው መናገር ፈልገው ሳይናገሩ እንደሚወጡና ለዚህም ምክንያቱ ባህሉ በሴቶች ላይ የፈጠረው ተፅዕኖ ሃሳባቸውን ለመግለጽ በመፍራታቸው ምክንያት እንደሆነ ቀጥሎ የቀረበው የአገሬ ገለጻ ያመለክታል።

> አገሬ፡- በባህላችን ለሴትም ለወንድም የሚሰጠው ዋጋ የተለያየ ስለሆነ፣ ይኸ ነገር በከፍተኛ ተቋማትም የሆነ ይመስለናል። በብዙዎች ስብሰባ ላይ አብዛኛዎቹ ተናጋሪዎች ቢረባም ባይረባም ወንዶች ናቸው የሚናገሩት... (ቡተቃ 201፣ መስመር 1264-1268 ያገናዝቧል)።

በተጨማሪም በቡተቃ 202 በተደረገው ውይይት ላይም ሴቶች ሃሳባቸውን በመግለጽ ሂደት ፍራቻ ትልቁ ተፅዕኖ እንደሆነ የተገለጸበትን አስረጅ እንመልከት።

> አበባ፡-...እኔ ከራሴም ስነሳ ዋናው ተፅእኖ አድራጊው ፍራቻ ነው። አንድም የእኔ ሀሳብ ጠቃሚ አይደለም ይህን ብናገር ምን አስተዋጽኦ አለው ብሎ መፍራት ወይም በራስ ያለመተማመን ልንለው እንችላለን። ሌላው ግን ትልቁ ነገር ከተናገርሽ በኋላ ሰው ምን ይለኛል አይን አውጣ ፈጣጣ ምናምን ብለሽ ትፈሪያለሽ። ይህ ደግሞ በኑሮሽ፣ በማህበራዊ ግንኙነትሽ በሞራልሽም ላይ ተፅዕኖ ስለሚያመጣ እና ከአንቺ የሚጠበቀው ቫሊው የሚሰጥሽ ጭምት ዝምተኛ የሚለው ነገር ስለሆነ ዝምተኛ መሆንን ነው ትክክል አድርገሽ የምትወስጅው።
> ህይወት፡- [የሚገርመው እኛ ራሱ የምትናገር ሴት ካለች እኮ ጎበዝ አንላትም ከእሷ ጋርም ጓደኛ መሆን ብዙም...ምክንያቱም እኔም ተናጋሪ የምባል ነው የሚመስለኝ። ቡተቃ 202፣290-302

የሌሎቹም ሴቶች ሃሳብ ከላይ ከቀረበው ሃሳብ ጋር የሚመሳሰል ሲሆን ሃሳብን በመግለፅ ሂደት ተፅዕኖ አድራጊው ባህሉ ነው ሲባል ማህበረሰቡና የተቋሙ ማህበረሰብ ለሴቶች የሚሰጠው ግምት የተዛባ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ሴቶቹ በራሳቸው ይዘውት የሚመጡት ዝቅተኛ የሆነ በራስ የመተማመን መንፈስና ተናጋሪነት ከሴት የማይጠበቅ ተግባር እንደሆነ እንደሆነ ማመናቸውም ነው። ራሳቸው ብቻ ሳይሆን ወንዶቹም ሴት መናገር የለባትም የሚለውን ልማድ ይዘው ስለሚመጡ ብዙ ጊዜ በሚደረግ ስብሰባ ላይ ድርሻ ለመስጠት ሰብሳቢው የሚያየውም ሆነ ድርሻ የሚሰጠው ለወንዶች ነው። ለምሳሌ በቁጥር አስር ሴቶችና አምስት ወንዶች በስብሰባው ቢሳተፉ ሁሉም ወንዶች እንደሚናገሩና ሁሉም ሴቶች ደግሞ ድርሻ ባለማግኘታቸው ምክንያት ሳይናገሩ እንደሚወጡ ውብነሽ ገልፃለች (ቡድን 201፣መስመር 175-77 ያገናዝቧል)።

በሌላ በኩል ሴቶች ለመናገር የሚፈሩ እንደሆነና እንዲያውም ለመናገር ሲፈልጉ እንኳ በመጀመሪያ በማስታወሻቸው ፅፈው እንደሚያነቡ ‹‹...ስትፅፍ ስትፅፍ ነው የቆየችው እና ያንን ማንበብ ገባች ለምን ፍርሃት ነው...›› (ቡተቃ 201፣ መስመር 206-07) በማለት ከበደ የተመለከተውን ዋቢ በማድረግ ገልጿል። ከዚህ በተጨማሪ ሴቶች በጣም ጠንቃቃ እንደሆኑና ከመናገር እንደሚቆጠቡ በቡድን ውይይቱ ወቅት ካሳ እንደሚከተለው አቅርቦታል።

> ... እና ምናልባት አንዱ ምክንያት የሚመስለኝ እኔ መጠንቀቅ ይመስለኛል። በጣም ጥንቃቄ የሚያበዙ ይመስለኛል። በጣም ጥንቃቄ ያበዛሉ። ያልኩት ነገር በየት በኩል ነው የሚመነዘረው፣ ምን ይወሰድበት ይሆን የሚል ነገር ያለ ይመስለኛል።ይህን የምላችሁ አንድ ተጨባጭ ተሞክሮም ስላለኝ ነው (ቡተቃ 201፣ከመስመር 1308-1312 ይመለከቷል)።

ይህ የስራ ቦታ ከፍተኛ ተቋም ከመሆኑም በላይ ሴቶቹም ሆኑ ወንዶቹ ከመጡበት ማህበረሰብ የተሻለ አስተሳሰብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። ሆኖም ግን ከማህበረሰቡ ይዘውት የመጡት ባህል ከፍተኛ ተፅዕኖ እንዳደረገባቸውና የረጅም ጊዜ መሰረት ያለው በመሆኑ ከዚህ ለመውጣት ጊዜ እንደሚወስድ ተጠኝዎቹ ይገልፃሉ። ከዚህ በተጨማሪ ግን ችግሩን ለመቅረፍ ቢሞከርም የተቋሙ ባህል ሲታይ ለሴቶች ብዙም ድርሻ ወይም ቦታ

የሚሰጥ ባለመሆኑ ያንን ሆነው እንዲኖሩ ይገደዳሉ። ከቡተቃ የተገኘው መረጃ እንደሚያስረዳው አንዲት ሴት ከዚህ ዩኒቨርሲቲ ከመምጣቷ በፊት የነበራት ተሳትፎ ከፍተኛ እንደነበርና ራሷንም በተለያዩ መድረኮች እየገለፀች የመጣች ቢሆንም በዚህ ዩኒቨርሲቲ ግን ሴቶች ተደማጭነትም ሆነ ተቀባይነት ስለሌላቸው ተሳትፎዋ መቀነሱንና ዝምታን እንደመረጠች ገልፃለች (ቡተቃ 201፣ መስመር327-43ያገናዝቧል)።

4.3.2.11 በስብሰባ ወቅት ሀሳብን ከመግለጽ በፊት የሚደረግ ቅድመ ዝግጅት

መድረክን በአግባቡ ተጠቅሞ ሀሳብንም ሆነ ራስን ለመግለጽ በመጀመሪያ ስለምንናገረው ጉዳይና አቀራረብ ማሰብና መዘጋጀት የንግግር የበላይነትን በማጎናፀፍ ረገድ ከፍተኛ ሚና አለው። በዚህ ጥናት ከቡተቃ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው አብዛኛዎቹ ወንዶች ወደስብሰባ ከመግባታቸው በፊት ለውይይት በሚቀርቡት ርዕሰ ጉዳዮች ላይና በተሳታፊዎች ሊቀርቡ የሚችሉት ሀሳቦች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ቅድመዝግጅት ያደርጋሉ።

አስረጅ1፡-

> ዮናስ፡ ብዙ ጊዜ ስብሰባው ከመካሄዱ በፊት ርዕሰ ጉዳዩን የማውቀው ከሆነ በተለይ ደግሞ በመደበኛ ወይም በኢመደበኛ ውይይት ጊዜ መነሳት ያለበትን ጉዳይ በመጀመሪያ ማስታወሻ ላይ ለማስፈር እሞክራለሁ። አንዳንዴ ስብሰባው ስለምን እንደሆነ ሳይነገር ስብሰባ አለ ተገኙ የሚባልበት አጋጣሚ አለ። በዛ ላይ ደግሞ የማደርገው አጀንዳዎቹ ምን ምን እንደሆኑ ለመፃፍ እሞክራለሁ። ምናልባት በዛ ዙሪያ ላይ እኔን የሚመለከት ጉዳይ ካለ አቀርባለሁ (ቡተቃ 203፣ መስመር 5-9)።
>
> ኤርሚያስ፡ ጉዳዩ አሳሳቢ ከሆነ ከአጀንዳው በመነሳት ቀድሜ እኔ እንዲህ እንዲህ ማለት አለብኝ ብየ እዘጋጃለሁ። አንዳንዴ ደግሞ እዛው ሄጀ እዛው ላይ በሚነሱት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያልገቡኝን ጥያቄዎች፣ አስተያየቶች ሊሆኑ ይችላሉ እዛው ላይ እዘጋጃለሁ። የምዘጋጀው እንዴት ነው አንደኛ ጉዳዩ ከሚነገረው ነገር ውጭ ንግግሬ እንዳይወጣ አዕምሮየ ውስጥ የማደራጅት ስራ እሰራለሁ። በማስታወሻ የመያዙ ባህሪ ብዙም የለኝም (ቡተቃ 203፣መስመር40-44)

ዮናስ ስብሰባው ከመካሄዱ በፊት በውይይቱ ላይ ስለሚነሳው ጉዳይ ቀድሞ ማስታወሻ በመያዝ እንደሚዘጋጅና አጀንዳውን ቀድሞ የማያውቀው ከሆነ ደግሞ በስብሰባው ጊዜ አጀንዳው ሲቀርብ በማስታወሻ ይዞ የሚመለከተው ጉዳይ ካለ ሀሳቡን ያቀርባል። በተመሳሳይ ኤርሚያስ መናገር ያለበት አሳሳቢ ጉዳይ ከሆነ ቀድሞ ዝግጅት እንደሚያደርግ መረጃው ያሳያል።

አስረጅ2፡-

> ገበየሁ፡ እኔ እንኳ ወደስብሰባ ስሄድ አጀንዳውን ካየሁኝ በቃ ሀሳቤን ወደእዛ ስብሰብ ለማድረግ እሞክራለሁ ከመግባቴ በፊት፡፡ አጀንዳውን የማላውቀው ከሆነ ስደነባበር ነው የምመጣው፡፡ ይሄን ይሆን እያልኩ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ጉዳየ አይደለም ዝም ብየ እመጣለሁ፡፡ እዛ ስገባ አገኘሁ የለም በሚል፡፡ በዛሬው ሁኔታ ቀደም ብየ አንቺን አንዳንድ ነገር ጠይቄሽ ስለነገርሽኝ አንዳንድ ነገር ዲስኮርስ ላይ ጭንቅላቴ ውስጥ መጣና እንደዛ አይነት ነገር ለማንበብ ሙከራ አድርጌያለሁ (ቡተቃ 203፣መስመር19-20)

ገበየሁ ወደስብሰባ ከመግባቱ በፊት በአጀንዳዎቹ ዙሪያ ከፍተኛ ዝግጅት የሚያደርግ ሲሆን ዝግጅቱ ደግሞ የሚያውቀውን አስቦ መምጣት ብቻ ሳይሆን አጀንዳው አዲስ ከሆነም አንብቦና ተረድቶ አንደሚመጣ ገልጿል፡፡ ከዚህ ውጭ ግን አጀንዳውን ባለወቀበት ሁኔታ ወደስብሰባ የሚሄድ ከሆነ ምን ይሆን በማለት እንደሚጨነቅ መረጃው ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ስለአጀንዳው ምንነትና በውስጡ ስለሚቀርቡት ዝርዝር ሀሳቦች ብቻ ሳይሆን በአጀንዳው ላይ ማን ምን ሊል ይችላል፣ ከምን አንፃር እስከሚለው ድረስ በጥልቀት አስበውና ለዛም ምላሽ የሚሆን ሀሳብ ቀድመው አዘጋጅተው የሚመጡ ወንዶችም እንዳሉ ከቡተቃ የተወሰደው መረጃ ያመለክታል፡፡

አስረጅ፡-

> ከፍያለው፡ በየትኛውም ስብሰባ ይሁን አንድም ሰው የምናገርበት ከሆነ እና በስብሰባ ፎርም የምሰበሰብ ከሆነ እዘጋጃለሁ፡፡ *መጀመሪያ ማለት* ነው፡፡ ከዛ ሰው *ጋር* ምን *መነጋገር* አለብኝ፣ ምንድን ነው የማወራው፣ ምን ሊያነሳ ይችላል፣ ይህን ስል እንዲህ ሊል ይችላል እስከሚለው ድረስ አስባለሁ፡፡ ትንሽም ትልቅም ስብሰባ ቢሆን፡፡ የጊዜ ማጠር እንጂ ዝግጅቱ ተመሳሳይ ነው፡፡ ለአንድ ግለሰብም ብዙም ቢሆን፡፡ ከዛ ባሻገር ደግሞ ማጠቃለያ፣ ምናምን እንትኖች አሉ፡፡ ያራሱ ፊዞች አሉ፡፡ ግን ለእነዛ ሁላ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ምን ላደርግ እንደምችል ቀድሜ ነው የማስበው (ቡተቃ 202፣መስመር 13-19)፡፡

በዋቢነት የቀረበውን አሃድ ስንመለከት ከፍያለው የስብሰባው ተሳታፊ አንድም ግለሰብ ይሁን ብዙም ከውይይቱ መጀመሪያ እስከ መጨረሻ ባሉት ደረጃዎች ላይ ምን ላይ ማን ምን ሊል ይችላል የሚለውን መሰረት አድርጎ በጥንቃቄ ተዘጋጅቶ እንደሚመጣና ለስብሰባ

ትልቅ ጥንቃቄ እንደሚደርግ ‹‹ስብሰባ እኮ የሰው አካል ነው›› በማለት ይገልፃል (ቡድ 202፣መስመር 31-32 ይመልከቱ)።

በተቃራኒው ሴቶች ወደስብሰባ ከመግባታቸው በፊት ቅድመ ዝግጅት እንደማያደርጉና ስብሰባን እንደስራ እንደማይቆጥሩት መረጃው ይጠቁማል። ቀጥሎ የቀረቡትን አሃዶች በዋቢነት እንመልከት፡-

> እየሩስ፡ እኔ ግን ተቃራኒ ነገር ነው። ማለት እኔ ስብሰባን እንደስራ ስራየ አድርጌ አልወስደውም። ይህን ያህል አልጨናነቅበትም። በዛው ሰኣት አጀንዳዎቹን ካወኩ በኋላ መናገር ካለብኝ እናገራለሁ። አጀንዳዎቹን ቀድሜ ካወኩ ምን አይነት ሀሳብ ባቀርብ ብየ ትንሽ ላስብ እችላለሁ። ግን ያልተነካ ጉዳይ አለ ብየ ካሰብኩ እዛው ጋ ነው እንትን የምለው እንጂ እንዲህ ወደ እሄዳለሁ በቃ እዛው ነው ልንነጋገርበት የምንችለው እንጂ ቀድሜ እንትን አልልም።
> ከፍያለው፡ ስብሳቢም ከሆነች በኋላ ምንም ዝግጅት አይጠይቀንም አለች። እንዴት ነው አጀንዳ ብቻ ይዛ የምትሄደው?
> እየሩስ፡ አይ እንደ አንተ እንደሰብሳቢ ሆኜ እኮሌ እንትን ቢናገር ይህንን ቢያስብ ምን ልለው እችላለሁ ብየ አላስብም።
> ከፍያለው፡ ስብሰባ ማለት ምን ማለት ነው ራሱ? ስብሰባ ማለት እኮ የሰው አካል ነው። እንደተራ ነገር አታይውም።
> እየሩስ፡ አንተ እኮ በጣም ስራ አድርገህ ተጨናነክ እኮ (ቡተቃ 202፣መስመር 20-33)።

ከቀረበው አሃድ እንደምንመለከተው እየሩስ ስብሰባን እንደስራ አድርጋ እንደማትወስደውና ወደስብሰባ ከመግባቷ በፊት ቅድመ ዝግጅት እንደማታደርግ ያሳያል። ዝግጅት የምታደርገው ውይይት በሚደረግበት ጊዜ አጀንዳዎቹን ካወቀች በኋላ በመዘጋጀት መናገር ያለባትን የምትናገር ሲሆን፣ ከዚህ ቀድማ ግን ስብሳቢም ብትሆን የውይይት አጀንዳ ከማዘጋጀት ያለፈ የተለየ ዝግጅት እንደማታደርግ መረጃው ያመለክታል።

አንዳንድ ወንዶች ደግሞ ስብሰባው ከመካሄዱ በፊት ምንም አይነት ቅድመ ዝግጅት እንደማያደርጉ ቀጥሎ የቀረበው መረጃ ይጠቁማል።

> እሱባለው፡ አጀንዳው ቀድሞ ቢታወቅም ባይታወቅም በመጀመሪያ ወደስብሰባ ስሄድ ምንም አይነት ዝግጅት አይኖረኝም። እዛ የሚነሱ ሀሳቦች ናቸው እኔን የሚገዙኝ። እድሉ መጀመሪያ ከደረሰኝ እናገራለሁ። ከዛ በፊት ግን ዝግጅት ያለው ነገር አይደለም። ማስታወሻም የመያዝ ልምዱ የለኝም። የሰማሁትን

ከላይ እስከታች በአዕምሮየ እይዝና የማነሳቸው ነገሮች ከዛ በፊት ውስጤ የነበሩ ነገሮች አስተያየት የምሰጥባቸው ጥያቄ የምጠይቅባቸው ነገሮች እዛ ውስጥ አዕምሮየ ውስጥ የነበሩ ይወጣሉና ሳላስበው ግን ብዙዎቹ ነገሮች የሚከሰቱ ናቸው። ማለት እኔ ሳልፈልጋቸው በዛ ላይ ጥሩ ግንዛቤ ኖሮኝ አንዳንድ ሰዎች ሲሳሳቱ ስለማያቸው የጋራ የሆነ መግባባት እንዲኖር ስል በውስጤ ያለውን የማውቀውን እናገራለሁ(ቡተቃ 203፣መስመር31-39)።

እሱባለው ቅድመ ዝግጅት እንደማያደርግ፣ ነገር ግን በውይይቱ ላይ ያዳመጣቸውን ሀሳቦች በሙሉ በመገንዘብና በውስጡ ካለው ጥያቄም ሆነ ሀሳብ ጋር በማገናኘት ቅድመ ግንዛቤውን ተጠቅሞ ሰፊ ማብራሪያዎችን የመስጠት ልምድ እንዳለው ገልጿል።

በሌላ በኩል አንዳንድ ወንዶች ደግሞ ከመናገራቸው በፊት የታዳሚውን ፆታ፣ ሃይማኖትና ደረጃ መሰረት ያደረገ ጥናት ያደርጋሉ። በተለይም ከፆታ አንፃር የማያውቋቸው ሴቶች ከሆኑ፣ እኩዮቹ ካልሆኑና የሃይማኖት ልዩነትም ካለ ነፃ ያለመሆን ሁኔታ እንደሚፈጠርና ከመናገርም እንደሚቆጠቡ ገልፀዋል (ቡተቃ 201፣ መስመር14-32)።

ከዚህ ሌላ በውይይት ሂደት ላይ ሀሳብን ከማቅረብ በፊት ያለውን ዝግጅትን በተመለከተ አብዛኛዎቹ ሴቶች ስብሰባው በመካሄድ ላይ እያለ ከመናገራቸው በፊት በውይይቱ ስለተነሳው ጉዳይ ካዳመጡና ከተገነዘቡ በኋላ መናገር የሚፈልጉትን ነገር በመሳታወሻቸው በመያዝ ቀድመው ይዘጋጃሉ። ይህንም የሚያደርጉት ለማቅረብ የፈለጉት ሃሳብ ተረስቶ እንዳይቀርና ከርዕሰ ጉዳዩ ላለመውጣት ቅድመ ጥንቃቄ ለማድረግ እንደሆነ ገልፀዋል (ቡድ 201፣ መስመር1-13)። ተጨማሪ አስረጅዎችን እንመልከት፡-

አስረጅ፡-

> አገሬ፡ በአብዛኛው የስብሰባውን አላማ፣ ስለማላውቅ፣ ስብሰባው ሲጀመረ አላማውን በመረዳትና ጅምሩን አይቼ በዚህ ስብሰባ ላይ ይሄ ሀሳብ ቢገለፅ ይጠቅማል የምለውን ሀሳብ ለማቅረብ እሞክራለሁ። ይህን ለማድረግ መነገር ያለበትን ሀሳብ ማስታወሻ እይዛለሁ። አንዳንዴ ደግሞ ዝም ብየም እናገራለሁ።(ቡተቃ 203፣ መስመር1-5)

> አልማዝ፡ ከመናገሬ በፊት ምን ጥያቄ እንደምጠይቅ፣ ምን አስተያየት እንደምሰጥ በአዕምሮየ አስባለሁ፣ ማስታወሻም እይዛለሁ (ቡተቃ 203፣ መስመር29-30)።

> ህይወት፡ በእኔ በኩል መቼውን ጊዜ ቢሆን ስብሰባ ከመግባቴ በፊት ምን እናገራለሁ ብየ አስቤ አላውቅም (ቡተቃ 202፣መስመር47-48)።

> ህይወት፡ ስብሰባ ላይ እንዲህ እላለሁ ብየ ቀድሜ ተዘጋጅቼ አላውቅም። ግን እዛው ስብሰባ ላይ ምናልባት እንድናገር የሚያስገድደኝ ነገር ከተፈጠረ የምጠቀምባቸውን ቋንቋዎች እንዴት መጠቀም እንዳለብኝ፣ ይዤኛውን እንዴት ብናገር አሳማኝ በሆነ መንገድ አቀርበዋለሁ ብየ እዘጋጃለሁ (ቡተቃ 202፣መስመር1-4)።

ከቀረበው መረጃ እንደምንረዳው አብዛኛዎቹ ሴቶች ወደስብሰባ ከመግባታቸው በፊት ቅድመ ዝግጅት እንደማያደርጉ ያሳያል። ዝግጅታቸውን የሚጀምሩት እዛው ስብሰባ ውስጥ በአዳመጡት ላይ በመመስረት ሲሆን ለዚህም ከመናገራቸው በፊት አብዛኛዎቹ ማስታወሻ በመያዝ አንዳንዶች ደግሞ ያለማስታወሻ እንደሚዘጋጁ መረጃው ያስያል። ሴቶች ምናልባትም ከስብሰባው በፊት ቅድመ ዝግጅት የማያደርጉትና በስብሰባው ላይም ለመናገር ማታወሻ በመያዝ ጥንቃቄ ከሚያደርጉበት ምክንያት አንዱ ስለስብሰባው ኣላማና አጀንዳ ቅድመ ግንዛቤ የሌላቸው ስለሆነ ሊሆን ይችላል። ለዚህም ቀጥሎ የቀረበውን መረጃ በዋቢነት እንመልከት።

> አገሬ፡ በአብዛኛው የስብሰባውን አላማ፣ ስለማላውቅ፣ ስብሰባው ሲጀመረ አላማውን በመረዳትና ጅምሩን አይቼ...(ቡተቃ 203፣ መስመር 1-2)

> ሮዛ፡- እኔ አብዛኛዎቹን የገባሁባቸው ስብሰባዎች ምንድን ነው? ስለምንድን ነው? እያልኩ እያልን ነው የምንሄደው። ምክንያቱም ቀድሞ አይነገርም። ሌላው ቀርቶ ሰብሳቢዎቹ የሆነ ተደዋውለው ዛሬ እንሰብስባቸው የሚሉ ነው የሚመስለኝ። እና ብጠይቅ ምንም የመፍራት ብቻ ሳይሆን አንዳንዴ የማይመለከተኝ ሁሉ ይመስለኛል (ቡተቃ. 202፣ መስመር 10-15)።

አብዛኛዎቹ ሴቶች ወደ ስብሰባ ከመግባታቸው በፊት ስለስብሰባው ኣላማና አጀንዳ ቅድመ ግንዛቤ እንደሌላቸውና በዚህም በውይይቱ ሂደት ሀሳባቸውን ለማቅረብ በመጀመሪያ ሌሎች ሀሳብ ሲያቀርቡ ካዳመጡና ከተረዱ በኋላ ሲሆን ይህንም ለማድረግ ማስታወሻ በመያዝ ስለሚናገሩት ሀሳብም ሆነ ቋንቋ ጥንቃቄ እንደሚያደርጉ መረጃው ይጠቁማል።

4.3.3 ማህበረ-ባህላዊ ልማድ

የዲስኩር ትንተና በባህርይው ሲታይ የንግግር ተግባቦትን በስብሰባም ሆነ በመሰል ቦታዎች ያለውን የሰዎችን የአነጋገርና የተግባቦት ሁኔታ በማህበራዊ ባህላዊ አውድ ዙሪያ በመተንተን ቁርኝቱን በማየት የማህበረሰቡን ማንነት መግለፅ የሚያስችል ነው። በመሆኑም በዚህ ደረጃ የሚደረገው ሶስቱን የማህበረ-ባህላዊ ልማዶችን ማለትም ሁኔታዊ፣ ተቋማዊና ማህበራዊ ደረጃዎችን መሰረት በማድረግ በድስኩራዊ መስተጋብሩና በማህበራዊ አውዱ መካከል ያለውን ግንኙነት መተርጎም ይሆናል። ትንተናው ከሶስቱ የትንተና ደረጃዎች አንፃር የቋንቋ፣ የስርዓተያታ እና የሀይል ግንኙነቱ ምን እንደሚመስል የሚያሳይ ይሆናል (ፌርክላፍ፣2006 እና ቫን፣ 2008)። ከዚህ አንፃር ቀጥሎ የማህበረ ባህላዊ ልማድ ደረጃዎችን መሰረት በማድረግ መረጃዎቹ ተተንትነው ቀርበዋል።

4.3.3.1 ሁኔታዊ ደረጃ

በማህበረ-ባህላዊ ማዕቀፍ ትንተና ሂደት የመጀመሪያው ደረጃ ሁኔታዊ የሚለው ሲሆን፣ ይህም ድስኩራዊ አሃዱ የፈለቀበት አውዳዊ ሁኔታ ምን እንደሚመስል የሚታይበት ደረጃ ነው። በዚህም መሰረት በዚህ ጥናት የተወሰዱትን ድስኩራዊ አሃዶች የአፍልቆት ሁኔታ ምን እንደሚመስል በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል።

በመጀመሪያ የተወሰደው በአኮ002 የቀረበው ድስኩራዊ አሃድ የአፍልቆት ሁኔታው በሁለት ትምህርት ክፍሎች መካከል የተፈጠረ የኮርስ ባለቤትነት ጥያቄ ላይ የተመሰረተ አካዳሚያዊ ዲስኩር ነው። የሁለቱም ትምህርት ክፍሎች ተጠሪዎች ለሁለት ኮርሶች የየራሳቸውን መምህራን በመመደብ ለፋካሊቲው ልከዋል። ፋካሊቲው ደግሞ የ001 ተጠሪ የላከችውን በመተው የ002 ተጠሪ የላከውን ባወጣው ፕሮግራም አካቶ በማውጣቱና የ001 ትምህርት ክፍሎች ኮርሱ የእኛ ሆኖ እያለ ለምን እነሱ መምህር ይመድባሉ የሚል ጥያቄ በማንሳታቸው ምክንያት የተጠራ አስቸኳይ ስብሰባ ነው። ሁለቱን ትምህርት ክፍሎች ለማወያየትና ወደስምምነት ለማምጣት የፋካሊቲው ፕሮግራም ማናጀር የሰብሰቢነት ድርሻውን ይዟል።

በዚህ ደረጃ የአሃድ አፍልቆት ሁኔታውን ስንመለከት የ002 ፕሮግራም ተጠሪ ሰፊ የንግግር ጊዜና ተደጋጋሚ ድርሻ በመውሰድ በንግግር የበላይነቱን የያዘበት ሁኔታ ሲታይ፤ በተቃራኒው ደግሞ የ001 ፕሮግራም ተጠሪ ሰፊ የንግግር ጊዜና ተደጋጋሚ ድርሻ ያልወሰደችበት ሁኔታ ታይቷል። ውብነሽ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ድርሻና የንግግር ጊዜ ወስዳ ለመናገር ፍላጎት አላሳየችም። በመረጃው እንደተመለከተው ‹‹ለተባለው ነገር ሁሉ መልስ ለመስጠት አይደለም›› የሚለው አገላለፅ ፋሲል ባነሳው እሰጥ አገባ ላይ መከራከርና በቀረበው ችግር ላይ አስከመጨረሻው መጋፈጥ አለመፈለጓን ያመለክታል። ሌሎቹን ተሳታፊዎች በተመለከተ ሁሉም ወንዶች የመናገር ድርሻ ሲወስዱ ከስድስቱ ሴቶች መካከል ግን የንግግር ድርሻ የወሰዱት ሶስቱ ብቻ ሲሆኑ ሁለቱ ሴቶች (አገሬና ኢሌኒ) ድርሻው የተሰጣቸው በተደጋጋሚ እጃቸውን ካወጡ በኋላ ነው። በአጠቃላይ የንግግር አፍልቆቱን ስንመለከተው የወንዶቹ ንግግር ሀይል የተላበሰ ሲሆን የሴቶቹ ግን ሀይል የለሽ ነበር።

የአኮ 003 ድስኩራዊ አሃድ የፈለቀበትን ሁኔታ ስንመለከት ደግሞ ፋካሊቲው በየሳምንቱ የሚያካሂደው አካዳሚክ ኮሚሽን ስብሰባ ሲሆን በዚህ ላይም የቀረቡት አጀንዳዎች ቃለጉባዔ ማፅደቅ፣ የተማሪዎችና የመምህራን ጉዳይ የሚሉ የተለያዩ አጀንዳዎች ናቸው። ስብሰባውን የመሩት የፋካሊቲው ዲን ስትሆን ተሰብሳቢዎቹ ደግሞ የየፕሮግራሙ አስተባባሪዎች ናቸው። ስብሰባው እንደተጀመረ የዩኒቨርሲቲው ምክትል ፕረዚደንት ሌላ ዲን ለማስመረጥ ወደስብሰባው የገቡ ሲሆን በመጀመሪያ የያዙትን አጀንዳ በማቅረብ ስብሰባውን የመሩ ሲሆን አውዱ እሳቸው ረጅም ንግግር በማድረግ የበላይነትን የያዙበትና በውይይቱ ጣልቃ ገብነትም ሆነ ተደራርቦ የመናገር ሁኔታ ያልተከሰተበት ሲሆን አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎችም የአዳማጭነት ሚና የነበራቸው በመሆኑ መደማመጥና ፀጥታ የሰፈነበት ነበር።

ከምርጫው በኋላ ምክትል ፕረዚዳንቱ ከስብሰባው የወጡ ሲሆን ሮዛ ስብሰባውን የመምራት ድርሻዋን ተረክባለች። በዚህ ውይይት ላይ የፈለቀውን አሃድ ስንመለከት በስብሳቢዋ ለሚቀርበው ጉዳይ ተሳታፊዎቹ ምላሽ የሚሰጡት እጃቸውን በማውጣት ድርሻ በመውሰድ ወይም በስብሳቢዋ በሚሰጣቸው ድርሻ መሰረት ሳይሆን ቀድሞ የተናገረ ይጀምራል፣ የሚቀጥለውም እንደዚሁ የቀደመ እየተናገረ የሚሄድበት ሲሆን፣ የጣልቃ ገብነት፣ የመደራረብና ድርሻ ነጠቃ በስፋት የታየበት ድስኩራዊ አሃድ ነው። ከዚህ በተጨማሪም

ሰብሳቢዋ አጀንዳውን ከማቅረብ ባለፈ በአብዛኛው ለሚቀርቡት ጉዳዮች የተብራራና ዘርዘር ያለ ዲስኩር ያላፈለቀች ከመሆኑም በላይ በውውይይቱ የምትሰጠው ምላሽ በአብዛኛው ‹‹እህ፣ እሽ›› በሚሉ አሻሚ ቃላት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይህም እንደሰብሳቢነቷ የሚወሰኑ ውሳኔዎችን ለተሳታፊዎችና ለቃለጉባዔ ፀሀፊው በግልጽ አፅንኦት በመስጠት ያላቀረበችበት ሁኔታ ይታያል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከተሳታፊ አባላቱ መካከል ጌትነት ጣልቃ በመግባትና ቀድሞ በመናገር የሰብሳቢዋን ሚና በመንጠቅ የንግግር የበላይነትን ይዞ ከመታየቱ በተጨማሪ በውይይቱ ላይ ቅድመግንዛቤውን መሰረት በማድረግ መረጃ በመስጠትና የውሳኔ ሃሳብ በማቅረብ ትልቅ ሚና ነበረው፡፡ አንዳንዴም ከእሱ በላይ የሚሆኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ሰብሳቢዋን ዋቢ በማድረግ ከማማከር ይልቅ ከተሳታፊዎች ውስጥ በእውቀቱን በመጠየቅ ሲያማክር ይታያል (አኮ 003፣መስመር...)፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ድስኩራዊ አሃድ ሰብሳቢዋ የሰብሳቢነት ሚናዋን ያልተወጣችበት፣ ጌትነት የሰብሳቢዋን ሚና የነጠቀበትና የንግግር የበላይነትን የያዘበት ሁኔታ ሲታይ በሁሉም ተሳታፊዎች ዘንድ ድርሻን ጠብቆ ያለመናገር ሂደት የታየበት አውድ ነው፡፡

በአጠመ.006 የቀረበው ድስኩራዊ አሃድ የፈለቀበት ሁኔታ ሲታይ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በዋናው ግቢ በተደረገ አጠቃላይ ውይይት ሲሆን፣ ውይይቱ ያተኮረው በ2004 ዓ.ም የስራ አፈፃፀም ግምገማ፣ የ2005 የስራ እቅድና ወቅታዊ ጉዳይ ላይ ነው፡፡ በዚህም 232 ወንዶችና 28 ሴቶች የተሳተፉ ሲሆን፣ ሶስት ተከታታይ ቀናትን የወሰደ ውይይት ነበር፡፡ የውይይቱ መሪዎች ዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ ሃላፊዎች ሲሆኑ፣ አውዳዊ ሁኔታው ሲታይ በሰብሳቢዎቹና በተሰብሳቢዎቹ መካከል ባለው የሃይል የበላይነትና የበታችነት ምክንያት ይመስላል መደማመጥና የንግግር ድርሻን በጠበቀ መልኩ የሀሳብ ልውውጥ የነበረበትና ፈፅሞ ጣልቃ ገብነትና በሌላ ተናጋሪ ላይ ተደርቦ መናገር ያልታየበት አውድ ነው፡፡ ሃሳብን በመግለጽ የነበረውን ተሳትፎ ስንመለከት ደግሞ የንግግር ድርሻ የጠየቁ ወንዶች ቢያንስ አንድ ጊዜ ሃሳባቸውን የገለጹ ሲሆን፣ አብዛኛዎቹ ሴቶች ደግሞ የመናገር ፍላጎት ያላሳዩ ሲሆን፣ ሶስት ሴቶች ግን ሶስቱንም ቀናት የንግግር ድርሻ ጠይቀው አልተሰጣቸውም፡፡ በውይይቱ መጨረሻ ሰዓት ላይ ከተሳታፊ ወንዶች ለሰብሳቢዎቹ ‹‹ሴቶችን አሳትፉ›› የሚል ማስታወሻ በቀረበላቸው መሰረት ለአንድ ሴት ድርሻ ተሰጧት ብዙ ጉዳዮችን የያዘ ረጅም ንግግር አድርጋለች፡፡ በአጠቃላይ ይህ ድስኩራዊ አሃድ የፈለቀበትን ሁኔታ ስንመለከት

ድርሻ የሚሰጠው በሰብሳቢዎቹ ፍላጎት ብቻ የነበረበት መሆኑ የሃይል ግንኙነቱ ሚዛናዊ ያልሆነበት አውድ እንደነበር ያመላክታል።

በኢመ 001 የቀረበውን ድስኩራዊ አሃድ የፈለቀበትን ሁኔታ ስንመለከት በትምህርት ክፍል ደረጃ የቀረበ ትምህርታዊ አውደጥናትን መሰረት በማድረግ በተደረገ የምሳ ግብዣ ላይ የፈለቀ ኢመደበኛ ውይይት ነው። በውይይቱ የተሳተፉት በፋካሊቲው የሚገኙ መምህራን ሲሆኑ መረጃው የተወሰደው በአንድ መመገቢያ ጠረጴዛ ከተቀመጡ ቡድኖች ነው። ውይይቱ 7 ሴቶች እና 2 ወንዶች የተሳተፉበት ነበር። በዚህ ውይይት የተነሱት ጉዳዮች አብዛኛዎቹ በነበረው አውደ ጥናት ላይ ንግግር በማድረግ በተሳፉ ሰዎች ላይ አስተያየት በመስጠት እና የአውደ ጥናቱን ይዘት በመተቸት ላይ ያተኮረ ነው።

አስረጅ፡-

> [አብይ፡ ዮናስ እኮ መከራውን አየ
> ዮናስ፡ እንዴት?
> አብይ፡ አስተያየት በመስጠት መከራውን አየ
> ዮናስ፡ አንተ አለህ አይደል አንዴ የምትናገርበት አጋጣሚ አተህ
> መዓዛ፡ የጨዋ አማርኛ ምናምን እልክ አይደል
> አዳነች። አይ አብይ(ሳቅ) ለነበረኝ ጊዜ እግዚአብሄር ይመስገን ብሎ ጮሆ ሳይናገር ቀረ
> ዮናስ፡ እንዲያውም አቡነዘበሰማት ሳይል መቅረቱ ገርሞናል። እንዝጋው በእንትን አለማለቱ
> አዳነች፡ የሰማነውን በልቦናችን... (ኢመ.001፣መስመር11-19)

መረጃው እንደሚያስረዳው በአውደጥናቱ ላይ ሃሳብ በሰጡ ሰዎች ላይ የቀረበ ትችትን ይዟል። ይኸውም በአውደጥናቱ ላይ ዮናስ በተደጋጋሚ ድርሻ ወስዶ እንደተናገረ፣ ያቀረበው ሃሳብ ደግሞ ትርፉ ድካም እንደሆነ ‹‹መከራውን አየ›› በማለት አብይ ገልጿል። በሌላ በኩል በዮናስ ላይ ትችት ያቀረበውን አብይን ደግሞ በአውደጥናቱ ላይ ያደረገውን ንግግር ‹‹ አንተ አለህ አይደል እንዴ የምትናገርበት አጋጣሚ አተህ›› በማለት ንግግር ያደረገው ሃሳብ ስላለው ሳይሆን መናገር ስላለበት እንደሆና የተናገረው ሀሳብም በአውደጥናቱ ሊቀርብ እንደማይገባው ‹‹የጨዋ አማርኛ...›› የሚለው ገለፃ ጠቋሚ ነው። ይህ ሰው በንግግሩ ሃይማኖታዊ ጉዳይ ላይ እንደሚያዘወትር ‹‹እግዚአብሄር ይስጥልን...፣ አቡነዘበሰማያት...››ብሎ ሊናገር እንደሚችል የሚጠበቅ እንደሆነ ገለጻው ያመለክታል። ይህ ሁኔታ በቡተቃ እንደቀረበው ከስብሰባ በኋላ እከሌ እንዲህ አለ/አለች የሚሉ አስተያየቶች

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. BOX 1176
ADDIS ABABA

እንደሚሰጡና በዚህ ምክንያትም ከዚህ ትንኮሳ ለመዳን በተለይ ሴቶች በስብሰባ ላይ እንደማይናገሩ ገልፀዋል።

ዋቢ፡-

> ቢንያም.....ሁለተኛው ነገር ምንድን ነው ከዚህ ወጥቼ እዛ ከተማ ቦታ ስንገናኝ ምን እባላለሁ፣ ስራ ላይ፣በአካባቢየ ምን እሆናልሁ ብሎ የማሰብ ይመስለኛል (ቡተቃ 202፣መስመር 271-72)
>
> አልማዝ.....ሌላው እንዳንዱ እንደተሰብሳቢ ሆነሽ አሁን ለተሰብሳቢዎች ሌላው ከኋላ ሆኖ አስተያየት ስለሚስጠው ስው ‹‹ኢንፎርማሊ››የሚናገሩት ነገሮች አሉ። እነሱ ነገሮች በራሳቸው ጫና ይኖራቸዋል። አሁን ይህን ብናገር ይህን እባላለሁ ማለት ነው፣ እንደዚህ እይነት አስተያየት ይሰጠኛል ማለት ነው፣ ምናምን ትያለሽ፣ የሆነ ትፈሪያለሽ፡ (ቡተቃ 203፣መስመር 350-54)

በዚህ ድስኩራዊ አሃድ ነገርን ነገር ያነሰዋል እንደሚባለው ዮናስ ላይ የቀረበው አስተያየት ውይይታቸው ከአውደ ጥናቱ ወጥቶ ወደሌላ ግለሰብ ባህርይ ገለባ እንዲያመራ አድርጓቸዋል። በዚህ ሂደት ከፍተኛ የሆነ ጣልቃ ገብነት፣ መደራረብና የጎንዮሽ ወሬ የነበረ ሲሆን እርስ በርስ ያለመደማመጥ የታየበት አውድ ነው። አብዛኛዎቹ ሴቶች ድርሻቸውን ጠብቀው ከመናገር ይልቅ ጣልቃ በመግባት፣ በመደራረብና በጎንዮሽ በማውራት የንግግር የበላይነትን የያዙበት ሁኔታ ታይቷል። የወንዶቹን ስንመለከት ደግሞ ከሴቶቹ በተቃራኒው ከመናገር የመቆጠብ ባህርይ አሳይተዋል።

በመጨረሻ የቀረበው ድስኩራዊ አሃድ በኢ.መ.004 የተደረገው ውይይት ሲሆን ከኢ.መ.001 ጋር ሲነፃፀር የተለየ ባህሪ እንዳለው ከአሃዱ ማስተዋል ይቻላል። የውይይቱ አወድ በተመሳሳይ በፋካሊቲ ደረጃ የተካሄደን ስልጠና መጠናቀቁን መሰረት በማድረግ የተደረገ የእራት ግብዣ ሲሆን ተሳታፊዎቹ ደግሞ አብዛኛዎቹ ወንዶች ሲሆኑ ሶስት ሴቶች ብቻ የተሳተፉበት አውድ ነው። ውይይቱ ኢመደበኛ ቢሆንም መሪ የነበረው ሲሆን ስም በመጥራት ለእንዳንዱ ተናጋሪ በየተራ ድርሻ በመስጠት እንዲናገሩ ተደርጓል። በዚህም ምክንያት ጣልቃ ገብነትና መደራረብ ባለመኖሩ ከፍተኛ የመደማመጥ ሁኔታ የታየበት ድስኩራዊ አሃድ ነው። በውይይቱ የተነሳው የመጀመሪያው ጉዳይ ስለስልጠናውና ስለአሰልጣኙ አስተያየት መስጠት ሲሆን በዚህም ሁለቱ ሴቶችና አብዛኛዎቹ ወንዶች የተሳተፉበት ሁኔታ ነበር። በሁለተኛ ደረጃ የቀረበው የውይይት ጉዳይ ለመዝናኛ የሚሆኑ

የተለያዩ ቀልዶችን ማውራት ነው። የውይይቱ መሪ አሁንም እጅ የሚያወጡትን ስም በመጥራት እንዲናገሩ ሲያደርግ፣ አብዛኞዎቹ ወንዶች ቀልዶቻቸውን ሲያቀርቡ ሴቶቹ ግን በጋራ ከማቅረብ ይልቅ በሹክሹክታ አንድ ሴት ቀልድ ያቀረበችበት ሁኔታ ታይቷል። በዚህ ድስኩራዊ አሃድ የቀረቡትን ቀልዶች ጭብጦቻቸውን ከስርዓተ-ፆታ አንፃር ሲታዩ ልዩነት እንዳላቸው እንመለከታለን። ይኸውም በአብዛኛው በወንዶች የቀረቡት ቀልዶች አይነኬ ወይም በእነሱ አገላለፅ ‹‹የፍስክ›› የሚባሉ ጭብጦች ያላቸው ሲሆኑ የሴቷን ስንመለከት አቀራረቡ ጎናዊ ቢሆንም መሰረት ለሴት ጓደኞቿ የነገረቻቸውን ስንመለከት (መስመር109-14 ይመለከቷል) ከስራ ቦታ ጋር የተያያዘ መሆኑ በመጠኑም ቢሆን ከርዕሰ ጉዳይ አንፃር ልዩነት እንዳለ አመላካች ነው።

4.3.3.2 ተቋማዊ ደረጃ

ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የሚመራበት የራሱ የሆነ መተዳደሪ ደንብ አለው። መተዳደሪያ ደንቡ በዋናነት የሚያጠነጥነው በመምህራንና በተማሪዎች ጉዳይ ሆኖ የመማር ማስተማሩን ሂደት፣ የእድገትና የሃላፊነት ሁኔታንና ጥቅማጥቅሞችንም በሚመለከት በዝርዝር የያዘ ሰነድ ነው። ሰነዱ የቋንቋ አጠቃቀሙን በተመለከተ ከስርዓተፆታ አንፃር ገና በመጀመሪያ ገፅ ላይ ሁሉም ነገር ሁለቱንም ፆታዎች የሚመለከት እንደሆነ ገልጿል። በዝርዝር ጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ስንመለከት ደግሞ በአብዛኛው በብዙ ቁጥር በመጠቀም ሁለቱንም ፆታዎች ለማሳየት የቀረበ ቢሆንም አልፎ አልፎ ግን ወንዶችን ብቻ የሚያመለክቱ ተውላጠ ስሞችን (እሱ/የእሱ) ሲጠቀም ይታያል።

ከዚህ ሌላ ለመምህራን የስራ አፈፃፀም መገምገሚያ ተብለው የተዘጋጁ በስራ ላይ ያሉ ሶስት አይነት ቅፆች አሉ (አባሪ 11፣12፣13 ይመልከቱ)። የመጀመሪያው በተማሪዎች የሚሞላ ሲሆን በዚህ ቅፅ ውስጥ ሃያ የሚሆኑ የመገምገሚያ መስፈርቶች ተካተዋል። መስፈርቶቹ የቀረቡበት አገላለፅ ከስርዓተ ፆታ አንፃር ሲታዩ የሁሉም ዓረፍተ ነገሮች ማሰሪያ አንቀፅ ሴቶችንና ወንዶችን በሚገልጽ አቀራረብ የቀረበ ቅፅ ነው።

ለምሳሌ፡-

የመምህሩ/ርዋ ስም....
የሚያስተምረው/ የምታስተምረው የት/ዓይነት...

መግለጫ

1. ከአነበብከው/ሽው የመገምገሚያ ነጥብ መምህራን...

መመሪያ 1፡- ከአነበብከው/ሽው የመገምገሚያ ነጥብ መምህራን...በመክበብ አመልክት/ች፤
የመገምገሚያ መስፈርት

1. ኮርስ ጋይድ ቡክ በወቅቱ አዘጋጅቶ/ታ ያቀርባል/ታቀርባለች...

የቅፁ አቀራረብ ከቋንቋ አጠቃቀሙ አንፃር ሲታይ ገምጋሚዎቹም ሆኑ ተገምጋሚዎቹ ሴቶችና ወንዶች እንደሆኑና በተቋሙ ውስጥ እንዳሉ ያሳያል፡፡

ሁለተኛውና ሶስተኛው ቅፅ በስራ ባልደረቦችና በሃላፊዎች የሚሞሉ መገምገሚያዎች ሲሆኑ የሁለቱም መስፈርቶቹ የቀረቡበት ዓረፍተ ነገሮች በሙሉ ተባዕታይ ፆታ አመልካች ናቸው፡፡

ለምሳሌ፡-

የተገምጋሚው ስም....
መግለጫ

1. እያንዳንዱን የመገምገሚያ ነጥብ በጥንቃቄ አንብብ
2. ከአነበብከው የመገምገሚያ ነጥብ አኳያ የስራ ባልደረባህን

2.1 ለማስተማር የሚያደርገውን ዝግጅት
2.2 ጥናትና ምርመር ለማድረግ የሚያደርገውን ጥረት...

የመገምገሚያ መስፈርት

1. በት/ክፍሉ የመማር ማስተማር ስራ የሚሻሻልበትን ሃሳብ ያቀርባል፣ ተሳትፎም ያደርጋል
2. በት/ክፍሉ ችግሮች ሲከሰቱ የመፍትሄ ሀሳብ ያመነጫል፣ ተሳትፎም ያደርጋል...

ለአብነት የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው በቅፁ የቀረቡት ሀሳቦች ገምጋሚውንና ተገምጋሚውን የሚመለከቱ ሲሆን ሁለቱም አካላት የቀረቡት በወንድ ፆታ ነው፡፡ ይህም በገምጋሚነትም ሆነ በተገምጋሚነት የቀረቡትና በቦታው ያሉት ወንዶች ብቻ እንደሆኑ የታሰበ ይመስላል፡፡ በመሰረቱ አማርኛ ወንዴ ተኮር ቋንቋ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ሆኖም ግን በዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ ለምንድን ነው ቅፆቹ በተለያየ ስርዓተ ፆታዊ አቀራረብ የቀረቡት የሚለው ነው፡፡ ይህ ጉዳይ ሴት መምህራን በተማሪዎቻቸው እንዲታወቁ ሲደረጉ በስራ ባልደረቦቻቸውና በሃላፊያቸው እንዲታወቁ የተደረገበት ሁኔታ አለመኖሩ ምናልባትም በስብሰባ ላይም ሆነ በየትኛውም ቦታና ጊዜ ሀሳብ መስጠትም ሆነ የተለያዩ

ተግባራትን መፈፀም የወንዶች ብቻ ተደርጎ ሊወሰድ ስለሚችል ሴቶች ንቁ ተሳታፊ እንዳይሆኑ በማድረግ በኩል የራሱ አስተዋፅኦ እንዳለው ይጠቁማል። ለዚህ ደግሞ የአቀራረቡ መለያየት ሁኔታው ትኩረት እንዲሰብ ሊያደርግ ይችላል። ይህም ቅፁ በሴቶችም ሆነ በወንዶች ዘንድ ተቋማዊ አሰራሩ የወንዶች የበላይነት መኖሩን ያመለክታል።

ከዚህም ሌላ ዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ሃላፊነቶች ለመስጠት ያዘጋጀው የመወዳደሪያ ቅፅ ያለው ሲሆን (አባሪ 14ን ይመልከቱ) ከተካተቱት መስፈርቶች ቀጥሎ የተመለከቱት ለአብነት እንመልከት።

መስፈርት፡-

- የአሰራር ለውጡን ለመቀበል ያለው ዝግጁነት
- ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ለመተግበር ያለው ቁርጠኝነት
- ዘመናዊ ዩኒቨርሲቲ ለመገንባት ያለው ዝግጁነት

በዚህ የመወዳደሪያ መስፈርትም ቀደም ተብሎ እንደቀረበው የመገምገሚያ ቅፅ የቋንቋ አጠቃቀሙ ወንዴ ተኮር ሲሆን ይህም በዩኒቨርሲቲው የሃላፊነት ቦታዎች የወንዶች እንደሆኑ አድርጎ የመጠበቅና የመውሰድ ልማድ እንዳለ ይጠቁማል። በአጠቃላይ ከሰነዶቹ እንደምንረዳው ተቋሙ ስለስርዓተፆታ ግንዛቤ እንዳለውና ለማስረፅም የሚፈልግ መሆኑን የመተዳደሪ ደንቡ የሚሳይ ቢሆንም ዝርዝር መመሪዎያዎቹ የሚያመለክቱት ግን የተቋሙ ባህል የወንዶች የበላይነት ያለበት መሆኑን ይጠቁማል። በቡድን ውይይቱ ላይ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በዚህ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በሚደረጉ የተለያዩ አካዳሚያዊ ስብሰባዎችና ውይይቶች ላይ ሴቶች ለመናገር የሚፈሩ ቢሆንም በአብዛኛው ግን የንግግር ድርሻ የሚሰጠው ለወንዶች እንደሆነ፣ አብዛኛዎቹ ሰብሳቢዎች ድርሻ ለመስጠት የሚያዩትም ወንዶችን እንደሆነ፣ ለሴቶች እባካችሁ ተራ ስጡ ተብለው ተጠይቀው እንደሚሰጡና የሴቶቹ ሃሳብ ጠቃሚና አስፈላጊ ነው ብሎ ያለማመን ሁኔታ እንዳለ ተገልጿል።

በተጨማሪ በትምህርት ክፍል ደረጃ በሚደረጉ ውይይቶች ድርሻውን አግኝተው ከተናገሩም ሀሳባቸውን እንደሚያቋርጧቸው፣ ብዙ ጊዜ ተቀባይነትን እንደማያገኙና

ያቀረቡትን ሀሳብም ለሴቶች መብት ተከራካሪ ከመሆን ጋር እንደሚያያይዙት ተገልጿል (ቡድን 203፣ መስመር 354-60 ያገናዝቧል)። በአኮ 001፣ መስመር 1280-1291 ድስኩራዊ አሃድ እንደተመለከተው ውብነሽ፣ አገሬና ኢሌኒ ሀሳብ ያቀረቡ ቢሆንም ፋሲል የአንዳቸውንም እንዳልተቀበላቸውና የወንዶቹን ግን እንደተቀበላቸው ስማቸውን በመጥራት ገልጿል። በሁለቱም ዖታዎች የቀረበውን ሀሳብ ስንመለከት ግን የጭብጥ ልዩነት የለውም።

ከዚህ ሌላ ተቋማዊ ባህሉ በተግባቦት ሂደት ተፅዕኖ እንደሚያደርግ የታየ ሲሆን፣ ለምሳሌ ውብነሽ በቤተሰብ ደረጃም ሆነ በማህበረሰብ ደረጃ የነበራት አስተዳደግ መልካም እንደነበረና ሀሳቧን ሳትፈራ እየገለፀች እንደመጣች፤ ከዚህም አልፎ ተርፎ በሌላ የስራ ቦታ ላይ በንግግር ጥሩ ተሳትፎ እንደነበራት ገልፃለች። ሆኖም ግን በዚህ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ተሳትፎዋ እንደቀነሰና ለመናገርም እንደምትፈራ፣ ለሴቶች ዋጋ እንደማይሰጥ፣ የተቋሙ ባህል ተፅዕኖ እንዳለው ይህም ከተናገሩ በኋላ ይህን አለች ስለሚባልም ከዚህ ነፃ ለመሆን ከመናገር እንደምትቆጠብ ገልፃለች(ቡድን 201፣ መስመር 327-43)። ከዚህ በተጨማሪም ሴቶች በፋካሊቲና በትምህርት ክፍል ደረጃ በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ ሀሳብ በሚያቀርቡበት ጊዜ ሀሳባቸውን ከተለያዩ ነገሮች ጋር በማያያዝ ውድቅ እንደሚያደርጉባቸውና በዚህም ምክንያት ከስብሰባ ውጭ ይህን አልሽ ተብለው ከሚደርስባቸው ትንኮሳ ለመሸሽ ሲሉ እንደማይናገሩ ከቡተቃ የተወሰደው ቀጥሎ የቀረበው መረጃ ይጠቁማል።

አስረጅ፡-

> መቅደስ፡ ትልቁ ነገር ሰው ምን ይለኛል የሚለው ነገር ራስሽን ቀርቶ ሀሳብሽን እንዳትገልጭ ያደርግሻል። እኔ የራሴን መጀመሪያ ልንገርሽና በፋካሊቲና በዲፓርትመንት ደረጃ ሀሳብ ሳቀርብ አብዛኛውን ጊዜ ከሆነ ነገር ጋር ያያይዙና ባላሰብኩት መንገድ እንዲህ ለማት ፈልገሽ ነው አይደል ብለው ሀሳቤን የማጣጣል ብቻ ሳይሆን ለምን ይህን አልሽ ተብየ የምጎነተልበት ጊዜ ብዙ ነው። እና ከስብሰባ ስወጣ የሚደርስብኝን ትንኮሳ ለመከላከል ስል ስለራሴ ብቻ ሳይሆን ያለኝንም ሀሳብ አልናገርም (አባሪ አስር፣ ቡተቃ.203፣መስመር 456-620)።

ሌላው በተቋሙ ውስጥ በተለይም ኢመደበኛ በሆነው የስራ ተራክቦ ላይ በምልከታ እንደታየው በቢሮ ደረጃ፣ በጓደኝነት ደረጃ፣ ሻሂ በመጠጣት፣ ምሳ በመብላት፣ በአብዛኛው የሚታዩት ሴቶች ከሴቶች ወንዶች ከወንዶች ጋር በመሆን ነው። ይህ ለምን ሆነ የሚለው

ጥያቄ ሌላ ጥናት የሚጠይቅ ነው። እንደሚታወቀው በዩኒቨርሲቲው የሴቶች ቁጥር አናሳ በመሆኑ በተለያዩ የሃላፊነት ቦታዎች የሚገኙት ወንዶች ናቸው። በዚህ ምክንያት በስራ ቦታ ላይ የሚካሄዱ ተግባራትን በተመለከተ ሰፊ መረጃ የሚያገኙት ወንዶች ናቸው። በመሆኑም ሴቶቹ ጓደኝነታቸው በአብዛኛው ከሴቶቹ ጋር በመሆኑና በስራ ቦታቸው ላይ የሚፈፀሙ የተለያዩ ጉዳዮች በወንዶቹ ስለሚፈፀሙ መረጃውን የማግኘት እድላቸው ጠባብ ነው። በዚህም የተነሳ የተለያዩ ስብሰባዎች ሲካሄዱ ለውይይት በሚቀርቡት አጀንዳዎች ላይ ቅድመግንዛቤ ስለሌላቸው ሀሳብ ከማቅረብ ይቆጠባሉ።

4.3.3.3 ማህበራዊ ደረጃ

በኢትዮጵያ ያለው ማህበረሰባዊ ሁኔታ በኢኮኖሚው፣ በማህበራዊና በፖለቲካው የወንድ የበላይነት የነገሰበት ሲሆን ይህም መነሻው ቤተሰባዊ መነሻ ይይዝና መድረሻው ማህበረሰባዊ ይሆናል። ሁኔታው በማህበረሰቡ የእለት ተዕለት ተግባር የሚፈፀም ልማድ ብቻ ሳይሆን አንዳንዴም የህግ መሰረት ይዞ ይገኛል።

ሴቶችና ወንዶች የተለያየ ማህበራዊ ልምድ ያላቸው በመሆኑ በተግባቦት ሂደት የተለያየ ባህርይ ሊያሳዩ ይችላሉ። ግሬይ (1992) እንዳሉት ሁለቱም የሚያድጉት በተለያየ ሁኔታ ውስጥ በመሆኑ የተለያየ ልምድ ይኖራቸዋል። በጥናቱ በተወሰዱት መደበኛ ውይይቶች ላይ ያልተናገሩት ሴቶች ስንመለከት በእድሜ ከእነሱ የሚያንሱት ወንዶች ሃሳባቸውን ሲገልጹና ድርሻ ሲነጥቁ የታዩ ሲሆን ሴቶቹ ግን ተመጣጣኝ ሀሳብ አላቀረቡም። ይህም ወንዶቹ ከልጅነታቸው ጀምረው እየተናገሩ የመጡ ስለሆኑ ልምድ ያላቸው መሆናቸውን ሲያሳይ፤ ሴቶቹ ግን ልምድ የሌላቸው በመሆኑ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

በአጠቃላይ በቋንቋ፣ በስርዓተያታና በስልጣን መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ሴቶች በስብሰባ ላይ ድርሻ ወስደው ለመናገር የተለያየ ችግር ያለባቸው ይመስላል። አንደኛው ከማህበረሰቡና ከራሱ ከስራ ተቋሙ በወረሱት ባህል ምክንያት ባለባቸው ፍርሃት፣ ሁለተኛው በወንዶች የበላይነት ድርሻቸውን ስለሚነጠቁና ጣልቃ በመግባት ስለሚያስቆሟቸው ሲሆን፣ ሶስተኛው ለተለያዩ ስራ ቦታዎች/ሃላፊነቶች ባለመጋለጣቸው ስለስራ ቦታቸው ጠለቅ ያለ ቅድመግንዛቤ ስለሌላቸው በራሳቸው አለመተማመናቸው ይመስላል። በቀረበው መረጃ እንደተመለከተው አልፎ አልፎ ከወንዶች እኩል የመናገር

ድፍረትና ችሎታ ያላቸው ሴቶች ቢኖሩም ድርሻ እንደማይሰጣቸው እና እነዚህ ሴቶች ደግሞ የንግግር ችሎታውንም ሆነ ድፍረቱን ያገኙት በዩኒቨርሲቲውና ከዩኒቨርሲቲው ውጭ በተለያዩ ስራዎችና የሃላፊነት ቦታዎች ተሳትፎ ያላቸውና የነበራቸው በመሆናቸው ነው፡፡ ለምሳሌ በአኮ.002 ከታደሙት ስድስት ሴቶች መካከል የተናገሩት ሶስቱ ሲሆኑ ሁለቱ ሴቶች ለመናገር ድፍረቱ፣ ፍላጎቱና ችሎታው እንዳላቸው ተመልክተናል፡፡ እነዚህ ሁለቱ ሴቶች አገሬና ኢሌኒ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በሃላፊነትም ሆነ በተለያዩ ቦታዎች በመስራት ልምድ ያካበቱ በመሆናቸው ምክንያት ከወንዶቹ እኩል የመናገር ፍላጎትና ድፍረት እንዳላቸው ድርሻ በመጠየቅና ባገኙት ድርሻም ረዘም ያለ ዲስኩር አድርገዋል፡፡ ይህ ደግሞ በስብሰባ ላይ በመናገር ራስን ማስተዋወቅን በተመለከተ እነዚህ ሴቶች እንደወንዶቹ ግንዛቤ እንዳላቸው ይጠቁማል፡፡ ለዚህም በቡድን ውይይት በመስመር (1611-1628) እንደተመለከተው አገሬ በተቋሙ ስልጣን የሚገኘው ስብሰባ ላይ በመናገር እንደሆነ ስልጠና እንደወሰደችና ከስልጠናው በኋላም አንድ ቀን መድረክ ስታገኝ በመናገሯ በማግስቱ ሹመት እንዳገኘች ገልፃለች፡፡ ስለሆነም ‹‹ከአነጋገር ይፈረዳል ከአያያዝ...›› የሚለው ማህበረ ባህላዊ አባባል የዩኒቨርሲቲው ባህል እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም ሰዎች ሃላፊነት/ስልጣን ላይ ሲሆኑ ሃሳባቸውንም ሆነ ራሳቸውን የመግለፅ አቅማቸው ከፍ እያለ እንደሚሄድ ያሳያል፡፡ ከዚህ በተለየ ደግሞ የምንመለከተው ወንዶቹ ምንም ልምድ ኖራቸው አልኖራቸው ለመናገር ፍርሃት እንደሌለባቸውና ድርሻ እንኳ ባያገኙ ሀይል በመጠቀም ጣልቃ በመግባት ሲናገሩ ተስተውሏል፡፡

በመሆኑም በተግባቦት ሂደት በስርዓተፆታና በቋንቋ መካከል ያለውን ግንኙነት ስንመለከተው የትምህርት ደረጃ፣ እድሜና ባህል የራሳቸው አስተዋፅኦ ቢኖራቸውም ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስደው ግን በስራ ተቋሙ ውስጥ በተለያዩ ስራዎችም ሆነ የሃላፊነት ቦታ ላይ ተሳታፊ መሆን እንደሆነ መረጃው ያረጋግጣል፡፡ በመስክ ማስታወሻ የተወሰደው መረጃ እንደሚያመለክተው በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ባሉ ከፍተኛ የሃላፊነት ቦታዎች ምንም አይነት ሴት የለም፡፡ ይህ ደግሞ በዚህ ተቋም ብቻ ሳይሆን ችግሩ ሰፊ ለመሆኑ በ2005 ዓ.ም በአማራ ክልል የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ፎረም 3ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ አጥኝዋ በመገኘት የወሰደችው የመስክ ማስታወሻ እንደሚያመለክተው በስብሰባው ከተገኙት 68 ተሳታፊዎች መካከል ከየዩኒቨርሲቲዎቹ የተገኙት 21 ከፍተኛ ሃላፊዎች ሲሆኑ እነዚህም ሁሉም ወንዶች ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጥናቱ በተካሄደባቸው ፋካሊቲዎች

የጥናቱ መረጃ በተሰበሰበበት ጊዜ እንደታየው ሴቶች ካላቸው ቁጥር አንፃር ሲታይ በ001 ፋካሊቲ 1ሴት፣ በ002 ፋካሊቲ 1 እና በ003 ፋካሊቲ 2 ሴቶች ብቻ የኮሚሽን አባል ነበሩ። በእርግጥ ይህ ቁጥር በየጊዜው የሚለዋወጥ ሲሆን አሁን ባለበት ጊዜ ሲታይ ሊቀንስም ሊጨምርም ይችላል። ለምሳሌ ለጥናቱ ከተመረጠው ድስኩራዊ አሃድ መካከል የአኮ003 ሰብሳቢ የነበረችው ዲን መረጃው በተወሰደ በሁለተኛ ሳምንት ሃላፊነቷን ለቃለች።

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት በተወሰዱት መረጃዎች ጥናቱ በተካሄደበት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ስራን በተመለከተ በሚደረግ ተግባቦታዊ መስተጋብር ሀሳባን ከመግለጽ አንፃር ሲታይ በትልልቅ ስብሰባዎች ላይ የወንዶች ቁጥር ከመብዛቱ ጋር ተያይዞ ቀድሞ ድርሻ የመጠየቅና የማግኘት ሁኔታ ቢኖርም፤ አንዳንድ ሴቶች በውይይቱ ሂደት ከመናገራቸው በፊት ዝግጅት ስለሚያደርጉ ሃሳባቸውን በግልጽና በትክክል ከማቅረብ አንፃር የተሻለ አቀራረብ እንዳላቸው በጥናቱ የተገኘው መረጃ ያመላክታል። በእድሜያቸው በጣም የገፉ ወይም በትምህርታቸው ከፍ ያሉ ሴቶች የተለያየ ሃላፊነት ተሰጧቸው ልምድ ያካበቱትን መድረክ ይዘው ስንመለከታቸው በጣም ገላጭና ሃሳባቸውንም ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ የማስኬድ አቅም አላቸው። ብዙ ጊዜ ሴቶች ለተለያዩ ገጠመኞች የመጋለጥ ሁኔታው እንደወንዶች ሰፊ አይደለም። ጓደኝነታቸውንም ስንመለከት ከተመሳሳይ ዖታ ጋር ነው። ይህ ደግሞ ለምሳሌ ሴቶቹ አንድ ላይ ሆነው ስለአንድ ጉዳይ ሲወያዩና በመሀላቸው አንድ ወንድ ሲገባ የሚገልጹት ሃሳብ አንድ አይነት አይሆንም። ምክንያቱም የተለያየ ልምድ በመኖሩ ነው። ስለሆነም ሴቶች በተለያዩ መድረኮች የመናገር ድርሻ ባለማግኘታቸውና በሃላፊነት ቦታ ባለመቀመጣቸው ምክንያት የተለያየ ልምድ ስለሌላቸው ሀሳባቸውን በመግለፅ ሂደት ተፅዕኖ ያደርግባቸዋል። የሴቶችን እንቅስቃሴ በአብዛኛው ስንመለከተው ከቤት ወተው ወደማስተማር የሚሄዱ በመሆናቸው ከማስተማር ውጭ ሌላ ተጨማሪ ልምድ የላቸውም። እንደአገሬ አገላለጽ ‹‹ምንም ኤክስፒሪያንስ በሌለበት ቦታ ስልጣኑን ሁሉ ወንዶች በያዙበት ሁኔታ ውስጥ ሆና ሴት ልጅ የመናገር አቅሟ ውሱን ነው›› በማለት ልምድ የሚያገኙበት መንገድ እንደሌለ ገልፃለች። አንዳንዱም ሴት በብዙ ሹክቻ ስልጣን ከያዘች በስራ ሂደት ለሚፈጠረው ስህተት ለወንዶችና ለሴቶች የሚሰጠው ምላሽ እኩል እንዳለሆነና ሴቷ እንደወንዱ ላጠፋችው ጥፋት ከሚሰጣት ቅጣት በተጨማሪ ‹‹ድሮውንስ ሴት አይደለች...ልጆቿን አርፋ ብታሳድግ›› የሚሉ ጉዳዮች እንደሚሰነዘሩ መረጃው ይጠቁማል። ይህ ደግሞ ሌሎች ሴቶችንም የማያበረታታ ከመሆኑም በላይ

ብሳሳት እንዲህ ልባል እችላለሁ ስለሚሉ አርፈው ይቀመጣሉ፡፡ ከዛ በኋላ እንደገና ለመመለስ ከባድ እንደሚሆን አገሬ ገልፃለች፡፡ በመሆኑም የመናገር ድርሻና የሃላፊነት ቦታዎችን እንዲያገኙ ከማድረግ በተጨማሪ ለተለያዩ ልምዶች ቢጋለጡ ለምሳሌ በዩኒቨርሲቲው በሃላፊነት ከሚቀመጡና አቅም ካላቸው ሰዎች ጋር የመገኛኘት፣ የመነጋገርና ሃሳብም ሆነ እውቀት የመለዋወጥ አጋጣሚዎች እየሰፉ ሲመጡ ሃሳባቸውን የመግለጽ አቅማቸው እየተለወጠ እንደሚመጣ ከቡተቃ 201፣ መስመር 344-59 የተወሰደው መረጃ ያረጋግጣል፡፡

ሴቶች ለመናገር እጃቸውን አውጥተው ድርሻ ካልተሰጣቸው እጃቸውን አጣጥፈው ይቀመጣሉ፡፡ ይህ ደግሞ ከማህበረሰቡ ይዘውት የመጡት ብናገር አጉራ ዘለል እባላለሁ የሚለው ባህል ተፅዕኖ በማድረጉ ነው፡፡ ሆኖም ግን በዚህ ደረጃ ያሉ ሴቶቹ ራሳቸው ድርሻው ይገባናል በማለት መጠየቅና ድርሻ በመንጠቅ መታገል እንደሚኖርባቸው በውይይቱ ተገልጿል (አባሪ አራትን መስመር 1399-1403 ይመለከቷል)፡፡

ሴቶች ጠንቃቆች በመሆናችው ከመናገራቸው በፊት ማስታወሻ በመያዝ ዝግጅት ስለሚያደርጉ ሃሳባቸውን ሳያንዛዙና ሳያሿዙሩ በግልፅ ቋንቋ በአጭሩ ያቀርባሉ፡፡ ሴቶች የሚናገሩት ለመታወቅ እንዳልሆነና በዚህም ስኬታማ እንደሆኑ ከበደ እንደሚከተለው ገልፆታል ‹‹ብዙ ጊዜ ለመናገር ብለው የሚናገሩ ሰዎች ወይም ለማስመዝገብ የሚናገሩ ሰዎች አይሳካላቸውም፡፡ ከልብ መናገር ሲኖርባቸው የሚናገሩ ሰዎች ግን ምንጊዜም ይሳካላቸዋል፡፡ እንደዚህ አይነት ሰዎች ደግሞ ሴቶች ናቸው››(አባሪ አራት፣መስመር1523-27 ያገናዝቧል)፡፡ በተጨማሪም ሀሳብን በአጭሩና በግልፅ ከማቅረብ አንፃር ሁለቱም ፆታዎች ችሎታው አላቸው፡፡ ቢሆንም ሀሳብን አሚልቶ ከማቅረብ አንፃር ተናጋሪ ሴቶች ጥቂት ቢሆኑም ከወንዶች ጋር ሲነፃፀሩ ሴቶች የተሻሉ ናቸው፡፡ በእርግጥ አንደበት በተናገሩበት ቁጥር እየተባ የሚሄድ መሳሪያ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ስንመለከተው ሴቶች የመጠንቀቁ ሁኔታ ቢኖራቸውም ሁልጊዜ የመናገር እድሉ ስለሌላቸው የተባ አንደበት ይኖራቸዋል ለማለት አስቸጋሪ እንደሆነም ተጠኝዎቹ ገልፀዋል፡፡

ሌላው ሴቶች ሆደባሻ በመሆናቸውና ብናገር ሰው ምን ይለኛል ብለው ስለሚጨነቁ ሃሳባቸውን በንግግር ከመግለጽ ይልቅ ማልቀስ እንደሚቀናቸውም ተገልጿል፡፡ ከዚህ ሌላ

ሁለቱም ፆታዎች ሃሳባቸውን በትክክል የሚገልጹና ሁለቱም መግባባት የሚችሉ ቢሆንም አንዳንዴ ወንዶች መድረክ ላይ መነገር የሌለበትን ነገር ወጣ ብለው ሲናገሩ ይታያል። አብዛኛዎቹን ሴቶችን ስንመለከት ደግሞ በሁሉም ርዕሰ ጉዳዮች ላይ አይናገሩም። በመጀመሪያ የሚናገሩባቸውን ርዕሰ ጉዳዮች የሚመርጡ ሲሆን፣ ብዙ ጊዜ በንግግራቸው ትኩረት የሚያደርጉት በችግሮች ላይ ነው። የሚናገሩበትን ርዕሰ ጉዳይ ከመረጡ በኋላ ደግሞ ቀድመው በመዘጋጀት ጥንቃቄ ስለሚያደርጉ ከወንዶች በተሻለ ሁኔታ ሃሳባቸውን የመግለፅ አቅም አላቸው።

በመጨረሻም በስራ ቦታ ላይ የሚደረግን ተግባቦታዊ መስተጋብር ራስን ከመግለፅ አንፃር ሲታይ ወንዶች ራሳቸውን በማስተዋቅና ስለራሳቸው ማንነት በመግለጽ በኩል የተሻሉ ሲሆኑ፣ ሴቶች ግን ራሳቸውን በመግለጽ በኩል የሚቸገሩ እንደሆኑ ከምልከታውና ከቡተቃ የተገኙት መረጃዎች ያመለክታሉ። ለዚህም የተላበሱት ትህትና ጫና እንደፈጠረባቸውና ስለራሳቸው መናገር የበላይነትን ማሳየት ስለሆነ ተገቢ መስሎ እንደማይታያቸውና ስልጣን የሚገኘው በንግግር ሳይሆን በስራ ነው ብለው እንደሚያምኑ የመሰረት አገላለጽ ‹‹ትሰራለች ብሎ ካመነ ጓደኛየ ሊገልፅልኝ ይችላል። ፕሮፖዝ ሊያረገኝ ይችላል›› የሚለው ያመለክታል። ግን ደግሞ ስለራሳቸው ባለመግለፃቸው ምክንያት እንዳንዴ ችግር እንደሚፈጠርባቸውና በተቃራኒው ደግሞ ስለራሳቸው በመናገራቸው ምክንያት ከደረሰባቸው ችግር ማምለጥ እንደሚችሉ ገልፀዋል። እንደካሳ አገላለጽ አንዲት ዶክተር በሆስፒታል አንድን ህመምተኛ በማከም ላይ እያለች ሲስተር ብሎ ሲጠራት ዶክተር ብሎ እንዲጠራት ሳትነግረው የህክምና ግልጋሎቱን ሰጥታ እንደጨረሰች የተመለከተውን ገልጿል። እሱ ግን ስለራሱ መናገር ባለበት ቦታና እንዲሁም በመናገሩ ሊያገኘው የሚችል ጥቅም ካለ ለምሳሌ የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሌክቸረር በማለት ከዛም በላይ በዩኒቨርሲቲው ያለውን የሃላፊነት ቦታም በመጨመር ስለራሱ ለመግለፅ ወደኋላ እንደማይል ገልጿል። ከዚህም በተጨማሪ ራስን በአግባቡ ማስተዋወቅና የሰሩትን ነገር መናገር ሌላውን ከማስተማር አንፃር ከሆነ ተገቢ ቢሆንም ብዙ ጊዜ ግን ወንዶች ራሳቸውን በትክክል ከመግለፅ አልፈው አንዳንድ ጥቅማጥቅም ለማግኘት ሲሉ ትንሽ የሰሯትን አጋነው የማቅረብና በሌሎች ላይ የበላይ ሆኖ የመታየት አይነት ነገር ይታይባቸዋል (ቡተቃ201፣ መስመር 505-526 ይመልከቱ)። ይህ ደግሞ የሚያሳየው ወንዶች የተቋሙን ባህል ቀድመው የተረዱ መሆናቸውን ነው። ይኸውም ተቋሙ ‹‹አፍ ሲከፈት ጨንቅላት ይታያል›› የሚለውን ማህበረሰባዊ ፍልስፍና የሚከተል ሲሆን የመምህራኑን ሙያዊ ችሎታና ብቃት ለማወቅ የሚጠቀምበት ስልት መምህራኑ በስብሰባ ላይ በሚያደርጉት ዲስኩር እንደሆነ ቀጥሎ የቀረበው መረጃ ይጠቁማል።

አስረጅ፡-

> ቢንያም፡- ቢሆንም ግን ስብሰባ በመቆጣጠር ለመታየትም የሚሞክሩት ወንዶች ናቸው። ስልጣንም ለመፈለግ ሆነ ለማሳየት ሚሞክሩት ወንዶች ናቸው። ምን ይሰራሉ፣ እንዴት ይሰራሉ፣ ምን አይነት አቅም አላቸው የሚለውን ለማሳየት። እንዲያውም እኔ ለዚህ ባለፈው አመት አጠቃላይ የመምህራን ስብሰባ ጊዜ ታስታውሳላችሁ ..... ምንድን ነው ያሉት ‹‹...በእያንዳንዱ ፕሮግራም እያንዳንዱ ሰው ምን አይነት ‹‹ካሊቲ››እና ብቃት እንዳለው አናውቅም። ስለዚህ እንደዚህ ትልልቅ ስብሰባዎች ሲኖሩ ፊታችሁን አስመቱ። ስለዚህ ሃሳብን በሃሳብ የማፍረስ፣ የመቃወም፣ ራሽናል የማቅረብ ችሎታ ማን ነው ያለው ስለዚህ ማን ምን ነገር ሰርቷል የሚለውን እናውቃለን። ስለዚህ አስፈላጊ ነው ከመቶ አምስት ሰው ቢፈለግ አምስት ሰው ብቃት እንዳለው እንዴት ማረጋገጥ እችላለሁ። ስለዚህ ፊታችሁን አስመቱ›› ሲሉ በግልፅ አስታውሳለሁ። ስለዚህ ለዚህ ይመስለኛል በትልልቅ ስብሰባዎች ላይ ተፅዕኖ የሚሳድሩት ወንዶች። ሴቶች ግን ችሎታውንና ብቃታቸውን የሚገልፅ ሀሳብ አያቀርቡም። ለቀረበ ሀሳብም ረገጥ አድርገው ተፅዕኖ አድርገው ለአመራር ብቁ መሆናቸውንም አያሳዩም (ቡተቃ 202፣ መስመር 438-453)።

ከቀረበው መረጃ እንደምንመለከተው የዩኒቨርሲቲው ሃላፊ መምህራኑ ምን እንደሰሩ፣ በሙያቸው ያላቸውን ብቃትና ችሎታ የሚለዩት በትልልቅ ስብሰባዎች ላይ መምህራኑ በሚያደርጉት ንግግር ነው። ይህን የተረዱት ወንዶች ደግሞ ‹‹ካለመናገር ደጃዝማችነት ይቀራል።›› የሚለውን ማህበረሰባዊ ፍልስፍና መሰረት በማድረግ እንደዚህ ያሉ የውይይት መድረኮችን በመጠቀም ራሳቸውን በመግለፅ ተፅዕኖ ለመፍጠር እንደሚሞክሩ ያሳያል።

4.4 የውጤት ማብራሪያ

በዚህ ክፍል በዓይነታዊ የምርምር መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች በሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ስልት ተተንትነው ያስገኙት ውጤት በምርምሩ ጥያቄዎች መነሻነት ለማብራራት ተሞክሯል። ምርምሩ ሁለት አብይ ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን አንደኛው ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታ ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር በሚያደርጉት የተግባቦት ሂደት ሀሳባቸውን እንዴት ይገልፃሉ? የሚል ሲሆን በዚህ ስር የሚመለሱ ዝርዝር የምርምሩ ጥያቄዎች ደግሞ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች፣ ሃሳባቸውን አድማጭ በሚረዳው ሁኔታ ባግባቡ እንዴት ይገልፃሉ? ድርሻን ጠብቆ ከመናገር አንፃር እንዴት ይሳተፋሉ? በንግግር ያላቸው ተደማጭነት ምን ይመስላል? በተግባቦት ሂደት የቋንቋ አጠቃቀማቸው ምን ይመስላል? በተግባቦት ሂደት የሚያሳዩት ድስኩራዊ ልማድ ምን ይመስላል?

በተግባቦት ሂደት ሀሳባቸውን ለመግለፅ ተፅዕኖ አድራጊ ጉዳዮች ምንድን ናቸው? የሚሉት ናቸው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የቀረበው አብይ የምርምር ጥያቄ ደግሞ ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታ ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር በሚያደርጉት የተግባቦት ሂደት ራሳቸውን እንዴት ይገልፁታል? የሚል ሲሆን በዚህ ስርም ጥናቱ የሚመልሳቸው ዝርዝር ጥያቄዎች ሴቶችም ሆኑ ወንዶች የሙያ ብቃታቸውን ለመግለፅ የሚያደርጉት ጥረት ምን ይመስላል? በስራ ቦታቸው ላይ ያላቸውን ድርሻ እንዴት ይገልፃሉ? ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በተግባቦት ሂደት ማንነታቸውን ለመግለጽ ተፅዕኖ አድራጊ ጉዳዮች ምንድን ናቸው? የሚሉት ናቸው፡፡

4.6.1 በተግባቦት ሂደት ሀሳብን የመግለጽ ሁኔታ

የጥናቱ የመጀመሪያው አብይ ዓላማ ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታ ከአቻዎቻቸው ጋር በሚያደርጉት ተግባቦት ሂደት ሀሳባቸውን እንዴት እንደሚገልጹ መመርመር የሚል ሲሆን በውጤት ትንተናው እንደተመለከተው በመደበኛ ውይይት ላይ ሴቶችና ወንዶች ሀሳብን በመግለጽ ያላቸውን ተሳትፎ ሻን (1999) እና ታነን (1994) እንዳረጋገጡት በዚህም ጥናት የውጤት ትንተናው እንደሚያሳው አብዛኛዎቹ ወንዶች ሀሳባቸውን በመግለጽ ከፍተኛ ተሳትፎ ያላቸው ሲሆን ሴቶች ግን ሀሳባቸውን በመግለጽ አይሳተፉም፡፡ ከንግግር ጊዜ አንፃር ደግሞ ወንዶች ከውይይቱ አጀንዳ የመጀመሪያ አካባቢ ጀምሮ እስከመጨረሻው አብዛኛዎቹ ወንዶች ተናጋሪዎች ሲሆኑ፤ ሴቶቹ ግን በአጀንዳዎቹ መጨረሻ አካባቢ ሲናገሩ ይታያል፡፡ ከዚህም ሌላ በተደጋጋሚ ድርሻ ከመውሰድና ረዥም ንግግር ከማድረግ አንፃር ወንዶቹ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡ ይህም ከሻንና ከታነን ጥናት ጋር ይደጋገፋል፡፡ በሌላ በኩል በኢመደበኛ ውይይት ላይ ያለው ተሳትፎ ከፆታ የበላይነት ጋር የተያያዘ ሲሆን ሴቶች በበዙበት አውድ ሴቶች፤ ወንዶች በበዙበት አውድ ደግሞ ወንዶች ይበልጥ ሀሳባቸውን ይገልፃሉ፡፡ በዚህ አውድ የቀረቡ ጭብጦችን ስንመለከት ወንዶች በበዙበት ኢመደበኛ አውድ አይነኬ የሚባሉ፣ ሴቶች ደግሞ ማህበራዊ ጉዳይን የሚመለከት ጭብጥ የሚያቀርቡ መሆናቸውን የውጤት ትንተናው ያመለከተ ሲሆን፣ ታነን (1994) በጨዋታ ጊዜ የወንዶቹ ጣፋጭነት የጎደለው አጉል የወሲብ ቀልድ ላይ እንደሚያተኩር ከገለጹት የጥናት ውጤት ጋርም ይደጋገፋል፡፡ ሴቶች በበዙበት ኢመደበኛ ውይይት ላይ ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ ተሳታፊዎቹ ሴቶች ሲሆኑ ማህበራዊ፣ ግለሰባዊ እና ጓደኛዊ በሆኑ ርዕሶችና ችግሮች ላይ የሚያተኩሩ እንደሆኑ የውጤት ትንተናው ያመለከተ ሲሆን ይህም

ከሻን (1999) ጥናት ጋር ተመሳሳይነት አለው። አውዱ ወንዶች የበዙበት ከሆነ ጭብጡ የሚወሰነው በወንዶች ሲሆን በአብዛኛው ግን ሀሳብ ከመስጠት ይልቅ አዳማጭ መሆንን ይመርጣሉ። ይህም የሴቶች ንግግር የሚያነጣጠረው በትብብር፣ በጓደኝነት፣ በአንድነት፣ በእኩልነት፣ በመረዳዳት፣ ወዘተ ላይ እንደሆነና የወንዶች ደግሞ በመታወቅ፣ የበላይነት ስሜትና ደረጃቸውን በመጠበቅ ዙሪያ እንደሚያነጣጥር ካሳዩበት ከታነን (1990,1991) ስራዎች ጋር ተደጋጋፊነት አለው።

በአጠቃላይ በመደበኛም ይሁን በኢመደበኛ አውድ ሴቶችና ወንዶች ሀሳባቸውንና ራሳቸውን እንዴት እንደሚገልጹ በጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች መሰረት ቀጥሎ ተብራርቶ ቀርቧል።

4.6.1.1 ሃሳባቸውን አድማጭ በሚረዳው ሁኔታ ባግባቡ የመግለፅ ችሎታ

ሃሳብን በአግባቡ ለመግለፅ በመጀመሪያ የውይይቱን ርዕሰጉዳይ መከታተልና መረዳት ያስፈልጋል። የውጤት ትንተናው እንደሚያሳየው አብዛኛዎቹ ሴቶች በተለይም በመደበኛ ውይይት ላይ ሀሳባቸውን አይገልጹም። ሆኖም ግን በቁጥር አነስተኛ የሆኑ የተለያየ ወይም ከፍ ያለ የስራ ልምድ ያላቸው ሴቶች ሀሳባቸውን ከመግለጻቸው በፊት ውይይቱን በጥልቀት በመከታተል መናገር የሚፈልጉትን ጉዳይ በማስታወሻቸው በማስፈር ዝግጅት ያደርጋሉ። አብዛኛዎቹ ወንዶቹ ደግሞ ውይይቱን የሚከታተሉት በማዳመጥ ሲሆን ንግግር ከማድረጋቸው በፊትም ባብዛኛው ማስታወሻ በመያዝ አይዘጋጁም።

ማስታወሻ በመያዝ የተዘጋጁት ሴቶችም ሆኑ ያልተዘጋጁት ወንዶች ሃሳባቸውን ለሌሎች በሚያቀርቡበት ጊዜ ሁለቱም የመግለፅ ችሎታው አላቸው። በእርግጥ በመደበኛ ውይይት ላይ ንግግር የሚያደርጉ ሴቶች በቁጥር አነስተኛ ቢሆኑም ተዘጋጅተው ስለሚናገሩ ሀሳባቸውን ግልጽና አጭር አድርገው የሚያቀርቡ ሲሆን፤ አንዳንድ ወንዶች ደግሞ ከርዕሱ በመውጣት ሀሳቡን የማወሳሰብ ሁኔታ ይታይባቸዋል። አብዛኛዎቹ ሴቶች ደግሞ በሰው ፊት የመናገር ልምዱ ስለሌላቸውና በጉዳዩ ላይ ያላቸው ቅድመግንዛቤ ዝቅተኛ በመሆኑ ሀሳባቸውን በስብሰባ ላይ አይገልጹም። አልፎ አልፎ የመናገሩ አጋጣሚ ሲኖርም ንግግራቸው ያልተሟላና ጥያቄ አዘል የሆኑ አሃዶች ይጠቀማሉ። ውጤቱ ታነን(1999) እና ውድ(2010) ሴቶች አጫጭር የሆኑ ድስኩራዊ ቃላትን

ይጠቀማሉ በማለት ካቀረቡት ጋር ተደጋጋፊነት አለው። ከዚህ በተለየ ሁኔታ ግን ሴቶች በበዙበት ኢመደበኛ ውይይት ላይ ሃሳባቸውን በመግለጽና አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ የሆነ የሀሳብ ልውውጥ የሚያደርጉ ሲሆን፤ በተቃራኒው ደግሞ ወንዶች በበዙበት ኢመደበኛ ውይይት ላይ የመደበኛው አይነት ባህርይ ያሳያሉ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ወንዶችም ቢሆኑ ሴቶች በበዙበት ኢመደበኛ ውይይት ላይ ሃሳባቸውን ለመግለጽ የሚቆጠቡ ሲሆን በተቃራኒው ደግሞ ሴቶች በበዙበት መደበኛ ውይይት ላይ ወንዶች ንቁ ተሳታፊና ሀሳባቸውን የሚገልጹ ሲሆን ሴቶች ግን ሃሳባቸውን አይገልጹም። ይህም ሴቶች ኢመደበኛ እና የሴቶች ቁጥር የበዛበት ወይም ሴቶች ብቻ ያሉበት የውይይት አውድ የሚመቻቸው እንደሆነ የውጤት ትንተናው ይጠቁማል።

4.6.1.2 ድርሻን ጠብቆ ከመናገር አንፃር ያላቸው ተሳትፎ

ድርሻን ጠብቆ ከመናገር አንፃር ያለውን ተሳትፎ በተመለከተ የውጤት ትንተናው እንደሚያሳው በተለይም መደበኛ በሆኑ አጠቃላይ የዩኒቨርሲቲው ስብሰባዎች ላይ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በአብዛኛው ድርሻን የሚወስዱት እጅ በማውጣት ሲሆን፤ በእንደዚህ አይነት ስብሰባ ላይ ብዙ ጊዜ ሴቶች ቁጥራቸው አነስተኛ ቢሆኑም ለመናገር እጅ በማውጣት ሲጠይቁ ድርሻ ይነፈጋቸዋል። እነዚህ ሴቶች እጅ ከማውጣት ውጭ ድርሻው ሲነፈጋቸው የተለያዩ ስልቶችን ተጠቅመው ጣልቃ ገብተው ለመናገር አይሞክሩም። ወንዶች ግን ድርሻ ጠይቀው ሲነፈጋቸው የተለያዩ ብልሃቶችን በመጠቀም ጣልቃ በመግባት ወይም ተደርቦ በመናገር ድርሻ ይነጥቃሉ። የውጤት ትንተናው እንደሚያሳው የሴቶች ሀሳብ ጠቃሚ ነው ተብሎ የማይወሰድ ሲሆን በአብዛኛው ድርሻ የሚሰጣቸውም ለተሳትፎ ሲባል እንደሆነ መረጃው ያሳያል። ይህም አንድ ማህበረሰብ በወንዶች የበላይነት የሚያምንና የሚመራ ከሆነ የስራ ተቋማቱም በተመሳሳይ ወንድ ተኮር ስለሚሆኑ በተቋሙ ጠቃሚ ሆነው የሚታዩት ወንዶች እንደሆኑ ከሚያሳየው ከዋርተን (2005) ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ ተደጋጋፊነት አለው።

ከዚህ በተለየ ደግሞ በትምህርት ክፍልና በፋካሊቲ ደረጃ በሚደረጉ ስብሰባዎች አብዛኛዎቹ ሴቶችና ወንዶች ለመናገር ሲፈልጉ እጃቸውን በማውጣት ድርሻቸውን ጠብቀው ሲናገሩ፤ አንዳንዶች በተለይም በእድሜያቸው፣ በስራ ልምዳቸውና በደረጃቸው ከፍ ያሉት ወንዶች

ደግሞ እጅ ሳያወጡ ጣልቃ በመግባት ብቻ የንግግር ድርሻ ይወስዳሉ። እንደዚህ አይነት ወንዶች በአብዛኛው ይህን የሚያደርጉት በፋካሊቲና በትምህርት ክፍል ደረጃ በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ ሲሆን በዚህ አውድም ሰብሳቢው ከእነሱ ያነስ የስራ ልምድ ያለው ከሆነ ነው። እጅ አውጥተው ድርሻ የሚጠይቁ ወንዶች ድርሻ ካላገኙ ሀሳቡን ጀምሮ በማቋረጥና ልብ በማንጠልጠል፣ ይቅርታ፣ተጨማሪ፣ ማስተካከያ፣ እዚህ ጋ የመሳሰሉትን ስልቶች በመጠቀም ጣልቃ በመግባት ድርሻ ይወስዳሉ ወይም ይነጥቃሉ። ውጤቱ ከዘመርማንና ዌስት (1975)፣ ፊሸማን (1980)፣እና ሻን (1999) ጥናቶች ጋር ተደጋጋፊነት አለው።

በሌላ በኩል ግን ሴቶች በኢመደበኛ ውይይት ላይ ድርሻን ጠብቆ በመናገር ረገድ ያላቸው ልምድ ከመደበኛው የተለየ ሆኖ ይታያል። ይኸውም በኢመደበኛ ውይይት በተለይም ሴቶች የበዙበት ከሆነ የንግግር ድርሻ ጠብቀው ከመናገር ይልቅ በመደራረብና ጣልቃ ገብቶ የመናገር ልማድ እንዳላቸው የውጤት ትንተናው የሚያሳይ ሲሆን ውጤቱ ከዋልተን 2005) ጥናት ጋር ተደጋጋፊነት ያለው ሲሆን ስፔንደር (1990) እና ስዋን (1989) ጣልቃ ገብነትና ተደራርቦ መናገር የወንዶች የንግግር ልማድ እንደሆነ ከገለጹት ጋር ደግሞ ይቃረናል።

4.6.1.3 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በንግግር ያላቸው ተደማጭነት

ተደማጭነት ከሃይል ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው። አጀንዳን በማስያዝ ደረጃም ሆነ የውሳኔ ሃሳብ በማቅረብ ደረጃ ሲታዩ በአብዛኛው የወንዶቹ ተቀባይነት ሲኖረው የሴቶቹ ግን ተቀባይነት አያገኝም። የውጤት ትንተናው እንደሚያሳየው ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ሃሳባቸውን በሚገልጹበት ወቅት ከእነሱ ቀድሞ የተናገረውን ወንድ እከሌ እንዳለው በማለት ሃሳቡን ዋቢ በማድረግ ሲያቀርቡ፣ በተቃራኒው ግን ሴቶቹም ሆኑ ወንድ ተናጋሪዎች እከሌ እንዳለችው ብለው የሴትን ሃሳብ በዋቢነት ወስደው አይናገሩም። ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ሀሳብ በሚያቀርቡበት ጊዜ ድጋፍ ወይም ሀሳባቸውን የሚያረጋግጥላቸው ሰው ሲፈልጉ ስም በመጥራት የሚጠይቁት በስልጣን ከወንድ የምትበልጥ ሴት እንኳ ብትኖርም ዋቢ የሚያደርጉት ወንዱን ነው። በመሆኑም የወንዶች ሃሳብ ተፈላጊ ሲሆን የሴቶቹ ግን በአብዛኛው ትኩረት የሚቸረው እንዳልሆነ የውጤት ትንተናው የሚያሳይ ሲሆን ይህም ለሴቶች ትኩረት አለመሰጠቱ ከባሬት እና ዴቢድሰን (2006) ጥናት ጋር ተመሳሳይ ነው።

ከዚህ ሌላ በሀሳብ አገላለጽ በኩል ሴቶች ሀሳባቸውን በቀጥታና ለስለስ ባለ ትህትና በተላበሰ ሁኔታ ስለሚያቀርቡ ተደማጭነት እንዳላቸውም የውጤት ትንተናው ያስረዳል።

4.6.1.4 በሴቶችም ሆነ በወንዶች በተግባቦት ሂደት የሚታየው የቋንቋ አጠቃቀም

የቋንቋ አጠቃቀምን በተመለከተ በውጤት ትንተናው የተገኘው በተለያዩ ውይይቶች ላይ ሀሳባቸውን የሚገልጹ ሴቶችና ወንዶች የሚጠቀሙበትን ቋንቋ ስንመለከት በአብዛኛው ተመሳሳይ ቢሆንም አልፎ አልፎ ግን ስርዓተያታ ተኮር ሆኖ እናገኘዋለን። በመደበኛ ስብሰባዎች ላይ በሚደረጉ ውይይቶች የሴቶች ንግግር በአብዛኛው ትህትና የተላበሰ ሲሆን በዚህም ገለፃቸው በቀጥታ እርግጠኝነትን የማያሳዩ ይመስለኛል፣ ቢሆን፣ ይሻላል የሚሉትን ቀጥተኛ ያልሆኑ ማለዘቢያ ቃላት ይጠቀማሉ። ይህ ደግሞ ታነን (1994) በተግባቦት ሂደት ሴቶች ቀጥተኛ ምላሽ እንደማይሰጡ ካሳዩበት ጥናት ጋር ይመሳሰላል። ከዚህም በተጨማሪ በሀሳብ ልውውጥ ሂደት የተብራራና የተሟላ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ በአብዛኛው ጭንቅላታቸውን በማነቃነቅ ‹‹እህ›› አልፎ አልፎ ደግሞ ‹‹እሽ›› የሚሉ ቃላትን በተደጋጋሚ በመጠቀም አዎንታዊነቱን ወይም አሉታዊነቱን የማይገልጽ ምላሽ ይሰጣሉ። በዚህ የቋንቋ አጠቀቃቀማቸው እህ የሚለውን ምለሽ የሚጠቀሙት አዎንታዊ ምላሽ ለመስጠት ሳይሆን ተናጋሪው ምን እንደሚል እየተከታተሉት እንደሆነ የሚያሳይ እንደሆነ የውጤት ትንተናው ያሳያል። ክትትሉ ደግሞ በመጨረሻ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ምላሽ ስለሌለው ተናጋሪው ትክክል እንደሆነና እንዲቀጥል ለማድረግ የተጠቀሙበት መሆኑን የሚያሳይ ነገር የለም። ይህ ውጤት ደግሞ ቀደም ጥናቶች ለምሳሌ ፊሸማን (1985)፣ ዘመርማን እና ቄስት (1975)፣ ኮትስ (1989) እና ሻን (1999) ሴቶች በንግግር ወይም በሰውነት እንቅስቃሴ ስሜታቸውን በመግለጽ ተናጋሪው ንግግርን እንዲቀጥል ወይም እንዲያቆም የማድረግ ሀይል እንዳላቸው ከገለጹት ጋር ተመሳሳይነት ያለው ቢመስልም ስሜታቸውን ይገልፃሉ ከሚለው ጋር ግን ይቃረናል።

ከዚህ በተጨማሪም ማብራሪያ ለመስጠት በሚፈልጉበት ጊዜ ደግሞ ሀተታዊ ዓረፍተነገር ከመጠቀም ይልቅ ነው እንዴ? አይደል? አይደለም ወይ? የሚሉትን ጥያቄዊ ዓረፍተነገሮች ይጠቀማሉ። ይህም የሚያውቁትን ጉዳይ ነው፣ እንደዚህ አይደለም ብሎ በእርግጠኝነት ድምዳሜ በመስጠት ላለመናገር በተዘዋዋሪ መንገድ ለመግለጽ የተጠቀሙበት ስልት

እንደሆነ ያሳያል። እንዲህ አይነቱ የሴቶች አቀራረብ ደግሞ በራሳቸው የማይተማመኑ ሆነው በሌሎች እንዲታዩ እንደሚያደርጋቸው ታነን(1990) ይገልፃሉ። ባንፃሩ ደግሞ የአብዛኞቹ ወንዶች ንግግር ወደ አፅንዖታዊና ድምፀታዊ አገላለፅ የሚያደላ ሲሆን ነው፣ ግድ ነው፣ አይደለም፣ አይሆንም፣ የሚሉ ቃላትን በመጠቀም ሀሳባቸውን በእርግጠኝነትና ሀይል በተላበሰ ሁኔታ ያቀርባሉ። ውጤቱም ከቀደምት ጥናቶች ግሪይ (1992)፣ ታነን(1997) ፣ሻን(1999) እና ሙላኒ (2007) ጋር ተደጋጋፊ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ጥቂት ወንዶች በተለይም በእድሜና በስራ ልምድ ከፍ ያሉት ድርሻን ለመውሰድ ጣልቃ በመግባት ሀይል ቢጠቀሙም ሀሳባቸውን በሚያቀርቡበት ጊዜ ግን ይሻላል፣ ይመስለኛል፣ ቢሆን የሚሉትን ቃላት በመጠቀም ትህትና የተላበሰ ንግግር ከማድረጋቸውም በላይ የሚያቀርቡት ሀሳብ በውይይቱ የተፈጠረውን ችግር በመፍታት ላይ ያተኮረ እንደሆነ የውጤት ትንተናው ያስረዳል።

ንግግራዊ አውድን በተመለከተ በአብዛኛው ሴቶቹ የሚጠቀሙት የንግግር ስልት (እኛ) እያሉ ነው። የወንዶቹን በተመለከተ ደግሞ አብዛኛዎቹ ግላዊ ሀሳባቸውን ለማቅረብ አንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር(እኔ) የሚለውን ተውላጠ ስም በመጠቀም ጉዳዩን ከራሳቸው አንፃር ያቀርባሉ። አንዳንዶቹ በስራ ልምዳቸው ከፍ ያሉት ወንዶች ከአንደኛ መደብ ነጣላ ቁጥር (እኔ) ወደ አንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር (እኛ)፣ እና በተቃራኒው ከእኛ ወደ እኔ በመቀላቀል ሲጠቀሙበት ይታያል። በሌላ በኩል ሴቶች በስራ ልምዳቸው ከፍ እያሉ ሲሄዱ (እኔ) የሚለውን ተጠውላጠ ስም በመጠቀም ስለራሳቸው እንደሚገልጹና ይህም በራስ የመተማመን ውጤት እንደሆነ የውጤት ትንተናው ያሳያል።

ምፀታዊ አገላለጾችን በተመለከተ ተዘውታሪ እንዳልሆነና አልፎ አልፎ አንዳንድ ወንዶች በመደበኛ ውይይት ላይ አሉታዊ ሀሳብን ለማቅረብ ይጠቀሙበታል። የአጠቃቀሙ አላማም አሉታዊ ሃሳብ የያዘን ጉዳዩ በቀጥታ ከማቅረብ ይልቅ በተዘዋዋሪ ለማቅረብ እንደሆነ የውጤት ትንተናው የሚያሳይ ሲሆን ውጤቱ ከታነን (1990) ወንዶች ቀጥተኛ የሆነና የመሰላቸውን መመለስ ይቀናቸዋል ከሚለው ውጤት ጋር ይቃረናል። ከዚህ በተለየ ሁኔታ ግን ሴቶች በበዙበት ኢመደበኛ ውይይት ላይ ሴቶች ምፀታዊ አገላለፅን በስፋት

እንደሚጠቀሙ የታየ ሲሆን ይህ ደግሞ ከታነን (1990) ጥናት ጋር ሴቶች ምላሳቸው ቀጥተኛ አይደለም ከሚለው ጋር በመጠኑ ይደጋገፋል።

አፅንያታዊ አገላለጽን በተመለከተ ወንዶች አራት ነጥብ፣ ሌላ ነገር የለውም፣ አንችልም፣ አይደለም፣ ለምንድን ነው፣ ግድ ነው የመሳሰሉትን ሀይል ያላቸውን አፅኖታዊ አገላለፆችን በስፋት ይጠቀማሉ። አጠቃቀማቸውም አፅንያታዊ ቃላቱን በቀጥታ ከመጠቀም በተጨማሪ ቃላቱን በመደጋገም ለምሳሌ ‹‹አራት ነጥብ...አራት ነጥብ፣ አለ...አለ፣ ለምንድን ነው...ለመንድን ነው›› እና በቃላቱ ውስጥ የሚገኙ ድምፆችን አቆራርጦ በመናገር ‹‹ት-ፈ-ሯ-ቸ-ዋ-ላ-ች-ሁ›› በማለት ሲጠቀሙ ይታያል። የሴቶቹ አቀራረብ ደግሞ ከአንዳንድ ሴቶች በስተቀር አብዛኛዎቹ ሀይል የለሽ ገለፃ እንደሚጠቀሙና በዚህም የወንዶች የበላይነት የሚንፀባረቅበት እንደሆነ የውጤት ትንተናው ያመለከተ ሲሆን ይህም ግረይ (2002) እና ውድ(2010) ሃይል የተላበሰ ንግግር ከማቅረብ አንፃር የወንዶችና የሴቶች አገላለፅ እንደሚለያይ ካቀረቡት ጋር ተመሳሳይነት አለው ። በሌላ መልኩ ደግሞ አንዳንድ ከፍተኛ የስራ ልምድ ያላቸው ወንዶች አፅንያታዊ አቀራረባቸው ልክ እንደሴቶቹ የተለሳለሰ እንደሆነ የውጤት ትንተናው አሳይቷል።

አብዛኛዎቹ ወጣት ወንዶች ሀሳባቸውን በንግግር በሚገልጹበት ጊዜ ድምፀታዊ ቃላትን ምንም ጥርጥር የለውም፣ ምናልባት፣ ለወደፊት፣ የግድ የተሰኙትን በመጠቀም ሀሳባቸውን ሀይል በተሞላበት ሁኔታ ሲገልፁ ይስተዋላል። ሴቶቹና በእድሜያቸውም ሆነ በስራ ልምዳቸው ከፍ ያሉት ወንዶች ግን በአብዛኛው ድምፀታዊ ቃላትን ሲጠቀሙ አይታዩም።

ስነምግባራዊ አቀራረብን በተመለከተ ቢሆን፣ አይሻልም፣ ይቅርታ፣ እንግዲህ፣ ቢኖር ይሻላል፣ ሊኖር ይችላል፣ እንዲህ ብናደርግ፣ የሚሉትን ስነምግባራዊ አጠቃቀሞች በሴቶችም ሆነ በወንዶች የሚታዩ ሲሆን፤ የወንዶቹን ስንመለከት ግን የትህትና ማላበሻ የሆኑ ቃላትን በመጠቀም ሀሳባቸውን የሚያቀርቡ በእድሜና በስራ ልምዳቸው ከፍ ያሉት ወንዶች ናቸው። የአጠቃቀማቸውን ምክንያት ስንመለከት ደግሞ ውይይቱ ወደመልካም አቅጣጫ እንዲሄድና ችግሩ በውይይት እንዲፈታ ለማድረግ የሚጠቀሙበት ስልት ይመስላል።

ሌላው ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ተጨማሪ ሃሳብ ለማቅረብ (በተጨማሪም፣ እና)፣ አማራጭን ለማሳየትና ውሳኔን ወይም ሃሳብን ለማጠቃለል (እና)፣ የሌላ ሰው ሃሳብን ለመቃወም (ግን፣ ነገር ግን፣ ቢሆንም) የሚሉትን የመሸጋገሪያ ቃላት እንደሚጠቀሙ በውጤት ትንተናው ተመልክቷል።

4.6.1.5 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በተግባቦት ሂደት የሚያሳዩት ድስኩራዊ ልማድ

በተግባቦት ሂደት የሚታዩ ድስኩራዊ ልማድን በተመለከተ በመደበኛ ውይይት ወቅት አብዛኛዎቹ ወንዶች ተራቸውን ሳይጠብቁ ድርሻ የመንጠቅ፣ የጣልቃ ገብነትና ተደርቦ የመናገር ድስኩራዊ ልማድ እንዳላቸውና ይህንም ለመፈፀም ማሳሰቢያ፣ ማስተካከያ፣ ተጨማሪ፣ ይቅርታ፣ የመሳሰሉትን ብልሃቶችን ይጠቀማሉ። ባንፃሩ ደግሞ አብዛኛዎቹ ሴቶች ተራን ጠብቆ የመናገር ልምድ እንዳላቸው ያላቸው ሲሆን፣ አንዳንድ የተሻለ የስራ ልምድ ያላቸው ሴቶች ግን ብዙ ጊዜ ባይሆንም ድርሻ ካልተሰጣቸው ጣልቃ በመግባት ድርሻ እንደሚቀሙ የውጤት ትንተናውን ያሳያል። የወንዶች ጣልቃ ገብነትን ስንመለከት ሁለት መልክ አለው። አንደኛው ድርሻ ጠይቀው ሲከለከሉ ድርሻን በሀይል ለመውሰድ ሲሆን፤ ሁለተኛው ግን በእድሜ፣ በትምህርት ደረጃና በተለያዩ የሃላፊነት ቦታዎች ያገለገሉ ወንዶች በተለይም በትምህርት ክፍልና በፋካሊቲ ደረጃ በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ የንግግር ድርሻን እጅ በማውጣት መውሰድ እንደማይፈልጉና ይልቁንም ጣልቃ በመግባት የንግግር ድርሻ የመውሰድ ልምድ እንዳላቸውና ይህም በሰብሳቢውና በተናጋሪው እንዲሁም በተናጋሪውና በአድማጮች መካከል ያለውን የሀይል ግንኙነት የሚያመለክት እንደሆነ የውጤት ትንተናው ያስረዳል።

በሌላ በኩል ደግሞ ሴቶች በበዙበት ኢመደበኛ ውይይት ላይ ሴቶች ተራን ያለመጠበቅ፣ የንግግር ድርሻን ብቻ ሳይሆን የውይይት ርዕሰ ጉዳይንም የመንጠቅ፣ ተደራርቦ የመናገር፣ የጎንዮሽ ወሬና ያለመደማመጥ ልማድ አላቸው። በተቃራኒው ሴቶች በበዙበት ኢመደበኛ አወድ ደግሞ ወንዶች የጣልቃ ገብነትም ሆነ ሀሳባቸውን በመግለጽ በኩል ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ እንደሆነና በእንደዚህ አይነት አውድ የመናገር ፍላጎት እንደሌላቸውና እንደሚፈሩም በውጤት ትንተናው ታይቷል።

በሀሳብ ልውውጥ ሂደት አብዛኛውን ጊዜ ሴቶች ከመናገራቸው በፊት ማስታወሻ በመያዝ ስለሚዘጋጁ ተናጋሪውን በመረዳት ተገቢ ምላሽ የሚሰጡ ሲሆን አንዳንድ ወንዶች ግን የተናጋሪው ንግግር በመረዳትና መሰረት በማድረግ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ መናገር የሚፈልጉትን ጉዳይ ለመናገር ሲሉ ከአጀንዳ እንደሚወጡ በጥናቱ ውጤት ተመልክቷል።

መድረክን ከመጠቀም አንፃር አብዛኛዎቹ ወንዶች ልምድ ያላቸው ሲሆን አብዛኛዎቹ ሴቶች ደግሞ መድረክን ተጠቅሞ ሃሳባቸውንም ሆነ ራሳቸውን የመግለጽ ልምድ የላቸውም። መድረክን ተጠቅመው ሀሳባቸውን የሚገልጹት ሴቶችም ሆኑ ወንዶች መድረኩን በመቆጣጠር ድርሻቸውን የሚወጡ ቢሆንም፣ አንዳንዶች ግን መድረክ የመቆጣጠር ችግር አለባቸው። የችግሩ መንስዔ ግን ስርዓተ ፆታዊ ልዩነት ያለው ሲሆን ይህም ሴቶች ከመድረኩ እንዲመልሱ ወይም እንዲያብራሩ ለሚጠየቁት ጉዳይ ተገቢውን ምላሽ ወይም ማብራሪያ መስጠት ሲገባቸው መናገር ባለመፈለጋቸው፤ ወንዶች ደግሞ ከአጀንዳ በመውጣትና የአድማጭን ስሜት መሰረት አድርጎ ባለመናገር የሚፈጠር እንደሆነ የውጤት ትንተናው ያሳያል።

በውይይት ሂደት ርዕስን ጠብቆ ከመናገር አንፃር የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ርዕስ ያለመጠበቅ ሁኔታ ይታይባቸዋል። ሆኖም ግን ርዕስ የማይጠብቁበት ምክንያት ሲታይ ወንዶቹ ማለት የሚፈልጉት ጉዳይ ተገቢውን ምለሽ አላገኘም ብለው ሲያስቡ እና የራሳቸውን ማንነት ማለትም የትምህርት፣ የእውቀትና የስራ ልምዳቸውን ለማስተዋወቅ ሲፈልጉ ከውይይቱ ርዕስ (አጀንዳ) ይወጣሉ። ሴቶቹ ደግሞ መጀመሪያ በቀረበው አጀንዳ ላይ ለመናገር ድርሻ ባለማግኘታቸው ምክንያት በመጨረሻ ድርሻ ሲያገኙ ከአጀንዳው በመውጣት ወደኋላ በመሄድ ስላለፈው ርዕሰጉዳይ በመናገር ዲስኩርን ወደኋላ የመመለስና ከውይይት አጀንዳ የመውጣት ባህርይ እንዳላቸው የውጤት ትንተናው ያሳያል። ይህም ሴቶች በተገቢው ጊዜ የንግግር ድርሻ የሚሰጣቸው ከሆነ የውይይቱን አጀንዳ ጠብቆ በመናገር ረገድ ከወንዶች የተሻሉ እንደሆኑ ይጠቁማል።

ሌላው የውጤት ትንተናው እንደሚያመለክተው አጀንዳን ማቅረብና ማስተዋወቅ የሰብሳቢው ድርሻ ሲሆን፣ ተጨማሪ አጀንዳና የመወያያ ጉዳይ ሁለቱም ፆታዎች በማቅረብ ይሳተፋሉ።

ሆኖም ግን አንዳንድ ጊዜ በሴቶች የሚቀርቡ ርዕሰ ጉዳዮችና ሀሳቦች ተቀባይነት የላቸውም፡፡

4.6.1.6 በተግባቦት ሂደት ሀሳብን ለመግለፅ ተፅዕኖ አድራጊ ጉዳዮች

በተግባቦት ሂደት ሀሳብን በመግለፅ ደረጃ አብዛኛዎቹ ወንዶች ያለምንም ተፅዕኖ ሀሳባቸውን በነፃነት የሚገልጹ ሲሆን፤ አንዳንድ ወንዶች ሰፊ ታዳሚ ባለበት ሁኔታ ብዙዎች ስለሚናገሩ ከመናገር አድማጭ መሆንን ይመርጣሉ፡፡ በአንፃሩ ሴቶች በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ ሃሳባቸውን መግለፅ እየፈለጉ ሳይናገሩ የሚወጡበት አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው፡፡ እንዳይናገሩ ከሚያደረጓቸውን ጉዳዮች መካከል ፍርሃት፣ ድርሻ አለማግኘት፣ በጉዳዩ ላይ ቅድመ ግንዛቤ አለመኖር፣ የወንዶች በንግግር የበላይ መሆንና የስብሰባው አውድ አንደሆኑ የውጤት ትንተናው ያስረዳል፡፡

ፍርሃት፡- በውጤት ትንተናው እንደታየው ለሴቶች ፍርሃት መንስዔው ቤተሰባዊ አስተዳደጋቸውና የመጡበት ባህል ሴት ልጅ ዝምተኛ እንድትሆን እየተገራች የመጣች ከመሆኗ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ፍርሃቱ ደግሞ ለረጅም ጊዜ መሰረት የጣለ በመሆኑ በአጭር ጊዜ ለመቅረፍ አስቸጋሪ ስለሆነ በስራ ቦታቸው ችግሩ አብሮ ዘልቋል፡፡ በመሆኑም በተለያዩ ስብሰባዎች በተለይም መደበኛ በሆኑት ውይይቶች ላይ ሀሳባቸውን አይገልጹም፡፡ አልፎ አልፎ መናገር ሲፈልጉ ከፍተኛ ፍርሃት እንዳለባቸውና በዚህም ምክንያት ለመግለጽ ያሰቡትን ሀሳብ አይገልጹም፡፡

ይሉኝታ፡- በዩኒቨርሲቲው በሚደረጉ ውይይቶች ላይ ብናገር ምን እባላለሁ፣ እንዲሁም ከስብሰባው ውጭ እንዲህ አለች እየተባለ የሚወራውን ወሬ በመፍራት መናገር የሚፈልጉትን ሃሳብ ሳይናገሩ ይወጣሉ፡፡ ሆኖም ግን በይሉኝታና በፍርሃት ምክንያት ሳይናገሩ ከወጡ በኋላ ሀሳባቸው ሌሎች ሲናገሩ የተሻለ እንደነበረ ከሚያገኙት ምላሽ ሲገነዘቡ እንደሚቆጫቸው የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡

በራስ አለመተማመን፡- በጥናቱ እንደታየው ከሆነ ሀሳብን ያለፍርሃት በድፍረት የሚገልጹ ሴቶች እጅግ በጣም ጥቂት ሲሆኑ እነዚህ ሴቶች በተለያየ አጋጣሚ በራስ የመተማመን

ችሎታቸውን ያዳበሩ ናቸው። አንዳንዶቹ በተለያየ የስራ ቦታና ሁኔታ በመጋለጣቸው ምክንያት ባከበቱት የስራ ልምድና ቅድመ ግንዛቤ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ባላቸው የትምህርት ደረጃና ውጤት በራስ የመተማመን ችሎታቸውን ለማዳበር ያቻሉ ናቸው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በቤተሰባዊ አስተዳደጋቸው እጅግ ፈሪ የነበሩና በዚህም ምክንያት በትምህርት ቤት እስከ ዩኒቨርሲቲ ደረጃ ሲማሩ ምንም ተናግረው የማያውቁና ጥያቄ ሲኖራቸው በጓደኞቻቸው አማካኝነት ሲያስጠይቁ የነበሩ ሴቶች አሁን በተወሰነ ደረጃ በራሳቸው እንደሚተማመኑና በትልልቅ ስብሰባዎች ላይ ባይናገሩም በትምህርት ክፍልና በፋካሊቲ ደረጃ በሚካሄዱ ውይይቶች ላይ ሀሳባቸውን በመግለጽ ደረጃ ለውጥ እንዳሳቸውና ከድሮው ማንነታቸው ጋር ሲነጻጸር አሁን ተናጋሪ የሚባሉ እንደሆኑ የውጤት ትንተናው ያሳያል። ይህም በራስ የመተማመን ችሎታን በአንድ አጋጣሚ ማዳበር የሚቻል ከሆነ ከቤተሰብ ወይም ከማህበረሰቡ ይዘውት የሚመጡትን ባህል መስበር የሚቻል እንደሆነ ያመለክታል።

በሌላ በኩል ግን በቤተሰባዊ አስተዳደጋቸውና ከዚህ ዩኒቨርሲቲ ውጭ በነበሩበት የስራ ቦታ ሀሳባቸውን በመግለጽ በኩል ደፋርና በራሳቸው የሚተማመኑ የነበሩ ሴቶች ወደዚህ ዩኒቨርሲቲ ካመጡ በኋላ ግን በራስ የመተማመን ችሎታቸው እንደቀነሰና በተለይም በመደበኛ ውይይቶች ላይ እንደማይናገሩ የውጤት ትንተናው ያስረዳል። ይህም ከቤተሰብና ከአካባቢ ዳብሮ የሚመጣ በራስ የመተማመን ችሎታ በተቋሙ ባህልና በተቋሙ ውስጥ ባለን ደረጃ ምክንያት ሊሸረሸር እንደሚችል ይጠቁማል። ውጤቱ ታነን (1994)፣ ሃሪሰን(1972) እና ሞርጋን(1997) ዲስኩር የማህበረሰቡ ባህል ብቻ ሳይሆን እንደስራ ተቋሙ ባህልም የሚወሰን እንደሆነ ከገለጹት ጋር ተደጋጋፊነት አለው።

ድርሻ አለማግኘት፡- በተለይ በትልልቅ ስብሰባዎች ላይ ለመናገር እጅ በሚያወጡበት ጊዜ በስብሰባ መሪዎች አለመታየትና ድርሻ አለማግኘት ብዙ ጊዜ ይታያል። በዚህም ባህሉ ሴት እንድትናገር የሚጠበቅ ጉዳይ ባለመሆኑና ስብሰባን የሚመሩ ሰዎችም ከዚሁ ባህል የመጡ በመሆናቸው የሴቶች ሃሳብ ያስፈልጋል የሚል እምነትም ሆነ ግንዛቤ ስለሌላቸው ለሴቶች ድርሻ እንደማይሰጡና ከሰጡም ለተሳትፎ እንደሆነ የውጤት ትንተናው ያመለክታል።

ቅድመ ግንዛቤ፡- በጉዳዩ ላይ ቅድመ ግንዛቤ አለመኖር አንዱ ለሴቶች አለመናገር ምክንያት ነው። ለውይይት በሚቀርበው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጠለቅ ያለ ግንዛቤ ከሌለ ማንኛውም ሰው

ሃሳብ ከማፍለቅ ይገታል። ሴቶች ብዙውን ጊዜ ከቤት ወተው ወደማስተማሩ ከመሄድ ባሻገር ለተለያዩ ጉዳዮችና ሁኔታዎች ተጋልጦ የላቸውም። ከዚህም በተጨማሪ በስራ ቦታቸው አካባቢ የተለያዩ መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ የስራ ጉዳዮችን ለመፈፀምም ሆነ ማህበራዊ ግንኙነታቸውም ከተመሳሳይ ፆታ ጋር ብቻ በመሆኑና የተለያዩ መረጃዎችን የያዙ ፅሁፎችን በማንበብ የተለያዩ መረጃዎችንና ልምዶችን በማግኘት ረገድ ክፍተት አለባቸው። በዚህም ምክንያት አንዳንድ ጊዜ በስብሰባ ላይ ለውይይት የሚቀርቡትን አጀንዳዎች ያለማወቅና ያለመረዳትም ሁኔታ በመኖሩ ሀሳባቸውን ካለመግለጻቸው በተጨማሪም ሀሳብ የለሾች ስለሚሆኑ የማይናገሩበት አጋጣሚ እንዳለ የጥናቱ ውጤት ያመለክታል።

የወንዶች በንግግር የበላይ መሆን፡- የውጤት ትንተናው እንደሚያሳው በተለያዩ ስብሰባዎች በሚደረግ ውይይት ላይ አብዛኛዎቹ ወንዶች በየትኛውም ስብሰባ ቢያንስ አንድ ጊዜ ሳይናገሩ የማይወጡ ሲሆን፣ ድርሻ ጠይቀው ባይሰጣቸው እንኳን ጣልቃ በመግባት፣ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ድርሻ በመንጠቅ ይናገራሉ። በአንፃሩ ሴቶች ፈርተው፣ ሀሳብ የሌላቸው ሆነው ወይም ድርሻ በማጣታቸው ምክንያት አብዛኛውን ጊዜ ሳይናገሩ ይወጣሉ። ድርሻ ከሚያጡበት ምክንያት አንዱ ደግሞ በወንዶች ድርሻቸውን የሚነጠቁበት ሁኔታ በመኖሩ ነው። ይህም ወንዶች ብዙ ጊዜ በተደጋጋሚ ድርሻ ስለሚወስዱና ረዥም ንግግር በማድረግ በንግግር የበላይነትን መያዝ ስለሚፈልጉ ለእነሱ ድርሻቸውን እንደሚለቁ የጥናቱ ውጤት ያሳያል። ይህም ፊሸማን (1980)፣ ኤድሌይና ዌዘርል(1997)፣ ሻን(1999) እና ዋርተን (2005) በጥናታቸው የሴቶች የበታችነት ስሜት በንግግር ወቅት መታየት ዋና ምክንያት የበላይነት ስሜት ማሳደር የፈጠረው ተፅዕኖ መሆኑን ከገለጹት ጋር ተደጋጋፊነት አለው።

የስብሰባው ድባብ፡- የውጤት ትንተናው እንደሚያሳየው በስብሰባ ላይ የሚቀርበው አጀንዳ አጨቃጫቂ ከሆነ እንዲሁም ስብሰባውን የሚመሩት ሰዎች ከታዳሚው የሚቀርበውን ሀሳብ የማይቀበሉና አካሄዱ የተለመደ ሁኔታ የማይታይበት ከሆነ፣ እንዲሁም የስብሰባው ተሳታፊ ስሜት ጥሩ ካልሆነ ከመናገር በመቆጠብ ዝም ማለትን ይመርጣሉ። በተለይም በመደበኛ ውይይት ላይ አብዛኛዎቹ ሴቶች ጭቅጭቅ ወይም ተግዳሮት ያለበት አውድ ከሆነ ከመሳተፍ ራሳቸውን እንደሚያገሉና ችግሩን ከመጋፈጥ ይልቅ የሚያፈገፍጉ ሲሆን፣

ውጤቱም ግረይ (1992) እና ታነን (1994) ሴቶች በተግባቦት ሂደት ችግርን መጋፈጥና መቋቋም እንደማይፈልጉና ከዚህ ይልቅ ተባባሪና ተግባቢ እንደሆኑ ከገለጹት ጥናት ጋር ይመሳሰላል።

4.6.2 በተግባቦት ሂደት ራስን የመግለፅ ሁኔታ

ሁለቱም ፆታዎች በስራ ቦታቸው ላይ ያላቸውን የሙያ ብቃት በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ በሚደረጉ ውይይቶች ላይ ከመግለፅ አንፃር ከፍተኛ ልዩነት እንዳለ የውጤት ትንተናው ያሳያል። ይኸውም ወንዶች በሙያቸው ምን እንደሰሩ፣ ምን እየሰሩ እንደሆነ፣ ምን ውጤት/ለውጥ እንዳገኙ በውይይቱ በሚነሱት አጀንዳዎች ላይ በመጨመር ሲገልጹ ይታያሉ። አብዛኛዎቹ ሴቶች ግን በዋናነት ከአጀንዳው ጋር የተያያዘ ሃሳብ በቀጥታ ከመናገር አልፈው ስለራሳቸውም ሆነ ስለሙያ ብቃታቸው ምንም አይነት ገለፃ ሲያደርጉ አይስተዋሉም። አልፎ አልፎ ግን አንዳንድ ሴቶች የሙያ ብቃታቸውን ይገልፃሉ። እነሱም ከፍተኛ የስራ ልምድ ያላቸውና ከዩኒቨርሲቲው ውጭም ሆነ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በተለያዩ የስራ ቦታዎች ላይ የሰሩ ናቸው። የውጤት ትንተናው እንደሚያሳየው ስለራሳቸው ለመግለፅ ምንም ፍርሃት አለማሳየታቸው ብቻ ሳይሆን ስለራስ መናገር በባህሉ ያልተለመደውን ነገር በቀጥታም ባይሆን የመስበር ሁኔታ ያሳዩ ሲሆን ውጤቱም ሴቶች በስራቸው ላይ ልምድ እያካበቱ ሲሄዱ በንግግር የበላይነትን ይይዛሉ፣ ስለራሳቸውም ይገልፃሉ በማለት ከቀረበው ከባስ (2001) ጥናት ጋር ተደጋጋፊነት አለው።

4.6.2.1 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በስራ ቦታቸው ላይ ያላቸውን ድርሻ የመግለፅ ልምድ

አብዛኛዎቹ ወንዶች በስራ ቦታቸው (በዩኒቨርሲቲው) ምን እንደሚሰሩ፣ ምን አይነት ሃላፊነት እንዳላቸው ወይም ከአሁን በፊት ምን እንደሰሩና ምን አይነት ስልጣን እንደነበራቸውና በዚህም ያስገኙት ውጤት ምን እንደሆነ ‹‹እኔ›› በማለት ስላራሳቸው ይገልፃሉ። አገላለፃቸው አንዳንዶቹ ከአንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ወደ አንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር በመሄድ፣ መጀመሪያ ጉዳዩን የግላቸው በማድረግ ስላራሰቸው ከገለጹ በኋላ መልሰው ደግሞ ጉዳዩን የጋራ በማድረግ የሚያቀርቡበት ስልት ነው። አንዳንዶች ደግሞ በተቃራኒው በመጀመሪያ ጉዳዩን የወል በማድረግ (እኛ) በማለት ካቀረቡ በኋላ መልሰው ጉዳዩን የራሳቸው በማድረግ (እኔ) እያሉ የሚያቀርቡበት ሁኔታ ይታያል። በሁለቱም መንገድ

ሲታይ ግን ወንዶች ራሳቸውን ለመግለጽ አጋጣሚዎችን በማመቻቸት እንደሚጠቀሙ ያመለክታል። አንዳንድ ወንዶች ደግሞ በዩኒቨርሲቲው የሌላቸውን የስራ ድርሻ እንዳላቸው አድርገው ከዩኒቨርሲቲው ውጭና ለተማሪዎች የሚናገሩ ሲሆን፣ ይህም ወንዶች ያላቸውን የስራ ድርሻ በመግለጽ በኩል ከፍተኛ ልምድ ያላቸው እንደሆነ የውጤት ትንተናው ያስረዳል።

በሌላ በኩል ሴቶች በስራ ቦታ ያላቸውን ድርሻም ሆነ በአጠቃላይ ስለራሳቸው የተለያዩ መድረኮችን በመጠቀም ሲገልጹ አይስተዋልም። የውጤት ትንተናው እንደሚያሳየው ድርሻ ወስደው የሚናገሩ አብዛኞዎቹ ሴቶች የቀረበውን አጀንዳ የሚመለከት ሀሳብ በቀጥታ ከማቅረብ ውጭ ስለራሳቸው (እኔ) ብለው አይናገሩም። በአብዛኛው ንግግራቸው የሚያተኩረው ጉዳዩን የወል በማድረግ መግለፅ ላይ ነው። በእርግጥ አንዳንድ ወጣ ያሉና ከቁጥር የማይገቡ በስራቸው ከፍተኛ ልምድ ያላቸውና የነበራቸው እንዲሁም በስብሰባ ላይ መናገር ራስን በማስተዋወቅ ረገድ ጠቀሜታ እንዳለው ግንዛቤ ያገኙ ሴቶች እኔ በማለት የነበራቸውን ሃላፊነትና የሰሩትን ስራ በድፍረት ይናገራሉ። ይህም ሴቶች ልምድ እያካበቱ ሲሄዱና ራስን መግለጽ ጠቃሚ እንደሆነ ግንዛቤ የሚኖራቸው ከሆነ ባህሉን የሚሰብሩ መሆኑን አመላካች ነው።

ከዚህም በተጨማሪ የውጤት ትንተናው እንደሚያመለክተው በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከዩኒቨርሲቲው ውጭ በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ወንዶች የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ‹‹ሌክቸረር›› እንደሆኑና ጠቃሚ መስሎ ከታያቸውም በተጨማሪ በዩኒቨርሲቲው ያላቸውን ሃላፊነትም የሚገልጹ ሲሆን፤ ሴቶቹ ግን ያላቸውን ሃላፊነትም ሆነ የት እንደሚሰሩና ሌክቸረር መሆናቸውንም አይገልጹም። የራሳቸውን ማንነት ባለመግለጻቸው ምክንያት አንዳንድ ጊዜ ችግር እንደሚፈጠርባቸውና በመናገራቸው ደግሞ ችግሩ እንደሚቀልላቸውም የጥናቱ ውጤት ያመለክታል።

4.6.2.2 በሴቶችም ሆኑ በወንዶች በተግባቦት ሂደት ማንነታቸውን ለመግለጽ ተፅዕኖ አድራጊ ጉዳዮች

ትህትና፡- ስለራስህ ሰው ይናገርልህ እንጅ አንተ አትናገር የሚል የማህበረሰቡ ባህል በሁለቱን ፆታዎች ተፅዕኖ የሚያደርግ ቢሆንም በሴቶች ላይ ግን ስር የሰደደ ችግር እንደሆነና ሴቶቹ ራሳቸውም ስለራስ ማንነት መናገር በሰዎች ላይ የበላይ የመሆን አይነት ስሜት ስለሚፈጥርና የበላይ ሆኖ መታየት ስለማይፈልጉ ስለራሳቸው ከመናገር እንደሚቆጠቡ የጥናቱ ውጤት ያስረዳል፡፡

ማህበረሰባዊ ባህል፡- በኢትዮጵያ ያለው ማህበረሰባዊ ሁኔታ በኢኮኖሚው፣ በማህበራዊና በፖለቲካው የወንድ የበላይነት የነገሰበት ሲሆን ይህም ቤተሰባዊ መነሻ ይይዝና መድረሻው ማህበረሰባዊ ይሆናል፡፡ ሁኔታው በማህበረሰቡ የእለት ተዕለት ተግባር የሚፈፀም ልማዳዊ ስርዓት ሲሆን፣ ይህ ልማዳዊ ስርዓት ደግሞ ሁለቱም በተለያየ ሁኔታ ውስጥ እንዲያድጉ ስለሚያደርጋቸውና በዚህም የተለያየ ማህበራዊ ልምድ ስለሚኖራቸው በተግባቦት ሂደት የተለያየ ባህርይ ሊያሳዩ ይችላሉ (ግሬይ፣1992)፡፡ በመደበኛ ስብሰባዎች ላይ በሁሉም ውይይች ላይ ካልተናገሩት ሴቶች ዝቅተኛ የስራ ልምድ ያላቸው ወንዶች ሃሳባቸውን ሲገልጹና ድርሻ ሲነጥቁ ሴቶቹ ግን ሀሳባቸውን ለመግለጽ አልሞከሩም፡፡ ይህም ወንዶቹ ከልጅነታቸው ጀምረው እየተናገሩ ስለሚመጡ ልምድ ያላቸው መሆናቸውን ሲያሳይ፣ ሴቶቹ ግን ከመነሻው ከአስተዳደጋቸው ጀምሮ ዝምታ ለእነሱ የተሰጠ ድርሻ እንደሆነ ግንዛቤ ይዘውና በዚሁ ውስጥ አድገው ስለመጡ የንግግር ልምድ የላቸውም፡፡

ተቋማዊ ባህል፡- አንዳንድ ሴቶች በቤተሰባዊ አስተዳደግም ሆነ ከዩኒቨርሲቲው ውጭ በሰሩባቸው የስራ ቦታዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ የንግግር ተሳትፎ እንደነበራቸውና ራሳቸውን እየገለጹ የመጡ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ቢሆንም በዩኒቨርሲቲው በሚደረጉ ውይይቶች ላይ ሀሳብ በሚሰጡ ሰዎች ላይ የሚሰነዘሩ ሀሳቦች እኔስ ምን እባላለሁ በሚል ይሉኝታ እንዳይናገሩ ከፍተኛ ተፅዕኖ አድርጎባቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለሴቶች የሚሰጠው ትኩረትም ሆነ ግምት መልካም ባለመሆኑና ስራን አስመልክቶ ውይይት በሚደረግበት ጊዜ የንግግር ድርሻ የሚሰጠው ለተሳትፎ እንጅ ሀሳባቸው ጠቃሚ ነው የሚል እምነት ኖሮ ባለመሆኑ ሃሳባቸውንም ሆነ ራሳቸውን ከመግለጽ እንደሚቆጠቡና ተስፋ የመቁረጥ ስሜትም እንደሚያሳዩ የውጤት ትንተናው አሳይቷል፡፡

በውጤት ትንተናው እንደታየው በዩኒቨርሲቲው የሚካሄዱ ተግባራት የሚመሩበት መተዳደሪያ ደንብ ያለው ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪም የተለያዩ ሃላፊነቶችን ለማግኘት ራሱን የቻለ መመሪያና አካሄድ አለው። ሆኖም ግን ከዚህም ሌላ አብዛኛዎቹ የሃላፊነት ቦታዎች የሚሰጡት ሰዎች በተለያየ መድረክ ከሚናገሩት በመነሳት እንደሆነ የውጤት ትንተናው ያመለክታል። ይህ ተቋማዊ ባህል መነሻው ‹‹ከአነጋገር ይፈረዳል፣ ከአያያዝ ይቀደዳል›› የሚለው የማህበረሰቡ ባህል ሲሆን፣ የተቋሙን ባህል የተረዱት ወንዶች ደግሞ ‹‹ካለመናገር ደጃዝማችነት ይቀራል›› የሚለውን የማህበረሰቡን ባህል መሰረት በማድረግ የሚያገኙትን መድረክ በመጠቀም መናገር የሚፈልጉትን ሀሳብ ብቻ ሰይሆን ስለራሳቸውም በመግለፅ ማግኘት ያለባቸውን ነገር ሁሉ ያገኛሉ። ሴቶቹን ስንመለከት ግን ሁሉም ነገር በስራ የሚገለፅና ስራችንም ጓደኞቻችን ስለሚያዩት ማግኘት የሚገባን ነገር በስራችን አማካኝነት እናገኛለን የሚል እምነት አላቸው። በመሆኑም የተቋሙን ባህል ባለመረዳታቸው ራሳቸውን በመግለፅ ሂደት ወደኋላ እንዲቀሩ አስተዋፅዖ አድርጓል።

ለተለያዩ የስራ ሁኔታዎች አለመጋለጥ፡- በዩኒቨርሲቲው በሚገኙ በተለያዩ ስራዎች፣ ኮሚቴዎች፣ ስብሰባዎች ወዘተ ላይ ተሳታፊ ከመሆን አንፃር ወንዶች የተሻሉ ሲሆኑ ሴቶቹ ግን ተሳትፏቸው ዝቅተኛ ነው። በውጤት ትንተናው እንደታየው፣ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ሆነ በፋካሊቲ ደረጃ ባሉ የሃላፊነት ቦታዎች ሴቶች ብዙም አይታዩም። በአብዛኛዎቹ ፋካሊቲዎች ሴቶች የአካዳሚክ ኮሚሽን አባላት አይደሉም። ሆኖም ግን በፋካሊቲዎቹ ያሉ ሴቶችን ስንመለከት በተለይም በማህበራዊ ሳይንስ ፋካሊቲዎች ውስጥ ብዙ ሴቶች የሚገኙ ሲሆን በኮሚሽን ግን ተሳታፊ አይደሉም። ይህም ሴቶች በዩኒቨርሲቲው በተለያየ የስራ ሁኔታ ባለመጋለጣቸውና በራስ የመተማመን ችሎታቸውን ባለማሳደጋቸው ሀሳባቸውን በተሻለና በነፃነት የመግለፅ ችሎታው እንዳይኖራቸው ተፅዕኖ እንዳደረገባቸው የውጤት ትንተናው ይጠቁማል።

ሌላው አብዛኛዎቹ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በዩኒቨርሲቲው ውስጥ መደበኛ በሆነው ስራም ሆነ በማህበራዊ እንቅስቃሴያቸው ከተቃራኒ ፆታ ጋር ያላቸው ግንኙነት ውሱን ሆኖ ታይቷል። ይህ ደግሞ በሁለቱም መረጃን ከማግኘት አንፃር ተፅዕኖ ቢኖረውም ከወንዶች ይልቅ በሴቶች ላይ ተፅዕኖው ከፍ ይላል። ምክንያቱም ወንዶች ለተለያዩ ስራዎችና

ሁኔታዎች ተጋላጭ በመሆናቸው ስለተለያዩ የስራ ሁኔታ መረጃው በእነሱ ቁጥጥር ስር ስለሆነና እነሱም ደግሞ እርስ በርሳቸው በመገናኘት ልምድ ስለሚለዋወጡ ከሴቶች ጋር ያላቸው ግንኙነት ውሱን መሆን በስራቸው ላይ ብዙም ተፅዕኖ ያሳደረባቸው አይመስልም። ሆኖም ግን ሴቶች በተለይም በተለያየ ሁኔታ ለሚፈጠሩ ችግሮች መፍትሄ የማግኘት ችሎታቸው ከፍተኛ ሲሆን፣ የእነሱን ሀሳብ አለመቀበል ማለት ደግሞ ይህንን ችሎታቸውን አለመጠቀም እንደሆነ የውጤት ትንተናው ያስረዳል።

በተቃራኒው ሴቶችን ስንመለከት ግን ግንኙነታቸው ከተመሳሳይ ፆታ ጋር ሲሆን፣ በዚህም አብዛኛዎቹ ሴቶች በተለያዩ ስራዎች ላይ ተሳታፊ ባለመሆናቸው ምክንያት የሚለዋወጡት መረጃም ሆነ የስራ ልምድ ተመሳሳይና ከመማር ማስተማሩ ያለፈ ስላልሆነ ሰፊ የሆነ የልምድ ልውውጥ አይኖርም። በመሆኑም ምንም ልምድ በሌለበት፣ ስልጣኑን ሁሉ ወንዶች በያዙበት ሁኔታ ውስጥ እየኖሩ ምንም ግብዓት ስለማያገኙ የመናገር አቅማቸው ውስን ነው። ስለሆነም ‹‹አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል›› ነውና አለመናገራቸው ደግሞ በሌሎች ማንነታቸው እንዳይታወቅ እንደሆነ የውጤት ትንተናው ያስረዳል።

ቅድመ ግንዛቤ፡- በተለያዩ መድረኮች ላይ በሚደረግ ውይይት ስለራስ መግለጹ ከማህበረሰቡ ባህል አንፃር ስንመለከተው የትህትና መገለጫ ባለመሆኑ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ራሳቸውን በመግለፅ በኩል ጫና አለባቸው። ሆኖም ግን ወንዶቹ በተለያየ የስራ ገጠመኞቻቸው ካካበቱት ልምድ ስለራስም ሆነ ሀሳብን መግለፅ ራስን የማስተዋወቂያ መንገድ እንደሆነ በማየታቸው፣ ይህን ቅድመ ግንዛቤ ተጠቅመው በሚያገኙት አጋጣሚ ሃሳባቸውን በመግለፅ ራሳቸውን ያስተዋውቃሉ። በአንፃሩ ግን ሴቶች ለተለያዩ ሁኔታዎች ባለመጋለጣቸው በመናገራቸው የሚደርስባቸውን ተፅዕኖ እንጂ የሚገኘውን ጥቅም ቀድመው ባለመገንዘባቸው ከመናገር እንዲቆጠቡ አንዱ ምክንያት እንደሆነ በውጤት ትንተናው ተመልክቷል።

ምዕራፍ አምስት፡- ማጠቃለያ፣ መደምደሚያ፣ የጥናቱ አንድምታና መፍትሄ

5.1 ማጠቃለያ

የጥናቱ ዋና ኣላማ በከፍተኛ ትምህርት ተቋም በስራ ቦታ ላይ የሚታየውን ስርዓተፆታዊ የተግባቦት ስልት ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው፡፡ ይህን አብይ ዓላማ መሰረት በማድረግ ምርምሩ ሁለት አብይ ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን አንደኛው ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታ ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር በሚያደርጉት የተግባቦት ሂደት ሀሳባቸውን እንዴት ይገልፃሉ? የሚል ሲሆን በዚህ ስር የሚመለሱ ዝርዝር የምርምሩ ጥያቄዎች ደግሞ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች፣ ሃሳባቸውን አድማጭ በሚረዳው ሁኔታ ባግባቡ እንዴት ይገልፃሉ? ድርሻን ጠብቆ ከመናገር አንፃር እንዴት ይሳተፋሉ? በንግግር ያላቸው ተደማጭነት ምን ይመስላል? በተግባቦት ሂደት የቋንቋ አጠቃቀማቸው ምን ይመስላል? በተግባቦት ሂደት የሚያሳዩት ድስኩራዊ ልማድ ምን ይመስላል? በተግባቦት ሂደት ሀሳባቸውን ለመግለፅ ተፅዕኖ አድራጊ ጉዳዮች ምንድን ናቸው? የሚሉ ናቸው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የቀረበው አብይ የምርምር ጥያቄ ደግሞ ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታ ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር በሚያደርጉት የተግባቦት ሂደት ራሳቸውን እንዴት ይገልፃሉ? የሚል ሲሆን በዚህ ስርም ጥናቱ የሚመልሳቸው ዝርዝር ጥያቄዎች ሴቶችም ሆኑ ወንዶች የሙያ ብቃታቸውን ለመግለፅ የሚያደርጉት ጥረት ምን ይመስላል? በስራ ቦታቸው ላይ ያላቸውን ድርሻ እንዴት ይገልፃሉ? ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በተግባቦት ሂደት ማንነታቸውን ለመግለጽ ተፅዕኖ አድራጊ ጉዳዮች ምንድን ናቸው? የሚሉት ዝርዝር ዓላማዎች ተነድፈዋል፡፡

በጥናቱ ለተነደፉት ጥያቄዎች ምላሽ ለማስገኘት የጥናቱ መረጃ በሶስት ፋካሊቲዎችና በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ከተደረጉ ውይይቶችና አውደጥናቶች 4 መደበኛና 2 ኢመደበኛ ውይይቶችን የያዙ አሃዶች ለትንተናው ተመርጠዋል፡፡ ምልከታ ከተደረገባቸው ሶስት ፋካሊቲዎች የተውጣጡ አስራ አንድ ሴቶችና አስራ አንድ ወንዶች በድምሩ ሃያ ሁለት መምህራንን በሶስት ቡድን በማደራጀት ቡተቃ ተደርጓል፡፡ የዩኒቨርሲቲው መተዳደሪያ ደንብ፣ የስራ አፈፃፀም መገምገሚያ ቅፆችና የሃላፊነት ቦታ ለመስጠት የሚሞላ

የመወዳደሪያ ቅፅ ከስርዓተፆታ አንፃር እንዴት እንደቀረቡ ተቋማዊ ባህልን በመፈተሽ ሂደት ተግባራዊ ሆነዋል።

ከዋናው ጥናት በፊት የተወሰኑ መረጃዎችን በናሙናነት በመውሰድ የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ መሳሪያዎቹን አስተማማኝነትና ትክክለኝነት ለማረጋገጥና የመረጃውን አካሄድ ለመፈተሽ ተሞክሯል። በዚህም መሰረት በአሳታፊ ምልከታ፣ በመስክ ማስታወሻ፣ በቡተቃና በሰነድ ፍተሻ አማካይነት የተሰበሰቡት መረጃዎች በፌርክላፍ (2006) ሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ማዕቀፍ መሰረት በድስኩራዊ አሃድ፣ በድስኩራዊ ልማድ እና በማህበረ-ባህላዊ ልማድ የትንተና ደረጃዎች ላይ የሙከራ ጥናቱ ተካሂዷል። በዚህ ሂደትም የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ትክክለኛነት ተፈትሾ አስፈላጊ የሆኑ ማሻሻያዎች ተደርጎባቸው በዋናው ጥናት ስራ ላይ ውለዋል።

በዋናው ጥናት ከቅድመ ሙከራ ጥናቱ የተገኘውን ልምድ በማካተት መረጃው ከአሳታፊ ምልከታ፣ ከቡተቃ፣ ከሰነድ ምርመራ፣ ከመስክ ማስታወሻ በተጨማሪ በድምፅወምስል ተቀርፀው የተሰነዱ ድስኩራዊ አሃዶችን በመውሰድ በመረጃ መሰብሰቢያነት ተጠቅሟል። በሁሉም መሳሪያዎች የተገኙት መረጃዎች እርስ በርሳቸው እየተጣቀሱ በሶስቱ የሂሳዊ ዲስኩር ትንተና ማዕቀፎች ደረጃ በደረጃ የተተነተኑ ሲሆን፣ በአጠቃላይ ከትንተናው የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ተጠቃሎ ቀርቧል።

1. ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታ ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር በሚያደርጉት የተግባቦት ሂደት ሀሳባቸውን እንዴት ይገልፃሉ?

በመደበኛ ውይይት ላይ ሴቶችና ወንዶች ሀሳብን በመግለጽ ያላቸው ተሳትፎ ሲታይ አብዛኛዎቹ ወንዶች ሀሳባቸውን በመግለጽ ከፍተኛ ተሳትፎ ያላቸው ሲሆን አብዛኛዎቹ ሴቶች ግን ሀሳባቸውን በመግለጽ አይሳተፉም። ከንግግር ጊዜ አንፃር ደግሞ አብዛኛዎቹ ወንዶች ከውይይቱ አጀንዳ የመጀመሪያ አካባቢ ጀምሮ እስከመጨረሻው ተናጋሪዎች ሲሆኑ፣ ሴቶቹ ግን በአብዛኛው በአጀንዳዎቹ መጨረሻ አካባቢ ሲናገሩ ይታያል። ከዚህም ሌላ በተደጋጋሚ ድርሻ ከመውሰድና ረዥም ንግግር ከማድረግ አንፃር ወንዶቹ ከፍተኛውን

ድርሻ ይይዛሉ። በሌላ በኩል በኢመደበኛ ውይይት ላይ ያለው የተሳትፎ ሁኔታ በተመለከተ ከተሳታፊው ፆታ ቁጥር የበላይነት ጋር የተያያዘ ሲሆን ሴቶች በበዙበት አውድ ሴቶች፤ ወንዶች በበዙበት አውድ ደግሞ ወንዶች ሀሳባቸውን ይገልፃሉ። በዚህ አውድ የሚነሱ ጭብጦችን ስንመለከት ወንዶች አብዛኛውን ጊዜ የሚያነሷቸው ጉዳዮች በተቋሙ ውስጥ ስለሚካሄዱ የተለያዩና ተግባራትንና ጉዳዮችን፣ በአገራቸው ላይ የተካሄዱ ታሪኮችን፣ ስለአገራቸውም ሆነ ስለአለም ወቅታዊ ሁኔታ፣ ስለታዋቂ ሰዎች እና ስለ እግር ኳስ ስፖርት መረጃ በመለዋወጥ፣ ውይይትና ክርክር በማድረግ ላይ ያተኩራል። ከዚህም ሌላ ወንዶች ለመዝናኛነት የሚያነሷቸውን ጭብጦች ስንመለከት ደግሞ አይነኬ የሚባሉ አይነት ሲሆኑ፣ ሌላው ደግሞ ኢመደበኛ ውይይቱ ሴቶች የበዙበት ወይም ሴቶች ብቻ ያሉበት ውይይት ከሆነ አብዛኛውን ጊዜ ቤተሰባዊ፣ ማህበራዊ፣ ግለሰባዊ እና ጓዳዊ በሆኑ ርዕሶችና ችግሮች ላይ እንደሚያተኩሩ የውጤት ትንተናው አመልክቷል። ከዚህ ሌላ አውዱ ወንዶች የበዙበት ከሆነ ጭብጡ የሚወሰነው በወንዶች ሲሆን ሴቶች በአብዛኛው ሀሳብ ከመስጠት ይልቅ አዳማጭ መሆንን ይመርጣሉ።

1.1 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች፣ ሃሳባቸውን አድማጭ በሚረዳው ሁኔታ ባግባቡ እንዴት ይገልፃሉ?

ሃሳባቸውን አድማጭ በሚረዳው ሁኔታ ባግባቡ የመግለፅ ችሎታን ስንመለከት አብዛኛዎቹ ሴቶች በተለይም በመደበኛ ውይይት ላይ ሀሳባቸውን አይገልጹም። ሆኖም ግን በቁጥር አነስተኛ የሆኑ የተለያየ ወይም ከፍተኛ የስራ ልምድ ያላቸው ሴቶች ሀሳባቸውን ከመግለጻቸው በፊት ውይይቱን በጥልቀት በመከታተል መናገር የሚፈልጉትን ጉዳይ በማስታወሻቸው በማስፈር ዝግጅት ያደርጋሉ። አብዛኛዎቹ ወንዶቹ ደግሞ ውይይቱን የሚከታተሉት በማዳመጥ ሲሆን ንግግር ከማድረጋቸው በፊትም ባብዛኛው ማስታወሻ ሲይዙ አይታዩም።

በመደበኛ ውይይት ላይ ንግግር የሚያደርጉ ሴቶች በቁጥር አነስተኛ ቢሆንም ተዘጋጅተው ስለሚናገሩ ሀሳባቸውን ግልጽና አጭር አድርገው የሚያቀርቡ ሲሆን፤ አንዳንድ ወንዶች ደግሞ ከርዕሱ በመውጣት ሀሳቡን የማወሳሰብ ሁኔታ ይታይባቸዋል። አብዛኛዎቹ ሴቶች ደግሞ በሰው ፊት የመናገር ልምዱ ስለሌላቸውና በጉዳዩ ላይ

ያላቸው ቅድመግንዛቤ ዝቅተኛ በመሆኑ ሀሳባቸውን በስብሰባ ላይ በስፋት አይገልጹም። አልፎ አልፎ የመናገሩ አጋጣሚ ሲኖርም ንግግራቸው ያልተሟላና ጥያቄ አዘል የሆኑ አሃዶች ይጠቀማሉ። ከዚህ በተለየ ሁኔታ ግን ሴቶች በበዙበት ኢመደበኛ ውይይት ላይ ሃሳባቸውን በመግለጽና አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ የሆነ የሀሳብ ልውውጥ የሚያደርጉ ሲሆን፤ ባንፃሩ ደግሞ ወንዶች በበዙበት ኢመደበኛ ውይይት ላይ የመደበኛው አይነት ባህርይ ያሳያሉ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ወንዶችም ቢሆኑ ሴቶች በበዙበት ኢመደበኛ ውይይት ላይ ሃሳባቸውን ለመግለጽ የሚቆጠቡ ሲሆን በተቃራኒው ደግሞ ሴቶች በበዙበት መደበኛ ውይይት ላይ ወንዶች ንቁ ተሳታፊ ናቸው።

1.2 ድርሻን ጠብቆ ከመናገር አንፃር እንዴት ይሳተፋሉ?

አብዛኛዎቹ ወንዶች በመደበኛ ውይይት ላይ፣ ሴቶች ደግሞ ሴቶች በበዙበት ኢመደበኛ ውይይት ላይ የንግግር ድርሻን ጠብቆ ከመናገር ይልቅ ጣልቃ ገብነትን ይመርጣሉ። በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በሚደረጉ አጠቃላይ ስብሰባዎች ላይ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በአብዛኛው ድርሻን የሚወስዱት እጅ በማውጣት ሲሆን፤ በእንደዚህ አይነት ስብሰባ ላይ ብዙ ጊዜ ሴቶች ቁጥራቸው አነስተኛ ቢሆንም ለመናገር እጅ አውጥተው ሲጠይቁ ድርሻ ይነፈጋቸዋል። እነዚህ ሴቶች እጅ ከማውጣት ውጭ ድርሻው ሲነፈጋቸው የተለያዩ ስልቶችን ተጠቅመው ጣልቃ ገብተው ለመናገር አይሞክሩም። ወንዶች ድርሻ ለማግኘት በመጀመሪያ ሰብሳቢው በሚያያቸው ፊት ለፊት ቦታ መርጠው በመቀመጥ ድርሻ የሚወስዱ ሲሆን በዚህ ሁኔታ ድርሻ ጠይቀው ሲነፈጋቸው የተለያዩ ብልሃቶችን በመጠቀም ጣልቃ በመግባት፣ ተደርቦ በመናገርና ሀሳባቸውን በወረቀት ጽፈው ለሰብሳቢው በመስጠት ድርሻ ለመውሰድ ይሞክራሉ። የውጤት ትንተናው እንደሚያሳው በተለይ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በሚደረጉ አጠቃላይ ስብሰባዎች በአብዛኛው የሴቶች ሀሳብ ጠቃሚ ነው ተብሎ የማይወሰድ ሲሆን በአብዛኛው ድርሻ የሚሰጣቸውም ለተሳትፎ ሲባል እንደሆነ በጥናቱ ውጤት ተመልክቷል።

ከዚህ በተለየ ደግሞ በትምህርት ክፍልና በፋካሊቲ ደረጃ በሚደረጉ ስብሰባዎች አብዛኛዎቹ ሴቶችና ወንዶች ለመናገር ሲፈልጉ እጃቸውን በማውጣት ድርሻቸውን ጠብቀው ሲናገሩ፤ አንዳንዶች በተለይም በእድሜያቸው፣ በስራ ልምዳቸውና በደረጃቸው ከፍ ያሉት ወንዶች

ደግሞ እጅ ሳያወጡ ጣልቃ በመግባት የንግግር ድርሻ ይወስዳሉ። እንደዚህ አይነት ወንዶች በአብዛኛው ይህን የሚያደርጉት በፋካሊቲና በትምህርት ክፍል ደረጃ በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ ሲሆን በዚህ አውድም ሰብሳቢው ከእነሱ ያነስ የስራ ልምድ ያለው ከሆነ ነው። እጅ አውጥተው ድርሻ የሚጠይቁ ወንዶች ድርሻ ካላገኙ ሀሳቡን ጀምሮ በማቋረጥና ልብ በማንጠልጠል፣ ይቅርታ፣ተጨማሪ፣ ማስተካከያ፣ እዚህ ጋ የመሳሰሉትን ስልቶች በመጠቀም ጣልቃ በመግባት ድርሻ ይወስዳሉ ወይም ይነጥቃሉ።

ከዚህ በተለየ ሁኔታ ግን ሴቶች በኢመደበኛ ውይይት ላይ ድርሻን ጠብቆ በመናገር ረገድ ያላቸው ልምድ ከመደበኛው የተለየ ሆኖ ይታያል። ይኸውም በኢመደበኛ ውይይት በተለይም ሴቶች የበዙበት ከሆነ የንግግር ድርሻ ጠብቀው ከመናገር ይልቅ በመደራረብና ጣልቃ ገብቶ የመናገር ልምድ እንዳላቸው ጥናቱ አመልክቷል።

1.3 በንግግር ያላቸው ተደማጭነት ምን ይመስላል?

ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በንግግር ያላቸውን ተደማጭነት ስንመለከት አጀንዳን በማስያዝ ደረጃም ሆነ የውሳኔ ሃሳብ በማቅረብ ደረጃ ሲታዩ በአብዛኛው የወንዶቹ ተቀባይነት ሲኖረው የሴቶቹ ግን ተቀባይነት አያገኝም። የውጤት ትንተናው እንደሚያሳየው ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ሃሳባቸውን በሚገልጹበት ወቅት ከእነሱ ቀድሞ የተናገረውን ወንድ እከሌ እንዳለው በማለት ሃሳቡን ዋቢ በማድረግ ሲያቀርቡ፣ በተቃራኒው ግን ሴቶቹም ሆኑ ወንድ ተናጋሪዎች እከሌ እንዳለችው ብለው ሴቶችን ዋቢ አድርገው ሲናገሩ አይታይም። ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ሀሳብ በሚያቀርቡበት ጊዜ ድጋፍ ወይም ሀሳባቸውን የሚያረጋግጥላቸው ሰው ሲፈልጉ ስም በመጥራት የሚጠይቁት በስልጣን ከወንድ የምትበልጥ ሴት እንኳ ብትኖርም ወንዱን ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ አንድ ሃሳብ በአንድ ወንድ ቀርቦ ሃሳቡን በማጠናከር ሴቷ ደግማ ስታቀርበው ጉዳዩ ተቀባይነት ሊያጣ የሚችልበት ሁኔታ ይፈጠራል። በመሆኑም የወንዶች ሃሳብ ተቀባይነት ሲኖረው የሴቶቹ ግን በአብዛኛው ትኩረት የሚቸረው አይመስልም።

1.4 በተግባቦት ሂደት የቋንቋ አጠቃቀማቸው ምን ይመስላል?

የቋንቋ አጠቃቀምን በተመለከተ በተለያዩ ውይይቶች ላይ ሀሳባቸውን የሚገልጹ ሴቶችና ወንዶች የሚጠቀሙበትን ቋንቋ ስንመለከት በአብዛኛው ተመሳሳይ ቢሆንም አልፎ አልፎ ግን ስርዓተያታ ተኮር ሆኖ እናገኘዋለን። በመደበኛ ስብሰባዎች ላይ በሚደረጉ ውይይቶች የሴቶች ንግግር በአብዛኛው ትህትና የተላበሰ ሲሆን በዚህም ገለፃቸው በቀጥታ እርግጠኝነትን የማያሳዩ (ይመስለኛል፣ ቢሆን፣ ይሻላል) የሚሉትን ማለዘቢያ ቃላት ይጠቀማሉ። በተጨማሪ በሀሳብ ልውውጥ ሂደት የተብራራና የተሟላ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ በአብዛኛው ጭንቅላታቸውን በመነቅነቅ ‹‹እህ›› አልፎ አልፎ ደግሞ ‹‹እሽ›› የሚሉ ቃላትን በተደጋጋሚ በመጠቀም አዎንታዊነቱን ወይም አሉታዊነቱን የማይገልጽ ምላሽ ይሰጣሉ። በዚህ የቋንቋ አጠቀቃቀማቸው ‹‹እህ›› የሚለውን ምላሽ የሚጠቀሙት አዎንታዊ ምላሽ ለመስጠት ሳይሆን ተናጋሪው ንግግሩን እንዲቀጥል እያዳመጡት እንደሆነ የጥናቱ ውጤት ያሳያል። ክትትሉ ደግሞ በመጨረሻ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ምላሽ ስለሌለው ተናጋሪው ትክክል እንደሆነና እንዲቀጥል ለማድረግ የተጠቀሙበት መሆኑን የሚያሳይ ነገር የለም። ይህ ደግሞ በቡተቃ የተገኘው መረጃ ሴቶች ሃሳባቸውን ሌሎች በሚረዱት መንገድ በቀጥታ ያቀርባሉ ከሚለው ጋር የሚጣረስ ሆኖተገኝቷል።

ከዚህ በተጨማሪም ማብራሪያ ለመስጠት በሚፈልጉበት ጊዜ ደግሞ ሀተታዊ ዓረፍተነገር ከመጠቀም ይልቅ (ነው እንዴ? አይደል? አይደለም ወይ?) የሚሉትን ጥያቄያዊ ዓረፍተነገሮች ይጠቀማሉ። ይህም የሚያውቁትን ጉዳይ ‹‹ነው፣ እንደዚህ አይደለም›› ብሎ በእርግጠኝነት ድምዳሜ ከመስጠት ይልቅ በተዘዋዋሪ መንገድ ለመግለጽ የተጠቀሙበት ስልት እንደሆነ ያሳያል። ባንፃሩ ደግሞ የአብዛኛዎቹ ወንዶች ንግግር ወደ አፅንዖታዊና ድምፀታዊ አገላለፅ የሚያደላ ሲሆን ‹‹ነው፣ ግድ ነው፣ አይደለም፣ አይሆንም›› የሚሉ ቃላትን በመጠቀም ሀሳባቸውን በእርግጠኝነትና ሀይል በተላበሰ ሁኔታ ያቀርባሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ ጥቂት ወንዶች በተለይም በእድሜና በስራ ልምድ ከፍ ያሉት ጣልቃ በመግባት ድርሻን በመውሰድ የሃይል የበላይነትን የሚያሳዩ ቢሆንም፣ ሀሳባቸውን በሚያቀርቡበት ጊዜ ግን ይሻላል፣ ይመስለኛል፣ ቢሆን የሚሉትን ቃላት በመጠቀም ትህትና የተላበሰ ንግግር ከማድረጋቸውም በላይ የሚያቀርቡት ሀሳብ በውይይቱ

የተፈጠረውን ችግር በመፍታት ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ አገላለጹ ግን በጉዳዩ ላይ ሙሉ እምነት አለመኖሩንም የውጤት ትንተናው ያስረዳል።

ንግግራዊ አውድን በተመለከተ በአብዛኛው ሴቶቹ የሚጠቀሙት የንግግር ስልት ‹‹እኛ›› እያሉ ነው። የወንዶቹን በተመለከተ ደግሞ አብዛኛዎቹ ግላዊ ሀሳባቸውን ለማቅረብ አንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ‹‹እኔ›› የሚለውን ተውላጠ ስም በመጠቀም ጉዳዩን ከራሳቸው አንፃር ያቀርባሉ። አንዳንዶቹ ከአንደኛ መደብ ነጣላ ቁጥር ‹‹እኔ›› ወደ አንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር ‹‹እኛ››፤ እና በተቃራኒው ከእኛ ወደ እኔ በመቀላቀል ሲጠቀሙበት ይታያል። በሌላ በኩል ሴቶች በስራ ልምዳቸው ከፍ እያሉ ሲሄዱ ‹‹እኔ›› የሚለውን ተውላጠ ስም በመጠቀም ስለራሳቸው እንደሚገልጹና ይህም በራስ የመተማመን ውጤት እንደሆነ የውጤት ትንተናው ያረጋገጠ ቢሆንም በቡተቃ ሴቶች ስለራሳቸው እንደማይናገሩ ከተገኘው መረጃ ጋር በተወሰነ ደረጃ የሚቃረን ሆኖ ይታያል።

ምፀታዊ አገላለጽ በአብዛኛው በመደበኛ ውይይት ላይ ተዘውታሪ እንዳልሆነና አልፎ አልፎ አንዳንድ ወንዶች አሉታዊ ሀሳብን ለማቅረብ ይጠቀሙበታል። የአጠቃቀሙ አላማም አሉታዊ ሃሳብ የያዘን ጉዳይ በቀጥታ ከማቅረብ ይልቅ በተዘዋዋሪ ለማቅረብ እንደሆነ የውጤት ትንተናው አመልክቷል። ከዚህ በተለየ ሁኔታ ግን ሴቶች በበዙበት ኢመደበኛ ውይይት ላይ ሴቶች ምፀታዊ አገላለፅን በስፋት እንደሚጠቀሙ የውጤት ትንተናው አሳይቷል።

አፅንዖታዊ አገላለጽን ስንመለከት በአብዛኛው ወንዶች (አራት ነጥብ፣ ሌላ ነገር የለውም፣ አንችልም፣ አይደለም፣ ለምንድን ነው፣ ግድ ነው) የመሳሰሉትን ሀይል ያላቸውን አፅኖታዊ አጠቃቀሞች በመጠቀም ያመኑበትን በፅናት ከመግለጻቸው በተጨማሪም በአጠቃቀማቸው የበላይነት የሚንፀባረቅበት እንደሆነ የውጤት ትንተናው ያመላክታል። በሌላ መልኩ ደግሞ ሴቶችና አንዳንድ ከፍተኛ የስራ ልምድ ያላቸው ወንዶች አፅንዖታዊ አቀራረባቸው የተለሳለሰ ሲሆን፣ የአፅንኦታዊ አጠቃቀማቸው ምክንያት ደግሞ ችግርን በሰላማዊ ሁኔታ ለመቅረፍ እንደሆነ የውጤት ትንተናው አሳይቷል።

አብዛኛዎቹ ወጣት ወንዶች ሀሳባቸውን በንግግር በሚገልጹበት ጊዜ ድምፀታዊ ቃላትን (ምንም ጥርጥር የለውም፣ ምናልባት፣ ለወደፊት፣ የግድ) የተሰኙትን አገላለጾች በመጠቀም ሀሳባቸውን ሀይል በተሞላበት ሁኔታ ሲገልፁ ይስተዋላል። ሴቶቹና በእድሜያቸውም ሆነ በስራ ልምዳቸው ከፍ ያሉት ወንዶች ግን በአብዛኛው ድምፀታዊ ቃላትን ሲጠቀሙ አይታዩም።

ስነምግባራዊ አቀራረብን በተመለከተ እንደ (ቢሆን፣ አይሻልም፣ ይቅርታ፣ እንግዲህ፣ ቢኖር ይሻላል፣ ሊኖር ይችላል፣ እንዲህ ብናደርግ) የሚሉት ስነምግባራዊ አጠቃቀሞች በሴቶችም ሆነ በወንዶች የሚታይ ሲሆን፤ የወንዶቹን ስንመለከት ግን የትህትና ማላበሻ የሆኑ ቃላትን በመጠቀም ሀሳባቸውን የሚያቀርቡ በእድሜና በስራ ልምዳቸው ከፍ ያሉት ወንዶች ናቸው። የአጠቃቀማቸውን ምክንያት ስንመለከት ደግሞ ውይይቱ ወደመልካም አቅጣጫ እንዲሄድና ችግሩ በውይይት እንዲፈታ ለማድረግ የሚጠቀሙበት ስልት ይመስላል።

ሌላው ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ተጨማሪ ሃሳብ ለማቅረብ ሲፈልጉ (በተጨማሪም፣ እና)፣ አማራጭን ለማሳየትና ውሳኔን ወይም ሃሳብን ለማጠቃለል (እና)፣ የሌላ ሰው ሃሳብን ለመቃወም (ግን፣ ነገር ግን፣ ቢሆንም) የሚሉትን የመሸጋገሪያ ቃላት በተመሳሳይ እንደሚጠቀሙ በውጤት ትንተናው ተመልክቷል።

1.5 በተግባቦት ሂደት የሚያሳዩት ድስኩራዊ ልማድ ምን ይመስላል?

ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በተግባቦት ሂደት የሚያሳዩት ድስኩራዊ ልማድን በተመለከተ በመደበኛ ውይይት ወቅት አብዛኛዎቹ ወንዶች ተራቸውን ሳይጠብቁ ድርሻ የመንጠቅ፣ የጣልቃ ገብነትና ተደርቦ የመናገር ድስኩራዊ ልማድ እንዳላቸውና ይህንም ለመፈፀም ማሳሰቢያ፣ ማስተካከያ፣ ተጨማሪ፣ ይቅርታ፣ የመሳሰሉትን ብልሃቶችን ይጠቀማሉ። ባንፃሩ ደግሞ አብዛኛዎቹ ሴቶች ተራን ጠብቆ የመናገር ልምድ ያላቸው ሲሆን፣ አንዳንድ የተሻለ የስራ ልምድ ያላቸው ሴቶች ግን ብዙ ጊዜ ባይሆንም ድርሻ ካልተሰጣቸው ጣልቃ በመግባት ድርሻ እንደሚቀሙ በቡተቃ ላይ የገለጹ ቢሆንም በምልከታ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ግን በመደበኛ ውይይት ላይ ጣልቃ በመግባት የንግግር ድርሻ ሲነጥቁ አልታዩም። ይህም ቀደም ብሎ እንደተገለፀው ጣልቃ ገብነትን የሚፈጽሙት ከስንት አንድ

ጊዜ በመሆኑ ነው። የወንዶች ጣልቃ ገብነትን ስንመለከት ሁለት መልክ አለው። አንደኛው ድርሻ ጠይቀው ሲከለከሉ ድርሻን በሀይል ለመውሰድ ሲሆን፤ ሁለተኛው ግን በእድሜ፣ በትምህርት ደረጃና በተለያዩ ዶሃላፊነት ቦታዎች ያገለገሉ ወንዶች በተለይም በትምህርት ክፍልና በፋካሊቲ ደረጃ በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ የንግግር ድርሻን እጅ በማውጣት መውሰድ እንደማይፈልጉና ይልቁንም ጣልቃ በመግባት የንግግር ድርሻ የመውሰድ ልምድ እንዳላቸው በጥናቱ ታይቷል። ይህም በሰብሳቢውና በተናጋሪው እንዲሁም በተናጋሪውና በአድማጮች መካከል ያለውን የሀይል ግንኙነት የሚያመለክት እንደሆነ የውጤት ትንተናው ያስረዳል።

በሌላ በኩል ደግሞ ሴቶች በበዙበት ኢመደበኛ ውይይት ላይ ሴቶች ተራን ያለመጠበቅ፣ የንግግር ድርሻን ብቻ ሳይሆን የውይይት ርዕሰ ጉዳይንም የመንጠቅ፣ ተደራርቦ የመናገር፣ የሳንዮሽ ወሬና ያለመደማመጥ ልማድ ታይቷል። በተቃራኒው ሴቶች በበዙበት ኢመደበኛ አወድ ደግሞ ወንዶች የጣልቃ ገብነትም ሆነ ሀሳባቸውን በመግለጽ በኩል ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ እንደሆነና በእንደዚህ አይነት አውድ የመናገር ፍላጎት እንደሌላቸውና እንደሚፈሩም በውጤት ትንተናው ታይቷል።

መድረክን ተጠቅመው ሀሳባቸውን የሚገልጹት ሴቶችም ሆኑ ወንዶች መድረኩን በመቆጣጠር ድርሻቸውን የሚወጡ ቢሆንም፣ አንዳንዶች ግን መድረክ የመቆጣጠር ችግር ይታይባቸዋል። የችግሩ መንስዔ ግን ስርዓተ ፆታዊ ልዩነት ያለው ሲሆን ይህም ሴቶች ከመድረኩ እንዲመልሱ ወይም እንዲያብራሩ ለሚጠየቁት ጉዳይ ተገቢውን ምላሽ ወይም ማብራሪያ መስጠት ሲገባቸው መናገር ባለመፈለጋቸው፤ ወንዶች ደግሞ ከአጀንዳ በመውጣትና የአድማጭን ስሜት መሰረት አድርጎ ባለመናገር የሚፈጠር እንደሆነ የውጤት ትንተናው ያሳያል።

በውይይት ሂደት ርዕስን ጠብቆ ከመናገር አንፃር የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ርዕስ ያለመጠበቅ ሁኔታ ይታይባቸዋል። ሆኖም ግን ርዕስ የማይጠብቁበት ምክንያት ሲታይ ወንዶቹ ማለት የሚፈልጉት ጉዳይ ተገቢውን ምለሽ አላገኘም ብለው ሲያስቡ እና የራሳቸውን ማንነት ማለትም የትምህርት፣ የእውቀትና የስራ ልምዳቸውን ለማስተዋወቅ ሲፈልጉ ከውይይቱ ርዕስ (አጀንዳ) ይወጣሉ። ሴቶቹ ደግሞ

መጀመሪያ በቀረበው አጀንዳ ላይ ለመናገር ድርሻ ባለማግኘታቸው ምክንያት በመጨረሻ ድርሻ ሲያገኙ ከአጀንዳው በመውጣት ወደኋላ በመሄድ ስላለፈው ርዕሰጉዳይ በመናገር ዲስኩርን ወኋላ የመመለስና ከውይይት አጀንዳ የመውጣት ባህርይ እንዳላቸው የውጤት ትንተናው ያሳያል። ይህም ሴቶች በተገቢው ጊዜ የንግግር ድርሻ የሚሰጣቸው ከሆነ የውይይቱን አጀንዳ ጠብቆ በመናገር ረገድ ከወንዶች የተሻሉ እንደሆኑ ይጠቁማል።

ሌላው የውጤት ትንተናው እንደሚያመለክተው አጀንዳን ማቅረብና ማስተዋወቅ የሰብሳቢው ድርሻ ሲሆን፣ ተጨማሪ አጀንዳና የመወያያ ጉዳይ ሁለቱም ፆታዎች በማቅረብ ይሳተፋሉ። ሆኖም ግን አንዳንድ ጊዜ በሴቶች የሚቀርቡ ርዕሰ ጉዳዮችና ሀሳቦች ተቀባይነት የላቸውም። ይህም አንድም የሚያቀርቡበት መንገድ አለያም ደግሞ የሚያቀርቡት ሃሳብ ጠንካራ ባለመሆኑ ሊሆን ይችላል።

2. ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታ ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር በሚያደርጉት የተግባቦት ሂደት ራሳቸውን እንዴት ይገልፃሉ?

2.1 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች የሙያ ብቃታቸውን ለመግለፅ የሚያደርጉት ጥረት ምን ይመስላል?

በተግባቦት ሂደት ራስን የመግለፅ ሁኔታ ሁለቱም ፆታዎች በስራ ቦታቸው ላይ ያላቸውን የሙያ ብቃት በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ በሚደረጉ ውይይቶች ላይ ከመግለፅ አንፃር ከፍተኛ ልዩነት እንዳለ የውጤት ትንተናው ያሳያል። ይኸውም ወንዶች በሙያቸው ምን እንደሰሩ፣ ምን እየሰሩ እንደሆነ፣ ምን ውጤት/ለውጥ እንዳገኙ በውይይቱ በሚነሱ አጀንዳዎች ላይ በመጨመር ሲገልጹ ይታያሉ። አብዛኛዎቹ ሴቶች ግን በዋናነት ከአጀንዳው ጋር የተያያዘ ሃሳብ በቀጥታ ከመናገር አልፈው ስለራሳቸውም ሆነ ስለሙያ ብቃታቸው ምንም አይነት ገለፃ ሲያደርጉ አይስተዋሉም። አልፎ አልፎ አንዳንድ ሴቶች የሙያ ብቃታቸውን ሲገልጹ ይታያሉ። እነሱም ከፍተኛ የስራ ልምድ ያላቸውና ከማስተማር በተጨማሪ ለተለያዩ የስራ ሁኔታዎች ተጋላጭ የሆኑ ናቸው። የውጤት ትንተናው እንደሚያሳየው ስለራሳቸው ለመግለፅ ምንም ፍርሃት አለማሳየታቸው ብቻ ሳይሆን ስለራስ መናገር በባህሉ ያልተለመደውን ነገር በቀጥታም ባይሆን የመስበር ሁኔታ አሳይተዋል።

ADAMA UNIVERSITY
LIBRARIES
P.O. BOX 1888
ADAMA

2.2 በስራ ቦታቸው ላይ ያላቸውን ድርሻ እንዴት ይገልፃሉ?

ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በስራ ቦታቸው ላይ ያላቸውን ድርሻ የመግለፅ ልምድ በተመለከተ አብዛኛዎቹ ወንዶች በስራ ቦታቸው ያላቸውን ድርሻ/ሃላፊነት ለመግለጽ አጋጣሚዎችን የሚጠቀሙ ሲሆን አብዛኛዎቹ ሴቶች ግን ስለራሳቸው የተለያዩ መድረኮችን በመጠቀም ሲገልጹ አይስተዋልም። አብዛኛዎቹ ወንዶች በስራ ቦታቸው (በዩኒቨርሲቲው) ምን እንደሚሰሩ፣ ምን አይነት ሃላፊነት እንዳላቸው ወይም ከአሁን በፊት ምን እንደሰሩና ምን አይነት ስልጣን እንደነበራቸውና በዚህም ያስገኙት ውጤት ምን እንደሆነ ‹‹እኔ›› በማለት ስለራሳቸው ይገልፃሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ከአንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ወደ አንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር በመሄድ፣ መጀመሪያ ጉዳዩን የግላቸው በማድረግ ስላራሰቸው ከገለጹ በኋላ መልሰው ደግሞ ጉዳዩን የጋራ በማድረግ የሚያቀርቡበት ስልት ታይቷል። አንዳንዶች ደግሞ በተቃራኒው በመጀመሪያ ጉዳዩን የወል በማድረግ (እኛ) በማለት ካቀረቡ በኋላ መልሰው ጉዳዩን የራሳቸው በማድረግ (እኔ) እያሉ የሚያቀርቡበት ሁኔታ ይታያል። በሁለቱም መንገድ ሲታይ ግን ወንዶች ራሳቸውን ለመግለጽ አጋጣሚዎችን በማመቻቸት እንደሚጠቀሙ ያመለክታል።

2.3 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በተግባቦት ሂደት ሃሳባቸውንና ማንነታቸውን ለመግለጽ ተፅዕኖ አድራጊ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?

በተግባቦት ሂደት ሀሳብን በመግለፅ ደረጃ አብዛኛዎቹ ወንዶች ያለምንም ተፅዕኖ ሀሳባቸውን በነፃነት የሚገልጹ ሲሆን፤ በአንፃሩ ሴቶች በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ ሃሳባቸውን መግለፅ እየፈለጉ ሳይናገሩ የሚወጡባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው። በአጠቃላይ ሀሳባቸውን እንዳይገልጹ ከሚያደረጓቸውን ጉዳዮች መካከል ፍርሃት፣ ድርሻ አለማግኘት፣ በጉዳዩ ላይ ቅድመ ግንዛቤ አለመኖር፣ የወንዶች በንግግር የበላይ መሆንና የስብሰባው አውድ ምቹ አለመሆን አንደሆኑ የውጤት ትንተናው ያስረዳል።

ከዚህም ሌላ ሴቶች በስራ ቦታ ያላቸውን ድርሻም ሆነ በአጠቃላይ ስለራሳቸው የተለያዩ መድረኮችን በመጠቀም ሲገልጹ አይስተዋልም፡፡ የውጤት ትንተናው እንደሚያሳየው ድርሻ ወስደው የሚናገሩ አብዛኛዎቹ ሴቶች የቀረበውን አጀንዳ የሚመለከት ሀሳብ በቀጥታ ከማቅረብ ውጭ ስለራሳቸው (እኔ) ብለው አይናገሩም፡፡ በአብዛኛው ንግግራቸው የሚያተኩረው ጉዳዩን የወል በማድረግ መግለፅ ላይ ነው፡፡ በእርግጥ አንዳንድ ወጣ ያሉና ከቁጥር የማይገቡ ከፍተኛ የስራ ልምድ ያላቸው እንዲሁም በስብሰባ ላይ መናገር ራስን በማስተዋወቅ ረገድ ጠቀሜታ እንዳለው ግንዛቤ ያገኙ ሴቶች እኔ በማለት የነበራቸውን ሃላፊነትና የሰሩትን ስራ በድፍረት ይናገራሉ፡፡ ሆኖም ግን ትህትና፣ ማህበረሰባዊ ባህል፣ ተቋማዊ ባህል፣ ለተለያዩ የስራ ሁኔታዎች አለመጋለጥና ቅድመ ግንዛቤ አለመኖር በሴቶችም ሆነ በወንዶች ተግባቦት ሂደት ሀሳባቸውንና ማንነታቸውን ለመግለጽ ተፅዕኖ አድራጊ ጉዳዮች ናቸው፡፡

ትህትናን በተመለከተ በወንዶችም ሆነ በሴቶች ላይ ተፅዕኖ የሚያደርግ ቢሆንም፣ በሴቶች ላይ ግን ስር የሰደደ ችግር ከመሆኑም በላይ ሴቶች ራሳቸው ስለራስ መናገር በሰዎች ላይ ሀይልን እንደመጫን እንደሆነ አድርገው እንደሚመለከቱት በቡተቃ ላይ የተመለከተ ቢሆንም በምልከታ በተወሰደው መረጃ ደግሞ አልፎ አልፎ ከፍተኛ የስራ ልምድ ያላቸውና ስለራስ መናገር ጠቃሚ እንደሆነ ቅድመ ግንዛቤ ያላቸው ሴቶች ‹‹እኔ›› እያሉ ሲናገሩ ከታየው ጋር መጠነኛ የሆነ መጣረስ ይታያል፡፡

በኢትዮጵያ የሚታየው ማህበረሰባዊ ባህል የወንድ የበላይነት የነገሰበት ሲሆን፣ ይህም መነሻው ቤተሰብ መድረሻው ማህበረሰብ ነው፡፡ በዚህም ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ማህበረሰቡ በተቀበለው ልማዳዊ ስርዓት ተኮትኩትው የሚያድጉ በመሆኑ እንደየታቸው ልዩነት በተለያየ ሁኔታ ስለሚያድጉና የተለያየ ማህበራዊ ልምድ ስለሚኖራቸው በተግባቦት ሂደት የተለያየ ባህርይ ያሳያሉ፡፡ በዚህ ጥናት እንደታየውም በተለይም በመደበኛ ውይይቶች ላይ በስራ ልምዳቸው ከፍ ያሉትም ሆነ ዝቅተኛ የስራ ልምድ ያላቸው ወንዶች ሀሳባቸውን የሚገልጹ ሲሆን በሁሉም ውይይቶች ላይ ካልተናገሩት ሴቶች ዝቅተኛ የስራ ልምድ ያላቸው ወንዶች ሃሳባቸውን ሲገልጹና ድርሻ ሲነጥቁ ሴቶቹ ግን ሀሳባቸውን ለመግለጽ አልሞከሩም፡፡ ይህም ወንዶቹ ከልጅነታቸው ጀምረው የመናገር ልምድ ያላቸው እንደሆነና ሴቶች ግን መናገር ለእነሱ የተሰጠ ድርሻ እንዳልሆነ በተማሩ ሴቶች ላይም የማህበረሰቡ ባህል ተፅዕኖ እንዳለው የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡

የጥናቱ ውጤት እንደሚያስረዳው የማህበረሰቡ ባህል በተቋሙ ባህል ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያለው ይመስላል። ይኸውም አንዳንድ ሴቶች በቤተሰባዊ አስተዳደግም ሆነ ከዩኒቨርሲቲው ውጭ በሰሩባቸው የስራ ቦታዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ የንግግር ተሳትፎ እንደነበራቸውና ራሳቸውን እየገለጹ የመጡ ቢሆንም በዩኒቨርሲቲው በሚደረጉ ውይይቶች ላይ ሀሳብ በሚሰጡ ሰዎች ላይ የሚሰነዘሩ ሀሳቦች እኔስ ምን እባላለሁ በሚል ይሉኝታ እንዳይናገሩ ከፍተኛ ተፅዕኖ አድርጎባቸዋል። ሌላው ‹‹የሴቶች ተሳትፎ›› ከሚለው ማህበረ-ፖለቲካዊ መርህ አንፃር በተቋሙ በሚደረጉ ውይይቶች ላይ ለሴቶች የሚሰጠው የንግግር ድርሻ ለተሳትፎ እንጅ ሀሳባቸው ጠቃሚ ነው የሚል እምነት ኖሮ እንዳልሆነና በዚህም ሃሳባቸውን ከመግለጽ እንደሚቆጠቡና ተስፋ የመቁረጥ ስሜትም እንዳለ ጥናቱ አሳይቷል።

በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ሃላፊነቶችን ለማግኘት ራሱን የቻለ መመሪያና አካሄድ አለው። ሆኖም ግን አብዛኛዎቹ የሃላፊነት ቦታዎች የሚሰጡት ሰዎች በተለያየ መድረክ በሚያሳዩት ተሳትፎ ተናጋሪነታቸውን መሰረት በማድረግ እንደሆነ ከቡተቃ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። በዚህም መሰረት ለተቋሙ ባህል ቅድመግንዛቤ ያላቸው አብዛኛዎቹ ወንዶች ‹‹ካለማናገር ደጃዝማችነት ይቀራል›› የሚለውን የማህበረሰቡን ብሂል በመጠቀም የሚያገኙትን መድረክ በመጠቀም መናገር የሚፈልጉትን ሀሳብ ብቻ ሰይሆን ራሳቸውንም በመግለፅ በንግግራቸው የሚፈልጉትን መልዕክት ያስተላልፋሉ። አብዛኛዎቹ ሴቶች ደግሞ በሚሰሩት ስራ መሰረት አብረዋቸው በሚሰሩ ጓደኞቻቸው አማካኝነት እንዲገለጹና በዚህም የሚገባቸው ቦታ ይሰጠናል የሚል እምነት እንዳላቸው ከቡተቃ የተገኘው መረጃ ያሳያል። ይህም የተቋሙን ባህል አለመረዳታቸውንና በዚህም የሚገባቸውን እንዳያገኙ ተፅዕኖ ሊፈጥር እንደሚችል ይጠቁማል።

በዩኒቨርሲቲው በሚገኙ በተለያዩ ስራዎች፣ ኮሚቴዎች፣ ስብሰባዎች ወዘተ ላይ ተሳታፊ ከመሆን አንፃር ወንዶች የተሻሉ ሲሆኑ ሴቶቹ ግን ተሳትፏቸው ዝቅተኛ ነው። በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ሆነ በፋካሊቲ ደረጃ ባሉ የሃላፊነት ቦታዎች የሴቶች ተሳትፎ ዝቅተኛ ነው። ሆኖም ግን በፋካሊቲዎቹ ያሉ ሴቶችን ስንመለከት በተለይም በማህበራዊ ሳይንስ ፋካሊቲዎች ውስጥ ብዙ ሴቶች የሚገኙ ሲሆን በአብዛኛዎቹ ፋካሊቲዎች የአካዳሚክ ኮሚሽን አባላት እንኳ አይደሉም። ይህም ሴቶች በዩኒቨርሲቲው በተለያየ የስራ ሁኔታ

ባለመጋለጣቸው ምክንያት በራስ የመተማመን ችሎታቸው ከፍ እንዳይል፣ በስራ ቦታቸው ስለሚከናወኑ ጉዳዮች ቅድመግንዛቤ እንዳይኖራቸውና በዚህም ሀሳባቸውን በተሻለና በነፃነት የመግለፅ ችሎታው እንዳይኖራቸው ተፅዕኖ ያደረገባቸው ይመስላል።

በዩኒቨርሲቲው ውስጥ መደበኛ በሆነው ስራም ሆነ ማህበራዊ እንቅስቃሴን በተመለከተ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ከተቃራኒ ፆታ ጋር ያላቸው ግንኙነት ውሱን ነው። ይህ ደግሞ በሁለቱም በኩል መረጃንም ሆነ ልምድን ከመለዋወጥ አንፃር ተፅዕኖ ያለው ሲሆን፣ ወንዶች ለተለያዩ ስራዎችና ሁኔታዎች ተጋላጭ በመሆናቸው ስለተለያዩ የስራ ሁኔታዎች ያላቸውን መረጃ ለማስተላለፍ ከሴቶች ጋር ያላቸው መስተጋብር አነስተኛ በመሆኑ ሴቶች መረጃን በማግኘት በኩል ምቹ ሁኔታ እንደሌለ ያሳያል። በሌላ በኩል ደግሞ ሴቶች በተለያየ ሁኔታ ለሚፈጠሩ ችግሮች መፍትሄ የማግኘት ችሎታቸው ከፍተኛ እንደሆነ በቡተቃ የተገለፀ ሲሆን፣ ይህም ሴቶችና ወንዶች ወደተቋሙ ይዘውት የሚመጡት የተለያየ ልምድና ችሎታ እንዳለ ይጠቁማል።

አብዛኛዎቹ ወንዶች በተለያዩ መድረኮች ላይ ስለሚደረጉ ትምህርታዊ ውይይቶች ቅድመግንዛቤ ያላቸው ሲሆን ሴቶች ግን የላቸውም። ስለውይይቱ አጀንዳ ብቻ ሳይሆን በስብሰባ ላይ በመናገር ያለውን አዎንታዊ ተፅዕኖ ወንዶች ቀድመው የተረዱ ሲሆን ሴቶች ግን ብዙም ግንዛቤው የላቸውም። ይህም ልዩነት የተፈጠረው ወንዶች ለተለያዩ የስራ ሁኔታዎች በመጋለጣቸው ያገኙት ልምድ ሲሆን ሴቶች ደግሞ በተቃራኒው ለተለያዩ የስራ ሁኔታዎች ባለመጋለጣቸው ያካበቱት ልምድ አናሳ በመሆኑ ለነገሮች ያላቸው ቅድመ ግንዛቤም ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጓል።

5.2 መደምደሚያ

የጥናቱ ዋና ኣላማ በከፍተኛ ትምህርት ተቋም በስራ ቦታ ላይ የሚታየውን ስርዓተፆታዊ የተግባቦት ስልት ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነበር። በጥናቱ በተገኘው ውጤት መሰረትም ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታ ከአቻዎቻቸው ጋር በሚያደርጉት ተግባቦት ሂደት በተለይም በመደበኛ ውይይት ላይ ወንዶች ሀሳባቸውን በመግለጽ ከፍተኛ ተሳትፎ ያላቸው ሲሆን ሴቶች ግን የላቸውም። ከንግግር ጊዜ አንፃር ደግሞ ወንዶች ከውይይቱ አጀንዳ የመጀመሪያ አካባቢ ጀምሮ እስከመጨረሻው አብዛኛዎቹ ወንዶች ተናጋሪዎች ሲሆኑ፤ ሴቶቹ ግን በአብዛኛው በአጀንዳዎቹ መጨረሻ አካባቢ ሲናገሩ ይታያል። ከዚህም ሌላ በተደጋጋሚ ድርሻ ከመውሰድና ረዥም ንግግር ከማድረግ አንፃር ወንዶቹ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ። ይህም ወንዶች ተደጋጋሚና ሰፊ የንግግር ድርሻ ማግኘታቸውና የሴቶቹ ተሳትፎ ደግሞ አናሳ መሆኑ በተቋሙ ያለው የሃይል ግንኙነት ከስርዓተፆታ አንፃር ሲታይ አቻዊ እንዳልሆነና የወንዶች የበላይነት እንዳለ ያመለክታል። በመሆኑም የቀረበውን የውጤት ትንተናና ማብራሪያ መነሻ በማድረግ የጥናቱ መደምደሚያ እንደሚከተለው ቀርቧል።

1. ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታ ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር በሚያደርጉት የተግባቦት ሂደት ሀሳባቸውን እንዴት ይገልፃሉ?

በጥናቱ ውጤት መሰረት አብዛኛዎቹ ሴቶች በመደበኛ ውይይት ላይ በሚያደርጉት ተግባቦታዊ ሂደት ሀሳባቸውን በስፋት ሲገልጹ አይታዩም። አልፎ አልፎ በሚገልጹበት ጊዜ ደግሞ ንግግራቸው የተበጣጠሰ፣ ያልተሟላ፣ ጥያቄ አዘልና በይመስለኛልና በይሆናል የታጀበ ሲሆን፣ በዚህም ማስተላለፍ የፈለጉትን ሃሳብ በትክክል ሳያስተላልፉ ይቀራሉ። ይህ ውጤት ከቡተቃ በተገኘው መረጃ ጋር ሲታይ ሴቶች አይናገሩም እንጂ ከተናገሩ ጥሩ ተናጋሪዎች እንደሆኑ ከተገኘው ውጤት ጋር ልዩነት ያለው ቢሆንም፣ ከቁጥር ከማይገቡትና በስራ ልምዳቸው ከፍ ካሉት ሴት ተናጋሪዎች ጋር ግን ተደጋጋፊነት አለው። ሌላው ሴቶች በበዙበት ኢመደበኛ ውይይት ላይ ሴቶች ሃሳባቸውን በመግለጽና አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ የሆነ የሀሳብ ልውውጥ በማድረግ ከፍተኛ ተሳትፎ ያላቸው ሲሆን፤ በዚህ አውድ ወንዶች ደግሞ ሃሳባቸውን ከመግለጽ ይቆጠባሉ። ከዚህ በተለየ ሁኔታ ደግሞ

ሴቶች በበዙበት መደበኛ ውይይት ላይ ወንዶች ንቁ ተሳታፊና ሀሳባቸውን የሚገልጹ ሲሆን ሴቶች ግን ሃሳባቸውን አይገልጹም። ይህም ከፆታ የበላይነት ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ ሴቶች ኢመደበኛ እና የሴቶች ቁጥር የበዛበት ወይም ሴቶች ብቻ ያሉበት የውይይት አውድ ይመቻቸዋል ማለት ነው።

1.1 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች፣ ሃሳባቸውን አድማጭ በሚረዳው ሁኔታ ባግባቡ እንዴት ይገልፃሉ?

በቁጥር አነስተኛ የሆኑ የተለያየና ከፍተኛ የስራ ልምድ ያላቸው ሴቶች ከመናገራቸው በፊት ሃሳበቸውን በማስታወሻ በማስፈር፣ የውይይቱን ዓላማ መሰረት አድርገው በጥንቃቄ ሀሳባቸውን አድማጭ በሚረዳው መንገድ እንደሚያቀርቡ የጥናቱ ውጤት ያመለክታል።። በሌላ በኩል አብዛኛዎቹ ወንዶች ሃሳባቸውን አድማጭ በሚረዳው መልኩ የሚያቀርቡ ቢሆንም ጥቂት የማይባሉ ወንዶች ሰፊ የንግግር ጊዜ በመውሰድ፣ ከውይይቱ ዓላማ ውጭ የሆነ ሃሳብ በማቅረብ፣ የተለያዩ ጉዳዮችን በአንድ ላይ በማወሳሰብ ሀሳባቸውን አድማጭ በሚረዳው መንገድ እንደማያቀርቡና አድማጭንም እንሚያሰለቹ የጥናቱ ውጤት ያመለክታል።

1.2 ድርሻን ጠብቆ ከመናገር አንፃር እንዴት ይሳተፋሉ?

በጥናቱ ውጤት መሰረት ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በዩኒቨርሰቲ ደረጃ በሚደረጉ ውይይቶች ላይ የንግግር ድርሻን የሚወስዱት እጅ በማውጣት ነው። ይሁን እንጅ በእንደዚህ አይነት ስብሰባዎች ላይ ለመናገር እጅ በማውጣት ድርሻ የሚጠይቁ አንዳንድ ሴቶች ቢኖሩም አብዛኛውን ጊዜ ድርሻው ሲነፈጋቸው ይታያል። በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኛዎቹ ወንዶች በፋካሊቲና በትምህርት ክፍል ደረጃ በሚደረጉ መደበኛ ውይይቶች ላይ፣ ሴቶች ደግሞ ሴቶች በበዙበት ኢመደበኛ ውይይት ላይ የንግግር ድርሻን ጠብቆ ከመናገር ይልቅ በሌላ ተናጋሪ ላይ በመደረብና ጣልቃ ገብነትንና በመጠቀም ድርሻ ይነጥቃሉ። በመደበኛ ውይይት ላይ ወንዶች ድርሻ ጠይቀው ሲነፈጋቸው ድርሻ የሚነጥቁበት ስልት አላቸው።ይኸውም ሀሳቡን ጀምሮ በማቋረጥና ልብ በማንጠልጠል፣ እዚህ ጋ፣ ይቅርታ፣ ማስተካከያ የሚሉትን ድስኩራዊ ቃላት በመጠቀም ጣልቃ በመግባት፣ ተደርቦ በመናገር

እና ይህ ካልተሳካለቸው ደግሞ ሀሳባቸውን በወረቀት ጽፈው ለሰብሳቢው በማቅረብ ሀሳባቸውን ይገልፃሉ። ሴቶች ግን እጅ በማውጣት ድርሻ ጠይቀው ሲነፈጋቸው የተለያዩ ስልቶችን ተጠቅመው ድርሻ ሲነጥቁ አይታዩም። ከዚህ በተለየ ደግሞ በፋካሊቲና በትምህርት ክፍል ደረጃ በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ በስራ ልምዳቸውና በደረጃቸው ከፍ ያሉት ወንዶች ሰብሳቢው ከእነሱ ያነሰ የስራ ልምድ ያለው ከሆነ ድርሻ የሚወስዱት እጅ በማውጣት ሳይሆን በቀጥታ ጣልቃ ገብቶ በመናገር ሲሆን ይህም የሀይል ግንኙነቱ አቻዊ እንዳልሆነ የሚያሳይ ሲሆን፣ የሀይል ግንኙነቱ አቻዊ ባልሆነ ውይይት ተግባቡቱ ቅደም ተከተሉ እንደማይጠብቅና ተገቢ ያልሆነ የድርሻ አወሳሰድ እንደሚኖር ይጠቁማል። ከዚህም በመነሳት የድርሻ አወሳሰድ ከሀይል የበላይነት ጋር ግንኙነት እንዳለው መናገር ይቻላል።

1.3 በንግግር ያላቸው ተደማጭነት ምን ይመስላል?

ከጥናቱ ውጤት መረዳት እንደተቻለው አጀንዳን በማስያዝም ሆነ የውሳኔ ሃሳብ በማቅረብ ከሴቶች ይልቅ የወንዶች ንግግር በሰብሳቢው ተቀባይነት ሲያገኙ ይታያሉ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች የቀደመ ተናጋሪን ዋቢ በማድረግ ሃሳባቸውን ለመግለጽም ሆነ ያቀረቡትን ሃሳብ ትክክል ለመሆኑ እንዲያረጋግጡላቸው ዋቢ የሚያደርጉት ወንዶችን ነው። ይህም በተቋሙ የወንዶች የሀይል የበላይነት ያለ ይመስላል።

1.4 በተግባቦት ሂደት የቋንቋ አጠቃቀማቸው ምን ይመስላል?

የቋንቋ አጠቃቀምን በተመለከተ ሴቶች በሀሳብ ልውውጥ ጊዜ ጭንቅላታቸውን በማወዛወዝ ‹‹እህ›› እና ‹‹እሽ›› የሚሉ ድስኩራዊ ቃላትና ‹‹ነው እንዴ?››፣ ‹‹አይደል?››፣ ‹‹አይደለም ወይ?›› የሚሉ ጥያቄያዊ ዓረፍተነገሮችን በመጠቀም ያልተሟላና ይልተብራራ ምላሽ ይሰጣሉ። ‹‹እህ›› እና ‹‹እሽ›› የሚሉት አጠቃቀማቸው ተናጋሪውን እያዳመጡ መሆናቸውን ለማመልከት የሚጠቀሙበት ሲሆን በዚህም ተናጋሪው ንግግሩን እንዲቀጥል በማድረግ በኩል አስተዋፅዖ አለው። ሆኖም ግን ያልተብራራና ጥያቄ አዘል የቋንቋ አጠቃቀም መጠቀማቸው አንድም ካሉበት ባህል አንፃር ሀሳብን ከመግለጽ ለመቆጠብ ወይም በጉዳዩ ላይ ጠለቅ ያለ ግንዛቤ ስለሌለ በእርግጠኝነት ይህ ነው ብሎ ለመናገር በራሳቸው ባለመተማመናቸው ይመስላል።

አብዛኛዎቹ ወንዶች ሀሳባቸውን ለመግለጽ አፅንኦታዊና ድምፀታዊ አገላለጾችን የሚጠቀሙ ሲሆን፣ በእድሜም ሆነ በስራ ልምዳቸው ከፍ እያሉ ሲሄዱ ግን ሀይል የሚያላብሱ አፅንኦታዊ ቃላትን ከመጠቀም ይልቅ ስነምግባራዊ ቃላትን መጠቀምን ይመርጣሉ። በተቃራኒው ደግሞ ሴቶች በእድሜያቸውም ሆነ በስራ ልምዳቸው ከፍ እያሉ ሲመጡ ሀሳባቸውንም ሆነ ራሳቸውን ለመግለጽ ደፋር እንደሚሆኑ ያመለክታል። ከዚህ በመነሳት ወንዶች በስራ ልምዳቸውና በእድሜያቸው ከፍ እያሉ ሲሄዱ ከአፅንዖታዊና ድምፀታዊ አገላለጾች ይልቅ ስነምግባራዊ አገላለጽን መጠቀም እንደሚመርጡ፣ በተቃራኒው ደግሞ ሴቶች ለተለያዩ የስራ ሁኔታዎች ሲጋለጡና ልምድ እያካበቱ ሲሄዱ በንግግራቸው አፅንዖታዊና ድምፀታዊ ቃላትን እንደሚጠቀሙ መናገር ይቻላል።

የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው ምፀታዊ አገላለጽ በመደበኛ ውይይት ላይ ወንዶች አልፎ አልፎ ሲጠቀሙበት ቢታዩም ተዘውታሪ እንዳልሆ ያመለክታል። ከዚህ በተለየ ሁኔታ ግን ሴቶች በበዙበት ኢመደበኛ ውይይት ላይ ሴቶች ምፀታዊ አገላለፅን በስፋት እንደሚጠቀሙ ውጤቱ ያሳያል።

ወንዶች ‹‹እኔ›› የሚለውን ተውላጠ ስም በመጠቀም ራሳቸውን የሚገልጹ ሲሆን ሴቶች ደግሞ ‹‹እኛ›› የሚለውን ተውላጠ ስም በመጠቀም ሃሳባቸውን የወል በማድረግ ያቀርባሉ። ሆኖም ግን ወንዶች በስራ ልምዳቸው ከፍ ሲሉ ‹‹እኛ›› ወይም ‹‹እኛ→ እኔ››፣ ‹‹እኔ →እኛ›› በሚል አካሄድ ቀላቅለው በመጠቀም ሃሳባቸውን የጋራ በማድረግ ያቀርባሉ። በተቃራኒው ደግሞ ሴቶች በስራ ልምዳቸው ከፍ እያሉ ሲሄዱ ‹‹እኔ›› የሚለውን ተውላጠ ስም በመጠቀም ስለራሳቸው ይገልፃሉ። ይህም የስራ ልምድ መጨመር ለሴቶች በራስ የመተማመን ውጤት እንደሆነና ወንዶች ደግሞ በእድሜ ከፍ እያሉ ሲሄዱ ነገሮችን ከራስ አንጻር ከማቅረብ ይልቅ የጋራ አድርጎ ማቅረብን እንደሚመርጡ ያሳያል።

1.5 በተግባቦት ሂደት የሚያሳዩት ድስኩራዊ ልማድ ምን ይመስላል?

ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በተግባቦት ሂደት የሚያሳዩት ድስኩራዊ ልማድን በተመለከተ በመደበኛ ውይይት ወቅት አብዛኛዎቹ ወንዶች ተራቸውን ሳይጠብቁ ድርሻ የመንጠቅ፣

የጣልቃ ገብነትና ተደርቦ የመናገር ድስኩራዊ ልማድ እንዳላቸውና ይህንም ለመፈፀም ማሳሰቢያ፣ ማስተካከያ፣ ተጨማሪ፣ ይቅርታ፣ የሚሉ የንግግር ብልሃቶችን ይጠቀማሉ። ባንፃሩ ደግሞ አብዛኛዎቹ ሴቶች ተራን ጠብቆ የመናገር ልምድ ያላቸው ሲሆን፣ አንዳንድ የተሻለ የስራ ልምድ ያላቸው ሴቶች ግን ብዙ ጊዜ ባይሆንም ድርሻ ካልተሰጣቸው ጣልቃ በመግባት ድርሻ እንደሚቀሙ ከቡተቃ የተገኘው የውጤት ትንተና ቢያሳይም በምልከታ የተገኘው መረጃ ግን በውይይት ላይ በሚደረግ ተግባቦት ምንም አይነት የሴቶች ጣልቃ ገብነትም ሆነ ድርሻ ለመንጠቅ ሌሎች ብልሃቶችን ሲጠቀሙ ያልታየ ሲሆን ይህም ሴቶች ጣልቃ ገብነትን ብዙ ጊዜ እንደማይተገብሩት ይጠቁማል። የወንዶች ጣልቃ ገብነትን ስንመለከት ሁለት መልክ አለው። አንደኛው ድርሻ ጠይቀው ሲከለከሉ ድርሻን በሀይል ለመውሰድ ሲሆን፤ ሁለተኛው ግን በእድሜ፣ በትምህርት ደረጃና በተለያዩ የሃላፊነት ቦታዎች ያገለገሉ ወንዶች በተለይም በትምህርት ክፍልና በፋካሊቲ ደረጃ በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ የንግግር ድርሻን እጅ በማውጣት ከመውሰድ ይልቅ ጣልቃ በመግባት የንግግር ድርሻ የመውሰድ ልምድ እንዳላቸውና ይህም በስብሳቢውና በተናጋሪው እንዲሁም በተናጋሪውና በአድማጮች መካከል ያለውን የሀይል ግንኙነት አቻዊ እንዳልሆነ ያስረዳል።

በሌላ በኩል ደግሞ ሴቶች በበዙበት ኢመደበኛ ውይይት ላይ ሴቶች ተራን ያለመጠበቅ፣ የንግግር ድርሻን ብቻ ሳይሆን የውይይት ርዕሰ ጉዳይንም የማስቀየር፣ ተደራርቦ የመናገር፣ የሳንዮሽ ወሬና ያለመደማመጥ ልማድ አላቸው። በተቃራኒው ሴቶች በበዙበት ኢመደበኛ አወድ ደግሞ ወንዶች የጣልቃ ገብነትም ሆነ ሀሳባቸውን በመግለጽ በኩል ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ እንደሆነና በእንደዚህ አይነት አውድ የመናገር ፍላጎት እንደሌላቸውና እንደሚፈሩም በውጤት ትንተናው ታይቷል። ስለዚህ ሴቶች ኢመደበኛ ሆኖ ሴቶች የበዙበትን አውድ የሚመቻቸው ሲሆን ወንዶች ደግሞ ሴቶች የበዙበት ኢመደበኛ አውድ የማይመቻቸው እንደሆነ ያሳያል።

ከጥናቱ ውጤት መረዳት እንደሚቻለው መድረክን ከመጠቀም አንፃር አብዛኛዎቹ ወንዶች ልምድ ያላቸው ሲሆን አብዛኛዎቹ ሴቶች ደግሞ መድረክን ተጠቅሞ ሃሳባቸውንም ሆነ ራሳቸውን የመግለጽ ልምድ የላቸውም። መድረክን ተጠቅመው ሀሳባቸውን የሚገልጹት ሴቶችም ሆኑ ወንዶች መድረኩን በመቆጣጠር ድርሻቸውን የሚወጡ ቢሆንም፣ አንዳንዶች ግን መድረክ የመቆጣጠር ችግር አለባቸው። የችግሩ መንስዔ ግን ስርዓተ ፆታዊ ልዩነት ያለው ሲሆን ይህም ሴቶች ከመድረኩ እንዲመልሱ ወይም እንዲያብራሩ ለሚጠየቁት ጉዳይ

ተገቢውን ምላሽ ወይም ማብራሪያ መስጠት ሲገባቸው መናገር ባለመፈለጋቸው፤ ወንዶች ደግሞ ከአጀንዳ በመውጣትና የአድማጭን ስሜት መሰረት አድርጎ ባለመናገር የሚፈጠር እንደሆነ ታይቷል።

በውይይት ሂደት ርዕስን ጠብቆ ከመናገር አንፃር የውጤት ትንተናው እንደሚያመለክተው አብዛኛውን ጊዜ ሴቶች ሲናገሩ ማስታወሻ ይዘው በጥንቃቄ ስለሚዘጋጁ ርዕስ ጠብቆ የመናገር ልምዳቸው ከወንዶች የተሻለ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ርዕስ ያለመጠበቅ ሁኔታ ይታይባቸዋል። ይህም የሆነው መጀመሪያ በቀረበው አጀንዳ ላይ ለመናገር ድርሻ ባለማግኘታቸው ምክንያት በመጨረሻ ድርሻ ሲያገኙ ከአጀንዳው በመውጣት ወደኋላ በመሄድ ስላለፈው ርዕሰጉዳይ በመናገር ከአጀንዳ ከመውጣቸውም በላይ ዲስኩርን ወደኋላ የመመለስ ባህርይ እላቸው። ወንዶች ደግሞ ማለት የሚፈልጉት ጉዳይ ተገቢውን ምለሽ አላገኘም ብለው ሲያስቡ እና የራሳቸውን ማንነት ማለትም የትምህርት፣ የእውቀትና የስራ ልምዳቸውን ለማስተዋወቅ ሲፈልጉ ከውይይቱ ርዕስ (አጀንዳ) ይወጣሉ። ይህም ሴቶች በተገቢው ጊዜ የንግግር ድርሻ የሚሰጣቸው ከሆነ የውይይቱን አጀንዳ ጠብቆ በመናገር ረገድ ከወንዶች የተሻሉ ሲሆኑ የንግግር ድርሻ በተገቢው ጊዜ የማያገኙ ከሆነ ደግሞ ዲስኩርን ወደኋላ የመመለስ ችግር እንዳለባቸው ይጠቁማል።

1.6 በተግባቦት ሂደት ሀሳባቸውን ለመግለፅ ተፅዕኖ አድራጊ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?

የጥናቱ ውጤት እንደሚያስረዳው በተግባቦት ሂደት ሀሳብን በመግለፅ ሂደት አብዛኛዎቹ ወንዶች ሀሳባቸውን ለመግለጽ ተፅዕኖ የሌለባቸው ሲሆን፤ ሴቶች ግን በተለያዩ ውይይቶች ላይ መናገር እየፈለጉ ሳይናገሩ የሚወጡበት ምክንያት ፍርሃት፣ ይሉኝታ፣ በራስ አለመተማመን፣ ድርሻ አለማግኘት፣ በጉዳዩ ላይ ቅድመ ግንዛቤ አለመኖር፣ የወንዶች በንግግር የበላይ መሆንና የስብሰባው ድባብ እንዳይናገሩ ተፅዕኖ ከሚያደርጉባቸው ጉዳዮች በዋናነት ተጠቃሽ ናቸው። ሆኖም ግን በምልከታ በተወሰደው መረጃ ከሁሉም በበለጠ ቅድመግንዛቤ አለመኖር፣ በራስ አለመተማመንና የንግግር ድርሻ አለማግኘት ዋናዎቹ ተፅዕኖዎች እንደሆኑ ያረጋግጣል። ይህም በመደበኛ ውይይት ላይ ለሴቶች ሃሳባቸውን አለመግለጽ ምክንያት ከሚሆኑ ነገሮች ቅድሚያ የሚይዙት ስለነገሮች ያላቸው

ቅድመግንዛቤ አናሳ መሆንና በተቋሙ የንግግር ድርሻ አሰጣጥ ባህል መሰረት ድርሻ አለማግኘታቸው እንደሆነ ያሳያል።

2. ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታ ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር በሚያደርጉት የተግባቦት ሂደት ራሳቸውን እንዴት ይገልፃሉ?

2.1 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች የሙያ ብቃታቸውን/ ያላቸውን ድርሻ ለመግለፅ የሚያደርጉት ጥረት ምን ይመስላል?

አብዛኛዎቹ ወንዶች የሙያ ብቃታቸውን የውይይት መድረኮችን በመጠቀምና ያላቸውን ቅድመግንዛቤ በመጠቀም ይገልፃሉ። አብዛኛዎቹ ሴቶች ያላቸውን እውቀትም ሆነ ሙያዊ ብቃት ሲገልጹ አይታዩም። በእርግጥ ቁጥራቸው አነስተኛ የሆኑ ከፍተኛ የስራ ልምድ ያላቸውና በስብሰባ ላይ ሃሳብንና ራስን መግለጽ ጠቃሚ እንደሆነ ቅድመግንዛቤ ያገኙ ሴቶች ሃሳባቸውንም ሆነ ራሳቸውን ይገልፃሉ። ከዚህም በመነሳት በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ያሉ ሴቶች ለተለያዩ ስራዎች ተጋላጭ ከሆኑና ሃሳብንና ራስን በመግለጽ ያለውን ጠቀሜታ በተመለከተ ቅድመግንዛቤ ካገኙ በራስ የመተማመን ችሎታቸው ከፍ እንደሚልና ከነበሩበት ባህል በመውጣት ሙያዊ ብቃታቸውን ሊገልጹ እንደሚችሉ ያሳያል።

2.2 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በተግባቦት ሂደት ማንነታቸውን ለመግለጽ ተፅዕኖ አድራጊ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?

በጥናቱ ውጤት መሰረት በሴቶችም ሆነ በወንዶች ተግባቦት ሂደት ማንነታቸውን ለመግለጽ ተፅዕኖ አድራጊ ጉዳዮች የሚባሉት ትህትና፣ ማህበረሰባዊ ባህል፣ ተቋማዊ ባህል፣ ለተለያዩ የስራ ሁኔታዎች አለመጋለጥና ቅድመ ግንዛቤ አለመኖር ናቸው። ሆኖም ግን እነዚህ ተፅዕኖዎች በሴቶች ላይ ከፍተኛ ጫና እንዳላቸውና የማህበረሰቡ ባህል በተቋሙ ዘልቆ በመግባት ተቋማዊ መልክ በመያዝ፣ ለተለያዩ የስራ ሁኔታ ባለመጋለጣቸውና ስለተለያዩ ጉዳዮች ያላቸው ቅድመግንዛቤ ዝቅተኛ መሆን ራሳቸውንም ሆነ ሃሳባቸውን በመግለጽ ሂደት ዋናዎቹ ተፅዕኖዎች እንደሆነ አመልክቷል።

የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው ወንዶች ስለተለያዩ ጉዳዮች ግንዘቤና እውቀቱ ያላቸው ሲሆን ለዚህም የተለያዩ ጽሁፎችን በማንበብ፣ በመገናኛና የመረጃ መረቦችን የመጠቀም

እንዲሁም ከተለያዩ ሰዎች ጋር ተግባቦታዊ መስተጋብር በመፍጠር ያገኙት ሲሆን፤ በተቃራኒው ግን ሴቶች በእለት ተዕለት ከሚገጥማቸው ማህበራዊ ገጠመኝ ከሚያገኙት የህይወት ልምድ ባለፈ ብዙም በንባብም ሆነ የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም ስለተለያዩ ጉዳዮች ግንዛቤያቸውንና እውቀታቸውን የማስፋት ልምዱ እንደሌላቸው ያመላክታል። በእርግጥ አንዳንድ ወንዶች ከአንባቢ ወንዶች ጋር ባላቸው ተግባቦታዊ መስተጋብር አማካኝነት አንባቢ ቢመስሉም ከቡተቃ ከተገኘው መረጃ አንፃር ግን ሁሉም ወንዶች አንባቢ ናቸው ለማለት አይቻልም።

5.3 የጥናቱ አንድምታና መፍትሄ

በጥናቱ ውጤት መሰረት አብዛኛዎቹ ሴቶች በመደበኛ ውይይት ላይ በሚያደርጉት ተግባቦታዊ ሂደት ሀሳባቸውን በስፋት ሲገልጹ አይታዩም። ሴቶች በበዙበት ኢመደበኛ ውይይት ላይ ደግሞ ሴቶች ሃሳባቸውን በመግለጽና አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ የሆነ የሀሳብ ልውውጥ በማድረግ ከፍተኛ ተሳትፎ ሲኖራቸው፤ ወንዶች ግን ሃሳባቸውን ከመግለጽ ይቆጠባሉ። ከዚህ በተለየ መልኩ ደግሞ ሴቶች በበዙበት መደበኛ ውይይት ላይ ወንዶች ንቁ ተሳታፊ ሲሆኑ ሴቶች ግን ሃሳባቸውን አይገልጹም። ይህም ሴቶች ኢመደበኛና የሴቶች ቁጥር የበዛበት ወይም ሴቶች ብቻ ያሉበት የውይይት አውድ የሚመቻቸው ሲሆን፣ በውይይት ሂደት ሃሳብን ለመግለጽ የተሳታፊዎች ብዛት ከጾታ አንፃር ተፅዕኖ አለው ማለት ነው።

ወንዶች ሃሳባቸውን አድማጭ በሚረዳው ሁኔታ ባግባቡ የማቅረብ ችሎታ ሲኖራቸው፣ ቁጥራቸው አነስተኛ የሆኑ ተናጋሪ ሴቶች ደግሞ ከወንዶች በተሻለ ሁኔታ ሃሳባቸውን አድማጭ በሚረዳው መልኩ የማቅረብ ችሎታ አላቸው። ለዚህም ዋናው ምክንያት ከመናገራቸው በፊት ዝግጅት በማድረጋቸውና በተደራጀ ሁኔታ ከውይይቱ ዓላማ ሳይወጡ በቀጥታ ሃሳባቸውን ስለሚገልጹ ነው። በዚህም በውይይት ሃሳብን በተሳካ መንገድ ለማቅረብ ቅድመዝግጅትና የውይይት ዓላማን መጠበቅ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንዳለው ያሳያል።

ድርሻን ጠብቆ ከመናገር አንፃር ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በዩኒቨርሰቲ ደረጃ በሚደረጉ ውይይቶች ላይ የንግግር ድርሻን እጅ በማውጣት ይወስዳሉ፡፡ በእንደዚህ አይነት ስብሰባዎች ላይ ድርሻ የሚጠይቁ ሴቶች ቢኖሩም አብዛኛውን ጊዜ ድርሻ ይነፈጋቸዋል፡፡ በዚህ አውድ በተደጋጋሚ እንደታየው ሰብሳቢዎች በውይይቱ መጨረሻ ላይ በተሳታፊዎች ጠያቂነት ለሴቶች ድርሻ የሚሰጡ ሲሆን አሰጣጡም ሃሳባቸው አስፈላጊ ስለሆነ ሳይሆን ‹‹ለተሳትፎ›› እንደሆነ የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ ይህም ሴቶች ሃሳባቸውን እንዳይገልጹ ከማድረጉም በላይ በራሳቸው እንዳይተማመኑ አስተዋፅዖ አለው፡፡

አብዛኛዎቹ ወንዶች በፋካሊቲና በትምህርት ክፍል ደረጃ በሚደረጉ መደበኛ ውይይቶች ላይ፣ ሴቶች ደግሞ ሴቶች በበዙበት ኢመደበኛ ውይይት ላይ የንግግር ድርሻን ጠብቆ ከመናገር ይልቅ ድርሻ ይነጥቃሉ፡፡ ከዚህ በተለየ ደግሞ በፋካሊቲና በትምህርት ክፍል ደረጃ በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ በስራ ልምዳቸውና በደረጃቸው ከፍ ያሉት ወንዶች ሰብሳቢው ከእነሱ ያነሰ የስራ ልምድ ያለው ከሆነ ድርሻ የሚወስዱት እጅ በማውጣት ሳይሆን በቀጥታ ጣልቃ ገብቶ በመናገር ነው፡፡

በጥናቱ ውጤት መሰረት ሁለቱም ፆታዎች ድርሻን ጣልቃ በመግባት ወይም በመደረብ ለመንጠቅ የተለያየ ብልሃት ይጠቀማሉ፡፡ ይኸውም ሴቶች ደምፃቸውን ከፍ በማድረግ የአድማጭን ጆሮ በመያዝ ሲሆን፣ ወንዶች ደግሞ ይቅርታ፣ እዚህ ጋ፣ ማሳሰቢያ፣ ማስተካከያ የሚሉ አገላለጾችን እንደብልሃት ሲጠቀሙ ይህ ካልተሳካለቸው ደግሞ ሃሳባቸውን በወረቀት ጽፈው ያቀርባሉ፡፡ የዚህ አንደምታም ሴቶችና ወንዶች ለሚሰሯቸው ስራዎች የሚጠቀሙበት ብልሃት የተለያየ እንደሆነ የሚያሳይ ሲሆን ይህ ችሎታቸው ደግሞ በስራ ተቋም ለሚታቀዱ ተግባራት የማስፈፀሚያ ብልሃቶችን (ስትራቴጂዎች) ከተለያየ አቅጣጫ ለመንደፍ ያስችላል፡፡ በተቃራኒው ግን በተቋማት በሚዘጋጁ የስራ አቅዶችም ሆነ የስራ ማስፈጸሚያ ብልሃቶች ሲዘጋጁ በአንዱ ፆታ ብቻ የሚዘጋጁ ከሆነና ሁለቱም ፆታዎች የማይሳተፉ ከሆነና በአተገባበሩ ሂደት ችግር እንደሚኖር ይጠቁማል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ድርሻን ለመንጠቅ ሁለቱ ፆታዎች የሚያፈልቁት የተለያየ ብልሃት መሆኑ ሲታይ በተለይም የማስተማሪያ ዘዴዎችን የተለያየ የመማር ስልት ካላቸው ተማሪዎች አንፃር ለማዘጋጀት ከሁለቱም የሚገኘው

ችሎታ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው ሲሆን፣ ይህም በትምህርት ተቋማት የሁለቱ ፆታ መኖር አስፈላጊ እንደሆነ ያሳያል።

አብዛኛዎቹ ወንዶች ሀሳባቸውን ሲገልጹ አፅንኦታዊና ድምፀታዊ አገላለጾችን የሚጠቀሙ ሲሆን፣ በእድሜም ሆነ በስራ ልምዳቸው ከፍ እያሉ ሲሄዱ ግን ሀይል የሚያላብሱ አፅንኦታዊ ቃላትን ከመጠቀም ይልቅ ስነምግባራዊ ቃላትን መጠቀምን ይመርጣሉ። በተቃራኒው ደግሞ ሴቶች በእድሜያቸውም ሆነ በስራ ልምዳቸው ከፍ እያሉ ሲመጡ ሀሳባቸውንም ሆነ ራሳቸውን ለመግለጽ የሚያስችሉ የቋንቋ አጠቃቀሞችንና ሀይል የሚያላብሱ አፅንኦታዊ ቃላትንም ይጠቀማሉ። ከዚህ በመነሳት ወንዶች በስራ ልምዳቸውና በእድሜያቸው ከፍ እያሉ ሲሄዱ በንግግር ያላቸው የሀይል የበላይነት እየቀዘቀዘ የሚሄድ ሲሆን፣ በተቃራኒው ሴቶች ደግሞ ለተለያዩ የስራ ሁኔታዎች ሲጋለጡና ልምድ እያካበቱ ሲሄዱ በንግግር ያላቸው የሀይል የበላይነት እየጨመረ ይሄዳል።

ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በተግባቦት ሂደት የሚያሳዩት ድስኩራዊ ልማድን በተመለከተ በመደበኛ ውይይት ወቅት አብዛኛዎቹ ወንዶች ተራቸውን ሳይጠብቁ ድርሻ የመንጠቅ፣ የጣልቃ ገብነትና ተደርቦ የመናገር ድስኩራዊ ልማድ ያላቸው ሲሆን፣ ተቀባይነት እንዲኖረውም ማሳሰቢያ፣ ማስተካከያ፣ ይቅርታ፣ እዚህ ጋ የሚሉ ብልሃቶችን ይጠቀማሉ። ሴቶች በበዙበት ኢመደበኛ ውይይት ላይ ሴቶች ተራን ያለመጠበቅ፣ የንግግር ድርሻን ብቻ ሳይሆን የውይይት ርዕሰ ጉዳይንም የመንጠቅ፣ ተደራርቦ የመናገር፣ የጎንዮሽ ወሬና ያለመደማመጥ ልማድ አላቸው።

መድረክን ከመጠቀም አንፃር ወንዶች ልምድ ያላቸው ሲሆን አብዛኛዎቹ ሴቶችና ጥቂት የማይባሉ ወንዶች ደግሞ መድረክን ተጠቅሞ ሃሳባቸውንም ሆነ ራሳቸውን የመግለጽ ልምድ የላቸውም። ምክንያቱ ደግሞ ሴቶች ከመድረኩ እንዲመልሱ ወይም እንዲያብራሩ ለሚጠየቁት ጉዳይ ተገቢውን ምላሽ ወይም ማብራሪያ አለመስጠት፤ ወንዶች ደግሞ ከአጀንዳ በመውጣትና የአድማጭን ስሜት መሰረት አለማድረግ ነው። ይህም ወንዶችም ሆኑ ሴቶች መድረክን በአግባቡ የመጠቀም ችግር እንዳለባቸውና ምክንያቱ ደግሞ ስርዓተ ፆታዊ ልዩነት ያለው መሆኑን ያሳያል።

ተግባቦታዊ መስተጋብር በመፍጠር አዳዲስ መረጃ እንደሚያገኙና አብዛኛዎቹ ሴቶች ደግሞ ከንባብ ይልቅ በእለት ተዕለት ከሚገጥማቸው ማህበራዊ ገጠመኝና የስራ ልምድ ለችግሮች መፍትሄ የማቅረብ ልምድ እንዳገኙ ይጠቁማል። ይህም ሴቶችና ወንዶች በውይይት ሃሳብ በመግለጽ ሂደት የተለያየ ችሎታ እንዳላቸውና በዚህም የንግግር ድርሻ የሚወስዱበት ጊዜ ሊለያይ እንደሚችል ያመለክታል። ከዚህም ሌላ ሴቶችና ወንዶች ወደስራ ተቋም ይዘውት የሚመጡት ልምድና ችሎታ የሚለያይ፣ ግን ደግሞ ሁለቱም ችሎታዎች አብረው መገኘት ያለባቸው እንደሆኑ ያመለክታል። ይህም ለስራ ተቋሚት ስኬታማ መሆን የሁለቱ ፆታዎች መኖር ብቻ ሳይሆን ሃሳባቸውን እንዲገልጹ ማድረግ ለተቋሙ ስኬታማ መሆን አስተዋፅዖ አለው።

በአጠቃላይ ቀደም ብሎ የቀረበውን የጥናቱን ግኝትና አንደምታ መሰረት በማድረግ የሚከተሉት የመፍትሄ ሀሳቦች ተጠቁመዋል።

ጥናቱ ለተካሄደበት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም፡-

በተቋሙ የመማር ማስተማሩንና ከዚሁ ጋር ተዛማጅነት ባላቸው ጉዳዮች በሚደረጉ ውይይቶች ላይ ለምሳሌ በሴኔት፣ በማናጅመንት ኮሚቴ፣ በአካዳሚክ ኮሚሽን የሚሳተፉ ሴቶች በተቋሙ ካሉት ሴቶች ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ ነው። በመሆኑም ተቋሙ ከሴቶች ሊያገኘው የሚችለውን አስተዋፅዖ ከማጣቱ በተጨማሪ በዩኒቨርሲቲው የሚወጡ መተዳደሪያ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ የሚታቀዱ እቅዶችና የማስፈፀሚያ ብልሃቶች በወንዶች ብቻ የሚዘጋጁ ከሆነ በአፈፃፀሙ ሂደት ተቋሙም ሆነ ሴቶች በስራቸው ስኬታማ እንዳይሆኑ ተፅዕኖ ያደርጋል። በመሆኑም ተቋሙ ከሁለቱም ፆታዎች የሚገኙ የተለያዩ ችሎታዎችንና ብልሃቶችን መጠቀም እንዲችል በተቻለ መጠን በሁሉም ተግባራት ሴቶችና ወንዶች እንዲሳተፉ ቢደረግ።

በተቋሙ ለሴቶች የንግግር ድርሻ የመስጠት ባህሉ ብዙም ካለማደጉ በተጨማሪ ለሴቶች የሚሰጠው ድርሻ አንደበታቸውን እንዲያፍታቱ በሚመስል ‹‹ለተሳትፎ›› እንደሆነ በጥናቱ ተመልክቷል። በመሆኑም ለሴቶችም ሆነ ለወንዶች ሃሳብ እኩል ዋጋ ለመስጠት የሚያስችል የውይይት ባህል መፍጠር ያስፈልጋል።

በጥናቱ መሰረት በመደበኛ ውይይት ሃሳባቸውንና ራሳቸውን የሚገልጹ ወንዶች እንደሆኑና ተቋሙ ደግሞ በአብዛኛው የተለያዩ ሃላፊነቶችን ለመስጠት በሰዎች ተናጋሪነት ላይ የመመስረት ባህርይ ይታይበታል። የተቋሙን ባህል የተረዱት አብዛኛዎቹ ወንዶችና ከቁጥር የማይገቡ ሴቶች ይህን ይጠቀሙበታል። በመሆኑም ተቋሙ የሃላፊነትም ይሁን የስራ ድርሻ ለመስጠት በአብዛኛው በተናጋሪነት ላይ ከመመስረት ስራቸውን በመመዘን ቢሆን ምናልባትም ተገቢ ሰው ለተገቢ ቦታ ከማስገኘቱ በተጨማሪ የሴቶችንም ሆነ የወንዶችን ችሎታና ልምድ በእኩል ለመጠቀም እድሉን ከማስፋቱ በተጨማሪ ሴቶችን ለተለያዩ ስራዎች ተጋላጭ ማድረግ በስራቸው ላይ ያላቸው ቅድመግንዛቤ ስለሚሰፋ ሃሳባቸውንም ሆነ ራሳቸውን የሚገልጹ ሴቶችን በማፍራት በኩል አስተዋፅዖ ይኖረዋል።

በተቋሙ ለሚገኙ ሴት መምህራን፡-

በዚህ ጥናት መሰረት ሴቶች በመደበኛ ውይይት ላይ ሃሳባቸውንም ሆነ ራሳቸውን እንደማይገልጹና በዚህም የተለያዩ ተፅዕኖዎች እንዳለባቸው ተመልክቷል። በመሆኑም በመደበኛ አውድ ላይ ለመሳተፍ ተፅዕኖ አድራጊ ጉዳዮችን እንደባህል፣ ይሉኝታ፣ ፍርሃት፣ ቅድመግንዛቤ የመሳሰሉትን ማስወገድ ያስፈልጋል። ከሁሉም በላይ በስብሰባ ላይ ሃሳብን ለመግለጽና የስራ ጉዳይን በተመለከተ ሰፊ የሆነ ቅድመግንዛቤ እንዲኖር መጣር ያስፈልጋል። ይህን ለማግኘት ደግሞ ከንባብ በተጨማሪ የተለያዩ ስራዎችን ከሚሰሩ ወንዶችና ሴቶች ጋር ተግባቦታዊ መስተጋብር መፍጠርና በተቋሙ በሚካሄዱ የተለያዩ ተግባራት ላይ ለመሳተፍ የግል ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ሴቶች የበዙበት ኢመደበኛ አውድ ሴቶች ሃሳባቸውንም ሆነ ራሳቸውን ለመግለጽ እንደሚመቻቸው ታይቷል። በመሆኑም ይህን አውድ በስፋት በመፍጠርና በተገቢው መንገድ በመጠቀም በሰው ፊት የመናገር ልምዱን ቢያዳብሩ በሌሎቹ አውዶች ሃሳብን ለመግለጽ ይረዳል።

ሴቶች በኢመደበኛ ውይይት ላይ ድርሻ ለመንጠቅ ድምፅን ከፍ አድርጎ የመናገር ብልሃት ሲጠቀሙ፣ በመደበኛ ውይይት ላይ ግን ድርሻ ሲነፈጋቸው እንደወንዶች የተለያዩ

ብልሃቶችን በመጠቀም ድርሻ አይወስዱም። በመሆኑም በመደበኛ ውይይት ላይ ድርሻ ለማግኘት የሚያስችል ተገቢ ብልሃት ሊኖራቸው ይገባል።

የመናገር ልምዱ ያላቸው ሴቶች ሃሳባቸውን ሲገልጹ አድማጭ በሚረዳውና በሚስብ መልኩ እንደሚያቀርቡ በጥናቱ ተመልክቷል። ለዚህም ቅድመዝግጅት ስለሚያደርጉና የውይይትን ኣላማ በመጠበቅ በቀጥታ ሃሳባቸውን ስለሚያቀርቡ ነው። በመሆኑም ይህ ልምድ የበለጠ ተጠናክሮ መቀጠል ይገበዋል።

በተቋሙ ለሚገኙ ወንድ መምህራን

በዚህ ጥናት መሰረት ወንዶች በመደበኛም ሆነ በኢመደበኛ ውይይት ሃሳባቸውንም ሆነ ራሳቸውን ይገልጻሉ። ለዚህ ደግሞ የባህል ተፅዕኖ ያለመኖሩ ዋናው ጉዳይ ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪ በማንበብ፣ ከተለያዩ ሰዎች ጋር ተግባቦታዊ መስተጋብር በመፍጠርና ራሳቸውን ለተለያዩ ስራዎች በማጋለጥ ስለተለያዩ ጉዳዮች ያላቸው ቅድመግንዛቤ ሰፊ መሆን አስተዋፅዖ አድርጎላቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ ሃሳባቸውን በመግለጽ ሂደት ድርሻ የማይሰጣቸው ከሆነ ድርሻ ለማግኘት የተለያዩ ብልሃቶችን ይጠቀማሉ። በመሆኑም እነዚህ በማጠናከር በተግባቦታዊ መስተጋብራቸው ያላቸውን ስኬታማነት መቀጠል የሚገባቸው ሲሆን ድርሻን ለማግኘት የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች ድግሞ የተግባቦትን ቅደም ተከተል በመጠበቅና የሌሎችን የንግግር ድርሻ በማይጋፋና አቻዊ ተግባቦታዊ መስተጋብርን በሚፈጥር መልኩ ለማድረግ ቢጥሩ በተቋሙ የተሻለ ተግባቦታዊ መስተጋብር እንዲኖር አስተዋጽዖው ከፍተኛ ነው።

በሌላ በኩል ግን በዚህ ጥናት እንደታየው ሀሳብን ባልተደራጀና በተወሳሰበ መንገድ በማቀረብ አድማጭን የሚያሰለቹ ወንዶች ቁጥራቸው ትንሽ የሚባል አይደለም። ይህን ችግር ለማሻሻል በመጀመሪያ ከመናገር በፊት ቅድመዝግጅት የማድረግ ልምዱን መፍጠር፣ ከዚህም ሌላ የሚገለፀው ሃሳብ ከውይይቱ ዓላማ ጋር የማጣጣምና ከውይይቱ አጀንዳ ውጭ የሆኑ ጉዳዮችን ሳይደባልቁ የመናገር ልምዱ ለመፍጠር ቢሞከር የተሻለ ይሆናል።

ወንዶች የንግግር ድርሻን በተደጋጋሚና በሀይል በመውሰድ በጥቂት ወንዶችና ሴቶች ላይ የንግግር የበላይነትን ያሳያሉ። ይህ ደግሞ በስራ ቦታ ላይ ተግባብቶ ጓዳዊ የሆነ መስተጋብር በመፍጠርና የስራ ተቋሙም ሆነ ሰራተኛው ስኬታማ እንዳይሆን ተፅዕኖ ያደርጋል። በመሆኑም ወንዶች ድርሻን በሀይል ከመንጠቅና በንግግር የበላይነትን ከማሳየት ይልቅ አቻዊ የሆነ ተግባቦታዊ መስተጋብር እንዲኖር መጣር የተሻለ ተግባቦታዊ መስተጋብርና የስራ ተቋም እንዲኖር ያደርጋል።

ለፖሊሲ አውጭዎች

ሴቶችና ወንዶች ከአንድ ማህበረሰብ የፈለቁ ቢሆንም የአስተዳደግ ሁኔታቸውም ሆነ ከአደጉ በኋላ ባላቸው አኗኗር ምክንያት የሚኖራቸው ማህበራዊ ተጋልጦ በመለያየቱ ወደስራ ተቋሙ ሲመጡ የተለያየ ችሎታ፣ እውቀት፣ የስራ ልምድና ብልሃቶች ይዘው ይመጣሉ። በዚህም የሚወጡት ፖሊሲዎችና የማስፈፀሚያ ብልሃቶች አንድን ፆታ ብቻ መሰረት አድርገው የሚወጡና የሚነደፉ ከሆነ ትግበራው ስኬታማ ካለመሆኑ ባሻገር የፍትሃዊነት ችግርም ይከሰታል። በመሆኑም ሁለቱንም ፆታዎች በማሳተፍ ፍትሃዊ የሆነና በሁሉም ዘንድ ተተግባሪነት ያለው ፖሊሲና ብልሃት (ስትራቴጂ) መንደፍ ይገባል። የሚነደፈው ፖሊሲ በጥቅሉ የሴቶች ተሳትፎ እንዲኖር በሚገልጽ ትዕዛዛዊ ዓረፍተ ነገር ከሆነ ግለሰቦች ሲፈቅዱ የሚያደርጉትና ሳይፈልጉ ደግሞ የሚተው ይሆናል። ስለሆነም ‹‹እሾህን በሾህ›› እንደሚባለው ከቤተሰብ እስከ ማህበረሰብ የተገነባውና ስር የሰደደውን ፆታዊ ስርዓት ስር መስደድ በሚችል ስርዓት መልሶ መገንባት ያስፈልጋል። የሚገነባው ስርዓት ተግባራዊ ሆኖ የተፈለገውን ውጤት መሰብሰብና ማግኘት እንዲቻል እንደንብ አበባ ቀሳሚ ሰራተኞች በማሰማራት ብቻ ሳይሆን እንደሸረሪት ድር የመዘርጋት ብልሃት መጠቀም ይገባል። እንደሚታወቀው ንብ ማር ለማምረት አበባ ቀሳሚ ካላሰማራችና ወደአበባው ካልሄዱ አበባው ወደእነሱ መጥቶ ማሩን ማምረት አይቻልም። የሸረሪትን ብልሃት ስንመከት ደግሞ ድሯን በዘዴ በማድራት እሷ ባለችበትም ሆነ በሌለችበት ሁኔታ የምትፈልገውን ታገኛለች። ስለሆነም ስርዓተፆታን በተመለከተ የሚወጡ ፖሊሲዎች በጉዳዩ ላይ ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ሲኖሩ የሚፈፀም፤ ከሌሉ ደግሞ የሚተው እንዳይሆን እንደሸረሪት ድር ስርዓት በመዘርጋት ማንኛውም ሰው ሊፈፅመው የሚችል ፖሊሲ መንደፍ ያስፈልጋል።

ይህን ለማድረግ ደግሞ በመጀመሪያ በማህበረሰቡ የተገነባው አሉታዊ አስተሳሰብና ግንዛቤ ምን አንደሆነና ይህንም ለማስፈፀም የተዘረጋውን ሰንሰለታዊ ስርዓት (system) ምን አይነት አወቃቀር እንዳለው መመርመር፤ ቀጥሎም ይህ የተገነባው ስርዓት የሚያደርሰው ተፅዕኖ ምንና ምን ያህል እንደሆነ ማህበረሰቡ በሚረዳው መንገድ መግለጽ ያስፈልጋል፡፡ በመጨረሻም የነበረውን አሉታዊ ስርዓት ለማፍረስ የሚያስችል ሰንሰለታዊ ስርዓት መልሶ መገንባትም ይገባል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በአገር አቀፍ ደረጃም ሆነ በየተቋማቱ የሚወጡ ህጎች፣ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎች... የሚቀርቡበት የቋንቋ አጠቃቀም ተባዕታይና አነስታይ ፆታን ከመግለጽ አንፃር ወጥ መሆን ይገባቸዋል፡፡ በመሰረቱ አማርኛ ቋንቋ በተፈጥሮው ወንዴ ተኮር መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሆኖም ግን አሁን ባለንበት ዘመን የስርዓተፆታ ፅንሰ ሃሳብን አብዛኛው ሰው ግንዛቤ እያገኘ ባለበት ሁኔታ ለወንድም ሆነ ለሴት ሁለተኛ መደብ ተባዕታይ ፆታ አመልካች ግስን በመጠቀም አንብብ፣ ፃፍ፣ ገምግም... በማለት ለመጠቀም አስቸጋሪ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ቋንቋ የሚፃፉ ህጎች፣ ፖሊሲዎችን፣ መመሪያዎች... ሶስተኛ መደብ ብዙ ቁጥርን በመጠቀም (ጻፉ፣ አንብቡ፣ ገምግሙ፣ ስሩ፣ ተናገሩ...) ማቅረብ ቢለመድ የተሻለ እንደሚሆን አጥኝዋ ታምናለች፡፡ ይህን ማድረግ የማይቻል ከሆነ ደግሞ ሁለቱን ፆታዎች በማካተት (ጻፍ/ጻፊ፣ አንብብ/አንብቢ፣ ገምግም/ገምግሚ...) ወጥ በሆነ መንገድ ቢቀርብ የተሻለ ይሆናል፡፡

ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፡-

በመሰረቱ በስራ ቦታ ስኬታማ የሆነ አንደበታዊ ተግባቦት መልካም ግንኙነትን ለመፍጠር ቁልፍ መሳሪያ ነው፡፡ መግባባት ካለ ደግሞ ስራ በታቀደውና በተፈለገው መንገድ ስለሚሰራ ተቋሙም ሆነ ሰራተኛው ስኬታማ ይሆናሉ (ባሬትና ዴቪድሰን፣ 2006)፡፡ በዚህ ጥናት መሰረት ደግሞ በከፍተኛ ትምህርት ተቋም በሴቶችና በወንዶች መካከል ሃሳብን በመግለጽ ረገድ ከፍተኛ ልዩነት እንዳለና ልዩነቱ ደግሞ ተግባቦታዊ መስተጋብሩ አቻዊ እንዳልሆነ ያመላክታል፡፡ ስለሆነም ሰራተኞች በስራ ቦታቸው መልካም ግንኙነት በመፍጠር በስራቸው ስኬታማ የሚሆኑት ስኬታማ የሆነ ተግባቦታዊ መስተጋብር መፍጠር ሲችሉ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ የስራቦታ ተግባቦታዊ መስተጋብር ግንዛቤና ክህሎት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

በመሆኑም ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወደስራ የሚሰማራ የሰው ሀይል የሚያመርቱ እንደመሆናቸው፣ በስልጠናቸው ውስጥ ስርዓተ ፆታን መሰረት ያደረገ ‹‹የስራ ቦታ ተግባቦታዊ መስተጋብር ክህሎት›› ስልጠናን በማካተት ሰልጣኞቹ ከወዲሁ ስለስራ ቦታ ተግባቦታዊ መስተጋብር ግንዛቤውና ክህሎቱ እንዲኖራቸው ማድረግና በስራ ላይ ላሉት ደግሞ ስራ ላይ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ለቋንቋ መርሃ ትምህርት አዘጋጆች

በከፍተኛ ትምህርት የሚገኙ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች የተማሩ ከመሆናቸውም በላይ የከፍተኛ ተቋም ተማሪዎችን የሚያስተምሩ ናቸው፡፡ ከሌላው የማህበረሰብ ክፍል ጋር ሲተያዩ በትምህርት ደረጃቸው የተሻለ ደረጃ ላይ ያሉ ናቸው፡፡ ሆኖም ግን በዚህ ደረጃ ያሉ አብዛኛዎቹ ሴቶች ሃሳባቸውንም ሆነ ራሳቸውን በመግለፅ ተፅዕኖ መፍጠር እንደማይችሉ በዚህ ጥናት ታይቷል፡፡ የንግግር ችሎታ ደግሞ የሚመጣው በየጊዜው በምናደርገው ልምምድ ሲሆን፣ ልምምዱ ከፍ እያለ ሲሄድ አንደበትም እየተባ ይሄዳል፡፡ ልምምዱ ባነሰ ቁጥር አንደበት ይተሳሰራል፡፡ በመሆኑም ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ ያለው የቋንቋ ትምህርት ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ከቤተሰባቸውና ከማህበረሰባቸው ይዘውት የሚመጡትን የንግግር ልማድ ለመቅረፍ በሚያስችል የቋንቋ ትምህርት ይዘትና የማስተማር ዘዴ መዘጋጀት እንዳለበትና በተለይም የንግግር ክህሎትን ሊያዳብር የሚችል የትምህርት ይዘት ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ያሳያል፡፡

በመጨረሻ ከጥናቱ ውጤት ለመረዳት እንደተቻለው ሂሳዊ የዲስኩር ትንተና በከፍተኛ ትምህርት ተቋም በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለው ተግባቦታዊ ስልት ምን እንደሚመስል ማሳየት አስችሏል፡፡ በተግባቦት ሂደት የስራ ተቋም ባህሉ ምን እንደሚመስልና በቋንቋ፣ በስርዓተ ፆታና በሀይል መካከል ያለውን ግንኙነት ለመፈተሸም ያስችላል፡፡ ይሁን እንጂ አጥኝዋ በዚህ ጥናት ግኝት ላይ በመመስረት በአጠቃላይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም እንዲህ ናቸው፣ እንዲህ ይሁኑ ለማለት አትደፍርም፡፡ ምክንያቱም ተቋማዊና ማህበረሰባዊ ባህል በእንዲህ አይነት ጥናት ተፅዕኖው ሰፊ በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም ሂሳዊ ዲስኩር ትንተና በተለይም በሀገራችን ባሉ ከፍተኛ ተቋማት በስፋት ተግባራዊ ቢደረግ የተቋማዊ ባህል ልዩነት በሴቶችና በወንዶች ተግባቦታዊ ስልት ላይ እስከምን ድረስ ተፅዕኖ እንዳለው

ለማሳየት ያግዛል። ሌላው ግን የዚህ ጥናት አድምታ በከፍተኛ ትምህርት የሚያስተምሩ ሴት መምህራን ሃሳባቸውንም ሆነ ራሳቸውን በስራ ባልደረቦቻቸው ፊት የማይገልጹ ከሆነ ተማሪዎቻቸውን በሚያስተምሩበት ጊዜስ ችግር ይኖር ይሆን ወይስ የተለየ ሁኔታ ይኖር ይሆን የሚል ሌላ የምርምር ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል። ስለሆነም ተመራማሪዎች የዚህ አይነቱን ምርምር በስፋትና በተከታታይ እንዲያካሂዱ ይህ ጥናት ይጋብዛል።

ዋቢዎች

ጎሩት ካሳው። (1997)። ‹‹በአዲስ አበባ ክልላዊ መስተዳድር በሚገኙ የመንግስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሴትና የወንድ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ አመራር ችሎታ ንፅፅራዊ ጥናት››። (አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ለአማርኛ ማስተማር (TeAm) ኤም.ኤ ዲግሪ በከፊል ማሙያነት የቀረበ ጥናት)።

ትምህርት ሚኒስቴር። (ሰኔ፣2002)። ‹‹አገር አቀፍ የሴቶች ትምህርት ስትራቴጂ።›› አዲስ አበባ።

Atkinson, P. (1999). Medical Discourse. In Sarangi, S. and Roberts, C.(eds) *Talk, Work and Institutional Order. Discourse in Medical, Mediation and Management Settings.* New York: Mouton de Gruyter:75-107.

Bass, J. (2001). *Gender Equity or Bust!: On the Road to Campus Leadership with Women in Higher Education* . San Francisco, California, Inc.

Boden, D. (1994). *The Business of Talk: Organizations in Action.* Polity Press, London.

Bariley, K. (1987). *Method of Social Research* . /3rd ed/ Toronto: Macrnillen.

Barrett,M. & Davidson,M.J. (2006). *Gender and Communication at work.* London: Ashgate Published Limited.

Bogden, R.C. and Biklen, S.K. (1982). *Qualitative research for education: an introduction to theory and methods.* Boston: Allyn and Bacon, Inc.

Bourdieu, P. (1977). *Outline of a theory of practice*. Cambridge: Cambridge University Press.

Brown, G. and Yule, G. (1991). *Discourse analysis*. Cambridge: Cambridge University Press.

Brown, D. (2007). *Principles of Language Learning and Teaching*. (5th ed.) White Plains, NY: Pearson Education.

Cecilia, L. (2007). "What Men Say, How Women Say: An Exploration of the Interactional Mechanisms at Play In Management Meetings". Un published PhD dissertation, University of South Africa.

Conrad, C. & Poole, M. (2002). *Strategic Organizational Communication in a Global*

Economy. Belmont, CA: Wadsworth.

Chant, S. (2007). *Exploring the 'Feminisation of Poverty' in Africa, Asia and Latin America*. London, Sage.

Crystal, D. (1987). *The Cambridge encyclopedia of language*. Cambridge: Cambridge university Press.

Deal, J.J. (2000). *Gender differences in the intentional use of information in competitive negotiations*. Small Group Research, 31, 702-23.

Dedaic, M.N. (2004). *Modality in political communication. IN Facchinetti, R. and Palmere, F. (eds) English modality in perspective: genre analysis and contrastive studies. Germany:* Peter lang GmbH: 45-66.

Denzin, N.K. (1997). *Interpretive Ethnography: Ethnographic Practices for the 21st Century*.Thousand Oaks: Sage.

Dornyei, Z. (2007). *Research methods in Applied Linguistics*. New York: OUP.

Dryanan, L. (2011). Communication Clash. New York,NY.

Edley,N. and Wetherall, M.(1997). *Jockeying for Position: the Construction of Masculine Identities.* Discourse and Society. 8(2):180-217.

Eriyanto, J. (2001). *Analysis Wacana*. Yogyakarta: LKIS.

Fairclough, N (1989). *Language and Power*. London: Longman.

Fairclough, N. (1992). *Discourse and Social Chang*. Cambridge politly Press.

Fairclough, N. & Wodak, R. (1997). "*Critical discourse analysis*". In T. van Dijk (Ed.), Discourse as Social Interaction (pp. 258–284). London: Sage.

Fairclough, N. and Wodak, R. (2000). *Critical Discourse analysis*. In Van Dijk, T.A (ed) *Discourse as social interaction, discourse studies: multidisplinary introduction 2:* London: sage: 258-284.

Fairclough, N. (2001). *Language and power*. Harlow: Longman.

Fairclough, N. (2003). *Analysing Discourse: Textual Analysis for Social Research.* London: Routledg.

Fairclough, N. (2006). *Discourse and Social Chang.* London: Routledg.

Fishman, P.M.(1980). *Conversational insecurity*. In Giles, H., Robinson, W. p. and Smith, P.(eds) *language :social psychological perspectives.* Oxford: Pergamon:127-132.

Fishman, P. (1983). Interaction: The Work Women do. In Thorn, B. Kramarae, C. and Henley, *N.*

(eds) Language, Gender and Society. Rowley, MA: Newbury House: 89-102.

Fraser, B. (1980). *Conversational mitigation.* Journal of Pragmatics 4(4): 342-350.

Gray,J.(1992). *Men are from Mars, Women are from Venus.* London:Thorsons.

Gray, J. (2002). *Mars and Venus in the Workplace.* New York.

Griggin, E. (2009). *A First Look at Communication Theory. Launching Your Study of Communication Theory.* New York.

Goodall, H.L. & Goodall, S. (2002). *Communication in Professional Context: Skills, Ethics, and Technologies.* Belmont, CA: Wadsworth.

Guba, E. G., & Lincoln, Y. S. (2005). *Competing paradigms in qualitative research.* In N. K. Denzin & Y. S. Lincoln (Eds.) (2005), *Handbook of qualitative research* (2nd ed., pp. 107–117). Thousand Oaks, CA: Sage.

Gumperz,J.J.(1982). *Discourse Strategies.* Cambridge :Cambridge University Press.

Hamilton, H and et als. (2001). *Handbook of Discourse Analysis.* Oxford: Blackwell.

Haney, W,V. (1986). *Communication and interpersonal relation: texts and cases.* Irwi series in management and the behavioral sciences. London: Irwin:77-89.

Harrison,R, (1972). Understanding your organisation's character. *Harvard Business Review* 50: 119-128.

Haylay,G.(2009). "Gender Difference in the use of Lingustic forms in the speech of men and women. A comparative study of selected Tigirigna Novels by men and women." M.A.Thesis, Addis Ababa University.

Holmes, J. and Stubbe, M. (2003). *Power and politeness in the workplace: a socio-linguistic analysis of talk at work.* London: Longman

Holmes, J., Stubbe, M. and Vine, B. (1999*). Constructing professional identity: doing power in policy units. In sarangi, S. and Roberts.* C. (eds*) Talk, work and institutional order: : Discourse in medical. mediation and management settings.* Berlin: Mouton de Gruyter: 351-385.

Huang, S. Y. L. & Fraser, B. J. (2009). Science Teachers' Perceptions of the School Environment: Gender Differences. Journal of Research in Science Teaching, 46(4), 404- 420.

Huckin, T.N. (2007). *Social Approaches* : Critical Discourse Analysis. Cambridge: MIT Press.

Hughes, C. (2003). *Disseminating Qualitative Reasearch in Educational Settings: A Critical Introduction.* London: Open University Press.

http://exchanges.state.gov/education/engteaching/pubs/ BRfunctionalisec 36.htm. Accesed Augest 1, 2007.

James P.G. (1999). *An Introduction to Discourse Analysis: Theory and Method.* Routledge:Taylor & Francis Group. London and New York.

Karau, S. J. and Eagly, A. H. (1999). 'Invited reaction: Gender, Social roles and the emergence of leaders', *Human Resource Development quarterly*,10(4):321-7.

Kendall, S. & Tannen, D. (1997), *"Gender and language in the workplace."* In Kotthoff, H.,

Lakoff, R. T. (1975). *Language and woman's place*. New York Harper & Row.

Langellier, K. and Hall, D. (1989). Interviewing women: a phenomenological approach to feminist communication. In Carter, K and Spitzack, C (eds) *Doing research on feminist communication.* Norwood, NJ Ablex: 193-220.

Licoln,Y.S. and Guba,F.G. (1985). *Naturalistic inquiry*. London: Sage Publication.

Morgan, G. (1997). *Images of organization* (2nd ed.). London: Sage Publications.

Marianne, J. and Louise, P. (2002). *Discourse Analysis as Theory and Method.* London: Ssge Publications.

McElhinny, B. (2003). Theorizing gender in sociolingustics and linguistics anthropology. In J. Holmes and M. Meyerhoff (eds), *The Handbook of Language and Gender*. Oxford: Blackwell. pp. 21-42

Mullany, L (2007).*Gendered Discourse in the Professional Workplace*. New York: Palgrave Macmillan,

Mumby,D.K. (1988). Communication and Power in Organisation: *discourse,ideology and domination*, Norwood,NJ: Ablex.

Mumby, D. (1993). *Critical organizational communication studies*: The next 10 years. Communication Monographs, 60, 18-25.

Mumby, K. and Clair, R.P.(2000). Organisational discourse. In Van Dijk, T.A.(ed) *Discourse as social interaction: a multidisciplinary introduaction.*vol.2:181-205.

Patton,M.Q.(1990). *Qualitative evaluation and research methods: clear exposition of approaches to qualitative analysis*. Newbury Park:Sage.

Platt, J.T. and Platt, H.K. (1975). The *social significance of speech: an introduction to and*

workbook in sociolinguistics. Amsterdam: North Holland.

Richards, J.C and Nunan, D. (1991). *Second Language Teacher Education*. Cambridge: CUP

Robson,C.(1997). *Real world research: a resourse for social scientists and practitioner researchers*. Oxford: Blackwell.

Rogers, R. (2004). *An Introduction to Critical Discourse Analysis in Education.* Mahwah,New Jersey: Lawrence Erlbaum Assocation,Inc.

Sacks, H., Schegloff, E.A. and Jefferson. G. (1974). *A simplest systematic for the organasation ot turn-taking for conversation. Language* 50(4):696-735.

Sacks,H.(1992). On the analyzability of children in Gumperz, J. and Hymes, D (eds) *Direction in Sociolinguistic.* New York: Holt, Rinehart and Winston: 325-345.)

Sarangi, S. and Robert, C. (1999). (eds) The dynamics of interactional and institutional orders in work-related settings. *Talk, work and Institutional order: discourse in medical, mediation and management settings*. New York: Mouton Gruyter:1-61.

Silverman,D.(1997). (ed) *Qulitative research: theory, method and practice*. London: Sage.

Smith,H.W.(1975). *Strategies of social research: the methodological imagination.* London: Prentice-Hall.

Shân, W. (1999). *Language and Gender: An introduction to Language, Society and Power.* London:Routledge.

Stubbe,M., Lane, C.,Hilder, J.,Vine, E.,Vine, B.,Marra,M., et al. (2003). *Multi-ple discourse analyses of a workplace interaction.* Discourse Studies, 5(3), 351-388.

Svecz, A. (2010). *Effective Organizational Communication*, available from http://www.suite101.com/content/effective-organizational-communication-a198603 Internet: accessed May 16, 2011.

Tanaka, L. (2009). *Communicative stances in Japanese interviews: Gender differences in formal interactions. Language & Communication.* 29(4), 366-382.

Tannen, D.(1990). *you just don't understand: women and men in conversation.* New York: William Marrow.

Tannen, D. (1991). *You Just Don't Understand : Women and Men in Conversation.* Virago: London.

Tannen, D. (1994). *Talking from 9 to 5. Women and Men in the Workplace: Language, Sex and Power.* New York: Avon.

Tannen, D. (1999). *The Display of Gendered Identities in Talk at Work.* In Bucholtz,M., Liang,A.C. and Sutton,L.A.(eds)Reinventing Identities: the gendered self in discoyrse. Oxford: Oxford university press:221-240.

Thornborrow, J. (Eds). (2005). *Language, Society and Power.* Second Edition. London: Routledge.

Thornborrow, J. (2002). *Power Talk: Language and Interaction in Institutional Discourse.* Edinburgh: Pearson Education.

Van Dijk,T.A.(1993a). *Elite discourse and racism.* Newbury park, CA:sage.

Van Dijk,T.A. (1993b). *Principles of critical discourse analysis. Discourse and Society.* 4(2): 249-283.

Van Dijk, T.A. (1996). *Discourse, power and access.* In Caldas, C.R. and Coulthard, M. (eds) Texts and practices: reading in critical discourse analysis. London: Routledge: 84-104.

Van Dijk, T.A. (1997). *Prejudice in discourse.* Amsterdam: Benjamins.

Van Dijk, T.A. (1997): *Discourse as Social Interaction.* London: Sage.

Van Dijk, T.A.(1998): *Ideology. A multidisciplinary study.* London: Sage.

Van Dijk, T.A. (1999). *Critical discourse analysis and conversation analysis. Discourse and Society.* 10 (4):459-460.

Van Dijk, T.A. (2000). (ed*) Discourse as Interaction in Society. Discourse as social interaction. Discourse studies: a multidisciplinary introduction.*vol.2: London: sage: 1-37

van Dijk, Teun A. (2001): "Critical Discourse Analysis". In: Tannen, D./ Schiffrin, D./ New York: William Marrow.

Van Dijk,T.A. (2002). *Multidisciplinary CDA*: a plea for diversity. In Wodak.R. and Meyer, M.(eds) Methods of critical discourse analysis. London:sage: 95-120.

Wallace, M.J. (1991). *Training Foreing Language Teachers.* Cambridge: CUP.

Wharton, A. S. (2005). *The Sociology of Gender: An Introduction to Theory and Research.*

Oxford: Blackwell.

West, C. and Zimmerman, D.H. (1987). 'Doing Gender', *Gender and Society*, 1:125-51.

Wirth. L. (2001). *Breaking Through the glass Ceiling: Women in Management.* Geneva: International Labour Office.

Wodak, R. (1996). (Eds), *Communicating Gender in Context.* Benjamins, Amsterdam.

Wood, J.T. (2010). *Communication, Gender, and Culture*. Boston, MA: Cengage Learning.

Yin,R.K. (1989). *Case study research: design and methods*. London;sage.

Yin. R. K (2011). *Qualitative Research From Start to Finish.* New York: The Guilford Press.

አባሪዎች

አባሪ አንድ

የቡድን ተኮር ቃለመጠይቅ (ቡተቃ) ጥያቄዎች

‹‹በከፍተኛ ትምህርት ተቋም መምህራን የሚታይ ስርዓተፆታዊ የዲስኩር ትንተና፡- በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ መነሻነት፡፡›› በሚል ርዕስ ለተደረገው የምርምር ስራ በምልከታ የሚገኘውን መረጃ ለማጠናከር በደጋፊ የመረጃ መሰብሰቢያነት የዋል የቡድን ተኮር ቃለመጠይቅ (ቡተቃ)፡፡

1. በስብሰባ ወቅት ከመናገራችሁ በፊት ምን ምን ታደርጋላችሁ?
2. ለመናገር ስትፈልጉ ሌሎች የመናገር እድል እንዲሰጧችሁ ምን ታደርጋላችሁ?
3. ሀሳባችሁን ሳትጨርሱ ወይም ሳትናገሩ ከስብሰባ ወጥታችሁ ታውቃላችሁ?
4. ሴቶችና ወንዶች በስብሰባ ወቅት የተለያየ ባህርይ ሳያሉ ብላችሁ ታስባላችሁ?
5. ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታ ከአቻዎቻቸው ጋር በሚያደርጉት የተግባቦት ሂደት ራሳቸውን አድማጭ በሚረዳ ሁኔታ ባግባቡ ይገልፅሉን?

መለያ ቁጥር፡- አኮ 002

1. አበበ፡- የመወያያ አጀንዳ፤የ-.....ና ..... ፕሮግራሞች ህልውና ላይ
2. ሲሆን የዚህ ስብሰባ ዓላማ ወደ ኮንሰንሰንስ መምጣት ነው ሌላ ነገር የለውም፡፡
3. [ከበደ፡- የኮርስ ባለቤትነት ጉዳይም ሁለተኛ አጀንዳ ቢሆንና ብንነጋገርበት አይሻልም?
4. አበበ፡- እሽ የኮርስ ባለቤትነት ላይ፣ እኔ አስቤ የመጣሁት ይህን ስለነበር በተነሳው ሁለተኛው
5. አጀንዳ ላይ አውርተን በዛ መንፈስ መነጋገር እንችላለን፡፡ የሁለቱን ፕሮግራሞች በሚመለከት
6. አንሱና ከዛ በመቀጠል ወደኮርስ ባለቤትነት መሄድ እንችላለን፡፡
7. መለሰ፡- ካሪክለም ሪቪዥኑን በሚመለከት እኛ ውስጣዊ ይዘቱን አናውቅም፡፡ እኔ በተለይ
8. አላውቅም፡፡ እዛ ውስጥ እንዴት አድርጌ ኮሜንትስ ለማድረግ የምችለው፡፡ አሁን ባለፈው
9. እነፋሲል ነግረውኝ ነበር፡፡ታያለህ ብለውኝ ነበር ፊተና ላይ ስለነበርኩ አላየሁትም፡፡ ያየ ሰው
10. ከሌለ በስተቀር ለውይይት አይመቸንም እኮ፡፡ ወይ እኛ ሰጥተውን እንድናይ ተደርጎ ቢሆን፣
11. ወይ ደግሞ እናንተ አይታችሁት የሆነ ኮንትሮቨርሻል የሆኑ ነገሮች ተነስተው ቢሆን እሱን
12. አንስታችሁልን ካልሆነ በስተቀር ካሪክለሙ ላይ የት ቦታ ላይ ለውጥ እንዳለው፣ የት ቦታ ላይ
13. ችግር እንዳለ፣ አይ ሃቭ ኖት አይዲያ፡፡ አሁን በማናውቀው እኔ በተለይ በማላውቀው ነገር
14. ነው አሁን እንትን አድርግ እየተባልኩ ያለሁት፡፡ ግር ስላለኝ ነው፡፡
15. አበበ፡- እ ልክ ነህ ግን ካሪክለሙን አይተነዋል ሪቫይዝድ የተደረገውን ካሪክለም፡፡ የፕሮግራም
16. ተወካይ ባሉበት ኤሲ ላይ አይተነዋል-ውብነሽ፡፡ እዛ ላይ መስተካከል ይገባቸዋል ያልናቸውን
17. ኮንሰርኖች ሬዝ ተደርገዋል፡፡ ሊነሱ የሚችሉ ነገሮችን አ ይ ቲንክ ውብነሽ ታውቃቸዋለች
18. እንደፕሮግራም ተወካይ፡፡ ሶ ሰው አይቶ መምጣት አለበት ምናምን ልንነጋገር ልናየው እንችላለን፡፡ በተረፈ
    ግን እንደፕሮግራም ተወካይ አይ ቲንክ ሊነሱ የሚገቡ((xxx)) ማድረግ ይቻላል፡፡ ውብነሽ!
19. [አለሙ፡- ማሳሰቢያ! እዚህ ጋ ይቅርታ፣ ከትናንት ወዲያ ኢንፎርማል ስብሰባ ነበር በዚህ ጉዳይ
20. የ..... ትምህርት ክፍል፡፡ እና የተስማማነው ምንድ ነው በጎነት፣ አብሮ መስራት፡፡ በጋራ
21. ማሰብ ሲቻል የ.....ውም የፎክለሩም አብሮ እያደገ እየጠነከረ ይሄዳል፡፡ በዛ መልኩ
22. ኢንተርዲስፕልነሪ አለ ኦልሞስት ይሳሳባል፡፡ እና ከዛ ቀጥሎ የባለቤትነት ጥያቄ ሊነሳ ይችላል
23. በዋናነት ማለት ነው፡፡ ግን ከዚህ በፊትም የተለመደ በሌሎች ድሮ የምናውቀው ከውጭ ድረስ፡
24. ከዛ ከዛ ከበጎ መንፈስ ይመስለኛል እንጅ ከተቀናቃኝነት በዛ መልኩ አልነበረም ትናንት ስንነጋገር
25. እንደነበረው ለማለት ፈልጌ ነው፡፡ ማሳሰቢያ ነው፡፡
26. አበበ፡- አይ ጥሩ ነው፡፡ እምንረዳው በዛ መንፈስ ይሁንና ዴልቨር ላይ ምናምን ላይ የሚነሱ
27. ጥያቄዎች እናነሳቸዋለን በኋላ ያንህል አስቸጋሪ አይደለምና፡፡ እንደው ከዛ ግን ጎላ ብሎ
28. ኮርሶችን ሼር ፐርሰንት ስላላቸው ማነው በባለቤትነት ሊይዛቸው የሚገባ የሚለው ቢለይና ይህ
29. ቢመለስ ጥሩ ነው፡፡ ኮርሶቹም እንደባለቤትነት እንዲያድጉ እንዲዳብሩ፡፡ የሁለቱ ፕሮግራሞች
30. ልዩነቱ፣ መንፈሱ አቶ አለሙ አሁን ባለው መልኩ እስካሁንም አልሆነም፤ ተባብሮ በውይይት
31. እንደሰለጠነ ሰው መስራት፡፡ በጣም ፎርማል ዲስኬሽን የምናደርገው ከሆነ ቃለጉባዔ ሁላ የሚይዝ
32. ሰው ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡ እንደዛ እናድርገው? ያው ፀሀፊ ስለሆንሽ፣
33. አገሬ፡- እ!
34. አበበ፡- በውጭ ግንኙነትሽ ስለምትፅፊ፡ አጀንዳዎቹን እናስይዝሽ፡፡ መጀመሪያ ስለካሪክለሙም
35. አጠቃላይ ለምን ሪቫይዝ ማድረግ እንዳስፈለገም ተጨባጭ የሆነ ነገሮችን እንዲያብራራልን
36. ለሁላችንም ለፋሲል እድሉን እንስጥ፡፡
37. ፋሲል፡- ጋሽ አለሙ ባለው እንስማማለን፡፡ የእኛም አይዲያ እሱ ነው ኮመንሊ ለመነጋገር ማለት
38. ነው፡፡ እኔ አሁን በተለይ ካሪክለሙ እኔ ካቀረብኩ በኋላ ያለው በግለጽ መነጋገር ስላለብኝ ነው፡፡
39. ..... ዲፓርትመንቶች ፊት ለፊት እኔን የተናገረኝ ሰው የለም፡፡ እና
40. [አበበ፡- ወደእዛ ከመምጣትህ በፊት ለምንድን ነው ካሪክለሙን ሪቫይዝድ ማድረግ ያስፈለገው?
41. [ፋሲል፡- አይሆንም አጀንዳውን ሚስ እንዳናደርገው ብዬ ነው፡፡ ለምሳሌ እኔን የጠየቀኝ ለምሳሌ
42. ጋሽ ደበበ ቢኖር ጥሩ ነበረ እሱ ፐርሰናሊ አናግሮኛል፡፡

43. (ተሰብሳቢው በህብረት)፡- አለ፣ አለ፣
44. [ደበበ፡- አለሁ፡፡
45. ፋሲል፡- አለ ጋሽ ደበበ፣ ኦኬ፣ አናግሮኝ ስለነበር፡፡ ጋሽ ከበደ ደግሞ ሰለሞንን አናግሯል፡፡ ..እና
46. እዚህ ላይ ውብነሽ ሚስአንደርስታንድ አድርጋቸዋለች ብዬ አስባለሁ፡፡ ኮርሶችን ምናምን፡፡
47. ..... ኤንድ ማስሚዲያ ከጋዜጠኝነት ትምህርት ክፍል የሚሰጥልን ሰው እንጋብዛለን፡፡
48. አርካይቭ ኤንድ ጆኦሎጂ የባህል ማዕከል ባለሙያ፣ ወዘተ. እነዚህን የተረዱት እነሱ ሁለተኛ
49. ውብነሽ የተረዳችው እነዚህ ኮርሶች ከፋካሊቲያችንም አስወጣችኋቸው፣ ከሶሻል ሳይንስ ምናምን
50. ነገር ወጡ፡፡ ዊች ሚንስ ከእኛ ፕሮግራም ወጥተው እንደለቀቅናቸው አይነት ነገር ነው
51. የተሰማቸው፤ ያለኝ ነገር ማለት ነው፡፡ እና በመካከላችን ፊት ለፊት መነጋገር ባይኖር እነዚህን
52. ኮርሶች ከእኛ እንዳስወጣናቸው፤ ዊች ሚንስ እናንተ ካልቻላችሁ ለምን ወደእኛ አታስጠጓቸውም
53. አይነት ነገርም ይመስላል ክሊርሊ ለመነጋገር፡፡ ከጋሽ ደበበ ጋር በዚህ ትናንት ተነጋግረናል፡፡
54. ወደውጭ ወደውጭ የሚሉ ኮርሶችን ወደዲፓርትመንታችን፣ ካልቻልንም ደግሞ
55. ወደፋካሊቲያችን የማስጠጋት ስራ ነው የሰራነው፡፡ እና እነዚህ ኮርሶች በትናችኋቸዋል የሚል
56. ነገር፣ ነገር ነው ያለው፡፡ እዚህ ጋ ሚስአንድርስታንዲግ አለ የምለው፣ ሌሎች ጓደኞቼም ሊያነሱ
57. ይችላሉ፡፡ ከዛ ተነስቼ ግን ካሪክለሙ ለምን ሪቫይዝድ ማድረግ አስፈለገው ወደሚለው ነገር
58. ስመጣ..
59. [አበበ፡- ይሄ ካሪክለም፣ ሶሪ? ተሰርቶ የነበረው በ..... ትምህር ክፍል ስለነበረ ነው፡፡ እና
60. ሁሉም አእምሮው ውስጥ ሊኖር ይችላል ይህ ጥያቄ ለምንድን ነው መቀየር ያስፈለጋቸው?
61. የሚለውን፡፡
62. [ፋሲል፡- መጀሪመያ ካሪክለሙን ሪቫይዝድ ማድረግ ያስፈለገበት ምክንያት አንደኛው ነገር
63. ወደሞጁላር ሲመጣ በተለይ በርካታ የተበታተኑ ችግሮች ነበሩ፡፡ ችግሩ የእኛ ዲፓርትመንት ብቻ
64. አይደለም፡፡ ሁሉም ፕሮግራሞች ችግር እንዳለባቸው ምንም ጥያቄ የለውም፡፡ ሞጅላሩ አንድ
65. የሚያስገድደው ነገር የተበታተኑ ኮርሶችን ወደአንድ ማምጣት ስለነበረ፣ የድሮው ካሪኩለም
66. እንደሚታወቀው የተበታተኑ ናቸው፡፡ አንድ ኮርስ ላይ ማለቅ የሚገባቸው ኮርሶች ራሳቸውን
67. ችለው ሁለት ኮርስ ሆነው በኮርስ ደረጃ የሚቀርቡ ነበሩ፡፡ ሪደንደንሲ እንዳሉ..ሞጅላሩን
68. መጀመሪያ ስንሰራ በማቀራረብ ነው የሰራነው፡፡ ተከታታይነት ያላቸውን ኮርሶች የትኛው
69. ለየትኛው ኮርስ ተመጋጋቢ ነው? የትኛው የትኛው ኮርስ በጋራ ሊሰጥ ይችላል? የሚለውን ነገር
70. መወሰን አስፈላጊ ነበረ፡፡ በፋካሊቲ ደረጃ አደም ታስታውሳለህ፣ ዶር መለሰም ያስታውሳል፡
71. ..... ፕሮግራማችሁ ችግር አለበት በተከታታይ ሰርታችሁ አቅርቡ የሚል ግፊቶችም ነበር፡፡
72. ዜን ከዛ ግፊት በመነሳት፣ በዋናነት ግን ግፊት ስለመጣ ብቻ ሳይሆን ፕሮግራሙ እንደገና
73. ሪቫይዝድ ማድረግ አለብን፤ በተበታተነ መንገድ ነው ኮርሶች የተቀመጡና እንጠቅልላቸው፡፡
74. አንድ ኮርስ መውሰድ የሚገባቸው ከሆነ ለምን? በአጠቃላይ የተማሪዎችን የዲፓርትመንቱንም
75. የዩኒቨርሲቲውንም ኢኮኖሚካሊ በርካታ ነገሮችን ሊያሳጣ ይችላል ከሚል ሪቫይዝድ ለማድረግ
76. ተገደናል፡፡ ምናልባት ..... ዲፓርትመንት የሚገናኙ ኮርሶችን ላንሳ፤ ሊንጉስቲክስ ፎር
77. ....ሪስት የሚባል ኮርስ ነበር፣ ሌላ ፎኖሎጂ ፎር ....ሪስት የሚል ኮርሶች አሉ፡፡ እነሱን
78. ኮርሶች አንድ ላይ መርጀ አድርገናቸዋል በአሁኑ፡፡ ለምን ሊንጉስቲክስ የሚለው ኮርስ
79. ኢትኖግራፊክ.. የሚባል አንድ ኮርስ አለ ..... ኤንድ ሶሳይቲ የሚባል ሌላ አንድ ኮርስ አለ፡፡
80. ስለዚህ ስለሊንጉስቲክስ በአንድ ወይ በሌላ በኩል በእነዛ ኮርሶች ውስጥ ይነሳል፡፡ ያም ሆኖ እያለ
81. ግን በሁለተኛ ደረጃ((xxx))ያመጣል፡፡ ስለዚህ አንድ ኮርስ በሶስት በአራት ኮርሶች ውስጥ
82. የሚነሳበት ሁኔታ አለ፡፡ ዜን ምን እናድርግ፣ ሊንጉስቲክስን በዋናነት በኢትኖግራፊ ውስጥ
83. ይሰጣል፤ በ..... ኤንድ ሶሳይቲ ስለሚያገኙት ተማሪዎች ምንእናድርግ፤ ሊንጉስቲክስ ኤንድ
84. ፕራክቲካል ፎነቲክስ የሚሉትን አንድ ላይ መርጀ እናድርጋቸው፡፡ አድርገናቸው ሴሚስተር
85. ዋይዝ እናድርጋቸው፡፡ .....ሪስት በሁለት ወር ፕራክቲካል ፎነቲክስ በሁለት
86. ወር፡፡ አሁን ግን ሊንጉስቲክስና ፕራክቲካል ፎነቲክስን ሁለት ሰኣት አድርገናቸው አንድ ኮርስ
87. አድርገናቸው ሴሚስተር ዋይዝ አድርገናቸው ላቭም ፕራክቲካል ሆኖ በተለይ ፎነቲክሱ ላቭም
88. ስለሚያስፈልገው ሴሚስተር ዋይዝ ይሁን፡፡ ስለዚህ መምህሩ ሁለት ሰዓት ነው
89. የሚያስተምረው፡፡ ዜር ፎር ሁለት ክሬዲት የነበረውን ፕራክቲካል ፎነቲክስ ወደሶስት

90. አሳድገነዋል፡፡ ሶስት አድርገነው ሊንጉስቲክስ ኤንድ ፕራክቲካል ..... ብለንአንድ ኮርስ
91. አድርገናል፡፡....ስለዚህ ስለሊንጉስቲክ ጀነራል የሆኑ ነገሮችን አቅፎ በዋናነት የእኛ ተማሪዎች እንዲማሩ
92. የምንፈልገው በዛ ኮርስ ፎነቲክሱ ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ እንፈልጋለን፡፡ በተለያዩ ቋንቋ የተሰሩ የተለያዩ
93. ቋንቋዎች ሲባል .....ን ባህልን ለማጥናት ቋንቋውን ማጥናት የግድ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ እሱን
94. ፕራክቲካሊ ለማሳየት .... ላይ ተማሪዎቻችን ማተኮር መቻል አለባቸው፣ በላብ መታገዝ አለባቸው
95. በሚል የላብ ኮርስ እንዲኖር አድርገናል፡፡ በዚህ ምክንያት አንደኛውን ኮርስ መርጅ ለማድረግ ተገደናል፡፡
96. ስለዚህ በአጭሩ ግን፣ በአጭሩ ግን እነዚህ ክፍተቶች ስለነበሩበት ሌሎችም ኮርሶች አሉ እነዚህ ክፍተቶች
97. ስለነበሩበት ከእኛ ዲፓርትመንት የሚወጡ በርካታ ኮርሶች አሉ፡፡ ..... ኤንድ ሶሳይቲ፣ ግን ከአማርኛች
98. ጋር አብረን ስለምንሰራ ስንሰራም ስለመጣን፣ ክሊርሊ ማወቅ ያለብን ነገር፡ ..... ኤንድ ሳይኮሎጂ
99. የሚባል ኮርስ አለ፣ 75 ፐርሰነት በፐርሰንት የሚገርማችሁ፣ እናንተ ፐርሰንት አላወጣችሁም
100. 75 ፐርሰንቱ ይሄ ኮርስ የእኛ ነው፤ ብለው በደብዳቤ ተጠይቀናል፤ ሳይኮሎጂ ዲፓርትመንት፡፡
101. ስለዚህ በፐርሰንት 25 ፐርሰንት ..... ነው እንዴት አድርገው በምን መስፈርት እንዳወጡት
102. ባይገባንም፡፡ ይሄ ክፍተት እያለ ዝም ብለን ልንቀመጥ አንችልም፡፡ ክሪቲካል ቲንኪግ ኤንድ
103. ቴክስት አናሊሲስ የሚባል ኮርስ አለ ሎጂኮች መተው ይሄ ኮርስ የእኛ ነው አሉ፡፡ ይሄ ሁሉ
104. የመጀመሪያው ካሪኩለም ክፍተት አለበት ማለት ነው፡፡ እሱን ሪቫይዝድ እያደረግን መሄድ
105. አለብን፡፡ ሌሎች በርካታ ኮርሶችን ከፋካሊቲያችን ውጭ የሆኑ ሰዎች እየጠየቁ ነው፡፡ ስለዚህ
106. ይሄንን ሪቫይዝድ አለማድረግ ማለት ዲፓርትመንቱን ዘግቶ እጅን አጣጥፎ ከመቀመጥ ሌላ
107. የተሻለ አማራጭ የለም ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በዋናነት ጥያቄዎች እየበረከቱ እየበዙ ስለመጡ
108. ማሻሻል አለብን የሚል የፕሮግራማችን እምነት ስለሆነ ሪቫይዝድ ለማድረግ የተገደድን በግልጽ
109. መቀመጥ ያለበት ማለት ነው፡፡ ሌሎች ጥያቄዎች ካሉ ልንቀበል እንችላለን፤ ግን ይሄ ኮርሶችን
110. ወደውጭ ምናምን የመላክ ነገር ተደርጎ ለ..... ፕሮግራም መምህራን ተነግሯቸዋል፡፡ እኛ
111. ባልተረዳነው፣ ባልጠበቅነው መንገድ፡፡ ስለዚህ አንዳንዶች ያኮረፉ ሰዎች ይኖራሉ፤ አንዳንዶች
112. ፐርሰናሊ እኔን አናግሮኛል አፐርሸት አደርጋለሁ፡፡ ስንነግራቸውም እንደዛ ከሆነ ኦኬ ምናምን
113. ብለውናል፤ ግልፅ መነጋገር ካለብን ማለት ነው፡፡ እና እኔ በጣም እኔ አፍራያለሁ በጣም...እከሌ
114. እኔን አኩርፋኛላች እከሌ እኔን አኩርፎኛል ምናምን ነገር መባባል ሁሉ ተጀምሯል፡፡ ለምንድ
115. ነው የምንኮራረፈው? እና ይሄ ነገር ትልቅ ትኩረት እንዲሰጠው ፈልጌ ነው ተጨማሪ
116. የሰጠሁት፡፡ አመሰግናለሁ፡፡
117. አበበ፡- 001 ትምህርት ክፍል ላይ ያለው ኮርስ ይሄ ብቻ ነው ወይ?
118. ፋሲል፡- ሌላ ኮርስ ላይ ልጨምር፡፡ ..... ራይቲንግ ስኪል ዋን፣ .....ቱ የሚባሉ ኮርሶች አሉ፡፡ በዛ ምክንያት በነገራችን ላይ ..... ኤንድ ፕራክቲካል .... መርጅ ለማድረግ የተገደድንበት ምክንያት፣ ቤዚክ ራይቲንግ ስኪል የሚባል ኮርስ አለ፤ ሌላ ዲፓርትመንቶች ይወስዱታል ቤዚክ ራይቲንግ ስኪል፤ ..የመጀመሪያው ካሪኩለም ይህ ኮርስ የለውም፡፡ ስለዚህ እሱን ማስገባት ነበረብን፡፡ እሱን ለማስገባት ደግሞ ከቶታል ክሬዲት ባላይ ነው የሚሆነው - እንዳሉ ኮርሶችን ሳንነካ መርጅ ሳንነካ ብንጨምር፡፡ ስለዚህ ኮርሶች መርጅ የማድረጋችን አንደኛው ምክንያት አዲስ ኮርሶች መጨመር ስለነበረብን፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎቻችን የመፃፍ ክሂላቸው ማቴሪያላቸው በ..... ፅሁፍ የለንም በ..... ናቸው፡፡ እሱን መጻፍ፣
119. ማንበብ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ በሚል ቤዚክ ራይቲንግ ስኪል ማስገባት የተገደድነው፡፡ ሌላው
120. የግራጁየት ፕሮፋይላችን ላይ የሚያሳየው ተማሪዎቻችን የህዝብ ግንኙነት ሆነው ይሰራሉ፣
121. ጋዜጠኛ ሆነው ይሰራሉ የሚል ግራጁየት ፕሮፋይል ላይ አለ የሚል ነው፡፡ ኤሲ ላይ ተነስቶ
122. የነበረው ጉዳይ ይሄ ጆርናሊዝም ኮርስ ፓብሊክ ርሌሽን ኮርስ ተማሪዎቻችሁ አልወሰዱም፤
123. ግራጁየት ፕሮፋይል ግን ይሄ ይላል፤ እዚህ ጋ ክፍተት አለው፡፡ ትክክል ነው አዎ፤ አክሴፕት
124. እናደርጋለን፡፡ መቀበል መቻልም አለብን፡፡ እንደኛ ለተማሪዎቻችን ስለሚጠቅም፡፡ ስለዚህምንድነው
125. የተደረገ የተሰጠን ክሊርሊ ለመናገር ማለት ነው፡፡ ..... ዋንና ቱን የተነገረውን ነው
126. የምነግራችሁ፡፡ ..... ብቻ ብላችሁ አንድ ኮርስ ሰታችሁ ሌላ ኮርስ መጨመር አትችሉም ወይ፡፡
127. በግልጽ መናገር ያለብኝ ለምንድን ነው ..... ዲፓርትመንቶችን ትፈሯቸውአላችሁ በአራት ነጥብ፡፡
128. የተጠየኩት ኤሲ ላይ ውብነሽም ስለምትናገር፡፡ ..... ዲፓርትመንቶችን ት-ፈ-ሯ-ቸ-ዋ-ላችሁ በአራት
129. ነጥብ፡፡ አንፈራቸውም እናከብራቸዋለን በአራት ነጥብ የተናገርኩት፡፡ ስለዚህ ይሄ ሁሉ አካሄድ
130. ተፈርቶ ..... ብለን አንድ ኮርስ አጥፍተን እንበል ሌላ ኮርስ መጨመር እንችል ነበር፡፡ ዜን ይሄን

ማጥፋት አንችልም ብለን ተከራከርን፡፡ ..... ቲዌሪ የሚማሩበት ነው፤..... ደግሞ ፕራክቲካል
የሚለማመዱበት ኮርስ ስለሆነ ከባድ እንደሆነ ገልጫለሁ ታስታውሳለች ውብነሽ ስለነበረች፡፡ ዜን
ፋይናሊ ምን እናድርግ ከፕሮግራማችን ጋር ተወያይተን ሁለቱን ኮርሶች መርጅ ከምናደርጋቸው ሰፊም
ስለሆኑ ..... 3 ክሬዲት የነበረው 2 እንዲሆን፤..... እንዳለ ሆኖ ማለት ነው ሁለቱም፣ 3 ሆኖ
እንዲቀጥል፤ ስለዚህ ..... 1 ክሬዲት፣ ሲኔር ኢሴያችሁን የእናንተን ካሪኩለም አይተነዋል
የአብዛኛዎቻችሁን ካሪኩለም አይተነዋል 3 ነው የሚለው፡፡ የእኛ 4 ነው የሚለው፡፡ ስለዚህ ሲኒየር
ኢሴይ ላይ አንዷን አጥፍተን ሁለት ክሬዲት አተረፍን ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ያን ምንድን ነው
ያደረግነው ግራጁየት ፕሮፋይል ላይ ያለውን ነገር ለማሟላት በ2 ክሬዲት ..... እንዲሰጥ ፍላጎቱም
ስላለን መውሰድም ስላለባቸው ያደረግነው ይሄን ነው፡፡ 001 ዲፓርትመንትን በሚመለከት፡፡ እንግዲህ
ተማሪዎቻችንን ታሳቢ እያደረግን መወያየት እንችላለን፡፡
ውብነሽ፡- ማብራሪያ ለመስጠት አይደለም፤ለሁሉም ለተነገሩት ነገሮች፡፡ እ ስህተት ነው
የተባለው ነገር ስህተት አይደለም፡፡ ወረቀት ነው ይገፍ የመጣሁት፤ ወረቀት ነው የሰጠሁት
ለመምህራን፡፡ እና ያወራነው ከዛ በኋላ ከወጣን በኋላ ..... ዲፓርትመንት ይስጥልን
ሊንጉስቲክስ ኮርስ፤አደም ታስታውሳለህ፡፡ ከዛን ጊዜ ጀምሮ ነው ይህን ሀሳብ ከተያዘ ጀምሮ ነው
እምነት ከሌለ ትልቁ ነገር፡፡ ትምህርት ክፍሉ ላይም አደም ታስታውሳለህ አንተም ላብ
ስላላቸው ነው፤ .....ም ላብ የለው፡፡ ዴሊቬሪው ላይ ነው ክፍተት ያደረጋችሁት፤ ስለዚህ
ይስተካከል ተባለ በዛው ነው የተለያየነው፡፡ ከዛ በኋላ በኮምፖዝሽን ላይ ስናየው ነው አስተያየት
የሰጠሁ፡፡ አደራው አስተያየት ሰጥቷል፤ ሁለቱን ብትጨፈልቁ፤የሚል ሃሳብ ሰጡ እንጂ
.....ን ት/ክፍል ትፈራላችሁ የሚል ነገር እኔ እንግዲህ እስከነበርኩ ድረስ አላስታውስም፡፡
ከወጣችሁ በኋላ ያንን አውርታችሁ ከሆነ አላቅም፡፡ ዞሮ ዞሮ ምንም የተሳሳተ መረጃ ይገፍ
ወደትምህርት ክፍሉ አልመጣሁም፡፡ አበበ መጀመሪያ ስትናገር ከካሪክለሙ ኤሲ ላይ ሲፀድቅ
አልክ፤ ኤሲ ላይ አልፀደቀም አልተነሳም፡፡
[አበበ፡- አልፀደቀም ገና?
ውብነሽ፡- አልፀደቀም፣
አበበ፡- ኤሲ ላይ ሳይፀድቅ ወደላይ አይላክም፤
ውብነሽ፡- አልፀደቀም፣አልተነሳም፡፡ ስብሰባ ጨርሰን ስንወጣ ዶር. አለባቸው ከወጣን በኋላ በር
ላይ ያን ካሪክለም ቶሎ በሉ ሲለው ሰምቻለሁ፤ ወደኋላ ቀርቼ ስለነበር፡፡ ኤሴ ላይ አልፀደቀም
ካሪክለሙ፡፡ ይሄንን ነው መናገር የምፈልገው፡፡
አበበ፡- አመሰግናለሁ፡፡ እስቲ ፋሲል እኔ ያልፀደቀ ካሪክለም ወደላይ አይሄድም፡፡
ፋሲል፡- ላቭ የሚለውን ነገር እናንሳና እዛው ጋ እንሂድ፡፡ ላብ ያስፈልገዋል ፕራክቲካል ፎነቲክስ
ብለን አላልንም፡፡ አሁን ውብነሽ ለዲፓርትመንቱ የሰጠቻቸው ካሪክለሙ ቁጭ ብሎ እያለ
ካሪክለሙን ኮፒ አድርገን ሰተን እያለ፤ ለዶር. አለባቸው እንዲያመቸው በሪፖርት መልክ
የተሰራውን ሪፖርት ነው ያመጣችው ዲፓርትመንት፡፡ ካሪኪለሙ ላይ ግን ከየት
ዲፓርትመንት ምን ያህል ሰዓት ሊሰጡልን እንደሚችሉ ሁሉ የተቀመጠ ነገር አለ፡፡ እሱን
እንግዲህ ምናልባት እንዴት እንዳላሳየቻቸው ሚስአንደርስታንዲግ የተፈጠረ በዚህ ነው፡፡
ሁለት ወረቀት ነው እዚህ ጋ እንትን ተደርጎ የተባለ፡፡ ካሪኩለማችንን አላሳየቻቸውም ሪፖርቱን
ነው እሷ ያሳየቻቸው፡፡
[አለማየሁ፡- እዚህ ጋ ይቅርታ ማስተካከያ?
ፋሲል፡- ሌላው ኤሲ ላይ የተባለው፡፡ ኤሲ ላይ ምንድን ነው ባለፈው ተብሎ የፀደቀው ኤሲ
ናምበሩ ስላለኝ ማለቴ ነው፤ በቤቱ የተሰጡ አስተያየቶች ተስተካክለው ለካሪክለምና ስታንዳርድ
ኮሚቴ ይላኩ ተብሎ ነው የፀደቀው፡፡
አበበ፡- እኔ በተሰበሰብኩበት ቀን?
ፋሲል፡- አዎ
ውብነሽ፡- አይደለም! አይደለም!
ፋሲል፡- አለ፣ አለ፡፡ አለ ካሪክለሙ ታድሷል፡፡ ስለዚህ ያኔ አፅድቀነዋል፤ አፅድቀነዋል፡፡
ካሪክለሙ እኔ በእጄ ላይ ስላለኝ፤አጀንዳው ማለቴ ነው አጀንዳው የዛኔ ስላለ በቤቱ የተነሱ
ማስተካካያዎች ተጨምረው ለካሪኩለምና ስታንዳርድ ኮሚቴ እንዲላክ ተስማምተናል ተብሎ

በአራት ነጥብ ተፅፏል። እሷም ነበረች የዛኔ በሁለተኛው ቀን ላይ እያንዳንዱ አጀንዳዎች አንድ
በአንድ እየተነሱ ዶር. አለባቸው እያነበበ ተስማምተናል፣ተስማምተናል፣ተስማምተናል አፅድቀን
ነው ያለፍን። ስለዚህ ያለው ሁኔታ ይሄ ነው ነበረች ተነስቷል።
አበበ፡- ኖርማሊ ግን ካሪክለም ሲፀድቅ በመጀመሪያ ይቀርባል በሚቀጥለው የዛ ኮሚቴዎች ቼክ
አድርገን ነው የምናፀድቀውና፣ ኮሜንት ከሌለበት ወይም ደግሞ በጣም ቀላል ኮሜንት ከሆነ
ብቻ ነው እንደዛ የሚደረገው። ግን እንደዛ አናደርግም ካሪክለም ላይ አናደርግም። ካሪክለም
በጣም ሲሪየስ ስለሆነ አናደርግም። ብዙ ነገሮች ናቸው የተነሱ ያኔ፣ እና እነዛን
ምክንያታቸውን ሳታዩ ነው ማለት ነው የፀደቀው።
ፋሲል፡- ለካሪኩለምና ስታንዳርድ ኮሚቴ እንዲላክ ተወስኗል አራት ነጥብ። የዛኔ ዶር. አለባቸው
ባለፈው ሳምንት አንተ የለህም።
አበበ፡- ቃለጉባዔውን እንግዲህ ቼክ ማድረግ ያለብኝ ይመስለኛል። ላ...ላስታውስም እ...
አገሬ፡- /
መለሰ፡- አንዳንደዜ እኮ ይቅርታ አድርግልኝና ቃለጉባኤ ሲፃፍም ስህተት ሊኖር ይችላል።
መንፈሱ ነው እንግዲህ ፋሲልን ይዞት ወይ እሷን ቅድም እንዳሰብነው ተፅፎ ሊሆን ይችላል።
ያ ግን አሁን በተባለው ከኢክስፒሪያንስ አኳያ አሁን ለውጥ ስለሆነ እንደገና መቶ መታየት
እንዳለበት ነው። እኔ አሁን ምንም ችግር ላይኖር ይችላል በካሪክለሙ ላይ ግን ፕሮሲጀራሊ
ስህተት ይፈጠራል ፕሮሲጀራሊ። ይሄ ግርማ ስብሰባውን የሚመራው የግርማ ስህተት ነው
ሊሆን የሚችለው እንጂ በዚህ መንገድ አይሄድም ቀደም ሲል ፋሲል ኤክስፒሪያንሱን አሁን
አደም እንደሚነግርህ ነው። ኤኒ ዌይ ችግር አይደለም እሱ እዛ ውስጥ ካለው ነገር ላይ
ተስማማ፤ የአካሄዱ ጉዳይ ብዙም የሚያጨቃጭቅ አይደለም።
አገሬ፡- /
አለማየሁ፡- ኦኬ፣ ሪፖርቱ ላይ በተወሰነ መልኩ ክፍተት አለበት። ማለት ሊንጉስቲክ ኤንድ
ፕራክቲካል ፎነቲክስ የሚለው ኮርስ ሪፖርቱ ላይ ሲፃፍ ከ..... ዲፓርትመንት የሚመጡ
መምህራን እንዲሰጡት ተብሎ ነው። ካሪክለሙ ላይ ግን በሊንጉስቲክ ባለሙያ ነው የሚለው።
ስለዚህ ይሄ መጣረስ ስለነበረበት የተነሳው አስተያየት ጥሩ ነበረ። ይህን የመሰለ ክፍተት
የተፈጠረው በዚህ ምክንያት ይመስለኛል። በተደረገው ማስተካከያ ግን ተስተካክሏል።
አበበ፡- ጥሩ ነው። ኤሲ ላይም ኮሜንት ተሰቷቸዋል ይህን((×××))
አገሬ፡- /
ደበበ፡- እኔ እንትን የማደርገው ምንድን ነው፣ ውብነሽ የሰጠችን ዶክመንቱን ነው። ይሄ
የተባለው ሪፖርቱ። የሚከተሉትን ኮርሶች የሚመለከታቸው ትምህርት ክፍሎች እንዲሰጡት
ሃሳብ እናቀርባለን አይነት ነገር ነው ያለው። ስለዚህ እዛ ላይ ያለውን ስናይ ነው እንግዲህ
የእኛ እንትን የተናገርነው። ሌላ ፋሲልን አነጋግሬዋለሁ። ዋት ዩ ግራንድ ..... ኤንድ
ሳይኮሎጂ የሚለው..ኤዲቲንግ የሚለው እንደዚህ እንደዚህ አይነት ነገሮች እዛ ውስጥ ምን
ያህል ነው ያሉት ምን ያህል ነው? ስታት ፎር ኢኮኖሚክስ ተብሎ እኮ ይሰጣል። ስታት ፎር፣
ስታስቲክስ ዲፓርትመንት አለ።ግን ስታት ፎር ተብሎ ማነው የሚሰጠው ራሱ ኢኮኖሚክስ።
ስለዚህ ይሄ ሁሉ እያለ ..... ኤንድ ሳይኮሎጂ ካለ ስለማነው የሚያነሳው? የሳኮሎጂ ፓር
ቱ ምን ያህል ነው? ይህን ሁሉ አንስተን ተነጋግረናል። እና ከእኛ እንትን ያረገው ምንድ ነው
ይኸ ነገር። አንደኛ ካሪክለም ሲቀረፅ የሚመለከታቸው ክፍሎች ኮንሳልት ይደረጋል። ለምሳሌ
.....ን ክሪቲካል የሚለው የ..... ኮርስ ሲገባ .....ን ማነጋገርና ከዛም መረጃ መውሰድ። .....ም ካለ
የሚመለከተው ካለ ያን እንዲህ እየተደረገ ነው የሚሆነው የሚመስለኝ፤ ካሪክለም ሲቀረፅ ይሄ እንትን
አለ። እና እዚህ ላይ ነው እንግዲህ ትልቁ እንትን። አንደኛ ኢንፎርሜሽኑ የለንም፤ አሁን እንደተባለ
ያንን አገኘን እኛ። ሌላው ፋሲል ሲነግረኝ ከዚህ ይህን ያህል እንትን ሳይኮሎጂ ብቻ ግን ይገባል።
እ..የዚህን ሎጅክ የሚለው የሲቪክስ ይኸ ብቻ ይገባል ይላል። ያ ሪፖርት ግን ያን አይልም።
አለማየሁ እንዳለው ነው። አለማየሁ ያለው ድፍን ያለ ነገር ስለሆነ ምን ማለት ነው የሚለው ነው።
..... ራሱ ሊንጉስቲክስ ኤንድ ፎነቲክስ የሚለው ኮርስ አለ ..... እንዲሰጡልን ይላል።
ለመሆኑ ሊንጉስቲክስ ያለው የት ነው ያለው? ሊንጉስቲክስ ያለው የት ነው? በእንትን ደረጃ እኮ
ያለበት በቼርፐርሰን ያለበት የት ነው? ማነው ሊሰጠው የሚችለው? ላብራቶሪ እኮ አይ ሲቲ

ሲስጥ አይ ሲ ቲ ያለው እዛ ነው ነገር ግን እዚ መቶ በሌላ ሰው ይሰጣል፡፡ ላቦራቶሪዎችን
በጋራ ካለን ማለት ነው በጋራ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ እንጠቀማለን የሚደረግ ስለሆነ፡፡ ስለዚህ
ያንን ቢሆን ላቦራቶሪ የለውም ተብሎ እዛ ከሚሆን መጀመሪያ ኢንፎርሜሽኑ ቢኖር ኖሮ ይሽን
ሁሉ አይሆንም ነበር፡፡ እና አንዱ ትልቁ ፋሲል በውብነሽ አንትን አደረገ እንጂ የእነሱ
የራሳችሁ ሪፖርት ነው፡፡ አንተም አይተኸዋል፡፡ አይደል? እዛ ላይ የሚሰጡልን እነማን ናቸው
የሚለው ግልፅ እኮ...እዛ ላይ ታዲያ የሰፈረው እዛው ውስጥ ካሪክለሙ ውስጥ እንዲህ
ተገልጿል ቢባል ይሄኛውስ፡፡ በዚህ አንባር ነው እንግዲህ ለመነጋገር እንትን ያልነው፡፡ ፋሲል
ጋር ግልፅ ሆኘ ተነጋግሬያለሁ፡፡ እኛ እኮ አንደኛ 70/30 ችግር እያመጣብን ነው፤ በየትኛውም
ሶሻል ሳይንስ፣ እርስ በርሳችን ተደጋግፈን፣ተደጋግፈን ዲፓርትመንቶቹን ሁለቱንም ማጠናከር
ሲገባን እንዲህ አይነቱ ክፍተት መስጠት፣ እኔ ነኝ ራሱ ይህን ተናግሬያለሁ ወደውጭ አሳልፎ
መስጠት ከፋካሊቲው ውጭ መስጠት ለምን ይገባል? እንዲያው ይሄን እኮ አስቡበት ነው
ያልኩ፡፡ እንዲህ ይሆናል ይሄን አድርጉ አልወጣኝም፤ አስቡበት፡፡ ምክንያቱም ለምሳሌ 001
ሊዘጋ ቢል ሙያ ያላቸው እዛ ውስጥ ሊያስተምሩ የሚችሉ ሰዎች አሉ፡፡ 002 ቢዘጋ
እዚህ ውስጥ ያሉ ስታፍ 001 ውስጥ ሊሰሩበት የሚችሉበት ሁኔታ አለ፡፡ ተደጋግፈን
አንደኛ ራሳችን ሰኪዩርድ መሆን፣ሁለተኛ ካሪክለማችን ማጠናከር፣ እሱን ስናጠናክር ሙሉ
አንድ አይነት ሃሳብ አንድ አይነት ፍላጎት ሲኖር፣ ምናልባት ችግር ካለ ከ001፣ ምናልባት
ከ002 ችግር ካለ፣ እ እየተነጋገሩ ያንን እያጠፉ መጠናከር ነው የሚሻል የሚመስለኝ፡፡ እና
በዚህ አንባር ብንሄድ ነው፡፡ እና ውብነሽ አሳስታለች፣ አይደለም ያ ራሱ ወረቀቱ ነው እንትን
ያረገ፣ የ002 ማጠቃለያ ተብሎ የተሰጠው ያ አሳስቷል፡፡ ስለዚህ ውብነሽ እንትን አላረገችም፡፡
ያንኑ ነው ያየነው፡፡ እና በዚህ አንባር ብትቀበሉ ጥሩ ነው፡፡
ፋሲል፡- [እዚህ ጋ ማስተካከያ ስላለኝ ነው፡፡ እዚህ ጋ ማስተካከያ ስላለኝ ነው፡፡
አበበ፡- አንተ ብዙ ስለተናገርክ በኋላ እሰጥሃለሁ፤ እሰጥሃለሁ ችግር የለም፡፡
አገሬ፡- /
ከበደ፡- ይሄ ካሪክለም ከቀረፁት ውስጥ አንዱ እኔ ነኝ፡፡ መጀመሪያ ጥናት አድርገን ነው
የቀረፅነው ጎንደርም፡ እና በኋላ ደግሞ በአገር አቀፍ ደረጃ ነው ካሪክለሙ የተሰራው፡፡ በተለይም
እና ለምን ለውጥ ተካሄደ፣ ተቃውሞ የለኝም ግን ለውጡ ቢያንስ ጥናት ተደርጎበት፣ ኦፒኒየን
ተሰብስቦ ቢሆን መልካም ይመስለኛል እንዲሁ በዘፈቀደ ሳይሆን፡፡ አንዳንድ ኮሜንት አሁን ያለ
ይመስለኛል፤ ለምሳሌ ፕሮፋይል ላይ ለምሳሌ ፓብሊክ ርሌሽን ኦፊሰር የማይሆንበት ምክንያት
የለም፡፡ እኔ የትምህርት ክፍሉንም የማስተዋወቅ ስራም ሰርቻለሁኝ፤ በዛን ሰዓት ንባብ
እንዲያውም አድርጌያለሁ ፑቲንግ ..... የሚለውን መፅሀፍ አንብብ፤ እዛ ጋ በስነስርዓት
....ፓብሊክ ርሌሽን ኦፊሰር ሆኖ ማገልገል ይችላል፡፡ በተለይ በባህል ሙያ፣ ስለዚህ እዛ
ጋ የምናስወጣበት ምክንያት አይታየኝም፡፡ እንዲውም ስንጠራ አንዱ ከባህል ነው የሚጠሩ ያሉ
ያንን ምክንያት በማድረግ በማለት ነው፡፡ ሜድሲን ውስጥ፣ ላይብረሪ ውስጥ የማይገቡበት ቦታ
የለም፡፡ ያ ፕሮፋይል አለ፡፡ ሁለተኛ ኮርሶች ከመቀናነሱ ላይ ተቃውሞ የለኝም፡፡ ከተሰበሰበ ግን
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ላይ ያረገው ምንድን ነው እኔም ጥያቄ አንስቻለሁ፡፡ ለምሳሌ ኦራል
ናሬቲቭ ዋን፣ ኦራል ናሬቲቭ ቱ አለ እንደዚሁም ደግሞ ፕሮቨርብ ላይ ፕሮቨርብ ዋን፣
ፕሮቨርብ ቱ የሚል አይነት ነገር ነበር፡፡ እና እዛ ጋ በቂ ያሰራል ወይ እዚህ መከፋፈሉ አግባብ
ነው፤ እንዲያውም ክሬዲቱን ለመቀነስ ሞክረናል እዛ ላይ፡፡ እና ችግራችን አሁን እኔ እዚህ ጋ
የምጠራጠረው ምንድን ነው አስፍቶ ከማንበብ የመጣ ችግር እንዳይሆን እጠራጠራለሁ፡፡ ለምን
ኢንተርዲስፕሊነሪ ናቸው፡፡ .....ም .....ም በባህሪያቸው፡፡ ስለዚህ አሁን ..... ኤንድ
ሳይኮሎጂ የሚለው ላይ ስንመጣ የ..... ሰው ሳይኮሎጂ ማንበብ ግዴታው
ነው፡፡...በሳይኮሎጂው በኩል ያለውን አስፍቶ ማንበብ አግባብ ነው፡፡ ያለበለዚያ የሳይኮሎጂው
ሰው ሲይዘው ....ን ደግሞ ይዘነገዋል፡፡ ...ነገሩ ውስጥ አለ እኮ ..... ኤንድ ሳይኮሎጂ
የሚለው ነገር አለ፡፡ ስለዚህ ይሄ ይሄ ቅሬታ ፈጥሮብኝ ስለነበር እኔ በቀጥታ ሰለሞንን
አናግሬዋለሁ፤ የሰጠውም መልስ ጥሩ ነው፡፡ ኖ ገስት ነው የምንጋብዘው ሰዓት መጥነን አንድ
ሰዓት፣ ሁለት ሰዓት ወስነን እዛ ላይ ነው እንትን የሚያደርገው እንጂ ኮርሱ የእኛው ነው
በሚለው መንፈስ የተግባባን ይመስለኛል፡፡ እና....ከሆነ መጥፎ አይደለም፤ ኮርሱን ግን አሳልፈን

የምንሰጥበት ምክንያት አይታየኝም። ለምን እኛ ነን ተደራጅተን ንባብ ማድረግ የሚገባን የሚል እምነት አለኝ። ክሪቲካል ቲንኪንግ ላይም በተመሳሳይ ሎጆኮች አይደሉም..ትልቁ ፕሮብለም እንደአገር እንደዜጋ አይደለም የምናስበው የኮርስ ጥቅም ነው የምናስበው። ስለዚህ የሳይኮሎጂው ሰው የእኛ ነው ይላል፣ የሎጂኩ ሰው የእኛ ነው ይላል፤ እሱ ጥቅሙን ነዋ የሚያስበው። ነገር ግን አሁን ክሪቲካል ቲንኪግ፡ ያ ቲዌሪ ነው መነፀር ነው የምናይበት ነው ነገሮችን። ስለዚህ ኦራል ኃ ከሄድን ናሬቲቭ ውስጥም ስንገባ እነዛ ዲስኮርሶች ናቸው፣ እነዛን ዲስኮርሶች የምናይበት መነፅር ነው። ስለዚህ እናንት ረሳችሁ ልታነቡት ልታሰፉት የምትችሉት ነገር አለ። ገስት መጋበዙ አግባብ ሊሆን ይችላል በአንድ ሰው ከሚማሩ ልጆቹ በሁለት ሶስት ሰው ቢማሩ እንግዳ ቢኖር ጥሩ ነው። ግን ኮርሱን አሳልፈን የምንሰጥበት ምክንያት አልታየኝም። እና ሊንጉስቲክስ ላይ ምናልባት መጨመር የምፈልገው አላቅም መጨረሻ ላይ ምን አይነት ስምምነት ላይ እንደተደረሰ፣ ልጆቹ የሚማሩት በ..... ይመስለኛል፤ ሚዲያቸው በ..... ነው። ስለዚህ ሊንጉስቲክስ በተለይም ወደ.....ው ሊንጉስቲክስ የምንመጣ ይመስለኛል። ላቭ መኖሩ ጥሩ ነው። ላቭ የሚኖር ከሆነ፣ አለ ለመሆኑ እኛ ኃ? ላቭ የለም፣ ላቭ ከሌለ ትርጉም ያለው አይመስለኝም። ..... ስለዚህ የምንቀራረበውን ነገር ተቀራርቦ መስራት ነው የሚሻለው። ለምን ኮንሰስ አላደረጉም? ለምን አልተመካከረንም? ነው እኔ ያልኩት። እኔ በመሰረቱ የሁለተኛውን አጀንዳ ያስጨመርኩበት ምክንያት .....ና ..... ልዩነት፣ ልዩነት የለውም ነው። አሁን ፕሮግራም ለማጥፋት ሲባል አርቲፊሻል መከፋፈል ላይ ልዩነት የለውም ባይ ነኝ። ስለዚህ በመካከላችን ቅሬታ ካሉ እነሱን አስወግደን እየተግባባን የምናድግበትን መንገድ ነው፣ ሌላ ፕሮግራም የምንቀርፅበትን ነገር ነው ማሰብ ያለብን የሚል እምነት አለኝ። እዛ ኃ ስደርስ እናገራለሁ።

አበበ፡- አቶ አስናቀ

አስናቀ፡-((xxx)) (እንዲናገር ቢጠየቅም መናገር እንደማይፈልግ በድምፅና በጭንቅላቱ መናገር እንደማይፈልግ ገለፀ)

አበበ፡- ያልተባለ ነገር ነው? (ጥያቄው ለአገሬ ነው ለመናገር እጁን በማውጣቷ)

አገሬ፡- አቶ አስናቀ ሲገልፅ አገሬ ያልተባለ ሀሳብ ነው ወይ ከተባለ ጊዜ አታጥፊ በሚል አይነት ስሜት እድሉን እፈልጋለሁ በማለቷ ተናገረች።

እሸ። ከጋሸ ከበደ ጋር ነው ሀሳቤ የሚስማማ። በተለይ እነዚህ ሳይኮሎጂ ክሪቲካል ቲንኪግ ኤንድ ቴክስት አናሊስስ ኮርሶችን ሌሎች በሌላ ዲፓርትመንት ሰዎች እንዲሰጡ ከማድረግ የእኛ ዲፓርትመንት ሰዎች ወይም ..... ውስጥ ያሉት ራሳቸው፣ እኔ አሁን ..... ኤንድ ሳይኮሎጂ የሚለውን ..... ስትሰጥ አይቻለሁ። ሙሉውን ኮርስ እሷ ነበረች የሸፈነችው ግን ገስት አድርጋ ጋብዛለች ከሳይኮሎጂ ትምህርት ክፍል። እናእንደዛ አድርጎ ማስቀመጡ አንደኛ እንትን ይላል፣ በጣም መምህሩንም ወደሌላ ሽፍት እንዲያደርግ ብዙ እንዳያነብ ያደርገዋል። ይህንን ነገር ማለት እና የሳይኮሎጂ እውቀት የቋንቋም፣ የ.....ም፣የፎክለርም መምህራን ሊኖራቸው ይገባል። ቢያንስ ለማስተማር ያህል ከሊትሬቸሩ ጋር እንዲሁም ከ..... ጋርም ቢሆን። ክሪቲካል ቲንኪንግ ኤንድ ቴክስት አናሊስስንም በተመሳሳይ መልኩ እኛ የማንሰጥበት ምክንያት የለም እያልኩ ነው። ወደሌላ ዲፓርትመንት መሄድ የለበትም። ከዛ ውጭ አሁን የሪፖርቱም ነገር ላይ የካሪክለሙ ነፀብራቅ ስለሆነ ሪፖርቱ ያ ነው ወደስህተት የመራው ነገር እዛ ኃ ነው፣ፋሲልም ትንሽ፡ ብየ ነው የማስበው። ምክንያቱም ካሪክለሙ የሚለው ሌላ ከሆነና ሪፖርቱ የሚለው ሌላ ከሆነ አሁንም መጣረስ አለ ማለት ነው። እዛ ኃ መስተካከል ያለበት ነገር አለ፤ በዚህ ከተስማማን

አበበ፡- ቆይ ይሰጣችኋል ችግር የለም። እ፡ ያው የሚነሱ ነገሮች ጥሩ ናቸው።ስለዚህ ..... ኤንድ ሳይኮሎጂ ክሪቲካል ቲንኪንግ የሚባሉ ኮርሶች ለእኛ በእኛ ይሰጡ ምናምን ነገር የሚባለው የኮርስ ባለቤትነት ጥያቄዎች ለምን እንደተነሱ እኔ ልንገራችሁ። እነፋሲልም አይደሉ ያነሷቸው እነዚህን ጥያቄዎች እነፋሲልም አይደሉም ያነሷቸው እነዚህን ጥያቄዎች ፎር ዛት ማተር። የሞጁላር ካሪክለም ሪቫይዝድ ሲደረግ ላስት ይር እላይ ሲፀድቅ ነው፣ ካሪክለም ኤንድ ስታንዳርድ ኮሚቴ ላይ ሲፀድቅ ለመሆኑ ..... ኤንድ ሳይኮሎጂ ማነው የሚያስተምርላችሁ ብሎ ብሄቬራል ሳይንስ ይጠይቃል። ክሪቲካል ቲንኪንግ እንደዚሁስ ማነው የሚስጠው ተብሎ

ተጠየቀ፡፡ እስከዛሬ ድረስማ የሚሰጠው ራሱ ፋካሊቲው ነው ተብሎ ተመለሰለት፡፡ እና ሊሆን
አይችልም ተብሎ ነው እዛ ላይ ተነስቶ የነበረው፡፡ በባለሙያ መሰጠት አለበት፡፡ ያ ጥያቄ ነው
ወደነፋሲል እንዲወርድ የተደረገው፡፡ እና ካሪክለሙ ሲታይ በተለይ ሳይኮሎጂዎች
እንዳስቀመጡት ኮንቴንቱ ሳይኮሎጂ ሳይኮሎጂ ነው የሚሸተው፤ እዛ ላይ ካሪክለሙ የሰፈረው
ማለት ነው፡፡ .... መሸተት ሲገባው ሳይኮሎጂ ሳይኮሎጂ ይሸታል፡፡ ክሪቲካል
ቲንኪንግም እንደዚሁ ለምን ወደቋንቋ ክሪቲካል ቲንክንግን ለምን አታመጡትም? ዋይ
ወደሎጅክ ታመጡታላችሁ ካሪክለም ስትቀርፁ የሚል ጥያቄ በኋላ ተነሳና፣ ካሪክለሙ ሪቫይዝድ
ሲቀረፅ ይሽን ነገር ማስቀረት መቻል አለበት፡፡ ከዛ ላይ የተዘረዘረው ኮንቴንቱ ፒዩርሲ ሳይኮሎጂ
ከሆነ ሳይኮሎጂ ክሌም ማድረጉ ትክክል ነበር ማለት ነው፡፡ የእኛ ተማሪዎች ሳይኮሎጂን
ለምንድነው የሚማሩት፣ ክሪቲካል ቲንኪንግ ለምንድነው የሚማሩት የሚለው ነገር ተመልሶ
.... በሚሸት መልኩ ሪቫይዝድ እንዲደረግ፡፡ አይ ቲንክ አሁን ያደረጉት ያንን ነው፡፡
ለዛም ነው አሁን እንጋብዛለን ወደሚል የመጣ ማለት ነው፡፡ የድሮው ኮንቴንት ኮንቴንቱ
ሲታይ በቃ በሙሉ ወደዚያ ነው የሚሄደው፡፡ ይሄማ አይሆንም እኛ ነን ማስተማር ያለብን
አሉ፡፡ አንድ ኮርስ ስለወሰደ እኮ አንድ ሰው፣አንድ የሳይኮሎጂ አንድ ሁለት ኮርስ ስለወሰደ
ማስተማር የለበትም፡፡ ምክንያቱም ባለሙያዎች ስላሉ የተሻለ ኮርሱን የሚያውቁት ስላሉ፡፡
የሚል ጥያቄ እዛ ላይ ተነሳና ካሪክለሙን እንደገና የመዳሰስ ነገር እንዲታይና ወደ.....
እንዲጠጋ፣ ሌሎች ኮርሶችም እንደዚሁ ቴክኒካል የሆኑ ኮርሶች ለምሳሌ የጆርናሊዝም
የሚመስሉ ሁሉ ኮርሶች መሆን ያልነበረባቸው ካሪክለሙ ግን ያንን ሪያሊቲ የሚያሳይ፡፡ እና
እነዚህ ነገሮች ፖሊሽ አድርጋችሁ ወደ..... አስጠጉ የሚል ሊሆን የባለቤትነት ጥያቄ እየሰፋ
እየሄደ ነው፡፡ ስለዚህ ጫናው የመጣባቸው ከላይ ነው፡፡ በዛ መሰረት ግን አሁን እየተስተካከለ
የመጣ ነው እንጅ የማስወጣት ስራ አልሰሩም እንዲያውም ማለት ነው፡፡ እሽ
ፋሲል፡- እኔ አሁን፡ ያመጣሁት ከምንድን ነው፣በጋራ መስራት ካለብን በግልፅ መነጋገር ስላለብን
ማለት ነው፤አሁን ለምንድ ነው ነጥቦቹን ብቻ የሰጠቻቸው የሚለው ምንድን ነው ሁለቱን
የ..... ካሪክለም ላይ ያለው ኮርስ ዛት ገስት ሌክቸር ብለን የካሪክለሙ አካል ነው
ያደረግነው በሰዓት ሁሉ ከፍለን፡፡ ለምሳሌ ክሪቲካል ቲንኪንግ የሚለውን ..... ኤንድ ቴክስት
ኣናሊስስ ብለነዋል፡፡ ቢጨንቀን ነው እንደዛ ያደረግነው ወደ..... ለማምጣት፡፡ ስለዚህ አሁን
ሁለት ሰዓት ኢንተርናል ገስት ሌክቸር እንጋብዛለን እያልን ነው፡፡ ለምን እዚህ ላይ ሎጅክ
የተወሰነ አለ፡፡ ያንን ሀቅ መካድ የለብንም፡፡ ስለዚህ ሁለት ሰዓት ብንጋብዛቸው፤ እኛ
ተማሪዎቻችንን ነው መሰረት የምናደርገው፡፡ እና እኔ ውብነሽ ጋ ችግር ያለኝ ምንድን ነው ይሄ
ሌሎቻችሁ እንድትረዱኝ የምፈልገው ይሄም አብሮ ኮፒ ተደርጎ ካሪክለሙ ለሁሉም ተሰጧል፤
አደም ጋር እንደሚኖር ምንም ጥያቄ፣ እንደሚኖር ምንም ጥያቄ የለኝም፡፡ በሰዓት ሁሉ
ከፍለናል፤ያን ያላሳየቻቸው ልምንድን ነው? አማረኛው ላይ ያለውን ሪፖርቱ ላይ እንደወጡ
ያሳያል ኮርሶች፡፡ ለምንድን ነው እኛ ለምንድን ነው የምንለቃቸው ኮርሶችን? አሁን አደም
እንዳለው እንትኖችን .... እንዲሸት የማድረግ፣ ወደእኛ የማምጣት ነው የሰራነው፡፡
ክሪያሊቲው መውጣት ስለማንችል ሁለት ሰኣት እንጋብዛለን ብለን ይህንን የካሪክለሙ አካል
ይሁን ብለን ነው ያስቀመጥነው፡፡ ..... ኤድ ሳይኮሎጂ ሶስት ሰዓት እንዲያስተምሩልን
ሳይኮሎጂ ዲፓርትመንቶችን እንጋብዛለን፡፡ ይሄንም የካሪክለሙ አካል አድርገነዋል፡፡ ይሄን
ውብነሽ ታውቃለች፡፡ ..... ካልቸር ኤንድ ማስሚዲያ ከጆርናሊዝም የመጣ ነው፣ እና
ያልተነሱትም አርካይቭ ኤንድ ሚሶሎጂ ሁለት ሰዓት ኤክስተርናል የሆነ ሰው ምናምን ነገር
በሙያው ልምድ ያለው ሰው ምናምን ነገር ይጋብዛል፡፡ ስለዚህ ሰዓቶችን ሁሉ ሊስት አውት
አድርገን የካሪክለሙ አካል እንዲሆኑ ነው ያደረግነው፡፡ ስለዚህ አሁን እኔ ምንድነው ጋሽ ከበደ
ያለውን እቀበላለሁ እስማማለሁ፤ ጋሽ ደበበ ያለውንም እቀበላለሁ ከሌሎቻችሁም በተመሳሳይ፡፡
ኮርሶች እንዲወጡ አላደረግንም፡፡ ለዚህ ነው ሌላ በሆነ መንገድ ውብነሽ ነው የነገረቻችሁ
የሚለውን ነገር የምለው፡፡
¯ [አበበ፡-ከሁለት አንድ መሆን ስላለበት ነው፡፡
_ [ከበደ፡- ለነገሩ((xxx))
ፋሲል፡- ማጠቃለያው ምንድነው፣ ማጠቃለያው ምንድን ነው፣ ኮርሶች አንዲወጡ ለማድረግ

ሳይሆን ኮርሶች ወደእኛ እንዲቀሩ የማድረግ ስራ ነው የሰራነው። ከ001ዶች ለማራቅ አይደለም
ለማቅረብ ነው።
[ደበበ፡- ማስተካከያ፣
አበበ፡- አይ ችግር የለም። እናስተካክለዋለን። አንደኛ አይድያ ነው እዚህ
የምናሸራሽረው፤ፐርሰናል የሆኑ ውብነሽንና ፋሲልን ማከራከር አይደለም። አይዲያዎችን
አምጥተን እየተወያየን ነው፤ እና ተጨባጭ የሆነ መረጃ አምጥተው እንትን ብለዋቸዋል። ይሄ
ነገር አይበጅም ይስተካከል በለዋችኋል። ይሄንን እኛም ነግረናችኋል አለማየሁ። በቃ መቀበል
ያለብንን እንቀበል ችግር የለውም። ስራው ላይ ከተስተካከለ ትልቅ ነገር ያ ነው። በቃ ሪፖርቱ
ላይ ተሳስቶ ካወራ ምንም አለ ኮሜንትም ተሰጠበት ይሄንን አስተካክል ሲባል ከተስተካከለ ችግር
የለውምና። አሁን ተስተካክሏል ስለሆነ በዚህ እንየው።
[ፋሲል፡- ሁለቱም ኮፒ አድርገን ነው የሰጠነው። ለምንድን ነው አንዱን ብቻ የሰጠችው ነው?
አበበ፡- አንከራከር አልተስተካከለም፤ ኤሲ ላይ የምናደርገው እኮ...
ፋሲል፡- አይደለም፣ አይደለም አሁንም አልተረዳሽኝም፤ ወደሊንኮስቲክስ ነው የወሰድከው።
ሊንኮስቲክስን ምንድን ነው ሪፖርት ላይ ነው። ካሪክለማችን ላይ...
ተሰብሳቢው፡- (አብዛኛው በአንድ ላይ በመደራረብ ተንጫጩ)
መለሰ፡- ይሁን ብንተወው። ከተሳሳተ ያኛው ደህና ከሆነ በቃ እንተወው
አበበ፡- በዛኛው እንዲስተካከል ተደርጓል፤ ተስተካክሏል ምንም ችግር የለውም እሱ።
ፋሲል፡- ለግንዛቤ ግን ሁለቱንም ወረቀቶች ልትሰጣቸው ይገባ ነበር...
ተሰብሳቢው፡- (አሁንም በአንድ ላይ የየራሳቸውን ተናገሩ ጫጫት) ከዚህ ውስጥ ድምፁን
ጎላ አድርጎ ደበበ እድል ሳይሰጠው ተናገረ
ደበበ፡- ሁለቱም ወረቀቶች ተሰጥተውናል ሁለቱም ሰታኛለች። አይተነዋል፤ ስናይ ግን የነበረብን
ጊዜ አለ። የራሴን ነው የምናገረው። ባለኝ ጊዜ ዋናውን አጠቃላይ ሪፖርት ነው ያየሁት።
አጠቃላይ ሪፖርቱ ላይ ስህተት የለም ከተባለ ይሄ ነው። እና ሁለት እንትን የያዘ ቅድም እኮ
አለማየሁ ያነሳው ነው። ስለዚህ ይሽንን ተስተካክሏል የውብነሽም ችግር አይደለም የእኛ
የአባላቱ የእያንዳንዱ ነው ሁለቱም ደርሶናል። ግን ያኛው ነው ያሳሳተን ስለዚህ ይሽ አሁን
ተስተካክሏል ወደዚህ ባንመለስ...
አበበ፡- አለማየሁ እኮ ነግሮናል፣ በቃ ተስተካክሏል ብለናል። ውብነሽም ሳትሆን ኤሲ ላይ
ተነግሯል። እንጅ ቅድም የተነገረው ማስተሩን ፕሮግራም ማነው የሚያስተዳድረው የሚለው
ጥያቄ ሁላ ነበር። እና ምንም ችግር የለውም ዙሮ ዙሮ መስተካከሉ ነው ዋናው
[አለሙ፡- እንደማሳሰቢያ ቅድም አሁን ካሪክለም የሚያፀድቀው ክፍል?
አበበ፡- የካሪክለም ኮሚቴ
አለሙ፡- የካሪክለም ኮሚቴው የጥያቄው አነሳስ መንፈስ አልገባኝም። ራሱ አንድ የሆነ ነገር ያለ
ይመስለኛል። ይህን ኮርስ የሚያስተምርላችሁ ማነው ብሎ ነገር መጠየቅ ያለበት አይመስለኝም።
ይሄ ኮርስ አፕሮፕሬት ነው ወይስ አይደለም የሚል እንጅ፤በቃ ማን ያስተምርልህ ብሎ ነገር፤
ይህን ኮርስ ለምን ፈለጋችሁት? ለምንድነው ከዲፓርትመንቱ ጋር የገባው? ፕሮፋይሉና ኮርሱ
አይመሳሰሉም። ይህን ነው መተቸት ያለበት። ያ ካሪክለም ኮሚቴ እዚህ ጋ ፕሮፋይሉን
ይይዛል፣ ይሄ ኮርስ እንዲህ ይላል ያፈነገጠ ነገር አለ የሚል እንጅ፤ አስተማሪ የመመደብ
አለመመደብ የዛ ኮሚቴ ስራ አይመስለኝም። እና አንዳንዴ ዲፓርትመንት መኖር አለበት ብዬ
የምከራከረው አንዳንዴ ዲፓርትመንቶች ውክልና በሌለባቸው ቦታ ላይ ሚስአንደርስቱድ የመሆን
ችግር እየተፈጠረ ያልሆነ አሁን በእኛም በማስተርስ ፕሮግራም ላይ እየተፈጠረ ያለ ችግር ስላለ
ነው ይህን የማነሳው። እ ሳይኮሎጂ የሌለበት የሊንኮስቲክስ እንትን የለም። ሎጅክ የሌለበት
ትምህርት እኔ አላውቅም ሎጂካሊ ነው ሁሉም ነገር፤ እና ክሪቲካል ቲንኪንግ ኤንድ ቴክስት
አናሊስስ ስለተባለ ብቻ ሎጅክ እኔ ባለሙያ ስለሆንኩ እኔ ላስተምር ብሎ፡ አይገባኝም እኔ
ስፈልገው ብቻ ነው፤ የአፕልኬሽን ጉዳይ ነው እዚህ ጋ። እና እያንዳንዱ ኮርስ ላይ የሎጅክ ነገር
ሊመጣ ይችላል፤ የሳይኮሎጂ ነገር ሊመጣ ይችላል። አሁን ከእኛ ማስተርስ ፕሮግራም ላይ
ቲዌሪ ኦፍ ላንጉጅ ለርኒግ የሚል አለ፣ ቲዌሪ ኦፍ ለርኒግ የሚል እዛ ጋ የሳይኮሎጂ ሰዎች
ባለሙያዎች የሚሰጡት ጉዳይ አለ። እኛ ደግሞ በአፕሌክሽኑ ቴዌሪ ኦፍ ላንጌጅ ለርንግ ብለን

እንሰራበታለን ስንሰራበት ነው የኖርነው። ይህንን ኮርስ አሁን ቢሰሙ ቀምተው ነው
የሚወስዱት። እና እንደዚህ መሆን ያለበት አይመስለኝም። ዲፓርትመንቱ ዲዛይን ሲያደርግ
ፕሮፋይል ያዘጋጃል፤ ለዛ ፕሮፋይል ነገር አቅርቦ ነው። ርዳታ ሲፈልግ እገሌ ድረስ ብሎ
ይጠራል። አለቆቻችን፡ መስራት ያለባቸው ይመስለኛል። በአጋጣሚ ይሄ የሳይኮሎጂ ሰው
ስለሆንኩ እዛ ባለኝ በተሰጠኝ ባጋጣሚ ባገኘኋት ቦታ ላይ ሆኜ አይ ይቺማ ወደእኛ
ዲፓርትመንት ትሂድ ማለት ያለብኝ አይመስለኝም። አለቃ ስንሆን የሁሉንም በተመሳሳይ
ሁኔታ መዳኘት መታሰብ ያለበት ይመስለኛል። ያው እግረ መንገድክን ኮሜንት መደረግ ያለበት
ጉዳይ ነው። ይሽን ኮርስ ማን ያስተምርላችኋል የሚለው ጥያቄ አፕሮፕሬት ጥያቄ እይደለም
በመሰረቱ ካሪክለም ሲቀረፅ በቃ። ማየት ያለባቸው ዶክሜንቱን ነው። ፕሮፋይሉን ነው
ምናምኑን ነው ያንን ይመስለኛል። ኮዱ በትክክል በዩኒቨርሲቲው ((×××))መልኩ ኮድ ተደርጓል
ወይ፣ ዲስክሪፕሽኑ በሙሉ ተሰርቷል ምናምን ያንን ያንን ነው።
አበበ፡- እ ጥሩ የኮርስ ባለቤትነት ጥያቄ እዚህ ላይ አናነሳውም በሰፊው ማለት ነው። እንጂ
በጣም አወዛጋቢ ኢሹ ባይ ዘ ወይ ለካሪክለም ኮሚቴ በጣም ራስ ምታት የሆነ ጉዳይ ነው።
ኤክሰፐት .... ኮርስ ውጭ ያሉ ኮርሶች በዩኒቨርሲቲው የሚሰጡ በብዛት ሲቃሙ
ይታያሉ። ስታትን ማንም ሰው ሲያስተምረው፡ የባለቤትነት ጥያቄ በጣም ስር የሰደደ ችግር ነው
በዩኒቨርሲቲው። ያም በመሆኑ ግን አለው ሪሊ አንተ ሪፍሌክት ባደረከው ጎኑ ብቻ አይደለም
የሚታየው አክቿሊ ማለት ነው። አግባብ ባልሆነ ሰው የሚሰጡ ኮርሶች በጣም ብዙ ጊዜ
በማይመለከተው አንደር ግራጁየት ላይ አንድ ኮርስ ብቻ ስለወሰደ ዩኒቨርሲቲው ውስጥ በጣም
ብዙ ምሳሌዎች አሉ። እና ይሄን ለማስቀረት ዩኒቨርሲቲው ህግ ስለሌለውም ኢሹው ጥቅም
ጋርም ስለሚያያዝ ስር የሰደደም ስለሆነ፤ አንዳንድ ፋካሊቲዎች ላይ ለምሳሌ ኤፍቢ ኮሚቴ
አላቸው። ኮሚቴ አቋቁመው አካውንቲንግ ላይ የሚሰጡ ኮርሶች አንዱ ለአንዱ ላይ በጣም ብዙ
ኮርሶች ኮመን ስለሆኑ ማን ይስጣቸው በሚለው ላይ ኮሚቴ አላቸው። ኢንጅነሪንግ ላይም
እንደዚሁ፤ የፕሮግራም ባለቤትነት ሁላ ጥያቄ ተነስቶ የውቃል ፎር ዛት ማተር። እንኳን
የኮርስ ማለት ነው፤ የኮርስ ባለቤትነትማ..። የፕሮግራም ባለቤትነት ጥያቄ ሲጠየቅ ማነው
ይሽን ፕሮግራም ራን ማድረግ ያለበት? ለሴኔት የደረሰበት ጉዳይ ሁላ ነበረ ማለት ነው። የእኛ
ኮሚቴ ራሱ አልችል ብሎ። አንተ ባነሳኸው መንፈስ ብቻም ቢታይ የአካዳሚክ ኪሊቲው ምንም
ጥርጥር የለውም ይደመሰሳል። ምክንያቱም ሰው ከጥቅም አንፃር ብቻ ስለሚያየው ማለት ነው።
ግን በጣም አጉልተንም የመቀማማት ጥያቄዎች ሁሉ መሆን የለባቸውም። እና ከዛ አንፃርም
የሚታዩ ነው የሚሆኑት። አሁን የመጀመሪያውን አጀንዳ እንጠቅልለው። ዙሮ ዙሮ ወደ
ሁለቱም ፕሮግራሞች ስንሄድ ያን ያህል ስር የሰደደ መጥፎ ነገር የለም። በሁለታችሁም
ርፍሌክት የሆነው አብረን እንስራ ተባብረን ወደተሻለ እናምጣቸው እንረዳዳ አንደርስታንድ
እንደራረግ የሚሉ ነገሮች ናቸው እስካሁን ሲቀርቡ የነበረ። ይህንን የሚያደፈርስ ነገርም ያን
ያህል እንደሌለ፤ የተፈጠሩት ነገሮች ተስተካክለዋል ማለት ነው። እና ሁላችሁም አእምሮ ላይ
ይሽ ነገር እንዳለ ነው እኔ የምረዳ ማለት ነው።
መለሰ፡- ለነገሩ ምንድን ነው በአጋጣሚ እኔ ራሱ ስማር ሊንጉስቲክስ ኤንድ ፎነቲክስ ኢን
ኢንግሊሽ ተብየ ነው የተማርኩት ፒኤችዲዬን ራሱ፣ ሁለቱን አንድ ላይ ማስኬድ ይቻላል። ኮርስ..ላይ
ፕራክቲካል የሆነውን አሁን እነፋሲል እንዳሉት ፎነቲክሱ ላይ ኤክሰርሳይስ ማድረግ
ካለባቸው ፕራክቲካሊ ማድረግ ስለሚገባቸው ያች ኢቭን ላቦራቶሪ ባይኖር በ-ትራንስክሪፕሽኑን
እንዲለማመዱ ለሱ ብዙ ጊዜ መስጠት። እንጂ ብዙ ችግር የለውም።
አበበ፡- ያልተነገረ ነገር ነው? (ለኢሌኒ እጇን ስላወጣች የተጠየቀ ጥያቄ)
ኢሌኒ፡- እኔ እንስማማ ብሎ ባይቋጭ ደስ ይለኛል።
አበበ፡- እንጣላ ብለን እንቋጨው።
ኢሌኒ፡- አይደለም! አይ አይደለም ማሾፌ አይደለም።
አበበ፡- አይ እኔም እውነቴን ነው የምልሽ።
ኢሌኒ፡- እኔን አስጨርሰኝና በኋላ ከዛ አንተ ትጨርሰዋለህ። እንሰማማ ብለን ከሄድን ፎርማል
የሆነ ነገር አይሆንም። አሁን እኔ በተረዳሁት መሰረት ይሄ ሁሉ ችግር የሚፈጠረው አባት
የሌለው አስተዳዳሪ የሌለው መሪ የሌለው ቤት ስለሆነ ነው። ሁለቱም 002ና 001።

ፎርማል የሆነ አካሄድ ስለሌለ ነው። ስለዚህ እኔ መሆን አለበት ብዬ እንደመፍትሄ
የማስቀምጠው ጋሽ አለሙ አሁን ያነሳው ነገር ጠንከር ተብሎ መያዝ ያለበት ይመስለኛል።
ሁለቱ ዲፓርትመንቶች ፕሮግራሞች ነው መሰለኝ አሁን ፕሮግራሞች እንደአንድ
ዲፓርትመንት ሆነው ራሳቸውን ችለው የሚቀመጡበት መፍትሄ ቢቀመጥ ጥሩ ነው።
እንደዲፓርትመንት አንድ ዲፓርትመንት ሆነው ሁለቱ ፕሮግራሞች በዲፓርትመንት፤
.... አለ አይደለ። 001 ዲፓርትመንት ሆነው እንደድሮው ማለቴ ነው። 001
ዲፓርትመንት ሆኖ 002ና 001 ሁለቱ ፕሮግራሞች በስሩ ቢቀመጡ። ከዛ በኋላ እነዚህ
ነገሮች ፕሮግራም የሚለው ነገር ይቀርና ኮርስ ቼር በሚለው መፍትሄ ያገኛል። አሁን ኮርስ
ቼር የኮርስ ባለቤትነት በኮርስ ቼር ይዳኛል። ነገር ግን አንድ ላይ የሚሆኑበት መፍትሄ
ማለትም ዲፓርትመንቱ ቢቋቋም ማለቴ ነው በቀጥታ። አዎ ማለት መታገል ያለብን
ይመስለኛል። አሁን ችግሩ አሁን ብቻ አይደለም ይሄ አሁን ለ..... ብቻ ከሆነ ያሰባችሁት
እኔ እንጃ፣ በጣም ብዙ ችግሮች አሉ። ከኮርስ ጀምሮ የኮርስ ባለቤትነትም በለው የኮርስ ምንም
ምንም። ስለዚህ ይሄ ፕሮግራም ሲከፈት የ001 ውስጥ ያሉ የ002ና የ..... ሰዎች
ስራ እንዳይፈቱ ብሎም ደግሞ የ..... ባለሙያ በዚህ አካባቢ እጥረት ስለነበረ ያንን
ለመሸፈን። ከትምህርት ክፍሉም ቀጣይነት፣ ለሀገሪቱም ደግሞ ለማበርከት የተከፈተ ነው።
እንደዚህ ተለይተው እንዲኖሩም አይደለም። ለምን የሚለያዩም አይደሉም መዓት የ.....
ኮርሶች እኛ ጋ አሉ፤ እነሱ ጋም የእኛ ኮርሶች አሉ። የምትነጣጥላቸው አይደለም። ስለዚህ ይሄ
መነጣጠላቸው አሳልፎ የመስጠት ያክል ነው የተሰማኝ። አሁን ኮርስ ቀይር እንደዚህ አሁን
የምሰማቸው ነገሮች በሙሉ ሁለቱን ዲፓርትመንቶች ወደማቀጨጭ የሚወስዱ ናቸው፤ ተፅዕኖ
ያለባቸው ይመስለኛል። ይሄ ደግሞ መሪ አባት የሌለው መሆኑን ነው የሚያሳየው። ስለዚህ
ሶሊሽኑ ዲፓርትመንቱ እንዲቋቋም አንተም ራስህ ብዙ ችግሮች እያየህ ነው ተፅዕኖ ልታደርግ
ይገባሃል የራስህን። በዲፓርትመንት ደረጃ ሁለቱ አንድ ላይ ቢሆኑ ብዙ ችግሮች ይፈታሉ
ብለህ አንተ ራስህ ይህን ሃላፊነት ልትወጣ ይገባል ብዬ ነው የማስበው። እንደእኛ ሆነህ ማሰብ
ነው፤ እንደጆርናሊዝም ብቻ ሳይሆን እኛንም እየመራህ ስለሆነ የእኛንም ችግር አይተህ
አስተዋፅኦ ማድረግ ይገባሃል። ሌላው መፍትሄ ብዬ የማስበው አሁን የወጣው ካሪክለም እንደገና
ሪቫይዝድ የሆነው ካሪክለም የሆነ ኮሚቴ ቢቋቋም ከእኛና ከእነሱ፤ ማለት የሚመለከታቸው
ኮሚቴ ስል የ..... የ..... ምናምን የሚመለከታቸው ባለሙያዎች ተቋቁሞ እንዲያው
አንዴ አይተውት የሚጨመር የሚስተካከል ምናምን የሚለውን ነገር ቢያዩት ጥሩ ነው ብዬ
ነው የማስበው። ጨርሻለሁ።
አበበ፡- ይሄ የዲፓርትመንት ጉዳይ ለምን ተነሱ የሚለው
[ኢሌኒ፡- ለምን ተነሱ ጥያቄ የለኝም፤ ይመለሱ ነው ጥያቄዬ።
ከበደ፡- ይሄ የሚቀጥለው አጀንዳ አይገባም ይሄ?
አበበ፡- እ እ
ከበደ፡- በሚቀጥለው አጀንዳ ውስጥ የሚገባ መሰለኝ።
መለሰ፡- ጊዜያችንን ባናጠፋ ይሄ ጉዳይ በጣም ከእኛ ጉዳይ የዘለለ ነው።
አበበ፡- ስላልገባት ግን በአጭሩ በጣም ሪፍሌክት እድርጌላት ብሄድ ብዬ ነው።
መለሰ፡- እሽ
አበበ፡- ዲፓርትመንቶች ወደፕሮግራም ጥናቶች ሲቀየሩ የቢፒአር ጥናት ነው።
[ኢሌኒ፡- ገብቶኛል
አበበ፡- እና ..... አምስት ዲፓርትመንቶች ናቸው ወደፕሮግራም ያልሄዱ። እነሱ
ያለተነሱበት ምክንያት በዩኒቨርሲቲ ኮርስ ስለሚሰጡ ማኔጅ ላማድረግ ያስቸግራል። ለጊዜው
በደንብ እስከሚለመድ ድረስ ይቆዩ ተብሎ ነው። የእነሱም ሴስቴኔብል ጉዳይ ነው። የአንድ
የፋካሊቲ ጉዳይ ምናምን አይደለም። አጠቃላይ የዩኒቨርሲቲው እከተለዋለሁ ብሎ የያዘው ጉዳይ
ነው። አንቺ የምታነሽው አንድ ጥያቄ በተለያዩ ሰዎች ይነሳሉ። ዲፓርትመንቶች
ይመለሱ፣የኒቨርሲቲው በጣም ፕሮግራሞች እየተዳከሙ ነው እየሞተ ነው ምናምን የሚል ሃሳብ
ይነሳል። ስቲል ግን አሁን ዩኒቨርሲቲው እየሰራበት ያለ ስትራክቸር ስለሆነ፤ ይሄ ስትራክቸር
እንዲህ በቀላሉ ስለጠየቅን አይመለስም። ስንት ደክመንበት አጥንተንበት አስበንበት የገባንበት

ነው ብሎ ነው ዩኒቨርሲቲው፡ እና ይሄ በመደረጉ ክፍተት የለም ወይ በጣም ብዙ ክፍተት
እየታየ ነው ከጠቀስሽው ውጭ የሆነ ክፍተት ታይቷል፡፡ አይ ቲንክ ዶር መለሰ በተግባር
ስለሚያየውና ሁልጊዜም ኤሲ ላይ ስለምናነሳው ሰፋ አድርጎ ሊያጫውትሽ ይችላል ብየ
አስባለሁ፡፡ ግን ስላነሳን ብቻ የማይመለስ ጉዳይ ስለሆነ ነው፡፡ እና የሁሉም ኦልሞስት የሁሉም
ፕሮግራሞች ኮንሰርን ስለሆነ ነው፡፡ ጆርናሊዛሞች በጎን እንደዛ ይላል ሌሎቹም እንደዛ ይላሉ
ማጠናከር ሲገባቸው አዳክመዋቸዋል ተብሎ ስለሚነሳ ማለት ነው፡፡ እና የስትራክቸር ጉዳይ
ስለሆነ ወደ ሁለተኛው አጀንዳ እንሂድና ሁለተኛውን አጀንዳ ስናይ የካሪክለም የሚለውን አብረን
ልናየው እንችላለን፤ የኮርስ ባለቤትነት ጥያቄ፡፡ እና ዙሮ ዙሮ ግን ቅድምም ያልኩትን አሁንም
የማሰምረው እሳጥረዋለን አብረን እንስራ የሚለውን የተናገርሽው ነገር አይገታውም፡፡ ጥሩ ከዚህ
የበለጠ አብረን እንድንሰራ ያደርገን ነበር ነው፡፡ ግን አሁንም ቢሆን ዩኒቨርሲቲው በፈቀደልን
ስትራክቸር ሂደን አብረን መስራት የምንችልበት ሩም አለ የሚለው ላይ የተስማማን
ይመስለኛል፡፡ ለውጦች ሲኖሩ አብረን እንደአንድ ዲፓርትመንት ሆነን እንስራ፤ያን ያሃል የገዘፈ
ቦርደር አይኖረውም፡፡ እየተመካከርን እንስራ የሚለው ነገር ነው አይ ቲንክ፡ እንስማማለን
ወደሁለተኛው እንሂድ? እሽ ሁለተኛው አጀንዳ የኮርስ ባለቤትነት ጥያቄ ነው፡፡ አብዛኛው
እስካሁን የተነሱ ነገሮች የከበቡት ነው ይሄን የከርስ ባለቤት ጥያቄ፡፡ ..... ፋሲል መድቦ ልኮልኛል
ውብነሽም መድባ ልካልኛለች፡፡ ፕሮግራሙን ስልከው በኋላ እንዴት ነው የሚል ነገር ተነሳ፡፡ እና
በኋላ ሲያስረዱኝ ነው የገባኝ እንጅ ለአንድ ኮርስ ኖርማሊ ሁለት የተለያየ ሰው ሲመደብ 001ም
የራሱን ሰርቶ ነው የላከ የመሰለኝ፤ ፋሲልም የራሱን ነው የላከ ነው የመሰለኝ፡፡ በኋላ ሳየው በዚህ
ጥያቄውን እናቅርበውና ..... እነፋሲል እስካሁን በ001 ይሰጥ ነበረ አሁን ግን እናንተ መድባችሁ
ልካችኋል፡፡
ፋሲል፡- ያው እኔ አይደለሁም የመደብኩት ኮሚቴ ነው የመደበው ያው፡ እኔ ነኝ፡፡ ሰርቬ ኦፍ
..... ባለፈውም ጊዜ እውነት መነጋገር ካለብን፡ እና አንድ ነን ምናምን
የሚባለው ነገር እኮ አመጣጣችንም አንድ ስለሆነ ይመስለኛ፡፡ 001 ቋንቋ እየተማርን ነው
የመጣነው፡፡ እኔ ዲፕሎማየ 001 ነው ዲግሪየ እሱ ነው፡፡ ምናልባት ኤም ኤ ላይ
002 የሚል ስለተጨመረበት ካልሆነ በስተቀር አንድ ነን ያልኩት ለምን እኔ ከዚህም አንግል
አየዋለሁ፡፡ ስለዚህ የእኔ ዲፕሎማየ የእነሱን ያህል ላናውቀው እንችላለን ግን አልፈንበታል፡፡
ማወቅና መማሩ የተለያየ ነገር ሊሆን ይችላል፡፡ ያለፍንበት በተመሳሳይ፡፡ ስለዚህ ኤም ኤ ላይም
ስንመጣ ..... ኤንድ ..... ነው ኤም ኤያችን፡፡ ስለዚህ ..... የእኛ ኮርስ ነው የሚል አቋም ነው ያለን
ፕሮግራማችን፡፡ ((xxx))ስለሆነ በፊት ከአንተ ጋራም አንስተናል ይህን ጉዳይ ክረምት ላይ ተነጋግረን
እኛ መምህር ባለፈው መደብን፤አደም ሰረዝከው፡፡ ከአንተ ጋርም ተነጋግረናል በ...ነው ወይ
እምትሰርዝ እስከማለት፡፡ ምንድን ነው የተነሳው ስታፋችሁ ትንሽ ነው፡፡ ከአቅማችን በላይ ነው ሁለት
መምህር ብቻ ስለነበርን፡፡ ስለዚህ ሁለት መምህር በነበረበት ጊዜና እንኳን አይደለም የራሳችን ጎረቤቶች
አሁን አንተ እንዳልከው እህትማማቾች እናትና ልጆች የሚለውን እንትን ባያረግም እህትማማቾች
በሚለው እንስማማለን ከውጭ መቅጠር እንፈልጋለን እንኳን ከእነሱ ጋ፡፡ ስለዚህ የዛኔ ወስደውታል
ተገቢ ነው እላለሁ፤ አንተም እንደዛው ነግረህናል፡፡ የመምህር እጥረት ስላለባችሁ ኦቨር ሎድ
ስለሆናችሁ አንተና ሰለሞን ይሄ በዚህ ኮንኩሉድ ላይ ደርሰናል እንጅ ዘንድሮ አይደለም የተነሳ
አምናም ተነስቷል፡፡ ስለዚህ ኦቨር ሎድ ስላልሆን ስምንት ክሬዲት ነው የያዝነው ፍሬሾችን
አይጨምርም ስለዚህ አንደር ሎድድ ነን፡፡ መምህር እያለ እኛ አንደርሎድድ ሆነን ማስተማር
የምንችለውን ኮርስ መስጠት አንችልም:: ምክንቱም ዲግሪያችን አለ የ..... ዲፓርትመንት
ውስጥ የሚሰጡ ኮርሶችን...ሁለተኛ ዲግሪያችን ግን ..... ኤንድ ..... ነው፡፡
እኛ ካላስተማርነው ማን ሊያስተምረው ነው? እንደዛ ከሆነ በቅርርብ እንስራ ምናምን ከተባለ
ያለበት ክሊርሊ መነጋገር ካለብን፡፡ እኛ ከነሱ የምንወስደው ኢንትሮዳክሽን ..... አሁን
አሁን ነው እንዲያውም ወደእኛ መምጣት የጀመረው፡፡ በርካታ የ..... ኮርሶች ሲባል ነበር
ከእኛ ጋር ሁለት ከ..... ውስጥ የሚሰጡ ሰባት ስምንት ኮርሶች አሉ፡፡ እኛ ከእነሱ
ኢንትሮዳክሽን ..... አሁን አሁን ነው መውሰድ የጀመርነው፡፡ ስለዚህ መግባባት ካለብን
እነዚህ እነዚህ ነገሮች መፈታት አለባቸው፡፡ ኮርሱን እኛ ማስተማር እንችላለን፤ብቻ ሳይሆን
ስፔሻላይዝ አድርገንበታል፡፡ የሚል ነገር ተከራክረን ከአንተ ጋር ብዙ ጊዜ ተጨቃጭቀንበታል፡፡

ስለዚህ ተሳስተን ሳይሆን በስህተት ሳይሆን ፐርፐርዝሊ የሆነ በሁኔታው ተነጋግረናል።
አበበ፡- የኮርሳ ባለቤትነት ላይ ጥያቄ አለኝ። ማስተማር ትችላላችሁ ብለህ ምክንያቱን
ነግረህናል። ባለቤቱ ግን ማነው? አሁን ኮርስ ቸሩ ማነው? በየትኛው ሞጁል ውስጥ ነው
ያለው? ባለቤቱ ማነው? የሚለውን ርፍሌክት አድርገው። ..... ነው ባለቤት ነው መሆን
ያለበት? ማነው ቸር የሚያደርገው እንደባለቤትነት? ከዛ ቀጥሎ ማን ያስተምረው የሚለውን
እንመጣበታል።
ዳኛቸው፡- ምናልባት እሱ ያነሳው ሀሳብ እንዳለ ሆኖ፤ በእነኚህም ኮርሶች እንዳውም ከአንተ ጋር
ትንሽ ተነጋግረናል።
[አበበ፡- ብዙ ነው የተነጋገርነው።
ዳኛቸው፡- በዛ ምንድን ነው የተነጋገርነው የኮርስ ኮድ ስፔስፊክ ትቀየር አትቀየር ማለት ፎክ
ኢላም፣ የእኛ ጠቅላላ የ..... ኮርሶች በፊት ኢላም ተብለው ነበር የሚጠሩት። ችግር የለም
ያኔ ላይ ተብለን ተውነው። አሁን የባለቤትነት ሲመጣ እኛ ኢንቴንሲቭ የ..... ኮርሶችን
በመጀመሪያም በሁለተኛም ዲግሪ ወስደናል። እኔ እዚ ..... ውስጥ ከመግባቴ በፊት እኔ
አክሱም እያለሁ የ.....ና የ..... ኮርሶችን ሞጁል አዘጋጅቻለሁ። ለምሳሌ አለማየሁ
ሰርቬን አዘጋጅቷል። እኔና አንድ ጓደኛየ ፋንዳመንታል ..... አዘጋጅተናል። እንደዚህ።
ይሄ ባለቤቱ አሁን ወደሞጁል ቦታ ባለንበት ሁኔታ ስንመጣ ምንድን ነው ያልነው ለእነኚህ
ኮርሶች የሰው ሀይላችን ፉል ነው፤ ተጠናክሯል። ከዚህ በኋላ አንደር ሎድድም ነን፣የኮርሱም
ባለቤት እኛው ራሳችን እንሆናለን። ነገር ግን ከታሪካቸው አነሳስ ሲነሳ ኢላም የሚለውን
ከምናጥፈው ስለዚህ ኢላም ይሁን ኢትዩጵያን ላንጉየጅ አንድ ..... እለ ስለሚሄድ ማለት
ነው፤ እሱ ኮድ ይኑር፣ የኮርሱን አስተዳዳሪ እኛ እንሁን ብለን ከዛው ተቀራራቢ ነገር
አስቀምጠነዋል። ግን ሲሆን ከ.....ው ስለሄደ የባለቤትነት መብት እንዴት መጣ የሚለውን
ነገር ስለኛም ፕሮፌሽን እነሱም የበለጠ ስለሚያውቁ ያው አብረንም ስላለን በዚህ ጉዳይ
እንዲውም ተዕዕኖና እንደዚህ አይነት ጥያቄዎች ይነሳሉ በግሌ አላሰብንም ነበር። መነሳታቸው
ግን ጥሩ ነው። ስለዚህ በባለቤትነትም የምናስተዳድረው ይህን ኮርስ እኛው ነን። ይህን ብቻ
አይደለም፤ ምናልባት በዚህ ከተጠየቀ ማለት ነው። የፋንዳመንታል .....ም ኢንቴንሲቪሊ
እኛ ጋ ነው መሆን ያለበት። ስለዚህ ለዛ ኮርስ የተመደብን አለን፤ በሞጁል በሞጁል አለን፤
ማቴሪያልም እኛው ነን የምናሰባስብ። ስለዚህ በዚህ አይነት ነገር ላይ እንነጋገራለን። ነገር ግን
አሁን እኛ ለትምህርትም እንሄዳለን ((×××))አዲሽናል ሰው ከምንቀጥር ይልቅ እህት ትምህርት
ክፍሎቻችን አሉ የሰው እጥረት በሚያጋጥመን ሰዓት ከውጭ አናመጣም ፓርትታይም
አንቀጥርም፣ ስለዚህ ኮርስንም ከመቀየርም ምንም ከማለትም እነሱን እየጋበዝን እየተጋገዝን እንሰራለን
በሚለው ነው። ስለዚህ አንደርሎድድ በሆንበት ሰዓት ውስጥ እንደዚህ አይነት ጥያቄዎች አይነሱብንም፤
ከዛ በለይ ከሄድን ደግሞ እነሱን ከእኛ ጋር እንዲሰሩ ቅድሚያ የምንጋብዛቸው እነሱን ነው ብለን
ስላመንበት ነው የወሰነው።
አበበ፡-ኮርሶቹ እነዚህ ብቻ ናቸው ወይስ ሌላም አለ?
ዳኛቸው፡- እነኚህ ሁለቱ ላይ ነው።
አበበ፡- ሞጁል አላቸው እናንተ ያዘጋጃችሁት?
ዳኛቸው፡- ለምን መሰለህ ሁለቱን ያነሳነው፣ አሁን ለምሳሌ አምሃሪክ አድቫንስድ ራይቲንግ
ስኪል አለ፤ እሱ በማስተር ደረጃ አልተማርኩም። የሊንጉስቲክና የቤዚክ ሪይቲንግ ስኪል እነሱ
ናቸው ሞር ፕሮፌሽን፤ አንደር ግራጁየት ሆኜ ተምሬዋለሁ ልስጥ ግን አላልኩም በዚህ ሰኣት።
ስለዚህ ..... ኤንድ ..... ማስተር ላይ ስንማር ከዚህ አንፃር ኢንቴንሲቪሊ
ከእኛ ጋ የሰው ሀይል አለ። ስለዚህ ለእነኚህ ኮርሶች ለእኛ ባለቤትነቱን እንስጥ እኛው ራሳችን
ነን ብለን አስቀምጠናል። ሌሎች ሌሎች ኮርሶች እኮ አሁን ለምሳሌ ፖይትሪ ብታነሳ
በማስተርስም ኤም ተምሬአለሁ፤ ግን ..... ውስጥ ስለሌለ .....ዎች ጋ ሄጀ አልጠየኩም።
ይህ ምንድነው የ..... ኮርሶች በዚህ ላይ የተስማማነው የተነጋገርንበትም በኮርሱ ዙሪያ
የተሻሉ ጥናቶችንም አገላብጠናል ሰርተናልም ብለን ስላመንን ነው። ስለዚህ የሊንጉስቲክስንና
አምሃሪክ ቤዚክ ራይቲንግ ስኪል በቲም ኤም ኤ ያላቸው ሰዎች ናቸው በጣም በተሻለ ከእኛም
በተለየ ሊያስተምሩ የሚችሉት። በእነኚህ ኮርሶች ግን...

አበበ፡- በ..... ፕሮግራም በኩል ያለውን አይተናል ማለት ነው፤ በ..... ..... ያለውን
ደግሞ እንስማ፡፡
አገሬ፡- እንደገለፀት ግን አዚህ ጋ መነሳት ያለበት ቅድምም ሲባል የነበረው ማለት ነው፤ አሁን
እነሱ መስጠት አይችሉም ከአቅም ጋር አይደለም፣ የተነሳው መስጠት አይችሉም፣ ስለሙያው
የሚያውቁት ነገር የለም የሚል አይደለም ጥያቄው፡፡ ጥያቄው ግን በማን ስር ነው የሚመራው?
የማን ፕሮግራም ነው? ያ ኮርስ የሚለውንና ቅድምም የተባለው ይሄ የመለያየት ነገር ያመጣው
ችግር፡፡ አሁን ለኮርስ ቼር እኔ አሁን የ..... ኮርስ ቼር ነኝ፡፡ እ በ..... ኮርስ ዙሪያ
የሚደረጉ ነገሮች ሪስፖንስብሊቲ አለብኝ፡፡ ማነው የሚሰጠው? እንዴት ነው የሚሰጠው? እነሱ
እነሱ ነገሮች ሁሉ መከታተል አለብኝና እኔ አትሊስት ትምህርት ክፍሉ ኮርሶቻችን የት የት
ይሰጣሉ? አሁን በቅርብ ያለው ..... ነው ሊንጉስቲክስና የ..... ኮርሶችን ነው
የምንሰጠው፤ በሊንጉስቲክስ ስር ያሉትን የሊንጉስቲክስ፣ በ..... ስር ያሉትን የ.....፤
እና የሰጡትን ሳይሆን አሁን ከግለሰብ ጋር ሳይሆን የሚያያዘው ኮርሱ ከፕሮግራም ጋር ነው፡፡
እንደፕሮግራም ደግሞ ከታየ ይሄ ፕሮግራም ኮርስ ቼር የተመደበለት ..... ጋ ነው፡፡ ስለዚህ
ከኮርስ ቼሩ ጋር ስምምነት መደረግ ነበረበት፡፡ እና ህገወጥ በሆነ መንገድ ድልድል ተደርጓል
እያልን ነው፡፡ አግባብነቱ የኮርስ ቼሩ ስልጣን ተነፍጓል በአጭሩ ማለት ነው፡፡ እንትን
የተሰጠውን ማለት ስትራክቸሩ የሰጠውን ነገር ስታል እያልን ነው፡፡ ግለሰቦቹ ችሎታው
ሊኖራቸው ይችላል፤ የትምህርት አቅሙም ሊኖራቸው ይችላል እሱን የካደ ወይም ክርክር
ውስጥ ያስገባው ነገር የለም፡፡ አሁን እዚህ ጋ ክርክሩ ምንድን ነው የፕሮግራም ባለቤቱ ለዚ
ኮርስ የተመደበለት ኮርስ ቼር አለ የእሱ የኮርስ ቼሩ ኮልሰንታንት በሌለበት የተሰራ ስራ አለ፡ ያ
ነው መስተካከል ያለበት እያልን ነው፡፡ ይሄ ጉዳይ ለጥያቄ እንዲጠራ ያደረግነው ማለት ነው፡፡
አበበ፡-ግልፅ እንድታደርጉልኝ እዚህ ጋ በምን ሞጁል ስር ነው ያለው ይሄ? ሰጣችሁታል እናንተ
ጋ?
ዳኞቸው፡- አዎ ..... ውስጥ፡፡
አበበ፡- ማነው ኮርስ ቸሩ?
ፋሲል፡- እኔ ነኝ ይመስለኛል፡፡ ያው ስለማላስታውሰው ነው ስለሞን ይመስለኛል የ.....
ኮርሶችን፡ እሱ ችግር የለም፡፡
አስናቀ፡- ያው ጥሩ ነው እንደተባለው ዞሮ ዞሮ ኮርሶቹ መሰጠታቸው ነው ጥሩው ነገር፡፡
ተማሪዎቹ በጥሩ ሁኔታ መማራቸው ነው ዋናው ነገር፡፡ እስካሁን ባለው አሰራር ያው አሰራሩ
ስህተት ከሆነ ይለወጣል፤ ችግር የለውም፡፡ ከልምድ ረገድ ግን ...የተነሱ ኮርሶች የ.....
ትምህርት ክፍል ሞጁል... በሞጁል የተዘጋጁ ለራሱ ትምህርት ክፍል የሚሰጡ ከእሱ
ትምህርት ክፍል አልፈው ደግሞ ሌሎች ትምህርት ክፍሎችም የሚሰጡ አሉ፡፡ ለምሳሌ
ለ..... የሚሰጠው የምንጠቅሰው ኮርስ፤ ..... ጋ ያሉ የ..... ደግሞ በ..... ስር ያሉ
ኮዳቸውም ባለቤትነቱም እዚያ ያለ ወደሌሎች ትምህርት ክፍሎች ሄደው የሚሰጡ አሉ፡፡ ስለዚህ
እንደእኔ እንደእኔ ከተባለውም ከቅርብ ጉረቤት መሆን ነበረበት ወይም መሆን አለበት ብዬ
የማስበው ባለቤትነቱን ለዛ ትምህርት ክፍል ሰቶ እኛም ልንሰጠው እንችላለን እኮ የሚል ነገር
ካለ በመነጋገር በመወያየት እኛ ጋ እኮ እንደዚህ ነው ያለነው ይሄን ኮርስ መስጠት እንችላለን፡፡
ለእኛ ትምህርት ክፍሎች ብንሰጠው፣ በእርግጥ ኮርሱን ቸር የምታደርጉት እናንተ ናችሁ፡፡
እኛም ደግሞ የ..... ኮርስ ካለ ምናልባት እኛ ትምህርት ክፍል ያሉ ሰዎች ይሰጡት ይሆናል
ብለን ስናስብ፣ በእርግጥ የእናንተ ነው እናንተ ስትመድቡ ቆይታችኋል፤ ከእናንተ መቶ ሰው
እየሰጠልን ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጂ አሁን እንዲህ አይነት ሰው ስላለን እንዲህ ብናደርግ፣
የመመካከር አይነት ነገር ቢኖር ይሻላል ብዬ አስባለሁ፡፡ እና እኔ እንደማስበው አሁን
እንደእንትን ሳስበው እዚህ አሁን ..... የሚባል ኮርስ አለ፣ .....የሚባልም አለ፣ ተውኔትም አለ፣
እዚህ ..... ትምህርት ክፍል፤ እና ..... አሁን የእነዚህ ሁሉ ኮርሶች አንድ ላይ ድምር ነው፡፡ ድምርም
ሆኖ .....
ሊሰጡት ይችሉ ይሆናል፡፡ እኔ አሁን ..... ጋ ሊሰጡት አይችሉም የሚል እንትን
የለኝም፡፡ እዛ ስታንድ ላይ ሆኜ አይደለም የምናገረው፡፡ ግን ኮርሱ ሰፋ ያለ ጊዜ እዚህ ትምህርት
ክፍል ከመሰጠቱ ረገድ እነዚህንም ኮርሶች ከግንዛቤ እያስገባ ሲሰጥ ከመሰጠቱ ረገድ ወደእንዲህ

አይነት ነገር ሲኬድ ዝምብሎ ከመመደብ መነጋገሩ መወያየቱ እዚህ ጋ ኮርስ ቼር ፐርሰንም
ስላለ አይ እንዲ እንዲህ ነገር እኮ አለ ቢባል ይሻል ይሆናል ብየ ነው የማስበው። ስለዚህ እንደኔ
እንደኔ አሁንም ቢሆን የመቀራረቡም ነገር ሊኖር ስለሚችል አብሮ መስራቱም ነገር ሊኖር
ስለሚችል እንዲህ አይነት ነገሮችን ወደ ለወደፊቱ ኢሚዴትሊ ጥሩ ጥሩ መንገድ አሳይቶናል።
ጥሩ ይሄ ነገር እንዳለ አይተናል ለወደፊቱ እንዴት እንስጣቸው እንዴት የሚለው ሰፊ ውይይት
የሚደረግበትና ፎርማሊም ኢንፎርማሊም ትምህርት ክፍሎች የሚነጋገሩበት ሁኔታ ቢፈጠር፤
ግን የ..... ኮርሶችን ከእኛ ጋ የሚሰጡትን ባንነካቸው ለጊዜው በእኔ እምነት ይህ የእኔ የግል
እተያየቴ ነው። ስለዚህ የ..... ከእኛ ጋ የሚሰጡት ባለቤቶቹ ....ናቸው። ኢላም
ብለው ያሉትንም ኮርሶች ለዚህ ሴሚስተርም ይሁን ለሁለት ሴሚስተር እንዲህ ተነጋግረን
ወደሆነ አቅጣጫ እስከምንሄድ ድረስ ባለቤትነታቸውን እንደያዘ ቢቀጥል ጥሩ ይሆን ይሆናል
የሚል እምነት አለኝ። ኦፊልስ ደግሞ ፕሮግራሞቹን ማንዴትድ ማድረግና ..... ትምህርት
ክፍል ከ..... የሚመጡ ኮርሶች አሉ፤ያመነበትን ያድርግ ተማሪዎቹም ፕሮግራሙም የእሱ
ስለሆነ። ያንን ካላልን ወደእያንዳንዱ ኮርስ የሚያስገባን ይመስለኛል አሁን። ሰርቬይን ዛሬ ሶልቭ
ልናደርግ እንችላለል። የሰርቬይን ኮርስ ኮንቴንት አይተን፣ ፕሮፋይሉን አይተን፣ ምኑን
አይተን፣ ሰርቬይ ላይ አይ ለእነገሌ ለዚህ ትምህርት ክፍል ልንል እንችል ይሆናል። ችግር
የለውም ልንስማማ እንችላለን። ግን የት ጋ ነው መቋሚያው? ዘን ሌላ ኮርስስ አይመጣም ወይ?
ዘን ለምሳሌ ቲሞች አለን እዚህ ሊንጉስቲክስ ..... አለ፣ አንዳንዴ ከሰራናቸው ሞጁሎችም
ረገድ አንደር ሎድ ሲሆን እኔ ..... ሄጀ የማስተምርበት፣ ሌላው ደግሞ ቲም ጋ መቶ
የቲም ኮርስ የሚሰጥበት ሁኔታ ነው ያለ፤ ከንባብም ከምንም ረገድ። በፊልዴ ብለን የመሄዱም
ነገር እንትን ነው። በእርግጥ በፊልድ መማራቸው ጥሩ ነገር ነውና ወደእንደዚህ አይነት
ከምንሄድ አቄርነሱ አለን እንትኑ አለን መፍትሄ በውይይትና በንግግር ለወደፊቱ እንትን
እስከምንል ድረስ ወደዚያ ብንሄድ ጥሩ ይመስለኛል። ይሄን ስል ግን ይሄኛው መስጠት ይችላል
ይሄኛው መስጠት አይችልም የብቃት ደረጃ የሚለውን ከጥያቄ ውስጥ አስገብቼ አይደለም። እኔ
ማነኝና ያንን እላለሁ። ግን ስቲል ማኔጅ ሲያደርገው ቆይቷል ትምህርት ክፍሉ። ለረጅም ጊዜ
ሲሰጠው ቆይቷል ትምህርት ክፍሉ። ሞጁሎችን ሲያዘጋጅበት ቆይቷል የተሰሩ ሞጁሎችን
ሳይቀር። አሁንም ሞጁል ተዘጋጅቶለት ..... ኮርሶች ተብሎ በዛ ስር ነው ያለ። ያ ያ
ፋሲሊቲውና ያለው ነገር ሲታይ በመነጋገር መሆን የነበረበት ነው። በዚህ መንገድ እንትን ይላል
የሚል ይሄ የእኔ የራሴ አስተያየት ነው። ዊ ካን ዲስከስ።
አበበ፡- ኦኬ ጥሩ ነው...ግን የኮርስ ባለቤትነት ነው አጀንዳው፤ ማን ይስጠው የሚለውን...ከዛ
በኋላ የሚመጣ ነው። አሁን አጥርተን የምናየው መጀመሪያ ግን የኮርስ ባለቤትነትን ነው።
የማን ፕሮግራም ኮርስ ነው መጀመሪያ። ማነው ራን የሚያደርገው ላይ እንስማማና ሀሳብ ሼር
እናደርጋለን። ማን ያስተምረዋል የሚለውን ከዛ በኋላ እናየዋለን።
ከበደ፡- የት ነው ኮርስ ያለው እዚህ ጋ ጥያቄ ያለው አይመስለኝም። መልሱ በ..... ይሆናል።
ያን ያልኩበት ምክንያት አርባና ሰላሳ ስምንት ክሬዲት ያህል የ..... ኮርሶች አሉት። ሶስት
አበይት እንትኖች ነው ያሉት። ..... አለ ሊንጉስቲክስ አለ የስኪል ኮርሶች አሉ። ግን እኔ
እዛም ውስጥ ሊያለሳልሰው ይችላል ብየ የማስበው ራሱ መጀመሪያ ትምህርት ክፍሉን ስንከፍት
.....፣ ..... ትምህርት ክፍል አማራጮችን ማስፋት ነው። ሌሎች ድራማ ሁሉ እያሰብን
ነበር በነገራችን ላይ ችላ አልነው እንጅ። ስለዚህ ያንን ስናደርግ የ..... ኮርሶች በ.....
ትምህርት ክፍል መምህራን ይሸፈናል፤ ..... መምህር ብዙ ሰው አይደለም ሁለት ሰው
ነው። ኢቭን ግዕዝ ራሱ ..... መምህር ሆኖ ግዕዝ የሚችል ከሆነ ሌላ ሰው አንቀጥርም
ነበር። እንደአጋጣሚ የፕሮግራሞቹ መለያየት ኮርሶቹን በደንብ እንድናስብ ያደረገን ይመስለኛል።
ያ ካልሆነ በስተቀር አንድ ነው ያልኩት ለዛ ነው። ለምን መጀመሪያ የተጠቀምን እኮ
እነአምላሉን ማነው የፊቶኞቹ ጆርናሊዝም ላይ ወርክሾፕ አን ክሬቲቭ ራይቲንግን እኮ
ተመድበው አስተምረዋል። ያ ማለት ምንድ ነው የሰለጠኑበት መስክ ይፈቅዳል ነው ዞሮ ዞሮ።
ግን ስንነሳ ያንን አስበን አይደለም የተነሳነው። አሁንም መሆን ካለበት ፕሮግራሙ እንዲህ
ሊሆን ይችላል...ኮርሶች ስላሉ። እዛ የሎድ ችግር አለ፤ አንዱ ፕሮብለም ይሄ ይመስለኛል።
የሎድ ችግር ካለ ነው ይሄን የሚያሳስበን ወይ የጥቅም ጉዳይ ካለበት ይመስለኛል። ስለዚህ

አስፈላጊ ከሆነ መተው እነሱም የስነፅሁፍ ኮርስ የማያስተምሩበት ምክንያት የለም። እነሱም
ይዘውት ያሉ እንኳ ኦር ሎድ የሚሆን ከሆነ እዚህ አንደር ሎድ ከሆነ አይችሉም። ፋካሊቱውም
የሚፈቅድ አይመስለኝም። ለምን ኮርሱን የሚያስተምር ሰው እዚህ አላ። ስለዚህ በኮመን ሴንስ
ተግባብተን ፕሮግራሙ((xxx))ችግር አይደለም፤ አንደር ሎድ የሚሆኑ ከሆነ የስነፅሁፍ ኮርስ
የማይሰጡበት ምክንያት የለም። እንዲያውም እኛ እዚህ እንባላለን እንጅ ፕሮግራሙ ሁሉ ፌዝ
አውት የሚያደርግ ነው ያለው ለመብታችን እስካልታገልን ድረስ። ታግለን እኮ ነው ያቆየነው፤
.....፣ 003 ትምህርት ክፍል ይከፈት ተብሎ ..... ይዘጋ ሲባል፤ እኛ ኒድ
አስስመንት ሰርተን የከፈትነውን እንትን እንዴት ይዘጋል ብለን ነው አይደለም እንዴ
ያስከፈትነው። እንዲያውም በዛ የተነሳ የ..... ትምህርት ክፍል እዛ ጋ ተዘጋ። ልጆቹ አሁን
ተቀጣሪ እየሆኑ እያገኙ አይደሉም በ..... ስር የሚመደቡት። ስለዚህ ነገ አደጋ ያጋጥበታል።
አደጋ ሲያጋጥበት የት ነው የሚኬደው ወደዚህ ወደ..... ትምህርት ክፍል መቶ መግባት
ያለበት ይመስለኛል። ...ተሳስበን ስንሄድ ነው። ሌሎች አማራጭ ነገሮችን ስናሰፋ ነው። የጥቅም
ጉዳይ እኛ ጋ በዚህ ኮርስ የተነሳ ክረምት ላይ ኤክስቴንሽን ላይ የጥቅም ነገር ካለ እሱን
ተነጋግረን የምንጨርስበት መንገድ ማመቻቸት እንችላለን።
ፋሲል፦ እሽ እ ...አንጣላ እኮ ከመጀመሪያውም ጀምሮ። ግን ጋሽ ከበደ ያመጣኸውን ነገር አምና
ክረምት ላይ ጠይቀንሃል።ለምሳሌ አሁን ኤክስቴንሽን እኛ የለንም፤ ዲስታንስ የለንም፤ ሰመር
የለንም። እኛ ሬጉላርና ሬጉላል ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ የራሳችን የራሴ ድክመት አድርጌ ነው
አክሴፕት የማደርገው እኔ። ...ይሆናል፣የሲስተሙ ችግር ይሆናል፣የፕሮግራሙ መምህራ ችግር
ይሆናል ወይም ደግሞ ባልከው ነገርም ሊሆን ይችላል። እኛ ጋ ይመጣል። አብረን መስራት
ካለብን አሁን እኛ እያልን ያለነው ..... እንደምናስተምር ያውቃሉ። ካወቁ ግን ሰመር እኛ
አምና ሶስት ነበርን። እንዲመድቡን ተነጋግረንበት ነበር። አናገራቸው፣ ኢንትሮዳክሽን ቱ
..... ምናምን ነገር ተሰጠን። ከዛ ግልፅ ለመናገር ቅሬታ ተሰምቶናል። የለ.....
መምህራን ነን። ክረምት ላይ ኮርስ እንደሌለን ይታወቃል። እነሰለሞን እነማናቸው እነ የእኛ
ዲፓርትመንት...እነሱ በነበሩበት ጊዜ ጋሽ ከበደ እንዳለው ነው። የ..... ኮርሶችን
ይሰጣል፣ ..... ጋሽ ከበደ ይሰጣል፤...በጋራ ሲሆኑ። እነአምሳሉ ሲሰጥ የነበረው እነ.....
ምናምን የ..... ኮርሶችን ሲሰጡ እንደነበር እናቃለን። አብረን መስራት ካለብን
ኢንትሮዳክሽን .....ን ብቻ ለምንድን ነው ወርውረው የሚጥሉልን። እኔ እኮ አንድ ኮርስ
ምናምን ነገር ለአንድ ኮርስ ብለን ከምንቀመጥ ሰለሞን ያዛት ብለን በየግላችን ሄደን የከረምንበት
ሁኔታ ነው ያለው አምና። ስለዚህ አብረን መስራት አለብን የስ! እኛም እያልን ያለነው እሱ
ነው። ግን ሰመር ሲመጣ፣ ኤክስቴንሽን ሲመጣ፣ ዲስታንስ ሲመጣ እኛ የለንም እዛ ጫዋታ
ውስጥ። ሬጉላር ላይ ኖ የሚባል ጥያቄ ከተነሳ የዚህ ዲፓርትመንት ህልውና ምንድን
ነው?...እንስማማ ከተባለ እኛም .... እንደምንሰጥ ከተግባባን እናንተም .....
እንደምትሰጡ ከተግባባን ማንበብ ነው። ሌላ የተለየ ታምር ያለው
አይመስለኝም። ...እንደመጣችሁ እኛም አልዘነጋነውም እሱን። ስለዚህ አሁን ለእኛ ሲባል ለእኛ
ሲባል ከእናንተ ዲፓርትመንት አንድና አንድ ኮርስ ነች ኢንትሮዳክሽን .....።
ኦፊሻሊ ...የተሰጠን አሁን ነው። ....ራሳችሁ እንደምታስተምሩት ነው አስዩም የምናደርገው።
አምና ምናምን ነገር ጀምሮ አሷው ብቻና ብቻ ወደእኛ መታለች። ስለዚህ መተሳሰብ ካለብን
ሰመርም የለንም። አብረን ከተጋገዝን ለምንድ ነው ሰመር እኛ እነዚህ ሰዎች እኮ ኮርስ
የላቸውም የማንባባለው ለምንድ ነው? ..... እንደምንሰጥ ከታወቀ የሚል ነገር አምና እሷን
ኢንትሪዳክሽን ..... ተሠተን አሁን ባልኩት መንገድ ተቋጨ። ይሄ ጉዳይ ትክክል ተገቢነት
የለውም ብለን ሰለሞንና እኔ ብሩክ እያለ...ቆየን። ስታፋችን እየተጠናከረ ሲመጣ... ስለዚህ
አንደር ሎድ ነን።°አንደር ሎድድ ስለሆንን .... ተምሬ ስፔሻላይዝ አድርጌ ማስተማር አለብኝ ወይም
አለብን። እናንተ አታስተምሩትም የሚል ነገር የለንም። እናንተም አታስተምሩም አላላችሁንም።
አሁን ወደጋራ ነው በነገራችን ላይ የመጣነው። .... ሆኖ .....ማስተማር ይችላል። ..... ሆኖ
..... ማስተማር ይችላል ወደጋራ መምጣታችንን ለማሳየት ይመስለኛል የ.... ከርሶችን
መስጠት እንችላለን ብለን ወደ...እየመጣን ያለነው። ስለዚህ እኛ እንደምንሰጥ ካመናችሁ እኔ
ይህን ያልኩ አንድ ኮርስና ሁለት ኮርስ ከዛ በላይ ...አብረን መስራት ካለብን በጋራ ከሰራን ብዙ

ነገር መስራት እንችላለን፡፡ ግን ወደእኛ ሲመጣ ኢንትሮዳክሽ ..... ብቻ ወደእናንተ ሲመጣ
ሰባት ስምንት ኮርስ ከሆነ ፌርም አይሆን፡፡ ክሊርሊ መነጋገር ካለበን ማለት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር
ስተፋችን አለን እኛ እንወያይበት፡፡ ዛት ኢዝ ኦኬ ውይይቱን እንፈልገዋለን እኛ፡፡ ሌላ ምናልባት
.... ቀጣሪ እያጣ ነው የሚለው ዲያሎግ ለማድረግ አልፈልግም፤ ሁሉም... መታረም
ያለበት ነው፡፡ ሁሉም ዲፓርትመንት ውስጥ ያለ አደጋ ነው፡፡ አገር አቀፍ ነው፡፡
አበበ፡- ለማለት የፈለገውም ስትራቴጂክ በሆኑ ነገሮች ላይ እናምጣው ነው፡፡ ስለዚህ የተብራራ
ጥያቄ ስለሆነ እሚለውን ባክአፕ ለማድረግ ስለሆነ አጀንዳቸው ስለሆነ አናነሳውም...፡፡ ይሄኛውን
እንቋጨው... በኢንዲቭዢል ደረጃ አውርደን ሳይሆን አሁን እየተነጋገርንበት የለ የኮርስ
ባለቤትነትን ጉዳይ ነው፡፡ ከዛ ሌላው ተከትሎ በመነጋገር የሚመጣ ነገር ስለሆነ ማለት ነው፡፡
ከሎድ ጋርማ ሲያያዝ እኛ ኖ እንላለን፤ ብለን እናቃለን፡፡ አኩርፋችሁ ትሄዳላችሁ ለወዲያው ዘን
ምናምን ...የስራ ባህላች ስለሆነ ምንም ችግር የለውም እንጂ፤ ከሎድ ጋር ሲያያዝማ አንደኛው
አንደር ሎድ ሆኖ ሌላኛው እንትን ሲል ኖ እንላለን እኛም ሀላፊነት ስላለብን፡፡ ከዛ ያለፈ ስለሆነ
ነው ባለቤቱ ማን ይሁን ማን ቼር ያድርግ ይሄን ኮርስ ማነው ሪስፖንስቢሊቲው የሚለውን
መወሰን ስለነበረብን ነው ቅድም ከበደ እንደጠቀሰው እንደኮርስ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ አሁን
በተነሳው ሀሳቦች መሰረት ማለት ነው፤ አሁን በተነሳው ሀሳቦች መሰረት እነዚህ የ.....
ኮርሶች በባለቤትነት .... ቼር ያርጋቸው፡፡ ኮርስ ቼሩ አንድ ነው የሚሆነው...ሁለት ኮርስ
ቼር አይኖረውም... ስለዚህ በባለቤትነት እሱ ይያዘው፡፡ ዴሊቬሪው ላይ ግን ስንመጣ ሎድን
ኮንሲደር ባደረገ መልኩ ይሁን፡፡ .... ላይ...በሚከሰትበት ሰዓት የ.... መምህር
ሊያስተምር ይችላል፡፡ ምንም ችግር የለም፡፡ ሎድ የስራ ጫና ካለ ኦር ሎድ ላይሆን ይችላል
የስራ ጫናን እኩል መካፈል ራሱን...የስራ ጫናን እኩል ከመካፈል አንፃር .....፡፡ እሱን ኮርስ ቼሩ
በሃላፊነት ይስራ፡፡ ከፕሮግራም ማናጀሩ ጋር እየተነጋገረ ሊሰራ ይችላል፡፡ ከፕሮግራም ተወካይ ጋር
እየተነጋገረ ሊሰራ ይችላል ማለት ነው፡፡ አጠቃላይ የመምህራንን ሎድ ማየት፡፡ የትኛው ላይ ነው ብዙ
የስራ ጫና ያለ፤ ነሰሰርሊ ኦር ሎድ ላይሆን ይችላል፤ ኦርሎድም ሊሆን ይችላል፡፡ ኦርሎድ ብዙ
ስለማይኖር ከዚህ በኋላ ሰባ ሰላሳ አፈክት ስለሚያደርገው ያን ያህል ስለማያስጨንቅ ነው፡፡ ግን
የስራ ጫናው ስለሚኖር ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የስራ ጫና ዝቅተኛ ባለበት እንዲሰጥ፡፡ ግልፅ ነው
አሁን፡፡
[ዳኛቸው፡- ሀሳብ አለኝ እኔ፡፡
አበበ፡- ብታሳጥርልኝ ደስ ይለኛል፡፡
ዳኛቸው፡- አሳጥርልሃለሁ፡፡ በተለይ እነኚህ ለሁለቱ አሁን ለተባለው ጉዳይ እኛም የምናምነው
ጉዳይ ምንድን ነው፤ ለእነኚህ ኮርሶች ..... ፕሮግራም አንጋፋ እንደሆነ እናቃለን፡፡ ለምን
እኛም ከሱ ሆድ ውስጥ የወጣን በመሆናችን ማለት ነው፡፡ ሌላ ስለ..... ተነስቷል፤ .....
አሁን እንደ ፕሮግራም ራሱን ችሎ ቁጭ የሚል ከሆነ የፕሮግራሙ አተነመስ ምንድን ነው፡፡
ስለዚህ ካሪኩለም ሲዘጋጅ ባለሙያው ፕሮፋይሎቹና ኮርሶቹን ዴሊቨር የሚያደርጋቸው ሰው
ማንነው ነው፡፡ ስለዚህ እንደዚህ ካሰብን ደግሞ ወደፕሮግራማችን የምንመጣ ከሆነ ታሪክን
ጠቅሰን አሁን ምናልባት እንደተባለው ረዥም ጊዜ ነው የተሰጠው ይህ ተብሏል፡፡ .....ም
ለራሱ ለእነኚህ ኮርሶች ማስቀመጥ ይላል፡፡ ስለዚህ የ..... ኮርስ ኢንቴንሲቭሊ ከ.....
እኩል ነን፡፡ አስር ኮርስ ስወስድ አምስት .... አምስት ..... ነው የወሰድኩ፡፡
እንዲያውም እኔ እነሱን የሚገዛ የሚያስማማ ወይም የጋራ ሀሳብ ይሁነን ከተባለ በእነኚህ
በሁለት ኮርሶች ላይ አተነመስ ነን እኛ፡፡ ስለዚህ እነሱ አይደሉም እያልኩ አይደለም፡፡ እነሱም
ባላቸው የሰው ሀይል ፕሮግራሙ የሚሰካው ባለው የሰው ሀይል ነው፡፡ ስለዚህ ያ የሰው ሀይል
ያለበትን ነገር አንስተው እነሱም ባላቸው ፕሮግራም ትክክል ናቸው፡፡ ስለዚህ ለእነኚህ ሁለት
ኮርሶች በተለያየ ፕሮግራም ውስጥ ተመሳሳይ ኮርሶች ስላሉ እከሌ አድምንስተር ያድርገው
እናንተ ደግሞ እየተቀበላቸሁ እነሱ እንዲሰጡላችሁ የሚባለው እኔ ሀሳብ አልቀበልም፡፡ ስለዚህ
የሰለጠንኩበትን ጊዜየንም ያጠፋሁበትን ብዙም ነገር የፃፍኩበትም ኮርስ ስለሆነ ማለት ነው፡፡
ስለዚህ በፕሮግራም ጉዳይ ላይ በሁለቱ ኮርስ ጉዳይ ላይ አንደራደርም አተነመስ ካለን ማለት
ነው፡፡
አበበ፡- ...መስጠቱ ላይ አይደለም አሁን እየተከራከርን ያለነው፡፡ አንተ ይህን ስለተማርክ ይሄን

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADDIS ABABA

782. አትሰጥም እያልን አይደለም። ባለቤቱ ማን ይሁን መጀመሪያውኑ ማለት ነው። ባለቤቱ .....
783. ነው መሆን ያለበት። ....ን ያቆመው .... ነው ወይ? በቃ ጥያቄውን በጣም አጥብቀን
784. ስናየው። ነው ወይስ ፋንዳመንታሊ ይሄ ኮርስ ለ.... ((xxx)) ካለዚህ ኮርስ በቃ ሊሄድ
785. አይችልም ማለት ነው። ቅድም አቶ ከበደ እንደጠቀሰው .... ነው የሚለው ስሙ ራሱ ማለት ነው። ...
786. ያን ያህል ... ነው ወይ ያለው በሚለው እንስማማና ዴሊቨር ላይ ምንም ችግር የለውም። የሎድ
787. ጉዳዮች እኮ ሲገባ እኮ ...። አታስተምሩም የሚል ጥያቄ አልተነሳም አሁን። ብዙ ወስደሃል
788. ታስተምራለህ ብለውሃል እነሱም ማል ነው። ግን ኮርሱን ማን ይያዘው የሚለው ላይ አሁን መነጋገር
789. ያለብን። እዛ ላይ... ብንስማማ ደስ ይለኛል።
790. ፋሲል፡- የባለቤትነት ጉዳይ ላይ ..... እንደራሱ ፕሮግራም ነው ራን የሚያደርገው።
791. እንዲለጠፍ አንፈልግም በነገራችን ላይ። ይሄ የእኔ አቋም ነው። ከ..... ጋር እንዲለጠፍ
792. አልፈልግም እኔ ፐርሰናሊ። እንደግ ከተባለ አብረን ነው የምናድገው። ከዛ ውጭ ግን የ.....ን
793. ፕሮግራም ካሪኩለም እኛ ሪቫይዝድ እናድርግላችሁ፣ እኛ እንስራላችሁ ከሆነ ኖ እዛ ላይ ልዩነት
794. አለን። በጋራ መስራት አለብን በ.....ው በኩል ራን ማድረግ አለብን። ከ..... ውጭ
795. ያለውን እኩል ራን ማድረግ አለባችሁ የሚለው ያስማማናል። ከዛ ውጭ ከሆነ ግን .....ና
796. .....ን ነጥለን የምናያቸው አይደሉም። ስለዚህ ..... የራሱ ፕሮግራም ስላለው
797. የፕሮግራሙ ስፔሻላይዝ ያደረጉ መምህራን ....ን...የሚሄድበት መንገድ የራሱ የሆነ
798. መንገዶች አለው። ለእኛ ሰርቬይ ኤንድ ሪሰርች አንድ ሞጁል ነው። ሞጁል ስምንት ሰርቬ
799. ኤንድ ሪሰርች ስኪል አንድ ሞጁል ነው። ስለዚህ በ.... ፕሮግራም ስር ራሱ
800. የሚመለከተውን .... የሚሸቱ ....ችን ነው እዛ ውስጥ የምናስገባው። ስለዚህ
801. እዚህ .....ካልን ሁሉም ቦታ አንድ ይሁን አይደለም። የምናይበት አንግል የእኛ
802. ይለያል። ከዚህ አንግል ነው የምናየው ፕሮግራማችን .....ን ለ.... እንዴት
803. እንደግብዓት ይጠቀምበታል? ስለዚህ የምናስተምረው .... የምናመርታቸው መፃህፍቶች
804. .... የሚሸቱ ናቸው። ስለዚህ እንደዛ ማድረግ የሚችሉ የፕሮግራሙ አባላት
805. ስለሆኑ ለዛ የሚመጥን ኮንቴንት ማዘጋጀት የፕሮግራሙ ሃላፊነት ነው የሚሆነው። ለዚህ ነው
806. እንደአንድ ሞጁል ወስደን እያዘጋጀን ያለነው።...ቢያዝ እኔ ጥሩ ይመስለኛል።
807. አገሬ፡- እ በ..... ትምህርት ፕሮግራም ውስጥ .....፣ ፒውር .... ማለት ነው።
808. ካለ ይሄ አያከራክረንም አሁን ነው ያሉት ማለት ነው። አሁን እኛ እያነሳን ያለነው ፕሮግራሙ
809. .....ነው የሚለው። በደንብ ይተኮርበት ..... ነው፣ኤንድ .... የሚል የለውም እኔ
810. እስከማውቀው ድረስ ማለት ነው። ስለዚህ ስለፕሮግራሙ የምንነጋገር ከሆነ .....ን
811. እንደዋና እንትን አልቆጥረውም ማለት ነው። ሁለት ኮርሶች ናቸው .... ኮርሶች ያሉት።
812. ፋንዳመንታልስ ኦፍ .... እና .....ነው። እራሱ አይደለም። አሁን ፋሲል ባለው መልኩ ከሆነ የ.....
813. ኢለመንቶችን ነው ፊልፍለን የምናስተምረው ከሆነ ..... ስለዚህ ዲፓርትመንቱ ይቅርታ ፕሮግራሙ
814. ..... አይደለም። እነሱ የተማሩበት የሰለጠኑበት መስክ አይደለም። ፕሮግራሙ ..... ነው
815. አይደለ? ያ ነው የሚያስማማን። ..... ከሆነ እኩል አይደለም የ..... እንትኑ ማለት
816. ነው። ብእርግጥ ኦራል ..... አለ እሱን ማነው የሚሰጠው ከ..... ጋር በጣም እንት
817. የተባለ ስለሆነ በእነሱ ውስጥ ሞጁል ሊኖረው ይችላል። አሁን የ..... ኮርስ ፒዩር
818. ..... በ..... ውስጥ እንደአንድ ሞጁል አለ ካልን ኢቪደንስ ማቅረብ ነው ምንም ችግር
819. የለውም። አለን ካለን ሁለት ኮርስ ቼር ተመድቦለታል ማለት ነው ችግር የለውም። አሁን
820. እንደ.....ስናየው በ..... ፕሮግራም ውስጥ የፎክለር ኮርሶች ናቸው በጣም ብዙ ያሉ። አሁን
821. ያው ግለሰቦች የተማሩትን ትምህርት ማንሳት የለብንም የምንለው እዚህ ጋ ነው። ከእኛ
822. ትምህርት ክፍል መተው ፖይትሪ ሊያስተምሩ ይችላሉ። ምህረት አስተምራለች፣ አምሳሉ
823. አስተምሯል፣ ..... አስተምራለች። እሱ አይደለም አሁን እያከራከረን ያለነው። ዲፓርትመንቱ
824. ወይም ፕሮግራሙ ..... ነው ኤንድ ..... የሚል ነገር የለውም። ስለዚህ የኮርሱ
825. ባለቤት የ..... ትምህርት ፕሮግራም አይደለም፤ እያልን ያለነው። ዴሊቬሪው ላይ ችግር
826. የለውም። እሱ ላይ ተስማምተናል እኮ። እነሱም እኛ ጋ መስጠት ይችላሉ፤ እኛም እነሱ ጋ።
827. ግን ባለቤትነት ላይ ስንመጣ ግን የሚያስማማን ነገር..... ውስጥ ነው የሚመጣው ማለት
828. ነው። ...አንብበዋል ብዙ የጥናት ወረቀቶችን ሰርተዋል፤ እሱ ላይ አልተከራከርንም አሁን፤ ግን የእነሱ

ፕሮግራም የሚለው የተለየው ለዛ ነው ...፤ አንዱ ..... ነው አንዱ ..... ነው። ስለዚህ የባለቤትነት
ጥያቄ ሲመጣ ወዴት እንደሚሄድ እንግዲህ በቀጥታ የሚያሳየን ይመስለናል።
አበበ፡- ቆይ አንዴ እሰቲ፤ በዚህ አይነት የምንጨርሰው አልመሰለኝም። ....ላድርገው .....
ትምህርት ክፍል፣..... ጎኔ ነው። .....ን አወጣችሁት ማለት.. ዜን የሚገባን ነገር
አለ። 38 ክሬዲት የሚደርሰው ..... ነው። .....ም ላይ እነዚህ የ.....ን ካሪክለም
የገነቡትን ፒላሮች ንገሩንና ..... የት ላይ እንዳለ እንወቅ። ከዛ በኋላ ሁለቱን ለመመዘን
ያስችለናል።
ዳኛቸው፡- ምናልባት ብሬክዳውኑን ለመስራት በጣም ስፔስፍኬሽን ይህ አሎኬሽን በዛ ላይ ሰፊ
ነገሩን ኢንቮልቭ ያረኩት እኔ ነኝ። ስለዚህ ..... ውስጥ ኢንኮርፖሬት የተደረጉ ኮርሶች
አጠቃላይ ካየናቸው ኦልሞስት ስድስት ኦር ሰባት ፌዝ አላቸው፤
አበበ፡- አንድ ..... ሶስት ኮርስ።
ዳኛቸው፡- ሶስት ኮርስ፤ ሶስት ሶስት ነው ትክክል ነህ። ሌላ ከዚህ ከ..... ጋር የሚቀራረብ
ለምሳሌ .... አለ።
አበበ፡- ኦራል ..... ብላችሁ ነው የምታስተምሩት?
ዳኛቸው፡- ኖ ....። እነሱ ኦራል የሆኑ ነገሮች ከስኪል ጋር ስለሚያያዙ ለብቻቸው
በስኪል ውስጥ ነው ትሪት የሚደረጉት።
አበበ፡-ይሄ አንድ ኮምፖናንት ነው የ.....?
ዳኛቸው፡- አንድ ኮምፖናንት ነው።
አበበ፡- ስንት ኮርስ ናቸው።
ዳኛቸው፡- ስድስት አካባቢ ናቸው።
[ፋሲል፡- ስድስት ኮርስ ናቸው። ኦራል ናሬቲቭ ዋን አለ፣ ኦራል ናሬቲቭ ቱ አለ፣ .....
አበበ፡- አይደለም ሁለቱን አትቀላቅል። የ.....ን ቅንታቶች እያወጣን ነው። እዚህ ውስጥ
ሁለት ነው የነገራችሁኝ ገና። ስትሪም ልንለው እንችላለን ወይም። እነሱን ነው እንድትነግረኝ
የምፈልግ።
ዳኛቸው፡- ልክ ነህ፣እኔም የነገርኩህ ለዛ ነው።
አበበ፡- አንድ ..... አልከኝ፣ ሶስት ኮርስ፤ ኦራል ፖይትሪ አልከኝ፣
ዳኛቸው፡- ..... የሚባል ሁለት ፌዝ ነው ያለው፤ ስትሪሙ .....
በሚል ነው የተካተተ። ከ..... ይለያል። አንደኛው ፓርት በዛ አለ። በሌላው ደግሞ አሁን
የ..... ያለበት ሶስት ኮርሶች ያሉበት ማለት ነው።
አበበ፡- እሽ ሌላ ንገረኝ ደግሞ
ዳኛቸው፡- ከዚህ ውጭ ያሉት ምንድን ነው ከሳይኮሎጂ እነኚህ ገስት ሌክቸረር እንጋብዝበታለን
ያልነው ኤክሌክቲክ ኮርሶችን አንድ ላይ ይቀራረባሉ ብለን ያመጣናቸው አሉ።
[አለሙ፡- መጠሪያቸው ምንድን ነው?
ዳኛቸው፡- ብሄቬራል ምናምን የሚል ነገር ይመስለኛል።ብሬክ ዳውኑን ይዘኸዋል?
ፋሲል፡- ሞጁል ላይ ሞጁል ቱ ላይ ኦራል ..... የሚል አንድ ሞጁል አለ። ኦራል ናሬቲቭ
ዋን አለ፣ ኦራል ናሬቲቭ ቱ አለ፣ኦራል ፖይትሪ አለ።
[አለሙ፡- ቅድም የነገረን
ፋሲል፡- ፕሮቨርብ አለ
አበበ፡-ስለዚህ ስኪል ሳይሆን አትቀላቅሉብና፣ስኪል ሳይሆን...
ፋሲል፡- አዎ እሽ።
አበበ፡- ኦራል ..... ብለን እንይዛቸዋል፣ ..... ለብቻ እራሱ አለ። ሁለት
ነግራችሁኛል። እነዚህን ምን ትሏቸዋላችሁ? አሁን የጠራችኋቸውን።
ዳኛቸው፡- ብሄቨራል ምናም፤
[መለሰ፡- በምን ውስጥ ነው ያሉት? የሞጁሉ ስም ማነው ፋሲል?
[ከበደ፡- ፎር ከስተም አለ። እኮ ያው ስለሚጠይቅ ነው እንትነው ይላል ወይ ከስተም ነው...
አበበ፡- ከስተም እንበላቸው ፎር ከስተም?
ፋሲል፡- ፎር ከስተም ኤንድ ሙሲኮሎጂ ማለት ይቻላል።

አበበ፡- ..... ማለት በካሪክለማቸው መሰረት የእነዚህ ስትሪሞች ውጤት ነው ማለት ነው።
..... 9፣ ኦራል ..... 9፣ ፎር ከስተም ኤንድ ምናምን የሚል ነገር አለበት ተጨማሪ
16 ክሬዲት አወር፤ ..... ኤንድ ብሄቨር 10፣ ኮመን ኮርስ 15 እና የእነዚህ ኮርሶች ናቸው።
አልተከፈለም አይደል ኦራል .....፣ ሪትን ..... ምናምን የሚል ነገር አይደለም።
ፋሲል፡- አዎ ኦራል ..... ካነሳህ ሪትን ..... ይነሳል።
አበበ፡- እዛ ወስጥ ነው?
[ዳኞቸው፡- በሞጁሉ ውስጥ ተከፍሏል።
[ደበበ፡- ወደዝርዝር ገባን፣...ማን ከማን ጋር ይሄዳል የሚለው ነው ዋናው።
አበበ፡-ወደዚያ ጥያቄ ልመጣ ነው። ወደስድስት ናቸው አንድ ሁለት ሶስት አራት አምስት
ስድስት፣
[ከበደ፡- እኔ ከዛ በፊት፣
አበበ፡- ከዛ በፊት፣
ከበደ፡- እኔ ይልቅ አሁን እየተደረገ ያለው ነገር ከልብ የሚያግባባ አይደለም። ለምን የልክ
አይነት አካሄድ ነው። እና ዝምብለን ተግባብተን በጋራ ብንሰራው ነው የሚሻለው።
አበበ፡- በምን እንግባባ እሽ፤ መፍትሄ ካመጣህ ደስ ይለናል።
ከበደ፡- አጠቃላይ ..... እኮ አርት ነው። ኦራል ከመሆኑ ውጭ አርት ነው። ኦራል
.....ም የምትለው አርት ነው። እዛ ውስጥ ኦራል ናሬቲቭ የተባለው ሌሎች አላነሷቸውም
እንጅ ፕሮቨርቡም ምኑም ምኑም እኮ አርት ነው። እና የምናወራው አሁን ስለሪትን ሊትሬቸሩ
እኮ ነው። ስለዚህ እነዛን አንደኛ ለልጆቹ የሚጠቅመው የትኛው ነው የሚለውን ነው ስናስበው፣
እና እዚህ ብዙ ኮርስ ነው ያሉት በኮርስም ብዛት እንደምረውም ካልን። እና ዝምብለን እዚህ
አድርገነው፣ በጋራ እንስራ እኛ ጋ እነሱም ያሰተምሩ ዞሮ ዞሮ ሎድ ባለበት ቦታ ላይ
የሚጠቅመው እሱ ነው።
አበበ፡- እሱን ተነጋግረንበታል። ባለቤትነት ላይ መስማማት ስላቃተን ነው። እነሱ ሌላ ነገር
ስለመዘዙ፣ ልንስማማበት የምንችል ሌላው ሎጅክ ያለውን ቦታ መመዘን ነው ወደሚል አቅጣጫ
መጥቼ ነው። አያስኬድም ከተባለ ይቻላል። ግን ካላስኬደ ሌላ አማራጭ፤
[ፋሲል፡- አሁን ሌላ አንድ ነገር የሚያስኬድ ሆኖ፣ጋሽ ከበደ ያለው ነገር የሚያስኬድ ሆኖ ግን
አያስማማንም። እነሱ ሰፊ ይዘዋል ..... ደግሞ...
[ከበደ፡- ኮሚቴ አልገባም፣በጋራ ነው የሚሰራው
አበበ፡- መጀመሪያ የምንተማመነው ባለቤትነት ላይ ነው። አለማየሁ የተለየ አቋም አለህ።
አለማየሁ፡- ኦኬ፣ በጋራ እንወያይ የጋራ አቋማችን ማለት ...እንነጋገርበት የጋራ አቋም እናውጣ
ያስኬደናል። እዚህ ላይ የባለቤትነት ላይ እስካሁን ልክ በመስኩ የባለሙያ እጥረት ስላለ ያው
አንዱ ከሌላው ጋር አብሮ እየሰራ ቆይቷል አይደለ፤ አሁን ግን ባለሙያ ከመጣ ዋይ ኖት
እሳካሁን ይሄ ጥያቄ ስላልተነሳ አሁን መነሳት የለበትም፤ እኔ አይታየኝም። ጥያቄው ተነሳ
በጋራ ለወደፊት እንስራው ያስኬደናል።
አበበ፡- መፍትሄ አምጣ እስኪ
አለማየሁ፡- እንወያይበት፤ ለምሳሌ ኮርስ ቼር አለው ብላለች ዝግጅታችን ይታይ፤ በ.....
ስፔሻላይዝ ያደረገ ሰው ካለ የተሻለ ሊሰጥ የሚችልው ለተማሪዎቹ እሱ ስለሆነ እሱ ይሰጣል
ማለት ነው።
አበበ፡-እኔ አሁን ባለቤቱን ነው። ባለቤቱ ..... ያልነው ነገር ይስማማናል?
[አገሬ፡-ያው እኔ አንድ
[ደበበ፡- እኔ አሁን ትንሽ እንትና ያለው የሚመስለኝ የሚመስለኝ የተነሳም ነገር አለ። የኮርስ
ባለቤትነት ጥያቄ አሁን ያመጣው ነገር አለ የሚል እንትን አለ። ግልጽ ሆኖ ተነግሯል። ይህን
.....፣ ..... የሚለውን ልተው፤ ..... እንትን አለ ..... ውስጥ ካሁን በኋላ፤
ስለዚህ እሱነው ባለቤቱ ብለን ከወሰን ሌሎች በሙሉ ስለዴሊቬሪው ጭምር አብሮ መነሳት
አለበት የሚል ነው የሰማሁት። እናም እንትን ማድረግ ያለብን ስለዴሊቬሪው ምክንያቱም
እየፈራህ፣ እየፈራን ኮርስ ስትሰጥ ችግር ያመጣል። አቶ ፋሲል እኮ ያነሳው አለ። ክረምት ላይ
ማነው? ኤክስቴንሽን ሲመጣ ማን ነው? ዲስታንስ ሲመጣ ማነው? .....ን እየሰጠን

ወደዚያ እንዲያ ከሆነ የሚል ጥያቄ ነውና እየተነሳ ያለውና ይልቅስ እንትን ማድረግ ያለበት
..... እዚህ ጋ ይሁንና ምንድን ነው እነዚህ ኮርሶች ..... ውስጥ ያሉት እዚህ ጋ
ይሁኑና ነገር ግን በማንኛውም ጥቅማጥቅም ሆነ ምን እኩል መሆን አለበት ወደሚለው
እንምጣ ይመስለኛል። ፍራቻው ይሄ ነው። የተነሳው ጥያቄ ይሄ ነው። አቶ ፋሲልም
አንስቶታል። እና ከዚህ ጋ ነው እንግዲህ እንትኑ ያለው። ስለዚህ ለዚህ መፍትሄ ከሰጠን፤
አበበ፡- ሌላውን ተነጋግረንበታል፤ አሁን አቶ ደበበ እንዳለው ዴሊቬሪ ላይ የሚነሳ
ጥያቄ፣ ዴሊቬሪ ላይ ፕሮግራሞቹ ባይሉትም እንኳ ኖ እንላለን። አንዱ ለብቻው ጥቅም ሲያጋበስ
እና ሌላኛው አንደር ሎድ ሲሆን ኖ ማለታችን አይቀርም። አክሮስ ዘ ፕሮግራም አንድ ላይ
ሲመጣ ማን ይሁን ምናምን ፈርዘር መወያየት ነው ምንም ችግር የለውም። ቁጭ ብሎ
መወያየት ነው። እንደባለቤትነት ላይ ግን እዚህ ላይ እንስማማ። እዚህ የመዘነው ነገር
የሚያሳየን .... ላይ ቦታ አለው የ.....ን ያህል የከበደ ቦታ የለውም። .....አታስተምሩም
አልተባሉም ይሄ መብቱ አላቸው። እ የሎድ ባላንስ አጠቃላይ የሎድ ሳመሪ ማየት።
የሁለቱም በፕሮግራም ደረጃ የሚያልቅ ጉዳይ ነው። ውብነሽና ፋሲል አጠቃላይ ..... ትምህርት ክፍል
ምን ያህል በኦቨር ሎድ አለ፣ ወይም አንደር ሎድም ሆኖ ምን ያህል በርደን አለው፤ ሶ .....ም ምን
ያህል በርደን አለው የሚለው ማየት። ከዛ ተነስተው ... ከአሁን በፊትም አላየንም፤ በዛ በኩል
የሚልቅ ይመስለኛል።
ዳኛቸው፡- ይሄ ባለቤት ለኮርሶቹ ባለቤት የምትለው ጉዳይ አንዱ ፕሮግራም ፕሮግራሙ ቆሞ
ለዛ ለፕሮግራም ኮርስ ባለቤትነት ኦቶኖሚውን ሲሰጠው የሚሰራውንና የሰለጠነበትን ጉዳይ
አይቶ ነው። እኔ የ002 ፕሮግራም ለእነኚህ ኮርሶች ባለቤት መሆን አይችልም ከተባለ
ውድቀት ነው። ስለዚህ ባለቤት የማይሆንበትን ምክንት የሚያስረዳ አካል ሊመጣ ይገባል ማለት
ነው። ይህን ሊመጣ ሲገባ ስፔስፍኬሽን ውስጥ ይገባል። እንዲያውም እኮ በጣም አከረርክ
አትበሉኝ እንጂ እንዲያውም አክሮስ ከ..... ልንሄድ እንችል ነበር ጊዜው ቢፈቅድ ማለት
ነው። ጊዜው አልፈቀደልንም።
አበበ፡- አልገባኝም
ዳኛቸው፡- አባባሌ ታቃለህ፣ ይሄ ለ..... ኮርሶች ኦቶነመሱን እኛ ነን የምንወስደው።
የፕሮግራሙ መሪዎች ከዛ ስልጠናቸው። ..... ሲከፈት እኮ ለዛ ባለሙያ ምን አይነት
ሰልጥኗል፣ ምን ነገር ወስዷል፣ ምን አዘጋጅቷል ነው። ስለዚህ ለእነኚህ ሁለት ኮርሶች
ፕሮግራሙ ባለቤትነት መብት ወይም የባለቤትነት የማይሰጠው ከሆነ ሌላ ጉዳይ ሊያስነሳ ነው
ማለት ነው።
አበበ፡- አንዴ እሰቲ ልጠይቅህ። አግሪካልቸር ፋካሊቲ ስታት ባለሙያ አላቸው። ከዚህ በኋላ
እኔ ማንንም ሰው መምህር መደብ አልልም። ባለሙያ አለኝና ራሴ ነኝ የምመድበው አለ። ...ሶ
አሁን አንተ እያነሳህልኝ ያለህ ስለዚህ ባለሙያ ስላለው ሊጠይቅ አይገባውም። ዲፓርትመንቱም
አግሪካልቸር ጋ ነው ክሌም ሊያደርግ አይገባውም ማለት ነው። ሰም በዲ ሃላፊነት መውሰድ
አለበት። ሪጀክት ነው የተደረገ ቅጥሩ። ስታት እዚህ አለ ባለሙያ አንተ ጋ ሊኖር ይችላል፣
ሌላም ጋ ሊኖር ይችላል። እዚህ ጋ ትምህርት ክፍሉ እስካለ ድረስ በባለቤትነት ራን ማድረግ
ያለበት እሱ ነው። ስታት ግን እኮ በጣም ያስፈልጋቸዋል። አስፈላጊ ነው በቃ፤ እሱን ካልወሰዱ
የሆነ ነገር ይጎላል ምንም ጥርጥር የለውም። እንደዛም በመሆኑ ይወሰዳሉ ኮርሱን። እና
..... አትወስዱም አይደለም፤ ..... የ..... ፓርት አይደለም፣ አይደለም ጥያቄው።
በሜጀሪቲው ሲነሳ ግን አንድ ነው ባለቤት መሆን ያለበት እሚለው ላይ እነዚህን ያየናቸውን ሌላ
ክራይቴሪያ ካመጣችሁ እንወያይባቸው።
[አለሙ፡- (ብዙዎች እድሉን ለመውሰድ በመደራረብ ሀሳብ ቢያነሱም የአለሙ ድምፅ ቀጥታ
ሀሳቡን ማውራት በመጀመሩ ሌላውን በመጫን በማድረግ ቀጠለ) መጀመሪያ እ እንትኑ የሚፈታ
መስሎኝ ነበር። በአንድ በኩል አብሮ የመስራት መንፈስ አለ፤ በሌላ በኩል የኮርስ ባለቤትነት
አለ። የኮርስ ባለቤትነት እንትን የዚህ ዲፓርትመንት ብቻ አይደለም። በዩኒቨርሲቲው የተለመደ
ነው። አሁን አሁን ኮመን ኮርስ እየሳሳ መጣ እንጂ እነሳይኮሎጂ፣ ..... ብዙዎች ኮርሶች
ኢዱኬሽን ሁሉ ባለቤት ሆነው የሚስተናገዱበት አግባብ አለ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ። እና ሁለቱ
አልጣጣም ስላለኝ ነው። በአንድ በኩል አብረን እንስራ የሚለው እንት የሚወደድ ነው። በሌላው

በኩል የባለቤትነቱ ጉዳይ ደሞ እነዚህ...ሆኖ ካልተገኘ፤ እና አሁን ምሳችን እየራበን ስለሆነ እኔ
ግን የምንጨርሰውም ስላልመሰኝ በዚህ አያዛችን ወይ አድረን መወያየት ካለብን መወያየት ነው
ያለዚ ደግሞ እንግዲህ
[መለሰ፡- አይ በቃ!
አበበ፡- ቆይ ሁላችሁም አንድ ጊዜ
[ደበበ፡- ጥያቄ፣ ጥያቄ ለሁላችንም የሚሆን፤ .....፣ ..... እኔ ..... ለንትኑ
ነው አጠቃላይ...የምጠይቀው፡፡ .... የሚል ቼር ማቋቋም ይቻላል ወይ?
አበበ፡- ሁለት ባለቤትነት አይፈቀድም፡፡
ደበበ፡- ቆይ እንደገና እንድናስብበት ነው፡፡
አበበ፡- ሁለት ባለቤትነት አይፈቀድም፡፡ ባለቤቱ አንድ ነው የሚሆነው፡፡ የተለያዩ ፕሮግራሞች
ግን ሊኖሩት ይችላሉ፡፡ ሶ አሁን በዚህ ሎጅክ መስማማት ካልቻልን በድምፅ ብልጫ
አናደርገውም፡፡ ወደአድሚንስትሬሽን ርምጃ መሄዳችን አይቀርም፡፡ ወደአድምንስትሬሽን ርምጃ
ለመሄድ ግን በተለመደው ስርኣት የኮርስ ባለቤትነት የእኛ ፋካሊቲ አዲስ አይደለም፡፡ ሁለቶችም
ፕሮግራሞች ተወያይተው ሎጅኮቻቸውን ይዘው ይመጣሉ፡፡ ከዚህ አድምንስትሬሽን እንትን ግን
ቅድም መጀመሪያ አጀንዳ አንድ ላይ ካፒታላይዝ አድርገን አብሮ መስራት የሚለውን ነገር
በሎጅክ ብንስማማ በጣም አሪፍ ነገር ነበር፡፡ ታይሙንም ያጠፋሁ ለዛ ነበር፡፡ እነፋሲል
ሃሳባችሁን የማትቀይሩ ከሆነ በዚህ እንሂድ፡፡
ፋሲል፡- መቀየር አለመቀየር ጉዳይ አይደለም ነው፡፡ በጋራ መስራታችንን እንስማማለን፡፡ ግን
እንዴት የሚለው ስቲል መፍትሄ አላገኘም፡፡ ተንጠልጥሎ ነው ያለ
አበበ፡- በቃላት አይደለም በተግባር ሲገለፅ ነው፡፡ ምንም በቃ አቶ አለሙ ያለው እኮ ነው ኢት
ወዝ አርቲፊሻል፡፡ መጀመሪያ የተነጋገርነው ነገር ከልባችን አልነበረም ማለት ነው፡፡
ኮምፕሮማይዝ ማድረግ አልቻልንም፡፡
[ከበደ፡- በጋራ የሚለውን ብንስማማበት ጥሩ ይመስለኛል፡፡ ወደአስተዳደር ውሳኔ የምንሄድ ከሆነ
ያ የጋራ ስምምነት ሁሉ ይፈርሳል፡፡ በጋራ ተግባብተን እያንዳንዷን ጥቃቅን ነገር እያየን
እንስራ፡፡
መለሰ፡- ግዴለም እንዲያው አንድ ነገር እንስራ፡፡ እስካሁን ያለው ነገር ጥሩ ነበር
አመጣጣችን፡፡ አሁን ወደመጨረሻ የመጣች አካባቢ ነች ነገሯን እያበላሸች ያለችው፡፡ ስሜቱ
የእንዳንዱ ስሜት ስለሆነ ያን ስሜት ብዙም ባንጠላው፡፡ ጥሩ ተመቶ እያለ አሁን የኮርስ
ባለቤትነት የሚመጣውን ... አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አሁን አንድ ላይ ተሰብስበው የለ፤
.....ና እንትን ወደዚያም እኮ እያሰብን እኮ መሄድ አለብን፡፡ እና ተለያይተን የኦቶነመስ ጥያቄ
ሊዘልቅ ይችላል ብለን ማሰብ አለብን? እሱ እኮ እኔ እንዲያውም እንድናስብም አልፈለኩም
ነበር፡፡ ኦቶነሚ የምትለው ነገር ኦቶነሚ የምትለው ወደአንድ የምንሆንበት ነው የሚሄደው፡፡
ትሬንዱ እንደሱ ነው፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኤም ኤ ፕሮግራም የከፈቱ ፕሮግራሞች
ታጥፈው አንድ ላይ መተዋል፡፡ ይሄ ትሬንድ የሌለውን ትሬንድ እያሳየን ነው ያለው፡፡ የእኛም
ትሬንድ እንደዚ ነው ላይክሊ የሚሆነው፡፡ ስለዚህ ይሄንን ነገር ኦቶኖሚ የሚለውን በታም
ኤግዛጆሬት በሆነ መንገድ ከምናስበው ጥሩ መተን መተን ያለንበትን መንገድ እንያዝና ትሬንዱ፣
ትሬንዱ የነበረውም ሂስቶሪካል ባክግራውንዱም የሚነግረን ..... ስለሆነ የ..... ሰው
ያስተምረው እያልኩ አይደለም ያለሁት፡፡ እነዚህ ሰዎች ሰልጥነዋል፡፡ እኔ ሊንጉስቲክስ ከመግባቴ
በፊት .....ን ለብዙ አመት አስተምሬዋለሁ፤ይሄን ሰርቼ ..... ፎር ዛት ማተር፡፡ ለብዙ አመት እዚህ
ብዙ ሰው የሚናገረው ነው፡፡ አንችልም አይደለም ሁላችንም የዛ ባክግራውንድ ያለን ሰዎች ነን፡፡
ሁላችንም ....ተብለናል፡፡ ሀላችንም የዛ ባክግራውንድ አለን፤ አለን፡፡ ግን ማን ጋ
ይሁን? ለመጠራቱ ነው፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ .... ተብሎ ነው የሚጠራው፡፡ ያን
ትሬንድ ይዘን ብንሄድና በማስተማሩ በኩል እየተመካከርን የሊትሬቸሩን ሰው ከፋሲልም ሆነ
ከሚመጣው ቸር ፐርሰን ጋር እየተመካከረ ሎድ አሳይን እያደረገ ቢሄድ የሚያበቃው ነገር የለም፡፡
በዚህ ብንሄድ ነው የሚሻለው፡፡ ፎርማል ወደሆነው መንገድ አንሂድ፡፡
አበበ፡- ለዛ ነው ጊዜያችንን ያጠፋን ማለት ነው፡፡ግን መፍትሄ ከሌለው ምንም ማድረግ
አንችልም፡፡ እና እነፋሲል...

ፋሲል፡- እንዲህ እናድርግ እንዲህ እናድርግ፡፡ አንድ የመጣልኝ ሀሳብ ምንድን ነው፤ የመጣልኝ
ብቻ ሳይሆን ዶር ሲሉ፣ ጋሽ ከበደም ሲሉ አልተለያየንም፡፡ አሁን የመጣልኝ ሀሳብ ምናልባት
ኤኒ ነገር መሄድ እንችላለን፡፡ ሪሊ በዛ መስማማት ከቻልን ችግር የለብንም፡፡ አሁን ሁልጊዜ ዶር.
ያልከው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ነገር ምናምን ነገር አማሪክ ላንጎጅ፣ .....፣..... ፔንድ
አይደለም አንድ አድርገውታል፡፡ እንደዛ ሲሆን 110 ክሬዲት መውሰድ ካለባቸው 15
.....፣15 ..... መርጅ ሲደረግ፡፡ እንትኑ አለ ችግር የለብንም፡፡ እንደዛም ለመስራት ግን
አሁን ያለው እንትን መፈጠር መቻል አለበት፡፡ እንደእኔ ግን አሁን በእርግጥ እንስማማለን፡፡
ውብነሽና እኔ ልንፈታው ስለማንችል እንዲያው አይዲያውን ለማስታረቅ ሌሎች አታግዙንም
ወይ የሚል ነገር አለኝ፡፡
አበበ፡- እሽ መተጋገዝ እንችላለን ምንም ችግር የለው፡፡ ሁለታችሁ መስራት ትችላላችሁ፡፡ እኛ
ጋ ኦረዲ ችግር የለውም ሶስት ሰው ያለበት ኮሚቴ ሶስት ሰው ጨምሮ ማድረግ ይቻላል፡፡
ጥቅማጥቅምን በሚመለከት ማለት ነው፡፡ ይህን የምናደርገው የመጀመሪውን ከተስማማን ነው፡፡
ቃለጉባዔ ፀሃፊ! እ ባለቤትነትን ..... ይይዘዋል፡፡
[ዳኛቸው፡- እ እዚህ ላይ ሀሳብ አለኝ፡፡
አበበ፡- እሽ በልዩነት ሊያዝልህ ይችላል፡፡
ዳኛቸው፡- በልዩነት ሳይሆን፣ የበላይ አካል ቢያንስ ይሄ ነገር ተካሮ ወደላይ ከሚሄድ መባሉ
ጥሩ ነገር ነው ይስማማኛል፡፡ የበላይ አካል ሲሄድ ምንድ ነው የሚያያቸው ክራይቴሪያዎች?
እነሱንም ጥቁምታ ውስጥ ማስገባቱ...
[አበበ፡- ልንወስደው እኮ አይደለም አሁን
ዳኛቸው፡- ይገባኛል፡፡ አሁን በባለቤትነት ደረጃ ይሰጥ ሲባል፤ እንግዲህ እነ እንትን በ.....
ፕሮግራም ውስጥ የባለቤት ደረጃ ራን የሚያደርገው ከሆነ የስፔሻላይዜሽን ጉዳይ ደግሞ በበላይ
አካል ሊታይ ይችላል፡፡ ስለዚህ እኔ አሁን የምከራከረው ከስፔሻላይዜሽን ነው፡፡
[አበበ፡- ምንም ችግር የለውም፤ ያ ዴሊቬሪው ነው፡፡ በዋናነት አሁን የምንይዘው እዛ ደረጃ
ስላልተደረሰ ቀድም በተነገሩት መንፈሶች ተባብሮ በመስራት መንፈሶች ሁሉም ትምህርት ክፍል
ለዛ ነው የሚሰራ ባይ ዘ ዌይ እንጂ ኮርስ ቼሩ ነው በዋናነት ሃላፊነት የሚወስደው፡፡ ማንኛውም
ሲመደብ የመደብከው ሰው በቃ ፊት አያደርግም ሁላ ተብሎ ሊጠየቅ የሚችል ማለት ነው፡፡ እዛ
ደረጃ ላይ ግን የምንደርስ አይመስለኝም፡፡ በርካታ፣ በርካታ ስራዎች ስላሉ እና ብዙ አሳሳቢ
አይሆንም .....
ዳኛቸው፡- ምናልባት የእኔ አባላቶች ከተስማሙ ቄል፡፡ ለእነሺህ ለሁለት ኮርሶች ግን እኔ በዚህ
ስንት አመት ስሰራ ቆይቼ ለሌላ አሳልፌ መስጠት ከፕሮግራሙ ህልውና አንፃር አይታየኝም፡፡
[አበበ፡- አሳልፎ በመስጠት መንፈስ ባታያቸው ደስ ይለኝ ነበር፡፡
ዳኛቸው፡- ስለዚህ እኔ
ተሰብሳቢው፡- (ሁሉም ለመናገር በመደራረብ ተናገሩ)
አለሙ፡- ለዚህ እኮ ነው እንሂድ ያልኩት ምክንያቱም አሁን የምንግባባ አልመሰለኝም፡፡
አበበ፡- አሁን እኮ ተግባብተናል፤ ተግባብተናል አሁን፤ በቃ ኢት ኢዝ ናችራል
አለሙ፡- ዶሚኔትድ እንዳይሆን እሰጋለሁ፡፡
[መለሰ፡- ሶሪ የስብሰባ ደንብም እንከተል እንጅ በጣም ሁለታችን ወደአንድ ፎረም
ከመጣን የሃሳብ ልዩነት ብዙም እኮ ሊኖር አይገባም፡፡ ፐርሰንቱን እንይ፣ የሀሳብ ልዩነት አሁን
ሁለት ሶስት ጊዜ እዋዥቅ የለ፣ ምን እንትን አለ፡፡ አሰራር ላይ ችግር ከተፈጠረ ፋሲል
እንደሚለው በመግባባት እዚህ አለን፣ ኮርስ ቼር አለች፣ ፕሮግራም ማናጀሩ አለ የእሱም
ምስክርንት የሚስፈልገው ለዚህ ነው፡፡ ሲኒየር ስታፎችም እዚህ አለን በመግባባት ሶልቭ
እናደርገዋለን፡፡ በቃ በዛ መንገድ ነው መኬድ ያለበት፡፡ ወደፎርማሉ በጭራሽ እኔ አልደግፍም፡፡
ደበበ፡- የ..... በሁለቱም ትምህርት ክፍሎች ያሉት ስታፍ እንትን እንዳለ....
[መለሰ፡- በቃ እንደዚህ ይሁንና በቃ...የሌላሰው ችግር ሄደን የምናቃልል ሰዎች የራሳችን
አበበ፡- አዎ በቃ፣እናመሰግናለን! በዚሁ ተፈታ ማለት ነው፡፡
ዳኛቸው፡- አይ፣ እኔ በልዩነት ይያዝልኝ!

መለያ ቁጥር አኮ.003

ይህ በጽሁፍ የተገለበጠው መረጃ ለ2 ሰዓት ከ40 ደቂቃ ያህል የተደረገ የአኮ003 ፋካሊቲ የአካዳሚክ ኮሚሽን ስብሰባ ነው። ይህ ስብሰባ በመረጃነት እንዲያገለግል የተመረጠው በዕለቱ የተለያዩ ጉዳዮች የተነሱበትና ረጅም ጊዜ የወሰደ በመሆኑ ወካይና ኑባራዊነት ያለው መረጃ ይሆናል ተብሎ ስለታመነ ነው።

የስብሰባው ቀን፡-16/09/2004
ሰዓት፡- 8፡00
ቦታ፡- የፋካሊቱው ዲን ጽ/ቤት
በስብሰባው የተገኙ አባላት፡-

1. ወ/ሮ ሮዛ፡- ሰብሳቢ የፋካሊቲው ዲን
2. አቶ ጌትነት፡- አባል የፕሮግራም ተጠሪ
3. አቶ ጋሻው፡- አባል የፕሮግራም ተጠሪ
4. ወ/ሮ መቅደስ፡- አባል የፕሮግራም ተጠሪ
5. ዶር አበበ፡- አባል የፕሮግራም ተጠሪ
6. አቶ ተስፋ፡- አባል የፋካቲው ሪጅስትራር ሃላፊ
7. ዶር ሀይሉ፡- እንግዳ የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ም/ፕ

1063. ...ሮዛ፡- እንጀምር በቃ አሁን መጀመር የምንችል ይመስለኛ። ስለዚህ አንደኛ አጀንዳ ቃለ ጉባኤ
1064. ማፅደቅ፣ ሁለተኛ የተማሪ ጉዳይ፣ : 3ኛ ኮንትራት የማራዘም ጉዳይ፣ አይደለም? የመምህር
1065. ጉዳይ ሶስተኛ ...
1066. ስለዚ-ህ ሁለት ናቸው : ያሉን... ቃለጉባዔዎች። አንዱን ዳዊት ነበር የፃፈው አንግዲህ ይዞ...
1067. በዛው ነው የቀረው። አኮ 20ን እንጀምርና ከዚያ ወደ አኮ 21 እንሄዳለን። አይደለም 20?
1068. ዶር. ሀይሉ፡- መግባት ይቻላል?...
1069. ሮዛ፡- አዎ
1070. ዶር. ሀይሉ፡- ወይ ካልሆነ የጀመራችሁት ትጨርሱ?
1071. ሮዛ፡- እ ይሄኛውን ብናስጀምር ይሻላል።
1072. ዶር ሀይሉ፡- እ
1073. ሮዛ፡- ይሄኛውን ብናስቀድም ይሻላል። አይሻልም?
1074. መቅደስ፡- እ
1075. ሮዛ፡- ምርጫው ይቅደም መሰለኝ።
1076. በእውቀቱ፡- ብዙም አልገፋንም።
1077. ሮዛ፡- ገና እየጀመርን ስለሆነ፣....
1078. ዶር. ሀይሉ፡- ለዲንነትና ለሃላፊነት በሁለት መልኩ ነው የምናስመርጠው፤ አንዱ
1079. ለህብረተሰቡ ለኮሌጆችና ኢንስቲቲዩት መምህራን እንዲያመለክቱ ይደረጋል። ሌላው ደግሞ
1080. ዩኒቨርሲቲው ማናጅመንት ከሚመለከተው ኮሌጆች ጋር በመነጋገር ዲን ጋር በተለይ በመነጋገር
1081. ((xxx))የሁለቱ ማለት በግል ያመለከቱትና በዩኒቨርሲቱው ማናጅመንት በኩል በእጩነት
1082. የቀረቡት በአንድ ላይ ለምርጫ ይቀርባሉ። አንዳንዴ ወጥነት እንደሌለው አያለው እኔም ራሴ።
1083. ለምሳሌ ((xxx)) የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ብዙ የሚልበት ሁኔታ የለም። ምናልባት መጀመሪያ
1084. ሀሳቡ እንደተጀመረ ብዙ ነገሮች ይመጡ ነበረ። በአካዳሚኩም ዘርፍ በአስተዳደሩም ዘርፍ..
1085. ሲባል የተወሰኑ ግለሰቦች ላይ ቢሆንም እና ደግሞ አንዳንድ ጊዜ ኦብጀክቲቪቲ ቢያጣውም
1086. አስተያየቶችን የምናገኝበት ሁኔታ ነበር። ያም ሆኖ አሁን በዚህ በ003 ፋካሊቲ ያደረግነው
1087. ባለፈው እንዳደረግነው ነው። ሰዎችን ጋብዘናል፣ ያመለከቱ አሉ፣ ማናጅመንቱ ቅድም
1088. እንዳልኩት በመመካከር ደግሞ ለዚህ ቦታ የሚመጥኑ የሁለቱ ውህድ፣ ባይ ዘወይ እነዚህ በግል

ነው እነዚህ በኛ ነው አንልም። ለምን ሰው በነፃነት እነዚህን ሰዎች መምረጥ መቻል
ስላለበት። በሂደት የተማርነው ነው። ቢፒአር ላይ ታስታውሱ ከሆነ በግላቸው ያመለከቱትን
ህዝቡ ይተቻቸው ምክንያቱም እኛ ((xxx))ስለማናስጠራቸው ራሳቸው የመጡ ስለሆነ ህዝቡ
ይተቻቸው በሚል ለይተን አውጥተን ነበር በመጀመሪያው ዙር። በኋላ ግን ያገኘነው ሌሰን
ምንድን ነው ኦኬ ይኸ ማለት ማናጅመንቱ የደገፋቸው ናቸው፤ ብሎ የሚያውቅበት ዘዴ
ተፈጠረ ማለት ነው ብለን ከዚያ በኋላ ውህዱን የምናቀርበው ይሄ የኛ ነው እከሌ የራሱ ነው
ብለን የምናቀርብበት አግባብ ነው። ይሄ ከመመሪያው ጋር የተያያዘ ነው። በነገራችን ላይ አሁን
አዲስ የከፍተኛና የነባሩ 2005 በፈረንጆች አቆጣጠር የነበረውን ሌጅስሌሽን ስንመለከት
የትምህርት አዋጁ ላይ ምንድን ነው የሚለው የሃላፊነት ቦታዎች እንዴት እንደሚሾሙ
ሃላፊዎች መመሪያው በዩኒቨርሲቲው እንደሚዘጋጅ ነው። እንጂ በሊጅስሌሽኑ ብቻ ይመለሳል
ማለት አይደለም። ስለዚህ አዋጁም እንደዚህ ስለሚል፣ ሌጅስሌሽኑም ስለሚቀየር ምናልባት
አሁን የምንከተለው ሂደት የመጨረሻው ሊሆን ይችላል ለዚህ ፋካሊቲ። እና በሂደት ከዚህ
በፊት የነበረውን አሁን የምንሰራበትንም ድክመቱንና ጠንካራ ጎንን ለይተን የተሻለ መመሪያ
አፀድቀን እንቀጥላለን የሚል ሃሳብ ነው ያለው። ይህን ስናደርግ አንድ መልካም ..ዩኒቨርሲቲው
ውድድር ተጀምሯል። ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ታስታውሱ እንደሆነ ባለፈው አመት ሶስተኛ ነው
የወጣነው። ዘንድሮ ዝቅ ብለን አራተኛ ነው የወጣነው። ይኸ የማወዳደር ሂደት የራሱ ከፍተት
ያለበት እንደሆነ ሁላችንም እናውቃለን፤ማመን አለብን። እዚህ ላይ አንዱ ኦብዘርብ
ያደረግነውና ከዚህ በተለይ ከትምህርት ፋካሊቲ የበለጡን ዩኒቨርሲቲዎች በምን በለጡን ብለን
ብናስብ በፕሮጀክት ነው። ፕሮጀክት ላይ ሲመጣ ደግሞ በአብዛኛው ኮምፕቴሽኑ አድቫንቴጅ
ባለበት ሁኔታ ነው። ለምሳሌ መቀሌን ብንወስድ((xxx)) ጅማንና ጎንደርን ብንወስድ ወደ
ህክምናው ላይ ነው። በዚህ እውነታ ላይ ተመርኩዘን ስንመጣ ወደባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ከ003
ፋካሊቲ ብዙ በጣም እንጠብቃለን። ያንን አላገኘነውም፤ በግልጽነው የምነግራችሁ። ሰለዚህ
አንዱ ቻሌንጅ፣ ለሮዛ ቻሌንግ ሳደርጋት የቆየሁት፣ እዚህ እምቅ አቅም አለ፤ ይህን እምቅ
አቅም ተጠቅመን ተወዳዳሪ መሆን እንችላለን። ዩኒቨርሲቲው((xxx))የትኩረት አቅጣቻዎች ሲ-
ሲያስቀምጥ 003 ኮምፒቲቱቭ አድቫንቴጅ አለው። ሴንተር ኦፍ ኤክሰለንሲ የመሆን
ፖቴንሽያሉም አለ። ከዚህ በፊትም ነን ብለን ስለምናስብ፣ ያንን ማስቀጠል አለብን በሚል ነው
የትኩረት አቅጣጫ ያስቀመጥን። እና እውነቱን ለመናገር ኦብጀክቲቭሊ፣ ኦብጀክቲቢሊ እከሌ
እከሌ ሰው ሰውኛውን ትተን ለኮሌጁና ለኮሌጁ አንድ ((xxx))እንኳንስ በኮሌጅና በፋካሊቲ ደረጃ
በዩኒቨርሲቲም ደረጃም እንዴት መስራት እንዳለብን ይህንን ፋካሊቲ ወደፊት ሊራምድ የሚችል
ኤክስፔቲሽኑን ሚት ማድረግ የሚችል፣ ካለን፣ እንጂ ከየትም አይመጣም በነገራችን ላይ አንድ
የማልስማማበት አባባል አለ። መቀሌ ዩኒቨርሲቲ መጀመሪያ የነበርነው ስታፍ አስራዎቹ ውስጥ
ነው የነበርነው በቃ ስራ ተከፋፍለን ጀመርን ዛት ኢዝ ኢት። ዛሬ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ተወዳዳሪ
ከሚባሉት ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ነው። ማነው ያደረሰው ብትሉ በቃ እንደኔ አይነቱ። ኧ-ሰው
የለም የሚባለው ነገር በፍጹም አይመስለኝም፣ አይመቸኝም። ሰው አለን። ስለዚህ ካሉት
ከቀረቡት እጩዎች ውስጥ የተሻለ ይህንን ፋካሊቲ፣ አንድ አባባል አለ እኔ በጣም የሚመቸኝ
‹‹ታላቅ ነበርን ታላቅ እንሆናለን›› የሚል አባባል አለ። እና ይሄ ፋካሊቲ ቦታውን ክሌም
እንዲያደርግ፣ የሚገባውን ቦታ እንዲይዝ እዚያ ሊያደርስ የሚችል ሰው በትክክል ከቀረቡት
ውስን አማራጮች ውስጥ እንድትመርጡ ነው፤ ምናልባት እ ጥያቄ ካለ እ-እ-እሽ እሽ።
በእውቀቱ፡- ተሰቶኛል እድሉ?
ዶ/ር. ሀይሉ፡- አዎ
በእውቀቱ፡- አመሰግናለሁ! አሁን ካመለከቱትም ዩኒቨርሲቲው ከጠቆማቸው ብናነፃፅር
በዩኒቨርሲቲው የቀረቡት አብዛኛዎቹ እንደሆኑ አስባለሁ። ምናልባ ኮተሳሳትኩ ታርሙኛላችሁ።
ዲን የሚሆን ሰው ከጠፋ እዚህ በፊት እንደማውቀው ዲን ሲመረጥ ቢያንስ ((xxx)) ዋናው
እኔን የሚያሳስበኝ ዲን ሲባል ለምንድን ነው የማያመለክተው፣ ለምንድን ነው የሚያንሰው፤
ይህንን ለምን ተቋሙ አይፈታውም። ስለዚህ ሁልጊዜ ስናይ ሁሉም ሰው ይቆጫል! አንተ
ቅድም ያልከው አለ፣ 003 ፋካሊቲ በአንድ መልኩ ብዙ ይጠበቅበታል። እያልን
እንናገራለን። ግን ዲን ሁን ሲባል ወይም ለዲንነት እጩ ሲሆን ሁልጊዜ ደስተኛ አይሆንም።

ስለዚህ በፋካሊቲያችን ውስጥ ከማንም ባልተናነሰ መልኩ ሊሰሩ የሚችሉ፣ ሊመሩ የሚችሉ
ብዙ ሰዎች አሉ። እና ፋካሊቲው እ ዩኒቨርሲቲው ወይም የሚመለከተው አካላት ለምንድን ነው
እነዚህ ሰዎችን ማሳተፍ ያልቻለበት ምክንያት? ይኸ ነገር እ መመለስ ቢቻል ወይም
‹‹ኮንዲዩሲቭ ኢንቫሮመንት›› ቢኖር፤ ምናልባትም እነዚህ ሊሰሩ የሚችሉ ሰዎች... ዛት ኢዝ
ኦል። እ... እነዚህ... መሆን እንዳለበት ይሰማኛል። ምንድነው ብዙ ጊዜ ሰዎች መስራት
እየፈለጉ ግን እዛ ውስጥ እጃቸውን ማስገባት አይፈልጉም እና ምናልባት የተወዳዳሪዎቹ ማነር
ሁለት ብቻ ያውም አሁን የቀረቡት ስታንዳርዱን የማያሟሉ ማመልከታቸው ምናልባት
በፋካሊቲው ((xxx)) ውስጥ የማስበው። እና ይኸ እንደው ትንሽ ማብራሪያ ቢሰጥ ብየ ነው።
ዶ/ር ሀይሉ፦ ተጨማሪ መልስ መሆን ያለበት አይመስለኝም። ምናልባት አንደኛ እ
አሲስታንስ ፕሮፌሰር የሚለው እ እስካሁን ድረስ አልሆነም ባለብን እጥረት ምክንያት። ላይ
እ በዛ ደረጃ ((xxx)) ሊሆን ይችላል። በዚህ እሳቤ ከሄድን ብጣም እ መስራት የሚችሉ ቤቱ
የሚያምንባቸው ባይ ዘ ወይ በወረቀት ማመን በእኛ አገር ያለ በሽታ ነው። ሌላው በሜሪት ነው
የሚያምን በብቃት። ኮርስ ቼር ለማስቀመጥ ቲችንግ ለርኒግ ዲዛይን ላይ በሜሪት አይደለም
የሚያስቀምጠው። አውትሻይን የሚያደርግ ሰው ከመጣ ለምሳሌ ጀርመን ሲስተም ፕሮፌሰር
ከሆነ...ነው። እኛ ግን ያን ሁሉ አውት ስማርት እናደርጋለን ብለን፣ አውትሻይን ካደረገው
አንዱ ጆኔር እንትን ወይንም አሲስታንስ ሊተካው ይችላል እስከማለት የሄድንበት ሁኔታ ነው
ያለው እና የአለም ቤንች ማርክን ብናይ ይኸ አሲስታንስ ፕሮፌሰር የሚለው ነገር እውነቱን
ለመናገር ((xxx)) ያም ሆኖ፣ ያም ሆኖ ከዚያ የወጣነው በነገራችን ላይ አሲስታንስ ፕሮፌሰር
መሆኑን ጠልተነው ሳይሆን ሁኔታዎች አስገድደውን ነው። ወደ ሁለተኛው ጥያቄ ስመጣ አሁን
እዚህ ቁጭ አድርጌ አንደዚሁ እሽ ማን ነው ብልህ፣ እከሌ ነው ልትለን ትችላለህ። ያን ሰው
አናግረን፣ ፈትሸን፣ ተመካክረን፣ ኤን ሶ ኦን የመጣንበት ጉዳይ ነው። ፎርቹኔትሊ ኢዱኬሽን
ፋካሊቲ አካባቢ ባለን ኢንተራክሽን፣ አሁንም ባለን ግንኙነት ማን ምንድንው የሚያስበው፣
ምንድነው የሚሰራው፣ ፍላጎቱ ምንድን ነው ኤንድ ሶ ኦን እናቃለን ብየ አስባለሁ። እና አሁን
እንዲያው ኦፕንሊ ብጠይቅህ ለምሳሌ ማነው ፖቴንሽያሊ መስራት የሚችለው? ብየ ብጠይቅህ
እና ብትመልስልኝ ደስ ይለኛል። ፍላጎትህ ከሆነ ማለት ነው። እኛ ግን እነማንን የት
ብናስቀምጣቸው። በነገራችን ላይ 003 ፋካሊቲ ላይ ጫናው ብዙ ነው። ጫናው
ስላችሁ በፋካሊቲ አመራር ብቻ ሳይሆን በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ራሱ ከ003 መምጣት
ያለባቸው ሰዎች አሉ። ለምሳሌ... እነማናቸው እሽ እነዚህን ቦታዎች የሚሸፍኑት? አር
ዘይ ዊሊንግ፤ ኦኬ ዊሊንግ አይደሉም ካልክ ለምን? ባለፈው የመምህራን ስብሰባ ላይ
የነበራሁ ሰዎች ታስታውሳላችሁ። ((xxx)) ማን ለምን
እና ፍራንክሊ ስፐኪንግ እዚህ ውስጥ አሁን ያሉ ሰዎች በአንድም በሌላ ሃላፊነት ላይ
የነበሩ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ።ዋይ ኖት ዘን? ኮሚትመንት። በግልጽ ነው መነጋገር ያለብን
ባይ ዘ ወይ። ይኸ እንደዚህ ቲም እንግዲህ ራስን ማወደስ አይደለም ባህላችን አይደለም
እንጂ፤ እንደዚህ ቲም እየለመነ የሚያሰራ መቼም የምናገኝ አይመስለኝም... እና ይህንን
ስናበቃ በነገራችን ላይ አምስት ለማድረግም ሰዎችን ዝም ብለን አናስገባም። እኔ ባለፈው
ለምሳሌ ጌትነት ላነሳ እችላለሁ። ባለፈው አወዳድረንሃል፤ ምንድን ነው የተባባልነው?
አትንኩኝ ነው ያልከው፤ አይደል? አትንኩኝ መማር እፈልጋለሁ። ... እንደማናጅመንት
የምናስበውም ነገር አለ። ከተመረጠ እና በፍጹም አልሰራም ካለ አንደርስታንድ
እናደርገዋለን፤ ሪኮግናይዝ እናደርገዋለን።... ስለዚህ በእኛ እንትን ራሳቸው አመልክተው፣
እኛም አፕሮች አድርገናቸው፣ ፈቃደኛ የሆኑ አሁን አራት ሰዎችን አቅርበናል። አይ እዚህ
ለምሳሌ አንዱ ፐርሰናሊ እዚህ ውስጥ ካሉት መወዳደር የሚችል ምናልባትም የሚሻል
ፈቃደኛ የሚሆን አለ ካልከኝ ዊ ካን ዲሳይድ። እስከዚህ ድረስ ነው የምንሄደው ባይ ዘ
ወይ፤ እና ይኸ ቤት በእርግጠኝነት በግልጽ የሚመጥኑን ሰዎች አሉ፤ እናመጣለን የሚል
ከሆነ ኢትስ ኦኬ። ከዚህ በኋላ ቅድም ያልኳችሁ የከፍተኛ ትምህርት አዋጁ አዲስ
ሌጅስሌሽን ስናወጣ ኢቭን ....ፕሮፖዛል ጽፎ አንድ ሰው ይህንን ፋካሊቲ ከዚህ እዚህ ጋ
አደርሳለሁ ብሎ ቢገባ ወደሚልም እንሄዳለን። አንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች ላይ
ይጠቀሙበታል። እኛም ጋ አለ ትሬንዱ የማመልከት ትሬንዱ አለ። ስለዚህ ዝምብለው

ሰዎች መተው ስላመለከቱ ብቻ ይዘናቸው ከምንቀር፤ ፕሮፖዛል አዘጋጅተው ድፈንድ
አድርገው፣ አወዳድረን ማ-ማርክ ሁሉ ሰጥተን ማለት ነው፤ ገና ክራይቴራውን አስቀምጠን፣
አብጀክቲቭ ክራይቴሪያ አስቀምጠን ማርክ ተቀምጦለት፣ እዚያ ሰዎችን እናስቀምጥ
እስከማለት ድረስ ደርሰናል። ባይ ዘ ወይ ላስት ዊክ አክሱም ዩኒቨርሲቲ ነበርኩ። አንዱ
ኤክስፐሪያንስስ እንትን ያደረኩበት በዚህ በዲን ውስጥ ያለው። ዌል ባህላችን እዚህ ላይ
ማነቆ ይሆናል። ባህላችን ማነቆ ሊሆን ይችላል። ለዚህ ነው ኢንሰቲቭ የሚያስፈልገው።
በነገራችን ላይ አንዱ ችግርም ይሽ ነው። አሁን እዚህ ላይ በመሆኗ ሮዛ ምን ተጠቀመሽ
ብትላት ትነግርሃለች። አይ ሎስት ዚስ ኤንድ ዛት። እንጅ ይህን አግኝቻለሁ አትልህም።
ለምን አሁን ከዚህ ላይ ሆና ከምታገኘው በላይ ሌላም ቦታ መምህር ኦርድነሪ ቲቸር ሆና
ልታገኘው ትችላለች፤ አሁን ባለው ሁኔታ። ስለዚህ ኮሚትመንት ያስፈልጋል። እና
ወደዚያም እየሄድን ስለሆነ አይ ቲንክ ጊዜ የሚፈታው ይሆናል ብየ ነው የማስበው።
ምናልባት አጣምሬ መልሻቸው ከሆነ በዚህ መልኩ እንትን ብንል።
በእውቀቱ፡- ተች ያደረካቸው ይመስለኛል። ግን አንዳንዴ ጌትነት እምቢ ስላለ እ
በሰውየው ከታመነበት ምናልባት ነገሮችንም በስነስርዓት ከተመቻቹለት፣ በሃላፊነት ወይም
ዲን ሆነህ ሁለት አመት ከሰራህ ከማንኛውም በተሻለ መልኩ የትምህርት እድል እሰጥሃለሁ
ከተባለ የማይመጣበት ምክንያት ያለ አይመስለኝም። እና አንዳንዴ ሁሉም ሰው ስራ
ሲባል፣ ሃርድሽፕ የሚፈልግ የለም በአሁኑ ሰዓት። ግን አትሊስት
[ዶር ሀይሉ፡- ለምንድነው ሃርድሽፕ የማይፈልገው? ለምንድነው?
በእውቀቱ፡- ዌል እንግዲህ ለምንድነው አሁን ሃርድሽፑን የማይፈልገው ከዛ ጋር ተመጣጣኝ
የሆነ ነገር የሚያገኝ ከሆነ አትሊስት ኮምፕሮማይዝ ያደርግለታል ብየ ነው የማስበው። ሮዛ
እዚህ ተቀምጣ፤ ከዚህ በመቆየቷ የሆነ ነገር የምታገኝ ከሆነ በተለይ ከማንኛውም በተሻለ
ትምህርት የምታገኝ ከሆነ እርግጠኛ ነኝ ያንን ሃርድሽፕ ትወጠዋለች ወይም ትቀበለዋለች
ብየ ነው የማስበው።
ዶ/ር ሀይሉ፡- አሁን ይህችን አሳብክን
በእውቀቱ፡- እህ
ዶ/ር ሀይሉ፡- አሁን ይች ሃሳብህ ሌጅስሌሽኑን ኮሜንት አድርጉ ብለን ልከን ነበር። ይች
ሃሳብህ በሌጅስሌሽኑ ላይ ብትካተት ኢት ዌል ቢ ኮሜንትህን ልከህልኛል ወይ? በቃ! አንዱ
ምን መሰለህ ((×××)) በየመድረኩ የምንነጋገረው እድሎችን እንጠቀም። ለእኔ በቢፒ አር
ውስጥ የማይቀየር ነገር የለም እንደፈለጋችሁ አድርጉ ብሎ እድል የተሰጠበት መንገድ
ማለት ነው። ኢት ወገ አፕ ቱ ራይት፤ ባጠቃቀም መጠቀምና አለመጠቀም የእኛ ነው።
አሁን ሌጅስሌሽኑን 20005 የነበረውን እየቀየርን ነው። ሁለት አመት ነው የፈጀው። ቁጭ
ብየ ሻይ ቤት ካወራሁት ወይ ምናምን እያያዝኩ እመጣለሁ። ግን አሁን ይህች ሀሳብ
አልመጣችም፤ በ003 ፋካሊቲ በኩልም አልመጣችም። እና በቃ ረሳችንን እንሁንና፣
ቁጭ እንበልና እስቲ እንደው ለውጥ እናምጣ። እናቅደው ነው ያልኩት ጥያቄና መልስ
አይደለም። ለምን መሰለህ እ-እንደአስተማሪ ጥያቄ እዚህ ጋ አልቀበልም። አሁን የሄድክበት
መሆኑን ብቻ እንመልከት ኢት ዳዝንት ኤኒ ቫሊዩ ተጎትተን እዚሁ ነው...። መሆን ግን
አልነበረበትም፤ መሆንም የለበትም። እና ፍራንክሊ እስፒኪንግ ይሽ ቤት 01 ፋካሊቲ ታምር
መፍጠር ይችላል። ባለፈው መምህራን ውይይት ላይ እኮ ተገፉ ተገፈተሩ ስንላቸው ነበር
አይደል! እንዴ ማንን ነው የገፈተርን? እንዴት አድርገን አልን ከዛ በኋላ ወጣሁና። አንድ
በአንድ ሰዎችን እያነሳን፤ እና እባካችሁ አንዳንድ ጊዜ የሆነ አውት ስታክ እናድርግ እና
አሁንም ቅድም እንዳለኳችሁ እከሌ ((×××)) ግልጽነት ካለ ፣ ካልሆነ ግን ቅድም የመቀሌ
ዩኒቨርሲቲን ታሪክ ያመጣሁላችሁ ሰዎችን ኮች ማድረግ ከቻልን አውቃለሁ፣ ኮሚትመንት
ካለ ኢንተግሪቲው ካለ፣ እንደቤተሰብ በአንድ ላይ 003 ፋካሊቲ ዝናውን ማስቀጠልና
ከፍ ማድረግ እንችላለን ብለን ከተነሳን እንችላለን። በእነዚህ ሰዎች፤ ምናልባትም ዘ ሊስት
የሚባለውን ወስድን ነገን መለወጥ እንችላለን አይ ቲንክ አነዚህን ነገሮች እንዲያው በጥሞና
ማየት ያስፈልጋል። ሌላ ሀሳብ ከሌለ ፕሮሲጀሩን ታውቁታላችሁ በአብዛኛው፣ ግን
በአጠቃላይ በሂደታችን ላይ መልካም አጋጣሚ ስለሆነ ነው መነጋገር ያለብን። እዚህ

ውስጥ ካንዲዴት ዶ/ር አበበ አለ። ማለት መመሪያችን ባይ ዘ ወይ አይከለክለውም።
የሌሎችን መምረጥ ይችላል። ግን ከዚህ በፊትኮምፕሌን ያስነሳብን ነገር አለ። ማለት
መመሪያው ባይከለክለውም በአንደርስታንዲንግ እሱን እለጅብል የሆነ። በዚህ እንጨርስ?
እሽ ካላችሁ አይ አም ሃፒ።
በእውቀቱ፡- እኔ ባለፈው ሮዛ የነገረችኝ ምንድን ነው ኮሚሽን ከመቅረቡ በፊት
በየፕሮግራሙ አራት አራት ሰው ተመርጠው እነሱ ይሳተፋሉ፤ ከዛ በኋላ ኮሚሽን ይቀርባል
የሚል ሰምቼ ነበር። እና ለዛም ደግሞ ከፕሮግራሙ አራት ሰዎች ልኬ ነበር።
[ሮዛ፡- አይደለም! እኔ እንደዛ አይደለም ያልኩህ
[ጌትነት፡- እሱ የመምህራን ኢቫሉየሽን ነው (በመደረብ)
[ዶ/ር ሀይሉ፡- አንዴ ክራሊቲ ልፍጠርና በዚህ ምርጫ ወቅት አራት አካላት ናቸው
የሚወስዱት። እያንዳንዱ አካል ኦብጀክቲቭሊ ለእከሌ ለእከሌ ብለው ሳይሆን..
እንደክሪይቴሪያም ኳሊፋይ ያደረግንባቸው ነገሮች አሉ። እና በተቻለ መጠን ሲኒየር የሆኑ፣
ተቆርቋሪ የሆኑትን ባይ ዘ ወይ ዚስ ኢዝ ሳብጀክቲቭ። አሁን የምንላቸው ነገሮች ራሳቸው
አንዳንዶች በኢቫሉየሽን በቁጥር ካልሆነ በቀር ያውም የራሱ ሊምቴሽን አለው። ሰብጀክቲቪቲ
ዙሮ ዙሮ ይኖራል። ግን እ-እንትኑን ሁሉ እናያለን። የሰሞኑን የእንትንን አይታችሁ ከሆነ
አንዱን ሰጠን የት ላይ ነው ክፍተት ያለው እስከሚለው ድረስ ይወስዳችኋል።
ሮዛ፡- ያው ያ በደንም አልተግባባንም ማለት ነው። እኛ ኮምሽን ላይ ስለምንመርጥ
ኮሚሽን ከሚገቡ ሰዎች ውጭ የሆነ ነበር ያልኩት። እንደዛ አይደለ? ጌትነት
ዶ/ር ሀይሉ፡- አንዱ የአንዱን ውጤት ማየት የለበትም...
ሮዛ፡- እህ
ዶ/ር ሀይሉ፡- ሌላ የሚነሳ ከሌለ ይፈቀድልኝ
ሮዛ፡- እሽ
ዶ/ር ሀይሉ፡- መልካም እድል...
በእውቀቱ፡- እኔ እንደዚህ መምህራን ከመረጡ በኋላ በኮሚሽን የሚ-ታይ ነበር የመሰለኝ።
[ሮዛ፡- አይደለም እንደዛ አይደለም ኮምሽን ላይ ያለን ሰዎች እዛ ስለምንመርጥ
ጌትነት፡- አውቃችሁታል አይደለም አሞላሉን
ሮዛ፡- እ...ሽ...
ጌትነት፡- በቃ ብሪፍ ማድረግ እችላለሁ እኔ። ባለፈው ስለነበርኩ፣ አምስት ...ነው ያለው
እንደምታዩት መጀመሪያ ፔጅ ላይ እያንዳንዱ ደግሞ ካታጎሪስ አሉት። ለምሳሌ መስፈርት
አንድ ላይ አራት ነገሮች አሉ፣ መስፈርት ሁለት ላይ ሁለት ነገሮች አሉ። ልክ እንደዚህ
ይቀጥላል እስከመጨረሻው ሶ 1.1 መስመር አንድ ላይ ያለው አምስት ማርክ ይሰጠዋል።
ስለዚህ የመጀመሪያው ተወዳዳሪ ከአምስት ስንት ትሠጡታላችሁ። 1.1 ማለት ምንድን ናት?
የሚለውን ገልበጥ ስናደርግ እናገኘዋለን።
ሮዛ፡- መጨረሻው ገፅ ላይ አለ። 1.1 ምናምን የሚለው
ጌትነት፡- መስፈርት አንድ ማለት የአሰራር ለውጡን ለመቀበል፣ ያሀገራቱን ፖሊሲዎች
ምናምን የሚል ነገር አለ። እ.. ስትራቴጂዎቹን ለመተግበር የተለያዩ ተሳትፎዎች
አድርገዋል።የሚለውን የሚያሳየው። መስፈርት ደግሞ ሁለት ነገሮች መስፈርት ሶስት አንድ
ነገር አለ መስፈርት አራት ከዚህ አንፃር ነው ነጥብ የምንሰጣቸው ማለት ነው። ሶ ለሁሉም
ሰው ዘ ሴም አንድ አይነት ነገር ነው እንትን የተባለው። መጨረሻ ፔጅ አፔንድ
የተደረገችው እያንዳንዷ ተቆራርጣ ተበጣጥሳ ነው የመጣችው 1.1 ማለት ምን ማለት ነው
ለአሰራር ለውጡ ያለው ዝግጁነት ከአምስት ማርክ፣ 1.2 ከአምስት ማርክ፣ ምን ማለት ናት?
ፖሊሲና ስትራቴጂ ለመተግበር ያለው ቁርጠኝነት። እንደዚህ እያለ እስከ 5.2 ይደርሳልና
መጨረሻ ላይ ደምረን ከመቶው እናስቀምጣለን። ግልፅ ነው።
በእውቀቱ፡- ምንድን ነው ቁጥር ነው የምናስቀምጥ?
ጌትነት፡- ቁጥር
ሮዛ፡- ገብቷችኋል? እዚህ ጋ ከ1.1 እስከ 1.4 ያሉት አሉ። ስለዚህ እዚህኛው ፊት ለፊት
ያለው ደግሞ ከ1.1 እስከ 1.4 አለ። ስለዚህ መጨረሻ ፔጅ ላይ ባለው መስፈርት መሰረት

1277. የእያንዳንዱን ሰው ፕሮፋይል ያው እ.. እንዲሁም ስለምናውቃቸው የፋካሊቲያችን
1278. መምህራን ስለሆኑ በዛ መስፈርት እየለካን እዚህ ጋ ማርክ እንሰጣቸዋለን፡፡
1279. ጌትነት፡- ቴብሉስ? የምናስገባው ምንድን ነው?
1280. መቅደስ፡- እዚህ ውስጥ ነው የምንሞላው?
1281. ሮዛ፡- አዎ የምንሞላው ቴብሉ ላይ ነው መጀመሪያ ገፅ ላይ ያለው ቴብል ላይ...
1282. ሮዛ፡- እሽ ወደጉዳያችን እንመለስ፡፡ እ አኮ 18 እና 19 ቃለጉባዔዎች ማስተካከያ
1283. ተደርጎባቸው...
1284. [መቅደስ፡- ፀድቀዋል፡፡
1285. ሮዛ፡- ፀድቀዋል፡፡ ግን ለወደፊቱ ምን ምን ነው ማስተካከያ የሚለው ዘርዘር ተብሎ ቢፃፍ
1286. ጥሩ ነው፡፡
1287. ጌትነት፡- እሱ ይቀራል፡፡
1288. ሮዛ፡- ምን ምን ማስተካከያ ስፔሊንግ ነው! ቄል ምንድን ነው የሚለው ዘርዘር ተብሎ
1289. ቢገለፅ፤ባለፈውም ተነጋግረን ነበር፡፡ አዎ
1290. ጌትነት፡- ያለበለዚያማ ሌላም የማይፈለግ ነገር ተጨምሮ ፀድቋል ልንል ነው፡፡
1291. ሮዛ፡- አዎ እንደዛ ተነጋግረን ነበር
1292. [ጌትነት፡- ስፔስፋይድ አድርጎ ይኸ በዚህ የሚስተካከል ተብሎ ነው መፃፍ ያለበት፡፡
1293. ሮዛ፡- ወደመምህራን ጉዳይ ስንሄድ አቶ ምህረቱ ጎበናና አቶ ለሰገ ሽበሽ ሶስተኛ
1294. ዲግሪያቸውን ለ ትጠፋለች ሶስተኛ ዲግሪያቸውን ለመማር የሚያስችላቸው እድል በዩኤሳ
1295. አይ ነው የምትሆነው አይደል? ይች ዩኤሳ
1296. መቅደስ፡- አዎ ኢ አይ ትሆናለች
1297. ሮዛ፡- እ በኩል ስላገኙ ፋካሊቲው እንዲፈቅድላቸው ጠይቀዋል፡፡
1298. [ጋሻው፡- እዚህ ላይ የማን ፊርማ ነው እዚህ ላይ የሚሆነው? (ከአጀንዳው ውጭ ጣልቃ
1299. በመግባት)
1300. ሮዛ፡- ያንተ
1301. ጋሻው፡- ለምን ፊርማ አስፈለገ?
1302. ሮዛ፡- ፊርማው የተፈለገው ሌላ ሰው የሞላው ነው ብለው ኮምፕሌን ቢያደርጉ..
1303. ሮዛ፡- እሽ እ፡ ወደ ጉዳያችን እንመለስ፡፡ እ፡ በዚህም መሰረት በሳይኮሎጂ ኦፍ ኢዱኬሽን
1304. አቶ ለገሰ ሽበሽ...
1305. ሮዛ፡- እህ
1306. ጌትነት፡- አቶ ምህረቱ ጎበናና አቶ ለገሰ ሽበሽ የ3ኛ ዲግሪያቸው ለመማር የሚያስችላቸውን
1307. እድል አግኝተዋል፡፡ ይላል፡፡ በዚህ መሰረት አቶ ይስማው ሳይኮሎጂ ኦፍ
1308. ኢዱኬሽን...ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ፈቅዶላቸዋል፡፡ ከሚባል
1309. ጋሻው፡- ኦል ሬዲ ተዘርዝሯል እኮ
1310. ጌትነት፡- አዎ መጠቀስ አለበት እንጂ፡፡ አቶ ምህረቱ ጎበና በዚህ ዘርፍ፣ አቶ ለገሰ
1311. ሽበሽ በዚህ ዘርፍ ለመማር የሚያስችላቸውን ከዩኒሳ እድል አግኝተዋል፡፡ ኮሚሽኑም
1312. የተጠቀሱት የትምህርት ዘርፎች አግባብ ሆነው ስለተገኙ እንዲቀጥሉ፡፡ ማግኘታቸው
1313. መታየት መቻል አለበት፡፡ እንደገና ደግሞ እኛ የወሰን ነው የሚመስለው፡፡ ቢማሩ አግባብነት
1314. ያለው ስለሆነ፣ቢማሩ እየተማሩ ያሉት ትምህርት ቢባል
1315. ሮዛ፡- እሽ ወደቀጣዩ እንሂድ? ኦኬ ለ መምህርት ትርሲት አሰፋ ከ02 ፋካሊቲ ወደ 01
1316. ዝውውር ጠይቀዋል፡፡ ይህን መነሻ በማድረግ ፕሮግራሙ መምህርቷ የሰለጠኑበት ሙያ
1317. ለፕሮግራሙ የሚጠቅም ስለሆነ ዝውውሩን ተቀብሎታል፡፡ ኮሚሽኑም የፕሮግራሙን ሃሳብ
1318. በመቀበል ከነበጀታቸው የሚመጡ ከሆነ እንደሚቀበላቸው ወስኗል፡፡ ይሄ ጥሩ
1319. ይመስለኛል፡፡...
1320. ሮዛ፡- ወደ ሀመር ውሃ ስንሄድ መምህር አበባው ደሳለኝ ከ001 ፋካሊቲ ወደ 003
1321. የዝውውር ጥያቄ ለፕሮግራሙ አቅርበዋል፡፡ ፕሮግራሙም የጓመልካቹ የትምህርት ዘርፍ
1322. ከፕሮግራሙ ጋር በእጅጉ የራቀ ስለሆነና የበለጠ ውጤታማ የሚሆኑት ባሉበት ፋካሊቲ
1323. መሆኑን በመገንዘብ ጥቂያቸውን አልተቀበለም፡፡ ከዚያ ኮሚሽኑም የፕሮግራሙን ሀሳብ

1324. ተቀብሎ አፅድቆታል የሚል ነገር ቢጨመርበት፤
1325. መቅደስ፡- አዎ
1326. [ጌትነት፡- እንትንስ ፈርስት ዲግሪው ነበር ሜን እንትን አሁን ...የራቀ ያስባለን ታስታውሱ
1327. ከሆነ የፈርስት ዲግሪው ነው፡፡ እ.. ጋሻው ነበርክ የዛን ጊዜ ስብሰባው ላይ የናንተ...
1328. ጋሻው፡- አዎ ነበርኩ
1329. ጌትነት፡- ፈርስት ዲግሪው ነበር ያች ጀስትፍኬሽን መቀመጥ አለባት
1330. ጋሻው፡- አዎ አዎ ነበርክ ያ ስብሰባው ላይ
1331. ጌትነት፡- ፈርስት ዲግሪው ነው፡፡ ሰከንድ ዲግሪውማ አይደለም፡፡ ፈረስት ዲግሪው ነው
1332. ችግሩ፡፡
1333. _ በእውቀቱ፡- ፈርስት ዲግሪውማ፣ በፈርስት ዲግሪው መሰረት ተደርጎ ከተነገረማ፣
1334. በፈረስት ዲግሪውም እዛኛውም ፋካሊቲ ላይ ውጤታማ የሚያደርገው ነገር ምንም ነገር
1335. የለም፡፡
1336. [ሮዛ፡- 08 እኮ ነው አይደል 08 ፈርስት ዲግሪው
1337. በእውቀቱ፡- አይደለም 07 ነው
1338. ጌትነት፡- እኮ እዚህም እኮ እዚህም የተነሳበት አንዱ ምክንያት ያው ፈረስት ዲግሪው ነው
1339. [መቅደስ፡- ግን ባሉበት የሚለውን እንችላለን
1340. በእውቀቱ፡- ግን 08 የበለጠ ውጤታማ ሊሆን የሚችለው ምኑ ታይቶ ነው
1341. ጌትነት፡- ምን አገባን ስለሱ
1342. በእውቀቱ፡- አይደለም
1343. ጌትነት፡- እኛ ግን አንቀበልም የምንለው እሱን ነው መነሻችን
1344. መቅደስ፡- የእኛ ሪዝን ጠቅሰን ነው ሪጀክት የምናደርገው እንጂ
1345. በእውቀቱ፡- ምን መሰለህ? ይኸ ሰውየ ከእኛ ቢመጣ በዚ በጣም የራቀ ነው፡፡ እዛው ባለበት
1346. ግን በጣም ውጤታማ ይሆናል ይላል፡፡
1347. ጋሻው፡- ኮርሱን ሁሉ ጠቅሰናል ... የሚባል ኮርስ ይኸ መምህር እኛ ጋ
1348. ቢመጣ ያን ብቻ ኮርስ .. እና ሌላ ተጨማሪ ስራዎች ስለማይኖሩት ሪሶርስ ማባከን ነው
1349. የሚሆነው፡፡
1350. ሮዛ፡- በቃ ተነጋግራችሁ አስተካክሉት፣ ሀሳቡን ስጡትና፡ ምክንያቱም ተፅፎ የመጣው
1351. እንደዚህ አይልም፤ አሁን የተናገርነውን ነው የሚለው፡፡
1352. ጌትነት፡- አሃ! ከእነሱ የመጣው?
1353. ሮዛ፡- ዶ/ር አስራት ፅፎ ያመጣውን እኮ አንብቤዋለሁ እዚህ ጋ ትዝ የሚላችሁ ከሆነ፡፡
1354. ጌትነት፡- መንፈሱ ግን እንዲህ አልነበረም
1355. ጋሻው፡- አልነበረም
1356. ሮዛ፡- እንደዚህ ነው
1357. ጌትነት፡- ኮሚሽን ላይ መንፈሱ እንዲህ አይደለም የነበረው
1358. ሮዛ፡- ኖ ዶ/ር አበበ፡ አሁንም ሊያመጣው ይችላል፡፡ እንደዚህ ነው የነበረው፡፡ ግን ለምን
1359. አይመጣም አሁን ?ሄደ እንዴ?
1360. በእውቀቱ፡- መሄዱ ነዋ እንግዲህ
1361. ሮዛ፡- አይ እንዳትሄድ እኮ ብየዋለሁ
1362. መቅደስ፡- ቃለጉባዔ...
1363. ሮዛ፡- እህ እሽ! ማሳሰቢያውንም እናብበው አይደለ?...
1364. ሮዛ፡- ((ሳቅ)) በስብሰባ ያልተገኙ አባላት ይባል፡፡ አባላት.. እ.. አቶ ጋሻው አየለ፣ አቶ አቶ
1365. ቢሏችሁ ምን ነበረበት፡፡ አቶ ጋሻው አየለ የፒዲጂቲ አስተባባሪ በስራ ምክንያት፣ አቶ
1366. ጌትነት ከበደ የድህረ ምረቃ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት አስተበባሪ በስራ ምክንያት፤
1367. አቶ ተስፋ ባልታወቀ ምክንያት
1368. [ተስፋ፡- ፈቃድ ነኝ፣ ፈቃድ ነኝ፣ ሙች ፈቃድ
1369. ጌትነት፡- በፈቃድ ምክንያት ይጨመራ
1370. ሮዛ፡- ነው እርግጠኛ ነህ! ቢሮ መታ እኮ መቅደስ ነግራህ ነው የቀረህ

ተስፋ፡- የትኛው ነው?
ሮዛ፡- የረቡ መቅደስ ቢሮህ መታ ነግራህ ነው የቀረህ
ተስፋ፡- አዎ፡፡ ሀብቱ ቢሮ ስብሰባ አለ ብሎኝ ነው የሄድኩት፡፡
በእውቀቱ፡- አዎ ደውሎ ነበር
ሮዛ፡- አይደለም መቅደስ ሄዳ ነግራው ሌላ ቦታ ሄደ፡፡ ኤኒ ዌይስ ሌላ ልንለው እንችላለን
ምክንያቱ ችግር የለውም፡፡
መቅደስ፡- በፈቃድ እንበለው
ሮዛ፡- በፈቃድ ይባል?
መቅደስ፡- ይሁንለት በእብሪተኝነት
ሮዛ፡- አጀንዳዎቹ ክፍል የሚቀሩ መምህራንን በተመለከተ፣ ሁለተኛ ትምህርት ላይ ያሉ
መመህራንን የትምህርት ጊዜ ማራዘም በተመለከተ፤
[ጌትነት፡- የትምህርት ነው የሚለው ትምህርት ይባል
ሮዛ፡- እህ
ሮዛ፡- እህ ኦኬ በ2004 ዓ.ም ክትንሳዔ በዓል በኋላ ያለውን አንድ ሳምንት ክፍል ያልገቡና
እንደዚሁም ከዚህ በፊት ያለምክንያት..
[ጌትነት፡- ያለምንም ምክንያት ይባል
መቅደስ፡- ያለ-ም-ንም
ሮዛ፡- ያለምንም ምክንያት በተደጋጋሚ ክፍል የማይገቡ መምህራንን አስመልክቶ ምን
ማድረግ አለብን በማለት የአካዳሚክ ካውንስሉ አባላት በስፋት ከተወያዩ በኋላ አንደኛ ወ/ሪት
አፀደ በላይ ... ፕሮግራም ባልደረባ በተለያዩ
ጊዜ በተደጋጋሚ ክፍል ያለበቂ ምክንያት ባለመግባት ፣ በፕሮግራሙ የተለያዩ ሃላፊነቶች
ሲሰጡ በእንቢተኝነት ባለመወጣትና በአጠቃላይ ከፕሮግራሙ አባላት ጋር በትብብር
ለመስራት ፈቃደኛ እንዳልሆኑ፣ እንዲሁም ስራ ቦታ ላይ ለማይገኙበትና የሚሰጣቸውን
ሃላፊነት ላለመወጣታቸው ማብራሪያ እንዲያቀርቡ ቢጠየቁም ባለማቀርባቸው ካውንስሉ
ጠንከር ያለ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጣቸው ወስኗል፡፡
ጌትነት፡- ግን አንዳንድ ነገር ከቶፒኩ ጋር የማይሄድ ነው ወደመጨረሻ ብናደርገው ደስ
ይለኝ ነበር፡፡ የ-አፀደን በተመለከተ፡፡
ሮዛ፡- እህ
ጌትነት፡- ታይትሉ የሚለው መጀመሪያ ምንድነው ክላስ መዝጋትን በተመለከተ ነው
የሚለው፡፡
ሮዛ፡- አዎ
ጌትነት፡- ከተወያየ በኋላ ከዛ ግን የተሰጣቸውን ሃላፊነት አያሚሉም ምናምን ይላል፡፡ ስለዚህ
ልናደርግ የምንችለው 1.1 ስለአፀደ በላይ ክላስ አለመግባት ስንት ጊዜ እንዳልገባች፤ አቶ
ዘመነ እና 1.2 ብለን ሰንት ጊዜ እንዳልገባ፤ ከዚህ በተጨማሪ ግን ብለን ወ/ሪት አፀደ በላይ
እንዲህ እንዲህ አይነት ነገር ያደርጉ ስለነበር፣ እንዲህ እንዲህ ተደርጎ ተወስኗል ቢባል ጥሩ
የሚሆነው፡፡
ሮዛ፡- እህ
በእውቀቱ፡- ይሽ ነገር የተዘረዘረው ለምን መሰለህ ከዚህ በፊት የተወሰነ ማስጠንቀቂያ
ተሰጥቷቸዋል..
[መቅደስ፡- እህ ማቅለያና ማክበጃ
[ጌትነት፡- ገብቶሃል እኔ የምልህ፣ እላይ ርእስህ በተደጋጋሚ ክፍል የማይገቡ መምህራንን
አስመለክቶ ምን ማድረግ አለብን ብለን ተወያይተናል፡፡ በዚህ መሰረት አንደኛ ወ/ሪት አፀደ
ያለበቂ ምክንያት ምናምን እሽ ተቀባይነት አለው፡፡ ከዚያ በእምቢተኝነት ...በአጠቃላይ
ከፕሮግራሙ አባላት ጋር በትብብር ለመስራት ፈቃደኛ እንዳልሆኑ፤ አሁን ፈቃደኛ መሆን
አለመሆን ከክላስ መግባትና አለመግባት ጋር አይገናኝም፡፡ ...ከዚህም በተጨማሪ ግን ብለን
ልናወራ እንችላለን፡፡ ወ/ሪት አፀደ በላይ ክላስ ከመቅጣታቸውም በላይ ከመዝጋታቸውም
በላይ እንዲህ እንዲህ ነሮች ሲያደርጉ የነበሩ በመሆኑ ማለት መቻል አለብን፤ በእንድ ቶፒክ

መሆን የለበትም ነው እኔ።።...
ሮዛ፡- እህ
መቅደስ፡- እህ..
ጌትነት፡- አይሻልም በእውቀቱ?
በእውቀቱ፡- እሱማ እንዳልከው ነው፤የ-አቀማመጡ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር፤ ዋና አጀንዳው አፀደ ደግሞ ከዚህ በፊት የነበረባትን ሪከርድ ለመስጠት ነው ዋናው፤ ከዛ ጋር ተጨማሪ ደሞ ክላስ ስለዘጋች ሀሳቡ አነተ ያልከው ነው።። የስትራክቸር ጉዳይ ነው።።
ጌትነት፡- ኦኬ ስትራክቸር ነው የሚሆነው
በእውቀቱ፡- አንጂ ሃሳቡ ከአንተ ውጭ አይደለም።።
ሮዛ፡- ሁለተኛው አቶ ዘመነ ነጋ የ... ፕሮግራም ባልደረባ እንዲሁ ፈቃድ ሳይጠይቁ እንድ ሳምንት በስራ ገበታቸው ላይ ባለመገኘታቸው ምን እናድርግ የሚል ሀሳብ ተነስቶ በሰፊው ከተንሸራሸረ በኋላ፣ እ፡ መምህሩ ለፋካሊቲው አዲስ በመሆናቸው ህጉን በደንብ ላያውቁ ይችላሉ፤ ከዚህም በተጨማሪ ከዚህ በፊት የታየባቸው ጥፋት የለም።።ለተማሪዎቻቸውም የሚነበቡ ፅሁፍ፡ ፅሁፎችን ይባል?
በእውቀቱ፡- ማቴሪያሎችን..
ጌትነት፡- ማቴሪያሎችን ይላል.. ?
ሮዛ፡- ፅሁፎችን ነው የሚለው።። ማቴሪያሎች ይባል?
ጌትነት፡- የሚል አለ?
መቅደስ፡- አይ
ሮዛ፡- የሚነበቡ ፅሁፎችን ነው፤ ነው የሚነበቡ ማቴሪያሎችን ይባል?
ጌትነት፡- አላየሁትም የቱ ጋ ነው ስለማን ነው? ስለመስከረም? አሃ
ሮዛ፡- ፅሁፍ ይባል ማቴሪያል ይባል ነው ጥያቄው አሁን
መቅደስ፡- ፅሁፍ
ሮዛ፡- የሚነበቡ ፅሁፎችን
ዶ/ር አበበ፡- ፅሁፍም ያው ነው።።
ጌትነት፡- ነገሮችን ብንለው ምን ችግር አለ?ነገሮችን።።
መቅደስ፡- ሃንድ አውት ነው
ሮዛ፡- ስለዚህ ምን ይባል?
ጋሻው፡- የሚነበቡ የትምህርት መርጃ...
ጌትነት፡- የሚነበቡ ነገሮችን ብትይው አንደርስቱድ ነው
መቅደስ፡- ነገሮች!
ጌትነት፡- ያው ነው ፅሁፍም ያው ነው፤ ነገሮችም ያው ነው።። ዶር. አበበ ነው መሰል ፀሃፊው
ዶ/ር አበበ፡- ኧረ አይደለሁም
ጌትነት፡- ድፌንድ አደረክ ብዬ ነው።።
ሮዛ፡- በፕሮግራማቸው ተወካይ በተሰጠው ሃሳብ መሰረት የቃል ማስጠንቀቂያ እንዲሰጣቸው።።የቃል ማስጠንቀቂያ በፅሁፍ ነው እንዴ ያልነው እኛ? የቃል ማስጠንቀቂያ ነው አይደል?
መቅደስ፡- አዎ
[ጌትነት፡- የቃል ተብሎ በፅሁፍ ምን ማለት ነው? ክብሮም ነው የፃፈው?
ሮዛ፡- ካውንስሉ ተስማምቷል።።
በእውቀቱ፡- ከዚህ በተጨማሪ ከዚህ በፊት የታየበት ጥፋት የለም።። ለተማሪዎችም የተለያዩ ፅሁፎች ሰጥተው የሄዱ ተብሎ፤ እኔ ከዚህ በፊት ጥፋት የለበትም አላልኩም።።
መቅደስ፡- አይደለም እኛ ነው ያልነው፤ እኛ ነን ያልነው።።
በእውቀቱ፡- ፕሮግራሙ እኮ ይላል።። ከፕሮግራሙ ተወካይ ነው እኮ የሚለው።።
መቅደስ፡- ዊ እውነትህን ነው እሱ።። ግን ምናልባት ሼር አድርገህ ሊሆን ይችላል።። ያንን እንትን

በእውቀቱ፡- እኔ የተረዳሁት ማቴሪያል እንደሰጠ ነው፡፡
ጌትነት፡- ኣ፡ እንትን ማለት ይቻላል፡፡ እየው ከዚህም በተጨማሪ ከዚህ በፊት የታየባቸው
ጥፋት የ-የሌለ በመሆኑና ከፕሮግራም ተወካያቸው በተገኘ መረጃ መሰረት ለተማሪዎቻቸው
የሚነበቡ ፅሁፎች ሰተው ስለሄዱ ፤ ሰተው ነው የሄዱ፡፡
[ሮዛ፡- እሽ ትምህርት ላይ ያሉ መምህራንን የትምህርት ጊዜ ማራዘም፡፡ የፒኤችዲ
ትምህርቷን እየተከታተለች...
[መቅደስ፡- ትምህርታቸውን እየተከታተሉ፤
[ጌትነት፡- ለምንድን ነው ወንድ ወንዱን አፀደን ጨምሮ ትምህርታቸውን፤ ፅሬዳን ደግሞ
ትምህርቷን! መምህር ደግሞ ለምንድን ነው የሚባል፡፡ ጋምቤላ አካባቢ ሰርቶ የሚያውቅ
ሰው ነው መምህር ማለት የሚወድ፡፡ መምህር መምህርት.. አቶ እና ወ/ሮ ለምን አይባልም?
ፎርማል አይሆንም እኮ፡፡
ሮዛ፡- መምህርት ፅሬዳ በለጠ ለምርምር
[ጌትነት፡- አዎ እንደዛ ነው መሆን ያለበት፤ ፎርማል ነው መሆን ያለበት
መቅደስ፡- ወ/ሮ ፅሬዳ ለምርምር የጠየቁት...
ሮዛ፡- እንደዛ ይባል ወ/ሮ ይባል
ጋሻው፡- አዎ
ሮዛ፡- እሽ ወ/ሮ ፅሬዳ በለጠ ለምርምር የጠየቁት ከ6 ወር እስከ 8 ወር ጊዜ እንዲሰጣቸው፤
እንዲሁም ውላቸው እንደገና እንዲታደስ፡፡
ዶ/ር አበበ፡- እንድታ የሚለው ዲ ነው
ሮዛ፡- አዎ፡ በማለት ወስነን የነበረ መሆኑን
[መቅደስ፡- ተወስኖ፤ ቢባል አይሻልም?
በእውቀቱ፡- የነበረ መሆኑ
ጌትነት፡- ተወስኖ ነው መባል ያለበት አዎ..
መቅደስ፡- የነበረ መሆኑ ይታወሳል፡፡
ሮዛ፡- ነገር ግን ከሰው ሃይል አስተዳደር በተሰጠ እቅጣጫ አካሄዳችን ትክክል እንዳልነበረ
ተጠቁሞ፤ ምክንያቱም የፒኤችዲ ተማሪ ሁለት አመት ድረስ ማራዘም ስለሚችል፤ነው
ስለሚቻል
ጌትነት፡- ስለሚችል
ሮዛ፡- ስለሚችል እንደገና ውል ማደስ አያስፈልግም በማለት የትምህርቷ
በእውቀቱ
ጌትነት፡- የመምህርቷ
ሮዛ፡- የመምህርቷ የትምህርት ጊዜ ከህዳር ወር 2003 ዓ፣ም ጀምሮ ለሁለት አመት
እንዲራዘም የአካዳሚክ ካውንስሉ ተስማምቷል፡፡ ምክንያቱም ባለፈው አመት 2003 ህዳር
ላይ ነበር ጨርሳ መምጣት የነበረባት፤፡ በገባቸው ውል መሰረት ማለት ነው፤፡ ከዛ ጀምሮ
ያለው ዝምብሎ እንዲሁ የጠየቃትም የለም እሷም አራዝሙልኝ አላለችም አሁን ነው
እንድታራዝም ተጠይቃ እሷም...
በእውቀቱ፡- ለሁለተ አመት ነው
ሮዛ፡- አዎ እስከ ህዳር 2005 ማለት ነው፡፡
[ጌትነት፡- የመስፍንም እንደዛ ነው፡፡
ሮዛ፡- አዎ የፒኤችዲ ትምርታቸውን ይባል ይሽ?
ጌትነት፡- አዎ
ሮዛ፡- የፈረሙት ውል የ3 አመት ቢሆንም፤ ትምህርቱ ከ4-5 አመት እንደሚወስድና ጊዜው
እንዲራዘምላቸውና አካዳሚክ ካውንስሉን በጠየቁት
ዶ/ር አበበ፡- እንዲራዘምላቸውና ውል እንዲይዙ
ሮዛ፡- እንዲራዘምላቸውና ውላቸው እንዲታደስ መወሰናችን ይታወቃል፡፡ ነገር ግን ውላቸው
ይታደስ ማለታችን አግባብ እንዳልሆነ በሰው ሃይል የስራ ሂደት በተጠቆምነው መሰረት
ምክንያቱም በያዙት ውል እስከ ሁለት አመት ሊራዘምላቸው እንደሚችል ስለተደራን

1512. ከ30/03/04 ኣ.ም ጀምሮ ለሁለት አመት እንዲራዘምላቸው ካውንስሉ ወስኗል።
1513. መቅደስ፡- ኧረ በስማም ሌላ ስራ ነው
1514. ሮዛ፡- ይኸ እንደገና መባፍ ነው። .....
1515. ጌትነት፡- እንትን በይ የዛሬ አጀንዳ ንገሪንና
1516. ሮዛ፡- ተይሂል፤ አንተ ዘግይተህ ነው የመጣኸው።
1517. ጌትነት፡- ነው? የተማሪ ጉዳይ አለ?
1518. ሮዛ፡- አዎ። አቶ ተስፋ አኮ 23 ብለህ ቀን ምናምን ፅፈሃል አይደል?
1519. ተስፋ፡- አዎ።
1520. ሮዛ፡- ከዛ አቴንዳስ ያዝ የተገኙ አባላት፡ የተገኙትን እንፅፍልሃለን ከዛ የተባፈውን
1521. ትወስደዋለህ። አንደኛው አጀንዳ ቃለጉባዔ በሚለው ስር አኪ 21 እና 22 ማስተካከያ
1522. ተደርጎባቸው ፀድቋል ትላለህ። ከዚህ በኋላ ያው የቀረውን እናያለን—
1523. ሮዛ፡- ...ሁለተኛው አጀንዳ
1524. በእውቀቱ፡- የተማሪ ጉዳይ
1525. ሮዛ፡- አዎ የተማሪ ጉዳይ ነው ሁለተኛው አጀንዳ፡ የመጀመሪያው የ014ፕሮግራም 3ኛ
1526. አመት ተማሪ ባለፈው አመት የነበረ የደምሰው ሆርዶፋ ባለፈው አይተነዋል ጉዳዩን
1527. ታስታውሱት ከሆነ
1528. መቅደስ፡- 013 ነበር?
1529. ሮዛ፡- አዎ 013
1530. ተስፋ፡- ስንተኛ አመት?
1531. ጌትነት፡- ሶስተኛ አመት
1532. ሮዛ፡- ሶስተኛ አመት
1533. መቅደስ፡- የ2003 ተመራቂ ነበረ።
1534. ሮዛ፡- እ ያመጣው ማስረጃ ከቀበሌ ነው። ከቀበሌ አስተዳደር በሰዎች አስመስክሮ ታሞ
1535. ከየካቲት፡ ከየካቲት 2003 እስከ 2004
1536. ጌትነት፡- እስከ ስንት እስከ እንቁጣጣሽ?
1537. ሮዛ፡- ከየካቲት 2003 ጀምሮ በጠበል መቆየቱን አውቃለሁ እያሉ ሶስት ሰዎች መስክረውለት
1538. ያን የተመሰከረበትን ወረቀት ነው ይዞ የመጣው።
1539. ጌትነት፡- የተመሰከረለትን
1540. ሮዛ፡- የተመሰከረለትን።
1541. ጌትነት፡- በጣም የሚገርም ነው።
1542. መቅደስ፡- እ
1543. ጌትነት፡- ምን ታደርጊዋለሽ የቤተክርስቲያን ተቀባይነት የለውም። ማህበራዊ ፍርድቤት ነው
1544. ተቀባይነት ያለው።
1545. በእውቀቱ፡- ማህበራዊ ፍርድቤት እኮ ማንኛውም ሰው ማውጣት ይችላል። ከአንተ
1546. የሚጠበቀው ሶስት ሰው ማቅረብ ነው።
1547. ጌትነት፡- አዎ ሶስት ውሸታም
1548. መቅደስ፡- አዎ ሶስት ውሸታም
1549. ጌትነት፡- አይ ኤኒ ዌይ ብቻ ልጁ ከሃጢያቱ ተመልሷል
1550. መቅደስ፡- እ!
1551. ጌትነት፡- እንትን ብንልለት ((ሳቅ))
1552. በእውቀቱ፡- እኔ እውነት ለመናገር የእኔ ኮርስ ግሬድ ገብቶለታል። ሀለተኛ የድፌንስ ቀን
1553. መቷል ግን እከታተለው ስለነበር እንዲያቀርብ አልፈቀድኩለትም። ስለዚህ እዛ ከሆነ
1554. እስከመስከረም ድረስ
1555. ሮዛ፡- እኔም እንደዛ አይነት ጥያቄ አንስቸለት ነበረ፤ ይህንን ይዞ ሲመጣ ማለት ነው ለልጁ።
1556. እና ያለው ምንድን ነው ጨንቆን ከተኛሁበት ነስቼ ነው የመጣሁና የተፈተንኩ ነው ያለ።
1557. ጌትነት፡- ምን ታደርገዋለህ! አንተም ስህተት አለብህ።
1558. በእውቀቱ፡- አቃለሁ፣ እኔ አቴንዳንስ ስላልወሰድኩ ልጁን ልከለክለው አልቻልኩም።

ጌትነት፡- መንገደኛ የለ፣ ልብስ ሰፊ የለ፣ ደላላ የለ መፈተን የለብህም። ተማሪ ብቻ ነው
ሮዛ፡- ስለዚህ ምን እናድርግ?
ተስፋ፡- ችግር ግን ያለበት ይመስላል።
ጌትነት፡- እ
ተስፋ፡- ችግር ያለበት ይመስላል
ጌትነት፡- ይመስላል እሱማ ((ሳቅ))
ሮዛ፡- አዎ እ..
ጌትነት፡- ደሞ ደህና ተማሪ ነው። ባይ ዘወይ ደህና ተማሪ ነው አሉ ጠይቁ ነበረ። በቃ
ራሱን እየገደለ የመጣ ተማሪ እንጂ ፖቴንሽያል አለው።
[መቅደስ፡- አዎ ልክ ነው ፖቲንሽያል አለው።
ሮዛ፡- እህ
በእውቀቱ፡- በራሱ የሚተማመን ነው፤ ፕሮጀክት ሲሆን እኮ ይሰራል ግን ትንሽ..
ጌትነት፡- አይ ጎበዝ ልጅ ነው ለዚህም ይመስለኛል አንድ አመት እንትን ማለቱ
መቅደስ፡- አሁን ምንድን ነው የቀረው?
በእውቀቱ፡- ኮርሶች አሉት።
ሮዛ፡- የሰከንድ ሴሚስተር ኮርስ በሙሉ ነው አይደል ያልወሰደ?
በእውቀቱ፡- የእኔን ነው የወሰደው
ሮዛ፡- የአንተን ነው
ጌትነት፡- አስፈራርቶህ ይሆናል አንተን፤ እንጅ አሁን አኛ እንትን አላልንም፤ ክላስ አቴንድ
ስላላረክ አላስገባልህም ግሬድ ብየዋለሁ።
ጋሻው፡- ኢንኮምፕሊት ነው ያልከው ወይስ?
ጌትነት፡- ኢንኮምፕሊት አዎ።
ጋሻው፡- ያ እኔም አንድ ኮርስ
ሮዛ፡- ኢንኮምፕሊት ያልከው
ጋሻው፡- አዎ ኢንኮምፕሊት።
ሮዛ፡- እህ! ስለዚህ አሁን ዊዝድሮ አድርጓል፣ ሪአድሚሽኑን እንድንቀበል ነው የጠየቀው
ጌትነት፡- አዎ። የአቴንዳስ ጉዳይ ስለሆነ ክላስ እንዲማር ነው የሚሆነው።
መቅደስ፡- ግን ኮርሶቹ ሁሉም አሉ አሁን?
ጌትነት፡- የሀብቱን እንዴት ነው የምናደርገው አሁን፤ ግሬድ ገብቷል ነው የሚለው
ሮዛ፡- እህ፡ ከዚህ የተሻለ ሌላ ምን አማራጭ ምን ይኖራል?
ጌትነት፡- የለም ለማለት በሀብቱ ጊዜ አለ በሌላው ጌዜ የለም እያልን እየተናገርን ነው።
ሀብቱ ግሬድ አስገብቶለታል ሶ ዊ አስዩም ዛት ሂ ወዝ አቴንድ ክላስ፤ በእኛ ጊዜ ደግሞ ክላስ
የለሁምና፡ ልክ አይደለም
በእውቀቱ፡- ማስረጃው ከየት ነው
ጋሻው፡- የባህርዳር ከተማ የበላይ ዘለቀ ማህበራዊ ፍርድ ቤት
ሮዛ፡- አዎ
መቅደስ፡- አፍንጫችን ስር
ሮዛ፡- ለዛው ነው እኮ እየመጣ የተፈተነው...
ጌትነት፡- የእኔ ጥያቄ ገብቷችኋል
ሮዛ፡- እህ
ጌትነት፡- እንትን አለብን የሆነች ነገር ‹‹ሚክሲድ›› የሆነች አለች እና ያች እንዴት
ማስተካከል እንችላለች ነው። ስለዚህ ... ማድረግ የሚፈልግ ሰው ግሬድ ገብቶለታል
በተወሰነ መልኩ ያን ኢምፕላይ የሚደርገው ምንድን ነው እየተማረ ነው ብሎ ነው። እዚህ
ጋ ደግሞ አልተማርኩም በህመም ምክንያት እና ሪ አድሚት አድርጉኝ እያለ ነው።
ሮዛ፡- ጋሽ ጌትነትም አስወጥተኸው ነው አይደል?
ጌትነት፡- እኔ አስወጥቸው ነው። ኖ አይ አስገባሁት መሰለኝ መልሼ ግን ግሬዱን ግን
አላስገባሁም፤፡ ኢንኮምፕሊት ነህ ብየዋለው።

ሮዛ፡- ግን ተፈትኗል
ጌትነት፡- አስፈተንኩት አስገብቼ እንደገና አስወጥቸው እንደገና አስገብቸዋለሁ
ጋሻው፡- የተወሰነውን እየተከታተለ እዚሁ ባህር ዳር ስለሆነ ማለት ነው፡፡
ሮዛ፡- እዚሁ ስለሆነ
በእውቀቱ፡- ባህርዳ ከተማ ነው
ጌትነት፡- እና ገብቶሃል እኔ የምልህ እየቀረበ ያለው ሪዝን የአቴንዳንስ ሪዝን ነው፡፡ እኔ
አሁን በአንተ እንዴት ተብሎ እንደገባ አላውቅም፡፡ እኔ የአቴንዳንስ ይመስለኛል ኢንኮምሊት
በአቴንዳንስ ምክንያት፤....የለም ይመስለኛል፡፡ ኮንቲንሰንስ ይመስለኛል፤አቴንድ
አላረገምና ፀበል ላይ ነበር ማለት አንድ ነው፡፡ ግሬድ አስገብተህ በተወሰነ መልኩ በተወሰነ
መልኩ አቴንድ አላረክምና ግሬድ አልሰጥህም ካልክ በኋላ፣ እንዲህ አይነት ውሳኔ መወሰን
ይከብዳል እኔ፡፡ የበእውቀቱ የግሬድ ጉዳይ ብቸኛ ከሆነች ማለቴ ነው ፕሮባብሊ፤ እንዴት
አድርገን ነው ልንወስን የምንችል፤ መቀበል እንዳለብን ይታየኛል ልጁን፣ እንዲው በቂው
ነው፤አንድ አመት ያክል ላጠፋው ጥፋት፡ ግን እንዴት እንተርቴን እናድርገው ነው
የገባውንና ያልገባውን ግሬድ፡፡
ጋሻው፡- ተስፋስ?
ተስፋ፡- በእኔ ከሄድንማ አንድ ተማሪ ከ16ቱ ሳምንት 8ሳምንት ተምሯል፤ ፈተና ካለፈበት
ፋይናል ፈተናውን ሜክ አፕ ነው የምንሰጠው፡፡ አሁን እንደአዲስ መማር አይችልም
ምክንያቱም ሴሚስተሩን እንደተማረ ነው የምቆጥረው ይህን ተማሪ፡፡ ግሬድ አለው
ተብሏል፡፡
ሮዛ፡- እህ
ጌትነት፡- አዎ ያን ነው የሚያሳየው፡፡
ተስፋ፡- ግሬድ ካለው ተማሪው በፈተናው ነበር፡፡
ጌትነት፡- አቴንድ አድርጓል ማለት ነው ትርጉሙ፡፡
መቅደስ፡- አዎ ወይንም ደግሞ አንተ ወንጀለኛ ነህ ማለት ነው ፈተና ላይ ማስቀመጥህ ራሱ
ፋይናል ኤግዛም ላይ ክላስ አቴንድ ካላደረገ፡፡
ጌትነት፡- እኔ ተናግሬአለሁ እኮ፡፡
[ተስፋ፡- ዋት ኤቨር ኢት ኢዝ ፈተና ውስጥ ከተቀመጠ የሌሎቹ አንኳ ላግ ቢያደርግ
መቅደስ፡- እህ
ተስፋ፡- እስከዛ ድረስ ተማሪው ይከታተላል ማለት ነው፡፡
ጌትነት፡- አይደለም እኔ ዲድንት አቴንድ ክላስ ነው የሚለው የእኔ፤ በጣም እያለቀሰ ውጭ ሆኖ
እንትን አለኝ ማነው የሆነ ሰው ነው ሳጀስት ያደረገኝ እዚህ ከምትጣላ ውጣ ብለህ ልጁ
ከሚረበሽ ዝም ብለህ አስገባው የራሱን ውሳኔ ይወስን አለኝ፡፡
በእውቀቱ፡- ኤቨር ግን ግሬድ የማይገባለት ከሆነ አትፈነው ነው የሚለው
ጌትነት፡- አዎ እና ግሬድ አላስተላለፍኩም፡፡
መቅደስ፡- መፈተን እኮ መብቱ ነው፤ ከተፈነ በኋላ ውጤቱን አንትን ማለት መብቱ ነው፤
መጀመሪያ ማስፈተን ነው ...
ጌትነት፡- መብት የለውም መብት የለውም
ዶ/ር አበበ፡- ፈተና ከፈተንክ ውጤት ማስገባት የግድ ነው
ተስፋ፡- ኤፍም ቢሆን ምንም ቢሆን ፈተና ከፈተንክ ውጤት ማስገባት ነው
ጋሻው፡- አይደለም
ጌትነት፡- አላስገባም
ሮዛ፡- በየተራ አድርጉት
መቅደስ፡- አዎ
ጌትነት፡- ...አቴንዳንስ ቼክ ሳደርግ እንዳልነበር ለራሱ ነግሬዋለሁ፡፡ የእኔ ክላስ ጀስት
ለሱፐርቪዥን አይነት እንደገባ ለመሞከር እንደገባ ነው ትሪት የማደርገው ይሽን ልጅ፡፡
እንጂ አንደተማሪየ አላየሁትም፡፡ አስወጥቸው እኮ ውጭ እኮ ነው ኦረዲ እያለቀሰ ነበር ቁጭ
ብሎ፡፡

1653. ጋሻው፡- እንደዚህ ቢሆንስ ኧ፡ የተወሰኑ ኮርሶችን ሀብቴ ...
1654. ጌትነት፡- ይሻላል ኤክዛክትሊ ጥሩ ነው ልክ ነው
1655. ጋሻው፡- አቴንድ ያላረጋቸውንና በዚህ ምክንያት ኮርሶችን አቴንድ አድርጓል ማለት
1656. ይቻላል፤...
1657. ጌትነት፡- አሃ ሁሉንም ሳይሆን አቴንድ ያላረጋቸውንና ኢንኮምፕሊት የተባሉትን
1658. መቅደስ፡- ኢንኮምፕሊት የተባሉበትን ነው እንጂ፤
1659. ጋሻው፡- ኦኬ አቴንድ ያላረጋቸውንና ኢንኮምፕሊት የተባሉበትን
1660. መቅደስ፡- አዎ
1661. ጌትነት፡- እንደዛ ቢባል ይሻልል
1662. መቅደስ፡- አሁን ግን
1663. ተስፋ፡- የእኔ ሃሳብ አንድ ተማሪ ተከታትሏል ከተባለ ተከታትሏል ነው፡፡ ወይ ግሬዱ
1664. ተሟልቶ መምጣት አለበት ወይም ደግሞ የገባው ግሬድ ህጋዊ አይደለም መባል አለበት፤
1665. መሰረዝ አለበት፡፡
1666. ጌትነት፡- ለእሱ ኮርስ
1667. ተስፋ፡- አዎ
1668. ጌትነት፡- ኖ አሁን እኮ ምን መሰለህ፣ ሁለት አይነት ነገር ነው ያለው፡፡ አንድ ሰው
1669. አቴንዳንስ ዊ ቶክ አባውት አቴንዳንስ ኢንተርምስ ኦፍ ሳብጀክትስ ነው፡፡ ኢንተርምስ ኦፍ
1670. ባህርዳር አይደለም፡፡ ስለዚህ ለእሱ ኮርስ ተከታተለ፣ ሂ ዲዘርቭስ ግሬድ፣ ግሬድ ገባለት፤
1671. የእኔን ኮርስ ካተከታተለ ግን የበእውቀቱን ኮርስ ተከታትሏልና ግሬድ ይገበዋል ማለት
1672. አልችልም፡፡ ኢንኮምፕሊት ነው የማስገባለት፡፡ ከዚያ ግሬድ ሲገባም ህጋዊ የሚሆነው ሀብቱ
1673. ተከታትሎልኛል ይሄው ግሬድ፣ እኔ አልተከታተለልኝም ኢንኮምፕሊት ሲሆን ነው ህጋዊ
1674. የሚሆነው፡፡ ያለዚያ ግን በበእውቀቱ ክላስ መከታተሉ ሁሉንም ተከታትሏል የሚለው
1675. አንትን አያደርግም፡፡ እና ሴፍ የሚያደርገን አሁን ጋሻው ያነሳው ፕሮፖዛል ነው
1676. የሚሆነው፡፡
1677. ተስፋ፡- ስለዚህ ያለው ግሬድ በሙሉ ይሰረዝና
1678. [መቅደስ፡-አይደለም
1679. [ጌትነት፡- አይደለም
1680. [ሮዛ፡- ያለው አይሰረዝም
1681. [ጋሻው፡- አልገባህም እንዴ! አንድ ተጨማሪ ማብራሪያ አለኝ፤ሶስት ኮርሶች አሉ እኔ
1682. የምወስዳቸው አንተ ታስተምራለህ፣..... ታስተምራለች፣በእውቀቱ ያስተምራል፤
1683. የበእውቀቱን ክላስ አልወደውምና ቀረሁ፣ አንድም ቀን አቴንድ አላረኩም፤የሁለታችሁን
1684. አቴንድ አደረኩ፡፡ የሁለታችሁ ግሬድ አለኝ፡፡
1685. ጌትነት፡- የበእውቀቱ ግን መግባት የለበትም
1686. ጋሻው፡- የበእውቀቱ ግን መግባት የለበትም አቴንዳንስ ስለሌለኝ
1687. ጌትነት፡- ያ ማለት ሁላችንም ተከታተለ ማለት አይደለም
1688. ጋሻው፡- አይቻልም አሁን
1689. ተስፋ፡- አይቻልም፡፡ ወይ አይ ማስተላለፍ አለበት፤ አይ ይዞ መቆየት...
1690. ጌትነት፡- አይ ተላልፏል እኮ! አይ እኮ ነው የተላለፈው
1691. ጋሻው፡- .. የእኔ እኮ አይ ገብቶለታል፡፡
1692. ጌትነት፡- አይ ነው አይ ነው አይ ነው ያስገባለት፡፡ የጋሻው አይ ነው፡፡
1693. ጋሻው፡- እኔ አይ አስገብቻለሁ
1694. ጌትነት፡- ሪአድሜት ስናረግ በከፊል ኮርስ ማስወሰድ አይቻልም ነው በእውቀቱ ማነው
1695. ተስፋ?
1696. ተስፋ፡- አዎ
1697. ጌትነት፡- ሀጉ እንደዛ ነው በከፊል የሚባል ነገር የለም ሪአድሚሽን
1698. ተስፋ፡- አዎ እንዴት ብሎ
1699. ጌትነት፡- መቶ ፐርሰንት ነው በቃ

ተስፋ፡- በቃ አሁን አንተ አቴንድ አላደረገም ካልክ በአቴንዳንስ ብቻ ትችላለህ
ጌትነት፡- እ-እ-አልችልም፣እሱ እንኳን አልችልም
ተስፋ፡- ኣ ሜክአፕ ካወሰደ ማለት ነው፤ ሜክአፕ አልወሰደም?
ጌትነት፡- አልወሰደም
መቅደስ፡- አሁን ግን እኔ ያልገባኝ ነገር አሁን ይሄ ልጅ እንደገና ኮርሱን ይውሰድ ሲባል
የነበሩት ውጤቶች እንዳለ ተሰርዘው ግሬድ የገባላቸው ሳይሆን ያልገባላቸው ኢንኮምፕሊት
የተባለው ፋይናል የወሰደበት አለ አንዳንድ
[ጌትነት፡- አዎ እሱ እሱማ ኤፍ ነው
ጋሻው፡- ወደ ኤፍ ተቀይሯል እኮ
ጌትነት፡- እሱ ላይ ልክ ነው
መቅደስ፡- ስለዚህ ኮርሱን እንደገና ሲወስድ እ-እንደአዲስ ነው የሚያዘው ማለት ነው፡፡
ጌትነት፡- አዎ አዎ
ሮዛ፡- እህ
ተስፋ፡- ያልወሰዳው ኮርሶች ወደ ኤፍ ሲቀየሩ..
መቅደስ፡- አዎ በዛ መሰረት እኮ ታዲያ
ተስፋ፡-ይኸ ያስማማናል
ጋሻው፡- ሬጅስትራር ከሳምንት በኋላ ኤፍ ያደርግ የለ አንዴ
በእውቀቱ፡- አዎ አዎ
ተስፋ፡- ይኸ ያስማማናል
ጌትነት፡- እኮ እሱነው የሚሆነው፡፡ ሚክሲድ የሆነ ውሳኑ እንዲሆን ነው
ተስፋ፡- ስታተስ አለ ማለት ነው
በእውቀቱ፡- ስታተስ አለ ማለት ነው
ጌትነት፡- እ
ተስፋ፡- ስታተስ አለ፣ ስታተስ ይወሰንና፣ እንግዲህ ፌይል ካደረገ፣ ሳፕ ወስዶ ሌሎቹን
ኮርሶች ተመዝግቦ ይቀጥላል ማለት ነው፡፡
ጌትነት፡- ስለዚህ ሲ ነው ማለት ነው የሚጠበቅበት፡፡
በእውቀቱ፡- እህ
ሮዛ፡- ስታተስ ሲሰራ እኮ እነዚህ አይ የሆኑ ነገሮች አይካተቱም
ጌትነት፡- እ ቆይቶ ኤፍ ሆኗላ
ተስፋ፡- አዲሱ ህግ አዎ ነው
ሮዛ፡- እህ
ጌትነት፡- ቆይቶ እኮ ኤፍ ሆኗል
ጋሻው፡- ኤፍ ይሆናል
ተስፋ፡- አዎ
ጌትነት፡- አዎ አዎ
ጌትነት፡- ዜሮ ዜሮ ተደርጎ ዲስሚሳል ይባላል፡፡ ከዚያ በኋላ ሪአድሚሽን ነው፡፡ ኮምፕሊት
ዲስሚሳል ይሆናል
ተስፋ፡- ኮምፕሊት ዲስሚሳል ከሆነማ....
ሮዛ፡- እህ
ጌትነት፡- እውነቱን ነው፡፡ ዜሮ ዜሮ ስለሚሆን ፎር ጉድ ነው የሚሆነው
ሮዛ፡- አዎ ነው የሚሆነው
ጋሻው፡- አይ እኔ ግን የሚመስለኝ ምናልባት አፈወርቅ አንተ ሀጉን ስለምታውቅ ልታርመን
ትችላለህ፡፡ ይሄ ልጅ ህክምና ላይ ነበርኩ ክላስ አቴንድ አላደረኩም ብሎ ቀርቧል፡፡ እርግጠኛ
አይደለንም ሁሉንም ፈተናዎች ፋይናል ኤግዛም እርግጠኞች ነበርን፡፡ የሁሉንም ፈተናዎች
ፋይናል ኤግዛም እንደተፈተነ እርግጠኞች ነን?
ሮዛ፡- ሁሉንም እንኳን የተፈተነ አይመስለኝም፡፡
ተስፋ፡- እዚህ ላይ አንድ ነገር አንድ ላይ ምንድን ነው መሰላችሁ፤እኔ ላጥናው የገቡትንና

ያልገቡትን ግሬዶች፤
ጌትነት፡- ኦኬ
ተስፋ፡- እንዳልከው ኮፕሊት ዲስሚሳል የሚሆንበት ምክንያት ካለም እስከ ሳምንት ይዘን
እንቀርብ፡፡
ጌትነት፡- ማለት
ሮዛ፡- ጊዜው ሄደበት፡፡ ይማር ለማለት አሁን ይሄ ልጅ ሚድ ሁሉ እያለፈው ነው፡፡
በእውቀቱ፡- ክላስ አቴንድ እያደረገ እኮ ነው አድቫይዘር ተመድቦለታል
ጌትነት፡- አቴንድ እያደረገ ነው?
ሮዛ፡- አቴንድ እያደረገ ነው ? ኦኬ
ዶ/ር አበበ፡- እየተማረ ነው፡፡
ጋሻው፡- ግን አሁንም እኔ((×××)) አስተምረዋለሁ ግን ክፍል ገብቶ አያውቅም
መቅደስ፡- ይሽ በራሱ ላይ ፈርዷል ማለት ነው፡፡
በእውቀቱ፡- አሁን ትናንት ያለኝ እኔ እንዴት አድርጌ የምበላው ምናምን የለኝም ነው ያለው
ሮዛ፡- ያው መወሰን ስንችል ነዋ እኔ አሁን ምግብ ምናምን ተብሎ ኮንትራት የምፈርመው
[ጌትነት፡- ቆይ ለምን መደወል አንችልም እነዚህ ሰዎች ስታተስ አልተሰራም እነዴ
እስካሁን፡፡ ኦልረዲ እኮ አመት እየሆነ ነው፡፡ አፈወርቅ አመት እኮ እየሆነ ነው ኦረዲ ይሽ
ጉዳይ፡፡
ተስፋ፡- የመቼ ነው የአምና ነው
ጌትነት፡- የአምና ነው፡፡ ስለዚህ ምንድን ነው ስታተሱ ማለት አንችልም ወይ? ኮምፕሊት
ዲስሚሳል ነው ወይም ደግሞ አይ ችግር የለም የሚሉ ከሆነ ራይት ናው መጠየቅ
አንችልም ወይ
ተስፋ፡- ....አልኩህ
ጌትነት፡- አሁን መደወል አንችልም ወይ ነው እኮ
መቅደስ፡- እስከሳምንት ከሆነ ልጁ ይጎዳል ነው
ጌትነት፡- እንዳይዘገይበት ራይት ናው መጠየቅ አንችልም ወይ?
ተስፋ፡- ማንን
ጌትነት፡- አገሬን ወይም አንዷን እስኪ እይልኝ ስታተሱ ምንድን ነው? አመት እኮ ሆኖታል
ብየ ነው፡፡
ሮዛ፡- ተመርቆ ሄዷል ባቹ
ጌትነት፡- አዎ፡ ማለት ልጁን እንድናስተናግደው ብየ ነው
ሮዛ፡- እህ ብዙ ጊዜ ሆነው
ጌትነት፡- አሁን እንድናስተናግደው፡፡ ነው ማንዴት እንስጠው? ለአፈወርቅ፡፡ እና ለአንድ ሰው
ማንዴት ሰጥተን፣ ኦን ኮንዲሽን ወስነን በዛ ማንዴት መሰረት ቃለጉባያችንን እናስተካክል፡፡
በእውቀቱ፡- እንት ቢሆንስ ለምሳሌ..
[ጌትነት፡- አሁን ሁለት አማራጭ ነው፡፡ ኮምፕሊት ዲስሚሳል ቢሆን ምን ይሁን ብለን
እንወያይ፡፡ በሚመጣው አውት ካም መሰረት ኮምፕሊት ዲስሚሳል ቢሆን ምን እንወያይ፤
ካልሆነስ ምን ይሁን ይሽን ነገር መነጋገር የምንችል ይመስለኛል፡፡ ከዛ ለሁለት ሰው
አሳይመንት መስጠት፡፡
ዶ/ር አበበ፡- ልጁ ባክግራውንዱ ደህና ነው የሚል...
ጌትነት፡- ልጁማ ደህና ጥሩ ነው አልኩህ፤ ደህና ልጅ ነው፡፡
ዶ/ር አበበ፡- ደህና ከሆነ እኮ ኮምፕሊት ዲስሚሳል አይሆንም ማለት ነው፡፡
በእውቀቱ፡- ደህና ነው ማለት እኮ ክላስ ውስጥ ይሳተፋል ማለት ነው እንጅ ችግር
እንዳለበት የምናውቀው ነገር የለም፡፡
ጌትነት፡- አይ አይ ኖ ጥሩ ፐርፎርም ያደርግ ነበር ነው የሚባለው መጀመሪያ አካባቢ፡፡
ስለዚህ የሆነ ነገር እንበል፡፡ አሁን ወስነንለት እንሂድ፡፡ ሶ ሁለት ነገር ነው የሚኖረው
አንደኛ ዲስሚሳል እንጂ ፎር ጉድ ላይሆን ይችላል፡፡
ተስፋ፡- ለአንተ፡ እንትን እንበልና እኔ ላቅርበው፡፡

ጌትነት፡- ቸግር የለም
ሮዛ፡- ግን ምንድን ነው የሚሆነው የሚለውን እንወስነው፡፡
ጌትነት፡- አሁኑኑ መወሰን አለበት ይሽ ጉዳይ፤ የኮሚሽኑ ውሳኔ እንዲሆን
በእውቀቱ፡- ኮምፕሊት ዲስሚሳል ከሆነማ ምን አማራጭ አለው፡፡
ተስፋ፡- ምን ታደርገዋለህ
ጌትነት፡- ኖ ሪቨርስ ማድረግ ይገባን ይሆን ወይ፣ ይሄ ነገር የበሽታ ነው ሪሊ ካልኩሌትድ
መደረግ አልነበረበትም ወደማለት እኮ ልንሄድ ነው፡፡ ምክንያቱም እስከ መስከረም ነው እያለ
ያለ፤
ሮዛ፡- እህ
ጌትነት፡- በወቅቱ ማመልከት አለበት እንዳትለው፤ አይ እስከ 2004 ታሚል ይሽ ልጅ፡፡
ስለዚህ አይ ሹድ ኖት ሹዱድንት ሃቭ ቢን ቸንጅድ ቱ ኤፍ ወደሚለው እያስኬደን ነው፡፡
ምክንያቱም ሪዝን እያቀረበ ነው ይሽ ልጅ፡፡
ዶ/ር አበበ ፡- አሱማ የሀብቱን መፈተን አልነበረበትም፡፡ ፈተናዎቹን መፈተን
አልነበረበትም፡፡
በእውቀቱ፡- ከሆነ
[ጌትነት፡- እሱ እኔ ወደተማሪዎች ሳይድ ብናደርግ
በእውቀቱ፡- ለምን ግሬድ ያልገባለትን ኮርሶች እንዲማርና እንዲፈት
ጌትነት፡- እሱንም መወሰን እንችላለን፡፡ ህጋዊ ከሆነ፣ ገብቶሃል አፈወርቅ፣ ‹‹አይ›› ተብለው
የገቡ ግሬዶች ካልኩሌት ሳይደረጉ ምክንያም በህመም ነው ለማመልከትም ጊዜ የለውም፤
ማስረጃው እንደሚያሳየው ስንት ወር ብዙ ወር ታመመ ነው የሚለው፤፡ ያው ሆዳችን
ይወቀውም አይወቀውም ..ደንግጨ ገባሁ ነው የሚለው ያን ቀን፤ እና..
ተስፋ፡- እኔ የአንተ ነገር እየከበደኝ ነው፡፡የካቲት ላይ ማስረጃ አቀረበ እያልክ ግን ግንቦት ላይ
ፈተና ወስዷል እያልክ ብትመጣ፤
ጌትነት፡- እኮ ፈርቸ ገባሁ ነው መስሎኝ የሚለው
ሮዛ፡- ፀበል ውሎ እኮ መቶ ሊፈተን ይችላል፡፡
ተስፋ፡- ለምን ይፈተናል፡፡ ከተፈተነ አጠናቋል
ሮዛ፡- ስለዚህ ምን እናድርግ ያንተ ሃሳብ ምንድን ነው አቶ አፈወርቅ
ተስፋ፡- የእኔ ሃሳብማ እንደተባለው ወደ እ፡ አካዳሚክ ኮምፕሊት ዲስሚሳል ከዛ በኋላ
ምናልባት እንደዛም ላይሆን ስለሚችል
[ጌትነት፡- ከሆነስ አሁን መነጋገር አያስፈልገንም ወይ ሊሆንም ስለሚችል አሁን መወሰን
አለብን፡፡ እንዲህ ከሆነ አንደዚህ ይሁን፤ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በዚህኛው በኩል
በእውቀቱ፡- ከሆነ ደግሞ ለምሳሌ ኮምፕሊት ዲስሚሳል..
ተስፋ፡- ከሆነ ምንም ሊሆንለት አይችልም፤ ገና ኮምፕሊት ዲስሚሳል ይሆናል ብለን ደሞ
የምንሰራው ነገር አይኖርም፣አይኖርም፡፡
ጌትነት፡- ኖ አሁን አይኖርም፣ማንዴቱን ለመስጠት
ተስፋ፡- አሁን ውሳኔ አሁን ወዴት እየሄድን ነው?
ጌትነት፡- ማንዴቱን ለመስጠት ነው የምልህ፡፡
ተስፋ፡- ኮምፕሊት ዲስሚሳል የሚሆን ከሆነ እንዲህ እንዲህ እናድርግለት ልንል እኮ ነው፡፡
ጌትነት፡- ያ ሃሳቤ እኮ እሱ ነው፡፡
ተስፋ፡- ያማ አይሆንም፡፡
ሮዛ፡- እኔ ግ ከዚህ በፊት የወሰነውን እንት ያረግነው ይመስለኛል፡፡ ከዚህ በፊት ማስረጃ
ያምጣ ነው ያልነው፡፡ ማስረጃ አመጣ ልምን አንቀበለውም፡፡
ጌትነት፡- ለቀረበት ምክንያት
[በእውቀቱ፡- ማስረጃ ያምጣ ያን ማስረጃ እስኪያመጣ ድረስ ግን ክላስ አቴንድ
ያድርግ ተብሎ...
[ጌትነት፡- ያለበለዚያማ ያለማስጃ እኮ አይ ወደ ኤፍ ተቀይሮ መቶም ክሌም ሊያደርግ ነው፡፡
አፈወርቅ ገብቶሃል

ተስፋ፡- እ!
ጌትነት፡- ያለማስረጃ መቶም ክሌም ሊያደርግ ይችላል ይሄ ስው። ኮምፕሊት ዲስሚሳል
እስካልገባ ድረስ ማስረጃው ዋጋ የለውም ማለት ነው። ምክንያቱም ‹‹ኤፍ›› አድርገህበታል፣
በአካዳሚክ ዲስሚሳል ነው የተባረረክው በሌላ ፕሮብለም ነው የተባረርክው በሚቀጥለው
አመት መግባት ይችላል። ችግር የለውም ብየአስባለሁ።
ተስፋ፡- ማስረጃ ያቅርብ ያልነው መልሶ ቅበላ ለማቅረብ ነው እንጂ፤
[ጌትነት፡- አካዳሚክ ዲስሚሳል እኮ ሆነ
ተስፋ፡- ውጤቱን እንይለት ለማለት አይደለም
ጌትነት፡- ገብቶሃል ይሽውልህ! አካዳሚክ ዲስሚሳል እኮ ሊሆን ነው። ማስረጃውን
ተወውና አይኦቹ ወደኤፍ ይቀየሩ። አካዳሚካል ዲስሚስድ ሆነ፤ አካዳሚካል ዲስሚስድ
የሆነ ልጅ ያለምንም ማስረጃ አናስገባም ወይ? እኔ ፎር አካዳሚክ ሪዝን የተባረረ ሰው
ሳይታመም ያለማስረጃ አይገባም ወይ? ይገባል።
ተስፋ፡- ስታተስ ይወሰንና፣ አካዳሚካ ዲስሚሳል ይሁን፣ካላለፈ ሳፕ ኤግዛም ይፈተን..
ጌትነት፡- አሃ እኔ የምልህ ገብቶሃል፣የህክምና ማስረጃው ጥቅም የለውም ለአሁኑ
ውሳኔያችን፤የህክምና መስረጃው ምንም ጥቅም የለውም ነው ለእኔ፤ ገብቷችኋል እያልኩት
ያለሁት ጋሻው?
ጋሻው፡- ገብቶኛል አዎ
ተስፋ፡- ደሞ የካቲት ላይ የታመመ ሰው፣ ግንቦት ላይ ተፈኗል አንልም።
ጌትነት፡- አለ እኮ ፈርቼ ማለት ነው ለመግባት አለ።
ተስፋ፡- ይሄ በፍፁም አያስኬደንም፡ አይዘር ፈተናዎቹ በሙሉ ‹‹አይ›› ተደርገው ከሆነ
ይሄ ማስረጃ በየካቲት ስለሆነ ትምህርት ከተጀመረ ሁለት ወር ስላልሞላ...
ጌትነት፡- የካቲት መጨረሻ ነው። አሁን የካቲት 2004 ነው።
ሮዛ፡- እህ አዎ
መቅደስ፡- እስከ 2004 ድረስ ማለት ነው?
ተስፋ፡- ስለዚህ ሰኔ ላይ ግን ፈተናውን፣ ፋይናል ፈተና ወስዷል፤ አይምታታም እንዴ ይሄ?
ጋሻው፡- አይ ይሄ አይምታታም ስለዚህ እኔ ጋ ‹‹አይ›› ያስገባሁለት ምክንያት ስላላሟላ
ነው። በሙሉ ምዘናዎችን ስላልወሰደ ነው። ስለዚህ ይሄ ልጅ ፀበል በሚሆንበት ጊዜ ክላስ
አቴንድ አያደርግም፣ አሳይመንትም አይሰራም ምንም አያደርግም። ከፀበል ውጭ ሲሆን
መቶ ክላስ ይገባል። እንደዚህ አይነት ችግሮች ተፈጥረውበት ሊሆን ይችላል። እኔ አንድ
ምናልባት ለዚህ ጉዳይ የመጨረሻ ሀሳብ ልስጥ። እ ለምን አይሰራም ምናልባት በልጁ
ህይወት ላይ ከፍተኛ ውሳኔ ሊወሰን ስለሚችል ምናልባት አካዳሚክ ስታተስ ተሰርቶለት
ማው አካዳሚክ ኮምፕሊት ዲስሚሳል የሚሆን ከሆነ፣ እ፡ የሆነ ነገር ማድረግ የሚቻል
ይመስለኛል። ምናልባትም ከተስፋ በተጨማሪም ሌሎችን ባለሙያዎች ማማከር ይቻላል።
አሁን ተስፋ ራሱ ብቻ የሚያስበው ሊሆን ይችላል። ሌሎችም ባለሙያዎችንም ይጠይቃል።
[ጌትነት፡- ግን ኦፕሽናል ሆኖ ስቴብል ለምን አናደርጋቸውም፤ እና ለማንዴት ለሚያጣሩ
ለምን አንሰጥም።
ተስፋ፡- ስቴብል እኮ አደረግን
ጌትነት፡- አይ ለምን መሰለህ የአሁኑ ቃለጉባዔ ጋር አብሮ እንዲካተት ውሳኔያችን...
ጋሻው፡- አይ የዛሬ ቃለጉባዔ ላይ ባይያዝ።
ጌትነት፡- እ
ጋሻው፡- ምንም ነገር ባይያዝ የዛሬው ቃለ ጉባዔ
ጌትነት፡- ያለበለዚያ ኔክስት ዊክ መቅረብ ያለበት ማለት ነው
መቅደስ፡- ሙሉ አይደለማ የመጣውም እኮ...
ተስፋ፡- ተማሪው እየተማረ ከሆነ ለምን
ጋሻው፡- ማቅረብ
[ጌትነት፡- እንዲያው አዲስ ነገር አናገኝም ባይ ዘዌይ
ጋሻው፡- እናገኛለን፤ለምን አናገኝም።

1888. ጌትነት፡- በፍፁም አታገኝም፡፡
1889. በእውቀቱ፡- እ
1890. ጌትነት፡- አዲስ ነገር ሊገኝ አይችልም፡፡
1891. መቅደስ፡- ስታተሱን ቢያንስ እናውቃለን፡፡
1892. ጌትነት- አም ስታተሱ ከሆነ ማዬት መስጠት እንችላለን፤ የስታተስ ጉዳይ ከሆነ ማንዬት
1893. መስጠት አይቻልም ወይ? የስታተስ ጉዳይ ከሆነ፤
1894. ተስፋ፡- ስታተሱን እናውቃለን፡፡
1895. ጋሻው፡- እነማን እነማን ፋይናል ፈተና እንደፈተኑ እናቃለን፡፡ እነማን አይ ግሬድ እንደሰጡ
1896. አናቃለን፡፡
1897. ጌትነት፡-እኔ እኮ የሁለት ቀን ስራ ሊሆን ይችላል ብየ ነው፡፡ ቃለጉባዔው ሲካተት
1898. እንዲፈጥን ፈልጌ ነው፡፡
1899. ሮዛ፡- እህ ልጁ እየተንገላታ ነው፡፡
1900. ጌትነት፡- ያኔ የፈራሁት ነው፡፡
1901. መቅደስ፡- ይሄ ካልተወሰነ ደግሞ ልጁ አየህ
1902. በእውቀቱ፡- ምን አማራጭ አለ አሁን የምናየው?
1903. ጌትነት፡- ይሄ የህክምና ማስረጃው ይች አይ ወደ ኤፍ እንዳትቀየር ለማስደረግ ካልሆነ
1904. በስተቀር ምን ጥቅም አለው፤ ለምን አምጣ አለው ነው፤
1905. በእውቀቱ፡- ይሄ ባይኖረውም...
1906. ጌትነት፡- ባይኖረውም መብቱ ነው፡፡
1907. ተስፋ፡- ትምህርቱን ያቋረጠበትን ምክንያት አቅርብ ነው እንጂ፤ በምን ምክንያት አቋረጠ
1908. ጌትነት፡- አያስፈልግም እኮ ተስፋ፣ ያስፈልጋል ወይ ለሜክአፕ እኮ ነው የሚያስፈልገው
1909. ተስፋ፡-እ
1910. ጌትነት፡- ለሜክ አፕ እኮ ነው የሚያስፈልገው፤ አይ ወደ ኤፍ ተቀይሮ፣ አይ እኮ ወደኤፍ
1911. የሚቀየር ከሆነ ያለማስረጃ ዝም ብሎ መግባት ይችላል አንድያውን፡፡ አካዳሚክ ሲሆን፤
1912. ዶ/ር አበበ፡- ይችላል እኮ
1913. ጌትነት፡- በቃ እንደዛ ነው፣ አባረኸዋል..
1914. ተስፋ፡- አሁን በአንተ አካሄድክ እኮ ሁሉንም አይ የምናደርግ ከሆነ ይሄን ለምን አቀረበ ነው
1915. የምትለው
1916. ጌትነት፡- ግን ወስነንለታል ባለፈው እንዲያቀርብ ይመስለኛል
1917. ተስፋ፡- እንዲያቀርብማ ነው፤ ለሪአድሚሽ-ን እንዲያቀርብ ነው፡፡
1918. ሮዛ፡- እኮ ሪአድሚሽኑን ለምንድን ነው የማንቀበለው ነው? ሪአድሚሽን እንድንቀበለው
1919. ማስረጃ ያምጣ አልን አይደለ? ማስረጃ አመጣ አሁን የማንቀበልበት ምክንያት ምንድን ነው?
1920. ተስፋ፡- ሪአድሚሽን መጠየቅና ስታተስ መወሰን አንድ ነው እንዴ! ይሁ ማንኛውም ተማሪ
1921. ለቋረጠበት ምክንያት ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡
1922. መቅደስ፡- አቀረበ
1923. ተስፋ፡- አቀረበ፣ ላቋረጠበት ነው ልብ አድርጉ፣ ለስታተሱ ግን አይደለም፣ ለግሬድ ጉዳይ
1924. አይደለም፤ኧ ተግባብተናል?
1925. ዶ/ር አበበ፡- ግልጽ ነው_
1926. ተስፋ፡- ላቋረጠበት ምክንያት አቀረበ፣ ስታተሱ ሲሰራ ግን የቋረጠበት ሰኣትና ፈተና
1927. የወሰደበት ሰዓት አንድ አልሆን አለ፡፡
1928. ጌትነት፡- እህ
1929. ተስፋ፡- ስለዚህ ይሄ የተምታታ ነው፡፡
1930. ጌትነት፡- እኔ ግን ከልጁ ሳይድ የምናገኘው ነገር የለም፤ተጨማሪ ብየ ነው የማስበው፡፡
1931. ሮዛ፡- እህ
1932. [ተስፋ፡- ለማንኘውም እሱን እናናግረው
1933. ጋሻው ፡- አዲስ ነገር ሊኖር ስለሚችል እንየው፡፡
1934. ዶ/ር አበበ፡- እንደዛ ነው የሚሻለው፡፡

ተስፋ፡- ግዴለም ሳምንት እንየው ችግር የለም፤ አትቸኩሉ።።
ጌትነት፡- ልጁ ግን እስከሳምንት ነው የሚጎዳው።።
ጋሻው፡- የለም፣አሁን እያልነ ያለነው እኮ ከልጁ ሳይድም መረጃ ማግኘት አለብን ነው።።
ጌትነት፡- እኮ ሳምንት ድረስ ከምንሄድ፣ ‹‹ማንዴትድ›› የሆነ ግሩፕ ሰተን ይሄ ቃለጉባዔ
ጋር ለምን አይፃፍም ነው...
መቅደስ፡- አዎ
ጌትነት፡- አንዲህ ቢሆን እንዲህ ነው፤ ምክንያቱም ከሁለቱ ውጭ ሊሆን
አይችልም።። ወይ ፎርስድ ኮምፕሊት ነው ወይ ...ሳምንት ሙሉ ምግብ እየከፈለ ነው።።
ተስፋ፡- ምን የምትለውን ውሳኔ?
ጌትነት፡- ቅድም ራሱ ተናግሬአለሁ እኮ፤
ተስፋ፡- ምን?
ጌትነት፡- አንደኛ ያን የህክምና ማስረጃ ምንድን ነው የሚባለው ማስረጃ አምጣ ብለናል።።
አይዎቹ ወደኤፍ እንዳይቀየሩ ማለት ነው፤ ኮምፕሊት ዲስሚሳል የሚሆነን ከሆነ፤ ይሄ
ለሪዝን ይጠቅመናል፤ ኮምፕሊትም ሆነ ኮምፕሊትም ባይሆን አይዎቹ ወደእንትን
እንዳይቀየሩበት በህመም ነው ካልን ይጠቅመናል፤፡ ትልቅ ምርጫ አድርጌ የማስበው ልጁን
ሴቭ ያደርገዋል ብየ ከልጁ ሳይድ ለመቆም ይሄ ነው ብየ ነው የማስበው።።
ጋሻው፡- ይቻላል ግን?
ጌትነት፡- እ
ጋሻው፡- አንድ ተማሪ መረጃ በማምጣቱ ምክንያት አይኦቹ ወደኤፍ እንዳይቀየሩ ይሆናል።።
ጌትነት፡- ዌል ሬጅስትራር ጊዜ ጠብቆ እንትን ይላል።።
ጌትነት፡- ቄቭ ቄብ እየተደረገ ቆይቷላ።።
[ተስፋ፡- እንኳን ሶስት ኮርስ ወስዶ አንድ ኮርስ ቢወስድ ሁሉንም ኮርሶች እንደተማረ ነው
የምንቆጥረው።። ምክንያቱም ሁለት ኮርሶችን ሰኔ ሃያዎቹ አንበል አስራ አምስት ውሰጥ
ወስዷል አይደል፤ እስከዛ ድረስ ነው በሬጅስራር በኩል የምናየው።።
በእውቀቱ፡- እንደዛ ከሆነማ የጋሻውንና የጌትነትን ፈተና የመፈተን መብት ነበረው ማለት
ነው።። የአኔን ኮርስ ወስዷል።። ምን ማለት ነው ጌትነትና ጋሻው ሊከለክሉት አይገባም
ነበር ማለት ነው።።
ጋሻው፡- ነበር
ሮዛ፡- አሃ አቴንዳስና...
መቅደስ፡- ካልገባስ ክላሳቸው
በእውቀቱ፡- እ
[መቅደስ፡- ካልገባስ ክላሳቸው፣ 85 ፐርሰንቱን እኮ መከታተል አለበት።።
በእውቀቱ፡- የእኔን አቴንድ ማድረጉ ለሌላው ዋስትና አለው።።
መቅደስ፡- አዎ።።
ተስፋ፡- አቴንድ አላረገም ብሎ የሚል ከሆነ አይ ማስተላለፍ የግድ ነው...
ሮዛ፡- አዎ
መቅደስ፡- አዎ
ጌትነት፡- አዎ
ሮዛ፡- እንዴት ነው የሚሻለው..
ጌትነት፡- ማንዴት እንስጥ ይሄ ቃለጉባዔ ጋር ይያያዝ።።
ተስፋ፡- በሚቀጥለው ተጠናቅቆ ለምን አይቀርብም?
ጌትነት፡- ሳምንት ሙሉ ሊበላ እኮ ነው እየከፈለ፤ በጣም ነው እኮ ኑሮው እሱ እኮ ነው
ተስፋ፤
ጋሻው፡- ለተስፋና ለበእውቀቱ አሸናፊና ጌትነት ሆነው ይህንን ጉዳይ ያጣሩትና ከዛሬው
ቃለጉባዔ ጋር እንዲካተት ቢደረግ።።
ጌትነት፡- አብሮ ይጠቃለል።።ይጠቃለል፤ አይሻልም?
ጋሻው፡- ስለዚህ ነገ ይህንን ነገር ...

መቅደስ፡- ልጁ ካፊ ላይጠቀም እኮ ነው፡፡ ይሄ ውሳኔ ካታወቀለት አይጠቀምም
ጌትነት፡- እንዳይጎዳ ነው እኔም ..
ተስፋ፡- እህ እንዳይጎዳ ነው የምትለው አሁን፣ ምንድን ነው ቅድም ስትል የነበረው?
ጌትነት፡- እ
ተስፋ፡- ምንድን ነው ስትል የነበረ?
ጌትነት፡- አሃ አንድ አመት እኮ ነው፡፡
ተስፋ፡- ዛሬ ነው የሚያውቀው?
ጌትነት፡- እህ?
ተስፋ፡- ዛሬ ነው የሚያውቀው?
ጌትነት፡- ነግሬዋለሁ ያኔም እኔ እስኪበቃው፡፡
መቅደስ፡- ኦ እሱ አሁንም እኮ ካልተስተካከለ ይኸው እጣ ይደርስበታል በራሱ ጊዜ፡፡
[ሮዛ፡- እሽ ወደሌላ ተማሪ ጉዳይ፡፡ ማስረጃውን ያዙ አጠናቅራችሁና..
ጌትነት፡- ውይ ሌላ..ሌላ ጉዳይ አለ
ሮዛ፡- ሌላ ባለጉዳይ አለ አዎ
ጌትነት፡- እንደዚህ አይነት ተመሳሳይ ሪአድሚሽን
ሮዛ፡- ሪአድሚሽን አይደለም
ጌትነት፡- ሪአድሚሽን አይደለም መሰለኝ፣ ማነው
ሮዛ፡- ፈንታ ምህረቴ
ጌትነት፡- ፈንታ ምህረቴ አይደለም፤ ፈንታ ምህረቴ ሪአድሚሽን ሞልቷል? አልሞላም
ሮዛ፡- ሪአድሚሽን እንድሞላ ይፈቀድልኝ ስለመጠየቅ ይላል
[ጌትነት፡- ዌል እሱን እንናገራለን፤ እሱ የእንትን ጉዳይ ነው የህግ አለመግባባት እኔ
አንደርስታንድ ያደረኩትና ተስፋ አንደርስታንድ ያደረገው የተለያየ መሆኑን ነው የተረዳነውና
ከዚህ በኋላ እናቅርበው ብየ ነው የማስበው፡፡
ሮዛ፡- እሽ
ጌትነት፡- ልክ እንደሱ አይነት የሪአድሚሽን ጥያቄ የጠየቀ ልጅ ነው፤ ከሁለት በኩል
አጣርቻለሁ፡፡ አፈወርቅ ስሙን ያዝልኝ፡፡
ተስፋ፡- ምህረቴ ነው?
ሮዛ፡- ምህረቴ አይደለም፡፡
ጌትነት፡- አይደለም ሌላ ሌላ ሰው ልሰጥህ ነው፣
ተስፋ፡- እ
ጌትነት፡- ሌላ ሰው ልሰጥህ ነው፡፡ ሌላ፣
ተስፋ፡- እህ
ጌትነት፡- አዎ የ018 የማስተርስ ተማሪ፣ አበራ ባልዳ የክረምት ተማሪ ነው፡፡
በእውቀቱ፡- አበራ
ጌትነት፡- አበራ ባልዳ አበራ ባልዳ፣
ተስፋ፡- ስንተኛ አመት?
ጌትነት፡- እ፡ 2001 ክረምት ነው የገባው፡፡ሁለተኛ አመት ነው፣2001 ክረምት ገብቶ፣
ክረምቱንና የ2002ን በጋውን ሙሉ ተማረ ኮርሶችን፤ ከዚያ በኋላ ክረምት ላይ 2002
ቶፒክ የቴሲስ ምናምን መስራት ሲጀምር አደጋ ይደርስበታል፡፡ አድቫይዘሩም በአጋጣሚ
... ነው፡፡ ቼክ አደረኩኝ፤በጣም የሚያሳዝን ሁኔታ ነው ያለው ሪሊ፤ መምጣትና
ማመልከት የሚችልበት ሁኔታም አልነበረም ነው የሚለው፡፡ የአካል ጉዳት ደርሶበታል ነው
የሚለው፡፡ በክራንች ነው አሁን መሄድ የጀመረ ነው የሚለው፡፡ ይህክምና መስረጃም
አያይዟል፡፡ጥቁር አንበሳ ወረፋ እንዳስያዘ የሚገልፅ ማስረጃ ነው ለው ለማከም እሱን፡፡ እና
ቴሲሴን እንደገና እንድጀምር ይፈቀድልኝ ነው የሚለው፡፡
ሮዛ፡- ሌላ ነገር ጨርሷል? ኮርስ ምናምን
ጌትነት፡-አዎ
ሮዛ፡- ነው!

2029. ጌትነት፡- ቼክ አድርጌያለሁ፤ ... ጠይቄዋለሁ፤ ስጠይቀው ምንድነው ያለው
2030. ኢንስቱሩመንት ደረጃ ጥሩ ከምላቸው ተማሪዎቼ እንዲያውም እሱ ነበር ነው የሚለው፡፡
2031. ኢንስትሩመንት ደረጃ እንደደረሰ ነው አደጋ የደረሰበት የሚለው፡፡ እዛ ግሬዱን ቼክ አደረኩ
2032. ሬጅስትራር ገብቼ፤ 3.13 አለው በግሬድ በኩል ችግር የለበትም፤ ፕሮሞትድ ነው፡፡ ስለዚህ
2033. ፍቀዱልኝ ቴሲሴን ልስራ ነው የሚለው፡፡
2034. መቅደስ፡- ቴሲሱን እንደገና ነው የሚሰራው ወይስ ከዛው ነው የሚቀጥል?
2035. ጌትነት፡- ከዛው ነው የሚቀጥል ኖርማሊ፤ኢንስትሩመንት ደረጃ ደርሷል ዋሴን ሁሉን
2036. አታች ልናደርገው እንችላለን፡፡
2037. በእውቀቱ፡- ቴሲሱን እንዲሰራ ነው?
2038. ጌትነት፡- አዎ ቲሲሱን እንድቀጥልበት ነው የሚለው
2039. መቅደስ፡- ቴሲሱን እንዲጨርስ...አዎ
2040. በእውቀቱ፡- ከዚህ በፊት እንዲህ አይነት ነገር አልተነሳም?
2041. ጌትነት፡- ሌላ ያ ሌላ ነው፡፡ ሌላ በመኪና የተገጨ! ይሄኛው ናቹራሊ አደጋ የደረሰበት ነው፡፡
2042. ሮዛ፡- ያ... ካቀረበ በኋላ አስተካክሎ መምጣት ምናምን ነው፡፡
2043. በእውቀቱ፡- አድቫይዘሩ አሁን...
2044. ተስፋ፡- አመልክቷል?
2045. ጌትነት- አዎ እየው
2046. ሮዛ፡- ስለዚህ ምንድን ነው?
2047. ጌትነት፡- ፍቀዱልኝ ነው የሚለው፡፡
2048. ሮዛ፡- እህ ሲፈቀድልት ወጭ ምናምን እንዴት ነው የሚሆነው?
2049. ተስፋ፡- ይከፍላል ወጭ?
2050. በእውቀቱ፡- በተለይ የአድቫይዘር፣
2051. ጌትነት፡- አዎ እሱን ነው እኮ እንግዲህ ያመጣሁት
2052. ሮዛ፡- እህ
2053. ተስፋ፡- እንደገና
2054. ጌትነት፡- እሱን ሞስት ላይክሊ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ስሙ ከፕራይቬትም አላገኘሁትም
2055. ከመንግስትም አላገኘሁትም ተነቅሷል፡፡ ከአቋረጡ ሊስት ውስጥ ነው ያገኘሁት፡፡ እና
2056. መንግስትም ቢሆን ምን ይሆን ኤኒ ዌይ የሆነ አካል ይከፍልለታል፡፡ እኛ ግን የሆነ ነገር
2057. መወሰን አለብን፡፡
2058. በእውቀቱ፡- አሁን የሚከፍለው ለምንድን ነው? ለአድቫይዘር ነው
2059. ጌትነት፡- ለአድቫይዘር ለኤግዛምነር ለምናምን...
2060. ሮዛ፡- ስለዚህ ሙሉ ወጭውን ነው?
2061. ጌትነት፡- በአዲሱ እንትን 3000 ያስከፍለዋል፡፡ 6ክሬዲት አወር ሲባዛ በ600 ብር 3600
2062. ብር፡፡
2063. በእውቀቱ፡- የቴሲስ
2064. ጌትነት፡- አይ የፈተና የምናምን...ይከፍላል፡፡ በአዲሱ ህግ እንደዛ ነው አይደለ ተስፋ?
2065. ማንኛውም ነገር ....ነው፡፡ ቴሲስ የለ፣ ኮርስ የለ፡፡
2066. በእውቀቱ፡- እና ይሄን ነገር መወሰን እንችላለን እንዴ?
2067. ሮዛ፡- እንዲከፍልና እንዲጨርስ፡፡
2068. ዶር.አበበ፡- እንዲከፍልና እንዲጨርስ
2069. ተስፋ፡- ያው ከፍሎ ቴሲስ እንዲጨረስ
2070. ሮዛ፡- ተወስኗል ይባል?
2071. ጌትነት፡- ተወስኗል፡፡
2072. በእውቀቱ፡- አሁን የሚያስቸግረው ክፍያው ነው፡፡ ክፍያውን ይክፈል ብለን የምንወስን
2073. ከሆነ...
2074. ሮዛ፡- እህ
2075. ጌትነት፡- አሁን እሷን ማቅረብ ትችያለሽ፡፡

2076. ሮዛ፡- የትኛዋን?
2077. ጌትነት፡- ወይም ላስረዳሽና፣
2078. ሮዛ፡- የተማሪ ፈንታ፡ ማነው?
2079. ጌትነት፡-ፈንታ
2080. በእውቀቱ፡- ምህረቱ
2081. ጌትነት፡- አዎ፣ እንዴት ግን አመለከተ? ወይ እኔ እንት ልበል ይሆን? ማመልከቻው
2082. መታየት አለበት? ቆይ አንዴ ላብራራልህ
2083. በእውቀቱ፡- የማነው የፈንታ ምህረቱ ነው?
2084. ጌትነት፡- እህ
2085. ተስፋ፡- አንዴ እኔ ላብራራልህ፡ እየውልህ ፈንታ ምንድን ነው መሰለህ፣ ((×××)) ዲ
2086. አለው፣ቢም አለው፡፡ የመጀመሪያውን ሴሚስተር ወስዶ ማለት ነው፣ አሁን ሁለት ኮርሶች
2087. ተመዝግቦ ዲስታንስ ሲሄድ ይሄ ልጅ ታመምኩ ይላል፡፡
2088. ጌትነት፡- ኦኬ፣ ዊዝ ድሮ አረገ
2089. ተስፋ፡- የዲስታንስ አንትን አልወሰድክም ስለው፣ አልወሰድኩም አለ፡፡ የዲስታንስ ሳይወስድ
2090. ግን ስታተስ ተወስኖበታል፡፡ በዚህም ሪአድሚሽን ለመጠየቅ ቀኑ ስላለፈ ቢፈቀድለት፡፡
2091. ሪከርደሩ በመከልከሉ ሪአድሚሽን ስላላለፈበት ይፈቀድለት፡፡
2092. ጌትነት፡- በስድስት ክሬዲት አወር ያለአግባብ ስታተስ ተወስኖበት ነው፡፡ ስለዚህ
2093. ፈቅደንለታል፡፡
2094. በእውቀቱ፡- እሽ ሌላ፣ የመምህራን ጉዳይ ነው?
2095. ሮዛ፡- የተማሪ ጉዳይ አለ ሌላ፣
2096. በእውቀቱ፡- አለ ከአንቺ?
2097. ሮዛ፡- አለ እኔ ጋ፣ አንድ የተማሪ ጉዳይ እ፡ ያጭበረበሩ ተማሪዎች ናቸው፤ ፈተና
2098. [ጌትነት፡- ማስረጃ ካለ ዜሮ
2099. [መቅደስ፡- ውይ!ማስረጃ ካለ ዜሮ ቀጥታ
2100. ሮዛ፡- በ-ሞባይል፣ ሲላላኩ ነው የተያዙት
2101. ዶር. አበበ፡- እጅ ከፍንጅ
2102. ሮዛ፡- አዎ፡፡ ስለዚህ የፈተናችው አስተማሪ ፈርማ በሜሴጅ ሲላላኩ ነው የያዝኩ ብላ
2103. ሞባይሉን ሁሉ ለተስፋ አምጥታ አሳይታለች በወቅቱ
2104. መቅደስ፡- ግን በእግዚቢቲነት ቢገባ ጥሩ ነበር ያ ሞባይል፡፡
2105. ሮዛ፡- እህ፣ ስማቸውን ልንገርህ ዘቢባ ኑር በኑር፣ የአይሲ ቲ ተማሪዎች ናቸው፤ ፖሊ
2106. ናቸው፡፡
2107. ጌትነት፡- ኢንጅነርስ ናቸዋ?
2108. ሮዛ፡- እህ
2109. በእውቀቱ፡- ስንተኛ አመት?
2110. ሮዛ፡- አንደኛ አመት
2111. ጌትነት፡- ምንኮርስ ነው?
2112. ሮዛ፡- ጀነራል ሳይኮሎጂ፡፡
2113. ጌትነት፡- አዎ ኮርሱን ያዘው፡፡
2114. ሮዛ፡- ኮርሱ ጀኔራል ሳይኮሎጂ ነው፡፡ ተማሪዎቹ የአንደኛ አመት የኢንፎርሜሽን...ተማሪ
2115. ናቸው፡፡
2116. [ጌትነት፡- የኢንፎርሜሽን ሲስተም ነው፡፡ ልክ ነው ዜሮ...
2117. ሮዛ፡- የመምህር ጉዳይ ነው ሌላ፤ እ፡ መምህር ጉዳይ የዶር. ሺሩካ ጉዳይ ነው፡፡
2118. መቅደስ፡- ሻሩካ!
2119. ሮዛ፡- ዶር ሻሩካ ያው በህመም ምክንያት ወደሀገሩ ሊታከም ሄዶ በአጭር ጊዜ..
2120. ዶር. አበበ፡- ሻሩካ?
2121. ሮዛ፡- አህ
2122. ተስፋ፡- ሻሩካ ማን ነው?

ሮዛ፡- ሻሩካ ሳሌም ነው።
ተስፋ፡- የምን መምህር ነው?
ሮዛ፡- የኢዲፒኤም
መቅደስ፡- የኢዲፒኤም
ሮዛ፡- በህመም ምክንያት ወደውጭ ወደሀገሩ ሂዷል ለመታከም። በአጭር ጊዜ ታክሞ
እንደሚመጣ ነበር ነግሮን የሄደ። የሰከንድ ሴሚስተር ኮርሶችንም ቴሲስ አድቫይዝ
የሚያደርጋቸውንም ተመልሶ ሊያስተካክል እንደሚችል ነበረ፣ በደብዳቤም በቃልም ነግሮኝ
የሄደው፤ አሁን ከሶስት ወር በኋላ ምናምን እንደሚመጣ ነው።
ጌትነት፡- እህ
ሮዛ፡- እና ደመወዝ ይከፈለዋል? ወይስ ምንድን ነው የምናደርገው?
ጌትነት፡- አድምንስትሬቲቭ ይመስለኛል። ሪፖርት ማድረግ ነው።
[በእውቀቱ፡- አለ እንትን አላቸው።
ሮዛ፡- ምን?
በእውቀቱ፡- ውል የሚይዙት ውል አላቸው። ከዩኒቨርሲቲው ወይም ከትምህርት ሚኒስቴር
ኢዱኬሽን ጋር። ስለዚህ የትራንስፖርቱን የህክምናውን ምኑን በተመለከተ እዛ ስላለ፤
ሮዛ፡- እህ
በእውቀቱ፡- እዛው ነው የሚጨርሱት ውል አላቸው።
ሮዛ፡- እኛ ዝም ብለን ቁጭ እንበል?
ጌትነት፡- ኖ ኖ ኮምኒኬት ማድረግ ትችያለሽ።
በእውቀቱ፡- አንቺ ራስሽ ነሽ የምታደርጊው።
ሮዛ፡- ለማን?
ጌትነት፡- ለልጅቱ ለዛች ለዝናሽ፤ ዝናሽ አይደል የሚመለከታት?
ሮዛ፡- አዎ
ጌትነት፡- እሷ ኮምንኬት ታድርጋቸው። ሶስት ወር እንደማይኖር።
ሮዛ፡- ለነማን?
ጌትነት፡- ለእነ ማርቆስ ቢሰጥ
በእውቀቱ፡- ለዩኒቨርሲቲው
ተስፋ፡- ሚኒትድ መሆን የለበትም?
ሮዛ፡- ይቅር?
በእውቀቱ፡- አዎ
ጌትነት፡- አዎ
በእውቀቱ፡- በቃ ከእሷ ጋር አንቺ ጨርሽ
ሮዛ፡- እሽ ሌላው ኩንትራት ማረዘም ነው። ኮንትራት ማራዘም የ-የሺወርቅ እጅጉ ሀብት
አጠቃቀም። ጡረታ ወታለች እና ማመልከቻ አቅርባለች። በኮንትራት እንድቀጠር
ይፈቀድልኝ ዘንድ የቀረበ ጥያቄ ይላል። እኔ ወ/ሮ የዘርፍሽዋል ንጉሴ.....በትህተና
እጠይቃለሁኝ። እና ትናንትና ጋሻው እኔና ቢኒያምም ሆነን እንዲሁ አናግረናት ነበር።
የተገዙ እቃዎችን ተረክባ ኤል ሲዲ ምናምን ተረክባ ለመምህራን እንድትሰጥ። አይ ኮንትራ
የማይራዘም ከሆነ ያለብኝ ራሱ ለመመለስ ጊዜው አይበቃኝም ክሊር ለማድረግ
ጋሻው፡- እሷ እንደነገረችኝ ከሆነ ስራ ማቆም የነበረብኝ ከሶስት ወር በፊት እንደሆነና ይህም
ሮዛ፡- ለራሷ ሌላ ስራ የምታፈላልግበት ምናምን እንደሆነ ነው፤ እሷ የነገረችን ኢንፎርሜሽን
ነው እንግዲህ።
ጌትነት፡- አዎ ግን ህጉን ከሰው ሀይል ማግኘት ያስፈልጋል።
ሮዛ፡- እህ
በእውቀቱ፡- እኛ ነን ወይ ማራዘም የምንችለው?
ሮዛ፡- እንዲራዘምላት መጠየቅ አንችልም?
በእውቀቱ፡- ዌል አሁን የመምህራን ከሆነ ፕሮግርሙ ፋካሊቲውን ይጠይቃል። ይሄ ሰውየ
ኢክእፕሪያንስ አለው፤ጥሩ ይሰራልናል ከአለብን የሰው ሃይል እጥረት አንፃር እንዲራዘምልን

መጠየቅ እንችላለን፡፡ ፕሮሰስ የሚደርገው ግን የሰው ሀይል ከሲቪል ሰርቪስ ጋር ተነጋግሮ
ነው የሚጨርሰው፡፡ ዩኒቨርሲቲው በራሱ አይችልም፡፡
ተስፋ፡- የአስተዳደር ሰራተኛ ነው?
በእውቀቱ፡- የመምህራን ራሱ
ጌትነት፡- የመምህር ራሱ
ዶር. አበበ፡- መጠየቅ ያለባት ለሰው ሀይል ነው፡፡
ሮዛ፡- ስለዚህ ለፋካሊቲው አዲስ ሰው መጠይቅ ነው ያለብን ማለት ነው?
መቅደስ፡- መጠየቅ የማይቻል ከሆነ አይቻልም ይሉሻል፡፡ ከዛ ሌላ ሰው መጠየቅ
ይቻላል፡፡
በእውቀቱ፡- ዙሮ ዙሮ ለፋካሊቲው መጠየቅ ነው፡፡
ሮዛ፡- ኮሚሽን አይያዝም አይደል?
ጋሻው፡- አዎ አይያዝም፡፡
ሮዛ፡- አበዛሁ አይደል ዛሬ? አመሰግናለሁ፡፡
መቅደስ፡ ኧረ ይገባናል ዛሬ፡፡

ተሰብሳቢው ከወጣ በኋላ ጌትነት ወደኋላ በመቅረት ሮዛን በሚከተለው መልኩ አነጋገራት፡-
ጌትነት፡- እህ ኧረ! ሌላ ሮዛ ለነገሩ የ-ሌላ ሰው እየተካሽ ነው እንጂ፤
ሮዛ፡- እህ
ጌትነት፡- ጎንደር ያየሁት ኤክስፐሪያንስ
ሮዛ፡- እህ
ጌትነት፡- አምና ማድረግ ነበረብን፡፡ ፕሮባብሊ ለማ ነው ማድረግ የሚገባው፤ የመጀመሪያ
የየፊሊዱ ግራጁቶችን
ሮዛ፡- እህ
ጌትነት፡- ትልቅ ሆቴል ወስደው መስተንግዶ ምናምን ከሚባል ነገር ያወጡና ትልቅ ዝግጅት
ያደርጋሉ፡፡
ሮዛ፡- እህ
ጌትነት፡- ተማሪና መምህር ያገናኛሉ፡፡
ሮዛ፡- እህ
ጌትነት፡-የመጀመሪያ ባች ተመራቂ ለምሳሌ በ... አስመርቀናልና
ሮዛ፡- አዎ
ጌትነት፡-እንደዛ ማድረግ እንችል ነበረ፡፡
ሮዛ፡- ባለፈው አመት ነው?
ጌትነት፡- እ
ሮዛ፡- ባለፈው አመት ነው?
ጌትነት፡-ባለፈው አመት፤አሁን ለእኔ አላቅም እንግዲህ አዲስ ለጀመርናቸው ነገሮች ለምሳሌ
እንደፒኤችዲ አይነት ፕሮግራሞች አሉን
ሮዛ፡- እህ
ጌትነት፡- ያው ለሚመጣው ሰው ኢንፎርሜሽን ትነግሪያለሽ
ሮዛ፡- ሲመረቁ
ጌትነት፡- አዎ ሲመረቁ ኢቭን የሆነ ታይም ላይ እንትን ነው ሪላክስድ ነው የጎንደር ኢንቫሮመንት
ሮዛ፡- ኦኬ

መለያ ቁጥር አኮ.004

የአኮ. 002 ፋካሊቲ በመኖሪያ ቤት አሰጣጥ መመሪያ ላይ ውይይት ካደረጉት ውይይት የተወሰደ ነው፡፡ የተመረጠበት ምክንያት የመኖሪያ ቤት ጉዳይ ሁሉንም ስለሚመለከትና ለመናገር ሊያነሳሳ ይችላል ተብሎ ስለታመነ ነው፡፡

2209. በለጠ፡- በኮንደሚኒየሙ እንነጋገር፡፡
2210. እየሩስ፡- አዎ፣ የቤት ማከፋፋያ መስፈርቱ ላይ በተመለከተ ኮሜንት አድርጉና መልሱ
2211. ስለተባልን፣ ኮሜንት እናድርግ፡፡
2212. ህይወት፡- ያ የተሰጠን ነው ከዚህ በፊት?
2213. እየሩስ፡- አዎ፡፡...
2214. ኤፍሬም፡- አንድ የማስታውሰው ዩኒቨርሲቲው ቤቱን ሲፈልገው በማንኛው ሰዓት፣ ለሶስት ውር
2215. ጊዜ ሰጥቶ ቤቱን ያስለቅቃል ይላል፡፡ ትክ ይሰጥሃል ምናምን አይልም የማስለቀቅ መብት አለው
2216. ይላል፡፡
2217. በለጠ፡- አባሮት ሊሆን ይችላል ሰውየውን፡፡ ኖ በማባረር ብቻ ነው ያሰቡት፡፡ ሰውየውን
2218. ከማሰናበት አንፃር ብቻ ነው ያዩት፡፡
2219. እየሩስ፡- አይደለም በማንኛውም ምክንያት ቤቱን ከፈለገው ነው የሚለው፡፡
2220. በለጠ፡- በማንኛውም ምክንያት?
2221. እየሩስ፡- አዎ፡፡
2222. በለጠ፡- ኤፍሬም የሚለው ነው ኢንተርቴን መደረግ ያለበት፡፡ እንዳስፈላጊነቱ መተካት መቻል አለበት ያለበለዚያ፡፡ ይኸ ግን መንፈሱ ምንድን ነው ለሚያባርሩት ነው፡፡
2223. [ኤፍሬም፡- ለሚያባርሩት ነው፡፡
2224. ህይወት፡- እህ
2225. በለጠ፡- ላባረረው ስታፍ ነው የሚመስለው መንፈሱ ይሄ፡፡ በሶስት ወር ጊዜ ልቀቅ ማለት
2226. ልሰጥህም አልችልም ስለዚህ አባርሬሃለሁ ማለት ነው መንፈሱ፡፡
2227. ኤፍሬም፡- ስለዚህ ምን ያህል ሴኪዩር ነው በቤቱ
2228. ወርቁ፡- እኔ ሌላ ያየሁት ትምህርት ክፍሎችን የማወዳደር ሁኔታም ያለ መሰለኝ፡፡
2229. እየሩስ፡- የሚል አለ አዎ
2230. ህይወት፡- አለ!?
2231. እየሩስ፡- እህ፣ ዩኒቨርሲቲው እንደአስፈላጊነታቸው ለሚፈልጋቸው ትምህትር ክፍሎች ቅድሚ
2232. ሊሰጥ ይችላል፡፡ አግኝቸዋለሁ፡፡ ማን ያብበው?
2233. ህይወት፡- ማንበብ ሳይሆን ለማስታወስ ነው እንጂ፤
2234. በለጠ፡- አሁን ያሉትን ነው? አሁን ከሚያድላቸው ቤቶች
2235. እየሩስ፡- አዎ
2236. በለጠ፡- ለእነሱ ነው የምንሰጠው ነው?
2237. እየሩስ፡- ለምሳሌ ለኢንጅነሪንግ ሞር ኮታ ሊሰጥ ይችላል፡፡
2238. በለጠ፡- አዎ እሱንማ ያደርጋሉ አትጠራጠሪ፡፡
2239. ህይወት፡- ኧረ ፌር ግን አይደለም
2240. በሶጠ፡- እንዴ ፌር አይደለም! መንግስት ኦልረዲ ያለውን ነገር፤ምን ታደርጊያለሽ፡፡ ባይ ዘ
2241. ወይ ደመወዝ ሁሉ ይጨምራል ስምታችሁ ከሆነ፡፡ የውጭ ዜጋ አንድ ሺ ዶላር ተጨምሮ ነው
2242. ኢንጂነሪንግ የሚቀጠረው፤ ሌላ ፊልድ ግን ሺ አምስት መቶ ዶላር ብቻ ትሰሪያለሽ፡፡ እና
2243. በተለያየ መልኩ ፊልዶቹ ማበረታታት ይፈልጋል፡፡

2244. ህይወት፡- እኛ ዝምብለን ልንወረወር ነው እንዴ! አሁንም የሴኪዩሪቲ ጉዳይ እኮ ነው፡፡
2245. እየሩስ፡- እህ
2246. በለጠ፡- አካሄድ ነው እኮ ችግሩ
2247. ህይወት፡- የሲኪዩሪቲ ጉዳይ እኮ ነው፡፡ዋንስ አንተ የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሰራተኛ ነኝ ብለህ
2248. እስከተቀጠርክ ድረስ በእኩል አይን እኮ እንደአባትነት እንደወላጅ ነው መታየት ያለብህ፤
2249. እንደወላጅ፣ ኧራ..
2250. እየሩስ፡- አህ
2251. ኤፍሬም፡- ዩኒቨርሲቲው በማንኛውም ጊዜ ቤቱን በሚፈልገው ጊዜ የሶስት ወር ማስጠንቀቂያ
2252. በመስጠት ቤቱን ይረከባል ይላል፡፡ ምናልባት ያች ቤት ለስራ ተፈልጋ ከሆነ ለመምህሩ ትክ ቤት
2253. ይሰጠዋል የሚል ነገር ቢኖር፡፡
2254. እየሩስ፡- እህ
2255. በለጠ፡- መምህሩ በስራ ላይ እስካለ ድረስ፤ በስራ ላይ ላሉ መምህራን ትክ ቤት የሚል
2256. እንዲካተትበት፡፡
2257. ህይወት፡- ያው ግን በጥፋት ግን ከሆነ ምንም ኤክስኪዩዝ የለውም
2258. በለጠ፡- አይ በስራ ላይ ላሉ ነው እኮ የሚልሽ፤ በስራ ላይ
2259. እየሩስ፡- እህ
2260. ኤፍሬም፡- የዩኒቨርሲቲው ማናጅመንት እንደአስፈላጊነቱ የትምህርት ክፍሎች ያላቸውን
2261. ሁለንተናዊ ጠቀሜታ ....ለትምህርት ክፍሎች፣ ኮሌጆች...፡፡ ለምሳሌ እነሱን የማቆይበት መንገድ
2262. እፈልጋለሁ ካለ በእድሌ ነው የማገነው፡፡ መቃወም የሚቻል አይመስለኝም፡፡ ምን ማድረግ
2263. እንችላለን፡፡
2264. ህይወት፡- እንደሱ አይደለም ግን አኔ አንደርስታንድ ያደረኩት፡፡
2265. በለጠ፡- ኖ አላማውማ እሱ ነው፡፡ ኢንጅነሪንግና ሳይንስን ነው፡፡
2266. ወርቁ፡- ለሚፈለጉ የትምህርት ክፍሎች ከተባለ ነው፡፡
2267. ዶር. በለጠ፡- ሌላ ነገር የለውም፡፡
2268. ኤፍሬም፡- 50 ቤት ቢኖር ለእኒጅነሪንግና ለሳይንስ 45ቱን ይሰጣቸዋል፡፡
2269. ዶር. በለጠ፡- 45ቱን ይሰጣቸዋል፡፡
2270. እየሩስ፡- አዎ
2271. ኤፍሬም፡- ተገቢ እንዳልሆ ግን ማሳየት እንችላለን፡፡
2272. እየሩስ፡- አዎ፣ በክራይቴሪያው መሰረት ይታደል፤ ሌላ እንትን መምጣት የለበትም ማለት
2273. እንችላለን፡፡
2274. ኤፍሬም፡- ሁላችንም ለሀገራቱ ጠቃሚ ዜጎችን ነው የምናፈራው፤
2275. እየሩስ፡- አዎ
2276. ኤፍሬም፡- ስለዚህ ምናልባት እነዚህ ፕሮግራሞች አስፈላጊ አይደሉም ከተባሉ መዝጋት ነው
2277. እንጅ፤ ሌሎቹን መምህራን ከሌሎቹ ጋር ምናልባት ማወዳደር፤ አንዱ ፕሮግራም ጠቃሚ
2278. ነው፤ሌላኛው ፕሮግራም ጠቃሚ አይደለም ማለት እንደማያዋጣና ጠቃሚ አይደለም ከተባለ
2279. መዝጋት፤ አይሻልም፡፡
2280. ወርቁ፡- ሌላ ደግሞ የተነሳው ምንድን ነው፤ ሶስት ሰዎች ባለእንድ መኝታ ቤት ባለሁለት
2281. ባለሰሶስት መኝታ ቤት አግኝተው፤ እነዚህ የህውስ አላውንስ ይቆማል የሁሉም፡፡ ያ ባለሶስስት
2282. ያሄ ባለሁለት ይሄ ባለአንድ አግኝቶ እንዴት ነው ለሁሉም አንድ የሚሆነው? አሁን ለምንድን
2283. ነው ስቲዲዮ የሚደርሰው ለምንድን ነው እኩል ክፍያ የሚቆመው?
2284. [በለጠ፡- አመዳደቡ፣ ፋሚሊ ሳይዝህን..
2285. ወርቁ፡- ለምንድን ነው ባለማግባቴ ያንን ነገር ላጣው የሚገባኝ?
2286. ህይወት፡- እህ!
2287. እየሩስ፡- ባይ ዘ ወይ የአሁኑ መመሪያ ላይ የቤተሰብ ምናምን ሁኔታ ብዙም... ብዙም
2288. ክፍተት የለውም ግን፡፡
2289. ህይወት፡- ግን እኔ ይሄ ጥያቄ ሁለተኛው ላይ ባለትዳርና ልጅ የሌለው ይላል፡፡ ባለትዳር ሆኖ
2290. ልጅ የሌለው ለምንድን ነው ከባለትዳርና ልጅ ካለው እንትን የሚባለው የሚለየው?

2291. በለጠ፡-የሚለየው?
2292. ህይወት፡- አዎ!
2293. ዶር. በለጠ፡- ብዙ መኝታ ቤት አያስፈልገውም፡፡ ይህን በተመለከተ ፋሚሊ ሳይዝ ልክ ነው፡፡ አንተ
2294. ራስህ ቤት ብታወርስ ለልጆችህ እንዴት ነው የምትሰጠው? ላገባው ነው ብዙ ነገር
2295. የምትሰጠው፡፡
2296. ወርቁ፡- ግን እኔ ሁልጊዜ ካላገባሁ... ሰፊ ቤት አልፈልግም?
2297. ዶር. በለጠ፡- ምን ያደርግልሃል? ዩኒቨርሲቲው ሊያዝናናህ አይደለም አላማው፡፡ እንድትቆይ ነው...
2298. ወርቁ፡- እንዴ አንተ ስትዲዮ፡ እንዴት ነው የምታደርገው?
2299. በለጠ፡- አግባ!
2300. ህይወት፡- አግባ ያልኩህ እኮ የሆነ ልጅ ምናምን እንድትይዝና ማሳደግም ምናምንም
2301. ይኖርብሃል፡፡
2302. አመለወርቅ፡- ከሌላው ማህበረሰብ መቼም አንተ ትሻላለህ በደንብ አሳድገህ ለማስተማር...
2303. ኤፍሬም፡- አዎ ወልዶ ዜጋን በመተካት ሃላፊነት አለብህ
2304. ወርቁ፡- ቀልዱን ተወዉና ለምሳሌ ላጤ ብሆንም ሶፋ መግዛት እፈልጋለሁ፤....
2305. በለጠ፡- ኦኬ ውድድር እኮ ነው አሁን፤ ግን ባለፋሚሊው ምን ይሁን? ስቲዲዮ ውስጥ ይግባ?
2306. አንተ ሶፋ ላይ እየረገጥህ እዚና እዚህ አንድ አግርህ ሶፋ እንድ እግርህ መኝታ ቤት ሆኖ፤
2307. ወርቁ፡- እንደዛ ከሆነ ደግሞ ክፍያው እኩል መሆን የለበትም ነው፡፡
2308. በለጠ፡- የምን ክፍያ ነው?
2309. ወርቁ፡- አሁን ለምሳሌ አንተ ባለሶስት መኝታ ይዘሃል፣እኔ ስቲዲዮ አለ አይደለ፤
2310. በለጠ፡- አሃ
2311. ወርቁ፡- አራት መቶ አራት መቶ የሚከፈል የነበረው ሁላችንም እናጣለን፡፡ ለአንተ
2312. ሊቀር ይችላል፡፡ ለእኔ ግን ቢያንስ የተወሰነ ሊከፈለኝ ይገባል፡፡
2313. ህይወት፡- ለላጤ እኮ ስቲዲዮ ሁላ ሊሰጥ ይችላል ማለት ነው፡፡ ፌር ግን አይደለም፡፡ መኝታ
2314. ቤት ትጠላለህ እንዴ አንተ፡፡ ሳኖል ትጠላለህ ላጤ ስትሆን፡፡...እረ ፌር ግን አይደለም፡፡
2315. ወይ የስቲዲዮን ነገር ሊያስቡበት ይገባል፡፡
2316. ኤፍሬም፡- አይ ይሽ ጉዳይ ለረጅም ጊዜ ሲያጨቃጭቅ የነበረ ጉዳይ ነው፡፡ ዛሬ የምንፈታው
2317. አይመስለኝም፡፡
2318. እየሩስ፡- ጨረስን?
2319. በለጠ፡- ያገኘነውን እናቅርበው እባካችሁ ይጠቅማል የምንለውን በኋላ እናቅርበውና...
2320. ዶር. ሳምሶን፡- አዎ ከፀደቀ በኋላ ለምን ከምንል አሁን ማለት ያለብንን እንበል፡፡
2321. ህይወት፡- ባይ ዘ ወይ ግን ብዙ ክራይቴሪያዎች ተስተካክለዋል፡፡ እንደበፊቱ አይለም ...
2322. እየሩስ፡- በጣም ብዙ ነገር ተስተካክሏል፡፡ የትዳር ሁኔታ እኮ አሁን በጣም ትንሽ ማርክ ነው
2323. ያለው፡፡ በፊት እኮ አስር ማርክ ምናምን ነበር ያለው፡፡
2324. ህይወት፡- ችግር የለም፡፡ መጀመሪያ እስቲ ይስጡን ቤቱንና ስለቤቱ..
2325. ኤፍሬም፡- እናቶች ካገቡ በኋላም እንደዚህ ይላሉ አሉ፡፡
2326. ህይወት፡- እዲያ
2327. ወርቁ፡- ግን ያለው ቤትና ፍላጎቱ ይመጣጠናል ነው የሚባለው፡፡ ማማረጥ
2328. እየሩስ፡- እህ
2329. በለጠ፡- ማማረጥማ የግድ ነው፡፡
2330. ወርቁ፡- ኢን ኬዝ ወርቁ ቤት ሰርቶ ከዛ እየኖረ ስቲዲዮ ግባ ቢባል አልገባም
2331. ቢል መብቱ ይጠበቅለታል፡፡
2332. ዶር. በለጠ፡- አራት መቶ ብር ትሰጥሃለች ነው፡፡
2333. ህይወት፡- አህ አራት መቶ ይሰጥሃል፡፡ትችላለህ መብትህ ነው፡፡ ሲፈልግ ያከራያል፡፡
2334. ኤፍሬም፡- የራስህ ቤት መኖር ትችላለህ፤ እንዲያውም ችግር የለም፡፡
2335. በለጠ፡- ይሻላል፤ እንድ ቤት እኮ በአራት መቶ ብር አታገኝም ባህር ዳር፡፡
2336. እየሩስ፡- ደብዳቤው የሚለው የመጀመሪያው ገፅ ላይ የቤት አበልንም ወጭ ለመቀነስ ምናምን
2337. ይላል፡፡

2338. በለጠ፡- እንደዚያ ይላል
2339. እየሩስ፡- ይላል፤ አዎ
2340. ዶር. ሳምሶን፡- መኖር እምቢ ካለ
2341. እየሩስ፡- እህ
2342. ዶር. በለጠ፡- አብዛኛው ግን ይገባል፡፡
2343. ህይወት፡- ኧረ እኛም ወጭ ይቀንስልናል እቴ፡፡
2344. በለጠ፡- የፈለገው ሊሆን ይገባል፡፡ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡
2345. ህይወት፡- ግን የስቱዲዮ ነገር ሊያስቡበት ይገባል አሁን ስቱዲዮ ምን እናደርግበታልን፡፡ እኔ
2346. ጨነቀኝ አሁንስ፡፡
2347. በለጠ፡- ስቱዲዮ አእምሯቸው ውስጥ መግባቱ ነው መጀመሪያ ትልቁ ጥፋት፡፡
2348. ህይወት፡ አዎ
2349. እየሩስ፡- አዎ
2350. ህይወት፡- አዎ
2351. በለጠ፡- ዲዛይኑ ውስጥ ስቱዲዮ መጥፋት ነበረበት፡፡
2352. ህይወት፡- ስቱዲዮ ወይ እንደስቶር ምናምን ነበር..
2353. በለጠ፡- ስቱዲዮ ለማስተርስ ተማሪ ነው፡፡ ለምሳሌ ውጭ ስትሄዱ ስቱዲዮ የሚባል
2354. ነገር አለ፡፡ ስቱዱዮ ትገባለችሁ፡፡ ሌላ ነገር አይደለም፡፡ በቃ ስቱዲዮ አላማዋ፡፡
2355. ህይወት፡- ግን እሱን አስተያየት እኛ መስጠት አንችልም አሁን?
2356. እየሩስ፡- የትኛውን?
2357. ህይወት፡- ስቱዲዮችን ለገስት ሀውስ ምናምን ምናምን ወይም ለስቶር
2358. በለጠ፡- አይፈልግማ! ሰው አይፈልግም ባይ ዘ ወይ፡፡ ለመኖር ያክል ነው እንጅ፤
2359. አፓርትመንት ውስጥ ስቱዲዮ አድርገሽ ገስት ሀውስ ማድረግ አይቻልም፡፡ ማንም ልጅ
2360. እንዲጫጫበት አይፈልግም፡፡ ከአዲስ አበባ ከአውሮፓ ከአሜሪካ አመጣሽ እንግዳ፡፡ እና ግባ
2361. እዚህ ተኛ፡፡ እንዴ የሰፈር ህፃን እንዴት ብሎ ነው የሚያስተኛው፡፡
2362. ህይወት፡- ኧረ ማንም እሽ አይልም፡፡
2363. ወርቁ፡- ግን አንተ በየትኛውም ሳይዝ መወዳደር ትችላለህ? ባለሶስቱ ባለሁለቱ ላጤ
2364. ሆነህ፤
2365. በለጠ፡- እህ
2366. ኤፍሬም፡- ምናልባት አስተያየት ስጡን የተባለ ይመስለኛል፡፡
2367. ህይወት፡- መልካም አዎ
2368. ኤፍሬም፡- አስተያየት ሲሰጥ ጠንካራ ጎንም ቢገለፅላቸው፤
2369. በለጠ፡- ጥሩ ትክክል
2370. እየሩስ፡- አዎ
2371. ኤፍሬም፡- ከአሁን በፊት የነበረው ለምሳሌ ብዙ ችግሮች እንደነበሩበትና ይሽ መስፈርት
2372. መውጣቱ በከፍተኛ ደረጃ....
2373. በለጠ፡- አብጀክቲቪቲ ጥያቄዎችን ምናምን
2374. እየሩስ፡- እህ
2375. በለጠ፡- በተለይ ደግሞ ከሃላፊነት አንፃር ቤት ቅድሚያ እንዲያገኝ ወይም ለበላይ
2376. ሃላፊዎች በተዘጋጀ መኖሪያ እንዲኖር ይፈቀድለታል አይደል፤ ከሃላፊነት ሲወርድ ቤቱን
2377. ለዩኒቨርሲቲው ያስረክባል፡፡
2378. ዶር. ሳምሶን፡- ትክክል ነው..
2379. እየሩስ፡- አዎ
2380. ኤፍሬም፡- ማለት ሃላፊ ሆነው፣
2381. በለጠ፡- ወዲያው ሲወርዱ
2382. ኤፍሬም፡- ቤት ያገኙና ሲወርዱ በዛው ነው የሚቀጥሉት፡፡
2383. ወርቁ፡- የት ይሄዳሉ?
2384. በለጠ፡- ሂዶ ይቀበላ!

2385. ኤፍሬም፡- በቃ ይለቃሉ ይላል፡፡ያልተያዘ ወይም የተለቀቀ ቤት ካለው በቅድሚያ እንዲያገኙ
2386. ይደረጋል፡፡
2387. በለጠ፡- ትክክለኛ አሰራር ነው ይኸ፡፡
2388. ኤፍሬም፡-እና ማለት እሸቱና ሀይሉ የሚኖሩበት ቤት አሁን ዘመናዊ ቤት በጣም ዘናጭ ቤት
2389. ዶር.እሸቱ ያለምንም ውድድር ነው የገባው፡፡
2390. በለጠ፡- የቱ ነው?
2391. ህይወት፡- እዚህ አዲሱ ፎቅ
2392. ኤፍሬም፡-ያለምንንም ውድድር፡፡ በእርግጠኝነት በድሮው ቢሆን ከስድስት ምናልባት ከስድስት
2393. ወር በኋላ ከሃላፊነት ቢወርድ በዛው ነው የሚቀጥል፡፡
2394. በለጠ፡- አዎ በድሮው እዛው ነበር የሚቀጥለው፡፡
2395. ህይወት፡- ይሄ የስቱዱዮ ነገር ግን እምልሽ አስተያየት መስጠት ግን አይከፋም፡፡
2396. በለጠ፡- ስቱዱዮ የሚባል ነገር ከጭንቅላታቸው ማውጣት ነበረባቸው፡፡
2397. እየሩስ፡- መስፈርቱን እኮ ነው ተቹት የተባለ፡፡ እዚህ ውስጥ ስለስቱዱዮ እኮ አያወራም
2398. በለጠ፡- ስለህንፃ ማንም አልጠየቀሽም
2399. ህይወት፡- ኧረ እኔስ አሳሰበኝ
2400. ኤፍሬም፡- ስለስቱዱዮ ምንም የተፃፈ ነገር የለም፡፡
2401. በለጠ፡- እሽ የተሰጡት አስተያየቶች በቂ ናቸው፡፡ ቃለጉባዔው በደንብ ይፃፍና
2402. ይላካል፤፤እናመሰግናለን፡፡
2403. ህይወት፡- ኧረ ይገባናል ዛሬ፡፡
2404.

መለያ ቁጥር አጠመ.006

በዩኒቨርሲቲው ሰብሳቢነት ከተካሄደ አጠቃላይ የመምህራን ውይይት የተወሰደ

1. ከበደ፡ ...ያለንን ፕሮግራሞቻችንን የመዳሰስ ነገር የሚለው ነገር ሁሉንም
2. ፕሮግራሞቻችንን ዳሰን እነዛን ፕሮግራሞች ሪቫይዝድ የማድረግ ብቻ ሳይሆን
3. አንዳንዱ... እኔ የምሄድበት ሁኔታ፡፡ ይሄን የምልበት እኔ ያለሁበት የራሴን
4. ፕሮግራም ጉዳይ ስለማውቅ ነው፡፡ እና አሁን የምናሰለጥነው የስርኣተ ትምህርት
5. ባለሙያ ነው፡፡ የስርዓተ ትምህርት ባለሙዎችን ስናሰለጥን የተነሳነው የፍላጎት ዳሰሳ
6. ጥናት አድርገን ነው፡፡ የዳሰሳ ጥናት ስናደርግ በአማራ ክልል ብቻ አሁን የትምህርት
7. ስራ ወደወረዳ ስለወረደ በወረዳ ደረጃ እንኳን አንድ አንድ የስርዓተ ትምህርት
8. ባለሙያ ብናስቀምጥ መኣት ሰው ያስፈልጋል ተብሎ ነው፡፡ በአገር አቀፍ ደረጃ
9. ማለት ነው፡፡ እነዛ ተማሪዎች ከተመረቁ በኋላ ግን ሊቀጠሩ አልቻሉም፡፡ ለምንድን
10. ነው የማይቀጠሩ ብለን እስከ ትምህርት ቢሮ ድረስ ሂደን ለማየት ሞክረናል፡፡ ...
11. ስለዚህ ያን ፕሮግራማችንን እንደገና ማየት አለብን፡፡ ሌላው መማሪያ ክፍሎችን ስንመለከት
12. ሁሉንም ክፍሎች እንኳ ባይሆን የተወሰኑ ክፍሎችን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የማደራጀት ነገር፡፡
13. እኔ አሁን ጥሩ ነው የምለው ነገር አለ፡፡ በእኛ ፋካሊቲ በተለይ እኔ አንዳንዶች ሊኖራቸው
14. ይችላል፡፡ እኔም አሁን የምለው ነገር አለ፡፡ በበኩሌ እኔ አሁን የተደረገልን ነገር ምንድን ነው
15. ላፕቶፕ አለኝ ተሰቶኛል፡፡ ኦቨር ሄድ ፕሮጀክተር ማግኘት እንችላለን፡፡ ኤል ሲዲ ተሰቶኛል
16. በግሌ ወስጃለሁ፡፡ እንዲያውም ፕሪንተርም ተሰቶኛል፡፡ ይሄ በጣም ምቹ ያደርግልናል
17. የመማር ማስተማሩን ነገር፡፡ እኔ አንድ አክቲቪቲ ከኢንተርኔት ባገኝ ወዲያውን
18. ዳውን ሎድ አድርጌ ፕሪንት አድርጌ ለተማሪዎቼ ማሰራት እችላለሁ፡፡ ግን ከዚህ
19. አኳያ ጥሩ ነው፡፡ ግን በኤል ሲ ዲ በፓወር ፖይንት አስተምራለሁ ብየ ሳስብ ላፕ
20. ቶፔን፣ኤል ሲ ዲውን ተሸክሜ ነው የምሄደው ወደመማሪያ ክፍል፡፡ በዛን ጊዜ
21. ዘግይቶ የገባ መምህር በሰላቱ አይወጣም፡፡ ያን ተሸክሜ በር ላይ እጠብቃለሁ
22. እየተንቀጠቀጥኩ፡፡ ይወጣልኛል ከዛ ገብቼ ማስተካከል እጀምራለሁ ስንት ደቂቃዎች
23. ናቸው የሚባክኑት በዚህ መሀል፡፡ እናም እዚህ ላይ መሰራት አለበት፡፡
24. እሱባለው፡ ጉዳዩ ግልፅ ነው፡፡ ምንም እንትን የለውም፡፡ ተፅዕኖው እኛ ላይ ያርፋል
25. የሚል፣ አገራችን ላይ ያርፋል የሚል፣ ልጆቻችን ላይ ወገኖቻችን ላይ ያርፋል
26. የሚል እምነት ስላለ ነው፡፡ ይህን ጉዳይ 2004 ዓ.ም ላይ አንስተነዋል፡፡ ምን
27. እናድርግ ይህን ስጋት ለመቅረፍ በሚል ተነስቷል፡፡ እና አይደለም ለእኛ ለኢትዮጵያ
28. ለአለምም በሚያሰጋበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ስለብዝሀነት የምለው
29. ነገር አለን፡፡ ስለብዝሃነት ስናነሳ እኔ ከማጠናው ጥናት ውስጥ ምናልባት ፊዚክስ
30. መምህር ፊዚክስን አስተምሮ ሊሄድ ይችላል፡፡ ሳይንስ ነው የሚያስተምረው...
31. ፕራክቲካል የሆነውን ነገር ሊያስተምር ይችላል፡፡ ግን ከዚህ ውጭ ሊሆኑ የማይችሉ
32. በርካታ የትምህርት መስኮች፣ዲስፕሊኖች ከዚህ ነፃ የሚሆኑበት መንገድ የለም፡፡ እኔ
33. እንደነገርኳችሁ የአንድ አምስት ፋካሊቲዎች፣ ኮሌጆች፣ ስኩል ካሪኩለማቸውን ብቻ
34. ሳይሆን እስከ ጋይድ ቡካቸው በእጄ አለ፡፡ ያን አሰስመት ስሰራ ያየሁት እነዚህ
35. ጉዳዮች ተካተው በይዘታቸው ውስጥ አሉ፡፡... እንድ ምሳሌ ልነግራችሁ እችላለሁ፡፡
36. ተሳታፊው፡ ጫጫታ፣ጭብጨባ (አቁም በቃን)
37. እሱባለው፡ እኔ ህዝብ ግንኙነት መምህር ሆኜ ሳስተምር ጥሩ ምሳሌ የሆነኝ ህዝብን
38. ከአንድ ፅንፍ ወደሌላ ፅንፍ ሊያንቀሳቅስ የሚችል የሚሊኒየም ዳም ምሳሌ ነበር ሁሌ
39. የማነሳው እሱን ነው፡፡ ከዛ በተጨማሪ ስለ ሪስክ ኮምንኬሽን ሳወራ የማነሳቸው
40. ጉዳዮች ነበሩኝ፡፡ ለምሳሌ...ስለአንድ ፕሮጀክት ማውራት ካለብኝ ጥሩ ምሳሌ አድርጌ

41. ስወስደው የነበረው ባለፈው አመት የዋልባ ገዳም የስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክት ገና
42. ከጅምሩ ተቃውሞ እየገጠመው መጣ። ይሄ እንግዲህ አንድ ችግር መኖሩን
43. ያሳየናል። ወደኋላ...
44. መልካሙ፣ መቼም የጉዳዩ አሳሳቢነት ምንም ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ
45. አልመሰለንም። በጣም አሳሳቢነቱ ይሰማኛል። ደሞ በጣም የሚያሳስበኝ
46. ሜቶዶሎጂው ነው። እንዴት እንግባባ ምን ብንል እንግባባለን፣ ምን ባንል
47. ደግሞ አንግባባም የሚለው ነገር ያሳስበናል። እንዴት ነው አንድ ጊዜ አንድ መጽሀፍ
48. ሳነብ ባልና ሚስት ለምን ይጣላሉ? ለምንድን ነው ሴትና ወንድ የሚጣሉት የሚል
49. ነገር አንስቶ የሆነ ለማሳመን ሲሞክር ሁለቱ ከተለያየ ፕላኔቶች ስለመጡ ነው።
50. አንዷ ከማርስ አንዱ ከጁፒተር። ስለዚህ ፕላኔቶቹ የተለያዩ ስለሆኑ ስለማይተዋወቁ
51. ይጣላሉ የሚል የመከራከሪያ ነጥብ እንዳየሁ ይሰማኛል። እና ትልቁ ነገር
52. መተዋወቅ መግባባት ይመስለኛል። ግን እንዴት የሚለው ጥያቄ ደግሞ ከባድ ሆኖ
53. አገኘዋለሁ። ከዛ ላይ ቅድም ሲነሱ እንደነበሩት አንድ ተናጋሪ ለምሳሌ ሰው በዛፍም
54. የማምለክ መብት አለው ሲል፤ ሌላው ደግሞ እኔ ደግሞ ለሀይማኖት... ጥቅም
55. ስለሌለው... ግን ምን ጉዳት አለው እንዲህ አይነት ነገሮች ሊነሱ ይችላሉ።
56. እንዲያው አምልኮትን እንተውና አሁን ዛፍ በኢትዮጵያ እና በአለም አሳሳቢ ነገር
57. ሆኗል። አንድ ፈረንጅ እንድ ጊዜ እኛን ልታሰለጥን የመጣች ልጂ የኢትዮጵያን ዛፍ
58. ሰላም በይልኝ ብላኛለች ብላ እዚህ ግቢ ያለውን ዋርካ ሰላም ስትል አይቻለሁ። ...
59. እና እንዲህ እንዲህ ያሉ ነገሮች ናቸው ናላየን የሚያዞሩት እና እኔ የተጨበጠ
60. ነገርም የለኝም ግን ዝም ብየ የሚያሳስበኝ ነገር አለ። አመሰግናለሁ።
61. ሰብሳቢው፣ እሽ ከማጠናቀቃችን በፊት አንድ ማስተዋሻ ደርሶናል። እባካችሁ ሴቶች
62. ሃሳብ እንዲሰጡ አድርጉ ይላል። ጊዜ ስለሌለን ለአንድ ሴት እድሉን እንሰጣለን። እሽ
63. አዛ ጋ
64. አልማዝ፣ የተሰማችኝን ነገር ወደእናንተ ለማቅረብ ነው። ህገ መንግስት ቨርሰስ
65. ሃይማኖት፤ ሃይማኖት ቨርሰስ ሃይማኖት፤ አክራሪነት ቨርሰስ መንግስት፤ የገበያ
66. ንረት ቨርሰስ ድህነት። እነዚህ ላይ ነው እኔ ያስተዋልኩት። ህገመንግስት ስንል የህገ
67. መንግስት ወጥነትና ጥሩነት ህዝቡን በሰላም እንዲኖር ለልማት እንዲሰለፍ
68. አድርጓል። ስለዚህ አሁንም ህዝቡም ህገመንግስቱን ጥበቃ ሊያደርግበት ይገባል።
69. ምክንያቱም ህገመንግስት በሃይማኖት ጣልቃ አይገባም። ህገመንግስቱ የሰብኣዊ
70. መብትን ያከብራል። ለህፃናት፣ ለሴቶች፣ ለጭቁን የተሻለ ኑሮ እድል ይሰጣል።
71. ስለዚህ ህገመንግስታችን ጥበቃ ለማድረግ ሃይማኖት ጣልቃ መግባትና አፍራሽ
72. ተልዕኮ እንዲኖረው የሚያደርጉት እውነትም የውጭ ጠላቶች ካልሆኑ የቆዩ
73. መንግስት እንኳ ህገሩን አስጨንቆ ለመግዛት ሃይማኖት ወይም ሞት እያለ በተለይም
74. ...ን ህዝብ በጦር በወታደር መሪነት ለጦርነት ሲማግደው ሲያስፈጀው ኖረ
75. እንጂ አልጠቀመውም። በዚህም የተነሳ ይህ የመንግስት አሸከርካሪው ወታደር ሹመት
76. እንዲያገኝ ብሎ የተወሰነው በሃይማኖት ለመቀደስ ብሎ ሳያውቀው ሲሞት ኖሮ
77. መጨረሻ ደግሞ ባለደምህ ነው እየተባለ እስካሁን ድረስ የሚታረደው ይህ ድህ
78. የ... ህዝብ አሁንም ደግሞ እንዲታረድ የሚያቅዱ የውጭ ጠላቶቻችን እንጂ
79. ኢትዮጵያውያን አይደሉም። .....እኔ የማውቃት ትንሽ በሃይማኖቴ ጌታችን ነፍሱን ሊያወጣ ሀሳይ
80. መሲህ ነው ብሎ ዲብሎስ በመስቀሉ ስር ግን አላወቀምና የማይገባውን ስልጣን ሲጋፋ ተይዞ ሲጠየቅ
81. ለካስ ተሳስቼ ነው። ሳምንት ስበጠብጥ ኖሬያለሁ ይቅርታ የምጠይቀው አስገድደኸኝ ሳይሆን እስካሁን
82. ያሰቃየሃቸውን ነፍሳት በነፃ እሰጥሃለሁ አለ ነው የሚሉ አባቶቻችን። እኔ ሃይማኖቴን ላስተምር
83. ሳይሆን ነፃነት፣ ዲሞክራሲ እንዲሰጠው ሲጠየቅ እንደፈለክ ነው ያለው። አልገዛው፣ አልቀጠቀተው፣
84. አላሰረው ይሂድ አንተን ያመነ ከአንተ ጋር ይሂድ፤ እኔን ያመነ ከእኔ ጋር ይሂድ።፤ ታዲያ
85. ዲሞክራሲዊ መብት ከዛ መሰረት አለ ..... አይቻልም። ይሄን ቤት የሚያፈርስ ቢመጣ እኛ ዝም
86. ብለን አናይም። ባለህንባው ይቀጠዋል እንጂ የሚያፀድቅ አይደለም። ይሄ አክራሪነት እንጂለቱ የውጭ
87. ጠላት ነው! የሚያቀነባብረው። እና ማለትም መንግስት በተለይ የቆዩ ጠባሳዎችን እያከመ መሄድ

88. አለበት፡፡ ማለት ጠባሳዎቻችን ድህነት፣ ጦርነት እንደገና እንዲያንሰራሩ የሚያደርጉትን ዝም
89. ብሎ ካየ ድህነት አለ ድህነት፣ አንድ ድሀ ዝም በል ይባላል፡፡ አፉ ዝም ቢል አፉ ይዘጋል፣ ሆዱ
90. ይጮሃል፣ አይኑ ይፈዛል፡፡ ይህን ችግሩን መፍትሄ ካልሰጠነው ባይናገርም እንኳ ቆዳው ይሸበሸባል፣
91. ሰውነቱ ይደክማል፡፡ ሊሞት ሲያጣጥር ርዳታ፣ መረባረብ መፍትሄ አይሆንም፡፡ ሳይሆን ልንደርስለት
92. ይገባል፡፡ ሰፊው ድሀ ህዝብ በረሀብ እየተወጠረ ሌላው የሃይማኖት አክራሪነት እኔ ለራሴ አይገባኝም!
93. ሌላው ደግሞ በተለይ በዚህ በልማታችን የአስተዳደር ችግር ሊኖር ይችላል፡፡ በነበረው መንግስት በአዬ
94. ሀይለስላሴ እኔ ህፃን እያለሁ የጤና ግብር፣ የትምህርት ግብር ትንሽ ልጅ ነበርኩ፡፡ አባቴ ይመጣና
95. ምን አለ አንዱ ገበሬ እኔ ጤነኛ አሁን ምን ታደርጉ ነው እኔን የጤና ግብር የምትጠይቁኝ ሀኪም
96. ቤት ሄጄ አላውቅም አለ አሉ፡፡ አያችሁ ድሮ የጤና ለብቻ የትምህርት ለብቻ እኔ የት ተምሬ ይሉ
97. ነበር አባቶች... በኋላ ግን ደርግ ምን አረገው አንድ ላይ ጠቅለው የመሬት ግብር አመታዊ ግብር
98. እንግዲህ ከሚያመርተው በላይ ግብሩ ሲመረው ገበሬው፣ እንደገና ደሞ የመንግስት ሰራተኛው ድህነቱ
99. ሲመረው አመፅ፡፡ በተለይም የባለስልጣኖች ለዚህ ለነበረው ገዥ መንግስት አስገባሪ የተባሉ
100. የባለስልጣኖች ልጆች ሳይቀሩ የህዝብ በደል መሯቸውና ገብቷቸው ወገንነታቸው ወደ ደሀው
101. ወግነው መሳሪያ ይዘው በርሀ እስኪሰደዱ ድረስ አስቸጋሪ የነበረውን ያንን አስተዳዳሪ
102. ለመዋጋት ወደ በርሀ ሄደው ህዝብን ይዘው አንድነታቸውን አጠናክረው ደርግን ያህል
103. ከሃዲውን ለድሀ ቆምኩ ያለውን ወታደር ሳይቀር ደምስሰው በህዝብ ጉልበት ነው በጦር
104. መሳሪያ እኮ አይለም ኢህአዴግ ይኸ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ ኢህአዴግ የህዝብን ድጋፍ፣
105. የህዝብን ጉልበት፣ የህዝብን ደጋፊነት ይዞ ነው ሊያሸንፍ የቻለው፡፡ በጦርነት ላይ እያሉ
106. ኢህአዴጎች እንዳይሸነፉ ክፍት የሆነውን መንገድ ወፍ ጠባቂው፣ ከብት ጠባቂው እየመራ ነው
107. ያወጣቸው፡፡ መንገድ እንኳ ቢሞቱ መሳሪያቸውን አንስቶ አብሮ እየተዋጋ ነው ያሸነፋቸው፡፡
108. የህዝብ ሀይል ነው የነበረው ጉልበት ውቅያኖሱን የወታደሩን ያን ያሸነፈው፡፡ ስለዚህ..... እኔ
109. ለራሴ የማውቀው ነገር አልነበረኝም፡፡ አሁን ግን በጣም ተገንዝቤያለሁ፡፡ ..... ለምንድን ነው
110. ለህዝቡ የማናቀርበው፡፡ እስቲ ቆም ብለን መጀመሪያ የኢትዮጵያን ህዝብ አንድ ልብ ያደረገውን
111. ለኢትዮጵያ ህዝብና ለአፍሪካ የሚጠቅመውን የአባይን ግድብ እንጨረስ፡፡ እኔ በበኩሌ...
112. አመሰግናለሁ፡፡

የመለያ ቁጥር ኢመ. 001

የምሳ ግብዣ (ከአውደ ጥናት ማጠናቀቂያ በኋላ)፡ የ001 ፋካሊቲ መምህራን (የአራት ትምህርት ክፍል መምህራን)
ከታዳሚዎቹ መካከል በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተሰባስበው የተቀመጡ መምህራን ናቸው፡፡

1. አዳነች፡ ተጫወቱ ደግሞ፡፡ ዋናው ጨዋታው ነው፡፡ ጨዋታ መልካም ነው፡፡ እና
2. ደግሞ እስክስታ ሊቀጥል ስለሆነ...
3. ሶፍያ፡ አዎ
4. ዮናስ፡ (በመደራረብ) ለምድን ነው እኔን ግን ያልጋበዛችሁኝ ልያቸው ብየ...
5. አልማዝ፡ እግዚአብሄርን
6. ዮናስ(በመደራረብ)እኔ እኮ ባጋጣሚ ነው የመጣሁት፡፡ የሆነ ነገር ልወስድ መጥቼ
7. እኮ ነው፡፡
8. ሄለን፡ ስምህ ሲጠራ...
9. ሶፍያ፡ ደብዳቤ ለየትምህርት ክፍሉ ተልኳል
10. አዳነች፡ ለየትምህርት ክፍሉ እኮ ተልኳል፡፡
11. [አብይ፡ (ጣልቃ በመግባት) ዮናስ እኮ መከራውን አየ
12. ዮናስ፡ እንዴት?
13. አብይ፡ አስተያየት በመስጠት መከራውን አየ
14. ዮናስ፡ አንተ አለህ አይደል አንዴ የምትናገርበት አጋጣሚ አተህ
15. መዓዛ፡ የጨዋ ..... ምናምን እልክ አይደል
16. አዳነች፡፡ አይ አብይ(ሳቅ) ለነበረኝ ጊዜ እግዚአብሄር ይመስገን ብሎ ጮሆ ሳይናገር ቀረ
17. ዮናስ፡ እንዲያውም አቡነዘበሰማት ሳይል መቅረቱ ገርሞናል፡፡ እንዝጋው በእንትን
18. አለማለቱ
19. አዳነች፡ የሰማነውን በልቦናችን...
20. አብይ፡ የሰማነውን በልቦናችን እናስቀምጥ
21. ዮናስ፡ እናስቀምጥ ነው እናድርግ ነው?
22. አብይ፡ ተግባራዊ እናድርግ ማለት ነው
23. አልማዝ፣ ውብነሽ እና ሳባ በግላቸው በሹክሹክታ ያወራሉ፡፡
24. መዓዛ፡ ዶር ከበደ እኮ ናቸው አስተምረው ጨርሰው ሊወጡ ሲሉ፣ ብርሀነ አይናችሁን
25. ይግለጥላችሁ››ይላሉ
26. አዳነች፡ እኔ ግን የማይመቹኝ ሰው ማን ናቸው ዶር. ከበደ ናቸው፡፡
27. ማርቆስ፡ ኧረ ባክሽ! አታውቂያቸውም?
28. አዳነች፡ ብዙ ኦፖርቹንቲስ ላይ አግኝቻቸው አልወዳቸውም፡፡
29. ማርቆስ፡ ዶር ከበደ?
30. መዓዛ፡(በመደራረብ) እኔ ደግሞ በጣም ነው የምወዳቸው፡፡ ሲያስተምሩ እኮ... በጣም ጎበዝ
31. ናቸው፡፡ እሳቸው!...
32. አዳነች፡ እህ
33. ማርቆስ፡ ለምን?
34. [ሶፍያ፡ (ጣልቃ በመግባት) ዶር. ከበደን እኔ በዝና ነው የማውቃቸው፡፡ አንዲ ልጅ መጣችና
35. ቢሯቸው ‹‹ምን ፈልገሽ ነው›› አሏት ‹‹ዶር. ከበደን ፈልጌ ነበር አለቻቸው ›› ‹‹የለሁም››
36. ‹‹መቼ ይመጣሉ ልጠብቃቸው››(ሳቅ) ስትላቸው በይ ግቢ ብለው አስተናገዷት ይባላል፡፡
37. ተረቴን መልሱ አፌን ቤዳቦ አብሱ(ሳቅ)፡፡

38. መዓዛ፡(ጣልቃ ገብነት) እንዴት መሰለሽ ልጅቷ ተማሪያቸው የነበረች አሁን ግን ጋዜጠኛ ነች፡፡
39. ቢሯቸው በር ላይ ቆማ አይተዋታል፡፡ ግን ረስተዋት ሌላ ስራ ሲሰሩ ቆዩና ቀና ሲሉ
40. ቆማለች፡፡ ‹‹ምን ፈልገሽ ነው›› አሏት፡፡ ‹‹ዶር ከበደን ፈልጌ ነበር›› ‹‹የለሁም›› መቼ
41. ይመጣሉ ልጠብቃቸው›› ስትላቸው በይ ግቢ ብለው አስተናገዷት፡፡ ሌላው አመላቸው ደግሞ
42. ደህና አደሩ ስትያቸው ምንአገባሽ፧ ያንች ጉዳይ ነው የእኔ ደህና ማደር
43. ሶፍያ፡ (ታልቃ ገብነት)እንዴት አደሩ ሲባሉ እንዴትስ ባድር ምን አገባሽ(ሳቅ) እንዴት አደሩ
44. ተብሎ ይጠየቃል ይሉሻል ሁሉም በመደራረብ ስለሚናገሩ መደማመጥ የለም
45. [ሶፍያ፡ (ጣልቃ በመግባት) እኔ ደስ የሚሉኝ ዶር ይመር...
46. [አዳነች፡ (ጣልቃ በመግባት) ዶር ይመር ፈኒ! በእውነት አንድ ቀን ሲያወሩ ሲያወሩ
47. ቆይተው እባካችሁ መልሱኝ ልጆች ይላሉ፡፡ ወይኔ ሲሞቱ እንዴት እንዳዘንኩ! በስማም፡፡ ከዛ
48. የህይወት ታሪካቸውን...
49. [ሶፍያ(ጣልቃ ገባች)፡ እሳቸው ሶደሬ ሄጀ አሉ፣ ውይ ሰው ውይ ሰው ልብስ እኮ
50. የማይሸፍነው ነገር የለም፡፡ ሰው ሁሉ ፎከቲያም አይደል እንዴ የተጫጫረ ገላ
51. [አዳነች፡ (ጣልቃ በመግባት(በመደራረብ)፡ ...ውያን አሉ ደግሞ፣ ...ውያን፣ ሴት
52. እኮ ማለት ...ውያን ነው አሉ አንድ ቀን ክላስ ውስጥ፡፡ አንድ ጊዜ ያኔ ወጣት ነኝ
53. እንደተቀጠርኩ ለስራ ጉዳይ ኤርትራ ተላኩኝ አሉ፡፡ ከዛ አንዲቱን ቆንጆ ያገኟት አሉ፡፡ በቃ
54. ስለሷ! አንድ ሰላሳ ደቂቃ ስለሴትዮዋ ዲስክርፕሽን፡፡ እና ዲስክርፕሽኑ ራሱ በቃ ሴትዮዋ
55. ፊትህ ሆና የምታያት ይመስልሃል፡፡ ሲያወሩ ሲያወሩ ቆዩና መጨረሻ ላይ ብር አይሰጥም
56. አሉ፡፡ ብር ለኤርትራውያን ብር እንኪ ዛሬ ያደርንበት ተብሎ አይሰጥም አሉ፡፡ ከትራስ ስር
57. ነው የምታስቀምጥ፡፡ እና እኔ በጣም ተደስቼአለሁ አለ፡፡ ልመጣ ስል ሁሉንም..
58. [ሶፍያ፡ (ጣልቃ በመግባት) በስመ አብ እያንዳንድሽ ሙልጭ አርገሽ ነው የበላሽው አይደል፡፡
59. አዳነች፡ አንዳንዶች አላቅማቸው አንስተው አልጨረስንም ይላሉ፡፡
60. አልማዝ፣ ውብነሽ እና ሳባ በግላቸው በሹክሹክታ ያወራሉ፡፡
61. ሶፍያ፡ አይ አዳነች እኔን ለመንካት ነው አይደል፡፡ ማያገጥ ጠፍቶብኝ ነው እንጂ፤ ማያያገጥ
62. ጠፍቶብኝ ነው ከምር፡፡
63. መደራረብ (መደማመጥ የለም)
64. ሶፍያ፡-አንዳንዶች ቃላችሁን ስጡ በእውነት፡፡
65. አልማዝ፡ (ጣልቃ በመግባት) እናመሰግናለን
66. [ሶፍያ፡- አቶ ዮናስ እንዴት ነው ፕሮግራሙን እንዴት አገኘሽው
67. አዳነች፡- የጎሪጥ ነው የማየው፡፡ እኔ እንደሆንኩ የጎሪጥ
68. ዮናስ፡ አሪፍ ነው፡፡ ፕሮግራሙ ከምግቡ ይበልጣል፡፡ ፕሮግራሙ ከምግቡ ይበልጣል፡፡ አሁን
69. ምንድን ነው የሚጠበቀው ያንን ያልጨረስነውን ምግብ ወደብር ተቀይሮ ቢሰጠን፡፡
70. ሶፍያ፡- እ
71. አዳነች፡ ሂሳቡ ይሰጠን ወይም ደግሞ ለራት እንድንመጣ ይዘጋጅልን
72. ሶፍያ፡ እሱን አስተያየት እቀበላለሁ፡፡ አቤም እሱ ነው አስተያየትሽ
73. አቦነሽ፡ እናመሰግናለን፡፡ በዚሁ ይቀጥል ነው የምንለው፡፡
74. አዳነች፡- የዛሬ ወርም እንደዚሁ
75. ሶፍያ፡ እንብላ
76. መዓዛ፡ ..ፍቅር እስከመቃብር እንዴት ተዛፈ ብለሽ
77. ሶፍያ፡ ተንትነሽ ሰርተሽ እንዳታመጭው
78. አዳነች፡- ከዛ በኋላ ደግሞ እኛ ኮሜንት ለማድረግ አታስቡ ችግር የለም
79. ሶፍያ፡-ሬዲ ነሽ
80. አዳነች፡ አዎ
81. ሶፍያ፡- ወ/ሪት መዓዛ እንግዲህ እንደ02 ዲፓርትመንት ሃላፊ
82. መዓዛ፡- ኖ አይ አም ኖት
83. ሶፍያ፡ 02 ዲፓራትመንት በምግብ ዙሪያ እንዴት ነው
84. አዳነች፡ ይሄ ምግብ እንዴት ተዘጋጀ ብለሽ ይዘሽ ነይ በሚቀጥለው

የመለያ ቁጥር ኢመ. 004

የእራት ግብዣ (ከስልጠና ማጠናቀቂ በኋላ)፡ የአኮ 004 ፋካሊቲ መምህራን (የአራት ትምህርት ክፍል መምህራንን ያካተተ)

1. ከፍያለው፡ እንግዲህ ያላችሁን ሃሳብ እያቀረባችው እንጨዋወት፣ተጫወቱ
2. ካሳ፡ እኔ ስለ ..... የምለው ነገር ባይኖርም እኔ በግሌ የት ላይ እንዳለሁ ራሴን
3. እንዳስቀምጥ ነው ያደረገኝ፡፡ የት ላይ ነው ያለሁት፡፡ ቃሎቹን አውቃቸዋለሁ አሁን
4. ግን አንድ ቦታ ላይ ሊውሉ እንዴት እንደሚችሉ ያስቻለን ትምህርት ነው፡፡ ግን ይሄ
5. ነገር ለወደፊትም ይቀጥላል ብሏል ዶር እሸቱ፡፡ ይህንን አደራ ነው የምለው፡፡ በጣም
6. ነው የምናመሰግነው፡፡ ይሄንን በማዘጋጀታችሁ፡፡ የሚያጓጓ ነገር ነው፡፡ ግማሺን
7. ተምሬ ግማሹን ቢሮ እገባለሁ እላለሁ፡፡ ግን እንደፊክሽን የሚጀመረው ነገር እንዲህ
8. ስለሚያሳሳ ያለነው እንዴት ብለን እንደተከታተልን አይታችኋል፡፡ በጣም
9. አመሰግናለሁ፡፡
10. ሊድያ፡ አመሰግናለሁ፡፡ እኔ ብዙ የምለው ነገር የለኝም፡፡ ምርምርን በተመለከተ
11. በተለይ ኪሊቴቲቭ የተለያዩ ስልጠናዎችን ወስጃለሁ፡፡ ግን እንደዚህ አዝናኝ በጣም
12. ደግሞ አለማወቃችንን በጣም እያሳላ የሄደ ኮንፊውዥን እየፈጠረ ብዙ እንድናነብ
13. ያደረገን ስልጠና ነው፡፡ የማደንቀው የመጀመሪያ ምናልባትም ኢትዮጵያዊ ነው ለእኔ
14. እንደዚህ አይነት ስልጠና ሲሰጥ፡፡ ምክንያቱም አፕሮቻችን ብዙ ጊዜ ኢትዮጵያውያን
15. ቲዌሪ ላይ ብቻ ነው፡፡ እዚህ ጋ ግን የእያንዳንዳችንን ልምድ በማውጣት እርስ
16. በርሳችን እንድንማማር .....ም ያለውን እውቀት በጣም ኤክስፕሎይት
17. ለማድረግ ጥረት እያደረግን...ለዛም ነው ወደፊት የገባልንን ቃል ከሆነ ጊዜ በኋላ
18. የቀሩትን እንዲጨርስልን እላለሁ፡፡ .....ን በጣም አመሰግናለሁ፡፡ በተጨማሪም
19. ደግሞ ለተሳታፊው ምክንያቱም እንዲህ አይነት ተሳትፎ ሲኖር እርስ በርሳችን
20. የመማማር ሁኔታ ከፍተኛ ነው የሚሆነው፡፡ ተሳታፊው ዝም ቢል ኖሮ ደባሪ ይሆን
21. ነበር፡፡ ያው በዘመኑ ቋንቋ፡፡ እና በጣም አመሰግናለሁ ለአስተባባሪውም ፡፡
22. ዳምጤ፡ ..... ከዚህ ውስጥ ያስተማርከው ተማሪ አለ፡፡
23. .....፡ ለምሳሌ እሱን አስተምሬያለሁ፣ እ ሌላ ማን አለ እሱን አስተምሬያለሁ፣
24. ሌሎቹም ታደለም አለ
25. ዳምጤ፡ እኬ እንግዲህ ያነሳሁት ሆን ብዬ ነው፡፤ እኔ አድቫንስ ነኝ ዲፕሎማ
26. አስተማሪ ነበርኩ፡፡ እና ያን ግዜ እሱ የመጀመሪያ ዲግሪውን ይዞ 1984/85 አካባቢ
27. ነው፡፡... ያሰራን ነበር፡፡ እና በጣም የሚገርመው ስለሱ ጥንካሬ ከፊቱ ባይሆንም
28. ዘወር ብዬ ልናገር፡፡ በሌለበት...
29. ዶ/ር ሲሳይ(ጣልቃ በመግባት)፡ ችግር የለም ሀቁን እስከሆነ ድረስ መናገር መቻል
30. አለብን፡፤ ፊት ለፊት መናገር መልመድ አለብን፡፡
31. ዳምጤ፡ የሚገርመው እንደገና 1993 እና 1994 ሲያስተምረን ኢነርጂው
32. አይሰለችም፣ አይደክመውም አሁንም ዛሬም አይደክመውም፡፡ እና ይሄ ኪሊቲ
33. በእውነት በርታ ተበራታ ነው የምለው፡፤ በተረፈ ደግሞ እኔ በጣም ደስ የሚለኝ ከሱ
34. የተማርነ ተማሪዎች ጥንቁቅ ነው፡፡ ነጥብ ያያል፡፡ ዛሬ አይታችሁ ከሆነ ነጥብ
35. እንዴት እንደምትቀመጥ አይታችሁታል አይደል? እና ያንን ባህሪ ወስጃለሁ፡፡ እና
36. እኔ ያን ሰሞን የፈራሁት ነገር ነበር፡፡ ብዙ ጊዜ እኛ ኢትዮጵያውን ለራሳችን ሰዎች
37. ዋጋ አንሰጥም፡፡ ይሄ መወገድ አለበት፡፡ ብዙ ሰዎች አሉ፡፤ ሌላ ሰው ሲሆን ነው
38. የተሻለ ይዞ የሚመጣ የሚመስል፡፡ ግን የእኛ ሰዎች ከሌሎች ያላነሱ እንደሆኑ፣
39. ከሌሎች የበለጡ እንደሆኑ አውቀን ብንጠቀምባቸው የምንፈልገውን ነገር ሊሰጡ
40. እንደሚችሉ በደንብ ያየነው ነው የሚመስለን፡፡ በሚቀጥለውም ሌላ ስልጠና አለ

41. ተብሏል፡፡ በደንብ እንደሚሰጠን ተስፋ እናደርጋለን፡፡ በጣም ለሀገራች እሴት
42. ነው ብየ ነው የምገልፀው፡፡ እንወድሃለን፡፡
43. ታዳለ፡ እኔ ቦታው ማለትም የስልጠና ክፍሉ አልተመቸኝም፡፡ እዛ ክፍል ተምሬበትም
44. ሆነ አስተምሬበት አላውቅም ለመጀመሪያ ጊዜ ነው፡፡ ስልጠናውን ማቆም የፈለኩት
45. ገና በመጀመሪያው ቀን ነበር፡፡ ግን ሁኔታው ስለተመቸን ጨረስኩት፡፡
46. ከፍያለው፡ መጀመሪያ ፕሮግራሙ ሲታሰብ 45 ስታፍ አለ ብለን ተነሳን፡፡ አሁን
47. የመጡ ሲቪክስ ላይ ሲደመር 50 ይደርሳል፡፡ ግን 5 ሊመጡም ላይመጡም ይችላሉ
48. ብለን 45 ነው የያዘው መጀመሪያም ሲነሳ፡፡ እነ ዶ/ር ሲሳይ ጋ ሂደን አልሞስት
49. ለዶ/ር እሸቱም ነግሬው ነበር፡፡ ግን ፕሮሰስ እንዳይበዛብኝ ብየ ነው ላማሳጠር እነ
50. ዶ/ር ሲሳይ ጋ የሄድነው፡፡ በጣም ነው የተባበረን፡፡ የእሱ ትብብር ባይኖር
51. ፕሮግራሙ ራሱ ላይካሄድ ይችል ነበር፡፡ እኔ ስጋት ነበረኝ፡፡ ምክንያቱም ከ.....
52. ጋር መጀመሪያ በ20 ነበር ፕሮግራም የያዝነው፡፡ እንደምታዩት በጣም ይጨናነቃል፡፡
53. አሁንም ልክ ስልጠናውን ጨርሶ ሲወጣ የሚይዘውን ስልክ ታዩታላችሁ፡፡ ለረጅም
54. ሰዓት ነው ስልክ የሚያወራው፡፡ ምክንያቱም ‹‹ሚስድ ኮል›› እየሆነ ብዙ
55. ስለሚቆየው ማለት ነው፡፡ ሀሙስ ነበር ፕሮግራሙ የተያዘው ወደአርብ ሲቀየር
56. እንቅልፍ አልተኛሁም ማለት ነው፡፡ ሀሙስ እለት ማታ ደምስ ጋር እያወራን ነበር፡፡
57. በቃ አንደኛ በደወልኩ ቁጥር እጨነቃለሁ እኔም አጨናነኩት ብየ ምንም ነገር
58. ማድረግ ስላልቻለ ነው እሱ፡፡ ልክ እዚያ እያለ አዲስ አበባ ደግሞ በአስቸኳይ ና
59. ተብሎ የተደወለለት ወደ አርብ የተቀየረው ፕሮግራም ማለት ነው፡፡ አርብ ደግሞ
60. ጧት ፕሌን ውስጥ ከገባ በኋላ ነው ፕሌኑ ውስጥ እንደዛ አይነት የቴክኒክ ብልሽት
61. ያጋጠመው፡፡ ዜን በጣም ሾክ አደርግ ነበር እኔ ከዶ/ር ሲሳይ ጋርም ሄደን ጧት ላይ
62. በጣም ነበር የተጨናነኩት እና ያ ሁላ አልፎ እዚህ ደረጃ ላይ በመደረሱ በግሌ
63. በጣም ተደስቻለሁ፡፡ ውድቅ አድርጌዋለሁ በራሴ፡፡ መጀመሪያውኑ ስሰራው በእኔ
64. አይደለም የሰራሁት፡፡ እና ያገኘነው ነገር በእውነት አደንቃለሁ በተለይ ከ.....
65. ሁለት ነገሮችን ተምሬያለሁ፡፡ የመጀመሪያው የትምህርት አሰጣጥ ዘዴው፡፡ ዘዴው
66. በራሱ ማለት ነው ትምህርት መስጠቱ ብቻ አይደለም፡፡ ሰው እኮ እውቀት ሊኖረው
67. ይችላል፤ ግን ማስተላለፍ መቻሉ የሚያስተምርበትን ዘዴ ማወቁ እሱ ትልቅ ነገር
68. ነው፡፡ የሚገርማችሁ እሚገረም ነበር ያሬድ፣ ታደለ፣ ከፍያለው፣ እምቢአለ... እያለ
69. ሲጠራ ማለት ነው፡፡ ተምሬያለሁ እኔ ኢዱኬሽን ነው የተማርኩት ስም መጥራት
70. ምን ያህል የመማር ፍላጎትን እንደሚጨምር ማለት ነው፡፡ አንድን ተማሪ ሶስት
71. አመት ያስተማርኩትን ተማሪ መጨረሻ ላይ ስሙን ብትጠይቁኝ አላውቅም፡፡
72. ልምድን ነው የማላውቀው...
73. ዶር እሸቱ፡ እንግዲህ ቀልዱ ሊያመልጠኝ ነው፡፡ ሌላ ቦታ ደግሞ ስለሚሄድ ነው፡፡
74. ደህና እደሩ፡፡
75. በለጠ፡ ግን አደራ የፍስክ ነው፡፡ የፍስክ የምትሉ ከሆነ ልናገር (ተጨበጨበ) በጣም
76. ጥሩ፡፡ በገጠር የሆነች ሻሂ ቤት ምናምን ታውቃላችሁ ኮማሪ የሚባሉት፡፡ እና የሆነች
77. ኮማሪ ናት እና ቆንጆ ናት የሆነ ገበሬ ያያትና ማደር እየፈለገ እየፈለገ አንድ ቀን
78. ይሳካለትና ያድራል ከሷ ጋራ አብሮ፡፡ ከዛ ሚስቱን እያሰበ ነው መሰለኝ ማታ ሊገናኝ
79. ቢል፣ ቢል፣ቢል ምንም ነገር የለም፡፡ አሁን በነጋው ቀስ ብሎ ሹልክ ብሎ ሄደ
80. ቤቱን፡፡ በሌላ ቀን እንግዲህ መንገዱ ያቺ ናት፡፡ ከዛ በበሯ ሲመጣ ከሷ ሲደርስ
81. ክንብንብ ብሎ ይሄዳል፡፡ ‹‹አንተ ሰውዬ፣ ሰውዬ›› አለችው፡፡ ድንግጥ ብሎ ‹‹አቤት››
82. አለ፡፡ እሷም ‹‹የዛ ሰውዬ ለቅሶ መቼ ነዋ?›› አለችው፡፡ ‹‹አይ እናቴ አንቺማ በቀብሩ
83. ደርሰሻል›› አላት ይባላል (ሳቅ)፡፡
84. ከፍያለው፡ ..... ደግሞ ሞክር
85. .....፡ እኔ ምንም ቀልድ የለኝም፡፡ አሁን ይለፈኝና በሚቀጥለው ስመጣ
86. ተዘጋጅቼ ልምጣ
87. ሊዲያ፡ ገጠመኝህንም ሊሆን ይችላል ስታስተምር

88. .....፡ እሽ ግን መጨረሻው ላይ እንደወረደ ነው ማወራችሁ፡፡
89. ተሳታፊ በህብረት፡ ጥሩ ችግር የለም አውራን
90. .....፡ አስተማሪዎች አስተምረው ክክፍል ሲወጡ ተማሪ ከፍል ውስጥ
91. የማይፅፈው ነገር የለም፤ ብላክ ቦርድ ላይ፡፡ እና ሲፅፉ አንድ ተማሪ ብላክ
92. ቦርዱ ላይ ‹‹...›› ብሎ ይፅፋል፡፡
93. አንዳንድ ተሳታፊ በህብረት፡ (በመደራረብ)ይሄማ ነውር ነው፡፡
94. .....፡ እንደወረደ ነው ብያችኋለሁ፣ እንደወረደ ነው ብያችኋለሁ
95. ተሳታፊ፡ አሽ እሽ
96. .....፡ ከዛ በኋላ የሚመጣው መምህር በጣም ይቆጣል፡፡ ሴት ናት
97. ባጋጣሚ፡፡ እና ሆን ብሎ እሷን እንትን ብለው ሊያናድዷት ነው የፃፉትና፡፡
98. ይሄን ማን ነው የፃፈው ትላለች፤ ትቆጣለች፡፤ የሚያጋልጥ ጠፋ፡፡ መጨረሻ
99. ላይ አንድ በአንድ፣ አንድ በአንድ እየጠየቀች የፃፈው ልጅ ተነሳ፡፡ አንተ ቆሻሻ
100. የፃፍካትን በምላስህ ላስ ትለዋለች፡፡ ብላክ ቦርዱን እንትን ሲያደርግ በሙሉ
101. ቾክ በቾክ ይሆናል፡፡ አልበቃ ይላትና ትናደድና አንተ ሂድና አባትህን
102. በአስቸኳይ ጥራ ትለዋለች፡፡ ከዛ ይሄዳል፡፡ አባትየው ጋር ይሄድና አባትው
103. ሲያየው አመድ በአመድ ሆኗል፡፡ ‹‹ምን ሆነህ ነው አንተ?›› ‹‹ አንተን ጥራ
104. ተብየ›› ‹‹ ለምን›› ‹‹አይ እትዬ ጥራው ብላ›› ‹‹ ደሞ አመድ በአመድ
105. የሆንከው ምን ሆነህ ነው?›› ‹‹ብላክ ቦርዱን አስልሳኝ እትዬ›› ‹‹እትዬ
106. አስልሳኝ? ምንድን ነው ያስላሰችህ?›› ‹‹አይ ‹‹...›› አስልሳኝ›› ‹‹ እኔ
107. እስከዛሬ ድረስ ብዙ ... አይቻለሁ እንደዚህ አመዳም ... አይቼ
108. አላውቅም፡፡›› (ከፍተኛ ጊዜ የወሰደ ሳቅ)
(አስናቀች፣ መሲ እናሊድያ በሹክሹክታ ያወራሉ)
109. አስናቀች፡ መሲ አንቺ አታወሪም እንዴ? ቀልድ የለሽም አንድ ነገር አውሪ
110. እንጂ
111. መሲ፡ አንድ ቀልድ አለኝ፡፡ ምን መሰለሽ አንዷ የመንግስት ሰራተኛ
112. ጭንቅላቷን በተደጋጋሞ ያማታል፡፡ ሀኪም ቤት ብትመላለስ አልሻል
113. ይላታል፡፡ በኋላ ቤተሰቦቿ ወደፀበል መሄድ አለብሽ ብለው ወሰዷት፡፡ ፀበሉን
114. ስትጠመቅ ሀይለኛ ጩኸት ጮኸች፡፡ ቄሶቹም መስቀላቸውን ይዘው
115. እያጠመቋት ምንድን ነህ ብለው ሲጠይቁ ‹‹እኔ ቡዳ ነኝ ቡዳ ነኝ›› አለ ‹‹ የት
116. አገኘሃት?›› ሲሉት ‹‹ ቢሮዋ ቢሮዋ ነዋ›› ‹‹ አንተ ማነህ ታዲያ›› ‹‹እኔማ
117. ቢፒ አር ነኝ›› አለች ይባላል፡፡
118. አስናቀች፡ በጣም አሪፍ ነው በናትሽ አውሪ
119. መሲ፡ እፈራላሁ፡፡ ያስፈራል እኮ፡፡ በእደዚህ አይነት ቦታ አውርቼ አላውቅም
120. ተይው ይቅርብኝ፡፡
121. በለጠ፡ ሌላ አንድ ነገር የረሳነው ነገር አለ፡፡ አሁን ነው የታየኝ ከፋካሊቲያችን
122. ውጭ የተሳተፈች አለች፡፡ አስናቀች ከእኛ ውጭ መጥታ ከመጀመሪያው እስከ
123. መጨረሻ የተሳተፈች፡፡ ሀሳብ ትስጥ፡፡ ሀሳብ ብትሰጥ ደስ ይለኛል፡፡
124. አስናቀች፡ እኔ የመጀመሪያውን ክፍለ ጊዜ እንደተሳተፍኩ አይደለም መቅረት
125. ማርፈድም አልፈልግም፡፡ በጣም የሚገርማችሁ አንዱን ጓደኞችንን አገኘነውና
126. ለምን አልገባህም ስንለው ‹‹ ፈረንጅ አይደለም አበሻ ነው አሉ›› አለ፡፡ እናም
127. ያሳዝናል፡፡ ስለዚህ የራሳችንን ሰው መቀበል፣ ማድነቅ በራሳችን መኩራት
128. ይገባናል፡፡ ..... ደግሞ ከራሳችንም በላይ የራሳችን ነው፡፡ ባህር ዳር
129. ዩኒቨርሲቲ ዘርታ፣ አብቅላ፣ ያፈራችው ..... ነው፡፡(ጭብጨባ)፡፡ እና
130. ስለማውቀው ነው አብረን ተምረናል ድሮ ማለት ነው፡፡
131. እና እዚሁ ተዘርቶ እዚሁ በቅሎ እዚሁ አብቦ እዚሁ
132. ያፈራ ..... ነው፡፡ አመሰግናለሁ፡፡(ከፍተኛ ጭብጨባ)
133. ከፍያለው፡ ሞገስ ቀልድና እንጨርስ

134. ካሳ፡ አንድ ጥያቄ አለኝ ለዶ/ር ሲሳይ። ዶ/ር
135. ዶ/ር ሲሳይ፡ አቤት
136. ካሳ፡ 06 ዲፓርትመንት ነህ አይደል?
137. ዶ/ር ሲሳይ፡ አዎ
138. ካሳ፡ አንድ መምህር 5ኛ ክፍል ላይ ሲያስተምር ህይወት ያላቸው ነገሮች
139. ያስተምራል። እና ህይወት ያላቸው ነገሮች ያድጋሉ፣ ይራባሉ፣ እለ
140. ይደረድራል። ከዛ አንድ አስተዋይ ተማሪ ጋሼ ይላል። ዛፎች ሲቆረጡ
141. ያድጋሉ ግን እንስሳ እጹ ወይም እግሩ ሲቆረጥ ለምንድን ነው የማያድገው
142. ብሎ ይጠይቀዋል። አንተ ብትሆን ምን ታደርጋለህ?
143. ዶ/ር ሲሳይ፡ ነገሩ አላውቀውም ግን የማውቀው ነገር አለ።
144. ካሳ፡ ቆይ መልሱን አያውቀውም መምህሩ። ና ውጣ ይላል መምህሩ።
145. ተንበርከክ አንተ የዛች ልጅ ተቆርጠህ ልታድግ አማረህ? አገላብጦ፣ አገላብጦ
146. ገረፈው። ያ ተማሪ ለወደፊት ምንም አይነት ጥያቄ አያነሳም።
147. ያሬድ፡ እኔ አንዳንዴ እንደ ገጣሚ ያደርገኛል። እናም አሁን ህሳቤን እንዴት
148. ልግለጽ አልኩና እዚሁ አሁን አንዲት ግጥም እኔኑ ከገለፀች ብየ
149. ቦጫጨርኳት። እና አዳምጡኝ። ርዕሱን ‹‹የልቤን እንጂ የአፌን አትይ››
150. ብየዋለሁ። አዳምጡኝ አፌ አይዘጋም አንዴ ከከፈትኩት ዝም ብዬ እተፋለሁ
151. ገደብ አላውቅለት አቤት! ሲስቁልኝማ እንዴት ደስ ይለኛል።
152. ከአፍ እስከ ገደብ ሀሴት ይሰማኛል። እይልኝ የልቤን በአፌ ባወራም
153. ክፉ አላስብም ተንኮልም አልሰራም።(ጭብጨባ)
154. ሞገስ፡ የኔን ቀልድ ላቅርብላችሁ አዳምጡ።
155. ተሳታፊው፡ (በአንድነት) እሽ ቀጥል
156. ሞገስ፡ አንድ ሌባ እስር ቤት የረገባና ሶስት አመት ይታሰራል። ጓደኞቹ ስለጥፋቱ
157. አያውቁም። እና ከእስር ቤት ሲወጣ ምንድን ነው ጥፋትህ ይሉታል። ገመድ ሰርቄ
158. ነው የታሰርኩት ይላቸዋል። እንዴ በገመድ ይዜን ያህል አመት እንዴት
159. ትታሰራለህ? ይሉታል። እሱም በእርግጥ ከገመዱ በኋላ በግ አለ አላቸው ይባላል።

የቡድን ተኮር ቃለመጠይቅ ምላሽ

የመለያ ቁጥር፡- ቡተቃ 201

ሰዓት፡ 9፡00 — 11፡10
ቦታ፡- C-28
ቀን፡-21/01/2005

በስብሰባ ወቅት ከመናገራችሁ በፊት ምን ምን ታደርጋላችሁ?

1. አገሬ፡- በስብሰባ ወቅት ከመናገሬ በፊት እኔ የማደርገው ነገር አንደኛ ሃሳቡን ለመረዳት
2. እሞክራለሁ አወያዩ በሚናገርበት ጊዜ ከዛ በኋላ ጠቃሚ ነገር ናቸው የምላቸውን
3. ነገሮች ካሉ እንዳረሳ ማንሳትም ያለብኝ ጥያቄ ካለ በጉዳዩ ላይ የእኔ አስተያየት ምን
4. እንደሆነ አጫጭር ማስታወሻዎችን በያዝኩት በወረቀት ላይ እፅፋለሁ፡፡ የማደርገውን
5. ዝግጅት ያው የስብሰባውን መንፈስ መረዳትና እኔ መናገር አለብኝ ብየ የማስባቸውን
6. ነጥቦች በወረቀት ላይ ማስፈር እወዳለሁ፡፡ አንዳንዴ በአእምሮየም ብቻ የማስቀምጥበት
7. ጊዜ አለ፡፡
8. መሰረት፡- ያው በመጀመሪያ እሷ እንዳለችው ማለት ይቻላል አይቻልም አላውቅም፡፡
9. የስብሰባውን አጀንዳ ለመረዳት ነው የምሞክረው፡፡ ዋጋ የሚሰጠው ከመድረክ ላይ
10. ወይም ደግሞ የተነሱሃሳቦችን በዛ ዙሪያ ያሉ ችግሮች ካሉ ማሰብ እጀምራለሁ፡፡ በዛ
11. ዙሪያ ማንሳት የሚገባኝ ነጥብ ካለ ማስታወሻ በመያዝ እዘጋጃለሁ፡፡
12. ሳባ፡- መሰ እንዳለችው እኔም ከእነሱ የተነገረውን ካዳመጥኩኝ በኋላ ማስታወሻ በመያዝ
13. ከርእሰ ጉዳዩ እንዳልወጣ አስተያየቴን ነጥብ በነጥብ እሰጣለሁ፡፡
14. ከበደ፡- እነሱ ያሉት ነው ግን ከእነሱ ለየት የምለው ምናልባት አጀንዳው ቀድሞ
15. የሚታወቅ ከሆነ፤ ሁለተኛ በስብሰባው ላይ እነዛ ሃሳቦች ካልተነሱ መድገም ግድ
16. አይደለም፡፡ ሃሳብ ለመረዳት፣ ለመከታተል፣ ለማድመጥ እሞክራለሁ፡፡
17. ካሳ፡- መጀመሪያ አዳምጣለሁ፡፡ የተናገሩት ነገር ካለ አሱን አድምጬ ሪአክት
18. አደርጋለሁ፡፡
19. በእውቀቱ፡- የተለየ ነገር የለም፡፡ በመጀመሪያ አጀንዳው ነው የምረዳው፡፡ የምናገረው ነገር
20. ካለ ደግሞ ከመናገሬ በፊት((xxx))
21. አለሙ፡- ከበእውቀቱ ጋር የምጋራው ነገር ያለ ይመስለኛል፡፡ ከተሰብሳቢዎቹ... ከነማን
22. ጋር ነው ያለሁት? እኩዮቼ ናቸው? ከያታም ጋርም የማላውቃቸው ከሆኑ ሪዘርቬሽን
23. አሳያለሁ፡፡ ሃይማኖታቸውም ነፃ ሆኜ መወያየት አልችልም ለጥንቃቄ ስል፡፡ ከመናገርህ
24. በፊት ምን ታደርጋለህ የሚለው፤ እንደየስብሰባው አይነትና እንደተሰብሳቢዎቹ
25. እንደአጀንዳው ሁኔታ፤ አጀንዳው ምንያህል ስሬየስ ነው? ብናገር ባልናገር አስፈላጊ ነው
26. ወይ የሚለውንም ከግንዛቤ በማስገባት ይሆናል፡፡

ያታ ስትል ከየትኛው ያታ ጋር ስትሆን ነው ከመናገር የምትቆጠበው?

27. አለሙ፡- እኔማ ያው ወንድ ነኝ፡፡ ከወንዶቹ ጋር ችግር የለብኝም ሴቶቹ ጋር ግን በጣም
28. የማላውቃቸው ከሆኑ ትንሽ ነፃ ያለመሆን ችግር አለ፡፡ በአጠቃላይ አለመተዋወቅ
29. በመግባባት ላይ ያው ተፅዕኖ አለው አይደል፡፡ ግን ደግሞ ሪዘርቭድ እሆናለሁ
30. እስከማውቃቸው ድረስ፤ ተማሪዎቼም ላይ ቢሆን ለመጀመሪያ ጊዜ ነፃ አልሆንም፡፡
31. በኋላ እሰማውቃቸው ድረስ፡፡ ባህላችን ይመስለኛል፡፡ ያው አስተዳደጋችን ገጠር አደግ
32. ነኝ፡፡ ...የዛ የዛ ተፅዕኖ ይመስለኛል፡፡

33. ለመናገር ስትፈልጉ ሌሎች የመናገር እድል እንዲሰጧችሁ ምን ታደርጋላችሁ?
34. አለሙ፡- አንድ ጊዜ አቶ ሰይፉ መታፈሪያ በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ ቆዩና ጨርሰው
35. ሌላ ርዕስ ሊጀምሩ እያሉ ነው ያሉና እንደጨረሱ እጄን ሳወጣ ተያየን፡፡ አዩኝና
36. ፊታቸውን ዙረው ሰሌዳውን ያጠፉሉ፡፡ እና ፊታቸውን እንደዞሩ እእእ አልኩ፡፡ ከዛ
37. እሳቸውም ፊታቸውን እንደዞሩ ‹‹አለሙ ድምፅ አሰማህ አሉኝ፡፡›› ስለዚህ ያ ስትራቴጂ
38. የሆነ እንደዚህ እንደዚህ አይነት ነገር እጠቀማለሁ፡፡ በጣም አስፈላጊ ነው ብየ ካሰብኩ
39. መናገሬ፣ እድል እንኳ ባይሰጠኝ ይቅርታ ብየ እገባለሁ፡፡ ብዙ ጊዜ ግን ጣልቃ የመግባት
40. እንትን አሳያለሁ እኔ መናገር ካለብኝ፡፡ በተለይ((xxx))
41. መሰረት፡- እኔ እንደ ተሰብሳቢው ይወሰናል፡፡ ከሁለትአመት በፊት በነበረ
42. ከዳር እስከዳር አዳራሹ ውስጥ ያለ ስው ሁሉ ነበር የሚያወጣው፡፡ መተውን ነው
43. የምመርጠው በጣም ብዙ ሰው የሚያወጣበት ሰዓት፡፡ ውስን በሆነበት ሁኔታ ግን ያው
44. እንደማንኛውም እጅሽን ታወጫለሽ፤ ጋሽ አለሙ እንዳለው ደግሞ እድል ከተነፈገኝ፡
45. ዲፓርትመንት አካባቢ የሚደረጉ ስብሰባዎች ብዙ ሰዎች አይተናታል ይሉና እኔ
46. እንዲያውም የእኔ ባህርይ በጣም ዝምተኛ ነገር ነው፡፡ በክፍተት የመግባት አይነት
47. ነገር ነው እንጂ ቀድሜ እንደሰው እጅ አውጥቼ ምናምን አልናገርም፡፡ ጋሽ ከበደ
48. እንዳለው በማስታወሻ ይጥቸው ያልተነገሩልኝ ላይ ነው ትኩረት የምሰጠው፡፡
49. አጀንዳው ሊዘጋ እንኳ ቢሞከር በተለይ ተሰብሳቢው ትንሽ ከሆነ ልክ እንዲፓርትመንት
50. ቁጥር የምፈልገው ነገር ካለ አዚህ ጋ ብየ እናገራለሁ፡፡ እናም በአጠቃላይ እንደኦዬንሱ
51. ብዛት ይወሰናል፡፡
52. በእውቀቱ፡- እኔ እንደ አጀንዳውና የእኔ የማቀርበው ሀሳብ፤ አጀንዳው ለእኔ በጣም
53. ጠቃሚና የማቀርበው ሀሳብ ስትሮንግ ከሆነ ኢንተርፊር አደርጋለሁ ቅድም ጋሽ አለሙ
54. እንደተናገረው፡፡ ግን እንዳንዴ ምናልባት ተናጋሪ ከመሆን በአንዳንድ ምክንያት እድሉ
55. ላይሰጥሽ ይችላል፡፡ የዛን ጊዜ እኔ እንዲያውም መድረክ ረግጬ የምወጣበት አጋጣሚ
56. አለ፡፡ ትዝ ይለኛል አንዴ ቸርፐርሰኑ ፕርፐዝሊ ነው እጄን ሳወጣ አያየኝም፡፡ አስተያየት
57. ማቅረብ አልቻልኩም፡፡ ዜን ምንድን ነው ያደረኩት ስወጣ ተቀመጥ አለኝ፣ እድል
58. ስጠኝ አልኩት፣ በዛን ሰኣት እድል ተሰጥቶኝ የተናገርኩበት አጋታሚ አለ፡፡
59. ሳባ፡- የተለየ ነገር የለም፣ ምናልባት መናገር አለብኝ ብየ ካመንኩኝ፣ ወይም አልተነገረም
60. ብየ ካሰብኩኝ ያው እነሱ እንዳሉት እድል ይሰጠኝ ብየ እጠይቃለሁ፡፡
61. አገሬ፡- እኔ እድል እንዲሰጠኝ እጅ ነው የማወጣው መጀመሪያ፡፡ ያለበለዚያ
62. እንደመቁነጥነጥ ነገር አይነት ነገር ያደርገኛል፡፡
63. ውብነሽ፡- መሰረት ካለችው ጋር እስማማለሁ፡፡ እንደ ሁኔታው በጣም ብዙ ሰው ባለበት
64. እንደተባለው ልል የምፈልገው ነገር ተነግሮ ከሆነ ምንም አልልም፡፡ ነገር ግን መናገር
65. ያለብኝ ነገር ካለ እጄን ነው የማወጣው፣ተነፍጎኝም አያውቅ፡፡ ብነፈግ እንደተባለው
66. ምጠይቅ ይመስለኛል፡፡ ትልልቅ ስብሰባ ላይ እጅ አውጥተሽ የማትታይባቸው
67. አጋጣሚዎች አሉ፡፡ በተሌዩ ምክንያቶች፡፡ ያጋጠመኝም ነገር አለ፡፡ እኛ ጋ አንድ ጊዜ
68. በነበረው ስብስባ ላይ እጄን አንስቼ አልታየሁም፡፡ እና መሪዎቹ አላየኝ ብለው ተስፋ
69. ቆርጬ እጄን መልሻለሁ፡፡ ድምፅም ብታሰሚ አይሰማም ሩቅ ነበር፡፡ ተስፋ
70. ትቆርጫለሽ፡፡ ለምን እንደማያዩ ምናልባት አይናቸውን ፊት ለፊት ብቻ ስለሚያዩ ዳር
71. ለዳር ላያዩ ይችላሉ፡፡ እኔ ደግሞ አጋጣሚ ሆኖ በዳር በኩል ነበርኩ፡፡ እና አንዳንዴ
72. እድሉ ይነፈግሻል፡፡

የተነፈገሽን እድል ለማግኘት ሌላ ምንም አታደርጊም?

73. ውብነሽ፡- መድረኩ በጣም ሩቅ ከሆነ ምንም አማራጭ የለሽም እጄን አ
74. ጥፌ እቀመጣለሁ፡፡ ያደረኩትም ይሄን ነው፡፤ ወጥቼ ግን ምናልባት የምቀርባቸው
75. ሰዎች ከሆኑ፡ ቅሬታየን እነግራቸዋለሁ፡፡
76. ከበደ፡- መናገር ካለብኝ እጄን ሳላወጣ የግድ እጅ ማውጣት አይመስልኝም ዝም ብየ
77. እገባለሁ ጣልቃ፡ በዛ መልክ እንትን አደርጋለሁ፡፡ ነገር ግን ሰፊ ስብሰባ ላይ ብዙ ጊዜ
78. አልናገርም፡፡ አንደኛ ፊትም የመቀመጥ ባህርይ የለኝም፡፡ ወይ መሀል ላይ ነው

79. የምቀመጠው፡፡ ፊትም ብሄድ እጂን አውጥቼ የምናገርባቸው አጋጣሚዎች በጣም
80. የተወሰኑ ናቸው፡፡ ምናልባት መረጃ ሲዛባ ሳይ ወይ ቀጥታ የሚመለከተኝ ነገር ሲሆን
81. ካልሆነ በስተቀር ብዙ ጊዜ እጂን አውጥቼ የመናገር እንት የለኝም፡፤ ብዙዎች
82. ይናገራሉ፡፡ ብዙዎች ስለሚናገሩ በዚ ጊዜ አድማጭ ነው የምሆነው፡፡ ነገር ግን በግለጽ
83. መነገር ያለበት ጉዳይ ካለና መረጃ ሲዛባ ካየሁኝ እጂን አወጣለሁ ከተሰጠኝ
84. እናገራለሁ፡፡ ካልተሰጠኝ አንዳንዴ እዚህ ጋ እዚህ ጋ ብየ ሁሉ ድምፅም የማሰማበት
85. ሁኔታ አለኝ፡፡ ከዛ ውጭ ግን የወጣሁበት አጋጣሚ አላስታውስም፡፡
86. ካሳ፡- እኔም አዲስ ነገር የለም፡፡ ሲጀመር መድረክ የሚመራ ሰው ነው እድል የሚሰጠው
87. ወይም እድል የሚነፍገውም፤ በእርግጥ በአይን መታየትን እፈልጋለሁ፡፡ መናገር
88. ካለብኝ ሳልናገር አልወጣም፡፡ ልናገር ስፈልግ ሌሎች ሰዎች ያነሱት ይሆናል ምናምን
89. ብየ ዝም አልልም፡፡ ሀሳብ ካለኝ መግለፅ እፈልጋለሁ ወደኋላ አልልም፡፡ እጂን
90. በማንሳት ሊሆን ይችላል ወይ ደግሞ በሰውነት እንቅስቃሴ መናገር ስፈልግ ሳልናገር
91. ቀርቼ አላውቅም፡፡
92. ሀሳባችሁን ሳትጨርሱ ወይም ሳትናገሩ ከስብሰባ ወጥታችሁ ታውቃላችሁ?
93. ሀብቱ፡- በትልልቅ ስብሰባ እኔ ብዙ ጊዜ አልናገርም፡፡ ቅድም ጋሼ ከበደ እንዳለው ነው
94. ሪዘርቭ ነው የምሆነው፡፡ ግን በዲፓርትመንትና ኮሚሽን ከሆነ ግን ሃሳቤን ሳልጨርስ
95. ወይም ሳልናገር የወጣሁበት ጊዜ የለም፡፡
96. ሳባ፡- እሱ እንዳለው ያው ብዙ አልናገርም ብዙ ጊዜ አድማጭ ነው የምሆነው፡፡ ግን
97. ሃሳቤን ጀምሬ አቋርጬ የወጣሁበት ሁኔታ የለም፡፡ ግን መናገር ፈልጌ ሳልናገር
98. የምወጣበት ሁኔታ አለ፡፡ የሰብሳቢዎቹን መንፈስ ነው የማጠና፤ ሰብሳቢዎች
99. የማይፈልጉት ነገር ካለ በሌሎች ሰዎች የሚያደርጉትን..አይቀበሉም፡፡ እና ያንን ካየሁኝ
100. ብናገርም እኔንም የማይቀበሉኝ ስለሚመስሉኝ ዝም ብየ ነው የምወጣው፡፡
101. አገሬ፡- ሀሳቤን ሳልጨርስ የወጣሁበት ጊዜ አለ፣ ሳልናገርም የወጣሁበትም ጊዜ አለ፡፡
102. በተለያዩ ምክንያቶች ማለት ነው፡፡ሀሳቤን ሳልጨርስ ወጥቼ የማቅበት ምክንያት
103. በትናንሽ ስብሰባዎች ላይ ነው፡፡ ቅድም እንደተጠየቀው እድል ለማግኘት የሚፈልጉ
104. ሰዎች ያቋርጡሻል ሃሳብሽን እየተናገርሽ፡፡ እና ሌላ ክርክር ውስጥ ይገባና ለማስጨበጥ
105. የምፈልገውን ነገር ሳላስጨብጥ ወደሌላ አቅጣጫ ሄዶ ስብሰባው የሚያልቅበት ሁኔታ
106. ይፈጠራል፡፡ ሳልናገር የምወጣው ጓደኞቼ እንዳሉት ትላልቅ ስብሰባ ላይ አንዳንዴ
107. በጣም ሀሳብ የለሽ ሆኜ ማለት ነው፡፡ ትዝ ይለኛል አንዴ አስተዳደር የሆነ በትምህርት
108. ጉዳይ ላይ ይመስለኛል የሆነ ውይይት ተደርጎ ነበርና ሰዎቹ የሚያወሩት ..... ቋንቋ
109. ነው ግን ምንም ሊገባኝ አልቻለም እና እንዴት ነው .....ም የማይገባበት ጊዜም
110. መጣ ወይ ብየ አውቃለሁ እንኳን ሀሳብ ልናገር፤የሚነገረው ነገር አንዳንዴ ካልገባኝ
111. ሃሳብ ሳልሰጥ እወጣለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ለመናገር ፈልጌ ፈርቼም ሳልናገር
112. የወጣሁበት ጊዜ አለ፡፡

ለምን?

113. አገሬ፡- ድምፄ እየተንቀጠቀጠ እጄ እየተንቀጠቀጠ መናገር አልፈልግም፡፤ በኮንፊደንት
114. ነውና፡፡ እሱ ነገር ውስጤ ካልሞላና ሀሳቤን በድፍረት መግለፅ አልችልም ብየ ካሰብኩ
115. እንትን አደርጋለሁ፡፡ ግን እድናገር የሚጎተጉተኝ ነገር አለ ውሰጤ፡፡

ሲያቋርጥሽ አንቺ ሀሳብሽን ለመጨረስ ምን ታደርጊያለሽ?

116. አገሬ፡- ተሰብሳቢዎች አንዳንዶቹ ዶሚኔት ማድረግ የሚቀናቸው ሰዎች አሉና ያንንም
117. በመናገር ለማሳየት ለሚፈልጉ ሰዎች በጣም እድል በመስጠት አምናለሁ፡፡ ነገሩን
118. ታቂዋለሽ እውነቱን ታቂዋለሽ ግን በጨዋነት በምናምን እንትን ሊሉሽ ሊጫኑሽ
119. ይፈልጋሉ፡፡ ስለዚህ ካለ በደንብ እንዲጨሀ እድሉን እሰጠዋለሁ፡፡
120. ውብነሽ፡- እኔ በተለይ በትልልቅ ስብሰባዎች ላይ ምንም አልናገርም፡፡ እንዳልኩሽ እጂን
121. አውጥቼ ጠይቁ እንኳን እድል አላገኘሁም፡፡
122. ለምን?
123. ውብነሽ፡- ብዙ ጊዜ ሃሳብ አጥቼ አይመስለኝም ራሴን ስገመግም፤ ሃሳብ ይኖረኛል ግን

ፍርሃት በጣም እፈራለሁ። ትልልቅ የማላውቃቸው ሰዎች በጣም ትልልቅ ቅድም ጋሽ
አለሙ ያለው ኦዲየንሱን ከፈራሁት መናገር አልችልም። ስለዚህ ሀሳቤን ይገፐው
እወጣለሁ። እንዳንዴ ሀሳቤ በሌሎች ሰዎች ሊነገር ይችላል። እንዳንዴ የእኔ ሀሳብ
ሳይነገር የሚወጣበት ጊዜ ሁሉ አለ። ለምሳሌ ሰሞኑን በነበረው ስብሰባ ላይ እኔ
ይገፐው የነበረ ሀሳብ ነበር። ውስጤን በጣም እንድናገር ሲገፋፋኝ የነበረው ሀሳብ
አልተነገረም። እንዲህ አይነት ነገሮች አሉ። ፍርሃት ነው እንግዲህ። በትንንሽ
ስብሰባዎች እኔ መናገር ካለብኝና ጉዳዩ እኔን የሚመለከት ከሆነ እኔ ካልተናገርኩ ጥሩ
ሀሳቡ እንትን ሆነ የሚል ደረጃ የሚል ከሆነ እናገራለሁ። ባልናገርም ችግር ከሌለም
ሀሳቡ ጠፍቶ አይደለም። ባህሪየ ሆኖ ይሆን አላውቅም ዝምታን አበዛለሁ።
ካሳ፡- መጀመሪያ አካባቢ እፈራለሁ። ስብሰባም ብዙ ባልተሰበሰብኩበት ጊዜ ማለቴ ነው።
አልናገርም ሃሳብም እያለኝ ዝም እላለሁ። ወይም ደግሞ ብናገርም ረብ ያለው ሃሳብ
የምናግር አይመስለኝም። እና ዝም እላለሁ። አሁን ግን እኔ እናገራለሁ። ስናገር ቅድም
እንዳሉት አዲየሱን ምናምን አይቼ ሁሉ ላይሆን ይችላል። ብናገር ይከፈዋል
ይመነዝረዋል ምናምን ይለዋል አልልም እናገራለሁ። ሆዴን እየበላኝ መውጣት
አልፈልግም። እና መናገር ለብኝን ነገር በአግባቡ እናገራለሁ። ምናልባት ይሄ
የሚመስለኝ እኔ ያደኩበት አካባቢ ሰዎች ምእራብ ሀረርጌ ምስራቅ አርሲ ኦልሞስት
አንድ አይነት ባህርይ ነው ያለው እና ሰዎች እዛው ተነጋግረው ተደባድበው ወዲያው
የሚታረቁበት፣ እንደፈለጉ ተነጋግረው የማይኮራረፉበት ቦታ ነው ያደኩትና በእርግጥ
እንደሰው ብናገረው ረብ ያለው ነገርነው፣ አደገኛ ነው እል ነበር ለተወሰነ ጊዜ አሁን ግን
ብዙ ያለ አይመስለኝም። ባልገደበኝ ሁኔታ ግን እናገራለሁ። ያሰብኩትን ነገር ሳልናገር
ወጥቼ አላውቅም።
አለሙ፡- የማልናገርበት ሁኔታም አለ። ለምሳሌ አንድ ጊዜ ዶር ባይሌ ከክልል ባለሙያ
ላኩልን ተብሎ የሆነ ጥናት ይቀርብ ነበር ሁለት ሰዎች ሄድን። የቅማንት ብሄረሰብ
ቋንቋውን ምን ያህል የሚናገር ሰው አለ ተብሎ ኮሚቴ ተቋቁሞ በዛ መሰረት ጥናት
ያቀረቡ ሰዎች ነበሩ። ያንንን ጥናት ሲያቀርቡ ጥቂውን ያቀረቡት ሰዎች ቁጥር ይበዛል
እዛ አዲስ አበባ ላይ። በመጀመሪያ ተናጋሪዎቹ ምንድን ነው ያሉት ጥናት እኮ
አያስፈልግም። አንድ ነገር የሚጠናው መኖሩ ጥርጣሬ ሲኖር ነው። የለም ተብሎ
ሲታሰብና አለመኖሩን ወይም መኖሩን ለማረጋገጥ በጥናት መደገፍ አለበት ተብሎ
ሲታሰብ ነው። የነበርን ያለን ወደፊትም የምንኖር ነን። በዚህ ጥናት መወያየት
የለብንም የሚል ጠንካራ እንትን ሲወስዱ አየንና፤ መናገሩ በዛ ላይ የበለጠ ነገሩን
የሚባብስ ስለሆነ በቃ መናገሩ አላስፈላጊ ነበር። ምክንያቱም መጀመሪያውኑ ጥናቱን
ጣሉት አላስፈላጊ ነው ብለው። ስለዚህ ላይ በዚህ ጥናት ላይ የሚደረገው ውይይት
የበለጠ ሁኔታውን ስለሚሻሻርም ስለገባን ሳንናገር ወጣን። ...በማውቃቸው ጉዳዮች ላይ
ግን በጣም እናገራለሁ። አንደኛ ..የሚነገሩት ጉዳዮች የማልስማማባቸው ሊሆኑ
ይችላሉ። ስለዚህ ካልተስማማሁ አለመስማማቴን መግለፅ ይኖርብናል። አንዳንዴ ደግሞ
ሁኔታው መነገር ባለበት መልኩ ሳይነገር ይቀራል የሚል ሀሳብ ሲኖረኝ። አንዱ
ለአንደኛ የሆነ ነገር ሲነግረው ይውላል። እና በአጋጣሚ ማታ አብረው ያድራሉ። ማታ
ያው የነገረው ሰውየ የነገረውን ነገር መልሶ ለነገረው ይነግረዋል። እንዴ ይሄን እኮ
ስነግርህ ነው የዋልኩ፣ ነግሬህ የል ይለዋል። ‹‹አላጣፈጥከውም›› አለው። ስለዚህ
በጣፈጠ መንገድ ወይም መነገር ባለበት መንገድ አልተነገረም የሚል ሃሳብ ሲኖረኝ፣
ራሱ አቅጣጫውን የሳተ ሲመስለኝ እናገራለሁ። ቢያንስ እንድ ጊዜ ሳልናገር አልወጣም።
መሰረት፡- እኔ እንኳን ሳልናገር የምወጣባቸው አጋጣሚዎች አሉ። አንደኛው((×××))
ማብራሪ ከመስጠት ዙሪያ ጥምጥም የተዞረበት ሁኔታ ሲኖር። ውስጤ ሀሳቦች ነበሩ።
ማለት ሰፊ የተብራራ ነገር ባይሆንም ውስን ሃሳቦች ይኖራሉ። በተለመደ አቅጣጫ
የማይመለሱ ከሆነ።.... ሌላው ሳልናገር የምወጣበት በቂ መረጃ ከሌለኝ ነው። ሀሳቡ
የሆነ ብልጭታ ይኖረኛል። ግን ስለዚያ ነገር መረጃ ከሌለኝ ልናገረው አልችልም
ሳልናገር ልወጣ እችላለሁ። ነገር ግን እድል ተሰጥቶኝ ሀሳብ ካለኝ እንደገና እድል

171. እንዲሰጠኝ እጠይቃለሁ። ሳይፈቀድልኝ ሁሉ ማይክ ወስጀ ተናግሬያለሁ። የቀረኝ ነገር
172. ካለ እንደገና ለመናገር እሞክራለሁ።
173. አገሬ፡- ሳልናገርበት ወጣሁበት ጊዜ ነበር። በባህላችን ለወንድም ለሴትም የሚሰጠው
174. ዋጋ የተለያየ ስለሆነ፣ ይሽ ነገር በከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም የሆነ ይመስለኛል።
175. በብዙዎች ስብስባ ላይ አብዛኛዎቹ ተናጋሪዎች ቢረባም ባይረባም ወንዶች ናቸው
176. የሚናገሩት። ይሄኛው ልዩነት እንዳለ ነው የሚያሳየው። ምክንያቱ ከኋላው ምን
177. እንደሆነ
178. ውብነሽ፡- አዎ ከአገሬ የተለየ ሀሳብ የለኝም። ሴትና ወንድ ብዙ ጊዜ ተሰብስበን
179. ከተሰብሳቢዎቹ መካከል አስር ሴቶች ቢኖሩና አምስት ወንዶች ቢኖሩ አምስቱ ወንዶች
180. ተናግረው ይወጣሉ። አስሩ ሴቶች ዝም ብለው ይወጣሉ።

ለምን ይመስልሻል?

181. ውብነሽ፡- እኔ እንደኛው ባህሉም ይመስለኛል። አስተዳደግሽም ይወስነዋል።
182. አስተዳደግሽ በቤትሽ ውስጥ ዝም በይ ከአንቺ ይልቅ ወንዱ እየተደመጠ ያደግሽ ከሆንሽ
183. እንዳትናገሪ ብዙ ነገር ያግድሻል። ከዛ ይዘሽው የመጣሽው ስለሆነ። ብዙ ጊዜ
184. የምናፀባረቀው አስተዳደጋችን ባህላችንን ስለሆነ። ሁለተናው ነገር ባህላችን ትልቁ ነገር
185. ትልቁን ድርሻ የሚወስደው። እኔ ዝም የምለው በአስተዳደጌ ምክንያት አይደለም። ባህሉ
186. ይመስለናል አንዳንዴ። ምክንቱም አስተዳደግ እንዳንል ከእኛ ቤት የነበረው አስተዳደግ
187. እንደ.. ባህሉ ግን አካባቢው ይይዝሻል። ወደሌላ ነገር እንዳንገባ እንጅ ስብሰባ ቦታም እኮ
188. ሰብሳቢውም እኮ ማንን ነው የሚያየው ለማን ነው እድል የሚሰጠው። ትናንትና
189. እንኳን በነበረው ስብሰባ እስካሁን ሴቶች እድል አላገኙም ተብሎ ተፅፎለት ነው እስኪ
190. ለሴቶች እድል ልስጥ ያለው። ለምን ከዛ በፊት ማበረታታቱን አላመጣውም። ከዛም
191. የሚሰጠው ትኩረት ለሴቶች ሳይሆን ለወንዶች ነው። በዚህ ምክንያት የሴትና የወንድ
192. የመናገር ተሳትፎ ልዩነት አለው።

ሴቶች ካልተጎተጎቱ አይናገሩም ማለት ነው?

193. ውብነሽ፡- አይ አይደለም ተናገሩ ተብለሽም እኮ ላትናገሪ ትችያለሽ። እንደዛ ማለቴ
194. አይደለም። ግን ቢያንስ እንትን እንዲሰጥሽ ዋጋ መሰጠት አለበት። የተለያየ ቦታ ዝም
195. ብለሽ እይው ዋጋ አይሰጥሽም። ዋጋ የሚሰጠው ለወንዱ ነው። ያ ነው እንጅ
196. ተጎትጉቶም እኮ አልተናገርንም። አንድ ሴት ብቻ ከዛ ሁሉ ሴት መካከል። እንጅ
197. መጎትጎቱ ብቻ መነገሩ ተናገሩ ተብሎ መገፋቱ ብቻ ሳይሆን ተንቀዋል ብየ እስባለሁ።
198. አንቺ እኔን ስታይኝ ነገ ጠዋት ይመጣል ዛሬ ብቻ ወዲያው ባልናገርም፤ ስለዚህ ተፅዕኖ
199. አለው። ያ በመደረጉ ተፅዕኖ አለው ብየ አምናለሁ። ያ ደግሞ የመጣው ከምንድን ነው
200. ማህበረሰቡ። ያንን ያመጣው ማን ነው ባህሉ።

ያ ባህል ምንድን ነው?

201. ውብነሽ፡- የወንድ ራስነትን ነው። መናገር ለወንድ ብቻ የተሰጠበት ሁኔታ ማለት ነው።
202. ከበደ፡- እኔ እየተለወጠ ያለ ይመስለኛል። ምናልባት ፊት ያ ባህል ሊኖር ይችላል።
203. አሁን ግን በጣም የምገረምባቸው ሁኔታዎች አሉ። በተለያዩ መድረኮች ላይ። ዋናው
204. ነገር ግን የመወያያ ጉዳይ ነው። የመወያያው ጉዳይ የሚመለከታቸው ከሆነ አሳክተው
205. የሚናገሩ ብዙዎች አሉ። አንዳንዴ ስርዓት የማይጠብቁ ጣልቃ የሚገቡበት ሁኔታም
206. አያለሁ። መወያያው ጉዳይ ግን ፍላጎት እና ያ ደግሞ ለወንዶችም ይመስለኛል። እኔ
207. በግድ ተጠርቼ የገባሁበት ስብሰባ ላይ መናገር አይደለም ጥሩ አድማጭም ሳልሆን
208. ልወጣ እችላለሁ። አንዳንዴ ፍርሃትም ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ባለፈው ስብሰባ
209. አንዲት የላብ ቴክኒሽል በፅሁፍ ስትፅፍ አያታለሁ። ስትፅ ስትፅፍ ነው የቆየችው እና
210. ያንን ማንበብ ገባች ለምን ፍርሃት ነው። እና ባህሉም በእርግጥ አንዳንድ ጊዜ ተፅእኖ
211. አለው። እንጂ እንደድሮው አይመስለኝም ታች ትናንሽ የምንላቸው ወይም ባላገር
212. የምንላቸው ዛሬ በጣም የሚናገሩ ነው የሚመስለኝ በሚመለከታቸው ጉዳዮች።
213. ካሳ፡- ግን በጣም ጥቂት ቁጥር ያላቸው ሰዎች ናቸው የሚናገሩት። ያለው ሀቅ ይሄ ነው
214. በብዛት።ድርሻን መጠበቅ ስናይ እንኳ ወንዱ አቋርጦ ሊናግር ይችላል እንደዚያ ያደረገች

ሴት ተሳታፊ እኔ አላስታውስም አጋጥሞኝ አያውቅም። ተናጋሪው የሆነ ነገር ሲያበላሽ
አግሬሲቭ በሆነ መንገድ እንኳ ተናጋሪውን አስቁሞ፣ ጣልቃ ገብቶ የማረም እንዲህ
እንዲህ አይነት እኒሼቲቭ መውሰድ አለ ወንዶች ጋ። እና ምናልባት አንዱ ምክንያት
የሚመስለኝ እኔ መጠንቀቅ ይመስለኛል። በጣም ጥንቃቄ የሚያበዙ ይመስለኛል። በጣም
ጥንቃቄ ያበዛሉ። ያልኩት ነገር በየት በኩል ነው የሚመነዘረው፣ ምን ይወሰድበት
ይሆን የሚል ነገር ያለ ይመስለኛል። ይህን የምላችሁ አንድ ተጨባጭ ተሞክሮም
ስላለኝ ነው። ምናልባት ታስታውሱ እንደሆነ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች የ..... ቋንቋ
አጠቃቀም ስብስባ ጊዜ እኔና አስናቀ አንድ ላይ ነበርን ጎን ለጎን ነበርን። ዜን እኔ የሆነ
ሰዓት ላይ መናገር ጀመርኩ እጄን አወጣሁ፣ እንዳገር አልፈለገችም። በጣም እንድናገር
አልፈለገችም። እንድቆጠብ ነው የፈለገችው የዛኔ። እና ምክንያቷ ደግሞ የዛኔ ቋንቋ
እንዳይደበላለቅ በጣም ጥንቃቄ ሲደረግበት የነበረ ቀን ነው ታስታውሳላችሁ። እኔ ደግሞ
ኦቢየስሊ የሚሆነው ነገር ይሄ ነው። ብዙ ጊዜ ሳልቀላቅል አውርቼ አላውቅም። እና በቃ
እንዳልናገር በጣም እንትን ትል ነበር። እሷ ከሆነች እንግዲህ ስለምትጠነቀቅ አትናገርም
ማለት ነው። አልፎ አልፎ እንዲህ ወጣ ያሉ ሰዎች የሚሳተፉበት ነገር ለምሳሌ ቶክ
ሾው አንደ ምሳሌ ብንወስድ ምናልባት...ሊሆን ይችላል። በጣም መናገር የሚችሉ ጉዳዩ
ላይ በጣም ያገባኛል አይነት ስሜት ያላቸው ከሆኑ በዚህ ላይ ዳይናሚክ የሆነ ተሳትፎ
ልታይ ትችላለህ።
ሴቶችና ወንዶች በስብሰባ ወቅት የተለያየ ባህርይ ሳያሉ ብላችሁ ታስባላችሁ?
ከበደ፡- አጀንዳውን ነው እኔ የምልህ። የእነሱ ጉዳይ ከሆነ አክቲቮች ናቸው። የራሳቸው
ጉዳይ ከሆነ በሌላው ላይ ግን ሪዘርቭድ የመሆን ሁኔታ ያሳያሉ።
ለምሳሌ በእኛ ደረጃ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ምን አይነት ጉዳይ ቢነሳ ይናገራሉ ትላለህ
ከበደ፡- የፆታ ጉዳይ ቢነሳ አሁን እና አንዱ ለምሳሌ በዛ በስብሰባ ላይ ትንሽ አንደርማይን
አድርጎ ቢያቀርብ እርግጠኛ ነኝ ከዛ ጋ ሆት ይሆናሉ በጣም ይወያያሉ።
አለሙ፡- እንግዲህ አጠቃላይ ሁኔታ ይሄ መናገር አለመናገር የሚባለው ነገር ሳይንሳዊ
በሆነ እንትኑ ካየነው ከፐርሰናሊቲ ጋር የሚያያዝ ይመስለኛል። አንዳንዴ በአገር ደረጃ
ለምሳሌ ጃፓኖችን አይታችሁ ከሆነ ወደዚኛው ወደአውሮፓ ካለው ህብረተሰብ ጋር
ሲያነፃፅሩት እነሱ በጣም ሪዘርቭድ ናቸው በጣም ቁጥብ ናቸው። እነእንግሊዝን ምናምን
ብታዩ በቃ ከእነሱ ጋር ቅጭ ካልሽ ይነዘንዙሻል። እና አንዳንዴ እንትን ሊሉሽ ይችላሉ።
ምግብ እየበሉ ራሱ ሳይቀር ይናገራሉ ሴቶቹም ወንዶቹም። እኔ ካልቸር ራሱ ወይም
ፐርሰናሊቲ የተያያዘ ነገር ይመስለኛል። እና ወደእኛ ሁኔታ ስመጣ ደግሞ የሴቶቹ
አለመናገር የሚጠበቅ ነው። አሁን ቅድም ስታነሱት የነበረው አድል አልተሰጠም
የሚለው ራሱ አለመናገራቸው ራሱ አርቴክትድ ነው በቃ። እንዲናገሩም አይጠበቅም
እንዲያው እድል እንስጣቸውና ይናገሩ አይነት ነገር እኛ ስንፈቅድ ብቻ ነው መናገር
ያለባቸው የሚልም አይነት እንት አለ። አርቴክትድ የመሆነ አሁን የእኔ ልጅ አለች
ትምህርት ቤት አንዱ ከሚቀርብብኝ ስሞታ አትናገርም። እቤት ግን ምላጭ ናት በቃ
እንዲያውም እንትነኗን ሁሉ መብቷን አሳልፋ አትሰጥም፣ ትናገራለች። ግን መኪና ከዚ
ልጆቹ ባለመናገሯ ነው የሚያውቋት። ሰርቪስ ላይ አሁን ለምሳሌ ከማይናገሩት ልጆች
አንዷ ነች። እና አንዱ የሚቀርበው እንትን አትናገርም። በሂደት ካለሆነ በስተቀር
እንትኑ አለ በቃ አይናገሩም ብዙ ጊዜ ሴቶቹ። እና ህብረተሰቡም የሚጠብቅ አይመስለኝ
እንዲናገሩ። የሚጠበቅም አይደለም። ፕራክቲከም ምናምን ስንወጣ ስናይ አስተማሪዎቹ
ወንድ ከሆኑ ምን ይላሉ ‹‹አሁን ደግሞ ለሴቶች ነው እድል የምሰጠው። ይላሉ
እስላኩን ለወንዶቹ ነበር አሁን ደግሞ ለሴቶቹ ይላሉ እና አሁን እኔ ይህንን ሁሉ
መለወጥ ካለብን ምንድን ነው መደረግ ያለበት ታስክ መስጠት። አንደና ነገር ንግግር
ስብሰባ ላይ እጅን በማውጣት ብቻ ነው የሚሰጠው እንጅ አንተ አስፈላጊ ነህ ወይም
አስፈላጊ ነሽ ተብሎ አይጋበዝም። እንደዚ አይነቱ ቢለመድ ጥሩ ይመስለኛል። በቃ አገሬ
አሁን አንቺ አስተያየት እንድትሰጭ እፈልጋለሁ እጅ አወጣሽም አላወጣሽም፤ ያንቺን
ሀሳብ እፈልገዋለሁ ብሎ ሰብሳቢው እስቲ አስተያየት ስጭኝ የሚል አይነት

ያስፈልጋል። ትምህርት ቤት ስናይ እጅ ማውጣት አለማውጣት ሳይሆን ታስክ
ለወንዶቹም ለሴቶቹም የሆነ ታስክ ትሰጫቸውና ያንን ታስክ የገድ ማቅረብ ካለባቸው
መስራታቸውን ለማረጋገጥ የግድ ስራቸውን ለማቅረብ ይናገራሉ። በዛ አይነት ካለሆነ
በስተቀር ይች እጅ ማውጣት የምትለዋ ነገር ብዙም፡ አንዱም ችግር ይሄ ይመስለኛል።
ካሳ ባቀረብከው ያ ስብሰባ ላይ የሀይስኩል መምህራን ቀምተው ከፕሮፌሰር ....
ተናግረዋል። በግድ እስካሁን አውተን አውተን ብለው ጮሁ መጨረሻ ለይ። መናገር
አለብን አሉና ጮኸው አንዷ ተናገረች። እንትኑ እየመጣ ይመስለኛል እልሁ። ግን ይሄ
የሚመጣው በቃ ሴቶቹ መናገር የለባቸውም ወይም ቢናገሩም ርባና የሆነ ነገር
አያመጡም የሚለው እንዳለ ሳይሆን እንደማንኛውም ሰው እንደሰው መወጣት ያለባቸው
ነገርአለ፤ የሚፈለግ ነገር አለ የሚጠቅም ነገር አለ እኩል ቢታይ። እኔ አንዱ
የሚቸግረኝ ነገር አፕሮቹ ነው። አሁን በቴሌቪዥን ምናምን ነገር የሚቀርቡ ነገሮች
ብዙ ጊዜ አልወዳቸውም። እና የበቀደሙን እንትን እ፤ አሁን አልወደድኩትም።
ያ ወረቀቱን እንደዛ ተብለው ነው ወይ መናገር ያለባቸው? እና ያ የሚያሳየው
የራሳችንን አመለካከት ነው፤ በቃ አመለካከታችን ገና ይቀረዋል።
ሀብቱ፡- እኔ በተቃራኒው ነው ያለሁት። ሴቶቹና ወንዶቹ በንግግር ተሳትፎ ልዩነት ያለ
አይመስለኝም። በአካዳሚክ ኮሚሽን በፕሮግራም ስብሰባ ላይ በጣም ነው የሚሳተፉት።
እንዲያውም በቃ ካልተባለ አያቆሙም። እና እየተለወጠ ነው የሚመስለኝ እኔ። አሁን
የምናወራው ከዚህ በፊት የነበረውን ወይም ደግሞ ከአካዳሚክ ኮንቴክስት ወጥን ያለውን
ሊሆን ይችላል እንጅ አሁን ይሄ ራሱ መድረክ አንድ ምስክር ሊሆን ይችላል። ሴቶች
በደንብ እየተናገሩ ነው ተገፍተውም አይደለም በራሳቸው ጊዜ ነው። በትልልቅ
ስብሰባዎች ሴቶች ብቻ አይደሉም። አሁን ከዚህ ካሉት እኮ ወንዶች ራሱ ሞማይሳተፍ
አለ። ከሴቶች ማነስ፣ከወንዶች ብዛት አንፃር ሊሆን ይችላል ብዙ ወንዶች መናገር
የቻሉት። ሶ እድሉን ካገኙ ግን ብዙ መናገር እየቻሉ እንደሆነ ነው የሚታየኝ።
መሰረት፡- በትልልቅ ስብሰባዎች የወንዶች ቁጥር ይበልጣል። ስለዚህ ቀድሞ
የማወጣትና እድል የመሰጠት ሁኔታ ይኖራል። ነገር ግን በሳል በሳል የሆነ ሀሳብ
ከማራመድ አንፃር ሴቶች የተሻለ ተናጋሪዎች ናቸው። ትልልቅ ስብሰባ ላይ ግን
አንዳንድ ጊዜ የሚፈጠሩ ነገሮች አሉ። ኢቪን አሁን በእኔ ውስጥ የሚፈጠር ነገሮች
አሉ። ስፔሻሊ ሁለት ሶስት አራት ሰው ሲናገር ከተናገረ በኋላ አብዛኛው ሀሳቤ
ይሸፈናል። መሸፈን ብቻ ሳይሆን እኔ ከማውቀው በላይ ይብራራል። በዛ ሰዓት እኔ
የያስኩት ሀሳብ ለካ ደካማ ነው እልና እኔ በዛ ምክንያት ሁሉ ልተናገርኩበት ሁኔታ
አለ።
አለሙ፡- ግን አንድ ነገር እዚ ጋ አሁን ‹‹አድል እንጅ ችሎታ አላጡም›› የሚለው
የ..... ኦፖርቹቲ የሚለውን እንትን አይተካም። እና ይሄ ራሱ እድል
አላገኙም የሚለው ነገር በቃ እንትናችንን ገና እና ይሄ አንዱ መጥፋት ያለበት ነገር
ነው። የ.....ው ኮኔቴሽን ምንድን ነው። ሴቶቹበቃ ያው እጣ ፈንታ ሴቶቹ በቃ
ተረግመዋል እንዳይናገሩ ማለት ነው የወንዶቹ ነው ቦታው። እና እድል የምትለዋ ነገር
ብዙ ጊዜ ጋዜጣ ላይ ይጠቀሙባቸዋል። እና ትክክለኛው ኦፖርቹኒቲ የሚለው
የ.....ው ኮኔቴሽን ያንን አይደለም የሚያሳየው። እና አንዱ ችግራችን ይሄ ነው።
አገሬ፡- ይሄ ትርጉም እኮ ማህበረሰቡ ውስጥም ያለ ይመስለኛል። አሁን ጋሽ አለሙ
ያለው ማለት ነው። ለምሳሌ ሴት ከፍተኛ ተቋም ላይ ያለውን ሳይሆን የምናየው፣
በአገር አቀፍ ደረጃ ያለውን ወጣ ብለን እንይ ብንል ሴት ልጅ በቃ መናገር የለባትም።
የሴት ልጅ ዱዩቲስ ኤንድ ሪስፖንስቢሊቲስ እነዚህ እነዚህ ናቸው ተብለው የጠቀመጡ
አሉ። እና ያንን አልፋ የምትሄድ ሴት እንደመረን ትባላለች ለጋብቻ የማትመረጥበት
ሁኔታ አለ እና ለመሳሰሉት ነገሮች። በስርዓትም አሁን የምናያቸው በርካታ ነገሮች
የሚያሳዩት ነገር ያ ነው። ስለዚህ እድሏ የሰጣት...ማህበረሰቡ እድል በሚለው ያ ነው።
ያንን ነው መኖር ያለባት ነው የሚለው። ወጣ ያለ ነገር ስታሳይ ያ ነገር ኩተመታ ያው
እድል የሚባለው ነገር ይቀራል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
LIBRARIES
P. O. BOX 1176
ADDIS ABABA, ETHIOPIA

ካሳ፡- ግን እዚህ ጋ አንድ ጥያቄ አለኝ፡፡ ችግሩን ለሆነ አካል ነው ያደረግነው፡፡ አሁን
ደግሞ እዚህ ጋ ሌላ ማህበረሰብ ውስጥ ነው ያለነው፡፡ ያንን በተወሰነ መልኩ
የሚያንፀባርቅ ግን ደግሞ አሁን ባህል ምናምን ብለን የምናነሳው ነገር እዚህ ሆነን
የምናደርገው ነገር እዛ የሚጠበቀው ነገር አልሆነም ወይ? ስለዚህ ሌላ ሰው ነው ማለት
ነው ይሄን ሜዳ ተዋግቶ ማስለቀቅ ያለበት?
ሳባ፡- ምናልባት እዚህ ላይ ተፅዕኖውን ይዘነው ነው የምንመጣው፡፡ አብሮን ተከትሎን
ስለሚመጣ ይመስለኛል፡፡ እኔ ራሴን ስገመግመው ተለውጫለሁ፡፡ ድሮ አልናገርም ነበር
ስብሰባ ላይ በየትኛውም ስብሰባ ላይ በዚህ በአካዳሚኩ ብቻ ሳይሆን በውጭ በግል
በተለያዩ ቦታወች ላይ እሳተፍ ነበርና ግን እፈራለሁ፡፡ መናገር ስጀምር ራሱ ድምፄ
ይንቀጠቀጣል ብዙ ጊዜና፡፡ ይሁ የሆነው ከቤትም ከታች ከማህበረሰቡም ይገር
የመጣሁት ነገር ስላለ ነው፡፡ ሴት ልጅ አድማጭ መሆን አለባት፣ ሴት ልጅ እንዲህ
ጮክ ብላ መናገር የለባትም ለሚል ማህበረሰብ ነው የመጣሁት የእዛ ተፅእኖ
ይመስለናልና ኢክስፒሪያንሱን እገኘን በሂደት በብዙ ስብሰባዎች ላይ እየተሳተፍን
በምንሄድበት ጊዜ ግን እሻሻልን እየቀረፍን የምንሄድ ይመስለኛል፡፡
ውብነሽ፡- የተለየ ሃሳብ አይደለም የማናሳው፡፡ ከባድ እኮ ነው! ካሳ፡፡ ባህል እኮ በጣም
በጣም ነው እኮ ከባድ ነገር ነው፡፡ ምናልባትም ይልቀቀኝ ብትል የረጅም ጊዜ ትግል ነው
የሚጠይቅህ፡፡ በአንዴ ልትቀርፈው የምትችለው ነገር አይደለም፡፡ እኛ እዚህ ግቢ ውስጥ
ያለን ኢክስፒሪያንስ በጣም ትንሽ ነው ከአደግንበት፣ ከመጣንበት በህል አንፃር ሲታሰብ፡፡
ስለዚህ እንዴት አድርገን ነው መቅረፉ ትክክል ነህ ያስፈልጋል፡፡ የተለያዩ አጋጣሚ ሳባ
እንዳለችው ልንቀርፈው እንቸድላለን፣ ወይም ሊቀረፍ ይችላል፡፡ ግን ጊዚውን አስብ
ወዲያው አይደለም፡፡ እንደገና ደግሞ ቅድም ያልኩት ነገር መዘንጋት ያለበት
አይመስለኝም፡፡ አንዳንዴ የምታገኛቸው ነገሮች በራሱ ከሌላው አንፃር የሚመጡ ነገሮች
በራሳቸው አሁንም ያንኑ ነገር ይዘህ እንድትሄድ ሁሉ ያደርጉሃል፡፡
ለምሳሌ?
ውብነሽ፡- ቦታ አለማግኘት፡፡ እድል የተባለው ድርሻ አለማግኘት፡፡ እንዲህ እንዲህ አይነት
ነገሮች አሁንም ያንኑ እንድታንፀባርቅ ያደርግሃል፡፡ በቃ በዛው ትኖራለህ፡፡ እርግጠኛ ነኝ
እኔ አሁን ብናገር የመናገር እድል ቢሰጠኝ አልፈራም፡፡ እነሳባ አገሬ እንዳሉት ቅድም
ድምፄ አጥንቀጠቀጥም፣ ሀሳቤን በትክክል መግለፅ እችላለሁ፡፡ ያንን ይዤው የመጣሁት
የተለያዩ ኤክስፒሪያንሶችን አልፌ ስለመጣሁ ነው፡፡ ድምፄ አይንቀጠቀጥም አልፈራም፡፡
መናገርን ከጀመርኩ አንድ ጊዜ እድሉ ተሰጥቶኝ ወይም ድርሻው ተሰጥቶኝ መናገር
ከጀመርኩ እንደዚያ ያለ ነገር የለኝም፡፡ ግን የምላቸው ተፅዕኖዎች ግን አሁንም....
እንዲያውም እኔ አንድ እንትን መናገር የምፈልገው ከነበረኝ ትክክለኛ መረጃ ነው
የምሰጥሽ ከነበረኝ ተሳትፎ እንዲያውም አሁን ዝቅ ብያለሁ፡፡
ለምን ተሳትፎሽ ዝቅ አለ? ከማህበረሰብ ባህል ወተሽ ወደተቋማዊ ባህል ገብተሸል፡፡ ስለዚህ የተቋሙ ባህል
ተፅዕኖ አድርጎብሻል ማለት ነው?
ውብነሽ፡- አዎ
ምን አይነት ባህል ነው ተፅዕኖ ያደረገብሽ የተቋሙ?
ውብነሽ፡- ቅድም ያልኩሽ ነገር እኛ ወይም ሴቶቹ እንዲደመጡ እድል አለመስጠት አንዱ
ነው ለእኔ፡፡ ስለዚህ በእነዚህ ምክንያቶች ራሴን አቅቤ እኖራለሁ፡፡ ተቀባይነት የለንም
ስለዚህ አበቃ እንደዚህ አይነት ነገርን ትተሸው ትኖሪያለሽ፡፡ የነበረኝ ኤክስፒሪያንስ ግን
ያ አይደለም፡፡ ለዛም ነው ቅድም አሁን ስናገር አልፈራም፣ አልቀጠቀጥም፣ ሀሳቤን
በትክክል እገልፃለሁ የምልህ የነበረኝ ኤክስፒሪያንስ ነው፡፡ ያደኩበት ሁኔታ ነው፡፡ ሳድግ
ተናግሬ ነው ያደኩት፣ ስወጣም በተለያዩ መድረኮች ራሴን ስገልፅ ነው የኖርኩት፣
ሌላም ሀሳብ እንትን ስል ነው የኖርኩት፤ እዚህ ግን ዝምታን ነው የመረጥኩት፡፡
መሰረት፡- ቅድም ስትናገር ኤክስፒሪያንስ በፊት አልነበረህም በኋላ ልምዱ ሲኖርህ
ችግር እንደሌለብህ ተናግረሃል፡፡ አንተ እንግዲህ ወንድ ነህ፡፡ እንዴት እንዳደግህ
ታውቀዋለህ፣ ሴቶች ደግሞ እንዴት እንደሚያድጉ ሁላችንም እናወቀዋለን፡፡ የእሷ ምን

ያህል ተፅእኖ ነበረባት የአንተ ምን ያህል ነበረብህ አንተ ምን ያህል ያንን ብቻ ይዘን
ችግሩ ምን ያህል ሊከፋ እንደሚችል ወደእኛ ሲመጣ ፕሪዲክት ማድረግ ይቻላል።
አንተ ከፈራህ ሴቷ ምን ያህል ትፈራለች የሚለውን ነገር። ኤክስፒሪንስ ደግሞ እንትን
ያደረግረዋል። አይታችሁ እንደሆን በእድሜያቸው በጣም የገፉ ትልልቅ ሰዎች
በእድሜያቸአው ብቻም አይደለም በትምህርትም ከፍ እያሉ በሚሄዱበት ሰዓት የተሌየ
ሃላፊነት ተሰጥቷቸው የተለያየ ልምድ ሲኖራቸው ሌቶች መድረክ ሲይዙ በጣም ገላጭ
ይሆናሉ። ሃሳባቸውንም ሎጅካል በሆነ አቅጣጫ የማስኬድ አቅምም እያዳበሩ
ይሄዳሉና፣ እንዲህ በቀላሉ የሚቀረፍ አይደለም። ፐርሰናሊቲ ደግሞ...ከዛ በኋላ እዚህ
ስትመጣ ምን ያህል ይቀየራል፣ እድልም ያልነው ነገር ነው። የቦታ ጉዳይ ፣የድርሻ
ጉዳይ፣ ሃላፊነት ላይ የመቀመጥ ጉዳይ፣ ከብዙ ሰዎች ጋር ለምሳሌ በዩኒቨርሲቲው
ትልልቅ ቦታዎች የሚቀመጡ ሰዎች ጋር፣ አቅም ካላቸው ሰዎች ጋር የመገናኘት
የመነጋገር ሃሳብ የመለዋወጥ እውቀት የማግኘት እድላቸው በዛው ልክ ሲሰፋ ሀሳብ
እንደልብ የመግለፅ እንትናቸው እየተለወጠ ይመጣል።
አለሙ፡- በነገራችን ላይ ይሄ እኮ በቀላሉ የሚሻር እንትን አይደለም። መሰረት ሲጥልም
ረጅም ጊዜ ወስዶ ነው።አሁን ተለወጥ ብንለው ቀላል አይደለም። ፀሃፊዎች የወንድ
ፀሃፊዎች ነበሩ ከዚህ ግቢ። ፈንታሁን ሲቀጠር የዲፓርትመንት ፀሃፊ ሆኖ ነው
የተቀጠረው። ሌሎች ደግሞ ነበሩ እና እነሱን ሰው ሲያገኛቸው ቁጭ ብለው
ኮምፒውተር ላይ ወይም ታይፕ ላይ ሲያገኟቸው ፀሃፊዋን ፈልጌ እኔ ነኝ ሲሉ ሰው
አያምንም።እና በጣም ተቸግረው ነበር። አንድ ሯጭ ነበር አንዱ ለምን አቋርጠህ ወጣህ
ሲሉት ‹በሴት ሰዓት አልገባም ብየ› ብሎ መከራውን ሲበላ ነበር። እና ማስተርስ ስንማር
ቤት ተሰጠን እንድ ብሎክ ለማስርስ ተማሪዎች ተብሎ። ደግሞ ሌላው ብሎክ ከጎን
ለአዲስ አበባ ሴት ተማሪዎች ተሰጠ። እና ወንድና ሴት እጠሆኑ ቼዝ ይጫወቱ ነበር።
አንድ ጊዜ ሴቷ ወንዱን አሸነፈችው። እኔ ወንዱን አሸነፍኩት እያለች ለጓደኞቿ
ወንዱን እኮ አሸነፍኩት እያለች እንደታምር ነበር። ይሄ ቀላል ነገር አይደለም። ግን
ደግሞ ቦታው ሲያዝ ጥሩ ይሆናል። የቁጥር ማነስ ይመስለኛል ብዙ ጊዜ ሌቶቹ ከታች
ነው የሚቀሩት። ቁጥር አሁን የወንዱን ያህል በቁጥር እኩል እንዲያው ቅጥሩን
ሌላውን ነገር ትተን ማለት ነው። እና በዚህ በማናጅመንቱ በምናምኑ አይታዩም።
ሲታዩ ደግሞ ትንሽናቸው ከቁጥር አይገቡም። አሁን በማስታወቂያው በጋዜጠኝነቱ
አሁን የሙሉዓለም አድናቂ ብዙ ነው። እንደሷ በሆንኩ የማየውል ወይም እሷ ስትናገር
አፉን ከፍቶ የማያይ የለም። ያቺ ደግሞ ማናት ሜሮን ሲይዙት እንትኑን ብዙ ተከታይ
ብዙ አድናቂ እንትን ይላሉ። ግን ያን ያህል ተመጣጣኝ የሆ እንትን ላይ አይታዩም።
እናም መግስትም የራሱ እጥረት አለው፤ እና ሂደት ይጠይቃል ለማለት ፈልጌ ነው።
ከራሳችን ራሱ ከእኔ አሁን እኔን አሁን ብትጠይቀኝ ከዚህ ነፃነኝ ልልህ አልችልም።
ካሳ፡- ችግሩ እንዳለ ሁላችንም እናውቃለን። ግን ደግሞ አያዎ የሚመስል ነገር አለ
እዚህ ጉዳይ ላይ ማለት ነው። እላይ የሚባል ቦታ ላይ የደረሱ ሌቶች ስናገር አጉራ
ዘለል እባላለሁ የሚለው ስጋት የማይገታቸው ያሉበት ሁኔታ አለ። ለምሳሌ ውብነሽ
ካነሳችው ልጆምርና ስብሰባ ቁጭ ብላ እጇን አውጥታ.. ትፈልጋለች። እጇን ማውጣት
የፈለገችው ምናልባት ባወጣም አልናገርም ይሆናል፣ አልተናገርንም ፣ ቢሰጠንም
አልተናገርንም እያለችን ነው። ከዚህ በተቃራኒ ግን ድርሻ አለመሰጠቱን ኮምፕሌን
እያደረግን ነው። ግን እዚህ ቦታ ያሉ ሌቶች ጉዳዩ እንዲሻሻል ፊት ቀድመው መጋፈጥ
ነው የሚጠበቅባቸው ኖርማሊ ግን ለራሳቸውም ራሱ እድል መውሰድ ወይም እድል
የሚሰጣቸው ሰው ሲጠፋ መንጠቅ ምናምን ካልቻሉ፣ ይሄ እኮ ሁሉም የየራሱን
ኮንፎርት ይዞ መቆየት ይፈልጋል፣ እውነት ለመናገር ከሆነ። ስለዚህ የያዙ ሰዎች
ይዘው መቆየት ይፈልጋሉ፤ ያንኑ ያለውን ነገር ሜንቴን ማድረግ ይፈልጋል። እና
እዚህ ጋ ማንኳኳት አያስፈልግም ወይ? እድሉን መንጠቅስ አያስፈልግም ወይ? እንደ
ብሌሲንግ የሆነ አካል ሰጥቶ እንዲቀየር የመፈለግ አይነት ነገር ያለ መሰለኝ።
አገሬ፡- ብዙውን ጊዜ ሌቶች በቁጥራቸው ትንሽ ናቸው እያልን ነው። የህይወት ልምድን

399. ደግሞ ብናይ ለተለያዩ ገጠመኞች የመጋለጥ አቅማቸው፣ ከቤት ወጥተው ትምህርት
400. ቤት ከመሄድ ውጭ ማለት ነው ከወንዶች የተሻለ አይደሉም ሴቶች። ምናልባት
401. በጓደኝነት እኔ ውብነሽ እንደዚህ ተሰብስበን ስለአንድ ኢሹ የምናወራውና በማህላችን
402. አንድ ወንድ ሲገባ ወይም ሌላ ከእኛ ተቃራኒ የሆነ ሰው ሲገባ የምንገልፀው ሃሳብ አንድ
403. አይነት ላይሆን ይችላል። ምክንያቱም እንደዚህ አይነት ልምድ ስለሌለን። እና የልምድ
404. ማጠር ነው ቅድም ጥሩዬ ስትለው ነበር። የልምድ ማጠር አለብኝ። እንዳልሽው በጉዳዩ
405. ላይ አሁን አኔን ብታይኝ ዛሬና ከዛሬ አራት አመት በፊት ብታይኝ እኩል ተሳታፊ
406. አይደለሁም። ለምን ዛሬ ለተለያየ ነገር ስለተጋለጥኩኝ በነዛነት የመግለፅ ነገሩ ስቲል
407. ችግር ቢኖርብኝም አሁን የተሸለ ሁኔታ ላይ ነኝ። ለምሳሌ አሁን የበቀደሙ ስብሰባ ላይ
408. ኤፍቢ ግቢ ጠዋት ላይ እጄን አውጥቼ ተናግሬያለሁ። ማንም ሴት አልተናገረም ነበር አ
409. ኔ ብቻ ነኝ የተናገርኩት። እዚህ ምንም አልተናገርኩም። እንዳልኩሽ ሀሳብ አልነበረኝም
410. አይደለም ነበረኝ። እና ምንድን ነው ለተለያዩ ነገሮች ያለመጋለጡ እንትን ይወስናል።
411. ካሳ ያችን ነገር እያዳበራት እንደመጣ ሁሉ ለእያንዳንዷ ሴት እንደዛ አይነት ገጠመኞች
412. በየጊዜው፣ በተወሰነ ጊዜ ርቀት ማለት ነው ቢኖሩ ሀሳባቸውን የመግለጽ የመናገር
413. ነገሮች አሉ። የተለያዩ ነገሮች አሁን ከአካዳሚክ ነገር ውጭ ሌላ ኢክስፒሪንስ ላይኖራት
414. ይችላል አንድ ሴት ልጅ። እና ምንም ኤክስፖሪያንስ በሌለበት ቦታ ስልጣኑን ሁሉ
415. ወንዶች በያዙበት ሁኔታ ውስጥ የመናገር አቅሟ ውስን ነው። ስልጣን ትያዝ በብዙ
416. ሽኩቻ (ሳቅ) አይ አንዳንድ ገጠመኞችን እላለሁ። አሁን ወንድ ልጅ የሰራው ስህተት
417. ቢሆን ምንም አይባልም፤ ማለት በቃ ተመጣጣኝ ቅጣት ተሰጥቶት ምናምን ምናምን፤
418. ሴት ልጅ ከቅጣቱም በተጨማሪም ለቀጣይዋ ሴት እንዳትበረታታ የሚያደርጉ
419. ንግግሮችም ይከተላሉ። ድሮውንስ ሴት አይደለች፣ ወይ ምን ልታመጣ ነበር፣ ልጆቿን
420. አርፋ ብታሳደግ፣ የመሳሰሉት ማለት ነው። እና እነዚህ ነገሮች ለምሳሌ እኔ ዳር ቆሜ
421. ስሰማ አንዳንዱ ሴት መሆኔንም ተጠራጥሮ የሚናገር ሰው አለ። ኢንከሬጅድ አልሆንም
422. በታሪክ፤ እንዴ አርፊ ብቀመጥስ ምክንያቱም ድንገት ብሳሳት እመታለሁ፣ ከዛ በኋላ
423. ለመነሳት በጣም ያቅታል።
424. ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታ ከአቻዎቻቸው ጋር በሚያደርጉት የተግባቦት ሂደት ራሳቸውን አድማጭ በሚረዳ ሁኔታ ባግባቡ ይገልፅሉን?
425. ውብነሽ፡- ቅድም አገሬ ስትናገር ወንዶቹ ረባም አረባም የሚል ነገር ተናግራለች፤
426. ወንዶቹ ብዙ ይናገራሉ። ሴቶቹ ሲናገሩ ቅድም ጋሽ ከበደ ሲናገር በቅርቡ በነበረው
427. ስብሰባ ላይ ሴትዮዋ ሀሳቧን ከመናገሯ በፊት ምን መናገር አለብኝ ብላ አስቀድማ አቅዳ
428. ነው። ስለዚህ ስታቀርብም የፃፈቻትን ነጥብ ነው ተናግራ ቁጭ ያለችው። ማንዛዛት፣
429. ማዛዟር ፣ ምናምን ወደሚል ነገር አልገባችም። እና ብዙ ጊዜ ሳይ ሴቶቹ ሀሳባቸውን
430. ሲያቀርቡ ጥርትና ግልፅ በሆነ ቋንቋ አጭር አድርገው ሃሳባቸውን የመግለጽ ሁኔታ
431. አለ። ከሚናገሩት ቁጥር አንፃር እንጂ ወንዶቹ ጥሩ ሀሳብ አይገልጡም ማለቴ
432. አይደለም። ወንዶቹም የሳሉ። ግን ሴቶቹ በጥሩ ሁኔታ የሚያቀርቡ ይመስለኛል።
433. በጣም ጠንቃቆች ሰለሆኑ ይመስለኛል።
434. ከበደ፡- የሚናገሩበት ሁኔታ ይመስለኛል። እኔ ጥሩ ተናጋሪን ስለማደንቅ ነው። አንዳንዱ
435. ሰው አነጋገሩ ይማርከኛል። ብዙ ጊዜ ግን ለመናገር ብለው የሚናገሩ ሰዎች ወይም
436. ለማስመዝገብ የሚናገሩ ሰዎች አይሳካላቸውም። ክልብ መናገር ሲኖርባቸው የሚናገሩ
437. ሰዎች ግን ምንጊዜም ይሳካላቸዋል። እንደዚህ አይነት ሰዎች ደግሞ ሴቶች ናቸው።
438. ወይ በሙያው ባለቤቱ ነው፣ ወይም የተነሳው ጉዳይ በሚገባ ይመለከተዋል።
439. አለሙ፡- ሴቶቹ ላይ ኢሞሽናል ኢንተሌጀንሲ የሚባለው ነገር ሆደባሻነት ያለ
440. ይመስለኛል። የሚናገሩት ነገር ፍሬ የለውም ምናምን ለማለት ሳይሆን፤ ቶሎ ብሎ
441. እንደዛ አይነት ያው ቅድም ስንነጋገረው ነገር እንዳለ ከራሳቸው ከውስጣቸው ምን
442. ይለኛል ሰው ብናገር፣ ምን ይሉኝ ይሆን የሚል አይነት ነገር ስላላቸውም ይመስላል
443. ቶሎ ብለው ወደኢሞሽናል ይሄዳሉ። እኔ ምክትል ፕረዚዳንት በነበርኩበት ጊዜ ግሩፕ
444. መጡ፣ እየተወያየን እያለ እንዲ በቃ ቀጥታ እየየዋን ለቀቀች፤ ከመናገር ይልቅ በቃ

ለቅሶ ከዛ እሰሷን ማባበል ያዝኩ። አንዱም አስታውሳለሁ ዶር. አዜብ አዲስ አበባ
ዩኒቨርሲቲ የሆነ ኮርስ ስታስተምረን የሆነ ነገር አየችና ወደለቅሶ ነው የገባችው።
ከመግለፅ ይልቅ ፊቷ በቃ በጣም ተቀያየረና...ሆደባሻነት ያጠቃቸዋል።
መሰረት፡- ሀሳባቸውን ያስረዳሉ፤ መግባባት ይቻላል በሁለቱም በኩል።
ሳባ፡- እኔም ሀሳባቸውን ሁለቱም እኩል ያስረዳሉ ብየ አስባለሁ። ብዙ ጊዜ ስብሰባዎች
ላይ አዳምጣለሁ፤ ሴቶች በሚናገሩበት ጊዜና የሚመርጧቸው፣ የሚናገሩባቸው ርዕሰ
ጉዳዮች ብዙ ጊዜ አስተውላለሁ በጣም ይመርጣሉ። አንድ ጊዜ እንዲውም ..ችግሮች ላይ
ነበር ፎከስ አድርገው ይናገሩ ነበር አገሬም ያኔ ተናግራለች። እና የሚመርጡ
ይመስለኛል። ያንን መርጠውም እንዴት መናገር እንዳለባቸው ቅድም የተባለው ነገር
የባህል ተፅዕኖ ሊሆን ይችላል ወይም ሌሎቹ ያመጡት ሊሆን ይችላል የሚጠነቀቁ
ይመስለኛል ከወንዶች ይልቅ። አንዳንዴ ወንዶች ሲናገሩ የማይባል ነገር ሲናገሩ
ይታያሉ፤ መድረክ ላይ እዛ ቦታ ላይ መነገር የሌለበት ነገር ሁላ ወጣ ብለው ሲናገሩ
የምንሰማበት ጊዜ አለ። ሴቶች ላይ እንደዚህ አይነት ነገር አላስታውልም። ለመማር
ብዙ ጊዜ ስለምከታተል ነው። ሴቶች ሲናገሩ ስብሰባ ላይ ብቻ ቅድም እንደነገርኳችሁ
ኤክስፒሪያንስ የለኝምና ጥሩ ተናጋሪን አደንቃለሁ። እንደዛ ለመሆንም ራሴን ሁሌ
አስተምራለሁና እከታተላለሁ። እና ብዙ ይመርጣሉ፣ጎኔ ስትናገር ባለፈው ማስታወሻ
ይዛ መሀል ላይ አነበበች ያም ፍርሃት ይመስለኛል እና ይመርጣሉ ጥንቁቅ ናቸው
የመረጡትን ቶፒክ ደግሞ በደንብ ያቀርባሉ።
እስካሁን በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ ስትሳተፉ ሰዎች ሃሳባቸውን ሲያቀርቡ ምን ለማለት
ፈልጎ ነው? ምን ለማለት ፈልጋ ነው? ያላችሁበትና ሳትረዱት የቀራችሁበት አጋጣሚ
የለም ወይ?
አገሬ፡- እኔ ኖየሰዎቹ እንትን ይመስለኛል ምንድን ነው የባክራውንድ ኖዎሎጂ፣ ሃሳብን
የመግለፅ ብቃት ሴትም ወንድም ማለት ነው። የመናገር እድሉን ካገኙ በኋላ አንዳንዴ
ሁለቱም ፆታዎች ላይ ከፍርሃት የተነሳ ሳይገልፁ የሚቀሩበት ጊዜ አለ። እድሉንም
አግኝተው እንትኑንም የመሳት ነገር ከርእሰ ጉዳዩ ወጥተው ሌላ እንትን ውስጥ ብዙ
ዋኝተው ምናምን በሰው ርዳታ የሚወጡም ሰዎች አሉ። እና በአግባቡ የሚገልፁ አሉ፣
የማይገልፁም ነገር አለ። እና ይሄ ከሴትነትና ከወንድነት ጋር ትንሽ በጣም በጥቂቱ
የሚያዝ ነው የሚመስለኝ። ከሰዎቹ አቅም ጋር ነው እኔ እንትን የምለው። አንድን
ሀሳብ በአጭሩ ግልፅ በሆነ መንገድ የማስቀመጥ ችሎታ ያላቸው ወንዶችም ሴቶችም
አሉ። በእርግጥ አማልተው የመሄድ ነገር ያላቸው ሴቶች ናቸው።
ካሳ፡- እኔ አገሬ ያለችው ይስማማኛል።... ንግግር ክህሎት ነው፣ አንደበት በተናገሩበት
ቁጥር የሚተባ መሳሪያ ነውና፣ ደጋግመው በተናገሩ ቁጥር የተሻለ ነገር ፐርፎርም
ያደርጋሉ። ተጠንቅቆ የማሰቡ ነገር ይኖራል። እኔ ጫና የሚያርፍባቸው ነው
የሚመስለኝ።
ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታ ከአቻዎቻቸው ጋር በሚያደርጉት የተግባቦት ሂደት ራሳቸውን/
ማንነታቸውን እንዴት ይገልፁታል?
ካሳ፡- ልዩነት ያለ ነው የሚመስለኝ ሊጠና የሚገባ ኤርያ ይመስለኛል። በእርግጥ አሁን
እያጠናሽው ነው። ሆስፒታል የገጠመኝን ልንገራችሁ።ዶክተር ነች ሌክቸኞፕ አንገቷ ላይ
አላደረገችም። ልብሱን ለብሰዋለች። ምንም ታግ የተደረገ ነገር የለም ዋይት ገዋኗ ላይ፤
ስለዚህ ሲስተር ይሏታል። በቃ ሲስተር እያላት ሰርቭ አድርጋው ጨረሰች። ምንም
አልነገረችውም እኔ ሲስተር አልባልም ዶር. ነኝ ምናምን አላለችውም። እኔ መግለፅ
ያለብኝ ቦታ ላይ ምናልባት የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ሌክቸረር እንደሆንክ እገልፃለሁ።
አሁን ባለሁበት ሁኔታ ለምሳሌ የውስጥ ግንኙነት ዳይሬክተር ነኝ ብየ እገልፃለሁ።
የሚገለፅበት ቦታ ላይ ወይም በመግለፄ ምናልባት ላገኘው የምችለው አንድ ነገር አለ
ብየ የማምን ከሆነ እገልፃለሁ። ይሄን ለማድረግ ምንም ወደኋላ አልልም። ምናልባት
ግን በምትይው አይነት መንገድ ያሉበት ሁኔታ ያላቸውን ነገር ለመግለፅ የሚቸገሩ
ይመስለኛል። በጣም እንትን የመሆን ነገር፣ ኦቨር ሞደስት የመሆን ነገር ሴቶች ላይ ጋ

ያለ ይመስለኛል።ወንዱ ሲሆን ራሱን አጋኖ ሁላ ይናገራል። ግን አጋኖ መናገር ሳይሆን
አክቿለ ያሉበትን አችቭ ያደረጉትን ነገር የያዙትን ቦታ ምናምን መግለፅ ያስፈልጋል።
አለሙ፡- እውነት ግን አይመስለኝም እኔ እንትን ነው፣ የት ላይ ናቸው የት አከባቢ
ቢሆኑ ወንዶቹም ሴቶቹም ራሳቸውን በደንብ ይገልፃሉ። ከነርስነት ይልቅ ዶክተርነት
የበለጠ የሚያስከብር ከሆነ ዶክተር መሆኗን ብትገልፅ፣ ጃንተር ነኝ ማለትን ወንዱም
ሴቱም ሪስቶርት ያደርገዋል። እዚህ በፊት የነበረ ሰው ዲን ነኝ ይል ነበር ከተማ ላይ።
ተማሪዎች ሁሉ ዲን ነበር የሚሉት።
ካሳ፡- እዚህ ጋ ጋሽ አለሙ ለምሳሌ እዚሁ የሰማሁት እከሌ ብሎ በስሙ ጠርቶት ዶር
እኮ ነኝ ያገኘሁትን ፒኤችዲ የት ጣልከው ብሎ ሪአክት ያደረገ አይነት ሰው አለ። ግን
ደግሞ ሜዲካል ፕራክሽነር ነች ዶር ነች ዶር ባለማለቱ አትሊስት አላስተካከለችውም።
እና በሁለቱ መካከል ራስን ከማሳወቅ አኳያ ከፍተኛ ልዩነት አለ ብየ ነው የማምነው።
ከበደ፡- ራስን ማስተዋወቅ ይሄን ሰርቼ ይሄን አድርጌ ማለት እንትን መጥፎ
አይመስለኝም። አግባብነት ባለው መንገድ ከሄደ ትምህር ከሆነ ምሳሌ ከሆነ። ችግሩ ግን
አንዳንዴ ከዛ ይወጣል። ምንድን ነው ራስን ከፍ አድርጎ ለማሳየት የሚደረጉ አይነት
ሙከራዎች ወይም እዛ ውስጥ አንድ እንትን የሚል ነገር ካለ ያችን አድቫንቴጅ
ለመጠቀም። እዛ እዛ ጋ ሲገባ ከእንትን ውጭ የሚሄድ ይመስለኛል። ምናልባትም ትንሽ
ይከብዳል። ከኮሚኒኬሽም እንትን ራቅ የሚል ነገር ነው የሚመስለኝ። እና እንዲህ
አይነት ሰዎች አሉ ምናልባትም ብዙጊዜ በወንዶች ላይ ሊስተጋባ ይችላል ከሴቶች
ይልቅ። ያልሰሩቱን ሰራሁ ማለት፣ ትንሽ የሰሯትን ነገር ከፍ የማድረግ፣ ሴሎች ላይ
ሰልጠን ብሎ መታየት የመሳሰሉት ነገሮች እኔ እንዲያውም አቮይድ አደርጋለሁ።
ብዙዎች አሉ። አሁን በቀደም ቢሮ ቁጭ ብየ ማታ ስሰራ አንዱ መጣ ማታ መብራት
ይበራል የእኔ አንድ ተኩል ምናምን አካባቢ ምሽት ላይ ማለት ነው። እና ቀጥታ ቢሮ
ገባ ኢንተርኔት አለ ወይ አለኝ አይ የለም አልኩት አልነበረም እሱም ኢንተርኔት፣ እና
ያችን ያዘና ጋሽ ከበደ እስከ አምስት ሰዓት ድረስ ነው የምቆየሁ እንዲህ እንዲህ አይነት
ነገር እያደረግኩ ነው ምናምን አለኝ። መገለፅ የሌለበትን ነገር ማለት ነው። አንዴም
እንደዚሁ ያው ሰው በሌላ ጊዜ አጋጣሚ እንዲሁ እንዲያውም ከተሾ መጋር ስናወራ
እንደዚህ አደርጋለሁ፣ እንደዚህ አደርጋለሁ፣ እንደዚህ አደርጋለሁ አራት አምስት ነገር
አወራ። አንዱን መያዝ ነው የሚበጀው አልነው። ውጤታማ የምትሆነው አንዱን
ስትይዘው ነው እንጂ ከዛም ከዛም ስትነከር እኮ ትርጉም የለውም አይነት ነገር አልነው።
በእርግጥ ጥሩ ኤክስፐሪያንስ ከሆነና ለሌሎች የሚያስተምር ነገር ከሆነ ማንሳት አግባብ
ነው። እኔ አነሳለሁ ሁልጊዜ፤ በስብሰባ ላይ አግባብ መስሎ ከታየኝ አነሳለሁ። አላግባብ
ከተጠቀምንበት ጥሩ አይመስለኝም።
አገሬ፡- ራስን የመግለፅ ነገር ደረጃ ከወጣለት ትንሽ ላቅ የሚሉት ወንዶች ይመስለኛል።
እንደተባለው አንዳንዴም የማጋነን ነገር አለ። ግን እንደአጠቃላይ ስናየው በባህላችን
ብዙም አይበረታታም እንዲህ አይነት ነገር፣ ማለት ሰው ይናገርልህ እንጅ አንተ
ስለራስህ አትናገር የሚል አለ ማለት ትክክለና ጥቅሱን ባላገኘውም። ሴቶች ላይ በጣም
ውስን ነው። እንዲያውም እኔ አንድ ስብሰባ ላይ እንደዚህ ሴቶች ተሰባስበን እዛ ላይ
እንዲያው የሚያበረታታ ነገር አግኝቻለሁ። አሁን ከዛ ስብሰባ በኋላ አሁን ራሴን
እንደዚህ እሰራለሁ ለምሳሌ ባህል ማዕከል ላይ እሰራለሁ፣ ኤክስተርናል ኦፊስ
እሰራለሁ፣ ልጆን እከባከባለሁ፣ ባለቤቴን እንደዚህ እያልኩ መናገር ጀምሬያለሁ። ማለት
ፖቴንሻላችሁን ካላዩ ሰዎች አይገልፅችሁም የሚል መረጃ ስለተሰጠኝ ነው። እና ሴቶች
እንደዛ አይነት ነገር ላይ የማይናገሩት የባህሉ ነገር ስላለ፤ ወንዶችም አይናገሩም ግን
ሲጠቅም ስላዩት ከኤክስፒሪያንስ ምናምን ነገር የሚጠቀሙበት ይመስለኛል። እና በስራ
ቦታ ላይ ስለራሳቸው በመግለፅ ረገድ ወንዶች ከፍ ያለውን ቦታ ይይዛሉ። አንዳንድ ወጣ
ያሉ ሴቶችም እንደዚሁ ማለት ነው። ምሳሌ አሁን በጣም ደፍራ የምትናገር ሴት ካለች
ለዛ ቦታ ተታጫለች። ለምሳሌ አሁን እኔ ለኤክስተርናል ኦፊስ የታጨሁት እውነቱን
ለመናገር አንድ ቀን የዩኒቨርሲቲውን አስረኛ አመት ባህል መድረክ ስለመራሁ ነው።

ሌላ ምንም ታሪክ የለውም። አዊርነሱ ቢኖራቸው በተለይም ይገልፃሉ ብየ ነው
የማስበው፤ ወንዶች ያው ስላላቸው ነው የተሻለ ባህልንም ደፍረው የመናገር ነገር አለ
ወጣም ብለው እንግዲህ በጊዜ ሂደት ይሸፈናል።
ሳባ፡- ምናልባት ቁጥራችን ስላነሰ ይሆናል እንጅ አሉ እኔ ፐርሰናሊ የማውቃቸው
ሴቶችም አሉ። ምናልባት የማደንቃቸው መጥቀስ ካስፈለገ ..... ያለምንም ፍርሃት
ሳትሻማቀቅ እንዲህ አድርጌያለሁ ብላ ስትገልፅ ታዝቤያለሁ። እና ሁለቱም ይገልፃሉ
የሚል ሀሳብ ነው ያለኝ። ምናልባት ቁጥራችን ስላነሰ ግን ወንዶች በጣም የሚገልፁ
እየመሰለን እንዳይሆን።
መሰረት፡- ምናልባት የያዝኩት ቦታ ምን ያህል እኔ ራሴን እድገልፅ ያስገድደኛል
የሚለው ነገር አንድ ኦፊስ ላይ ቁጭ ብለሽ ያንን ኦፊስ እየመራሽ ስብሰባ ጠርተሽ
ብታወያይ መጀመሪያ ተሰብሳቢው ስለአንቺ ማንነት ማወቅ መቻል አለበት። ግን ትልቁ
ችግር በማንኛውም ስብሰባ ላይ ተነስቼ እኔ ስለራሴ ተናግሬ አላቅም። እንኳን አይደለም
ፖዝሽኔን ምናምን እና ሁሌም እንዲሁ ከሰዎች ጋር ስገናኝ ዝም ብየ ስሜን ነው
የማስተዋውቀው። ከዛ እንደማንኛውም ነው የምግባባው። ከዛ በሂደት ነው በጣም
ፈልገው ቆርቁረው ነው ማንነቴን የሚያውቁት እንጂ፤ የት እንደሆንኩ፣ ምን
እንደምሰራ፣ ምን እዳጠናሁ፣ ምን ልምድ እዳለኝ አያቁም ከእኔ በኩል አይነገራቸውም።
እና ያ ምናልባት ብዙ ጊዜ ያስጨንቀኛል ያን መናገር በራሱ፤ ለምን
እንደሚያሰውጨንቀኝ ባላቅም፣ እንደዛ ብየ ስናገር እኔ የናንተ የበላይ ነኝ ብየ ማስብ
ይመስለኛል። እና ለዛ እየተጨነኩ ብዙ ጊዜ አልናገርም። እና ብዙ ከተግባባን በኋላ
ቆይተው ቆይተው ማንነቴን ሲያውቁ ግን በጣ-ም ያቀርቡኛል፣ በጣም ይወዱኛል፣
በጣም ትልቅ ክብር ይሰጡኛል። ምናልባት እሱ እያበረታታኝ ይሁን አላቅም። አንዳንዴ
እንዲሁም ጉዳትም ያጋጥምሻል። በነገራችን ላይ ባለመናገርሽ። የሆነ ጉዞ ላይበ
የተፈጠረን ችግር ማንሳት እፈልጋለሁ።ለሆነ ጉዳይ ወደአዲስ አበባ እየሄድኩ ነበርና።
መኪና ውስጥ የነበረው ሾፌር ሰዎቹን ካራገፈ በኋላ ከእኔ ጋር ድርድር ማድረግ
ፈለገ። ማለት የማንኛውም የሴት ጥያቄ ማለት ነው። ከዛ የግድ አሁን ሊመጣ ነው
እንግዲህ መወሰን አለብኝ። ምክንያቱም እሱ መኪና ይዟል የት እንደሚወሰድኝ
አላቅም። ከዛ ራሴን መግለፅ እኔ የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ መምህር ነኝ፣ እንደዚህ
እንደዚህ አይነት ፖዝሽን አለኝ ብየ በዛ ማስራራት የሞከርኩበት ሁኔታ ነው ያለውና፣
ብዙ ጊዜ አለመግለፄ ማህበራዊ ህይወቴ ላይ የራሱ የሆነ ጥቅም ቢኖረውም፤ እሱን
አስቤው አላቅም በመሰረቱ፤ እንደዛ አሳይን ልደረግ እችላለሁ ብየ ማንነቴን ገልጬ
አላውቅም። አልፈልግም እንደዛ ማድረግለ። ምክንያቱም ትሰራለች ብሎ ካመነ ጓደኛየ
ሊገልፅልኝ ይችላል ፕሮፖዝ ሊያረገኝ ይችላል ብየ ነው ብዙ ጊዜ የማስበው። ከዛ አንፃር
ይመስለኛል እኔ አልናገርም።
አለሙ፡- እርግጠኛ ነኝ አሁን አንቺ የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ እንደዚህ ነኝ ምናምን
ስትይው ሰውየው
መሰረት፡- አዎ ሳልጨርሰው፤ በጣም ደነገጠ ሰውርኣት ያዘ። እና ቢያንስ
የማርፍባቸው ዘመዶቼ ስልክ ደውየላቸዋለሁ፣ ከዛ ውሰደኝና ያንተን ስልክ እንቀያየርና
ከዛ በኋላ ከእነሱ በኋላ ከተዋወኩ በኋላ መጥቼ አብረን እንወጣለን አልኩት። ከዛ በኋላ
እቤት አደረሰኝ እቃየን አደረስኩና በል ቻው...

ከርዕሰ ጉዳዩ(ከአጀንዳው) የሚወጡ እነማናቸው?

ካሳ፡-ሞደስቲ የኢትዮጵያ ካልቸር ነው። ቅድም ጥሩየም አንስተዋለች፤ ጋሽ ከበደም፣
ስለራስ መናገር እንደነጌቲቭ እንድ ትክክለኛ እንዳልሆነ ነገር አድርገን ስለን ነው
ያደግነው። ግን አሁን ሽህ ምናምን ሰው ባለበት ግቢ ውስጥ ራሴ ስለራሴ ...እንዴ እኔን
የሚያሳውቅ ነገር እኔ ካላልኩ፣ አገሬን የሚሳውቅ ነገር አገሬ ካላለች፣ ውብነሽን
የ-ሚያሳውቅ ነገር ውብነሽ ካላለች ሀው ካን እንዴት አድርጎ ነው ሰው ሌላው ሰው
ሊያቀኝ በቅርብ ሊመሰክርልኝ ይችላል የሚባለው በጣም ጥቂት ሰዎች ከአንቺ በጣም
የሚቀርቡሽ ሁለት ሶስት ሰዎች። ምናልባት ከራሳቸው ነገር የሚተርፋቸው ጊዜ

ካልሆነ ለዛም በጣም ከወደዱሽ። አዘር ዋይዝ ግን በሚያውቁሽ መልኩ የሚያውቁትን
ነገር ይዘው ይቆያሉ እንጅ አንቺን ፕሮፓጌት የሚያደርጉ አይመስለኝም።። የሞደስቲው
ልክ በጣም ከመጠን ያለፈ ነው የሚመስለኝ። ይህ ደግሞ የጎዳን ነገር አለ ብየ ነው
የማስበው። ጎድቶናል ብየ የማስበው ምንድነው እኛ ልንሰራ የምንችለውን ነገር
ባላማሳወቃችን ምክንያት፣ ባለመናገራችን ምክንያት ምናልባት በማይሆኑ ሰዎች እጅ
ላይ ስራው ይወድቃል። ጥሩየ በጣም በሰላ መልኩ የምትሰራው ነገር ካሳ ለይ ይወድቅና
ስራው ተልኮስኩሶ ይቀራል። ምናልባት ያ ውሳኔ የተወሰነው ጥሩየ ስላልታወቀች ነው።
እና በጣም ሞደስቲ ከልክ አልፏል። ወንዶችም ጋ አለ ግን አሁን ያነሳነውን የባህል
ጣጣ ምናምን አብረን ደምረን ስናየው ሴቶች ላይ በጣም የዞረ ድምሩ ይበዛል።

የቡድን ተኮር ቃለመጠይቅ ምላሽ
የመለያ ቁጥር፡- ቡተቃ 202

ሰዓት፡ 8፡00 — 10፡00
ቦታ፡- C-28
ቀን፡- 7/03/2005

1. ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታ ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር በሚያደርጉት የተግባቦት ሂደት ሀሳባቸውን እንዴት ይገልፃሉ?

1.1 በስብሰባ ወቅት ከመናገራችሁ በፊት ምን ቅድመ ዝግጅት ታደርጋላችሁ?

1. ህይወት፡ ስብሰባ ላይ እንዲህ እላለሁ ብየ ቀድሜ ተዘጋጅቼ አላውቅም፡፡ ግን እዛው ስብሰባ
2. ላይ ምናልባት እንድናገር የሚስገድደኝ ነገር ከተፈጠረ የምጠቀምባቸውን ቋንቋዎች እንዴት
3. መጠቀም እንዳለብኝ፣ ይሄኛውን እንዴት ብናገር አሳማኝ በሆነ መንገድ አቀርበዋለሁ ብየ
4. እዘጋጃለሁ፡፡
5. ቢንያም፡ እኔ ሁለት ነገሮች ነው የማደርገው፡፡ ለምሳሌ በዲፓርትመንት ስብሰባ ሲኖር
6. ምንድን ነው የስብሰባውን ዋና አላማ አረጋግጣለሁ፡፡ ግን ፓብሊክ ስብሰባ ሲኖር ምን
7. ማድረግና መደረግ አለበት የሚል ነገር ሲኖር እዘጋጃለሁ፡፡ የስብሰባው አይነት ይወስነኛል፡፡
8. ኤፍሬም፡ ብዙ አልዘጋጅም፡፡ ግን ስብሰባ መኖሩን አውቃለሁ፡፡ ስብሰባው መደበኛ መሆኑን
9. ካወኩ ምን ምን መናገር እንዳለብኝ፣ ሰው ማስቀየም እንደሌለብኝ አስባለሁ፡፡ ስብሰባ
10. እየተካሄደ ያ ሰው ስብሰባው ላይ ያለው ሰው በሙሉ ማለት ነው በተለይ እኔ ከመናገሬ
11. በፊት ሀሳብ የሚሰጠውን ሰው በደንብ እከታተለዋለሁ፡፡ ማዳመጥ አለብኝ ጥያቄ ጠይቆ
12. ከሆነ፣ መልሶ ከሆነ፣ የሆነ መልዕክት አስተላልፎ ከሆነ፣ በደንብ እንትን ካላልኩ በስተቀር
13. ካልገባኝ ደፍሬ አልናገርም፡፡ መጀመሪያ ከእኔ በፊት የተናገረው ሰውየ ወይም ደግሞ እኔ
14. እንድናገር የሚጠበቅብኝ ነገር በደንብ አዳምጬ ነው የምናገረው፡፡
15. ከፍያለው፡ በየትኛውም ስብሰባ ይሁን አንድም ሰው የምናገርበት ከሆነ እና በስብሰባ
16. ፎርም የምሰበሰብ ከሆነ እዘጋጃለሁ፡፡ መጀመሪያ ማለት ነው፡፡ ከዛ ሰው ጋር ምን መነጋገር
17. አለብኝ፣ ምንድን ነው የማወራው፣ ምን ሊያነሳ ይችላል፣ ይህን ስል እንዲህ ሊል ይችላል
18. እሰከሚለው ድረስ አስባለሁ፡፡ ትንሽም ትልቅም ስብሰባ ቢሆን፡፡ የጊዜ ማጠር እንጂ ዝግጅቱ
19. ተመሳሳይ ነው፡፡ ለአንድ ግለሰብም ብዙም ቢሆን፡፡ ከዛ ባሻገር ደግሞ ማጠቃለያ፣ ምናምን
20. እንትኖች አሉ፡፡ ያራሱ ፈዞች አሉ፡፡ ግን ለእነዛ ሁላ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ምን
21. ላደርግ እንደምችል ቀድሜ ነው የማስበው፡፡
22. እየሩስ፡ እኔ ግን ተቃራኒ ነገር ነው፡፡ ማለት እኔ ስብሰባን እንደስራ ስራየ አድግሬ
23. አልወስደውም፡፡ ይህን ያህል አልጨናነቅበትም፡፡ በዛው ሰኣት አጀንዳዎቹን ካወኩ በኋላ
24. መናገር ካለብኝ እናገራለሁ፡፡ አጀንዳዎቹን ቀድሜ ካወኩ ምን አይነት ሀሳብ ባቀርብ ብየ
25. ትንሽ ላስብ እችላለሁ፡፡ ግን ያልተነካ ጉዳይ አለ ብየ ካሰብኩ እዛው ጋ ነው እንትን የምለው
26. እንጂ እንዲህ ወደ ውስጥ ገብቼ እንደስራ አድርጌ አላየውም፡፡ ሰብሳቢም ብሆን
27. አጀንዳዎቹን ይገፍ እሄዳለሁ በቃ እዛው ነው ልንነጋገርበት የምንችለው እንጂ ቀድሜ እንትን
28. አልልም፡፡
29. ከፍያለው፡ ሰብሳቢም ከሆነች በኋላ ምንም ዝግጅት አይጠይቀንም አለች፡፡ እንዴት ነው
30. አጀንዳ ብቻ ይዛ የምትሄደው?
31. እየሩስ፡ አይ እንደ አንተ እንደሰብሳቢ ሆኘ እከሌ እንትን ቢናገር ይህንን ቢያስብ ምን ልለው
32. እችላለሁ ብየ አላስብም፡፡
33. ከፍያለው፡ ስብሰባ ማለት ምን ማለት ነው ራሱ? ስብሰባ ማለት እኮ የሰው አካል ነው፡፡

34. እንደተራ ነገር አታይውም።
35. እየሩስ፡ አንተ እኮ በጣም ስራ አድርገህ ተጨናነክ እኮ።
36. ኤፍሬም፡ አይ አልጨናነቅም ብለሻል ቅድም። ግን እኮ የሚያጨናንቁ ስብሰባዎችም አሉ።
37. ከፍያለው፡ ለምሳሌ ያህል መምህራን ስብሰባ አለ። ባለፈው ሃላፊዎች የሚመሩት ስብሰባ
38. ማለት ነው። ለምሳሌ ያንን ስብሰባ ምሪ ብትባይ እና የሆነ ነገር ቢልሽ...
39. እየሩስ፡ (ጣልቃ በመግባት) እንደ እሱ አይነት ልምድ ስለሌለኝ እስካሁን ባለኝ የዲፓርትመንት
40. ሃላፊነት ሰብስቤ አውቃለሁ። ግን እንዲህ እከሌ ይህን ቢያነሳብኝ ምናምን ብየ ከፍያለው
41. እንዳለው አልጨናነቅም።
42. ከፍያለው፡ የኮርስ ክፍፍል ነው ወይስ ስብሰባ?
43. እየሩስ፡ አይደለም! ስብሰባ
44. ከፍያለው፡ አጀንዳዎች ተይዘው?
45. እየሩስ፡ አዎ። እንጂ አንተ እንዳልከው ይህን ሀሳብ ቢነሱ ምን ልላቸው እችላለሁ ብየ ራሴን
46. እንትን አልልም፡፤ እዛው ጋ ሲናገሩ አጀንዳውን መሰረት አድርጌ ከዛ ሁሉም ሀሳብ
47. ይመጣል። የዛን ሰኣት ነው ምን ማለት እንዳለብን የማስበው እንጂ ይህን ሳቀርብ ይህንን
48. ቢሉ ብየ ካልኩሌት አድርጌ እንትን ብየ አልሄድም።
49. ህይወት፡ በእኔ በኩል መቼውን ጊዜ ቢሆን ስብሰባ ከመግባቴ በፊት ምን እናገራለሁ ብየ
50. አስቤ አላውቅም። ግን ጥያቄውን እኔ እንደተረዳሁት እዛ ስብሰባ ቦታ ላይ ሆነሽ የሆነ ሀሳብ
51. ቀርቦ መናገር ብትፈልጊ ምን ታደርጊያለሽ? ዝም ብለሽ እንደመጣልሽ ንግግር ታደርጊያለሽ
52. ወይ? ቅድሚያ ዝግጅት ታደርጊለሽ ወይ ከመናገርሽ በፊት? የሚለውን መሰለኝ።
53. እየሩስ፡ በጣም ካለኝ ባህሪ ቀድሜ ብዙ ሰዎች እንዲናገሩ እንትን እላለሁ። ማለት ቶሎ
54. ለመናገር አልሞክርም።
55. ከፍያለው፡ ሰብሳቢ ሆንሽ እንበልና ጥያቄ አነሳን። ጥያቄውን እንዴት አድርገሽ ነው
56. የምትመልሽው?
57. እየሩስ፡ ቀድሜ ተዘጋጅቼ አልመጣም። ማለት ማን እንዲህ ሊል ይችላል ብየ አስቤ
58. አልመጣም ነው አባባሉ ገብቶሃል?
59. ከፍያለው፡ ለምሳሌ ሂሩት ወደዚህ ስትመጣ ምን ልታደርግ እንደምትችል ካላሰበች ይህን
60. ስብሰባ መምራት አትችልም። እነዚህን አጀንዳዎች በደንብ ማወቅ መቻል አለባት።
61. እየሩስ፡ እሱማ አጀንዳውንማ ሰብሳቢ ሆኜ ማወቅ አለብኝ። ግን አንተ ያልከው በጣም
62. ወደውስጥ ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ ገባህበት። እንደዚህ አይነት ሃሳብ እንኳ ቢቀርብ ከጀርባ
63. ሄጀ ነው የማስበው ስትል እኔ ያን ያህል አጀንዳው ምን እንደሆነ ከማወቅ ባለፈ አላሰብም።
ቆስቋሽ ጥያቄ፡- ለምሳሌ ከከፍያለው አንድ ሰው ሲናገር በቀጥታ የሚያቀርበውን ሀሳቡን ብቻ አይደለም
64. የሚረዳው። ከጀርባ ምን ደብቅ አላማ ሊኖረው ይችላል? የሚል ነገር አስቦ ያንንም መሰረት
65. አድርጎ ምላሽ ይሰጣል። አንቺ አሁን ካዳመጥሽ በኋላ ከዛ የሆነ ቦታ ላይ ሃሳብ መስጠት
66. ስትፈልጊ ሀሳብሽን በቀጥታ ከማቅረብሽ በፊት ምን ታደርጊለሽ?
67. ከፍያለው፡ ሂሩት ላይ ለመጨመር ለምሳሌ አንድ ሰው ያነሳው ሃሳብ ስህተት ቢሆን፣ አይ
68. አንተ ያነሳኸው ሃሳብ ስህተት ነው ትይዋለሽ ወይስ ምንድን ነው የምትይው?
69. እየሩስ፡ አይ እንደዛ አይነት ኢሞሽናል ምላሽ አይኖረኝም። እኔ እንዲያውም ካለኝ ባህሪ
70. ምንድን ነው ብዙ ሰዎች እስኪናገሩ ቀድሜ አልናገርም። ሌላው ቀርቶ ሃሳብ እንኳ ቢኖረኝ
71. በሌሎች ካልቀረበ ነው መጨረሻ ላይ የማቀርበው። ብዙ ማለት የራሴ ባህሪ ነውና። እንዲህ
72. ደግሞ በቀጥታ ስሜታዊ ሆኖ ምላሽ የመስጠት እንትን የለኝም።
73. ኤፍሬም፡ ስብሰባ ላይ እንደስብሰባውና እንደሰብሳቢው ነው። እኔ ከመናገሬ በፊት ብዙ ነገር
74. ነው የማስበው። አሁን ለምሳሌ ከፍያለው ሲሰበስበኝና የዩኒቨርሲቲው ምክትል ፕሬዚዳንት
75. ሲሰበስበኝ አንድ አይነት አይደለም ያለን እንትን። አሁን ምክትል ፕሬዚዳንቱ ፊት የሆነ
76. ነገር የሚያስቀይም ነገር ብናገር ብየ ይቅርታ ሊደረግልን እንደማይችል አስባለሁ። ከፍያለው
77. ጋ የምናገረው ነገር አስቀያሚ መስሎ ቢታየኝም ይቅርታ ይደረግልኛል ብየ ላስብ
78. እችላለሁ። እና የምትናገረውን ነገር ስትዘጋጅም እንኳ እንደሰብሳቢውና እንደሰብሰባው
79. ይለያያል።

80. ከፍያለው፡ እዚህ ለመጨመር ኤፍሬም ላይ እንደተሰብሳቢ ሆኝ መጀመሪያ የስብሰባውን
81. አጀንዳ ይገፎ አጀንዳው የሚመለከተኝ ከሆነና ብሳተፍ የማመጣው ወይም የምጨምረው ነገር
82. አለ ብየ የማስብ ከሆነ ብቻ ነው በትክክል የምከታተለው፡፡ አለበለዚያ ግን ምንም የማመጣው
83. ለውጥ የለም ብየ ካሰብኩ ሌላ ስራ እየሰራሁ ምንም ነገር ሳልከታተል እወጣለሁ፡፡ ግን
84. አጀንዳው እኔን የሚመለከት ከሆነ በጣም ነው የምሳተፈው፡፡ ቅድም ኤፍሬም እንዳለውም
85. ሰብሳቢው የዩኒቨርሲቲው ምክትል ፕረዚዳንት ቢሆን ... እንደዚህ ተባለ አለ ምናምን
86. እንዳይባል ጭምር ምንም እንኳ የምናገረው ነገር ትክክል ቢሆንም በሌሎች ዘንድ
87. የሚተረጎምበትን መንገድ ራሱ ትኩረት ሰጥቼ ነው የምናገረው፡፡
88. ቢንያም፡ አዎ ምናልባት ያነሱት ነገር ትክክል ቢሆንም ከስብሰባው በፊት ምንድን ነው
89. ቅድመ ዝግጅቱ ተሰብሳቢውን መለየትና ለዛ ስብሰባ የሚሆኑ ቃላትን ለመናገር መዘጋጀት
90. ነው፡፡

a. ለመናገር ስትፈልጉ ሌሎች የመናገር እድል እንዲሰጧችሁ ምን ታደርጋላችሁ?

91. ከፍያለው፡ አይ እኔ ብዙ ጊዜ የሚያጋጥመኝ ስለሆነ በተለይ አካዳሚክ ኮሚሽን ስንሰበሰብ፣
92. ሰብሳቢው ብዙ ጊዜ እኔን አያየኝም፡፡ የምቀመጠው ከሰብሳቢው ወደጎን ፀኩል በመሆኑ፡፡ እና
93. እሱ የሚያየው ፊት ለፊት የተቀመጠውን ብቻ ነው፡፤ እና ለመናገር ስፈልግ እጀን
94. አወጣለሁ፡፡ እጀን ሳላወጣ መናገር አልፈልግም፡፡ ግን ስለያየኝ ‹‹እእ...›› እላለሁ፡፡
95. ካልተሳካልኝ ግን መጨረሻ ላይ ጥልቅ ብዬ መግባት ነው፡፡ ሌላም እየተናገረ ቢሆን
96. እናገራለሁ ማለት እድሉ በትክክል የማይሰጠኝ መስሎ ከታየኝ፡፡
97. እየሩስ፡እንዳልኩሽ ብዙ አልሳተፍም፡፡ አንዳንዴ ስናገርም ጣልቃ ገብቼ አልናገርም፡፡መጀመሪያ
98. ሀሳቡ ተነስቶ ሁሉም ከተናገረ በኋላ ሀሳብ ካለኝ ቆይ እዚህ ጋ ምናምን እንዲህ ቢሆን ብየ
99. ነው የማወራው አንጂ ጣልቃ አልገባም፡፡ እኔ ኖርማሊ መናገር ፈልጌ ያጣሁበት ጊዜ የለም፡፡
100. እንዲውም ለምን አትናገሪም የሚለው ጥያቄ ነው ሁሌም ከጓደኞቼ የሚቀርብልኝ፡፡
101. ቢንያም፡ አሁን እዚህ በቅርብ ቀን የተደረገ ስብሰባ ነበር፡፡ ፕሮግራሙን የሚመራው
102. ሰው ሀሳብ ካለኝ ሌሎቹን አዳምጬ ከጨረሱ በኋላ ወደሌላ ከመሻገራቸው በፊት
103. ሀሳብ አለኝ እላለሁ እሰጣለሁ፡፡ ደግሞ ለመናገር ስራየ ብየ ካሰብኩ እናገራለሁ፡፡
104. ለመናገር መጀመሪያ የማደርገው ምንድን ነው በዛ ስብሰባ ላይ መናገር እንዳለብኝ
105. እርግጠና ከሆንኩኝ ሰብሳቢው ወይም ስብሰባውን የሚመሩት ሰዎች ሊያዩኝ
106. የሚችሉበት ቦታ በእነሱ ፊት ለፊት እቀመጣለሁ፡፡ ከተሳካልኝ ማለት ነው ከዛ እጀን
107. ላወጣ እችላለሁ፡፤ ነገሮች እነኚህን ሁሉ አድርጌ ሊሳኩልኝ ካልቻሉ ግን ሃሳቤን
108. በወረቀት ፅፌ እሰጣለሁ፡፡
109. ህይወት፡ ስብሰባ ላይ እኔ ከመናገር ዝምታን እመርጣለሁ፡፡ ግን የግድ ከሆነብኝ እና
110. የማልፈራ ከሆነ ያው እጀን አውጥቼ ሀሳቤን ለመግለፅ እሞክራለሁ፡፡
111. ኤፍሬም፡ እኔ በጣም ጠቃሚ ሃሳብ ነው ብየ ካሰብኩና ልናገረው የፈለኩት ነገር
112. ከሆነ ሰብሳቢው እንዲያየኝ ነው በመጀመሪያ፤ ካላየኝ ተሰብሳቢው እኮ አንዳንዴ
113. እዚህ ጋ እሱ ምናምን ሊል ችላል፡፡ ወይ ደግሞ ተቀድሜያለሁ ከሱ ቀጥሎ
114. አወጣለሁ ብሎ የማያወጣ ሊኖር ይችላል፡፡ በነገራችን ላይ አንዱ መንገድ ይሄ ነው፡፡
115. ሌላው ደግሞ በእጅ ምናምን አቴንሽን ካልሳብኩና እድሉ ሊሰጠን ነው ብየ ካላመንኩ
116. የሆነች ነገር ጀምሬ ‹‹ይሄ እኮ›› ስል እሽ ቀጥል ምናምን ትባላለህ፡፡ ዝም ብሎ ገብቶ
117. ማውራትም ነውር ነው፡፡ የሆነ ነገር ትጥልና ድምፅህን አሰምተህ ፀጥ ስትል ሰፍ
118. ብሎ ምን አልክ ስትባል ትቀጥላለህ፡፡

b. ሀሳባችሁን ሳትጨርሱ ወይም ሳትናገሩ ከስብሰባ ወጥታችሁ ታውቃላችሁ?

119. እየሩስ፡ ያው ሳልጨርስ ሳሆን ሳልናገር የምወጣባቸው ጊዜያት እጅግ ብዙ ናቸው፡፡
ቆስቋሽ ጥያቄ፡ ለምን?
120. እየሩስ፡ አትሞስፔሩ ካልተመቸኝ፡፡ በጣም የሚያናድድ ነገር ካየሁኝ፣ በጣም ተናድጄ
121. ሳልናገር እወጣለሁ፡፤ ምክንያቱም ብናገር ስሜታዊ ሆኝ በጣም መጥፎ ነገር
122. ከምናገር ብዬ ስለማስብ፡፡

ቆስቋሽ ጥያቄ፡ በመናደድሽ ብቻ ነው ሳትናገሪ የምትወጭው?

123. እየሩስ፡ አም በስብሰባው ላይ ሌሎች ‹‹ሚስትሪት›› ሲደረጉ ካየሁኝ እናደዳለሁ፤፤ ከዛ
124. ሳልናገር እወጣለሁ፡፡
125. ከፍያለው፡ ሀሳብ ከጀመርኩን እጨርሳለሁ፡፡ ግን አንዳንዴ ሳልናገር እወጣለሁ፡፡
126. ምክንያቱ እየሩስ እንዳለችው ‹‹አትሞስፔሩ›› ብቻ ሰይሆን በመናገሬ የማመጣው
127. ነገር ከሌለ አልናገርም፡፡ ለምሳሌ ተወስኖ ያለቀለትን ነገር ተወያዩበት ተብሎ
128. ሲመጣ ብሞት አልናገርም ዝም እንዳልኩ እወጣለሁ፡፡ ምክንያቱም በመናገሬ ሌላ
129. ትርጉም ወደእኔ ከማምጣቱ ባሻገር የምጨምረው አንድም ነገር አይኖርም፡፡ ስለዚህ
130. ከመናገር ዝም ይሻላል፡፡
131. ህይወት፡ ለመናገር ስለምፈራ ብዙ ጊዜ አልናገርም፡፡ መናገር እየፈለኩ ራሱ ግን
132. ብናገር ምን ይሉኛል የሚል ነገር አስብና ብዙ ጊዜ ሳልናገር እወጣለሁ፡፡ ግን በኋላ
133. እናደዳለሁ፡፤ ማለት እኔ የነበረኝን ሀሳብ ሌሎች ካቀረቡት ጋር እኔ የነበረኝ ሀሳብ
134. የተሻለ እንደሆነ ስረዳ ምነው በተናገርኩ ብየ እናደዳለሁ፡፡ በእርግጥ የስብሰባው
135. አይነት ይወስነዋል፡፡
136. ከፍያለው፡ (ጣልቃ በመግባት) ድሮ ነው አሁን?
137. ህይወት፡ አሁን እንጂ እዚህ ግቢ፡፡ ከዛ ሳልጨርስ ደግሞ ከፍርሃት ጋር በተያያዘ
138. ሀሳቤን እንደዚህ እገልፃለሁ ብዬ ብዙ ሃሳብ እያለኝ ግን በፍርሃት ምክንያት አሳጥሬ
139. አቀርበዋለሁ ሳልጨርስ ማለት ነው፡፡
140. ቢንያም፡ ስብሰባ ውስጥ አንድ ሰው ሃሳብ ሲያነሳ አንዳንድ ሀቅ ወይም መረጃዎች
141. በዛ ሰው ትንሽ ሳስተው ሲቀርቡ ያንን ነገር ለማስተካከል ጥረት አደርጋለሁ፡፡
142. ካልተሳካልኝና የመናገር እድሉን ካላገኘሁ ያንን ሰው ከስብሰባው ውጭ ፈልጌ
143. በማነጋገር መረጃውን ለመንገር እሞክራለሁ፡፡
144. ኤፍሬም፡ ስብሰባው ይወስናል፡፡ ትልቅ ስብሰባ ሲሆን እና ትንሽ ስብሰባ ሲሆን አንድ
145. አይደለም፡፡ አሁን ለምሳሌ ኮሚሽን ስብሰባ ላይ መቶ ጊዜ ሊሰጠን ይችላል፡፡ እድል
146. እንደፈለኩ ነው ተሳታፊው ትንሽ ስለሆነ፡፡ ሀሳብም መስጠት ከፈለኩ እጄን
147. አወጣለሁ ወይም ጥልቅ ብየ ገብቼም ቢሆን የመናገር እድሉ ሰፊ ነው፡፡ ትልቅ
148. ስብሰባ ላይ ግን እድሉ ቶሎ ስለማይደርሰኝ ስለዚህ በዛች እድል ብዙ ነገር ለመናገር
149. እዘጋጅና ከዛ ንግግሩን ከጀመርኩ በኋላ ሀሳቡ ይጠፋብኝና ትንሽ ነገር ብየ ነው
150. የምወጣው፡፡ ሳልጨርስ የምወጣው ትልቅ ስብሰባ ላይ ብቻ ነው፡፡ ትንሽ ስብሰባ ላይ
151. ሀሳቡ ሳልጨርስ የምወታበት እንትን ብዙም አይደለም፡፡

1.4 የሴቶችና የወንዶች ንግግር በስብሰባ ወቅት ልዩነት አለው ብላችሁ ታስባላችሁ? ከሆነ እንዴት? (የቋንቋ አጠቃቀማቸው ምን ይመስላል)

152. ቢንያም፡ ወንዶችና ሴቶች አንድ ላይ በተሰበሰቡበት ሁኔታ በቁጥርም እኩል
153. ቢሆኑም እንኳ ሴቶች ወንዶችን ‹‹ዶሚኔት›› አድርገው ያንን የሚሰራ የሚተገብር
154. ስራ ሰርተው ወንዶችን በንግግርም፣ በማሳመንም፣ በተፅዕኖ ስር አድርገው
155. የመምራት አቅም ችሎታ ነገሮችን የማሳመን ነገር አላቸው ብየ አላምንም፡፡ ነገር
156. ግን የመብት እኩልነት ላይ ወይም እንደዚህ ቀለል አድርገሽ ከፖለቲካ ከምናምን
157. አቀላቅለሽ ተናገሩ ብትይ በጣም ልዩ እንደሆኑ ልንግርሽ እችላለሁ፡፡ ነገር ግን እዚሁ
158. አካዳሚካሊ ግን እስካሁን ከተገነዘብኩት ነገር ካጋጠመኝ አጋጣሚ የሴት
159. ‹‹ዶሚኔሽን›› አላየሁም፡፡
160. ከፍያለው፡ እስካሁን የተመለከትኩት ምንድን ነው የሚናገረው ሰው ወንድ ከሆነ
161. ባአብዛኛው በንግግሩ ከበስተጀርባ ሊያስተላልፍ የሚፈልገው መልዕክት አለ፡፡ ሴቶች
162. ግን ሲናገሩ በተግባር ያለውን ነገር ነው ሲያቀርቡ የሚታየው ተናጋሪዎቹ
163. ጥቂትም ቢሆኑ፡፡ ወንዶች ግን ሲናገሩ ከንግግራቸው በስተጀርባ ማስተላለፍ
164. የሚፈልጉት መልዕክት አለ፡፡ በኋላም ከስብሰባው ሲወጣ ደግሞ እንደዚህ አልኩ
165. እንደዚህ እንትን አልኩን አይነት ነገር ማለት ነው፡፡ ይህን ልዩነት ተመልክቻለሁ፡፡

ቆስቋሽ ጥያቄ፡ ከበስተጀርባ የሚስተላልፉት መልዕክት ለምሳሌ ምን አይነት ነው?

166. ከፍያለው፡ ለምሳሌ ሰብሳቢው እኔ ሆኝ ተሰብስበው አይ ከአንተ የበለጠ እንትን አለኝ
167. ብሎ ይናገራል ቶኑ ማለት ነው፡፡ በንግግሩ ውስጥ ይሄ ተቃውሞ አለ፡፡ እንዴ አንተ
168. እኮ እኔን ልትሰበስበኝ አትችልም የሚል እንትን አለ፡፡ ምክንያቱም የሚናገረው ነገር
169. ከእንትኑ ጋር የማይገናኝ ስለሚሆን ማለት ነው፡፡ ያለውን ነገር የለም ይላል፤
170. የተሰራውን ስራ ወደታች የማድረግ ነገር፤ ያልተሰሩትን ስራዎች በቃ ይሄ ተሰርቶ
171. የለ እንዴ ብሎ የግጥላት ነገር ማለት ነው፡፡ የእዚህ ኢምፕልኬሽን ደግሞ ይህን
172. መስራት፣ ማወቅ ይጠበቅብህ ነበር፤ አልሰራህም ማለት ነው፡፡ ስለዚህ እሱ ካልሰራ
173. ሌላው ትክክል ነው ብሎ የማያምን፡፡ እሱ ነው ማለት ነው ያንን መስራት
174. የሚችለው፡፡ ሴቶቹ ግን መፍትሄ ላይ ነው የሚያተኩሩት፡፤ ልክ ሲናገሩ ይሄ ነገር
175. አልሆነም ግን እንዲህ ቢሆን ኖሮ ብለው ይናገራሉ፡፡ የወንዶቹ ግን እንደዚህ አይነት
176. ነገር ላይ አያተኩሩም፡፡ በኋላ የመፍትሄ ሀሳብ ተብለው ተጠይቀው ካልሆነ በስተቀር
177. የመፍትሄ ነገር እንትን የማለት ነገር ብዙም እኔ ካየሁት አንባር ማለት ነው፡፡
178. እየሩስ፡ ሀሳባቸውን ሲገልፁ ሴቶችና ወንዶች በአንድ አይነት መንገድ አይደለም
179. የሚገልፁት፡፡ የመሳተፍ እንትናቸው እንዳለ ሆኖ፡፡ ለምሳሌ አሁን ባለፈው ስብሰባ
180. ላይ ሴቶችም ነበሩ፡፡ ግን ሴቶችስ የት አሉ? የሴቶች ተሳትፎ ምናምን ተብሎ
181. ተጠይቆ ነው የተናገሩት የተወሰኑ ሴቶች፡፡ እና ሲናገሩ ሳይ ወንዶቹ ለምሳሌ ትዝ
182. ይላችሁ እንደሆነ እንዴት እንደዚህ ይሆናል? ይህ እኮ ራሳችሁ የመጣችሁት ችግር
183. ነው ምናምን ብለው ስሜታዊ ሆነው ነበር ሲናገሩ የነበረ፡፡ ሴቶቹ ግን እንደዚያ
184. አይነት ባህሪ አልነበራቸውም ለስለስ ብለው ነበር የሚናገሩት፡፡ እና ቅድም
185. እንደተባለው ወደፊት መሆን የሚገባውን መፍትሄ በማቅረብ ነበር የተናገሩት፡፡ እና
186. እኔ የተረዳሁት ምንድን ነው ወንዶቹ ከበስተጀርባው መቆጣታቸውን ለማሳወቅ
187. የሞከሩበት ሁኔታ ነበር በዚያ ንግግር፡፡
188. ቢንያም፡ ወንዶች ይህን አናደርግም፣ አናቀርብም በማለት ተቃውሞ ያማቅረብ ባህሪ
189. አላቸው፡፡ አሁን እሱ ባነሳው ስብሰባ ላይ የሴቶቹ ቁጥር ብዙ ነበር፡፡ ግን ምንድን
190. ነው ሪፖርት አቅርቡ ሲባል ወንዶች ገና ከመጀመሪያው ‹‹ኖ›› ማለት ጀመሩ፡፡ ይሄ
191. ሀሳብ እንደዚህ ማለት ነው ብለው ተከራከሩ፡፡ ሌላው ሴቶቹ ሪፖርት አቅርቡ ሲባሉ
192. በትንሹ አጠር አጠር አድርገው ምንም ‹‹ሪአክት›› ሳያደርጉ ተናገሩ፡፡ ሌላው ያላቸው
193. ልዩነት ሴቶች ይመስለኛል፣ይሆናል፣ እንደዚህ ቢደረግ መልካም ነው በማለት
194. ማለሳለሻ ቃላትን ይጠቀማሉ፡፡ ወንዶቹ ግን በሚያቀርቡት ጉዳይ ላይ‹‹ነው›› የሚል
195. ማስረገጫ ይዘው ይነሳሉ፡፡ እንደዚህ እንደዚህ መደረግ የለበትም፣ ይሄ ስህተት ነው
196. ይላሉ፡፡ ሴቶች ግን ከዛች ባውንደሪ እንዳይወጡ ጥንቃቄ ሲደያርጉ አያለሁ፡፡
197. ምናልባት ከአቅም ጋር የሚገናኝ፣ ከአስተዳደግ፣ ከባህል ጋር የሚገናኙ ነገሮች
198. በውስጣቸው ሊኖርባቸው ይችላሉ የሚል ግምት አለኝ፡፡
199. አበባ፡ እኔ ከማየውም ሴቶች ብዙም ተሳታፊ አይደሉም፡፡
200. እየሩስ፡ ሴቶች ነፃ ሁነው መደበኛ ባልሆነ ስብሰባ ሃሳብን ለመግለጽ ወይም ነገሮችን
201. ለማቅረብ ሲፈለግ ለብቻቸው ሲሰበሰቡ ጥሩም ይሆናል እርግጠኛም ነኝ፡፡ እንደዛ
202. መደበኛ በሆኑ ስብሰባዎች የማይናገሩትን ኢመደበኛ ስብሰባ ከሆነ ሊናገሩ ይችላሉ፡፡
203. ካለኝ ልምድ ነው፡፡ ለብቻችን እንሰባሰባለን አንዳንዴ መሪ የምሆንበት ወቅትም
204. ኣለኝ፡፡ ፕሮሲጀራል የሆነ ነገር አይደለም፡፡ እና ደስ ይላል፡፡ እና ያ ሁኔታ በጣም
205. ይመቸኛል እኔ፡፡ ...እናም ኢንፎርማል በሆኑ ስብሰባዎች ከሴቶች ጋር መሆን ደስ
206. ይለኛል፡፡

1.5 ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታ ከአቻዎቻቸው ጋር በሚያደርጉት የተግባቦት ሂደት ሃሳባቸውን አድማጭ በሚረዳ ሁኔታ ባግባቡ ይገልፃሉን?

207. ኤፍሬም፡ ይሄ ከፆታ ግር የሚገናኝ አይመስለኝም፡፡ የሰው የግል የንግግር ችሎታ
208. ነው፡፡ አንዳንድ ሰው ሃሳቡ እለው ወንድም ሆነ ሴት ሀሳቡን በትክክል መግለፅ
209. የማይችል ሰው አለ፡፡
210. ህይወት፡ ኤፍሬም ያላውን እጋራለሁ፡፡ እንደሰው ባህሪ ይለያል፡፡ በደንቡ የመግለጽ

211. ችሎታ ያላቸው ሴቶች ይኖራሉ። ሀሳብን ለመግለፅ ብዙ ጊዜ ይቸገራሉ ብየ
212. አላስብም።
213. ቢንያም፡ የታዘብኩት ነገር ብዙ ጊዜ ስብሰባዎችን ላይ ሴቶች ተለምነው ነው
214. የሚናገሩት። አንዳንድ ጊዜ በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ የወንዶችና የሴቶች ቁጥር
215. ሲታይ ብዙ ሴቶች እያሉ ግን ቁጥራቸው ትንሽ የሆነ ወንዶች እጅ በማውጣት
216. ይናገራሉ። ይህን በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ አጢኛለሁ። ከዛ በኋላ ደግሞ ምንድን
217. ነው ሴቶች እጅ ሲያወጡ ምናልባት ትንሽ በተለያዩ ኮካሪኩላር ስራዎች ላይ
218. ተሳትፎና ልምድ ያላቸው ሴቶች ሲናገሩ በምንም ነገር ውስጥ ሳይገቡ ወይም
219. ያልተሳተፉ ሴቶች ምንም አይናገሩም። አዳምጠው ነው በብዛት የሚወጡት። ስለዚህ
220. በትላልቅ ስብሰባዎች ላይ የሚታየው ነገር ሴቶች ወደማዳመጡ የዘነብላሉ የሚል
221. ግምት አለኝ። ሴቶች እስቲ እባካችሁ፣ ተለምነው፣ ተፈልገው ነው ከተናገሩም
222. የሚናገሩት።

ቆስቋሽ ጥያቄ፡ ከቋንቋ ችሎታ አንፃርስ?

223. ቢንያም፡ ከቋንቋ ችሎታ አንፃር በጣም የሚገርመው ነገር ሴቶች በጣም ጎበዝ
224. ናቸው። በሚያወጡት ሃሳብና በቋንቋ ችሎታቸው ከሴቶች የሚወጣው ማህበራዊ
225. ጉዳይንም አይበታለሁ። ወንዶች ላይ ደግሞ ስመጣ ምንድን ነው ተፅዕኖ ወይም
226. በንግግር ወይም በኢንፎርሜሽን የማሳመን እዛ ጋ ያለው ድባብ ረገጥ አድርጎ
227. የመያዝ። ስለዚህ የሚሆነው ነገር ከሚቀርበው ተግባር ጋር ወንዶቹ ሃሳቡ ጥሩም
228. ይሁን አይሁን በተፅዕኖ አሳማኝ እንዲሆን ለማድረግ ይሞክራሉ። ሴቶቹ ግን
229. እንደወንዶቹ ረገጥ ያለ ባይሆንም ነገር ግን የቋንቋ ችሎታቸውን ስንመለከት ሴቶቹ
230. በጣም ተናጋሪዎች ናቸው። ሞር ደግሞ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ያተኩራሉ።
231. ከማያቸው ማለት ነው። ሌላው ወንዶች ተቀባይነትና አቴንሽን ማግኘት ይፈልጋሉ።
232. ሴቶች ላይ ግን ለምትናገረው ነገር ምንድን ነው የሚያስከትለው ተፅዕኖ ሊሆን
233. ይችላል ወይም የሚስቡት ነገር ወይም ርዕሰ ጉዳዩ ሴቶችን ሊጠቅም ይችላል ሊጎዳ
234. ይችላል ወደማህበራዊ ጉዳይ ላይ ማተኮራቸው ለማሳመንም ተፅዕኖ ለማድረግም
235. አይሞክሩም። በተለይ በሴቶች ላይ የማየው ነገር ተመልሰው ጥያቄ ሲጠይቁ አያለሁ
236. እንደዚህ ለማለት ፈልጌ ነው። ወንዶች ግን ተከራክረው ለማሳመን ይሞክራሉ።
237. ሴቶች ግን የቋንቋ ችሎታ ቢኖራቸውም አንድ ጉዳይ ሲነሳ ተከራክረው ተፅዕኖ
238. አያደርጉም።
239. ከፍያለው፡ በሴቶችና በወንዶች መካከል በማስረዳት ችሎታ ልዩነት አለ ብየ
240. አላስብም። ስልችት የሚደርግ ሲጨበጨብለት ሞራል የተሰጠው የሚመስላቸው
241. ወንዶች አሉ። አሁን እዚህ እንኳ በፋካሊቲ ደረጃ ስንት ልምድ አለ። እየተጨበጨበ
242. ሞራል የተሰጠው እየመሰለው የሚቀጥል። በተሳትፎ ደረጃ ስንመለከተው አንዳንድ
243. ወንዶች አሉ ስብሰባ ገብተው ካልተናገሩ የሚሞቱ የሚመስላቸው አሉ። ምን
244. እንደሚናገር እንኳ የማውቅ አሳጥረው ሲባል ጨርሻለሁ ይላል ከዛ የሚቀጥል።
245. እንደዛ አይነት ወንዶች አሉ። ሴቶች ላይ ይህንን አላየሁም። ማለት ሴቶች
246. መጀመሪያውኑ አይናገሩም፤ ከተናገሩ ደግሞ በጣም የተመጠነ ነው። እሱም የራሱ
247. ፋክተር ሊኖረው ይችላል ለምን ተመጠነ የሚለው። ለምሳሌ ቅድም ኤፍሬም
248. ትልልቅ ስብሰባዎች ላይ ንግግሬን አሳጥራለሁ አለ ስለሚጠፋው እና አነሱም
249. እንግዲህ ጠፍቷቸው ሊሆን ይችላል። ግን ይህ ሌላ ጥናት የሚያስፈልገው
250. ይሆናል። ግን ከንግግር አንፃር ሃሳባቸውን በደንብ የሚገልጹ ወንዶችም ሴቶችም
251. አሉ። በደንብ የማይገልጹ ሴቶች አላጋጠሙኝም። በደንብ የማይገልጹ ወንዶች ግን
252. ሞልተዋል ያየሁት ማለት ነው።
253. እየሩስ፡ ከዚህ ግቢ ካላን ልምድ ሴቶች እንግዲህ ለመናገር ጉትጎታ ሊፈልጉ ይችሉ
254. ይሆናል። ከማየው ነገር ነው። ትልልቅ ስብሰባዎች ላይ እስቲ ለሴቶች እድል ልስጥ
255. ተናገሩ በሚባሉበት ሰዓት የሚናገሩት ነገር እኔ በጣም ነው የሚያስደስተን። ማለት
256. ካለኝ ልምድ ንግግራቸው አጭርም ቢሆን በጣም አሪፍ ነው። አሪፍ ሀሳብ፣ በጣም

257. በአጭር አገላለጽ ያቀርባሉ፡፡ ወንዶች በጣም አሪፍ አሪፍ ሀሳብ የሚያቀርቡም አሉ፡፡
258. ግን ከፍያለውም እንዳለው በጣም የሚያሰለች ሌላው ቀርቶ ሀሳቡ ምን ላማስተላለፍ
259. ነው የፈለገው የሚባል በጣም ከመንዛዛቱ የተነሳ የሚከብድ አለ፡፡ እንግዲህ ሴቶችም
260. ወንዶችም በጥሩ ሁኔታ ሀሳባቸውን የሚገልጹ አሉ፡፡ ግን ሴቶች ላይ ድክመት
261. አላየሁም፡፡ ምናልባት ከማሳጠር የዘለለ፡፡ ማሳጠሩ ደግሞ ሃሳባቸውን በትክክል
262. እንዲገልጹ የረዳቸው ይመስለኛል፡፡ በሚያቀርቡበት እትን ሀሳባቸውን ሳልረዳ
263. ያለፍኩት ጊዜ የለኝም፡፡ ወንዶች ግን ብዙ ጊዜ ማለት እችላለሁ ምን ለማለት ፈልጎ
264. ነው ዙሪያ ጥምጥም ሄዶብኝ ሀሳቡን ሳልይዘው ሃሳቡን ሳልረዳው የምቀርበት ጊዜ
265. አለ፡፡
266. ኤፍሬም፡ ወንዶች ያንዛዛሉ ሴቶች ያሳጥራሉ ብሎ መደምደም ተገቢ አይደለም፡፤
267. ምክንያቱም ወንዶች ብዙ ናቸው በቁጥር ሴቶች ትንሽ ናቸው፡፡
268. ከፍያለው፡ ከተናገሩት ሴቶችና ወንዶች ብቻ ማለት ነው፡፡ እስካሁን ባለው
269. ባየነው በተለያዩ ቦታዎችና ጊዜያት ከተናገሩት ወንዶችና ሴቶች ማለቴ ነው፡፡

1.6 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በተግባቦት ሂደት ሀሳባቸውን ለመግለጽ ተፅዕኖ አድራጊ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?

270. ቢንያም፡ ምክንያቱ ምንድን ነው የሚለውን ነገር ሳይ አንዳንድ ጊዜ ከፊዚካል
271. አፒራንስ ማለት ምንድን ነው ይሄ ከጉልበት ጋር የተያያዘ ነገር ከአቅም ጋር
272. የተያያዘ ነገር እንደዚህ አይነት ነገር ሊሆን ይችላል ብየ አስባለሁ፡፡ ሁለተኛው ነገር
273. ምንድን ነው ከዚህ ወጥቼ እዛ ከተማ ቦታ ስንገናኝ ምን እባላለሁ፣ ስራ ላይ፣
274. በአካባቢየ ምን እሆናልሁ ብሎ የማሰብ ይመስለኛል፡፡ ግን የአብዛኛዎቹ ሴቶች
275. ንግግር ደስ የሚለኝ ጉዳይ ምንድን ነው ባህላችን መሰረት የሚያደርግ ነገር
276. ስለሚናገሩ የሚያስከፋ ነገር ብዙም በሴቶች ላይ ስብሰባ ላይ አይቼ አላውቅም፡፡
277. ከፍያለው፡ እንዳልከው ሲናገሩ ባህላቸውን መሰረት በማድረግ ለስለስ ብለው ይናገሩ
278. እንጅ መጀመሪያውኑ ለመናገር የሚቸገሩበት ምክንያት ግን በባህሉ ምክንያት ነው፡፡
279. በባህላችን ተናጋሪ ሴት ጎበዝ አትባልም ወረኛ ምላሳም ነው፡፡ ምን ይች ደግሞ...
280. ነው የሚባለው፡፡ እና እንደኔ ዋናው ተፅዕኖው ባህል ነው፡፡
281. ቆስቋሽ ጥያቄ፡ በዚህ ደረጃም ባህል ተፅዕኖ ያደርጋል ማለት ነው
282. ከፍያለው፡ እኔ እንዲያውም እስካሁን አላሰብኩትም ነበር አሁን እዚህ ቁጭ ብየ
283. ሳስበው ባህሉ በጣም ተፅዕኖ እያደረገብን ያለው በእኛም ጭምር ነው፡፡ ለምን
284. መሰለሽ ተፅዕኖ አድራጊዎቹ እኛ ነን፡፡ አሁን ባለንበት ሁኔታ ሴቶች ሲናገሩ መቼ
285. እናደንቃቸዋለን፡፡ እንዲያውም የሚገርመው በጣም ሰማርት የሆነ ሀሳብ ተናግረው
286. እንዴት ተናገረች የሚለውን ነው የምናስበው እንጅ አናበረታታም፡፡ እኔም አድርጌ
287. አላውቅም ሰው ሲያደርግም አላይም፡፡ ዝም ተብሎ ለተሳትፎ ያህል ሴቶች ተሳተፉ
288. ሲባል ነው የምሰማው ሁልጊዜ እንጅ ከእነሱ ጠቃሚ ነገር ይኖራል እስቲ ሲባል
289. አላውቅም፡፡ ዘመኑ የሴቶች ተሳትፎ ስለሚባል ብቻ ነው የሚመስለኝ፡፡
290. አበባ፡- እኔ ከራሴም ስነሳ ዋናው ተፅእኖ አድራጊው ፍራቻ ነው፡፡ አንድም የእኔ
291. ሀሳብ ጠቃሚ አይደለም ይህን ብናገር ምን አስተዋጽኦ አለው ብሎ መፍራት ወይም
292. በራስ ያለመተማመን ልንለው አንችላለን፡፡ ሌላው ግን ትልቁ ነገር ከተናገርሽ በኋላ
293. ሰው ምን ይለኛል አይን አውጣ ፈጣጣ ምናምን ብለሽ ትፈሪያለሽ፡፡ ይህ ደግሞ
294. በኑሮሽ፣ በማህበራዊ ግንኙነትሽ በሞራልሽም ላይ ተፅዕኖ ስለሚያመጣ እና ከአንቺ
295. የሚጠበቀው ቫሊው የሚሰጥሽ ጭምት ዝምተኛ የሚለው ነገር ስለሆነ ዝምተኛ
296. መሆንን ነው ትክክል አድርገሽ የምትወስጅው፡፡
297. ህይወት፡(ጣልቃ በመግባት)፡ የሚገርመው እኛ ራሱ የምትናገር ሴት ካለች እኮ ጎበዝ
298. አንላትም ከእሷ ጋርም ጓደኛ መሆን ብዙም...ምክንያቱም እኔም ተናጋሪ የምባል
299. ነው የሚመስለኝ፡፡

ቆስቋሽ ጥያቄ፡ እና መማር ባህሪ ለውጥ አያመጣም ማለት ነው?

300. ህይወት፡ ያመጣሽ መማር ለውጥ ያመጣል እንደዛ ማለት በጣም ከባድ ነው፡፡ ግን

301. ትምህርት ለውጥ የሚያመጣው ብቻውን አይደለም ባህሉን ሁሉም መስበር ሲችል
302. ነው። ባህል ደግሞ በግማሽ አይደለም። ሴቶቹ ከባህል ጭፅእኖ ለመውጣት ፍላጎትና
303. አቅሙ ቢኖራቸው ያንን ባህል ወንዶቹ ማህበረሰቡ የተጠመደበትና እሴቱ ከሆነ
304. ከማህበረሰቡ ተገሎ መኖር የሚፈልግ ማንም ስለሌለ መማርሽ በማወቅሽ አይ እኔ
305. ከማለት ውጭ ጥቅም የሌለው ይሆናል። ግን ምን አይቻለሁ መሰለሽ ከመማራቸው
306. ጋር የተለያዩ ልምዶችን ያካበቱ ሴቶች በጣም ደፋር ናቸው በማንኛውም ነገር ይህን
307. ተመልክቻለሁ።
308. ኤፍሬም፡ እኔም በዚህ በጣም እስማማለሁ። እንዴ በተለይ ወጣት ከሆነች እኮ ይች
309. ምላሳም ይችንማ አልችላትም ሊል ይችላል ለጋብቻ የሚመርጣት እንኳ...
310. ምክንያቱም መናገርን እንደ ጥሩ ነገር አይደለም ይዘነው የመጣን።

2 ሴቶችና ወንዶች በተግባቦት ወቅት ራሳቸውን እንዴት ይገልፁ? (ሃሳባቸውን በመግለጽ ሂደት ራሳቸውን እንዴት ይገልፁ? ያስተዋውቃሉ?)

311. ከፍያለው፡ ለምሳሌ ስብሰባ አጀንዳ ይቀርባል ዝርዝር ጉዳዮችም ይቀርቡና ከዛ
312. ጥያቄ፣ ሃሳብ ያላችሁ ሲባል አንዱ እጁን አንስቶ እኔ እንትን ላይ ያየሁት፣
313. ያነበብኩት መፅሀፍ፣ ከእንትና ጋር የመገናኘት እድል አግኝቼ ነበር እና፣ እንትን
314. በነበርኩበት ሰላት ስሰራበት የነበረው፣ እንትን ላይ ሃላፊ ሆኘ ስሰራ እያለሁ፣
315. የሚሉ ወንዶች ብዙ ናቸው። የዚህ ኢምፕልኬሽን ምንድን ነው ለእኔ እዚህ እዚህ
316. ቦታ አለሁና ይህን እንትን ስጡኝ፣ እኔ ነኝ የምችለው፣ የማውቀው የሚል ነው።
317. አሁን የምልሽ ሁሉም ማለቴ አይደለም። አንዳንዶች ደግሞ መስጠት ስለፈለገው
318. አስተያየት ብቻ የሚሰጡ አሉ። ይህ ነገር ግን በአብዛኛው ሴቶች ላይ አጋጥሞኝ
319. አያውቅም።
320. ቢንያም፡ ምናልባት እሱ ያለው ጉዳይ እንዳለ ሆኖ ወንዶች እንደዚህ ነን ብለው
321. የሚያቀርቡ ወንዶች በብዛት አሉ። እንዲያውም እንደዚ የሚያደርጉት ጉዳይ ምንድን
322. ነው ሀሳባቸውን የሚያቀርቡት ጉዳይ ለማስረጃ ጭምር ይጠቀሙበታል። ያንን
323. ማቅረባቸው ክፋት የለውም፡፤ ምክንያቱም ተጨማሪ ልምዳቸውን በማቅረብ በዛውም
324. ራሳቸውን የሚያስተዋውቁበት መንገድ ነው። ሴቶች ስለራሳቸው ልምድ አይናገሩም
325. ማለት አይቻልም። ለምሳሌ እኔ በነበርኩበት ዩኒቨርሲቲ የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር
326. ሆና ተሹማ እሷ የምታቀርባቸው ጉዳዮች በፊት ምን ምን ቦታዎች ሰርታ ምን ደረጃ
327. እንደደረሱ ማስረጃ እየጠቀሰች እንዲውም ዩኒቨርሲቲውን የሰራተኞች አስተዳደር
328. የቀየረችበት ሁኔታ ነበር። ስለዚህ ሴቶችም ይናገራሉ። የማይናገሩ ካሉ አብዛኛዎቹ
329. በአስተዳደር ላይ ወይ በመምራት ላይ ያልነበሩ ልምድ የሌላቸው ናቸው ብየ
330. አምናለሁ።

ቆስቋሽ ጥያቄ፡ የአስተዳደር ልምድ ስለሌለ አይናገሩም። ግን ከሙያቸው አንፃር ወንዶች እና ሴቶች መካከል በሙያ እንዲህ ነኝ፣ ይህን አውቃለሁ ብሎ ከመግለፅ አንፃርስ?

331. ቢንያም፡ እሱ አሁን ቁጥራቸው እኩል እኩል እናድርገውና ሶስት ሴት ሶስት ወንድ
332. በፕሮግራም ስብሰባ ውስጥ ቢኖሩ ለምሳሌ እኔ ፕሮግራም ላይ ያየሁት ነገር
333. ከመቀሌ፣ከጅማ፣ ከአዲስ አበባ፣ ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲዎች የመጡ ናቸው
334. መምህራኖቹ። ወንዶቹ እኔ እንደዚህ እንደዚህ የሚባል ኮርስ ወስጃለሁ። ስለዚህ
335. ይሄ በዚህ መልኩ ቢሰራ፣ ያኛው ደግሞ እኔ እንደዚህ ይላል። ስለዚህ ራሳቸውንና
336. በሙያቸው ያላቸውን ችሎታ ከማስተዋወቁ ላይ ሴቶች ወደኋላ ይላሉ በአብዛኛው።
337. አንዳንድ ሴቶች ግን ልምድ ያላቸው ራሳቸውን ይገልፃሉ በጣም ያስተዋውቃሉ።
338. ያንን ማስተዋወቃቸው ምንድን ነው በሚሰሩ ስራዎች ላይ የራሳቸውን ምላሽ
339. የሚሰጡበት ሁኔታ አለ። ግን የሌላው ተፅዕኖ ወይም ጫና ጠንከር ካለ ግን
340. ወደወንዱ ሀሳብ የመመለስና የመንሸራተት ነገር፣ አቋም ይዘው ራሳቸውን ገንጥለው
341. ለብቻቸው አይሄዱም።
342. ህይወት፡ አብዛኛውን ጊዜ ወንዶች እንዲታወቅላቸው የሚፈልጉትን እኔ እንደዚህ
343. አደረኩ፣እንደዚህ ሰራሁ፣ እኔ እንደዚህ ቦታ ላይ ነው ያለሁት፣ እውቀት ደረጃቸውን

344. ለማሳወቅ ጥረት የሚያደርጉ ብዙ ናቸው። ሌላው ደግሞ ሴቶችን ስንመለከት
345. አብዛኛዎቹ ስራቸውን በመስራት ሰው በራሱ እንዲያውቅላቸው የሚፈልጉ አሉ።
346. አንዳንዶች ደግሞ ከስንት አንድ ቢሆኑመ ራሳቸውን እንዲህ ነን ብለው
347. በማስተዋወቅ እወቁኝ እወቁኝ የሚሉ አሉ። ብዙ ጊዜ እንደነዚህ አይነቶቹ የተናቁ
348. አይነት መስሎ ከታያቸው ማንነታቸውን ለማሳወቅና ለማሳየት ስለራሳቸው
349. ኮስተር ብለው ይገልፃሉ።
350. ኤፍሬም፡ ከዚህ ላይ የያታ ልዩነት ብዙም አይታየኝም። ምክንያቱም ማንም ሰው
351. ተቀባይነትን ማግኘት ይፈልጋልና ማንኛውንም አጋጣሚ ይጠቀማል። ያንን ከንግግሩ
352. ጋር አገናኝቶ የመናገር ሁኔታ አለ። ምናልባት ሴቶች የሚመሩት ስብሰባ ወይም
353. ስልጣን ላይ ያሉ ሴቶች ያልገጠመን ሊሆን ይችላል እንጅ ሳስበው ሁለቱም ጋር
354. አለ ብየ አስባለሁ። ምናልባት ልዩነት ያለው ብየ የማስበው ምንድን ነው ወንዶቹ
355. ከአጀንዳው ጋር የማይገናኝ ከሚናገሩት ነገር ጋር የማይገናኝ ነገር ሁሉ ሲያቀርቡ
356. ይታያሉ ሆን ብለው ራሳቸውን ለማሳየት ሲሉ። እንደምሳሌ አስመስለው በዛ
357. እንግዲህ ራሳቸውን ከመግለፅ አንፃር ከሴቶቹ ይበልጣሉ።
358. እየሩስ፡ ምናልባት በስራ ቦታ ስለሚል እለት ተዕለት ባለን ግንኙነትም ራሳቸውን
359. መግለፅ በስልጣን እንደዚህ ስላሉ ራሳቸውን ከማሳየት አንፃር ነው ግን ለመደምደም
360. አይደለም። ወንዶች ላይ ይህ ነገር ይጎላል ብየ ነው የማስበው። ማለት
361. አብረሽ ስትሰሪ የነበረ ሰው ሙሉበሙሉ እስከማታውቂው ደረጃ እንዴ ምናምን
362. ብለሽ አስክትገረሚ ድረስ ሁላ ራሱን ቀይሮ የምታገኝበት አጋጣሚ አለ።
363. እስኪገርምሽ ማለት ነው። እና ስልጣናቸውን ለማሳወቅ የሚፈለግበትን ሁኔታ
364. ሲፈጥሩ ታያለሽ። ያ ደግሞ ብዙ ጊዜ የሚታየው እኔ ካለኝ ልምድ ወንዶች
365. ላይ ነው። ግን ያንን የሆነበት ምናልባት አሁን ባለው ሁኔታ ብዙም ሴቶች ስልጣን
366. ላይ የሚወጡ ስለሌሉ ይመስላል። ካሉት የዩኒቨርሲቲው ስልጣኖች
367. ከዲፓርትመንት ኃላፊነት ጀምሮ እስከላይ ስንሄድ ብዙም የለም ከዛ ከዛ ነገር ስናየው
368. ካለውም አንፃር ግን ሳየው ወንዶች ላይ ብዙ ጎልቶ ነው የማየው። የሙያ ብቃት
369. ለማሳየት ብዙም በዚህ ዙሪያ እንኳን ስብሰባ ላይ ይታያል። ከአጀንዳ ውጭ ምን
370. አስፈለገ እዚህ ቦታ ላይ ሄዶ ደረገው ስራ እዚህ ጋ ለእኛ መግለጽ ለምን አስፈለገ
371. ብለን እስክንገረም ድረስ። ሌላው ቀርቶ ስብሰባውን የራሳቸው የግላቸው አድርገው
372. ስብሰባው እስኪያልቅ ድረስ እነሱ ብቻ እያወሩ ስብሰባዉን ሙሉ በሙሉ
373. ተቆጣጥረውት የሚውሉ አሉ። እነዛ ሰዎች ደግሞ ሁሌም ነው ይህን
374. የሚያደርጉት። ሴቶች ግን እንዳልከው በዛው በአጀንዳው ዙርያ ብቻ ነው
375. የሚያወሩት። ስለራሳቸው ስላላቸው እንትን የሚገልጹበት ነገር የለም እና ወንዶች
376. ላይ ካለኝ ልምድ ብዙ አያለሁ እነዚህን ነገሮች።

ቆስቋሽ ጥያቄ፡ የትኛው ያታ ነው ስብሰባን የመቆጣጠር ሁኔታ የሚያሳይ?

377. ከፍያለው፡ ቅደም ካልኩት ነገር ጋር የሚገናኝ ነገር ነው። አዎ አሉ እድል
378. ተሰጥቶት በተደጋጋሚ የሚያወጣ ስብሰባውን መቆጣጠር የሚፈልግ። እኔ ብቻ ነኝ
379. ተናጋሪ የሚል ረጅም ሰዓት የሚወስዱ አሉ የተወሰኑ በየስብሰባው ይታያሉ። ግን
380. ይህ የሚወስነው በስብሰባው ነው። ሰብሳቢው ሌሎች ተናጋሪዎች እያሉ ለአንድ ሰው
381. ሁለት ጊዜ ልሰጥ አልችልም ብሎ ሊመጣ ይችላል። ግን አንዳንድ ስብሰባዎች ላይ
382. ሰብሳቢው ራሱ ስብሰባውን የማይቆጣጠርበት መምራት የማይችልበት ሁኔታ አለ።
383. በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ተመሳሳይ ነገር በተለያዩ ሰዎች በተመሳሳይ ሰዎች ሁላ
384. ሊሰማ ይችላል። እና ሰብሳቢው ይወስነዋል።
385. ከፍያለው፡ ወንዶች ናቸው። ግን ከቁጥራቸው አንፃር ትንሽ ስለሆኑ በእንደዚህ
386. አይነት ነገር በተደጋጋሚ እንትን ውስጥ አይገቡም። ግን ወንዶች ሲቀመጡ ራሱ
387. ክፊት ይቀመጣል። ከነ ይታያል እጁን ያወጣል ዶሚናንት ለመሆን ይችላል።

ቆስቋሽ ጥያቄ፡ ምን አይነት ዘዴ ይጠቀማሉ? ይህን ሁሉ አድርገው እድል ቢያጡ።

388. ከፍያላው፡ ቦጣም ባተደጋጋሚ እጅ ያወጣሉ። በተለይ ደግሞ ሌሎች ተናጋሪዎች

389. ለምሳሌ አጀንዳው የማይስማማኝ ከሆነ ብየሻለሁ ላልናገር እችላለሁ፡፡ ብዙ ሰዎች
390. እንደዚህ ናቸው ብየ አስባለሁ፡፡ አጀንዳው በቃ ተስማማውም አልተስማማውም
391. ደግሞ እጅ የሚያወጣ አለ፡፡ ብቻ መናገር አለብኝ ብሎ የሚስብ ማለት ነው፡፡ እና
392. ይሄ ግን የሚስተዋለው ወንዶች ላይ ነው ብየ አምናለሁ፡፡
393. እየሩስ፡ ስብሰባውን ለመቆጣጠር አስቦ ያድርገው አያድርገው አለውቅም ግን አሉ
394. እንደዚህ አይነት ሰዎች፡፡ በትልቅ ስብሰባዎችም ላይ በቃ የታወቁ እከሌ እሱን
395. ምናምን ነው የሚባለው፡፡ ስናየው ራሱ ዛሬማ ምናምን የሚባሉ ሰዎች አሉ፡፡
396. ኤፍሬም፡ (ጣልቃ ገብቶ) አለቀልን ይባላሉ፡፡
397. እየሩስ፡ ግን አውቀውት ማለት ስብሰባውን ለመቆጣጠር አስበው ነው ወይስ
398. የሚለውን አላውቅም፡፡ አሉ! ወንዶች ላይ ሴቶች ላይ እንግዲህ ሴቶች አንዱ ነው
399. የሚናገሩት እኔ ካለኝ ልምድ፡፡አንዱ ሲናገሩም በጣም መጥነው ነው፡፡ ሁለት ዙር
400. የተናገረ ሰው እኔ አጋጥሞኝ አያውቅም በሴቶች፡፡

ቆስቋሽ ጥያቄ፡ ከአንቺ ልምድ አንፃር ስብሰባን ለመቆጣጠር ምን አይነት ስልት ይጠቀማሉ?

401. እየሩስ፡ በአካዳሚክ ኮሚሽን ስብሰባ ላይ እንዲውም አንድ ጊዜ አስተያየት ተሰቶኛል፡፡
402. ለምንድን ነው የማትሳተፊው ሲሉኝ ዶሚናንቶች አሉ ብያለሁ፡፡ እንግዲህ ሰው
403. አስቦበት እና ብዙ ጊዜ እኔ ብዙ አልናገርም ዶምኔትም የማድረግ ያህል ሳይሆን
404. ለተሳትፎም ያህል አልናገርም፡፡ ዝም ብሎም ይናገራል ሰው እድል ተሰጥቶትም
405. ላይሆን ይችላል፡፡ ቆይ እዚህ ጋ እንዴት ነው ብሎ ይናገራል፡፡
406. ኤፍሬም፡ አብዛኛው ሰው ሀሳብ ለመግለጽ ነው ወንዶችም ይሁኑ ሴቶች ስብሰባውን
407. ለሌላ አጀንዳ ለመጠቀም አይደለም፡፡ አሉ የተወሰኑ ሰዎች ስብሰባውን እንደጥሩ
408. አጋጣሚ ለመጠቀም አስበውበት ነው ሳያውቁ አይደለም፡፡ በዛ ስብሰባ ምክንያት
409. ተናገሪ መሆኑን ለማሳወቅ ከዛ በኋላ እንዲያውም አንዳንድ ሰዎች ምን
410. ብለው ያምናሉ ስብሰባ ላይ ብዙ በማውራት ምናምን መታየት አለ ከዛም
411. መታጨት አለ ለስልጣን እንደዛ ብለው የሚስቡ ሰዎች አሉ፡፡ ይሄ ደግሞ
412. የሚታየው ብዙ ጊዜ ወንዶቹ ጋ ነው፡፡ እኔ ሴቶቹ ጋ አላየሁም፡፡ ብዙ ጊዜ
413. ወንዶቹ እንደ ጥሩ አጋጣሚ ተጠቅመው እና ትኩረት ለማግኘት ሆን ብለው ስብሰባ
414. አለ ሲባል ቀድመው ነው የሚገኙት ከፊት ነው የሚቀመጡት የማይፈነቅሉት
415. ድንጋይ የለም በቃ የመናገር አጋጣሚውን ለማግኘት የተለያየ መንገድ ይጠቀማሉ፡፡
416. ሌላው ቀርቶ ሀሳብ ባይኖራቸውም የሆነ ነገር ለማለት እጃቸውን በተደጋጋሚ
417. ማውጣት በተለይ በትልልቅ ስብሰባ ላይ ዝም ብሎ ሀሳብ ባይኖረውም እድሉ
418. ከገባለት የሆነ ነገር ብሎ ቁጭ ይላል፡፡ እና ለመየት ብሎ የሚደርጉት ብዙ
419. ጊዜ ወንዶች ናቸው፡፡

ቆስቋሽ ጥያቄ፡ ስብሰባን የሚቆጣጠሩ (ዶሚናንት) የምንላቸው ሰዎች ከየታ አንፃር ወንዶች ናቸው ብላችኋል፡፡ ይህን የሚያደርጉት ከምን አንፃር ነው? (ሙያቸውን፣ስልጣናቸውን፣ ወይስ ጾታቸውን ነው መሰረት የሚደርጉት ?)

420. እየሩስ፡ ሰልጣን ለማሳየት ፈልጎ የሚንቀሳቀስ ሰው እኔ ብዙ አጋጥሞኛል፡፡ ማለት
421. ስልጣን ላይ ሲወጣ ኮምፕሊትሊ እንዴ እከሌ ነው እንዴ ከዚህ በፊት የማውቀው
422. ሰው ነው እስከምል ልገረምበት እችላለሁ፡፡ ያም የከፍያለውኝ ያው በወንዶች ነው
423. ቅድም እንዳልኩሽ፡፡ ስልጣን እንዲያውም በጣም ራስን ‹‹ፓርትሽን›› ፈጥረው
424. ለመሳየት የሚጠቀሙበት፡፡ ሙያቸውን ሳይሆን ስልጣናቸውን ተጠቅመው ክፍተት
425. መፍጠር ራሳቸውን ማሳየት የሚፈልጉ ብዙ ወንዶች አጋጥሞኛል፡፡ ቅድም
426. እንዳልኩሽ ያው ሴቶች ብዙም ስለሌሉ ስልጣን ላይ በእነሱ ማየት ላይቻል ይችላል፡፡
427. ግን ትንሽ ካለችን ካገኘኋት ልምድ ሴቶች እንደዚህ አይነት ብዙም አላየሁም፡፡ ግን
428. ወንዶች ላይ በጣም አለ፡፡

ቆስቋሽ ጥያቄ፡ እድሜስ? ለምሳሌ አንቺ ሰብሳቢ ስትሆኝ

429. እየሩስ፡ ለእነሱ ካለኝ ክብር አንፃር በጣም እጠነቀቃለሁ፡፡ በጣም ሀሳባቸውን
430. አቀበላለሁ፡፡ ትክክል እስከመሰለኝ ድረስ፡፡ ተፅዕኖ አለ ማለት ነው፡፡

ቆስቋሽ ጥያቄ፡ ያላመንሽበት ሀሳብ ቢቀርብ እድሜያቸው ተፅዕኖ ያደርግብሻል?
431. እየሩስ፡ አይ እቋቋማቸዋለሁ ግን እንደእድሜ እኩዮቼ ላይሆን ይችላል፡፡ ብዙ ገፍቼ
432. ላልናገር እችላለሁ ከእነሱ ጋር ስሆን፡፡ ግን በመጠኑ እንትን እላለሁ፡፡
433. ኤፍሬም፡ ስልጣን እያላቸው ግን ብዙም ልምድ እያላቸው ወይም አካብተው
434. ስብሰባውን መቆጣጠር አይደለም ስብሰባ ላይ የማይናገሩ አሉ፡፡ ስልጣን ከመፈለግ
435. አኳያ ስብሰባን እንደ አንድ አጋጣሚ አድርገው የሚወስዱ ጥቂት ሰዎች አሉ፡፡
436. ስለዚህ ስልጣን የማግኘት ወይም የማስጠበቂያ መንገድ አድርገው የሚያስቡ አሉ፡፡
437. ይህ ደግሞ ወንዶች ላይ አንጂ ሴቶች ላይ አይቼ አላውቅም፡፡
438. ቢንያም፡ በስብሰባው ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር ደጋግመው ይናገራሉ፡፡ተፅዕኖ
439. የሚያሳድረው በምን ምክንያት ነው የሚለው ሊያጠያይቀን ይችላል፡፡ ቢሆንም ግን
440. ስብሰባ በመቆጣጠር ለመታየትም የሚሞክሩት ወንዶች ናቸው፡፡ ስልጣንም
441. ለመፈለግ ሆነ ለማሳየት ሚሞክሩት ወንዶች ናቸው፡፡ ምን ይሰራሉ፣ እንዴት
442. ይሰራሉ፣ ምን አይነት አቅም አላቸው የሚለውን ለማሳየት፡፡ እንዲያውም እኔ ለዚህ
443. ባለፈው አመት አጠቃላይ የመምህራን ስብሰባ ጊዜ ታስታውሳላችሁ ፕሬዚዳንቱ
444. ምንድን ነው ያሉት ‹‹...በእያንዳንዱ ፕሮግራም እያንዳንዱ ሰው ምን አይነት
445. ‹‹ካሊቲ››እና ብቃት እንዳለው አናውቅም፡፤ ስለዚህ እንደዚህ ትልልቅ ስብሰባዎች
446. ሲኖሩ ፊታችሁን አስመቱ፡፡ ስለዚህ ሃሳብን በሃሳብ የማፍረስ፣ የመቃወም፣ ራሽናል
447. የማቅረብ ችሎታ ማን ነው ያለው ስለዚህ ማን ምን ነገር ሰርቷል የሚለውን
448. እናውቃለን፡፡ ስለዚህ አስፈላጊ ነው ከመቶ አምስት ሰው ቢፈለግ አምስት ሰው
449. ብቃት እንዳለው እንዴት ማረጋገጥ እችላለሁ፡፡ ስለዚህ ፊታችሁን አስመቱ››ሲሉ
450. በግልፅ አስታውሳለሁ፡፡ ስለዚህ ለዚህ ይመስለኛል በትልልቅ ስብሰባዎች ላይ ተፅዕኖ
451. የሚሳድሩት ወንዶች፡፡ ሴቶች ግን ችሎታውንና ብቃታቸውን የሚገልፅ ሀሳብ
452. አያቀርቡም፡፡ ለቀረበ ሀሳብም ረገጥ አድርገው ተፅዕኖ አድርገው ለአመራር ብቁ
453. መሆናቸውንም አያሳዩም፡፡

2.1 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ባተግባቦት ሂደት ማንነታቸውን ለመግለጽ ተፅዕኖ አድራጊ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?
454. ኤፍሬም፡ ራስን በመግለጽ ላይ ተፅዕኖ ያለባቸው በአብዛኛው ሴቶች ናቸው፡፡ ለዛም
455. ምክንያቱ የመጀመሪያው ባህል ይመስለኛል፡፡ ያው እኔ እንግዲህ ስለራስህ አወራህ
456. እንዳትሉኝ እንጅ ሙያየ ከባህል ጋር በመሆኑ ከአሁን በፊት የታዘብኩትን ብናገር
457. ለእሷ ይጠቅማታል ብየ ስላሰብኩ ነው፡፡ ያደግንበት ባህል ብቻ አይደለም ተፅዕኖ
458. የሚያደርገው፡፡ ከአደግን በኋላ ስራ ይዘን የምንኖርበት አካባቢ የስራ ቦታችን ራሱ
459. ተፅዕኖ ያደርግብናል፡፡ ለምሳሌ በእኛ ፋካሊቲ በጣም ምን ብየ ልንገራችሁ ቀልቃላ
460. ደፋር የምትባል ሴት በቢሮ ደረጃ ስትቀለቀል ስታወራ የምናያት ሴት በስብሰባ ላይ
461. ግን አንድም ቀን ስትናገር አናያትም በትምህርት ክፍል ስብሰባም ይሁን በፋካሊቲ፡፡
462. መቼም አንግዲህ እንደዚህ አይነት ሴቶች እንዳሉ እናውቃለን ግን በተፅዕኖ ካደጉት
463. ጋር ተመሳሳይ ነው ስናየው፡፡ ስለዚህ የሚኖሩበት ሁኔታ እንበለው ወይም አካባቢ
464. ተፅዕኖ ያደርግባቸዋል፡፡

ቆስቋሽ ጥያቄ፡ በማይናገሩ ወንዶችስ?
465. በነገራችን ላይ አሁን እኔ በማየው በአብዛኛው ዝም የሚሉት አንጋፋዎቹ ናቸው፡፡
466. እና ነገር ቢቃኝ ብሎ የመናቅ ወይም ራስን የማግለል ይመስላል፡፡ እድሜያችን እየገፋ
467. ሲሄድ እኮ እንደዝንጀሮ ያደርገናል ይባላል ብቸኛ መሆን ዝም ማለት በቃ እንደዛ
468. ይመስለኛል፡፡ አልፎ አልፎ ካልሆነ ሲናገሩ አላይም፡፡ በአብዛኛው መካከል ላይ ያሉት
469. ጎልማሶች ናቸው የሚናገሩት፡፡ ወጣቱም ባብዛኘው ተናጋሪ ነው ያው ንግግራቸው
470. በአብዛኘው ሃቃውሞ የበዛበት ነው እንጅ፡፡
471. ቢንያም፡ እኔ ቅድምም ተናግሬያለሁ ልምድ እና ከዚሁ ጋር ተያይዞ ደግሞ እድሜ
472. ይመስለኛል፡፡ በእድሜ የበሰሉ ሴቶች የተለያዩ ስራዎችን በመስራት በተለይ
473. በሃላፊነትም ይሁን በኮሚቴ ስራ ልምድ ካላቸው ራሳቸውን በዚህ ስሰራ ምናምን
474. እያሉ ይገልፃሉ አንደበተ ርዕቱም ናቸው፡፡ ከዚህ ውጭ ግን ልምድ ከሌለ ባህሉን

ሰብሮ የመውጣቱም ነገር አብሮ ስለሚስራቸው ተፅዕኖ ያደርግባቸዋል።
ህይወት፡ ሴቶች ጉራ ሳለሚመስላቸው አይናገሩም ባህሉ ትህትና የሚባል ነገር
ስላለው። ወንዶች ደግሞ ባህሉ ስለሚፈቅድላቸው መናገርን ይናገራሉ። እና
እንደተባለው ነው።
እየሩስ፦ ያው ነው የእኔም ሀሳብ ልምድና ባህል ነው። እምልሽ የመጣሽበት ባህል
ብቻ ሳይሆን የሚትሰሪበት ቦታም ብናገር ጓደኞቼ እንዲሁም አለቆቼ እንዲህ
ይሉኛል የሚለውም አንድ ትልቅ ተፅዕኖ ነው። ለተለያዩ የስራ ልምዶች ስትጋለጭና
ብዙ ነገር በውስጥሽ ስታካብች ሙሉ ስለምትሆኝና መቻልሽንም ደግሞ
ስለምታረጋግጭ ባህሉ ተፅዕኖ ማድረጉን ታስቆሚዋለሽ። ለምሳሌ እኔ የፕሮግራም
ተጠሪ ከመሆኔ በፊት እንኳ መናገር በጓደኞቼ ፊት መዜድ ሁሉ እፈራ ነበር።
አሁን ግን ስዜድም አልፈራም በትልልቅ ስብሰባዎች ላይ አልናገርም እንጅ እሱም
ቀስ ብሎ ይመጣል ብየ አስባለሁ በኮሚሽን ላይ ተናጋሪ ባልሆንም መናገር
ሲኖርብኝ እናገራለሁ። ለውጥ አለኝ ይህ ደግሞ የመጣው ለስራው ተጋላጭ ስሆን
የመጣ ነው።
ከፍያለው፡ ተብሏል። ትህትና ፣ ባህል፣ ልምድ ናቸው ሌላ የለም።

የቡድን ተኮር ቃለመጠይቅ ምላሽ
የመለያ ቁጥር፡- ቡተቃ 203

ሰዓት፡ 4፡00-5፡50
ቦታ፡- C-28
ቀን፡-24/2005 ዓ.ም

1. ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታ ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር በሚያደርጉት የተግባቦት ሂደት ሀሳባቸውን እንዴት ይገልፃሉ?
   1.1 በስብሰባ ወቅት ከመናገራችሁ በፊት ምን ምን ታደርጋላችሁ?

1. አገሬ፡ በአብዛኛው የስብሰባውን አላማ፣ ስለማላውቅ፣ ስብሰባው ሲጀመረ አላማውን
2. በመረዳትና ጅምሩን አይቼ በዚህ ስብሰባ ላይ ይሄ ሀሳብ ቢገለፅ ይጠቅማል የምለውን ሀሳብ
3. ሰማቅረብ እሞክራለሁ፡፡ ይህን ለማድረግ መነገር ያለበትን ሀሳብ ማስታወሻ
4. እይዛለሁ፡፡ አንዳንዴ ደግሞ ዝም ብየም እናገራለሁ፡፡
5. ዮናስ፡ ብዙ ጊዜ ስብሰባው ከመካሄዱ በፊት ርዕሰ ጉዳዩን የማውቀው ከሆነ በተለይ ደግሞ
6. በመደበኛ ወይም በኢመደበኛ ውይይት ጊዜ መነሳት ያለበትን ጉዳይ በመጀመሪያ ማስታወሻ
7. ላይ ለማስፈር እሞክራለሁ፡፡ አንዳንዴ ስብሰባው ስለምን እንደሆነ ሳይነገር ስብሰባ አለ
8. ተገኙ የሚባልበት አጋጣሚ አለ፡፡ በዛ ላይ ደግሞ የማደርገው አጀንዳዎቹ ምን ምን እንደሆኑ
9. ለመፃፍ እሞክራለሁ፡፡ ምናልባት በዛ ዙሪያ ላይ እኔን የሚመለከት ጉዳይ ካለ አቀርባለሁ፡፡
10. ሮዛ፡- እኔ አብዛኛዎቹን የገባሁባቸው ስብሰባዎች ምንድን ነው? ስለምንድን ነው? እያልኩ
11. እያልን ነው የምንሄደው፡፡ ምክንያቱም ቀድሞ አይነገርም፡፡ ሌላው ቀርቶ ሰብሳቢዎቹ የሆነ
12. ተደዋውለው ዛሬ እንሰብስባቸው የሚሉ ነው የሚመስለኝ፡፡ እና ብጠይቅ ምንም የመፍራት
13. ብቻ ሳይሆን አንዳንዴ የማይመለከተኝ ሁሉ ይመስለኛል፡፡ ጥያቄ ብዙም አልጠይቅም፡፡
14. የፋካሊቲ ላይ ምናምን እጠይቃለሁ፡፡ እና እዛው ለመፃፍ እሞክራለሁ አንዳንድ ነገሮችን
15. ምንድን ነው ዋናው ነገር ብየ እፅፋለሁ፡፡

ቆስቋሽ ጥያቄ፡ የምትፅፊው ላመናገር የምትፈልጊውን ሀሳብ ነው?

16. ሮዛ፡ አይ ዋና ዋና ነጥቦችን ለራሴ ማስታወሻ እይዛለሁ፡፡
17. ቆስቋሽ ጥያቄ፡ ለመናገር ስትፈልጊ ከመናገርሽ በፊት ምን ታደርጊያለሽ?
18. ሮዛ፡ እኔ ከምናገር መናገር የምፈልገው ነገር በሰዎች ሲባልልኝ ደስ ይለኛል፡፡
19. ገበየሁ፡ እኔ እንኳ ወደስብሰባ ስሄድ አጀንዳውን ካየሁኝ በቃ ሀሳቤን ወደእዛ ስብሰብ
20. ለማድረግ እሞክራለሁ ከመግባቴ በፊት፡፡ አጀንዳውን የማላውቀው ከሆነ ስደነባበር ነው
21. የምመጣው፡፡ ይሄን ይሆን እያልኩ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ጉዳየ አይደለም ዝም ብየ
22. እመጣለሁ፡፡ እዛ ስገባ አገኘሁ የለም በሚል፡፡ በዛሬው ሁኔታ ቀደም ብየ አንቺን አንዳንድ
23. ነገር ጠይቂሽ ስለነገርሽኝ አንዳንድ ነገር ዲስኮርስ ላይ ጭንቅላቴ ውስጥ መጣና እንደዛ
24. አይነት ነገር ለማንበብ ሙከራ አድርጌያለሁ፡፡
25. አልማዝ፡ ብዙ ጊዜ ስብሰባ ሲባል ቦርድ ላይ አጀንዳዎችን ሳይ ወደስብሰባ ከመግባቴ በፊት
26. ካጓደኞቼ ጋር ምናምን ኢመደበኛ የሆነ ውይይት እናደርጋለን፡፡ በስብሰባው ሂደት በትኩረት
27. እከታተላለሁ፡፡ ማን ጥያቄ ምናምን ጠይቄ አላውቅም፡፡ በተለይ በትላልቅ ስብሰባዎች ላይ፡፡
28. በዲፓርትመንት ደረጃ ሲሆን ሀሳብ ካለኝ እሰጣለሁ፡፡

ቆስቋሽ ጥያቄ፡ ባዲፓርትመንት ደረጃ ስትሰበሰቢ ከመናገርሽ በፊት ምን ዝግጅት ታደርጊለሽ?

29. አልማዝ፡ ከመናገሬ በፊት ምን ጥያቄ እንደምጠይቅ፣ ምን አስተያየት እንደምሰጥ በአዕምሮየ
30. አስባለሁ፣ ማስታወሻም እይዛለሁ፡፡
31. እሱባለው፡ አጀንዳው ቀድሞ ቢታወቅም ባይታወቅም በመጀመሪያ ወደስብሰባ ስሄድ ምንም

32. አይነት ዝግጅት ላይኖረኝም። እዛ የሚነሱ ሀሳቦች ናቸው እኔን የሚገዙኝ። እድሉ
33. መጀመሪያ ከደረሰኝ እናገራለሁ። ከዛ በፊት ግን ዝግጅት ያለው ነገር አይደለም።
34. ማስታወሻም የመያዝ ልምዱ የለኝም። የሰማሁትን ከላይ እስከታች በአዕምሮየ እይዛና
35. የማነሳቸው ነገሮች ከዛ በፊት ውስጤ የነበሩ ነገሮች አስተያየት የምሰጥባቸው ጥያቄ
36. የምጠይቅባቸው ነገሮች እዛ ውስጥ አዕምሮየ ውስጥ የነበሩ ይወጣሉና ሳላስበው ግን
37. ብዙዎቹ ነገሮች የሚከሰቱ ናቸው። ማለት እኔ ሳልፈልጋቸው በዛ ላይ ጥሩ ግንዛቤ ኖሮኝ
38. አንዳንድ ሰዎች ሲሳሳቱ ስለማያቸው የጋራ የሆነ መግባባት እንዲኖር ስል በውስጤ
39. ያለውን የማውቀውን እናገራለሁ።
40. ኤርሚያስ፡ ጉዳዩ አሳሳቢ ከሆነ ከአጀንዳው በመነሳት ቀድሜ እኔ እንዲህ እንዲህ ማለት
41. አለብኝ ብየ እዘጋጃለሁ። አንዳንዴ ደግሞ እዛው ሄጀ እዛው ላይ በሚነሱት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ
42. ያልገቡኝን ጥያቄዎች፣ አስተያየቶች ሊሆኑ ይችላሉ እዛው ላይ እዘጋጃለሁ። የምዘጋጀው
43. እንዴት ነው አንደኛ ጉዳዩ ከሚነገረው ነገር ውጭ ንግግሬ እንዳይወጣ አዕምሮየ ውስጥ
44. የማደራጅት ስራ እሰራለሁ። በማስታወሻ የመያዙ ባህሪ ብዙም የለኝም።
45. መቅደስ፡ እኔ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ወይም ሰው የበዛበት ስብሰባ ላይ እስካሁን ፈፅሞ ምንንም
46. አይነት ነገር ተናግሬ አላውቅም። በትምህርት ክፍል ደረጃ እንዲሁም ሴት መምህራን
47. በምንሰባሰብበት ጊዜ እናገራለሁ። የሚገርመው ግን በሁለቱም ስብሰባዎች ላይ ስሳተፍ
48. የተለያየ ስሜት አለኝ። በትምህርት ክፍል ደረጃ ስንሰበሰብ ብሞት ቀድሜ አልናገርም።
49. ሁሉም ሰው ከተናገረ በኋላ በእኔ ላይ ችግር ያመጣብኛል ብየ የማስበው ጉዳይ ካለ
50. እናገራለሁ። ግን ከመናገሬ በፊት ምን እንደምናገር አስቀድሜ በማስታወሻየ ሀሳቤን
51. አሰፍራለሁ። ለመናገር ስወስን ደግሞ በተለይ ተሰብሳቢው ትንሽ በዛ ካለ ልቤ ድው ድው
52. ይላል። መናገር ስጀምር ለመናገር ያሰብኩት ሁሉ ይጠፋብኛል ማስታወሻየ ላይም
53. የያዝኩትን እዘለዋለሁ አንደበቴ ይተሳሰራል። እና ቀስ በቀስ ነው የማስተካክለው በዚህ
54. ምክንያት ማለት ያለብኝን ሁሉ ሳልናገር እቀራለሁ።ከሴቶች ጋር በምሰበሰብበት ጊዜ ደግሞ
55. ቀድሜም እናገራለሁ፣ ሀሳቤን ለመግለጽ ደግሞ ምንም አይነት ዝግጅት አላደርግም
56. እንደመጣልኝ በነፃነት ነው የምናገረው። እኔ ብቻ ሳልሆን እንደታዘብኩት ሌሎች ሴቶም
57. ለብቻችን ስንሰበሰብ የማትናገር ሴት የለችም።

1.2 ለመናገር ስትፈልጉ ሌሎች የመናገር እድል እንዲሰጧችሁ ምን ታደርጋላችሁ?

58. ኤርሚያስ፡ በጣም ትንሽ ከሆን አንድ ሰው ሲናገር የሚናገረው ነገር ከእኔ ጋር የሚጋጭ
59. እንትን የሚል ከሆነ መሀል ልገባ እችላለሁ። ላቋርጠው እችላለሁ። በጣም መደበኛ
60. የምንለው ስብሰባ ከሆነ እጅ በማውጣት ነው ዞሮ ዞሮ የሚገኘው። አንዳንዴ ደግሞ
61. ስብሳቢዎቹ ራሳቸው እንድትናገሪ ይጠይቁሻል። በዚህ ሁኔታ እድሉን አገኛለሁ።
62. እሱባለው፡ እኔ ከዚህ የተለየ ነገር ብዙ ባይኖረኝም አንደኛ እጅን ቀድሞ ማውጣት፣
63. ሁለተኛ የምቀመጥበት ቦታ በራሱ ለዚህ ትልቅ አስተዋፅኦ አለው። እናም
64. መቀመጫየን ወይ ከፊት መቀመጥ ወይ ትክክለኛ የሆነ ሁሉንም ማየትና እኔም
65. መታየት በምችልበት ቦታ እቀመጣለሁ። ኤርሚያስንኛውም የእኔ ምርጫ ሁሌም
66. ፊት ላይ ነው። ምንም አይነት ነገር እንዲረብሸኝና እንዲያመልጠኝ አልፈልግም።
67. በዛውም እድሉን እጠቀምበታለሁ ማለት ነው።
68. መቅደስ፡ እኔ እጀን ብቻ ነው የማወጣው። እድሉ ካልተሰጠኝ ከወጣሁ በኋላ
69. ለሚቀርበኝ እና ላገኘሁት ሰው እናገራለሁ። ሰብሳቢውን ማናገር የምችል
70. የማልፈራው ከሆነም ወይ እንደወጣሁ ካልሆነ በሌላ ጊዜ እነግረዋለሁ ያም
71. አንገብጋቢ ነው ብየ ሳስብ ማለት ነው። ካልሆነ ሀሳቤ እኔው ጋ ይቀመጣል።
72. አቶ ገበየሁ፡ እኔ ወደመሀል ላይ ነው ብዙ ጊዜ የምቀመጠው። ወደኋላም አልሆንም
73. በጣም ወደፊትም አልቀመጥም። መሀል ሰፋሪ ነኝ። ለመናገር ስፈልግ መጀመሪያ ለሌሎች
74. ቅድሚያ እሰጣለሁ ለሌሎች ሰዎች ጥያቄ የሚጠይቁ ከሆነ፣ አስተያየት የሚሰጡ
75. ከሆነ ሳዳምጥ ቆይቼ ከተባለው ነገር ጋር በቂ ግንዛቤ ከተሰጠ መናገር አልፈልግም።
76. ግን አስፈላጊ ?ሆኑ ነገሮች የተዘነጉ አሉ ወይም አቅጣጫ ተስቷል ብየ ሳስብ የዛን

77. ጊዜ እጄን ለውጥቼም፣ ጣልቃ ገብቼም እናገራለሁ።
78. ሮዛ፡ እኔ ዶሎ አልናገርም። ማብራሪያ እስኪሰጥ እጠብቃለሁ። ከዛ በኋላ ግን
79. መናገር ከፈለኩ እጄን አወጣለሁ። ካላዩኝ ደግሞ እዚህ ጋ ጥያቄ አለ እላለሁ
80. የዲፓርትመንት ብሎም የፋካሊቲ ሲሆን በዛ መልኩ እንዲያልፈኝ ካልፈለኩ ማለት
81. ነው። በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ያው ቅድም እንደገለጽኩት ለመጀመሪውም አልናገርም።
82. አገሬ፡ በአብዛኛው እጅ በማውጣት ነው። ካልሆነ ግን ይቅርታ እዚህ ጋ የተረሳ ነገር
83. አለ፣ ማስተካከያ፣ ማሳሰቢያ ሁሉ እላለሁ። ማሳሰቢያና ማስተካከያ ከተባለ ስለሚሰጥ
84. ያቀረብሽው ማሳሰቢያ ነው ይበሉም አይበሉም ዝም ብየ በቀጥታ ሀሳቤን አቀርባለሁ።
ቆስቋሽ ጥያቄ፡ ይህን የምታደርጊው በትልልቅ ስብሰባ ላይም ነው?
85. አገሬ፡ እኔ የታዘብኩት ምን መሰለሽ በየትኛውም ስብሰባ ላይ ለሴቶች እድል
86. አይሰጥም። ቢሰጥም እንኳ ለተሳትፎ ሴቶች ተብሎ ጉዳዩ ከተጠናቀቀ በኋላ
87. ይሰጥሻል። እኔ ሶስት ቀን ሙሉ እጄን ሳወጣ ውየ አልሰጠኝ ብሎ በኋላ ስብሰባው
88. ተጠናቀቀ ሲባል ለሴቶች እድል ስጡ ተብለው ለእኔ ተሰጠኝና ያደረኩት ምንድን ነው
89. የሶስት ቀን ስብሰባ ስለነበረ በአጠቃላይ የነበረኝን ሀሳብ አቀረብኩ በሰዓቱ ከሚባለው ጉዳይ
90. ጋር አይያያዝም ግን መናገር ስለነበረብኝ ተናገርኩ። እና እኔ ትልቅ ትንሽ ስብሰባ አልልም
91. መናገር ካለብን እጄን አውጥቼ ካልሰተጠኝ ማሳሰቢያ ማለቴ አይቀርም።
92. ዮናስ፡ እድል እንዲሰጠኝ የማደርግበት አጋጣሚ እጅ በማውጣት ነው። ብዙ እጅ
93. የወጣ ቢኖርም እድሉ ካልተሰጠኝ ወይም የማይሰጠኝ መስሎ ከታየኝ እዚ ጋ
94. መረሳት የሌለበት ተጨማሪ ጉዳይ አለኝ ስለዚህ እድሉ ቢሰጠኝ እላለሁ። ሌሎች
95. እጃቸውን ያወጡ ሰዎችን ሁሉ እጫናለሁ። የእኔ መታለፍ የሌለበት ጉዳይ ነው
96. እድሉን ስጡን ይቅርታ ምናምን እላለሁ። ይሄ በዲፓርትመንትም በፋካሊቲም
97. ደረጃ በሚደረግ ስብሰባ ላይ ነው፤ ትልልቅ ስብሰባዎች ላይ ግን የሚነሱት ሀሳቦችም
98. ብዙም አይመቹኝም...
ቆስቋሽ ጥያቄ፡ ሳብሳቢ ኳትሆንስ እድል የምትሰጠው እንዴት ነው
99. ዮናስ፡ ሰብሳቢ ስሆን ሁልጊዜ ልምዱ ወዳላቸው ወጣቱን ያስተምራሉ ይመራሉ
100. ለሚባሉ ሰዎች እሰጣለሁ።

1.3 ሀሳባችሁን ሳትጨርሱ ወይም ሳትናገሩ ከስብሰባ ወጥታችሁ ታውቃላችሁ?

101. እሱባለው፡ በትልልቅ ስብሰባዎች ላይ አንድም ቀን የእኔም ሆነ የሌሎች ሰዎች ሀሳብ
102. ጨርሰን የወጣንበት ጊዜ የለም። ሰፊ ጊዜ አይሰጥምና።
103. አልማዝ፡ እኔ መናገር ጀምሬ ሀሳቤን አቋርጬ አላውቅም። ቀድሞ ነገር
104. አልሳተፍም። መናገር ፈልጌ ሳልናገር የቀረሁባቸው ጊዜያት ብዙ ናቸው ማለት
105. ይቻላል። ግን ሳልናገርም ስቀር አንዳንዴ ጥያቄ የሚቀሰቅሱብን ነገሮች አሉ።
ቆስቋሽ ጥያቄ፡ ለምንድን ነው የማትናገሪው?
106. እኔ እንደዚህ አይነት ቦታ ላይ ልምድ የለኝም አንዳንዴ ደግሞ የሆነ መናገር
107. አስብና ጥያቄ ብየ የማስበው ነገር የሆነ ዝም ብየ እገመግመዋለሁ ይሄ ተነሳ
108. አልተነሳ ምን ፋይዳ አለው እልና ያሰብኩት እጥለዋለሁ።
109. አቶ ገበየሁ፡ አያድረስና አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ሰው ይሰበሰብና ከዛ ባኋላ
110. ከሰው ሀሳብ ሳይቀበል ድፍንፍን አድርጎ የራሱን ጉዳይ ከፈፀመ በኋላ ውጡ
111. እንባላለን። የዛን ጊዜ የምወጣው፣ የምሄደውም ብቻየን እየተነጋገርኩ ነው...
112. ሮዛ፡ እኔ አልሚ እንዳለችው ያው አልናገርም። ግን አንዳንዴ አልፎ አልፎ
113. እንኳ ብናገር አጠር ኦድርጌ ነው ሀሳቤን መግለጽ የምፈልገው። ግን ሀሳቤን
114. ሌሎች እንዲገልጽላችኝ እፈልጋለሁ። ከዛ ሰዎች ሀሳብ ሲሰጡ የእኔው እዛው
115. ይካተትና እተወዋለሁ። ከዛ ውጭ ግን ሀሳብ ጀምሬ ማንም ሰብሳቢ አቋርጦኝ
116. አያውቅም። ሳልናገር የወጣሁበት ግን ተይው። በእርግጥ አንዳንድ ጊዜ
117. አለመናገሬ ከወጣሁ ቦኋላ ብዙ ጊዜ ይቆጨኛል። በተለይ ቦፋካሊቲ ላይ

ምንም ይሁን መንገር ነበረብኝ ሊያውቁት ይገባል ማለት ነበረብኝ ያልኩባቸው
ጊዜት አሉ።
ቆስቋሽ ጥያቄ፡ ሳትናገሪ የወጣሽበት ምክንያትሽ ምን ነበር?
ሮዛ፡ ያ ክፍተት ማለት ለእኔ ጥሩ እንትን የላቸውም ስለዚህ ምንድን ነው
የእኔ መናገር የሚፈይደው በማለት።
አገሬ፡ በተለይ አንዳንድ ጊዜ ውስጤ እየበሸቀ ራሱ ሳልናገር እወጣለሁ።
ምክንያቱም የሰብሳቢዎቹ አላማ አንድ ነገር አስቀምጦ መሄድ እንጅ ከእኛ
ሀሳብ መቀበል አይፈልጉም። በዚህ ጊዜ መናገሬ ለውጥ የማያመጣ ከሆነ
እልና ዝም እላለሁ። አንዳንዴ ደግሞ የማደርገው ለውጥ ባመጣም እንኳ
ጭንቅላታቸው ውስጥ አስቀምጠውት አንድ ቀን ይህ ሀሳብ ይቀይራቸዋል ብየ
ካሰብኩ እናገራለሁ። ስናገር ግን ይቅርታ ጊዜ ስለሌለ ብለው አቋርጠውኝ
ያውቃሉ። በተለይ ዲፓርትመንት አካባቢ። ምክንያቱም እኔ ፍርጥርጥ
አድርጌ የመናገር ባህሪ አለኝ። ምንም ይሁን ምን አንድ ቀን ይለወጣል ያንቀን
ተግባራዊ ይሆናል ብየ።
ቆስቋሽ ጥያቄ፡ መናገር እያለብሽ ሳትናገሪ ወተሽ ታውቂለሽ?
አገሬ፡ አዎ ሳልናገር እወጣለሁ። ምክንያቱም ቅድም እንዳልኩሽ እድል
የመስጠት የማሳተፍ ሁኔታ የለም። ለምሳሌ ባለፈው የተደረገው አጠቃላይ ስብሰባ
ላይ ሶስት ቀን ሙሉ እጄን ባወጣ ባወጣ ሊሰጠን አልቻለም። ግን ካስታወሳችሁ
የሆነ ሰው ማን እንደሆነ አላውቅም በወረቀት ፅፎ እባካችሁ ሴቶችን አሳትፉ ብሎ
ለሰብሳቢዎቹ ሰዶ ሰብሳቢዎቹም ማስታወሻውን አንብበው እንዲህ ተባልን ብለው
ነግረውን እሽ ሰዓት ስለሌለ ለአንዲት ሴት እንስጥ አሉ። ያኔ እኔ የምናገረውን ሁሉ
ማስታወሻ ይገፎ ሁሉ ስለነበረ ከፊት አካባቢም ነበር የተቀመጥኩት እጄን
ቶሎ አወጣሁ እድሉ ተሰጠኝ ተናገርኩ። እንዳያችሁኝ የተናገርኩት ስለዛቀን
አጀንዳ ሳይሆን ሶስቱንም ቀን ሀሳቤን በርዕስ በርዕስ አድርጌ አቀረብኩ።
የሚገርማችሁ ከወጣን በኋላ አንድ ሁለት ሴቶች እጄን ባወጣ ባወጣ
አልሰጠኝ አለ እያሉ መናገር ፈልገው ሳይናገሩ የወጡ ሴቶች አሉ። ለዛም
መሰለኝ እጃችንን በተደጋጋሚ፣ ስናወጣ ያየ ሰው ሴቶችን አሳትፉ ብሎ
ማስታወሻ የሰጣቸው።
መቅደስ፡- በትልልቅ ስብሰባዎች አዎ መናገር የምፈልገው ያውም የመፍትሄ
ሀሳብ ይሆናል የምለውን ሀሳብ ስለምፈራ ብቻ ሳልናገር ሁሌም እወጣለሁ።
እንዳልኩሽ ሀሳቤን አጠገቤ ላለች ወይም ወንድ ሊሆን ይችላል እነግረዋለሁ።
ካልሆነ ስወጣ ለጓደኞቼ ይዤ ነገር እኮ እንዲህ ነበር ብየ እናገራለሁ። በጣም
ጥሩ ሀሳብ ነበር ይዤ ሲሉኝ ደግሞ በጣም እናደዳለሁ ባለመናገሬ።
የሚገርማችሁ ግን አንድ ሁለት ቀን ከሆነ ወንድ ባልደረባየ ጋር ተቀመጥኩና
መናገር የምፈልገውን ሀሳብ ይዤ እኮ እንዲህ ማለት ነው እና እንዲህ ቢሆን
ይሻል ነበር ብየ ነገርኩት። እሱም እጁን አወጣ ሁለቱንም ቀን እድሉ
ተሰጠው የእኔን ሀሳብ ከራሱ ጋር አዋህዶ አቀረበው።
ቆስቋሽ ጥያቄ፡ ምን ስሜት ተሰማሽ እሱ ሲናገርልሽ?
እውነቱን ለመናገር ቦመጀመሪያ ሀሳቤ እንዲቀርብ ነበር የምፈልገውና ደስ
አለኝ። በኋላ ግን ሰብሳቢው እከሌ እንዳለው እያለ እያደነቀ ሲናገር በጣም ነው
የቆጨኝ። ምክንያቱም ሀሳቤ ትክክልና ትልቅ መሆኑን ተረዳሁ።
ዮናስ፡ እኔ ብዙ ጊዜ ሳልናገር የምወጣባቸው ጊዜያት ብዙ ናቸው። ለምን ቢባል
የጉዳዩን ተደጋጋሚነትና የቸከ ሁሌም እየተነሳ ምላሽ የማያገኝ ጉዳይ
ከሆነብን ብናገርም መልስ ስለማይሰጠው አልናገርም። ሌላው የጊዜ
ማነስ ራሱ አንዱ ምክንያት ነው። ከተሳታፊዎች ሀሳብ ላለማስተናገድ
የራሳቸውን ጉዳይ ብቻ ለመፈፀም ስለሚፈልጉ ጊዜ የለም ምናምን ይላሉ።
በእንደዚህ አይነት ምክንያቶች አልናገርም።

1.4 የሴቶችና የወንዶች ንግግር በስብሰባ ወቅት ልዩነት አለው ብላችሁ ታስባላችሁ?(የቋንቋ አጠቃቀማቸው ምን ይመስላል?)

159 . አገሬ፡ በጣም

ቆስቋሽ ጥያቄ፡ እንዴት

160. አገሬ፡ በጣም የሚገርመው አብዛኛዎቹ ሴቶች በስብሰባ ላይ አይናገሩም። እንዲውም
161. በስብሰባ ላይ የሚገኙት ሴቶች በጣም አናሳ ናቸው። ቢመጡም እንኳ ስብሰባው
162. ጠንካራ ቁጥጥር ከሌለው ፊርማ ፈርመው አቋርጠው ነው የሚሄዱት። እንደገና
163. ሲናገሩ ፍራቻ የሚታይባቸው ሴቶች አሉ። ማለት ሀሳባቸው የመቆራረጥ ፣
164. ሀሳባቸው ራሱ ሳይገልጹ ቆርጠው ሲያስቀሩት ይሰማል። በአጠቃላይ ከሚናገሩት
165. ሃሳብ ሳይናገሩት የሚቀረው ይበልጣል። ምክንያቱም ለሴት መናገር ያልተለመደ
166. ባህል ነው ሴቶች በወንዶች ፊት የመናገሩ ሁኔታ ብዙ ትልቅ ስብሰባዎች:: ብዙ
167. ትላልቅ ስብሰባዎች ላይ ሰብሳቢዎች የሚጋብዙት ወንዶችን ነው። የእሷ ሀሳብ ግን
168. ከትልቆች የተሻለ ሊሆን ሁሉ ይችላል። እውነቴን ነው ሊጠቅም የሚችል
169. ለወደፊቱም ሊረዳ ሚችልና ከአዕምሮ ውስጥ አንድ መሰረት ጥላ ልታልፍ ስትችል
170. እነዚህ ሰዎች ምን ይሉኛል፣ ወንዶች ተቀምጠው የሴት ቀልቃላ እባላለሁ አይነት
171. እንዲህ መጥፎ ባህል አለ። ምንድን ነው የሚባለው ሞኝ አባት የተከሎውን ብልህ
172. ልጅ አይነቅለውም። ሞኝ እናቶቻችን ያኖሩትን እኛም ብልሆች የሚባሉ ሴቶች
173. እሱን ወይም እያሉ ያን የማይጠቅም ባህል አሁንም እየተገበርነው መሆኑ በትክክል
174. እየታየ ነው።

162. ዮናስ፡ በጣም አለ። የሚነሱት ሀሳብ ላይ ግን አይደለም ልዩነቱ። እጅ
163. አውጥቶ ከመጠየቅ ተሳትፏቸውን በተመለከተ በጣም አናሳ ነው።
164. ብዙዎች የባህል ሰለባም ከመሆን አንጻር ሊሆን ይችላል። ብዙዎች
165. ሃሳባቸውን መግለጹ ላይ ያን ያህል በንቃት የሚሳተፉ አላይም። እጃቸውን
166. አውጥተው ከመናገር ይልቅ ካጠገባቸው ካለ ሰው ጋር በሹክሹክታ ሲያወሩ ነው
167. የማያቸው እንደሚመስለኝ እኔም ካጋጠመኝ አንጻር መናገር የፈለጉትን ነው
168. ከጎናቸው ላለ ሰው የሚናገሩት። ግን ደግሞ አንዳንዶች አሉ በጣም ጎበዝ
169. ተናጋሪዎች ከስን አንድ ናቸው እንጅ።

ቆስቋሽ ጥያቄ፡- ከምታውቃቸው ሴቶች አንጻር በሚሳተፉና በማይሳተፉ ሴቶች መካከል ለመሳተፋቸው ልዩነት ይኖር ይሆን?

170. ለልዩነቱ እንግዲህ ማህበር ባህላዊ ዳራቸው ሊሆን ይችላል። ተወልደው
171. ያደጉባቸው፣ የበቀሉበት ባህል ሴት ልጅ እንድትናገር፣ ሀሳቧን እንድትገልጽ
172. በነጻነት። አስተዳደግ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። ግን ለምሳሌ ወደ ምስራቁ አካባቢ
173. የመጡት ኢ.ሚደበኛ በሆነው ተግባቦት የተሰማቸውን ሀሳብ ከመግለጽ ወደ ኋላ
174. ኦይሉም። ከወደዚህ ያሉት በዚህ አውድም ብዙም አይደሉም ጭምት ይመስላሉ።
175. እና የባህል ልዩነት ነው ብዬ አስባለሁ። ግን ደግሞ እነዛም ቢሆኑ በመደበኛ ስብሰባ
176. ላይ ሲሳተፉ አታያቸውም። በተለይ ሰፋ ባለ ስብሰባ ላይ አኔ ሲናገሩ አላየሁም።

ቆስቋሽ ጥያቄ፡ የቋንቋ አጠቃቀም ለዩነት በወንዶች እና በሴቶች መካከል ይኖር ይሆን?

177. ዮናስ፡- እሱን ለዩነት ልብ አላልኩም እስካሁን
178. አገሬ፡- እኔ ለዩነት አለ ኣላለሁ። ምክንያቱም የመናገሩን ለዩነት አመጣው የምለው
179. እኔ ባበኩሌ አስተዳደግ ነው። በቤተሰብ ውስጥ ስትናገር ተቀባይነት እያገኘች ያደገች
180. ከሆነች ጥሩ እንትን ይፍራታል። ሌላው ቀርቶ በትምህርት ቤትም መምህሮቹ፣
181. ጓደኞች የሚያበረታቷት ገቤተሰብም ትክክል ነሽ እየተባለች ኣሜኔታ የሚጣልበት
182. ከሆነች የምትናገር ትሆናለች። እኔ በበኩሌ መሪ ልጅ ነኝ :: እኔ ሳድግ ሴትና ወንድ
183. የሚለውን ልዩነት ፈጽሞ ሳላውቅ ነው ያደኩት። ጓደኛየ አባቴ ናቸው አጎቶቼ
184. ናቸው። ከእነሱ ጋር እኩል ሀሳቤን አቀርባለሁ። ሓቃውሞየን አቀርባለሁ። በጣም

185. የሚገርመው ወንዶች ጋር ተጣልቼ አባቴ ጋር እወያያለሁ በግልጽ የወንድ ጓደኛ
186. ስመርጥም ከአባቴ ገሰር ተወያይቼ ነው። ይህ የአስተዳደግ ሁኔታ ነው። የሚገርምሽ
187. ከእኔ በታች የሆኑት ደግሞ ዝም በይ ቁልቃላ እየተባሉ ያደጉ ናቸው። እኔ
188. የመጀመሪያ ስለሆንኩ ነው ፈጽሞ ለመናገር የማይወዱ አሉ። እና አስተዳደግ ነው።
189. አልማዝ፡- በሁለቱ ጾታዎች መካከል ለዩነት አለ በፋካሊቲም ሆነ በትልልቅ ስብሰባ
190. ላይ ስንመለከት ብዙ ጊዜ የሚሳተፉት ሀሳባቸውን የሚገልጹት ወንዶች ናቸው። እና
191. ብዙ ጊዜ የሴቶችንና የወንዶችን ንግግር ስመለከት ሴቶች ብዙ ጊዜ አስተያየት ነው
192. የሚያበዙት እንደዚህ ቢሆን አይሻልም አይነት ነገር የሚመርጧቸው ቃላት ለስለስ
193. ያሉ ናቸው። የሚያፋጥጥ አይነት ጥያቄ የሚጠይቁ ወንዶች ናቸው። በነገራችን ላይ
194. የሚሳተፉ ሴቶች ይታወቃሉ። ግን በጣት የሚቆጠሩ ናቸው እንጅ። ብዙ ስብሰባ ለይ
195. እገሌ ካለች ትናገራለች የምንለው ገና ስንገባ ለምሳሌ አንዷ --------ናት።

ቆስቋሽ ጥያቄ፡ ለመናገር ያበቃት ምን ይሆን?

196. አልማዝ፡- አንዱ እንደተባለው አስተዳደግ ሊሆን ይችላል:: ሌላው ደግሞ ለነገሮች
197. የምንሰጠው ዋጋ ራሱ ተጽዕኖ ያላድራል። ይህ ምን ያደረጋል ብለሽ ብዙ ቦታ
198. ሳትሰጭው ለአቴንዳንስ ብቻ ፈርሜ እወጣለሁ ብለሽ የምትሳተፊባቸው ስብሰባዎች
199. ይበዛሉ።
200. ሮዛ፡- በተሳትፎ ደረጃ ምንም ጥርጥር የለውም ሴቶች አይሳተፉም ቁጥራቸውም
201. ቢበዛም። ግን ሲሳተፉ ሀሳብን ከመግለጽ አንጻር ለዩነት አለው ብዬ አላስብም፣
202. አንዳንድ ጊዜ በጣም የሚገርም ጥያቄ ሲጠይቁ አያለሁ። በእርግጥ አስተዳደግ በጣም
203. ወሳኝ ነው። ግን የራሳችን ዝግጁነት እኔ ለመለወጥ የማደርገው ጥረት በራሱ
204. ተጽዕኖ አለው። አሁን እኔ በእኛ አካባቢ ሴት ልጅ ወንድ ባለበት በተሰበሰበበት ቦታ
205. ድምጿን ተሳስታ እንኳ ጮክ ብላ ከተናገረች በጣም ነውር ነው። እንዴት ነው
206. የምትሰነጠቀው የምታቢርቀው ምናምን ነው የሚባለው። ሴት ልጅ አንገቷን ደፍታ
207. ስትሄድ ነው ሳርዓት ይዛ ያደገች የምትባለው። እኔ ክፍል ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ
208. ይከብደኝ ነበር ዩኒቨርሲቲ አራት አመት ስማር አንድም ቀን ጠይቄ አላውቅም።
209. ልጆች እንዲጠይቁና እንድረዳ ግን እፈልጋለሁ። የዛ ተጽዕኖ ማለት ነው። ግን አሁን
210. ምንድን ነው ከበፊቱ አንጻር ሳየው በጣም ተናጋሪ ሆኛለሁ ብዬ ነው የማስበው እና
211. ብናገር ማንም እንዲህ ይለኛል እከሌ የሚል አይደለም። ግን የማልናገረው ለምንድን
212. ነው ይህ ጥያቄ ጠቃሚ ነው፤ ተገቢ ነው ብቻ ይህን ለራሴ ስጠይቅ ያው ስብሰባው
213. ያልቃል እንጅ የመፍራት አይደለም። እና ለነገሮች የምንሰጠው ዋጋ ጭምር ተጽዕኖ
214. አለው። እኔም ድርሻ አለብኝ፣ ይህን ብል ይሄ ሀሳብ እኮ ብዙ ነገር ይቀየራል
215. የሚለው ወስደሽ ራስሽን እዛ ውስጥ ማስገባትና ሀላፊነት የመውሰዱ ነገር የለም።
216. ገበየሁ፡ መሰረታዊ የሆነ በሴቶችና በወንዶች መካከል አንድ ትልቅ ለዩነት አለ
217. ለአንድ ችግር ቶሎ በቀጥታ ደንበኛውን መልስ የሚያገኙት ሴቶች ናቸው። ይህም
218. በሴቶችና በወንዶች መካከል (intution power) ለአንድ ነገር ቶሎ ብሎ መፍትሄ
219. ማግኘት፣ መላ ማግኘት መቻል ሴቶች ላይ ከፍተኛ ሲሆን፣ ወንዶች ለይ ይህ
220. ችሎታ ዝቅተኛ ነው። በምሳሌ ላስረዳ፣ በድሮ ጊዜ ክርክር ያደርጉ ነበር። በክርክሩ
221. ላይም እንቆቅልህ/ምናውቅልህ አንዱ መከራከሪያቸው ነበር። እናም እየተከራከሩ ሳለ
222. አንዱ እንቆቅልህ ተብሎ ጥያቄ ይጠየቃል። ምን አውቅልህ ሲለው "የመሬት
223. መካከሏ የት ነው?" ይለዋል። ከዚያ ግራ ይጋበዋል፤ ተጨነቀ፤ ዳኛውን አስፈቅዶ
224. ሌላ ጊዜ ቀጠሮ ተሳቶ ሄደ። ከዚያ ቤት ውስጥ ገብቶ አይበላ አይጠጣ ዝም ብሎ
225. እህህ ብቻ ሆነ። ምግብ ሲቀርብለት አይበላ፣ ሚስትም በሁኔታው ተጨንቃ ምን
226. ሆንክ ብላ ስትጠይቀው ዝም በይ ደግሞ አንች ይላታል እንደ ትንሽ በመቁር። በኋላ
227. ሲጨነቅ ንገረኝ ዛሬ ካልነገርከኝ ብላ በቁጣ ትጠይቀዋለች እንደነገ ሲሆን ቀጠሮው።
228. "እባክሽ እንደዚህ ሆኖ ነው" ይላታል። ይች ናት! ይች ናት! በል ታጠብና ብላ
229. አለችው። ምንድን ነው ቢላት አሁን እነግርሃለሁ መጀመሪያ ብላ ትለዋለች። ከዚያ
230. በደንብም ሳይጠግብ ኮክቶ ተወውና በይ መልሱን ንገሪኝ ሲላት፣ ‹‹እዚህ ጋ ነው

ብለው›› አለችው፡፡ እንዴት ቢለኝስ ሲላት ‹‹ለካና ድረስበት በለው› አለችው፡፡በኋላ
በቀጠሮው ዳኛው ጋ ሂዶ እንደዛ ሲል አሸነፈው፡፡ እና ይህን የፈጠራ ችሎታ ወይም
ሀይል አለ፡፡ ይህንን እያጣን ነው፡፡ ምናልባት በሴትነታቸው የማናናግራቸው፣ እድል
የማንሰጣቸው ከሆነ ይህንን ነገር እያጣን ነው የምንሄደው ትልቅ መፍትሄ
የሚሰጡትን፡፡
እሱባለው ፡- ልዩነት አለ ሴቶች ጥሩ ጥሩ ሀሳቦችን ያነሳሉ ከሀሳብ ጀምሮ ቋንቋ
አአጠቃቀማቸውም፡፡ በትክክል ባህላቸውን ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ከወንዶች
የተሻለ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ የቋንቋ አጠቃቀም ያየሁት ነገር በቁጣ ይሄ በሀይል
የመናገር ነገር ወንዶች ላይ ታያለሽ፡፡ ሴቶች ላይ ግን እንደዛ አይነት ስሜት ሴቶች
ላይ አላይም፡፡ ከዚህ ጋር ደግሞ የሚያነሱት ሀሳብ ራሱ ገዥ ሀሳብ ነው፡፡
የሚያነሱት ሀሳብ ከወንዶች የተሻለ ሲታይ ገዥ ሀሳብ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ በንግግር ላይ
ሴቶች የተቃውሞ ሀሳብ ሲያነሱ አላይም፡፡ የመጠየቅ መፍትሄ ሀሳብ የመስጠት
ነገር፣ እንዲህ ቢሆን የሚል ነገር ነው፡፡ አንዳንዴ ምንድን ነው ከአጀንዳ ጋር
የሚሄድ ነገር የማምጣት ነገር አለ፡፡ የቋንቋ አጠቃቀሙ ያየሁት ደግሞ
እንግሊዘኛውን የመቀላቀል ነገር ሴቶች ላይ የለም፡፡ ለምሳሌ እኔ አይዶሎጅዎች
ከሆኑ፣ አካዳሚያዊ ነገሮች ከሆነ፣ ..... መጠቀም በጣም እቸገራለሁ እና አንድ
አይነት ቋንቋ በመጠቀም በዙ አስተውያቸዋለሁ፡፡ እንዲያውም ሁሌ አስብ ነበር
ምነው እንደነሱ ችሎታው ቢኖረኝ እላለሁ፡፡ በእርግጥ አንዳንድ ወንዶችም አሉ
የማይቀላቅሉ፡፡
ኤርሚያስ፡- ብዙ ጊዜ የመጨረሻው ንግግራቸውን የመዝጊያ የመዝጊያው ላይ
የመሰሳለስ ነገር አለ፣ ቢሆን አይነት ነገር፡፡ ሌላው ሴቶች ብዙ ጊዜ ከወንዶች የበለጠ
ጥንቃቄ ያደርጋሉ፡፡ የወንድ ቃላት በአብዛኛው ቁጣ የተሞላበት እና ስሜታዊ ሲሆን
የሴቶች ደግሞ ድምዳሜ ከመስጠት ይልቅ ቢሆንስ፣ እንዲህ
እንዲህ ቢደረግስ፣ አይሻልም ወይ፣ የሚል ነው፡፡ ግን አንዳንድ ሴቶች አሉ ይሄ
ይሁን ይሄ ይሁን የሚሉ፡፡ ቁራቸው ግን ከዚህ ይግባ የሚባል አይደለም፡፡
አብዛኛዎቹ ተጠንቅቀው ተጠበው ነው የሚናገሩት፡፡ እና የሚናገሩት በአብዛኛው
ስብሰባ ላይ ያሉትን ሰዎች በሚሰብ መልኩ ነው የሚናገሩት፡፡
መቅደስ፡ የተለየ ሃሳብ የለኛም እኔም የታዘብኩት የሚናገሩ ሴቶች አብዛኛዎቹ
ሃሳባቸውን በአጭሩና ሁሉም ሰው በሚረዳው መንገድ ያቀርባሉ፡፡ ወንዶቹ ግን
ሲናገሩ በመረጃ በማስደገፍ እኔ በዚህ ጊዜ በዚህ ቦታ እንዳየሁት፣ እንደሰራሁት፣
እንዳነበብኩት በማለት ያራዝማሉ እናም በዚህ ምክንያት ስለሚንዛዙ ከመሰልቸቴ
ውጭ ምን ለማለት ፈልጎ ነው እከሌ ብየ የምጠይቅበት ጊዜ ሁሉ አለኝ
አልገባኝ እያለ መልዕክቱ፡፡

1.5 ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታ ከአቻዎቻቸው ጋር በሚያደርጉት የተግባቦት ሂደት ሃሳባቸውን አድማጭ በሚረዳ ሁኔታ ባግባቡ ይገልፃሉን?

እሱባለው፡ ሴቶች ጋር በአብዛኛው ያለማንበብ ችግር አለ፡፡ እናም ሴቶች ጋ
የመግለጹ ሁኔታ ትንሽ ደከም ያለ ሁኔታ አለ፡፡ ምክንያቱም ከንባብ ማነስ የመነጨ
ነው ወይ ደግሞ አንድም በንባብ እውቀት ማነስ ነው፡፡ ያለዚያም ደግሞ በዛ
በሚነገረው አውድ ውስጥ ከዚህ በፊት ያላቸውን እውቀት ያለማምጣት
ሁኔታ ያለ ይመስለኛል፡፡
ኤርሚያስ፡- ሴቶች በተቻላቸው መንገድ ሲናገሩ ለዘብ ባለና ለስለስ ባለ ሁኔታ
ሳለሚያቀርቡ ተደማጭነት አላቸው፡፡ ወንዱ ጋ የምንጠቀምበት ቃላት በአብዛኛው
ጥሩ ግንኙነትን በሚፈጥር መልኩ የመናገር ሁኔታ አይታይበትም፡፡ ሴቶች ግን
የሚጠቀሙት ቋንቋ ራሱ መደበኛውን በመሆኑ ከእኛ ይሻላሉ እላለሁ፡፡
አቶ ገበየሁ፡- እኔ ልምሳሌ ከተማሪዎች ስነሳ ወደ እኔ ወንድ እና ሴት ተማሪዎች
ሲመጡ ሀሳባቸውን በመግለጽ ሁኔታ ይለያያሉ፡፡ ወንድ ልጆች ከመጡ ቶሎ

275. አያስረዱኝም። ወደዚህ ወደዚያ ሲሉ አገኛቸዋለሁ። ሴቶች ተማሪዎች ሲመጡ ግን
276. የሚፈልጉትን ጉዳይ በቀጥታ ያስረዱኛል።
ቆስቋሽ ጥያቄ፡ በእኛ ደረጃስ?
277. በእኛ ደረጃ ስንመጣ ስብሰባ ላይም ሆነ እንዲሁም በቢሮ ደረጃም ስንነጋገር ሴቶች
278. ጥቂት ነው የሚናገሩት አይንዘባዘቡም። ሀሳባቸውንም ሁሉም በሚረዳው መልኩ
279. ነው የሚያቀርቡት። ወንዶች ግን ስናይ በጣም ያስረዝማሉ፣ አንዱን ከአንዱ
280. ያወሳስባሉ። ስለሚዘባዘቡ ምን ለማለት እንደፈለጉ አንዳንዴ ግልጽ
281. የማይሆንልኝ ጊዜ አለ።
282. አልማዝ፡ አንዳንድ ወንዶች በተለይ የስብሰባ መድረክን የማስተማሪያ መድረክ
283. ያደርጋሉ። ያነበቡትን ነገር ሁሉ ያዩትን ሁሉ ሲያወሩ ሲያወሩ ስንቱ
284. ተጨብጭቦባቸው፣ ተጨሆባቸው ምናምን የሚያቆሙ ወንዶች አሉ። አንዳንዶቹ
285. እንዲያውም እምቢ ብለው የሚቀጥሉና ትዕግስታችንን አስጨርሰው የሚጨርሱ
286. ሁሉ አሉ። እሱባለው ያለውን ግን ያለማንበብ የተባለውን ነገር አልስማማም።
287. ምክንያቱም ሴቶች ሆኑ ወንዶች ሀሳባቸውን መግለጽ አያቅታቸውም።
288. እሱባለው፡ እኔ በደንብ ከመ.ያየም አንጻር ከአሁን በፊት ገምግሜዋለሁ። እንዲያውም
289. የሰጠሁት አስተያየት ምንድን ነው ያንን ነገር እንዲህ እንዲህ ብሎ ለማስረዳት
290. መረጃ ያስፈልጋል። መረጃው ደግሞ እውቀት ማለት ነው። እውቀት ከሌለሽ
291. አትናገሪም። ብትናገሪም ትንሽ ነገር ነው የምትናገሪ። እውቀት ካለ ግን መናገርም
292. መጻፍም ትችያለሽ የሚል ነገር ነው አስተያየት የሰጠሁት ።
293. መቅደስ፡- ሃሳብን መግለጽ እኮ ማንም ይገልፃል። ችግር ያለበት የለም። በእኔ
294. ምልከታ ቅድም የተናገርኩ መሰለኝ ሴቶች ‹‹to the point›› ስለሆነ የሚናገሩት
295. ግልጽና አጭር ነው ሁሉም ሰው በቀላሉ ይረዳቸዋል። ወንዶች ግን አንድን ጉዳይ
296. እንዲሁ ማቅረብ አይፈልጉም ከተለያዩ ነገሮች ጋር በማገናኘት በምሳሌ በማስደገፍ
297. ነው የሚናገሩት በዚህ ጊዜ ጉዳዩ ለአድማጭ ስለሚውሰበሰብ ምን ለማለት ፈልጎ
298. ነው ወይም ወደሌላ ትርጓሜ ውስጥ ይገባና ከአጀንዳው ይጣል ስብሰባውንም
299. መንገዱን ያስቀይራል።
ቆስቋሽ ጥያቄ፡ ወንዶች ለምን ይመስልሻል በቀጥታ ጉዳዩን የማያቀርቡት የሴቶቹስ ምክንያት ይኖረው ይሆን?
300. ወንዶች በሚናገሩበት ጊዜ ሃሳብ ብቻ አይደለም የሚስተላልፉት የራሳቸውን
301. ማንነት፣ ልምዳቸውን አብረው ነው የሚያሳዩት። ሌላው ዋናው ነገር እኔ
302. የሚመስለኝ ሀሳባቸው ተቀባይነት እንዲኖረው በምሳሌ በማስደገፍ ማስረዳት
303. ይፈልጋሉ። ሴቶች ላልሽው ከራሴ ብነሳ በምሳሌ አስደግፎ ለመናገር የተለያየ ልምድ
304. ሊኖረኝ ይገባል። በተለያዩ ክፍሎች፣ ኮሚቴዎች፣ ቦታዎች ወዘተ መስራት ሌላው
305. ቀርቶ ከትላልቅ ሰዎች ጋር የመገናኘቱ አጋጣሚ ቢኖረኝ እንኳ እከሌ እንዳለው
306. በዚህ ጊዜ ቦታ እያልኩ እናገራለሁ። ግን ይህ ሁሉ ነገር ስለሌለኝ በትምህርት እና
307. በንባብ ያገኘኋትን እውቀት በቀጥታ አቀርባለሁ።
ቆስቋሽ ጥያቄ፡ ቅድም የተነሳው ከንባብ ጋር በተያያዘ ሴቶች ስለማያነቡ ነው የሚለውንስ ከአንቺ ልምድ አንፃር እንዴት ታይዋለሽ?
308. አንድ ሚስጥር ላውጣ መቼም ይቅርታ ታደርጉልኛላችሁ ወንድሞቼ። ሁሉም
309. ወንዶች እኮ አንባቢ አይደሉም። የሚያነቡ ሴቶችም አሉ በተለይ በእኛ ደረጃ
310. በእርግጥ ሁሉም ሴትም ሆነ ወንድ የሚያስተምረውን ነገር ያነባል። አሁን
311. የሚያነጋግረን ከዛ ባለፈ የሚለው ነገር ነው። እንዲያው በጀንደር ላይ ብዙም
312. ስለሰራሁ ብቻ ሳሆን ሴንሲቲቭ በመሆኔ ስለምታዘብ ሴቶች ከምናስተምረው ባለፈ
313. አናነብም። በጣም በጥቂት የሚቆጠሩ ናቸው ጋዜጣ፣ መጽሄት ሌላም የሚነቡት።
314. እንደዚሁም ብዙ ወንዶችም ከሚያስተምሩት ውጭ የማያነቡ ኢቭን
315. የሚስተምሩትንም የማያነቡ አሉ። ልዩነቱ ግን በእይታ ስትመለከቸው ሁሉም
316. ወንዶች አንባቢ መስላው ይታዩሻል። ለምን መሰላችሁ ከሚያነቡ ወንዶች ጋር
317. ሳለሚውሉ መረጃ ያገናሉ ልክ እንዳነበቡ አድርገው ይነግሯችኋል፤ሴቶች ደግሞ ይህ

318. ላጋጣሚ ?ላቸውም እና እኔ ይህ ነው ልዩነቱ ነው ብየ ነው ?ማስበው።
319. እልማዝ፡ ባሃሳቡ እስማማለሁ። ግን ሴቶች አያነቡም ብሎ መደምደም ትክክል
320. ነው ብየ አልወስድም።

1.6 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በተግባቦት ሂደት ሀሳባቸውን ለመግለጽ ተፅዕኖ አድራጊ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?
321. ኤርሚያስ፡- በእኔ ምልከታ አንዱ ባህል ነው፣ ሌላው ስነ-ልቦናዊ የምንለው በራስ
322. መተማመን አለመቻል ነው። ማህበራዊ ጉዳዮች አሉ። ርዕሰ ጉዳዩ ራሱ እና
323. በመሃላችን ያለው የሃይል (የስልጣን) ልዩነት ካለ ተፅዕኖ ያደርጋሉ። እኔ ከማየው
324. ነው ይህ ምንላቸው። አሁን አንዳንዱን ነገር ስናይ በራስ የመተማመን የመጣ ነገር
325. አለው። ሌላው ያለን ግንኙነት ለምሳሌ የሀላፊነት ለዩነነት ሲኖር ተጽእኖ ይኖራል።
ቆስቋሽ ጥያቄ፡ አንተ ሃሳብ ያልገለጽክበት ጊዜ ካለ ተጽእኖ ያደረገብህ ነገር ምንድን
326. ነው? እኔ ለምሳሌ ርእሰ ጉዳይ፣ የሚነሳው ነገር ለእኔ አላስፈላጊ ነው ብዬ ካላመንኩ
327. ዝም እላለሁ። ሌላው የሰዎቹ አቀራረብ ዝም ብላችሁ ተቀብሉ ከሆነ ተቃውሞየን
328. በዝምታ ነው የምገልጸው።
329. አገሬ፡- በተለይ ሰብሳቢዎች ቂመኞች ይሆኑብሻል። ስህተታቸውን በሰው ፊት
330. ብትነግሪያቸው እንዲያርሙ ብትናገሪ በዛ ስብሰባ ጠቃሚ እንኳ ቢሆንም ሌላ ቀን
331. ሊበቀሉሽ ይፈልጋሉ። ስለዚህ ባልናገርስ ትያለሽ፡
332. አልማዝ፡ አስተዳደግ ዋናው ሲሆን የአስተዳደጋችን ችግር እንደፈጠርብን አውቀን
333. ራሳችንን ከዛ ለማውጣት ጥረት የማናደርግ ከሆነ ያው ይቀጥላል ማለት ነው፡
334. ያ ማለት በራስ የመተማመናችን ደረጃ እየወረደ ይሄዳል። ሲቀጥል ሰብሳቢ ሆነው
335. የሚመጡት ሰዎች ኮተሰብሳቢው ጋር መግባባት ከሌለና ጭቅጭቅ ለበት ስብሰባ ከሆነ ዝም
336. ብለሽ እንደ ተግሪ ያሉሽን ተቀብለሽ ትወጫለሽ።
337. ገበየሁ፡- አንዱ ጉዳይ ቅደም እንደተገለጸው የሰብሳቢዎቹ ሀኔታ ተፅዕኖ
338. ያደርጋል። ሌላው የሚቀርበው ጉዳይ አይመለካተኝም የሚለው ጉዳይ ወይም ደግሞ
339. ቢመለከተኝም እኔ ብናገር የሚሰማኝ የለም የሚለው ራሱ ተጽእኖ ነው።
340. ይመለከተኛል ያለ ይናገራል። ቢመለከተውም ደግሞ እድሉ ካሌለ ዝም ብሎ
341. ይወጣል። ብዙ ጊዜ ደግሞ እድሉ (opportunity) የሌላቸው ሴቶች ናቸው። ሌላው
342. ግን የሚመስለኝ ሁለት ነገሮች አሉ ከዚህ ጋር ተጽዕኖ የሚያደርጉ። እድሜ እና
343. እውቀት። እውቀት ያላት ከሆነች ዝም ብለው ያዳምጣታል፣ እድልም በተደጋጋሚ
344. ይሰጣታል። እድሜም ደግሞ ብዙ ልምድ ሲኖራትና ልምዷን ተጠቅሞ ሰፋ ያለ ነገር
345. ስለምታቀርብና የመፍትሄ ሀሳብ የመስጠት ችሎታዋ ስለሚታይ ተደማጭነትና
346. ተቀባይነት ይኖራታል።
347. አልማዝ፡- የምታቀርቢውን ሀሳብ የሚቀበልሽ ሰው ከሌለ ወደኋላ ትያለሽ። አንዳንዴ
348. በአንድ አጀንዳ ላይ ብዙ ሰብሰባዎች ሲደረግ እና በጣም አሰልች ሲሆን እንዳትናገሪ
349. ያደርግሻል። ሌላው እንዳንዴ እንደተሰብሳቢ ሆነሽ አሁን ለተሰብሳቢዎች ሌላው
350. ከኋላ ሆኖ አሰተያየት ስለሚስጠው ስው ‹ኢንፎርማሊ›የሚናገሩት ነገሮች አሉ።
351. እነሱ ነገሮች በራሳቸው ጫና ይኖራቸዋል። አሁን ይህን ብናገር ይህን እባላለሁ
352. ማላት ነው፣ እንደዚህ ኣይነት አስተያየት ይሰጠኛል ማለት ነው፣ ምናምን ትያለሽ፣
353. የሆነ ትፈሪያለሽ። ሌላው አንዳንዴ የሚመራው ስው ራሱ ሳቢ የሆነ የስብሰባ መሪ
354. ኦላ፤ ሌላው ደግሞ ላሰልች የሆነ ሰብሳቢ አለ በዚህ ጊዜ ስለምትሰላች። ሌላው
355. ታላላቅ ሰዎች ሲኖሩ የእነሱን ተሞክሮ መጋራት ይሻለኛል ብለሽ ከመናገር
356. የምትቆጠቢበት አጋጣሚ ይኖራል።
357. እሱባለው፡- አንዱ እድልን አለማግኘት ሲሆን፣ ሌላው ፍርሃት ነው። አንደኛው
358. ፍርሃት አላውቅም ማለት፣ ሁለተኛው ፍርሃት ትችት መፍራት፣ ሶስተኛው
359. ፍርሃት ሌሎችን ለመጠበቅ ሲባል ሌሎች ሌላ ነገር ያደርጋሉ ይደርስባቸዋል ተብሎ
360. የሚያስብ ከሆነ ላለመናገር ይፈልጋል ያ ሰው። የመጨረሻው ደግሞ ብናገር
361. ተጋላጭ እሆናለሁ ይህን ብናገር ቂም ይይዙብኛል ብሎ የማሰብ ሲሆን፣ ሌላው

362. ተመሳሳይ ግንዛቤ ከሌለ ዝምታ ይፈጥራል።
ቆስቋሽ ጥያቄ፡- ይህ አሁን የገለጽካቸው ተጽእኖዎች ከጸታ አንጻር እንዴት ትመለከታቸዋለህ?
363. አብዛኞቹ ተጽእኖዎች በሴቶች ላይ የሚታዩ ናቸው። ምክንያቱም ሴቶች
364. የራሳቸውንም ሆነ የሰውን ስሜት የመቆጣጠር ባህሪ ስላላቸው። በወንዶች ላይ ግን
365. ብዙም አይደሉም።
2. ሴቶችና ወንዶች በስራ ቦታ ከአቻዎቻቸው ጋር በሚያደርጉት የተግባቦት ሂደት ራሳቸውን/ማንነታቸውን እንዴት ይገልፁታል? (የሙያ ብቃታቸውን፣ የስራ ድርሻቸውን፣ ስልጣናቸውን፣
366. ኤርሚያስ፡- እኔ አሁን እስካሁን በታዘብኩት የስራ ድርሻቸውን፣ ሙያቸውን፣
367. እውቀታቸውን በመግለጽ ሂደት በአብዛኛው እኔ የማየው ወንዱን ነው።
368. እሱባለው፡- ማንነትን መግለጽ ቀላል ነገር አይደለም። በተለይ ስብሰባን ተጠቅመሽ
369. ራስሽን ብታስተዋውቂ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው።
370. አልማዝ፡- ከዚህ አንጻር በጣም በጣም የሚገልጹት ወንዶች ናቸው። ለምሳሌ
371. ወንዶችና ሴቶች ውጭ አገር ሂደው ቢማሩ፣ በማንኛውም ወሬም ሆነ ስብሰባ
372. ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የተማሩበትን ከተማ፣ ዩኒቨርሲቲ በተደጋጋሚ ሲያወሩ
373. ትሰሚያለሽ። ሴቶች ደግሞ ጉራ ነው የሚመስላቸው። ስብሰባም ከሆነ
374. ስለተሰበሰቡበት ጉዳይ ነው የሚያስቡት አንጂ ራሳቸውን የማስተዋወቅ እንትን
375. የላቸውም። እና ወንዶች ትንሽም ስራ ሰርቶ ከሆነ ያችን እኩል ሰርተን ቢሆን እኔ
376. መነገር አለበት ብየ የማላምንበት ሊሆን ይችላል፣ ግን በጣም ትልቅ አድርገው
377. አግዝፈው ወንዶች ሲገልጹ ታያለሽ። ከዚህ አንጻር እንዲያውም ሴቶች ብዙ
378. ሰርተው ትንሽ ሪፖርት የማድረግ አይነት ወይም ትንሽየ ራሳቸውን የሚግለጽ፤
379. ወንዶች ግን ራሳችውን አግዝፈው የመታየት ባህሪ በጣም ነው ያለው። እና ወንዶች
380. በጣም ራሳቸውን ይገልጻሉ እኔ ካለኝ ልምድ አንጻር ማለት ነው። ይሄ በግልጽ
381. የሚታይ ነው ሁላችንም ካለን ልምድ። ሲያነቡም ራሱ ማንበባቸውን፣ ማወቃቸውን
382. ሌላው እንዳያቅላቸው የበላይነታቸውን ሌላው እንዲያረጋግጥላቸው የመፈለግ
383. እንትን ስላለ በማያስፈልግ ቦታ ሁሉ ያን እየጨመሩ በቀጥታ ወደ ጉዳዩ ያለመግባት
384. ወንዶች ጋር በጣም አለ። ይህም ነው ተናጋሪ የሚያስኛቸው ብየ የማስበው። ሴቶች
385. ግን በቀጥታ ወደ ጉዳዩ በግልጽ ቋንቋና በአጭሩ ገልጸው ነው የሚያልፉት።
386. እሱባለው፡- አይ እኔ ጥያቄ ልጠይቅ ማንነትሽን እንዲያው አንቺ አስተዋውቂኝ
387. አታውቂም?
388. አልማዝ፡- በስብሰባ አላደርገውም። ስለተሰበሰብኩበት ጉዳይ ነው እንጂ
389. ያለቦታው ምንም ስለራሴ አልናገርም። እንግዲህ አሁን ከተነሳው አንፃር ስመለከተው
390. ጥቅሙንም አላውቅም ነበረ በስብሰባ ላይ ራስን ማስተዋወቅ። በስብሰባ ለይ ወንዶች
391. ሲያደርጉት እናየለን እኮ ይህን መጽሀፍ እንዳነበብኩት፣ ይህ ጸሀፊ እንዳለው፣ በዚህ
392. ዩኒቨርሲቲ ካለኝ ልምድ... ምናልባትም ይህንን ማለታቸው ምንም ላይፈይድ
393. ይችላል። ዋናው አላማ ራሳቸውን ለማስተዋወቅ ነው።
394. ገበየጉ፡- እኔ እንደታዘብኩት ሴቶች ቁጥብ ናቸው። ምክንያቱም አስተዳደግ፣
395. የበላይነቱ ሁሉ ተጽእኖ ያደርግባቸዋል። ሌላው ኮስታራነትን በወንዶች ብንወሰደው
396. በእድሜ ገፋ ያሉት ናቸው ኮስተር የሚሉት፤ ሴቶች ግን ለስንወስድ ገና ከታች
397. ጀምረው ኮስተር ብለው ነው ነገሮችን የሚያቀርቡት። ይሄ ይመስለኛል እኔ ልዩነቱን
398. ያመጣው እላለሁ።
399. አገሬ፡- ሴቶች በአብዛኛው ሀሳባችን በአጭሩ ያቀርባሉ። ወንዶች ግን
400. ዝንባሌያቸውን፣ አመለካከታቸውን፣ ችሎታቸውን ብዙ ጊዜ የመግለጽ ድፍረቱ
401. አላቸው።
ቆስቋሽ ጥያቄ፡- በስብሰባ ላይ ራሳችንን መግለጽ ለምን እንፈልጋለን?
402. እሱባለው፡- በእኛ ሙያ ራስን ማስተዋወቅ ዋናው ጉዳይ ነው።
403. ኤርሚያስ፡- በተፈጥሮ ብዙ ጊዜ ወንዶች በየትኛውም አለም የበላይነት የማሳየት
404. ሁኔታ አለ። ሌላው ነገሮችን በሙያዊ ማስረጃ በማስደገፍ በመናገር ተቀባይነት

405. ሥማርሚኘትም ተብሎ ይጻረጋል።
406. እሱባለው፡- ሁኔታው ራሱ ለመኖር(survive) ለማድረግ መወዳደር አለብሽ። ለዚህ
407. ደግሞ ራሳሽን ማስተዋወቅና እውቅና ማግኘት አለብሽ።
408. መቅደስ፡- ትክክል ነው ስበሰባ ለይ ራስሽን በማስተዋወቅ መታወቅ አለብሽ።
409. እንዲያውም አንዳንዴ በትልልቅ ስብሰባዎች ይሄን ሰርቼ፣ይህን አይቼ፣ እዚህ
410. በነበርኩበት ጊዜ-- ሲሉ አገሌ ለሹመት CV እያስገባ ነው እንላለን። እና ለውድድር
411. ያልከው ነገር ትክክል ነው። በስብሰባ ላይ እራስሽን ካላስተዋወቅሽ አንዳንድ ነገር
412. ሲመጣ እጩ አትሆኝም። ሁሌም የምናየው አብዛኛውን ጊዜ ሰው በሚሰራው
413. አይደለም የሚመዘነው በስብሰባ ላይ ተናጋሪ የሆኑት ሰዎች ቢአብዛኛው በምንም ቦታ
414. ቀዳሚ ይሆናሉ ከሚሰሩት ይልቅ። አንዴ የማስታውሰው አንድ የዩኒቨርሲቲው
415. ባለስልጣን ሰብስቦን እኛ የት እናውቃችኋለን በእንደዚህ አይነት ስብሰባ ላይ
416. እየተናገራችሁ ፊታችሁ አስመቱ ብሎናል። እና ሁሌ ይህ ንግግር አስታውሰዋለሁ
417. ለምን መሰለሽ አለቃየ ምን እንደምሰራ አያውቅም ስለዚህ እኔ ስለራሴ ወይም ሌላ
418. ሰው ስለኔ ማውራት አለበት ማለት ነው ለመታወቅ።
419. እሱባለው፡- ዋናው ነገር እድሉ ሲፈጠር በመጠቀም application ማስገባት ነው
420. ለውድድሩ እኔ አሁን በጣም ታርጌት የምላቸው ውይይቶች (ስብሰባዎች) አሉ።
421. ለምሳሌ በአንድ ጊዜ በጣም ህዝብን የሚወክሉ ወገኖች ባሉ ሰዓት ታርጌት
422. እመታለሁ።

2.1 ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በተግባቦት ሂደት ማንነታቸውን ለመግለጽ ተፅዕኖ አድራጊ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?

423. እሱባለው፡- ራስሽን ለመግለጽ አውዱ ራሱ ይወስንሻል። ሌላው እኔ እንዲህ ነኝ
424. የሚሉ ሰዎች እኮ ኖሩትን፣ የሰሩትን፣ ያነባቡትን ነው የሚገልፁት። እኔ
425. የኖርኩትን ነው የምገልጸው። ይህን ለማስለት በዚህ ልምድ ማለፍ አለብሽ።
426. ስለዚህ ለዚህ ደግሞ ዋናው የኖርሽውና የነበርሽበት (lived experience) ነው።
427. አገሬ፡- ከእኔ የተሻለ ተምረዋል፣ ያውቃሉ ብየ ሳስብ እኔ የማውቀውን፣ ያነበብኩትን
428. እንዳለውም ያለኝንም የስራ ልምድ አልናገርም። አንዳንዶች ስራቸው ራሱ ይናገር
429. እንጅ በራሳቸው አፍ ስለራሳቸው መናገር አይፈልጉም። በጣም በሳል
430. ሆነው ብዙ እያወቁ እያሉ ማንነቴን ስራየ ይግለጸው የሚሉ ጭምቶች አሉ።ይህ
431. አስተዳደግም ነው። ሌሎቹ ደግሞ አጋጣሚው ሁኔታው የሚጋብዛቸው ከሆነ
432. ራሳቸውን ይግልጻሉ። አብዛኛውን ጊዜ ሴቶች ግን አይገልጹም ለምን መሰለሽ
433. በመጀመሪያ ለመናገር ሀሳባቸው ደካማ መስሎ ስለሚታያቸው አይናገሩም፤ ሲቀጥል
434. ደግሞ ያፍራሉ። ለምሳሌ እኔ የወጣሁት ከገበሬ ቤተሰብ መውጣቴ ዝቅ አድርጎ
435. የሚያሳይ መስሎ ይታያቸዋል። ይህም ደግሞ ለእኔ ደስ ይለኛል ምክንያቱም
436. ከታች ተነስቶ ማውጣት ትልቅ ነገር ነው።
437. ገበየሁ፡- ስልጣን ያለው ተቆጥቶ ይናገራል። ስልጣን የሌለው ፈገግ ብሎ
438. ይናገራል። አንዳንዱ ግሩፕ ይፈጥራል። እሱ ሲናገር ያጨበጭቦበታል ሌላው
439. ሲናገር ተጽእኖ ፈጥሮ ቁጭ ይላል።
440. አልማዝ፡- አንደኛ እኔ የሚመስለኝ ራስን መግለጽ አስፈላጊ መሆኑን
441. አለማወቅ። ለምሳሌ እኔ ራስን መግለጽ ጠቃሚነቱ አስቤው አላውቅም። ገለሸበት
442. የስራ ቦታ ራስሽን ማሶተዋወቁ ተወዳዳሪና ተቀባይነትን ኣንደሚያስገኝ ጠቃሚ ነው
443. ብየ አስቤው አላውቅም። ሁለተኛው ያለሁበትን ሁኔታ ወይም ደረጃ ዋጋ
444. አለመስጠት። ግን ላደረገሁትና ላደረስሁበት ነገር ትልቅ ዋጋ መስጠት ኦለብኝ እኔ
445. ራሴ። እና እነዚህ ሁለት ነገሮች ትልቅ ሀሳብ ናቸው ብየ ነው የማስበው።
446. ሮዛ፡- አንዱ ለራስሽ የምትሰጭው ግምት ተጽዕኖ ያሳድራል። ሌላው ቅድም
447. እንደገለጽኩት ሰብሳቢዎቹ ለተሰብሳቢው ዋጋ ካልሰጡ፣ አንዱ ሲናገር ሌላው
448. የሚጎነትል ከሆነ፣ በስብስባ ላይ በአጠቃላይ ሀሳብሽንም ሆነ ራስሽን ለመግለጽ

ተጽዕኖ የማያሳድሩብሽ ይሆናሉ።
ኤርሚያስ፡- አብዛኛው ተብሏል የቀረው ይሉኝታ የሚባል ነገር አለ። ይህም ነገር
ብናገር ሰዎች ሊያቀሉኝ ይችላሉ ወይም ራሱን ካበ /ካበች ይሉኛል የሚል ነገር
ውስጡ የማይደሰት ሳው አለ። እና ያን በመፍራት አለመናገር አለ። በራስ
የመተማመን አንዳንድ ጊዜ ባለን ነገር መተማመን አለመቻል አጋንኜ ልናገር
ስለምችል ብለው ዝም የሚሉ አሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ስራና ይግለጸው የሚሉ
አሉ። አንዳንዴም ደግሞ እታወቃለሁ ተብሎ ራስን አለማስተቃወቅ።
መቅደስ፡ ትልቁ ነገር ሰው ምን ይለኛል የሚለው ነገር ራስሽን ቀርቶ ሀሳብሽን
እንዳትገልጭ ያደርግሻል። እኔ የራሴን መጀመሪያ ልንገርሽና በፋካሊቲና
በዲፓርትመንት ደረጃ ሀሳብ ሳቀርብ አብዛኛውን ጊዜ ከሆነ ነገር ጋር ያያይዙና
ባላሰብኩት መንገድ እንዲህ ለማት ፊልገሽ ነው አይደል ብለው ሀሳቤን
የማጣጣል ብቻ ሳይሆን ለምን ይህን አልሽ ተብየ የምጎነተልበት ጊዜ ብዙ ነው። እና
ከስብሰባ ስወጣ የሚደርስብኝን ትንኮሳ ለመከላከል ስል ስለራሴ ብቻ ሳይሆን
ያለኝንም ሀሳብ አልናገርም።
አቶ ገበየሁ፡- ሁለት ባህሪያት አሉ። አርቆ አሳቢ ሰዎች ካሉ ስራየ ይገለጽ በሚል
አይናገሩም። ግን ይሄ አጭር ከሆነ አስተሳሳቡ ዛሬ ይህን ካላልኩ አለም
ትከፋብኛለች ብሎ የሚያስብ ከሆነ ሁሉንም ዘርግፎ ያለውንም የሌለውንም
ይዘረግፍና ቁጭ ይላል።
አልማዝ፡- ራሳቸው የሚያደርጉትና የሚናገሩት አይገናኝም። ሲሰሩ በጣም ደከም
ያሉ ይሆናሉ ግን ራሳቸውን በጣም የሚያስተዋውቁ አሉ። በጣም በቃ ጎበዝ፣
ታታሪ፣ ጠንካራ ሆነው ደግሞ ራሳቸውን መግለጽ የማይፈልጉ አሉ በጣም ትሁት
የሆኑ ሰዎች አሉ። እና ከራሳችን ባህሪ ጋር ይያያዛል።

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን መገምገሚያ መስፈርቶች /ባተማሪዎች የሚሞላ

የመምህሩ/ርዋ ስም ----------

የሚያስተምርው/የምታስተምረው የት/ አይነት ----------

የተማሪው/ዋ የጥናት መስክ/ ዲፓርት መንት ----------

ቀን ----------

መግለጫ

1. ከአነበብሽው/ከው የመገምገሚያ ነጥብ መምህራን
1.1 የማስተማር ዝግጅት
1.2 የትምህርት አቀራረብ
1.3 አጠቃላይ ባህሪ በማዛናዊነት መምግም/ሚ

ክፍል አንድ

መመሪያ 1፡- ከአነበብሽው/ከው የመገምገሚያ ነጥብ አካያ የመምህራን የስራ አፈፃፀም ከበጣም ዝቅተኛ እስከ በጣም ከፍተኛ በቁጥር ተመንዝሮ ካተቀመጠው ውስጥ አ|ንዱት በማክበብ አመልክት /ች

ተ.ቁ	የመገምገሚያ መስፈርት	በጣም ዝቅተኛ	ዝቅተኛ	መካከለኛ	ከፍተኛ	በጣም ከፍተኛ	አይመለከተኝም
1	ኮርስ ጋይድ ቡክ በወቅቱ አዘጋጅቶ/ታ ያቀርባል ታቀርባለች ።	1	2	3	4	5	X
2	ባዘጋጀው ኮርስ ጋይድ ቡክ ዝርዝር በአቅዱ መሰረት	1	2	3	4	5	X
3	የትምህርቱ ይዘት ያስተምራል ታሳተምራለች	1	2	3	4	5	X
4	ኮርሱን እንደአስፈላጊነቱ ከተጨባጭ እውነታዎችና ምሳሌዎች ጋር በማዛመድ ለማዝረብ ይጥራል /ትጥራለች	1	2	3	4	5	X
5	በክፍል ውስጥ የተማሪዎች ጥያቄና አስተያየት ተቀብላ ታስተናግዳለት ያስተናግዳል ።	1	2	3	4	5	X
6	ተማሪወች የሰሩትን ስራ አስፈላጊውን ግብረ መልስ አስተያየት የሰጣል ትሰሐለች	1	2	3	4	5	X
7	ጠቃሚ የሆኑ ተከታታይ ምዘናዎች /አሳይመንቶች ፕሮጀክቶች የመጽሀፍ ግምገማዎች ይሰጣል /ትሰጣለች	1	2	3	4	5	X
8	የተሰጡ ተከታታይ ምዘናዎች አርሞ ውጤቱን የሰጣል /ትሰጣለች	1	2	3	4	5	X
9	የምዘና ጥያቄዎችን ከክርሱ ይዘት ጋር አዛእዶ ያወጣል/ታወጣለች	1	2	3	4	5	X
10	በኮርሱ ያሉ በቤተ መከራ ሊሰሩ ያመባቸዋ ስራዎችን ይሰራል/ ትስራለች	1	2	3	4	5	X
11	የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳራያዎችን እንደየአስፈላጊነቱ በመጠቀም ያስተምራል/ ታስተምራለች	1	2	3	4	5	X
12	ለሚሰጠው ትምህርት ጠቃሚና ወቅታዊ የሀኑትን የማጣቀሻ ዝርዝር መጽሀፍት አዘጋጅቶ /ታ ይሰጣል /ትሰጣለች	1	2	3	4	5	X
13	በማጣቀሻ ኮርስ ጋይድ ቡኩ ላይ የተቀመጡ መጽሀእትን በቤተ መጽሀፍ እንዲገኙ ያደርጋል /ታደርጋለች	1	2	3	4	5	X
14	ትምህርቱን በተግባር የተደገፈ ለማድረግ ጥረት ያደርጋል /ታደርጋለች	1	2	3	4	5	X
15	በማስተማሪያ ቋንቋ በመጠቀም ትመህርቱን ግልጽ ታደርጋለች/ ያደርጋል	1	2	3	4	5	X
16	በተመደበው ጊዜ ስአት አክብራ/ት ትመጣለች ይመጣል	1	2	3	4	5	X
17	ከአቅም በላይ በሆነ አጋጣሚ ለቦኮ ጊዜ ለማክካስ ጥረት ያርጋል /ታደርጋለች	1	2	3	4	5	X

18	ተማሪውን ለማማከር የቢሮ ስአት ይመድባል /ትመድባለች	1	2	3	4	5	X
19	በተመደበው ስአት ተማሪዎች ለሚያቀረቡት የአካዳሚ ችግሮች መፍትሄ ይፈልጋል /ትፈልጋለች	1	2	3	4	5	X
20	የተማሪውን/ዋነ ክብር ትጠብቃሉች /ይጠብቃል	1	2	3	4	5	X
21	ከተማሪው/ዋ ለመማር ዝግጁ ናት/ነው ።	1	2	3	4	5	X

ክፍል ሁለት

መመሪያ ሁለት :- ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ መልሽ /መልስ

1. በአጠጠላይ በኮርሱ አሰጣጥ ዙሪያ የታዩ ጠንካራና ደኮማ ጐኖችን ዘርዝር

ሀ. ጠንካራ ጐን

ለ. ደካማ ጐን

---

2. የመምህሩን /ሯን አጠቃላይ ሙየዊ ብቃትና ስነምግባር እንዴት ትገመግማዋለህ ትገመግሚውአለሽ / የታዩ የስነምግባር ግድፈቶች ካሉ ይዘርዘሩ /

---

3. የመምህሩን ሯን አጠቃላይ የኮርስ አሰጣጥ ሲመዘን /አክብብ/ቢ/

ሀ. እጅግ በባም ጥሩ ለ. በጣም ጥሩ ሐ .ጥሩ መ. ደካማ ሠ. በጣም ደካማ

<u>በቢሮ የሚሞላ</u>

ግምገማውን ያካሄዱት ተማሪወች ብዛት ----------

ትምህርቱን የተከታተሉት ተማሪዎች ብዛት ----------

አማካኝ ውጤት ----------

ስሌቱን ያጠናከረው ስም .....ፊርማ.....ቀን .....

የተፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን መገምገሚያ መስፈርቶች በስራ ባልደርቦች የሚሞላ

የተገምጋሚው ስም ----------

የትምህርት ክፍል ----------

መግለጫ

1. እያንዳንዱ የመገምገሚያ ነጥብ በጥንቃቄ አንብብ
2. ካነበብከው የመገምገሚያ ነቅብ አካያ የስራ ባልደረባህን
2.1 ለማስተማር የሚያደርገውን ዝግጅት
2.2 ጥናትና ምርምር ለማድረግ የሚያሳየውን ጥናት
2.3 ስራ በጋራ ለመሰራት የሚያሳየውን ፍላጐት
2.4 ላት/ክፍሉ ሆነ ለተቋሙ ሥራ መቃናት መሸሻል የሚያሳየውን ዝንባሌ
2.5 ላተቋሙ ንብረት የሚያሶየውን ተቶርቋሪነት
2.6 የስራ ስአት ፣የቢሮ ስዓትና የቀጠሮ ስዓት አክባሪነቱን
2.7 ያለውን ልምድና እውቀት ለባልደረቦቹ ለማካፈል ዝግጁነቱን
2.8 ኦጠቃላይ ባህሪውን

በሚዛናዊነት ገምግም

3. ከአነበብከው የመገምገሚያ ነጥብ አካያ የስራ ባልደረባህን የስራ አፈፃፀም ከበጣም ዝቅተኛ እስከ በጣም ከፍተኛ ተመንዝሮ ከተቀመጠው ውስጥ አንዱን በመክበብ አመልክት
4. ምናልባት አንዱ የመገምገሚያ ነጥብ የስራ ባልደረባህን በምትመዝንበት ጊዜ ነገሩ የሚመለከተው ከሆነ <<አይመለከተውም>> " በሚለው ስራ የተቀመጠውን << X >>ምልክት አክብብ

ተ.ቁ	የመገምገሚያ መስፈርት	በጣም ዝቅተኛ	ዝቅተኛ	መካከለኛ	ከፍተኛ	በጣም ከፍተኛ	አይመለከተኝም
1	በት/ክፍሉ የመማር ማስተማር ስራ የሚሻሻልበትን ሃሳብ ያቀርባል፣ ተሳትፎ ያደርጋል ፡	1	2	3	4	5	X
2	በት/ክፍሉ ችግሮች ሲከሰቱ የመፍትሄ ሃሳብ ያመነጫል ፣ ተሳትፎም ያደርጋል ።	1	2	3	4	5	X
3	በመ.ያው ጥና.ና ምርምር ያደርጋል	1	2	3	4	5	X
4	የጥናትን ምርምር ሂደት ላት/ክፍሉ መምህራንና ተማሪዎች የሚዘጋጅለት መድረክ ያ.ርጣል።	1	2	3	4	5	X
5	ኮጥናት የ.ገኘውን ውጤት ላማመለከታቸው የኮሌጅ ህብረተሰብ ያሳውቃል ።	1	2	3	4	5	X
6	ለሚያስተምራቸው ኮርሶች የማስተማሪያ ጹሁፎችን ማቴሪያልና ወይም መጽሀፍት ያዘጋጃል ይጽፍል ፡	1	2	3	4	5	X
7	እውቀቱን ፣ልምዱን ፣ ጉልበቱንና ጊዜውን ለተመደበበት ስራ ያውላል።	1	2	3	4	5	X
8	እንደአስፈላጊ.ነቱ ከተቋሙ ውጭ ላለው ሕብረተሰብ ሙያዊ አገልግሎት ያበረክታል	1	2	3	4	5	X
9	ለመማር ለመመራመር ልዩልዩ የማስተማሪያ ጹፎችንና መጽሃፍትን	1	2	3	4	5	X

	ለማዘጋጀት አዳዲስ አሰራሮችን ለመጠቀምና ራሱን ለመሻሻል ጥረት ያደርጋል።						
10	ከስራ ሃላፊዎች ፣ ባልደረቦች ፣ ተማሪዎችና ሰራተኞች ጋር ተግባብቶና ተባብሮ ይሰራል ።	1	2	3	4	5	X
ተ.ቁ	የመገምገሚያ መስፈርት	በጣም ዝቅተኛ	ዝቅተኛ	መካከለኛ	ከፍተኛ	በጣም ከፍተኛ	አይመለከተኝም
11	ያለውን ልምድና እውቀት ለባልደረቦቹ ለማካፈል ዝግጁነው ።	1	2	3	4	5	X
12	በክፍሉ በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ ይሳተፍል ።	1	2	3	4	5	X
13	በክፍሉ የሚሰጠውን የፊተና ውጤት በጋራ ይገመግማል ።	1	2	3	4	5	X
14	በክፍሉ የሚደረጉ የመምህራን ብቃት ስብሰሳ ይሳተፋል።	1	2	3	4	5	X
15	የኮሚቴ ስራ ይቀበላል ።	1	2	3	4	5	X
16	ከስራ ባልደረቦቹጋር የተሰጠውን የኮሚቴ ስራ /ስብሰባ/ በተገቢው ያከናውናል ።	1	2	3	4	5	X
17	ተማሪዎችን የሚገመግምበትን ዘዴ በግልጽ ያስቀምጣል ፣ በማሪዎችን በስራቸው ያለአድሎአዊ በሚዛናዊነት ይገመግማል።	1	2	3	4	5	X
18	ለማስተማሪያ ስራዎች የተረከበውን መሳሪያዎች በጥንቃቄ እንዲቀመጡ ያደርጋል።	1	2	3	4	5	X
19	የተበላሹ መሳሪያዎችና እቃዎች በየጊዜው እንደሁኔታው ይጠግናል ወይም እንዲጠገኑ ያደርጋል ።	1	2	3	4	5	X
20	የስብሰባ ስአት ያከብራል ።	1	2	3	4	5	X
21	በስራ ምክንያት ላስራ ጓደኞቹ የጎጠውን የቀጠሮ ስአት ያከብራል ።	1	2	3	4	5	X
22	በተቋመ የስራስአት በተቋመ አዘውትሮ የመገኘት ልምድ አለው ።	1	2	3	4	5	X
23	ግምግማ ከስራ ሂደት አንዱ መሆኑን ይቀበላል ።	1	2	3	4	5	X
24	በግምገማ የተገኙ ገንቢ አስተያየቶችን ይቀበላል አስተያየቶችንም በስራው ለማካተትና ለመተርጉም ይጥራል ።	1	2	3	4	5	X
25	የአልኮል መጠጥ ወይም የሌሎች አደንዛዥ እፃች ተገዥ ላለመሆን ይጥራል ።	1	2	3	4	5	X
26	የስራውን ደረጃና የሙያውን ክብር ይጠብቃል ።	1	2	3	4	5	X
27	ለጓደኞቹ ተገቢውን ክብር ይሰጣል ።	1	2	3	4	5	X
28	ያለውን ሁኔታ በግልጽና በተገቢው መድረክ ያቀርባል ።	1	2	3	4	5	X
29	የሌሎችን ስራ እንደራሱ ስራ አድርገ ለማቅረብ ይጥራል ።	1	2	3	4	5	X
30	የሌሎችን ስራ የተረከባቸውን እቃዎች ካስፈለገ በሌሎች በመስኩ ከሚያስተምሩ መምህራን ጋር በጋራ ለመጠቀም ፈቃደኛ ይሆናል ።	1	2	3	4	5	X
31	ሌሎች መምህራን የመሳሪያ እጥረት ሲያጋጥማቸው ለትምህርታቸው መሳካት የሚያስፈልጋቸውን መሳሪያ በውሰት ለመስጠት ፍላጐት አለው ።	1	2	3	4	5	X
32	የተዋሰውን መሳሪያዎች በጊዜውና በተረከበበት ሁኔታ የመመለስ ግዴታውን ይወጣል ።	1	2	3	4	5	X

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን መገምገሚያመስፈርቶች /በኃላፊው የሚሞላ

የተገምጋሚው ስም ----------

የትምህርት ክፍል ----------

መግለጫ

1. እያንዳንዱ የመገምገሚያ ነጥብ በጥንቃቄ አንብብ
2. ካነበብከው የመገምገሚያ ነቅብ አኳያ የስራ ባልደረባህን
2.1 ለማስተማር የሚያደርገውን ዝግጅት
2.2 ጥናትና ምርምር ለማድረግ የሚያሳየውን ጥናት
2.3 ስራ በጋራ ለመሰራት የሚያሳየውን ፍላጎት
2.4 ለት/ክፍሉ ሆነ ለተቋሙ ሥራ መቃናት መሸሻል የሚያሳየውን ዝንባሌ
2.5 ለተቋሙ ንብረት የሚያሳየውን ተቶርቋሪነት
2.6 ?ስራ ስአት ፣የባ.ሮ ስዓትና የቀጠሮ ስዓት አክባሪነቱን
2.7 አጠቃላይ ባህሪውን
3. ከአነበብከው የመገምገሚያ ነጥብ አኳያ የስራ ቦልደረባህን የስራ አፈፃፀም ከበጣም ዝቅተኛ እስከ በጣም ከፍተኛ ተመንዝሮ ከተቀመጠው ውስጥ አንዱን በመክበብ አመልክት
4. ምናልባት አንዱ የመገምገሚያ ነጥብ የስራ ባልደረባህን በምት መዝንበት ጊዜ ነገሩ የሚመለከተው ከሆነ <<አይመለከተውም>> " በሚለው ስራ የተቀመጠውን << X >>ምልክት አክብብ

ተ.ቁ	የመገምገሚያ መስፈርት	በጣም ዝቅተኛ	ጀቅ.ኛ	መካከለኛ	ከፍተኛ	በጣም ከፍተኛ	አይመለከተኝም
1	ለሚያስተምረው ኮርስ በተዘጋጀው ሲለበስ /ኮርስ ዲስክሪፕሽን/ መሰረት ኮርስ አውትላይን ያዘጋጃል።	1	2		4	5	X
2	ፈተናውን በጊዜው አርሞ ያስረክባል	1		3	4	5	X
3	የማስተማሪያ መረጃ መላሪያዎችን አግባብነት ይገመግማል ።	1			4	5	X
4	ያስተማረውን ኮርስ ይዙት ኣአላማው አኳያ ብቃቱን ይገመግማል ።	1	2	3	4	5	X
5	ተማሪዎች ትምህርቱን ዶመረዳት የሚያስችላቸውን የቤት ስራዎች ያዘጋጃል ።	1	2	3	4	5	X
6	የማስተማሪያ መረጃዎችን ይመርጣል /ያዘጋጃል/።	1	2	3	4	5	X
7	ለትምህርቱ አስፈላጊ ሆኑ ጹሃፎችን /ሃንደድ አውት/ ያዘጋጃል።	1	2	3	4	5	X
8	ለሚያስተምረው ኮርሶ ለተ ሪወች የሚነበቡ ጹህፎችን ዝርዝር ያዘጋጃል ።	1	2	3	4	5	X
9	በሙያው ጥናትና ምርምር ያደርሪጋል ለተማሪወች በተዘጋጀለት መድረክ ያሳውቃል ።	1	2	3	4	5	X
10	ከጥናቱና ምርምሩ የተገኘ ውጤት ለሚመለከተው የተቋሙ ህብረተሰብ ያሳውቃል ።	1	2	3	4	5	X
11	በጥናቱ የተገኘው ውጤት ለህብረተሰቡ ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ በስራ ላይ የሚልበትን ዘዴ ይፈልጋል		2	3	4	5	X
12	ለሚያስተምራቸው ኮርሶች ዖማስ.ማሪያ ጽሁፍ /ቲቸንግ ማቴሪያል ወይም መጽሃፍት ያዘጋጃል ይጽፋል ።	1	2	3	4	5	X
13	ተቋሙ በሚያዘጋጀው ትምህርታዊ ስብሰባዎች ይሳተፋል ።	1	2	3	4	5	X
14	ከተቋሙ ውጭ በሙያው የሚዘጋጅና እሱ እንደገኝ በታዘዘበት ስብሰባ ይሳተፍል ።	1	2	3	4	5	X

15	በመ.ያው ምርት በሚያስገኘው ስራ ላይ ይሳተፍል።	1	2	3	4	5	X
16	የተቋሙን የገቢምንጭ ሊያሳድግ በሚችል አገልግሎት ስራ ላይ ይሳተፋል ።	1	2	3	4	5	X
17	በሚያስተምረው ኮርስ አዳደስ ሁኔታወችን ለመረዳት የሚያስችሉ መጽሃፍት እንዲገዙ ይጠይቃል ክትትል ያደርጋል ።	1	2	3	4	5	X
18	በመ.ያው የሚታተሙ ጆርናሎች በተቋሙ እንዲገኙ ይከታተላል ።	1	2	3	4	5	X
19	ከስራ ጎላፊዎች፣ ባልደርቦችና ተማሪዎች ና ሰራተኞች ጋር ተግባብቶና ተባብሮ ይሰራል ።	1	2	3	4	5	X
20	ፕሮግራም አውጥቶ ለተማሪወች የአካዳሚክ ምክር ይሰጣል ።	1	2	3	4	5	X
21	ተማሪወችን እንደአስፈላጊነቱ ቱተር ያደርጋል ።	1	2	3	4	5	X
22	ተማሪዎች የሚገመገሙበት በግልጽ ያስቀምጣል ፣ተማሪዎች በስራቸውና በተጨባጭ ውጤታቸው ያአድሎ በሚዛናዊነት ይገመግማል ።	1	2	3	4	5	X
23	ለማስተማሪያ ስራ የተረከባቸውን መሣራያወች በጥንቃቄ እንዲቀመጡ ያደርጋል ።	1	2	3	4	5	X
24	የተበላሹ መሳሪያዎችና እቃዎች በየጊዜው እንዲጠገኑ ይጠይቃል ።	1	2	3	4	5	X
25	ለስራው የተሰጠውን የጽህፈት መሳሪያ የቢሮ	1	2	3	4	5	X
	መገልገያ እቃዎች በቁጠባና ብተገቢው ስራ ያውላል						
26	አስቸኮይና አጣዳፊ ስራዎች ሲከሰቱ ሀላፊው በሚመድበው ስራ ላይ ይሳታፋል ።	1	2	3	4	5	X
27	በተቋሙ ንብርት ተቆርቋሪነት ይሳያል ።	1	2	3	4	5	X
28	የተሰጠውን ተደራቢ ስራ በተሰጠው የጊዜ ገደብ በሚፈለገው ሁኔታ ሰርቶ ለመጨረስ ይጥራል ።	1	2	3	4	5	X
29	የተቋሙ ንብረትና የትምህርት መማሪያዎች	1	2	3	4	5	X
	ለተቋሙ ስራ ብቻ ያውላል	1	2	3	4	5	X
30	ለክፍሉ የተመደበለትን ስአት ይጠቀማል ።	1	2	3	4	5	X
31	የሚያስተምረውን ኮርስ በስአቱ ጀምሮ በትአቱ የፈጽማል ።	1	2	3	4	5	X
32	ያለበቅ ምክንያትና የክፍል ሃላፊው ሳያውቅ የሚያስተምርበትን የክፍል ስአት አይለውጥም አያሳተላልፍል ።	1	2	3	4	5	X
33	የስብሰባ ሳአት ያክብራል ።	1	2	3	4	5	X
34	የቢሮ ስአት ነው ብሎ ባወጣው ሰሌዳ ይገዛል ።	1	2	3	4	5	X
35	በተቋሙ የስራ ስአት በተቋሙ አዘውትሮ የመገኘት ልመድ አለው ።	1	2	3	4	5	X
36	ከስራው ጋር ስአት በተያያዘ የሰጠውን ወይም የተቀበለውን የቀጠሮ ስአት ያክብራል ።	1	2	3	4	5	X
37	ራሱን የመገምገም የሌዙለችን የራስ ብቃትና ውጤት የመገምገም ሁኔታ መብትና ግዴታ መሆኑን ይቀበላል ።	1	2	3	4	5	X
38	በግምገማ የተገኙ ጎምቢ ኣስተያየቶችን በስራው ለማካተትና ለመተርጉም ይጥራል ።	1	2	3	4	5	X

በሰው ሀይል ድልድል መመሪያ መሰረት ለፕሬዘዳንትነትና ለዲንነት የሚያበቁ መስፈርቶች

ተ.ቁ	መስፈርት
1	የአሰራር ለውጡን ለመቀበል ያለው ዝግጁነት
	• ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በመተግበር ያለው ቁርጠኝነት
	• ዘመናዊ ዩኒቨርሲቲ ለመገንባት ያለው ዝግጁነት
	• በለውጡ ውስጥ ያለው የእስካሁን ተሳትፎ
2	ለአመራር ያለው አካዳሚያዊ ዝግጅት
	• የማኔጅመት/ ብቃትና ውጤታማት
3	ሙያዊ ብቃት
	• ሙያዊ ውጤታማነት
4	ሙያዊ ሥነምግባር
	• ሙያዊ አርአያነት
5	ስተማሪዎች፣ከድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችና አቻዎቹ ጋር ያለው መስተጋብር፣ መልካምነትና አብሮ የመስራ ብቃት
	• የአገርና የዩኒቨርሲቲውን ህጎች አክባሪነት